

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ችሎት ውሣኔዎች



ቅጽ- 11

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች
ቅጽ- 11

www.chilot.me

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ - 11

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

www.chilot.me



ህዳር 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ ሥር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ እነዚህን የሰበር ውሣኔዎች አሣትሞ ማሠራጨት ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኃላፊነት እንደሆነም ተመልክቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ አስገደጅ የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸውን የሰበር ውሳኔዎች ማሣተም የተጀመረ ሲሆን ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህም ከቅፅ 5 እስከ ቅፅ 10 ያሉትን አሣትመን አሠራጭተናል፡፡ እነሆ አሁን ደግሞ ቅፅ 11 እና ቅፅ 12 የሰበር ውሣኔዎች ሊታተሙ በቅተዋል፡፡ ይህም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸው የሰበር ውስኔዎቻችንን የማሣተሙ ሥራ ወቅቱን የጠበቀና ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲሆን የምናደርገው ጥረት ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ያሣያል፡፡

ባለፉት እትሞች መልእክቴ እንደገለፅሁት እነዚህ ፍርዶች ምንም እንከን የላቸውም የሚባሉ እንዳልሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በፍርድ ቤቶቻችን በየትኛውም ደረጃ ላይ ባለን ዳኞች በአንፃራዊነት የልምድም ሆነ የብቃት ውስንነቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶችና ውሳኔዎች ላይ አልፎ አልፎ ቢታዩ ሊገርመን አይገባም፡፡ የብዙ ዓመታት ተሞክሮ ያላቸው ሀገሮች ልምድም የሚያሣዩን ይህንኑ ነውና፡፡

የሀገራችን ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥና ተገማች እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የሰበር ውሣኔዎች ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህን አጠናክሮ ለመቀጠልና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን በሰበር ውሣኔዎቻችን ላይ

በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሠማሩ የሕግ ምሁራንና ተማሪዎች ገንቢ አስተያየቶችን እና ትችቶችን ሊሠጡበት ይገባል፡፡

www.chilot.me

እነዚህ አስተያየትና ትችቶች ከሌሎች በተመሣሣይ ጎዳና ካለፉ ሀገሮች ከምናገኛቸው ልምዶች ተደምረው አቅማችንን በማሣደግ የተጣለብንን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት ጉልበት ስለሚሆኑን የሙያው ባለቤቶችና መላው ህብረተሰባችን ለጥረታችን መሣካት የሚጠበቅባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት እንዲወጡ በአክብሮት እየጠየቅሁ ውሳኔዎቻችንን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረ ገፅ ላይ ማግኘት የሚቻል መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት

www.chilot.me

# በ2003 ዓ.ም. የሰበር ችሎት

# የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ቤተሰብ** | | | | |
| 1. | • ባል ሁለት ሚስቶችን በአንድ ጊዜ አግብቶ የሚኖር በሆነ ጊዜ በመካከላቸው የሚፈራ ንብረት ለተጋቢዎቹ ሊከፋፈል የሚችልበት አግባብ<br>• ሚስቶች ጋብቻ እንደተፈፀመ ከሚቆጠርበት ጊዜ ጀምሮ ከባል ጋር ያፈሩትን ሀብት ብቻ መካፈል ስለመቻላቸው<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/96 አንቀጽ 62/1/ | 50489 | ወ/ሮ ዘይነባ ከልፋ<br>እና<br>ወ/ሮ ከድጃ ሲራጅ | መስከረም 24/2003 | |
| 2. | የኮንዶሚንየም ቤት ለማግኘት የተደረገ ምዝገባ ከጋብቻ በፊት ቢሆንም ዕጣ የወጣው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ከሆነ ተጋቢዎቹ የመካፈል መብት የሚያገኙ ስለመሆኑ | 46606 | አቶ ገ/ሥላሴ ጫኔ<br>እና<br>ወ/ሮ አብረኸት ተጫኔ | ጥቅምት 02/2003 | |
| 3. | ወራሽ የሆነ ሰው ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ ንብረቴ ይለቀቅልኝ በሚል የሚያቀርበው ክስ /አቤቱታ/ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ይርጋ የሚቆጠረው ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን አንስቶ ሳይሆን ንብረቱ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ | 47201 | እነ በላቸው አስፋው<br>እና<br>ወ/ሮ መኪያ አወል | ጥቅምት 05/2003 | |
| 4. | የጋብቻ ውል አስገዳጅ የህግ ድንጋጌን እስካልተቃረነ ድረስ በፍቺ ምክንያት የሚከተለውን የተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል እልባት በመስጠት ረገድ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 42, 47, 73, 44 | 47889 | እነ ወ/ሮ ሠላማዊት አስራት /አምስት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ መሠረት ዘውዴ | ጥቅምት 04/2003 | |
| 5. | በሁለት የተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ቤቶች የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ ለባልና ሚስት ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ | 49171 | ዶ/ር ደስታ አቡኑ በለጡ<br>እና<br>ሲ/ር አስቴር ካሣ ወልደየስ | ጥቅምት 16/2003 | |
| 6. | የውርስ ሀብትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ገደብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851/ለ/ መሰረት ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ስለመኖራቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 | 49359 | ወ/ሮ ቀለሚ ወርቅነህ<br>እና<br>ሻምበል ጌታሁን ገብሬ | ጥቅምት 04/2003 | |
| 7. | • ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ሰዎች ግንኙነታቸው በንብረት ረገድ ያለውን ውጤት በተመለከተ በውል ሊወሰኑ ስለመቻላቸው<br>• በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ አላባ የመጠቀም መብት ጥቅም ተቀባዩ ሲሞት የሚቋረጥና ለወራሾቹ | 53663 | እነ አቶ ጊላጋብር ገብረህይወት /ሦስት ሰዎች/<br>እና | ጥቅምት 29/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማይተላለፍ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731, 1322/1/ | | እነ ወ/ሮ አረጋሽ አብረሃ<br>/ሁለት ሰዎች/ | | |
| 8. | የኑዛዜ መኖርን የማስረዳት ሸክም ስላለበት ወገንና ኑዛዜውን ለማስረዳት ሊቀርቡ ስለሚገቡ ማስረጃዎች<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 896, 897 | 49831 | ወ/ሪት ሮማን ግዛው<br>እና<br>አቶ ግርማ አብርሃም | ጥቅምት<br>02/2003 | |
| 9. | በኑዛዜ ላይ ስለሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ እና ተፈፃሚነት ስላለው የይርጋ ደንብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973, 974 | 53223 | እነ አቶ ሐዲስ ዓለመስላሴ<br>እና<br>ወ/ሮ ብሌን ዓለመስላሴ | ጥቅምት<br>15/2003 | |
| 10. | • የጋብቻ መኖርን አስመልክቶ ቀዳሚና ዋናው ማስረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ<br>• በማንኛውም ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርቦ ሊመዘገብ የሚችልና በዚህ መልኩ የሚገኘው ሰነድ የጋብቻ መኖርን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው ስለመሆኑ<br>• በዚህ መልኩ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የተመዘገበ ጋብቻ ውጤት አለው ለማለት የሚቻለው ምዝገባው ከተከናወነበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን የጋብቻው ሥርዓት ከተፈፀመበት ዕለት አንስቶ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992 አንቀጽ 28/3/ | 54258 | ወ/ሮ ዘነበች በቀለ<br>እና<br>አቶ ዮናስ ፀጋዬ | ህዳር 02/2003 | |
| 11. | • በትዳር ወቅት የተወሰደ /በአንደኛው ተጋቢ/ ብድር ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚገመት ስለመሆኑና ከዚህ በተቃራኒ የሚከራከር ተጋቢ ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም ያልዋለ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ደመወዝ የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው በሚል ሊወሰድ የሚችለው ተጋቢዎቹ በጋብቻ ባሉበት ወቅት የትዳርን ወጪ ከመሸፈን አኳያ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>• ተጋቢዎች ከህጋዊ ፍቺ  በፊት ተለያይተው በቆዩባቸው ግዜያት በግል ያገኙት ደመወዝ የጋራ ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ<br>• በጋብቻ ወቅት የተወሰደና በፍቺ ወቅት ተከፍሎ ያላለቀ ዕዳ እንደ የጋራ ዕዳ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/92 አንቀጽ 62/1/ | 56184 | ወ/ሮ ኑን ስንታየሁ ጐዝ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል | ህዳር 02/2003 | |
| 12. | ባል/ሚስት በጡረታ መልክ የሚያገኘውን ክፍያ ሌላ ባል/ሚስት ባገባ ጊዜ የሚቋረጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀጽ 21<br>አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 35/2/ | 52569 | ወ/ሮ ሙሉወርቅ ዋቼ<br>እና<br>ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን | ህዳር 13/2003 | |
| 13. | • የውርስ ሃብት እንዲጣራ በሚል በንብረቱ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ ከሟች ጋር ህጋዊ ግንኙነት ባልነበረበት ሁኔታ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን እንደ ጭብጥ በመያዝ እልባት ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ<br>• በዚህ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤት የሚሰጠው ብይን ጊዜያዊ አገልግሎት እንዳለው ትዕዛዝ የሚወሰድ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320/3/, 247/1/ | 46726 | ነጋሲ አየለ ኢትቻ<br>እና<br>እነ ሳሙኤል ዮሃንስ<br>ገ/እግዚአብሔር /ሁለት<br>ሰዎች/ | ታህሳስ 13/2003 | |
| 14. | • ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት መኖርን ማስረዳት የሚቻልበት አግባብና ይሄው ግንኙነት በህግ ጥበቃ ያለው ነው ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ<br>• ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በንብረት ረገድ ውጤት ሊያስከትል የሚችለው ግንኙነቱ ሦስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ የፀና ከሆነና በዚሁ ጊዜም የተፈራ ንብረት ያለ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 106/2/, 95 | 50580 | ዶ/ር አለልኝ መኮንን<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር አርአያ | ታህሳስ 14/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 15. | • ሟች ካለው ሀብት እጅግ አነስተኛ የሆነ መጠን ያለው ንብረት ለተወላጁ እንዲሰጠው የተናዘዘ እንደሆነ ተናዛዡ በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጁን እንደነቀለው የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>• የሟች ኑዛዜ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ በሆነ ጊዜም የተነቀለ ተወላጅ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊካፈል የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 951, 938, 939, 937, 912 | 54385 | አቶ ፍቃዱ ሽፈራው<br>እና<br>አቶ ግሩም ኤድሚያስ | ጥር 27/2003 | |
| 16. | • የጋብቻ ውል በአግባቡ ተደርጓል ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>• የጋብቻ ውል በሚል በተጋቢዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ከነሙሉ ይዘቱ ሊታይና ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 40 እና ተከታታዮቹ 73, 46/1/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 826/2/ 2427 2428 857 | 56157 | እነ ወ/ሮ ፀሐይ ተሰማ<br>/ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የህፃን አማኑኤል ወንደሰን ሞግዚት | ጥር 09/2003 | |
| 17. | አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚችልባቸው ሁኔታዎች ላይ ሳይንሳዊ የደም ምርመራ (DNA test) በማስተባበያ ማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ስለመሆኑና ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች በዚህ ረገድ የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች በአግባቡ ሊያስተናግዱ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92<br>አንቀጽ 144, 143 /ሠ/, 145 | 62041 | ጥሩወርቅ ወርዶፋ<br>እና<br>ጥሩነሽ ወርዶፋ | የካቲት 11/2003 | |
| 18. | ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ኑዛዜ በውል አዋዋይ ፊት ካልሆነ በስተቀር አይፀናም ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881/3/, 1728/3/, 340, 343/2/ | 50971 | አቶ ሃይሌ ስሙጋ<br>እና<br>ሰላማዊት ተኮላ | የካቲት 25/2003 | |
| 19. | ከውርስ ሃብት ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነና አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ላይ የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው አካለመጠን ከደረሰበት ወይም በመብቱ መጠቀም ከቻለበት ጊዜ አንስቶ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 | 57114 | ወ/ሮ ሃና ፀጋዬ<br>እና<br>ወ/ት ጣዕሙ ደስታ | ግንቦት 03/2003 | |
| 20. | በጋብቻ ውስጥ የተወለድኩ በመሆኔ ልጅነቴ እንዲረጋገጥልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ህጋዊ መሰረት ያለውና ፍ/ቤቶችም ተቀብለው በፍሬ ነገር ረገድ ሊጣሩ የሚገቡትን በማጣራት መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ | 57607 | ኤርምያስ ኬስታንትኖስ ግሊፕትስ<br>እና<br>ሰለሞን ኬስታንቲኖስ ግሊፕትስ | ግንቦት 30/2003 | |
| 21. | • ኑዛዜ አድራጊ "ስታመም አላስታመመችም " በሚል ምክንያት ተወላጅን በኑዛዜ ለመንቀል የሚያስችለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>• ኑዛዜ በተደረገበት ንብረት ሟች መብት የሌለው በሆነ ጊዜ ሊከተል ስለሚችለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1047, 938, 939, 915, 912 | 57836 | ወ/ሮ አስናቀች ደሳለኝ<br>እና<br>የድርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን | ግንቦት 17/2003 | |
| 22. | • ኑዛዜ ህጋዊ አይደለም እንዲሻር በሚል ተቃውሞ እስከቀረበ ድረስ በየትኛውም ህጋዊ መስፈርት መሰረት ፍ/ቤት ኑዛዜውን ውድቅ ሊያደርገው ስለመቻሉ<br>• በኑዛዜ ላይ የነበሩ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ስለሚኖረው ዋጋ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881-883 | 59268 | ወ/ሪት ዝባድ ታዬ<br>እና<br>እነ ብፁአን ታዬ /ሦስት ሰዎች/ | ግንቦት 03/2003 | |
| 23. | ከውርስ ጋር በተገናኘ በህግ ወራሽ የሆኑ ሰዎች ሟችን ለመውረስ ያልተገቡ ናቸው ሊባል የሚችልበት ሁኔታ ሟች በኑዛዜው ከውርስ ሊነቅላቸው ከሚችልበት ሁኔታ የተለየ ስለመሆኑ | 49713 | እነ የጥሩነሽ አየለ ወራሾች<br>/አራት ሰዎች/ | ሚያዝያ<br>03/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 838, 937/1/, 938/2/, /3/ | | እና<br>ወ/ሮ ወጋየሁ ሠለሞን | | |
| 24. | • ተናዛዥ የሆነ ሰው ተወላጁ የሆነ ሰው በውርስ ሊደርሰው ከሚገባው ድርሻ ከሩብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የሰጠው ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆኑ በዳኞች ሊመረመር የሚገባው ስለመሆኑ<br>• “ስላልረዱኝ ወይም ስላልጠየቁኝ” የሚል ምክንያት በመስጠት ተወላጅን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ድርሻ ሩብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913, 1123 | 55648 | እነ ወ/ሮ እቴቱ ሽፈራው<br>/ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መንበረ ሽፈራው<br>/ሦስት ሰዎች/ | ሚያዝያ<br>20/2003 | |
| 25. | የልጅ አባት ነህ የተባለ ሰውን በተመለከተ የመካድ ክስ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 177/3/ | 61677 | አቶ ፈቃደ መክብብ<br>እና<br>አቶ ዳንኤል ብስራት | ሚያዝያ<br>18/2003 | |
| 26. | ከጋብቻ በሞት መፍረስ ጋር በተገናኘ የሚቀርብ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው ከፈረሰበት ዕለት አንስቶ እንጂ ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1846, 826/1/ | 59539 | እነ አቶ ስዩም ወ/መስቀል<br>/አራት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሪት አምሳለ ሙሉነህ | ሰኔ 29/2003 | |
| 27. | አስቀድሞ የተደረገን የጋብቻ ውል በማሻሻል የተደረገ የጋብቻ ውል ህጋዊ ተቀባይነት እንዲኖረው ፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ ያለበት ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 47/1-3/ | 60725 | አቶ አብርሃ የኒላሸት<br>እና<br>ወ/ሮ አበባ ዘመን | ሰኔ 27/2003 | |
| 28. | ባልና ሚስት በፍቺ ወቅት የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል ስምምነት ላይ ያልደረሱ ከሆነና ንብረቱ በአይነት ሊካፈል የማይችል እንደሆነ ንብረቱ ተሽጦ የተገኘውን ዋጋ እኩል እንዲካፈሉ መደረግ ያለበት እንጂ በእጣ እንዲካፈሉ ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 103/1/ | 61788 | ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለማ<br>እና<br>ታፈሰ ተሰማ | ሰኔ 14/2003 | |
| 29. | በሁለት ሰዎች መካከል የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያዝ ጭብጥ በሁለቱ ሰዎች መካከል ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማረጋገጥ በሚል ከሚያዘው ጭብጥ የተለየ ወይም አንድ አይነት ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 | 60691 | ወ/ሮ ገዛችን ገብሩ<br>እና<br>ወ/ሮ ዓለምነሽ በየነ | ሐምሌ 12/2003 | |
| 30. | አባትነትን /ልጅነትን/ ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታና ክርክር የዲኤን.ኤ (DNA) ምርመራ እንዲደረግለት በመጠየቅ ክርክር የሚያቀርብ ወገን ለዚሁ የህክምና ማስረጃ የሚያስፈልገውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 259/1/ | 63195 | ገረመው ሙሜቻ<br>እና<br>ወ/ሮ አሰፋ ነበበ | ሐምሌ 26/2003 | |
| 31. | ጋብቻ ሳይፈርስ የትዳር ግንኙነቱን ትቶ የሄደ ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት የተፈራን ንብረት የጋብቻ ውጤት ነው በማለት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ በጋብቻ ወቅት የተፈራን ንብረት የጋራ ይሆናል በሚለው የህግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/1/ | 43988 | ወ/ሮ ሰኒያ ሼሳ ተማም<br>እና<br>እነ ወ/ሮ በላይነሽ ማቴቦ<br>/ሁለት ሰዎች/ | መስከረም<br>24/2003 | |
| 32. | ወደ ሌላ አገር ለሥራ በሄደበት ወቅት ህይወቱ ያለፈ ሰው ጋር በተያያዘ የግለሰቡ መደበኛ መኖሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ውርሱ በኢትዮጵያ ውስጥ መከፈት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/በ/ህ/ቁ. 826/1/ | 65621 | እነ ወ/ሮ ታደለች መንግስቱ<br>/አምስት ሰዎች/<br>እና ተጠሪ፡ የለም | ሰኔ 27/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 33. | • የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በሦስት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ/<br>• ከውርስ ሀብት ክርክር ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ንብረቱ በእጅ ከተደረገበት ጊዜ እንጂ ስመሃብቱ ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ ስላለመሆኑ / | 52407 | እነ ወ/ሮ ውለታ ደስታ ወ/ማርያም /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ እቴቴ ደስታ | ህዳር 24/2003 | |
| 34. | • የውርስ ሃብት አጣሪ ሪፖርት በፍ/ቤት መጽደቅ ውጤት<br>• በፍ/ቤት የፀደቀ የውርስ ሃብት አጣሪ ሪፖርትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 አግባብ ተቃውሞ ሲቀርብበት ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | 45905 | ሚስስ ሚላን ፒሲጂ ማልጂ<br>እና<br>እነ ሃንድሬ ፒስ ማልጂ /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 03/2003 | |
| 35. | ከጋብቻ በፊት አንደኛው ተጋቢ የግል መኖሪያ ቤትኖሮት ከጋብቻ በኂላ ሌሎች ተጨማሪ ቤቶችና ግንባታዎች ተካሂደዋል በሚል ከጋብቻ በፊት በስሙ ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት በጨረታ ተሸጦ ለተጋቢዎቹ እንዲካፈል በሚል የሚሰጥ ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | 53814 | እነ አቶ ነስሩ ሰማን /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ ሙህሊሳ ኒጋኒ | ጥቅምት 05/2003 | |
| 36. | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 መሰረት የተደረገ ግልጽ ኑዛዜ ላይ ያለን የተናዛዡ የጣት አሻራ በተመለከተ ክርክር በቀረበ ጊዜና በፎረንሲክ ምርመራ ለማረጋገጥ ካልተቻለ በኑዛዜው የተገኙ ምስክሮች ቀርበው እንዲመሰክሩ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 1677/1/, 2007/2/, 897/1/, 896 | 54013 | ወ/ሮ አስመረት ነጋሲ<br>እና<br>ወ/ሮ ጽጌረዳ ስዩም | ጥር 12/2003 | |
| 37. | • በጋብቻ ውስጥ የሚወለድ ልጅ አባት ባል እንደሆነ የህግ ግምት ሊወሰድ የሚችልበት አግባብ<br>• የዚህ የህግ ግምት የሚቋቋምበት አግባብ እና እንደ ማስረጃ ተወስዶ በፍ/ቤት እውቅና ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 126, 143 | 54024 | አቶ ገ/ሊባኖስ ረዳ<br>እና<br>ወ/ሮ አዜብ አሰፋ | ጥር 10/2003 | |
| 38. | አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ሞግዚት የልጁ ሀብት የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ለመሸጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የኦ/ብ/ክ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 69/95 አዋጅ ቁ. 83/96 አንቀጽ 294, 316<br>የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 277/1/, 292 | 54827 | እነ ሮም ወርቁ ተስፋዬ /አምስት ሰዎች/<br>እና<br>አሰግድ ሽነገለኝ | ሚያዝያ 21/2003 | |
| 39. | አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሞግዚት የልጁ ንብረት የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ስለመሆኑ | 54129 | አቶ ከፍያለው በቀለ<br>እና ወጣት ሶፊያን አብዱልቃድር | ህዳር 01/2003 | |
| 40. | • ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሆኖ የሚችን የውርስ ሃብት ሊካፈል የሚገባ ስለመሆኑ<br>• "በህይወቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥረውብኛል" የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ተወላጅን ለመንቀል የማይቻል ስለመሆኑ<br>• ሟች ካለው ሃብት እጅግ አነስተኛ የሆነ ንብረት /ሀብት/ ለተወላጁ በኑዛዜ የሰጠ እንደሆነ በውጤት ደረጃ ተወላጁ የተነቀለ መሆኑን መገንዘብ የሚቻልና ተወላጁ ከሌሎች የጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚዎች ጋር እኩል መካፈል ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 912, 938, 939, 915, 1014, 1123 | 58338 | እነ አቶ ዳንኤል ጽጌ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የህፃን አሳለፈ ጽጌ ሞግዚት | ሚያዝያ 06/2003 | |
| 41. | • የውርስ ሃብት አጣሪ የሆነ ሰው የሟችን ንብረት በማጣራት ረገድ ሊኖረው የሚችለው የስልጣን አድማስ<br>• በወራሾች መካከል አንድን ንብረት በተመለከተ የውርሱ ሃብት አካል ስለመሆኑ ክርክር በተነሳ ጊዜ አጣሪው ግራ | 66727 | ወ/ሪት ዝናሽ ዘውዱ<br>እና | ሐምሌ 29/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ በሪፖርቱ ላይ በማስፈር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍ/ቤት ማቅረብ እንጂ ማስረጃዎቹን በራሱ መዝኖ አከራካሪው ንብረት የውርሱ ሃብት አካል ነው ወይም አይደለም በማለት ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956 | | የወ/ሮ መድሐኒት ካሣ ወራሽ<br>እነ ወ/ሮ ደብሪቱ ስዩም | | |
| 42. | ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የተፈራ ቤት በጋብቻ ወቅት እድሳት የተካሄደለት መሆኑ ብቻ ንብረቱን የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት የማያደርገው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥ. 213/92 አንቀጽ 42/1/, 57 | 45207 | ወ/ሮ አየለች ከበደ<br>እና<br>በላቸው ዋለ | ሰኔ 16/2002 | |
| 43. | • ተወላጅ የሆነ ሰው ከውርስ ተነቅሏል ሊባል የሚችለው ተናዛዡ ንብረቱን በጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ለሌሎች ተወላጆች ወይም ሌሎች ሰዎች የሰጠ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>• ሚች ያለው አንድ የታወቀ ንብረት ብቻ ሆኖ ይህንኑ ከተወላጆቹ መካከል አንዱን ወይም ሁሉንም ሳያካትት ለሌሎች ሰዎች በኑዛዜ የሰጠ እንደሆነ ተነቀልኩ የሚል ወገን ኑዛዜው ላይ ተቃውሞ ሊያነሳ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 937-939, 842/2/, 915 | 47917 | እነ ወ/ሮ መልካምሥራ አሰበል /አራት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ አንለይ ሲበን | ግንቦት 05/2003 | |
| | **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | |
| 44. | • በህብረት ስምምነት ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር የህብረት ስምምነት ከተፈረመበት ዕለት አንስቶ የሚፀና ስለመሆኑ<br>• የህብረት ስምምነት በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ እንዲመዘገብ የሚደረገው ድርድር ተደርጐበት ከተፈረመበት በኂላ ስለመሆኑ<br>• በተደራዳሪ ወገኖች በተሟላና በአግባቡ ያልተፈረመ የህብረት ስምምነት በፍርድ ሃይል እንዲመዘገብ የሚደረግበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124-135 | 54451 | የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ<br>እና<br>የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ መ/ሰ/ማህበር | መስከረም 27/2003 | |
| 45. | አንድ ሰራተኛ ለሥራ ከሚጠቀምበት መሳሪያ ብልሽት መከሰት ጋር በተገናኘ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው አሰሪው ግዴታና ኃላፊነቱን በአግባቡ የተወጣ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 12/1//ሀ/ | 48945 | አቶ አየለ አበበ<br>እና<br>የፊንፊኔ የደን ድርጅት | ህዳር 27/2003 | |
| 46. | የህብረት ስምምነት የሌለው አሰሪ ሰራተኛው የዲሲፒሊን ጉድለት ፈጽሟል የሚልበትን ጉዳይ ለማጣራትና ለመመርመር ሰራተኛውን ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ለማገድ ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/ | 53985 | ዳሸን ባንክ አ.ማ<br>እና<br>አቶ ዘነበ ድንቁሳ | ህዳር 13/2003 | |
| 47. | በህብረት ስምምነት ላይ ከተመለከቱ ሁኔታዎች ውጪ ሰራተኛን ያለአግባብ አዛውሮ የማሰራት ተግባር ህጋዊ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ | 54326 | አንበሳ ጫማ አ.ማ<br>እና ወ/ሮ እትሁን አያሌው | ህዳር 03/2003 | |
| 48. | በስራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተያያዘ የአሰሪው ኃላፊነት በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ (strict liability) ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96, 97 | 57068 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሰናይት መጫ /ሦስት ሰዎች/ | ህዳር 28/2003 | |
| 49. | ከስራ ተሰናበትኩ በማለት አቤቱታ የሚያቀርብ ሠራተኛ በእርግጥም ስለመሰናበቱ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማቅረብ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ | 57541 | የቻይና መንገድና ድልድይ ሥራ ድርጅት<br>እና ግርማ ቡሽራ | ህዳር 14/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 50. | በአዋጅ በተቋቋመ የት/ት ተቋም ውስጥ በሚገኝና በራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደርና ሠራተኞችን ቀጥሮ በሚሠራ ክበብ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ እና ተቋሙን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ተፈፃሚ ይሆናል ለማለት የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96<br>አዋጅ ቁ. 515/96<br>አዋጅ ቁ. ደንብ ቁጥር 61/96 | 46075 | አቶ ንጉስ ሃዱሽ<br>እና<br>የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ዲን | ታህሳስ 25/2003 | |
| 51. | ከሥራ ክርክር ጋር በተገናኘ አሰሪና ሠራተኛው ያደረጉት የሥራ ቅጥር ውልን አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን የሚገዛው ከኢትዮጵያ ሌላ /ውጭ/ የሆነ አገር ህግ መሆኑንና የሥራ ቦታውም ቢሆን ከኢትዮጵያ ውጪ እንዲሆን የተስማሙ እንደሆነ ጉዳዩ በአጠቃላይ የአለም አቀፍ የግለሰብ ህግ (private international law) ጥያቄን የሚያስነሳ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው?፣ በየትኛው አገር ህግ መሰረት?፣ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/ | 60685 | አቶ በዛብህ እሸቴ<br>እና<br>ሳሊኒ ኮንስትራክሽን | የካቲት 21/2003 | |
| 52. | አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ታግዶ /የሥራ ውሉ ተቋርጦ/ በነበረበትና ባልሰራበት ዓመት አሰሪው ለሌሎች ሠራተኞች የከፈለውን የቦነስ ክፍያ ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43, 45/5/, 53 | 59320 | ጊዮን ሆቴሎች ድርጅት<br>እና<br>አቶ ስለሺ አምዴ | ግንቦት 15/2003 | |
| 53. | አሰሪ ሠራተኛው ጥፋት እንደፈፀመ አውቆ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማሰናበት እርምጃ አለመውሰዱ ስንብቱን ህገ ወጥ የሚያደርገው ቢሆንም ሠራተኛውን ወደ ሥራው እንዲመልስ ላይገደድ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/ | 64079 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ ጌትነት መኮንን | ግንቦት 17/2003 | |
| 54. | በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተያያዘ የጉዳቱን አይነትና መጠን መለየት የሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ /ሀ/ለ/ 101/2/ 100 96/1/ 99/1/ | 60464 | የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ግርማ ወዩሳ | መጋቢት 06/2003 | |
| 55. | ከአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪው ሠራተኛው የሚጠይቀውን የገንዘብ ክፍያ በማመን የፃፈው ደብዳቤ ሠራተኛው መብቱን ለማስከበር በሚያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ የሚቆጠረውን ይርጋ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 164/3/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852/1/ | 63635 | አቶ ጉልላት ወልዴ<br>እና<br>የሽቀጦች ጅምላ | ሰኔ 27/2003 | |
| 56. | • አንድ ሠራተኛ ቦነስ ወይም ድጉማ ሊያገኝ የሚችለው ከአሰሪው ጋር በሚደረግ /በሚኖር/ ስምምነት እንጂ በህጉ አሠሪ ለሠራተኛው በቦነስ ድጉማ እንዲከፍል በአስገዳጅነት የተመለከተ ነገር የሌለ ስለመሆኑ<br>• የቦነስና ድጉማ አሰጣጥና አፈፃፀምን በተመለከተ በህብረት ስምምነት የተመለከተ ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 4, 12, 13, 53 | 64758 | እነ ተመስገን ገ/እየሱስ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ሰኔ 17/2003 | |
| 57. | •አንድ ሠራተኛ አሰሪው በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሰረት ሊከፍለው የሚገባውና ያልከፈለው ክፍያ መኖሩን /እንዳለ/ በተረዳ ጊዜ አሰሪውን የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>•የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት በቀጠለበት ሁኔታ ሠራተኛው በአንድ ወቅት ሊከፈለኝ /ሊጠበቅልኝ/ ይገባል በማለት ያቀረበው የመብት ወይም የክፍያ ጥያቄ በፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በሌላ ጊዜ መብቱን ከመጠየቅ የሚያግደው | 66242 | ወ/ሮ ሙሉ ደምሴ<br>እና<br>ሸራተን አዲስ | ሐምሌ 13/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 12<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 216 | | | | |
| 58. | በአዋጅ ቁ. 147/91 መሠረት በተቋቋመ ማህበር ውስጥ ላሉ ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 377/96 ተፈፃሚ ስለመሆኑ | 59579 | ወ/ሮ አሞኘሽ ገብሬ<br>እና<br>የአቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎች<br>የእጅ መሣሪያዎች አ/ማ<br>ሠራተኞች የገንዘብና ቁጠባ<br>ብድር ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ግንቦት 16/2003 | |
| 59. | የጡረታ መብት ያለው የመንግስት ልማት ድርጅት ሠራተኛ ሊያገኝ ስለሚገባው ካሣ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9/1/ | 65427 | ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ<br>እና ወ/መድህን ቢረዳ | ግንቦት 15/2003 | |
| 60. | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ሠራተኞች እየሠሩ የሚገኙትን ሥራ በተመለከተ የሥራ ውል አላደሱም ወይም ለማደስ ፈቃደኛ አይደሉም በሚል ለማሰናበት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ | 62370 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪከ ኃይል<br>ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ እዮብ መለሰ /አራት<br>ሰዎች/ | ታህሳስ 26/2003 | |
| 61. | • በአዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የሠራተኛ ማህበር ለማቋቋም የሚቻልበት አግባብ<br>• የሰራተኛ ማህበር ለማቋቋም መብት የተሰጣቸው በአዋጅ ቁ. 377/96 የሚተዳደሩ ሰራተኞች ብቻ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 114, 115, 118, 2/4/, 113<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 42/1/ /ሀ/, 31 | 55731 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ<br>ሰራተኛ ማህበር<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ማህበራዊ ጉዳይ<br>ሚንስቴር | የካቲት 22/2003 | |
| 62. | • የሠራተኛ ደመወዝ ሊቀነስ የሚችለው በህግ፣ በህብረት ስምምነት፣ ወይም በሥራ ደንብ በተወሰነው መሰረት ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ብቻ ስለመሆኑ<br>• አሰሪ የሠራተኛን ደመወዝ በራሱ ውሣኔ ሊቀንስ፣ ሊይዝ ወይም የዕዳ ማቻቻያ ሊያደርግ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 59/1/ | 59666 | የኦሮሚያ መንገዶች<br>ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ አቡ ጉበና | ግንቦት 04/2003 | |
| 63. | • የደረጃ እድገት በድርጅት ውስጥ በሥራ ላይ ባለ የእድገት አሰጣጥ ስርዓት እና ደንብ መሰረት የሚካሄድ ስለመሆኑ<br>• የደመወዝ ጭማሪ ሊገኝ የሚችለው በእድገት ወይም አሰሪው የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ የሚችልበት አግባብ ኖሮት ሲጨመር ስለመሆኑ<br>• በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) መሠረት የተደረገ የሥራ ምደባ የደመወዝ ጭማሪ የማያስገኝ ስለመሆኑ | 64821 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃየል<br>ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አያሌው ሕብስት | ግንቦት 01/2003 | |
| 64. | ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ አቤቱታ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ | 53527 | የኢትዮጵያ ፖስታ<br>አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ በዳሶ መልካቶ | መስከረም<br>27/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 65. | የመከላከያ ሰራዊት አባል ያልሆነ የመንግስት ሰራተኛ በፍቃዱ ሥራ በለቀቀ ጊዜ የስንብት ክፍያ ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ<br>የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95 | 61872 | የኢትዮጵያ ፐልፐና ወረቀት አ/ማ<br>እና አብዱልቃድር አደም | የካቲት 10/2003 | |
| 66. | ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውና በባለሃብትነት ሊያዝ የሚችልን የአሰሪ የሆነ ነገር ላይ ሠራተኛው ሆን ብሎም ሆነ በቸልተኝነት በማናቸውም ሁኔታ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/ | 64988 | ዳሸን ባንክ አ/ማ<br>እና<br>አቶ ሃይሉ ሽመልስ | ግንቦት 30/2003 | |
| 67. | • የመንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ የሚነሳ ክርክር የሚስተናገድበት ህግና የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ<br>• ይግባኝ ለማቅረብ ጊዜ ያለፈበትን አቤቱታ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚቻልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 76/2/<br>አዋጅ ቁ. 6/2000 አንቀጽ | 61843 | ሰይፉ ናስር<br>እና<br>የአ.አ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዮች | መጋቢት 23/2003 | |
| 68. | ለተወሰነ ጊዜና ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ ጊዜው ደርሶ መሰናበቱ ምንም እንኳን ሌሎች ሠራተኞች በእሱ ምትክ የተቀጠሩ ቢሆንም ህገ ወጥ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ | 57337 | አድቬንቲስት የልማት ተራድኦ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ገበየሁ ወ/ሚካኤል | ሰኔ 15/2003 | |
| 69. | በአሰሪና ሰራተኛ ስምምነት የሚዘጋጅ የህብረት ስምምነት ውስጥ የተካተቱ ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችሉ ምክንያቶች ጥፋትን መሰረት ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1//ተ/ | 64734 | ካንትሪ ክለብ ዴበሎበር የረር ቪው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት<br>እና<br>እነ አቶ በቀለ ለማ /ሦስት ሰዎች/ | ሰኔ 16/2003 | |
| 70. | የግንባታ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት ከ3ኛ ወገን ጋር ባደረገው የግንባታ ሥራ ውል መነሻነት የቀጠረውን ሰራተኛ የግንባታ ሥራው ውል በመቋረጡ ምክንያት ማሰናበቱ ህገ ወጥ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/4/, 4/1/, 10, 9 | 66306 | አምሳሉ ወረዳ ኮንስትራክሽን አ/ማ<br>እና<br>እነ አቶ መሐመድ ሰይድ /ስድስት ሰዎች/ | ሰኔ 03/2003 | |
| 71. | የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል በመጠርጠሩ የተነሳ ከሥራ ታግዶ የነበረና በኋላም የተሰናበተ ሠራተኛ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ የፍ/ቤት ውሣኔ ያልቀረበ በመሆኑ ብቻ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑና ጉዳዩን በማስተናገድ ላይ የሚገኝ ፍ/ቤት የሠራተኛውን ስንብት አግባብነት ለመወሰን ማናቸውንም ማስረጃ አስቀርቦ በመመልከት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያለበት ስለመሆኑ | 59906 | የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት<br>እና<br>ኃይለማርያም ሻረው | የካቲት 09/2003 | |
| 72. | ከሥራ ጋር ባልተገናኘ /ተፈጥሮአዊ/ ሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሥራ ስንብት ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ | 18495 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና ወ/ሮ አሚናት ገበየሁ | መጋቢት 18/1999 | |
| 73. | • የቦነስ ክፍያ ለሠራተኛ የሚከፈለው በሥራ ላይ ያለ ሰራተኛ ወደፊት በርትቶ እንዲሰራ ለማበረታታት ብቻ | 20869 | አቶ አዲሱ አቦሴ | ሰኔ 30/1998 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሳይሆን በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት የሰራው ሥራ ለአሰሪው ትርፋማ ውጤት በማስገኘቱ የትርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ጭምር ስለመሆኑ<br>• የቦነስ ክፍያ ተጠቃሚ ለመሆን ሠራተኛው ድርጅቱ /ተቋሙ/ ትርፋማ ውጤት ባስገኘበት ዓመት በሥራ ላይ የነበረና አስተዋጽኦ ያደረገ መሆን ያለበት ስለመሆኑ | | እና<br>የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን | | |
| **ንብረት** | | | | | |
| 74. | ቤትና ቦታዬን ያለአግባብ ተነጠቅሁ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ታይቶ ፍርድ ሊሰጥበት የማይችል አስተዳደራዊ ጉዳይ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4 | 48217 | ወ/ሮ አባዲት ለምለም<br>እና<br>እነ የዛለአንበሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 03/2003 | |
| 75. | የመሬት ይዞታ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በተወሰደ ጊዜ ካሣ የሚከፈለው በተወሰደው ይዞታ ላይ ንብረት የነበረ መሆኑ እንዲሁም ንብረቱን ለመተካት ከሚያስፈልገው ወጪ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 401/96 አንቀጽ 9/1/, 10<br>አዋጅ ቁ. 455/97 | 52496 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>እነ አቶ ከድር ኃሌጅንሶ /አስራ ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 16/2003 | |
| 76. | • አንድ ሰው የንብረት ባለቤት የሚሆነው በጉልበቱ፣ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንብረትን ያፈራ እነደሆነ ስለመሆኑ<br>• የፍርድ ባለዕዳ የሆነ ሰው ንብረቱ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዳይውል አስቦ አካለ መጠን ባልደረሰ ህፃን ልጁ ስም ማዞሩ ብቻ ከኃላፊነት ሊያድነው የሚያስችል ስላለመሆኑና ይህ በመሆኑም ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የለም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/2/ | 55081 | ወ/ሪት ራሔል ሥነ ፀሐይ<br>እና<br>አቶ መስፍን ታምራት | ጥቅምት 18/2003 | |
| 77. | • መንግስት አንድን የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚወስድበት ጊዜ ሊከተለው ስለሚገባው ሥነ ሥርዓት<br>• ለህዝብ ጥቅም ሲባል ንብረቱ የተወሰደበት ሰው የተሰጠው ግምት ከንብረቱ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ አይደለም በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1460-1488 | 50810 | እነ አቶ ፀጋዬ መሠረት /ሰባ ዘጠኝ ሰዎች/<br>እና<br>የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን | ጥቅምት 30/2003 | |
| 78. | የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ስመ ሃብት ይዞ መገኘት የንብረቱ ባለቤት አድርጐ የማያስቆጥር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196 | 47139 | አቶ የሱፍ ሁሴን<br>እና<br>አቶ አደን አብደላ | ህዳር 30/2003 | |
| 79. | አዋጅ ቁ. 47/67 ከመውጣቱ በፊት የተደረገ የመሬት ኪራይ ውል ህጋዊ አስገዳጅነት ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67 | 48086 | እነ ወ/ሮ አሰለፈች ወልደሚካኤል /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ቶታል ኢትዮጵያ አክሲዮን | ህዳር 03/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ማህበር | | |
| 80. | • ፍ/ቤቶች በሚቀርቡላቸው አቤቱታዎች ላይ ህግን ተፈፃሚ ለማድረግ የቀረበውን የክስ አርእስት ብቻ ሳይሆን ይዘት ጭምር መመልከት የሚገባቸው ስለመሆኑ<br>• ከንብረት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149/1/ መሰረት ሁከት የተፈጠረበት ሰው እንዲወገድለት ይዞታው የተወሰደበት ሰው ደግሞ እንዲመለስለት በሚል ዳኝነት የሚጠየቀው አቤቱታ የቀረበበት ንብረት ተገምቶ ተገቢው ዳኝነት ከተከፈለበት በኋላ ስለመሆኑና በጥቅሉ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድ (cessation of interference) እንደሆነ ተቆጥሮ ልክ አቤቱታቸው በገንዘብ የማይገመቱ አቤቱታዎች አይነት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑና የይርጋ ደንብ ተፈፃሚ የማይሆን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149/2/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 16, 226/3/ | 49985 | ሻለቃ አሰፋ አየለ ደምሴ<br>እና<br>ፍቃዱ ሙሉጌታ | ህዳር 28/2003 | |
| 81. | መሬት በፍ/ብሔር ግንኙነት የተፈጠረን ዕዳ ለመክፈል ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/3/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678/2/ | 49200 | አቶ ጋሻው በጉሰው<br>እና<br>አቶ አለበል መከተ | ህዳር 01/2003 | |
| 82. | የከተማ መሬት ይዞታን እንዲለቅ የተደረገ ባለይዞታ በተወሰነለት የካሣ መጠን ላይ ካልተስማማ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት በከተማው አስተዳደር ሥር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አካል ስለመሆኑ እና በመደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ሊታይ የሚችለው በይግባኝ ብቻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 11/2/, /4/ | 57271 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ጃዳ ብሩ | ታህሳስ 27/2003 | |
| 83. | • የማይንቀሳቀስ ንብረት /ህንፃ/ ግንባታ ሥራ ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ድንጋጌዎች<br>• የሥራ ተቋራጭነት ውል ተፈጽሟል /አለ/ ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>• የግንባታ ሥራ ውል በልዩ ፎርም መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3019-3040 | 47526 | ዛፍኮ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ብሔራዊ መሐንዲሶች ስራ ተቋራጭ ድርጅት | ግንቦት 15/2003 | |
| 84. | • የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በቅን ልቦና የተደረገ ነው በሚል ምክንያት ብቻ በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የማይችል ስለመሆኑ<br>• በህግ ፊት በማይፀና ሁኔታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው ይህንኑ ንብረት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የሚያደርገው የሽያጭ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>• የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ መብት ከሌለው ሰው እያወቀ የሽያጭ ውል የፈፀመ ገገር በቅን ልቦና የተደረገ ነው በሚል የሕግ ጥበቃ የሚደረግበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196, 2882-2884 | 60720 | ወ/ሮ ሄርያ መሐመድ ግርግቦ<br>እና<br>አቶ ሽምሱ የሱፍ | ግንቦት 15/2003 | |
| 85. | ተከራይ ለሆነ ወገን በተከራየው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት ወይም ሌላ መብት አለን በማይሉ 3ኛ ወገኖች አድራጐት ለሚነሳ ሁከት አከራይ ዋስትና እንዲሰጥ የማይገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2914/1/, /2/, 2913/1/, /2/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 | 63042 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ሰለሞን ነጋሽ | ግንቦት 01/2003 | |
| 86. | ለህዝብ ጥቅም ሲባል ይዞታውን እንዲለቅ የተደረገ ሰው በመሬቱ ላይ የሰፈረውን ንብረት ለመተካት ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ በይዞታው ላይ የነበረው ንብረት በመፍረሱ የተነሳ የተቋረጠ ገቢ /የታጠ ጥቅም/ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ 2/1//ለ/, 7/1/2/ ደንብ ቁ. 135/99 | 63352 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ቱሌ አብዶ | ሐምሌ 13/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 87. | • ተከራይ በይዞታው ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ ባለበት ዕዳ ምክንያት ባለገንዘብ የሆነ ወገን ንብረቱን መረከቡ በተከራዩ ላይ የሁከት ተግባር ፈጽሟል የማያስብል ስለመሆኑ<br>• የተከራዩ እና በንብረቱ ላይ መብት ያለው ባለገንዘብ የሚኖራቸው ተነፃፃሪ መብት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140 1149 2933/1/ 2899 2931<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 6 | 62858 | ፐዝፋ ይንደር ኢንተርናሽናለ ኢትዮጵያ<br>እና<br>እነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ /ሁለት ሰዎች/ | ግንቦት 16/2003 | |
| 88. | ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚመለከተው የአስተዳደር አካል እንዲፈርስ መረጃ የደረሰው በመሆኑ ቤቱን ያፈረሰ ሰው የአስተዳደር አካሉ የዲዛይን ለውጥ አድርጐ ቤቱ ከፈረሰ በኂላ የግለሰቡን ይዞታ /ንብረት/ መፍረስ የማያስፈልግ መሆኑን መግለፁ ካሣ የመክፈል ግዴታውን ቀሪ የማያደርግ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 322/97<br>አዋጅ ቁ. 455/97 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት art. 40/2/ | 62293 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>እነ አቶ መስፍን ጀንበሩ<br>/ሁለት ሰዎች/ | ግንቦት 15/2003 | |
| 89. | • አንድ ሰው የሌለውን ነገር ሽጦ በተገኘ ጊዜ ገገርው በህግ ሊያገኝ ስለሚገባው መፍትሔ<br>• በሌለ መብት መሥራት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2884/1/ /2/, 2282-2285, 1716 | 51034 | ታሪክ ጌታቸው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አልጋነሽ ተጠምቀ<br>/ሁለት ሰዎች/ | የካቲት 22/2003 | |
| 90. | • የኮንዶሚንየም ቤትን ዋጋ በአጠቃላይ የከፈለ የኮንዶሚንየም ቤት ባለቤት በፍርድ የተወሰነበት የሌላ ሰው ዕዳ ያለበት በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ቤቱ በአፈፃፀም ተሽጦ ለዕዳው መክፈያነት እንዲውል ለማዘዝ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>• የኮንዶሚንየም ቤት ባለህብት የሆነ ሰው በራሱ ፈቃድ ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም ለ3ኛ ወገን ለማስፈላለፍ የሚችለው ያለበትን የቤቱን ዋጋ አጠናቅቆ ከከፈለበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት ካለፈ በኂላ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 19/97 አንቀጽ 21, 14/2 | 56011 | አቶ ሳሙኤል ታደሰ<br>እና<br>ወ/ሮ እጥፍወርቅ ኃይለማርያም | መጋቢት 23/2003 | |
| 91. | • በህጋዊ መንገድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ውል ያገኘ ገገር የሚመለከተውን የአስተዳደር አካል የስም ዝውውር እንዲፈጽምለት በፍ/ቤት ለመክሰስ የሚችል ስለመሆኑ<br>• የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት ካልተወጣ ገዥ መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚገባው በዚሁ የአስተዳደር አካል ላይ ስለመሆኑ<br>የአማራ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ. 91/96 እና ደንብ ቁጥር 12/2000 | 49428 | እነ ወ/ሮ ከበቡሽ ልሳነወርቅ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>እነ አቶ ፀዳሉ አዳነ /ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 28/2003 | |
| 92. | ሚች ከቀበሌ ተከራይቶት የነበረን መኖሪያ ቤት ወራሽነትን በማረጋገጥ ብቻ በቤቱ ውስጥ የመኖር ህጋዊ መብት ሊገኝ የማይችል ስለመሆኑና ተቀባይነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊቀርብ ስላለመቻሉ | 57045 | የልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ አሰፋ | ጥር 25/2003 | |
| **ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር** | | | | | |
| 93. | በስህተት ለጉምሩክ የተከፈለ ቀረጥ ተመላሽ የሚደረገው ስህተቱ መኖሩን ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወቀና ዕቃውም የጉምሩክ ስነ ስርዓትን አጠናቅቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ ባለው 6 ወር ውስጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 15 | 53749 | የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ<br>እና<br>አቶ አዱኛ አበሉ | ጥቅምት 18/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 53, 55 | | | | |
| 94. | ከቀረጥ ነፃ በሆነ መልኩ ለግል አገልግሎት እንዲውል የገባ መኪናን ለንግድ ማዋል በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/, 78 | 54203 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ ሙሉእመቤት ኃ/ሚካኤል | ህዳር 27/2003 | |
| 95. | ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎችን አስመልክቶ ስለሚካሄድ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሥርዓት እና በዕቃው ላይ ስለሚከፈል ግብር /ታክስ/<br>አዋጅ ቁ. 173/91 አንቀጽ 6/1/, 4/1/ | 50375 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ለተብርሀን አድሀኖም /ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 13/2003 | |
| 96. | የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግን ተላልፏል በሚል በወንጀል የተከሰሰና ስራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው አልነበረም ወይም አያውቅም በሚል ምክንያት ከወንጀል ኃላፊነት ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 56/1/ 55<br>አዋጅ ቁ. 609/209 አንቀጽ 22/1/ 50/ለ//1/ | 51090 | እነ ዘ ቲዊንስ ባርና ሬስቶራንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/<br>እና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን | ታህሳስ 12/2003 | |
| 97. | • የጉምሩክ ባለስልጣን ኮንትሮባንድ እንደተፈፀመበት በበቂ ሁኔታ የጠረጠረውን ተሽከርካሪ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ለሚያደርገው ማጣራት ለባለንብረቱ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፈል የማይጠየቅ ስለመሆኑ<br>• ባለስልጣኑ በቁጥጥሩ ሥር የሚያውላቸው ተሽከርካሪዎች የተያዙበትን ጉዳይ ለማጣራት ከሚያስፈልገው ተገቢና ምክንያታዊ ጊዜ በላይ የሆነ እንደሆነ የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ<br>• በባለስልጣኑ ቁጥጥር ሥር የቆዩ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የተቋረጠ ገቢ ይከፈለን በሚል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤት የተጠየቀውን ገቢ ህጋዊነት እና ትክክለኛነት በማረጋገጥ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 6/5/ 58/1//1<br>አዋጅ ቁ. 368/95 | 43996 | የሰሜን ምስራቅ ጉምሩክ ሚሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>በረከት አሰፋ | ጥር 10/2003 | |
| 98. | • አንድ ግብር ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ግብር ከፋይነት ተመዘገበ የሚባለው በባለሥልጣኑ ከተመዘገበበት ዕለት ወይም ምዝገባው እንደሚፀና ከተገለፀበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ<br>• የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ተመዝጋቢ የሆነ ሰው ከተመዘገበበት ዕለት ጀምሮ ለሚያደርገው ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለተጠቃሚው ወዲያውኑ ያልሰጠ መሆኑ በወንጀል የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ<br>• እውቅና ያልተሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መጠቀም በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 471/98 አንቀጽ 5<br>አዋጅ ቀ. 285/94 አንቀጽ 64, 3/1/ና/2/, 22/1/<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 117<br>ደንብ ቁጥር 139/99 አንቀጽ 22<br>መመሪያ ቁጥር 46/99 | 59851 | አቶ አለሙ ጋባ<br>እና<br>የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | የካቲት 11/2003 | |
| 99. | • በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 368/95 /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 74 ሥር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ሊጣልበት ስለሚችለው የቅጣት አይነትና መጠን | 48628 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ | ግንቦት 05/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • በኮንትሮባንድ ዕቃ ሲያጓጉዝ የተገኘ ተሽከርካሪ ሊወረስ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 60/89<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 64/4/, 74 | | እና<br>አቶ በርሄ ሐጐስ | | |
| 100. | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አስቀድሞ በዋስትና ለሌላ ሰው ያልተሰጡ የግብር ከፋይ ንብረቶች ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/, 78/1/ | 57100 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስለጣን በጅማ ቅ/ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ አቶ አዳራ ሰይድ /ሁለት ሰዎች/ | ግንቦት 30/2003 | |
| 101. | የተሽከርካሪ ባለንብረትና ሹፌር በመሆን የኮንትሮባንድ ወንጀል በተሽከርካሪ በመታገዝ የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የግለሰቡን የወንጀል ጥፋተኝነት ውሣኔ ተከትሎ ተሽከርካሪው እንዲወረስ ትዕዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 91/2/, 2/1/ | 64819 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ አንተነህ ካሣዬ | ሰኔ 30/2003 | |
| 102. | ከቀረጥ ነፃ፣ በቅናሽ ቀረጥ ወይም በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ የገባን ዕቃ ህግን በሚቃረን መልኩ የቀረጥ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት ምክንያት ውጪ መጠቀም /ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት/ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/ /ሀ/ /ለ/ /2/ | 58266 | ወ/ሮ አልማዝ ደሴ<br>እና<br>የጉምሩክ ዓ/ህግ | ሰኔ 03/2003 | |
| 103. | • አንድ ዕቃ /ንብረት/ ኮንትሮባንድ ነው ወይም የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈፀመበት ነው በሚል በቁጥጥር ስር ሊውል የሚችልበት አግባብ<br>• የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ዕቃው ኮንትሮባንድ እንዲባል የሚያደርግ ስለመሆኑና የኮንትሮባንድ ወንጀልን የሚያቋቁም ስለመሆኑ<br>• "የጉምሩክ ክልል" በሚል የተጠቀሰው ሃረግ አጠቃላይ የኢትዮጵያ የግዛት ክልልን የሚያመላክት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 2/17/, 12/4/, 13/1/, 91/1/, 2/7/ | 60400 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>ኤፍታታ እና ቢኤም ኤም ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ሐምሌ 12/2003 | |
| 104. | በህግ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈፀመበት ዕቃ/ንብረት/ የኮንትሮባንድ ዕቃን ለማሳለፍ በሽፋንነትና በከለላነት ያገለገለ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ የጉምሩክ ባለስልጣን ይህን በሽፋንነትና በከለላነት ያገለገለውን ዕቃ ለመውረስ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 6/5/ 58/1/ /ለ/ 16-18<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 22 | 65656 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሪት ትዕግስት ጥላሁን | ሐምሌ 26/2003 | |
| 105. | የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃን በማጓጓዝ የተያዘ ተሽከርካሪ እንዲወረስ ላይታዘዝ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 104/3/ /ሀ/ አንቀጽ 91/1/ | 57243 | የሚሌ ገቢዎች እና ጉምሩክ<br>እና<br>አቶ ደረጀ ክፍያለው ሲማ | መስከረም 27/2003 | |
| 106. | • ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በደረሰ የአካል ጉዳት ወይም በሞት አደጋ ምክንያት ከሚሰጥ የካሣ ክፍያ በስተቀር ሌሎች በማናቸውም ሁኔታ የሚከፈሉ የካሣ ክፍያዎች ከግብር ነፃ ናቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>• ከሥራ መሰናበት ጋር በተገናኘ ለሰራተኞች የሚሰጥ የመልሶ ማቋቋሚያ የድጋፍ ክፍያ የሥራ ግብር | 65330 | የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር<br>እና<br>እነ አቶ ተክሌ ጋረደው<br>/ስድስት ሰዎች/ | ሰኔ 30/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚከፈልበት ገቢ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 10/1/, 2/10/, 1/11/ | | | | |
| 107. | በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ግብር ከፋይ ይግባኙን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ለማቅረብ የሚችለው በጉባኤው የተወሰነበትን ግብር ይግባኝ ሙሉ በሙሉ ሲከፍል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 112/4/<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43/4/ | 59711 | ሸበል ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ | ሰኔ 14/2003 | |
| **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | | |
| 108. | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በመኪና ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ የመኪናው ባለቤት በደረሰው ጉዳት የተነሳ ሊከተል የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ ተገቢውን ጥረት የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091, 2097/1/ /2/ | 54021 | አቶ ዱላ ያሲን<br>እና<br>ወ/ሮ አበበች እሸቴ | ህዳር 03/2003 | |
| 109. | የህንፃ ተቋራጭ ሠራተኛ በመሆን በሚሠራው ህንፃ ላይ ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ ከህንፃው ወድቆ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሚሰራውን ህንፃ ባለቤት ከውል ውጭ የሆነ ግንኙነትን መሰረት በማድረግ የጉዳት ካሣ ሊጠይቅ የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2077 | 52595 | ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሻሎም ተስፋዬ /አራት ሰዎች | ታህሳስ 15/2003 | |
| 110. | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የዘረጋቸው የኤሌክትሪክ መስመር ገመዶች ለሚያደርሱት ጉዳት ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው ጉዳቱ የደረሰው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በተጐጂው ጥፋት መሆኑን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2086/2/ | 57904 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ ወልዱ ገ/ስላሴ | ታህሳስ 15/2003 | |
| 111. | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተፈፃሚ ከሚሆነው የይርጋ ጊዜ ጋር በተገናኘ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና ጥፋት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ አጥፊው በወንጀል ጉዳይ ክስ ያልቀረበበትና ያልተቀጣ እንኳን ቢሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 /1/ እና /2/ | 58920 | አለምነው አበበ አካሌ<br>እና<br>ህብረት ኢንሹራንስ አ.ማ | የካቲት 22/2003 | |
| 112. | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ፍ/ቤቶች የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የሚሰጡት ውሣኔ በይግባኝ ሊለወጥ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2152, 2153 | 53598 | አቶ ይልማ ደጀኔ<br>እና<br>ወ/ሮ መዲና ዲታሞ | ግንቦት 19/2003 | |
| 113. | የባንክ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ጥፋት ፈጽሟል በሚል በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልበት ብሎም ላደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2524/2/, 1676/1/, 1790/2/, 2090 | 44427 | አቶ ለገሰ ጥቀኔር<br>እና<br>ንብ ኢንተርናሽናል አ.ማ | መጋቢት 09/2003 | |
| 114. | • አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሁብቱ ወይም በጉልበቱ ለደከመው ሰው የመካስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• አንድ ሰው ባለዕዳ መሆኑን ያመነ እንደሆነ ዕዳው የታመነለት ሰው ባለዕዳው ዕዳውን ያመነበትን ምክንያት የማስረዳት /የማረጋገጥ/ ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162 2164 2019 | 59698 | አቶ ሚኪያስ ከበደ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ምስራቅ ንጉሴ /ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት 06/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 115. | • በህክምና ጉድለት ሀላፊነት ሊከተል የሚችልበትና ካሣ የሚከፈልበት አግባብ<br>• የጉዳት ካሣን ለመወሰን የጉዳቱን ልክ በማስረጃ ለማረጋገጥ አዳጋች ሲሆን በርትዕ ለመወሰን የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090, 2102 | 64590 | ሜሪስቶፐስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ<br>እና<br>ወ/ት ሠናይት ዓለማየሁ | ሚያዝያ 18/2003 | |
| 116. | የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥ ተሽከርካሪ ተሳፋሪ በመሆን ሲጓዙ ለሚደርስ ጉዳት አጓገዡ ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችልባቸው ልዩ ሁኔታዎች፣ ኃላፊ በሆነ ጊዜ የኃላፊነቱ መጠን እንዲሁም አጓገዡ በህግ ከተደነገገው የጉዳት ካሣ መጠን በላይ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች<br>የንግድ ህግ ቁ. 595, 596, 599, 588, 597<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2092, 2091 | 67973 | አቶ በቀለ ወልቻም<br>እና<br>አቶ ጥበቡ ጦራ | ሐምሌ 25/2003 | |
| 117. | • መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ልዩ የምዝገባና የባለሀብትነት ስም ዝውውር የሚያስፈልገው ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ንብረት ስለመሆኑ<br>• የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤትነት /ባለሃብትነት/ ወደ ሌላ ሰው ተላልፏል ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>• መኪኖች እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ለሚያደርሱት ጉዳት በኃላፊነት ስለሚጠየቀው ወገን<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1186/1/ /2/, 2081/1/, 2082/2/, 2083/1/, 2267/2/, 2324/1/<br>አዋጅ ቁ. 256/60 አንቀጽ 6<br>አዋጅ ቁ. 468/97 አንቀጽ 21<br>ደንብ ቁ. 360/61 አንቀጽ 6 7/1/ /3/, 8, 11/1/ /2/, 42-45 | 24643 | ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም<br>እና<br>አቶ አለማየሁ አህመድ | ሐምሌ 29/2000 | |
| 118. | ባለሞተር ተሽከርካሪ ከሚያደርሰው ጉዳት ጋር በተያያዘ የመጨረሻው ኃላፊነት (ultimate liability) የሚወድቀው መኪናው ሲሽከረከር የነበረው ባለቤቱ በቀጠረው ሹፌር እንኳን ቢሆን በወቅቱ በመኪናው ሲገለገል የነበረው ሰው ላይ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2082/1/, 208/1/, 2083/1/ | 55228 | አቶ አብራር ሳቢር<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አለምፀሐይ ወሰኔ /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 25/2003 | |
| 119. | ከውል ውጭ የሌላ ሰው ሃብት የሆነን ነገር በመያዝ ለተገለገለበት ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል በሚል የቀረበ አቤቱታ ጋር በተያየዘ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024 | 54518 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ፀሐይ ዘሙይ /ሁለት ሰዎች/ | የካቲት 14/2003 | |
| 120. | • ለአካለ መጠን ያልደረሱ ህፃናት ላይ ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ሲደርስ የጉዳት ካሣ መከፈል የሚገባው ስለመሆኑና የካሣ አወሳሰኑ ስሌት<br>• በገንዘብ ለመተመን የሚያዳግት የአካል ጉዳት በደረሰ ጊዜ ካሣ በርትዕ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090, 2091, 2092/2/, 2095/2/ | 38117 | አቶ ብርሃነ ፈይሳ ቢፍቱ<br>እና<br>እነ ናይል ኢንሹራንስ /ሁለት ሰዎች | ሐምሌ 09/2001 | |
| **አፈፃፀም** | | | | | |
| 121. | በዕዳ ምክንያት በፍ/ቤት የተከበረ ንብረት እንዲሸጥ በተደረገ ጊዜ ንብረቱን ያስከበረው ወገን የሚኖረው መብት ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ የቀዳሚነት መብት ካላቸው ባለገንዘቦች የሚተርፍ ካለ መውሰድ ነው እንጂ ንብረቱን በሽያጭ ውል የተነሳ ባለቤት የሆነን ወገን መጠየቅ ወይም ንብረቱን የመከተል ስላለመሆኑ | 48042 | ጉና ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ<br>እና<br>እነ ቡሬ ባጉና የማዕድን ውሃ | ጥቅምት 03/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፋብሪካ /ሦስት ሰዎች/ | | |
| 122. | የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው ደርሶት የፍርድ ባለዕዳ ሳይቀርብ በሚቀርበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/"ን" ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ስላለመሆኑ እና የተሰጠን ትዕዛዝም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት ለማስነሳት የሚቻልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/, 78 | 53943 | እነ ወ/ሮ አስካለ ደሣለኝ<br>/ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ የትምወርቅ ታደሰ<br>/ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 16/2003 | |
| 123. | በአንድ የፍርድ ባለዕዳ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ባለገንዘቦች አፈፃፀም ሊቀጥል የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403, 378 | 40945 | ኮለኔል ግርማ ሃይለስላሴ<br>እና<br>አቶ አስማማው መንግስቱ | ጥር 13/2003 | |
| 124. | ፍርድን የሚያስፈጽም የአፈፃፀም ችሎት የተሰጠውን ፍርድ በአግባቡ ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የገመተውን ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 392/1/ | 62804 | እነ አቶ ብርሃን<br>ገ/እግዚአብሔር<br>እና<br>ወ/ሮ ለታይ ገ/ጊዮርጊስ | ሰኔ 15/2003 | |
| 125. | በፍ/ብሔር ክርክር የተፈረደበት ሰው የፍርዱ አፈፃፀምን ለማሰናከል የተንቀሳቀሰ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እስራት ሊቀጣ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 389/1//ሀ//ለ/ | 63754 | አቶ ዓለም ባህታ<br>እና<br>ወ/ሮ ኑኑሽ ሽህምሎ | ሰኔ 15/2003 | |
| 126. | • ፍርድን የሰጠ ፍርድ ቤት ፍርዱ በውክልና እንዲፈፀም ለሌላ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ባስተላለፈ ጊዜ በውክልና ፍርድ ለማስፈፀም ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ ከሰጠው ፍርድ ቤት ማረጋገጫ እንዲላክለት ለመጠየቅ የሚችለው የፍርዱ ወይም የትዕዛዙ ግልባጭ ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ካለው ብቻ ስለመሆኑ<br>• ፍርድን በውክልና እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ የደረሰው ፍርድ ቤት ስለፍርዱ ትክክለኛነት ወይም በግልባጮቹ ላይ ስለሰፈረው ነገር ሌላ መግለጫና ማብራሪያ ሳይጠይቅ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 373/2/ 371/1/ | 66988 | አቶ ቀደመ ተሾመ<br>እና<br>አቶ ኢብራሂም ሐመዱ | ሐምሌ 25/2003 | |
| 127. | ፍርድን የሰጠ ፍ/ቤት ፍርዱ እንዲፈፀምለት ለሌላ ፍ/ቤት የውክልና ስልጣን ስለሚሰጥበት አግባብና የፍርድ አስፈፃሚ ፍ/ቤት የስልጣን አድማስ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371-455 | 64354 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ<br>አ.ማ<br>እና<br>ወ/ሮ ኡልባሬ ሰማን | ሰኔ 13/2003 | |
| 128. | ፍርድ የማይፈፀመው ፍርዱ በይግባኝ ስርዓት የተለወጠ እንደሆነ ወይም ፍርዱን ላለመፈፀም ህጋዊ ምክንያቶች ያሉ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 386 | 59301 | መምህርት አታቱ ከበደ<br>እና<br>ስቴፕስ አት.ኢዲኬሽናል<br>ኃ.የተ.የግል ማህበር | ግንቦት 04/2003 | |
| 129. | በአፈፃፀም ደረጃ የሚገኝ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78/1/ ያለው አግባብነት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 /1/ | 52110 | እነ ወ/ሮ ይህደጋ ሳሙኤል<br>/ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አሰፉ ሳሙኤል<br>/አራት ሰዎች/ | ታህሳስ 26/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 130. | • በክርክር ሂደት ተሳታፊ ያልነበረና ፍርድ ያልተሰጠበት ሰው ንብረት በፍርድ አፈፃፀም ሲያዝበት /በሃራጅ ሲሸጥበት/ ሊከተለው ስለሚገባው አካሄድ<br>• በፍርድ ሊያዝ ስለሚችል ንብረት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447/1/, 418, 234/1/ /ሠ/, 235/2/, 414/2/, 423, 425, 443, 453/1/ /3/ | 58009 | እነ አቶ ስለሺ ወርቅነህ /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ አቶ ሁሪሳ ደመሳ /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 262003 | |
| 131. | ከግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም ደረጃ የሚቀርብ የቀዳሚነት መብት ይከበርልኝ ጥያቄ የህግ መሰረት ያለውና ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 32/1/<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 | 48997 | የቦሌ ክ/ከ/ገቢዎች መምሪያ<br>እና<br>እነ አቶ መዓዛ ሽፈራው /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 16/2003 | |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | |
| 132. | በጤና ጥበቃ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ከጤና ሥነ ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ በጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ክስ በቀረበባቸው ጊዜ በተገቢው መንገድ መልስ የመስጠትና የመሰማት መብታቸው ሊጠበቅ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎችን መማክር ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 16/1/ /2/ | 56934 | እነ አሰገደች የእናቶች እና የህፃናት ሆስፒታል<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | መስከረም 26/2003 | |
| 133. | በውጭ አገር የተደረጉ ሰነዶች (foreign documents) በኢትዮጵያ ውስጥ ህጋዊ ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ<br>አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 26/1/ | 32282 | ሚ/ር ካርሎ ካስቴሊ እና የወ/ሮ ዘውዴ ደሚኒኮ ውርስ አጣሪ አቶ ታምራት ኪዳነ ማርያም | መስከረም 25/2003 | |
| 134. | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሻሻለ አዲስ የባንክ ስራ ፈቃድና የዳይሬክተሮች እና የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሹመትን አስመልክቶ የሚያወጣው መመሪያ ህጋዊ መሰረት ያላቸውና በተግባር ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ<br>መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ/39/ 2006 አንቀጽ 5.1.4 አንቀጽ 5.1.5<br>አዋጅ ቁ. 83/89<br>አዋጅ ቁ. 84/86 | 44226 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ<br>እና<br>እነ ህብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ /ሦስት ሰዎች | ታህሳስ 15/2003 | |
| 135. | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በህግ ከተጣለበት የጡረታ አበል የመክፈል ግዴታው ጋር በተያያዘ የአንድን ሰው ባልነት /ሚስትነት/ በማረጋገጥ የተሰጠ ውሣኔን የመቃወም መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | 53221 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ንጋት ወ/ሰንበት | ታህሳስ 27/2003 | |
| 136. | የጥብቅና ፈቃድ ክልከላ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ ለሚመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ ታይቶ የሚወሰን እንጂ በቀጥታ ክልከላ እንዲወገድ በሚል ለፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብበት ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 29/1/ | 59261 | የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር<br>እና<br>አቶ ታዬ በዛብህ ፊኖ | ጥር 24/2003 | |
| 137. | በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40/8/ መሰረት ለተወሰደ ንብረት የሚጠየቅ ካሣ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1143 እና 2143 በሁለት ዓመት ይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ | 59979 | የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና አቶ ከበደ ወዳጆ | የካቲት 09/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 138. | የቡና ላኪነት ፈቃድ አውጥቶ በግብይት ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅን ጥሷል በሚል በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ መሰረት ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 602/2000 አንቀጽ 14/3/, 15/3/ ደንብ ቁ. 159/2001<br>የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር መመሪያ | 58008 | እነ ኤርሰዱ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | ግንቦት 16/2003 | |
| 139. | በጡረታ የተገለለ ሰው በሌላ ሥራ ላይ በተቀጠረበት ጊዜ መንግስት ለጡረተኞች ያደረገውን የጡረታ ጭማሪ መሰረት በማድረግ አሰሪው የደመወዝ ጭማሪ እንዲያደርግለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 60025 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ ወለዴ በየነ /አራት ሰዎች/ | ግንቦት 02/2003 | |
| 140. | • ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ "እስከመጨረሻ ድረስ በመያዝ ለመከራከር" በሚል የሚያደርገው ስምምነት ጉዳዩ ሊያስኬድ የሚችል እስከሆነ ድረስ በአንድ ፍ/ቤት ሳይወሰን በይግባኝና በሰበር ደረጃ ሁሉ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ<br>• ጠበቃ ከደንበኛ ጋር ባለው ግንኙነት ደንበኛው ማድረግ ያለበትን ነገር ከህግ አንፃር የማስረዳትና ግልጽ የማድረግ ብሎም የማማከር ኀላፊነት ያለበት ቢሆንም በአንፃሩ አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ሁኔታ ክስና ክርክር ለማቅረብ የማይገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732<br>ደንብ ቁ. 57/92 አንቀጽ 28, 8/2/ | 60353 | አቶ ባልቻ ወ/ፃጽቅ<br>እና<br>አቶ ግርማ ቀለታ | ግንቦት 04/2003 | |
| 141. | የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በህግ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት በማድረግ አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በድጋሚ በማየት የተለየ ውሣኔ በሰጠ ጊዜ የተለወጠውን /የተሻረውን/ ውሣኔ መሰረት በማድረግ የተከናወኑ ተግባራትን ለማስተካከል ወይም የተከራካሪ ወገኖችን መብት ለማስተካከል ተገቢ የሆነ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349, 6 | 60508 | እነ ወ/ሮ ሮዛ አባተ /አራት ሰዎች/<br>እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ግንቦት 15/2003 | |
| 142. | በፌዴራል ፍ/ቤቶች በጥብቅና ለመስራት የሙያ ፈቃድ የሚሰጥበት አግባብ | 67280 | የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚ/ር<br>እና እነ አቶ ተስፋዬ በርሄ /አምስት ሰዎች/ | ግንቦት 15/2003 | |
| 143. | የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራን ዜግነት መርጦ የያዘ ሰው "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ" ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 270/94 አንቀጽ 2/2/<br>ደንብ ቁ. 101/96 አንቀጽ 2/1/ | 55238 | እነ የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ ህዳት ፍስሃ ጽዮን | መጋቢት 09/2003 | |
| 144. | • ጠበቃ የሆነ ሰው ደንበኛውን ወክሎ ለፍ/ቤት የሚያቀርበው አቤቱታ እውነት ስለመሆኑ በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ማንኛውም ጠበቃ የህግ ሙያውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ ለደንበኛው፣ ለሌሎች የህግ ባለሙያዎች፣ ለተከራካሪ ወገኖች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለሙያው ብሎም በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ኃላፊነቱን በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት የመወጣት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 92/1/<br>የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁ. 57/92 አንቀጽ 3 29/2/ 56/4/ /6/ | 67146 | ሻምበል ተሾመ ደምሴ<br>እና<br>የፍትህ ሚኒስቴር ዓ/ህግ | ሐምሌ 01/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 145. | እጣው ከመድረሱ በፊት አባልነቱን ያቋረጠ የእቁብ አባል ለእቁብ የከፈለውን ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል የኃላፊነት ጥያቄ ሊያቀርብባቸው ስለሚችሉ አካላት | 55794 | አቶ ለማ አበበ<br>እና ወ/ሮ ሃና አሰፋ | ጥር 24/2003 | |
| 146. | • በፍርድ ቤት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ፀንቶ ባለበት ወቅት እግድ የተሰጠበት ንብረት ተሸጦ በተገኘ ጊዜ የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን ሊኖረው ስለሚችለው መፍትሔ<br>• የፍርድ ቤትን የእግድ ትዕዛዝ አለማክበር /መጣስ/ ኃላፊነትን የሚያስከትል ተግባር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2028, 2035, 2126 | 54567 | የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ /ሦስት ሰዎች/ | የካቲት 10/2003 | |
| 147. | • በአንድ በቀረበ ክርክር ላይ የተሰጠው ውሣኔ የቀረቡትን ማስረጃዎች ይዘት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነጥብ ከሕጉ ጋር በአግባቡ ተዛምዶ አልታየም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሕግ ነጥብ /ክርክር/ እንጂ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ነው ተብሎ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>• የሰበር ችሎት በሥር ፍ/ቤቶች የቀረበን ማስረጃ ክብደትና ተዓማኒነት ለመመርመር በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ስለመሆኑ | 44804 | ወ/ሮ ሰናይት ተመስገን<br>እና<br>ወ/ሮ እጥፍወርቅ በቀለ | ጥቅምት 04/2003 | |
| 148. | በወንጀል ድርጊት በኤግዚብትነት ተይዞ የነበረ ወርቅ ከተሸጠ በኋላ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ከተሻረ ሻጩ አካል የወርቁን ዋጋ መክፈል ያለበት በተሸጠበት ወቅት በነበረው ዋጋ ስለመሆኑ | 58822 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ<br>እና አይንሽምስ ሁሴን | መጋቢት 05/2003 | |
| 149. | • የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአንድ ወቅት በአንድ ጉዳይ /ጭብጥ/ ላይ የሰጠው የህግ ትርጉም እንደተለወጠ /እንደተሻሻለ/ ሊቆጠር የሚችለው በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ በህግ አግባብ የተለየ ግልጽ ትርጉም በሰጠ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ<br>• የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ ተቀብሎ ማስተናገድ ብሎም የውርስ አጣሪ መሾም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በህግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ/ /የሰ/መ/ቁ. 35657፣ 42015፣51329 ይመለከቷል/<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41<br>አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/4/ | 52530 | እነ አቶ ሰናይ ልዑልሰገድ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ትዕግስት ኃይሌ | ህዳር 14/2003 | |
| 150. | የይርጋ መርህ ክስን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከትና ንብረትን በመያዝ ወይም ባለይዞታ በመሆን የባለህብትነት መብት ከሚገኝበት መርህ የሚለይ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1168, 1808 | 53328 | ዓብዱል መሐመድ እና ወ/ሮ ዘበናይ ኃይሌ | ጥቅምት 18/2003 | |
| 151. | • የድምጽ ብክለት ተከስቷል ለማለት የሚቻለው የሚሰማው ድምጽ ከመጠን በማለፉ በሌሎች ላይ ሁከት የሚፈጥር መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>• የድምፅ ብክለት (Nuisance) ተፈጥሮብኛልና እንዲወገድ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በሁለት ዓመት ይርጋ ታግዷል ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>• አንድ ሥራን ለመስራት የንግድ ፍቃድ የሰጠ አካል ሥራው የሚፈጥረው የድምጽ ረብሻ አለ በሚል የንግድ ፈቃዱን የሚሰረዝበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 10<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1225, 1226, 1149 | 42824 | አቶ ብርሃነ ተሰማ<br>እና<br>እነ አቶ ታምራት ኪዳኔ /ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 08/2002 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 152. | • የአስተዳደር አካል የሰጠው ውሣኔ ወይም የወሰደው እርምጃ ህገ ወጥ መሆኑን እስካረጋገጠ ድረስ ውሣኔውን ለማረም /እንዲስተካከል ለማድረግ/ ስለመቻሉ<br>• በተሳሳተ መንገድ በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሣኔ ቅን ልቦና አድሮበት ለኪሣራ የተዳረገ ሰው ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>• በስህተት በተሰጠ የግንባታ ፈቃድ ግንባታ ያካሄደ ሰው የአስተዳደር አካሉ ስህተቱን በማረም ግንባታው እንዲፈርስ መግለጫ በሰጠ ጊዜ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ | 57044 | እነ የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04/14 ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>አቶ ታሪኩ ኡርጌሳ | ጥር 25/2003 | |
| 153. | • ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባህሪይው ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ስርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ህግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚል ጥያቄን የሚያስነሳ እንደሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የፍ/ብሔር ስልጣኑ ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ<br>• ተዋዋይ ወገኖች በማናቸውም ሁኔታ የአገሪቱን ህግ ወደ ጐን በማድረግ ወይም በሚፃረር መልኩ ስምምነት ስላደረጉና ክርክር ስለተነሳ ብቻ አንድ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ህግ ጥያቄን/private international law issue/ የሚያስነሳ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>• በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ካልተወሰነ በቀር አዋጅ ቁጥር 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3//ለ/<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/ /ሀ/ | 54121 | ሲ.ኤ.ኤስ ኮንስልቲንግ ኢንጂነርስ ሳልዝ ጊተር ጂ.ኤም.ቢ.ኤች<br>እና<br>አቶ ካሣሁን ተወልደብርሃን | ህዳር 01/2003 | |
| 154. | • የክስ ይዛወርልኝ (change of Venue) ጥያቄ ከተከራካሪ ወገኖች የሚነሳ ስለመሆኑና ፍ/ቤትም ጥያቄውን ሊያስተናግድ የሚችለው በህግ የተመለከቱት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ<br>• የክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክሶችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው ለማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 136/3/, 138/2/, /1/, 139/1/ /ሀ/<br>አዋጅ ቁ. 322/95 አዋጅ ቁ. 25/88 | 66945 | የእንግሊዝ ህፃናት አድን ድርጅት<br>እና<br>አቶ ገአስ አስማን | ሰኔ 02/2003 | |
| 155. | ለብድር በመያዣነት የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ውሉ መሰረት በህጉ አግባብ በዋስትና ከመያዙ በፊት በሽያጭ ለሦስተኛ ወገን ተላልፎና ስመ ሃብቱ ለገዢው ተላልፎ በተገኘ ጊዜ ሊኖር ስለሚችለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/2/ | 65688 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ንጉሴ በያን | ሐምሌ 27/2003 | |
| 156. | የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 14/1//ረ/, 66/1/<br>አዋጅ ቁ. 2/95 አንቀጽ 52 | 53551 | የቀበሌ 10 ባለአደራ ቦርድ<br>እና<br>አቶ ዳንኤል አድርሴ | መስከረም 25/2003 | |
| 157. | ይዞታን አስመልክቶ ከሚነሳ የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት አቤቱታ አቅራቢው የይዞታ መብቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ካገኘበት ቀን ጀምሮ እንጂ አቤቱታ የቀረበበት ድርጊት መፈፀም ከጀመረበት ዕለት አንስቶ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149, 1146/1/, 1144/2/ | 60392 | አቶ ጌትነት የኔ<br>እና<br>አቶ እዮብ ቢንያም | ታህሳስ 26/2003 | |

# ቤተሰብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 50489

መስከረም 24 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘይነባ ከልፋ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ከድጃ ሲራጅ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በአላባ ቆሊቶ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

በተጠሪ እና በተከሳሽ አቶ ሐጂ መሐመድ ሐሊስ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ እንዲፈርስ መደረጉን ተከትሎ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ተጠሪ አቅርባለች፡፡ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ከተከሳሽ ጋር ከ1984ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስራ ያለች መሆኗን ገልፃ የሚሰጠው ውሳኔ መብቷን የሚነካ ስለሚሆን ጣልቃ ገብታ ለመከራከር አመልክታለች፡፡ የከተማው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ጣልቃገብ ለመካፈል የጠየቀችው ንብረት በተጠሪ እጅ ያለ ከመሆኑም ሌላ ይህንን ቤት የገነባች ለመሆኑ አልያም ወጪ ያወጣች ስለመሆኑ አላስረዳችም በሚል በቤቱ መብት የላትም ሲል አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጎ ተጠሪና ባለቤቷ ሐጅ መሐመድ ሐሊስ ለሁለት እኩል እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝታ ለአላባ ልዩ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረበች ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 23 ቀን 2002ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የስር ፍ/ቤት አመልካች ነዋሪነቷ ሳውዲ አረቢያ በመሆኑ ገንዘብ ልካ ለጣውንቷ ቤት ትሰራለች ተብሎ አይታመንም የሚለው አገላለጽ የተሳሳተ መሆኑን ቤቱ የተሰራው የአመልካች ባለቤት/የሥር ተከሳሽ/ ከሳውዲ አረቢያ በላከው ገንዘብ ስለመሆኑ የአመልካች እና የስር ተከሳሽ ጋብቻ አሁንም ፀንቶ ያለ ስለመሆኑና በክልሉ የቤተሰብ



www.chilot.me

ሕግ አንቀጽ 71/2/ መሠረት በባለቤቷ ስም የተፈራ ንብረት የጋራ ስለመሆኑ ጠቅሰው በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

የሰበር ችሎቱም የሰበር አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ሚስት መሆኗ ካልተካደ እና ከባለቤቷ ጋር የምትኖር መሆኗ ከተረጋገጠ የንብረት ክፍፍል ድርሻ ጥያቄዋ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ወይም አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 27 ቀን 2002ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም አመልካች ከሐጅ መሐመድ ሐሊስ ጋር ጋብቻ ያልመሰረተች ስለመሆኑ ንብረቱንም በሚመለከት ቤቱ የተሰራው በተጠሪ እና ባለቤታቸው ሐጅ መሐመድ ሐሊስ የጋራ ጥረት ብቻ ስለመሆኑ ስር ፍ/ቤት በማስረጃ ስለማረጋገጡ አመልካች ንብረቱን በማፍራት ረገድ ያደረገችው አስተዋጽኦ ስለመኖሩ በስር ፍ/ቤት ጭብጥ አስይዛ ያላስረዳች መሆኑን በመዘርዘር በተጨማሪም ለማዘጋጃ ቤቱ ከ1990-2001ዓ.ም ድረስ ግብር ብር 16,516.50 ውስጥ ግማሽ ድርሻውን ብር 8,258.25 የከፈሉ መሆኑን ጠቅሰው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች ጠበቃም የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልስ በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃርና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው ፍሬ ነገር አመልካች ከሐጅ መሐመድ ሐሊስ ጋር በ1984ዓ.ም ጋብቻ መስርታ አብረው ሳውዲ አረቢያ የሚኖሩ ስለመሆኑ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ በ1987ዓ.ም ከሐጂ መሐመድ ሐሊስ ጋር ጋብቻ የመሠረተች ሲሆን ባለቤቷ ለረዥም ዓመታት ውጪ አገር የሚኖር በመሆኑና እሷንም ወደ ውጪ እወስድሻለሁ ብሎ የገባውን ቃል ባለማክበሩ ፍቺ እንዲወስን ለመጠየቅ ምክንያት እንደሆናት ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጉዳይ ተጠሪም ሆኑ አመልካች ከሐጅ መሐመድ ሐሊስ ጋር ጋብቻ መስርተው የነበሩ ስለመሆኑ ነው፡፡ የተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ እንዲፈርስ መደረጉን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ከመቅረቡ ወጪ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈፀመ በሚል የቀረበ ክስ ስለመኖሩ አልተጠቀሰም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ሁለቱም ሚስቶች በየፊናቸው ከአንድ ወንድ ጋር ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ ቆይተው ጋብቻው በአንደኛዋ ተጋቢ ጥያቄ በፍቺ ሲፈርስ የንብረት ክፍፍል አፈፃፀም በምን መልክ ሊከናወን ይገባል የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡

የፌዴራሉም ሆነ የክልሎች የቤተሰብ ሕግ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል የሚደነግገው ክፍል አንድ ጋብቻ ብቻ መኖርና መፍረስን ታሳቢ በማድረግ እንጂ ጋብቻ ላይ ጋብቻ ሲኖር የሚከተለውን ውስብስብ ጥያቄ ታሳቢ ያላደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሕጉ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዳይፈፀም ግልጽ ክልከላ ያደረገ በመሆኑ ነው፡፡

ሆኖም ግን በማህረሰቡ በተግባር እየተከናወነ ያለተግባር እንደመሆኑ ክርክር በተነሳ ጊዜ የሚሰጠው ውሳኔ ማህበራዊ ቀውስ እንዳያስከትል ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የዳኝነት አካሉ ኃላፊነት ይሆናል፡፡

ስለሆነም የሕጉን መሠረታዊ ዓላማና ግብ ለማሳካት በሚቻልበት አግባብና ፍትሀዊ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል አግባብ ለሕጉ ትርጉም መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ የሚከራከሩት በአላባ ቆሊቶ ከተማ በ1250 ካ.ሜ ቦታ ላይ የተሰራ ቤትን በሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በዚህ ቤት ላይ ከባለቤቷ ጋር ገንዘብ በማውጣት የሰራች መሆኑን በመጥቀስ የቤቱ ግማሽ (50%) የባለቤቷ የተቀረው ግማሽ (50%) ለእሷ እና ለተጠሪ

እንዲካፈል እንዲወሰን የጠየቀች መሆኑን የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት ያመለክታል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ይህንን ቤት የሰራችው በራሷ እና በባለቤቷ እንዲሁም ቤተዘመዶቻቸው ጥረት መሆኑን ገልፃ ቤቱ የተጠሪ እና የባለቤቷ ብቻ እንደሆነ ትከራከራለች፡፡ በዚህ ረገድ የግራ ቀኙን ማስረጃ የሰማውና የመረመረው የወረዳ ፍ/ቤት አመልካች በቀጥታ ባለመብት ሊያደርጋት የሚያስችል አስተዋጽኦ ስለማድረጓ አላስረዳችም ሲል ደምድሟል፡፡

ይልቁንም ቤቱ የተሰራው ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ መሆኑን እና ተጠሪ ቤቱን ተቆጣጥረው ይዞታዋ ስር ያለመሆኑን በመጥቀስ በተሻለ ማስረጃ ባለመብት መሆኗን አረጋግጣለች ብሏል፡፡

ይህንን የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መነሻ አድርገን ከሕጉ ማገናዘብ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመርህ ደረጃ ጋብቻ ሲፈርስ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት እኩል የሚከፋፈል መሆኑ በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግም ሆነ በክልሉ ተቀባይነት ያለው መሠረት ሐሳብ ነው፡፡የማጣራቱ ተግባርም በስምምነት አሊያም በሕጉ ሊወሰን ይችላል፡፡ ንብረቱ ሲጣራ ተጋቢዎች የግል ንብረታቸውን አስቀድሞ እንዲለዩና እንዲወስዱ ከዚያም የጋራ ንብረት ላይ እኩል መብት እንዳላቸው ሕጉ ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠቃሹ ቤት የተጠሪና የባለቤቷ የሐጂ መሐመድ ሐሊስ የጋራ ንብረት ነው ሲል የስር ፍ/ቤት ደምድሟል፡፡ የአመልካች ክርክር ባለቤቷ ሐጂ መሐመድ ሐሊስ ያፈራው ንብረት ነው ቢባል እንኳ በሕጉ ህሳቤ መሠረት ግማሽ ድርሻ ይገባኛል ባይናት፡፡

የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 62/1/ እንደሚያመለክተው በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት ከግል ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች የጋራ ሐብታቸው ይሆናሉ፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተጠቀሰውን ንብረት ለማፍራት አስተዋጽኦ ስለማድረጓ አላስረዳችም ቢባልም በባሏ ጥረት የተፈራ ንብረትም ቢሆን የጋራ መብት እንደሚያስገኝላት ሕጉ ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተፈራ ንብረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሐብት ነው እስካልተባለ ድረስ የጋራ እንደሆነ ሕጉ ግምት የሚወስድ በመሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም ተጠቃሹን ቤት በተመለከተ ተጠሪ ቤቱ ላይ ቀጥታ አስተዋጽኦ ስለነበራት 50% /አምሳ በመቶ/ ድርሻ አላት ሲል የስር ፍ/ቤት የደረሰበትን ድምዳሜ ከማስረጃ የመነጨ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ነው ቢባልም በተቀረው 50% /አምሳ በመቶ/ ላይ አመልካች ድርሻ የላትም ሊባል የሚገባ አይደለም ምክንያቱም በሕጉ አገላለጽና እሳቤ አመልካች ባለቤቷ በስሙ ያፈራው ንብረት ላይ ድርሻ እንዳላት ተመልክቷልና፡፡ ስለዚህም የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በአከራካሪው ቤት ላይ ምንም ድርሻ የላትም ሲሉ የሰጡት ውሳኔ የሕጉን መንፈስና ዓላማ በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ስለዚህም አመልካች ከባለቤቷ ድርሻ ላይ እኩል የመካፈል መብት ይኖራታል ማለት ነው፡፡

በክርክሩ ሒደት እንደተገለጠው በአመልካች እና በባለቤቷ /ሐጅ መሐመድ ሐሊስ/ መካከል ያለው ጋብቻ ያልፈረሰ በመሆኑ አከራካሪውን ንብረት ይካፈሉታል ባይባልም አመልካች ድርሻ



www.chilot.me

እንዳላት ሊታወቅ ይገባልና፡፡ በዚሁ መሠረት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማረም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአላባ ቆሊቶ ከተማ የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 02464 በ10/09/2001ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01969 በ4/10/2001ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ 29217 በ05/02/2002ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡
2. በአላባ ቆሊቶ ከተማ በ1250 ካ.ሜ ቦታ ላይ የሰፈረው ቤት በሐጅ መሐመድ ሐሊስ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ተጠሪና ሐጅ መሐመድ ሐሊስ ለሁለት ከተካፈሉ በኂላ በሐጅ መሐመድ ሐሊስ ድርሻ ላይ አመልካች እኩሌታ መብት አላት ብለናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ መጋቢት 7 ቀን 2002ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሶ/በ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 46606

ጥቅምት 2 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ገብረሥላሴ አማረ አልቀረቡም

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አብርኸት ተጫኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሚያከራክረው ጉዳይ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍያ የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍች መፍረሱን ገልፀው በጋብቻ ወቅት በጋራ ያፈሩት የቤት ቁሣቁስ በልደታ ክፍለ ከተማ ተከራይተው ከሚኖሩበት ቤት ግቢ ውስጥ የሰሩት አንድ ክፍል ቤትና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ 2 ሣይት ህንፃ ቁጥር 29 የቤት ቁጥር ቢ.29/48 የሆነ ኮንደሚኒየም ቤት የጋራ ስለሆነ ያካፍለኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በቀበሌ ቤት ግቢ ውስጥ የተሰራው ቤት ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት የተሰራ መሆኑን የኮንደሚኒየም ቤቱ ደግሞ ከተጠሪ ጋር የነበረንን ጋብቻ ታህሣሥ 18 ቀን 1999 ዓ.ም በስምምነት አፍርሰን ተጠሪ ብር 1300/አንድ ሺ ሶስት መቶ ብር/ ተቀብላ ከሄደች በኋላ የደረሰኝ ስለሆነ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከቀበሌ ከተከራዩት ግቢ የተሰራው አንድ ክፍል ቤት አመልካች ተጠሪን ከማግባቱ በፊት የሰራው የግል ንብረቱ መሆኑን በተሻለ ማስረጃ አስረድቷል፡፡ የኮንደሚኒየም ቤቱ የደረሰው የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሣኔ በፍች ከመፍረሱ በፊት ነው፡፡ የተጠሪና የአመልካች ጋብቻ የፈረሰው መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም እንጂ ታህሣሥ 18 ቀን 1999 ዓ.ም አይደለም፡፡ ስለዚህ ኮንደሚኒየም ቤቱ የጋራ ንብረት ስለሆነ በቤቱ ላይ ያለውን መብትና ግዴታ አመልካችና ተጠሪ እኩል ይካፈሉ ፡፡ የቤት ቁሣቁስ ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ኮንደሚኒየም ቤት ለማግኘት የተመዘገብኩት ተጠሪን ከማግባቴ በፊት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እኔና ተጠሪ በስምምነት ጋብቻችንን ኀዳር 23 ቀን 1999 ዓ.ም አፍርሰናል፡፡ ስለዚህ የተመዘገብኩት ተጠሪን ከማግባቴ በፊት እጣ የወጣልኝና ያገኘሁት እኔና ተጠሪ በስምምነት ጋብቻችንን ካፈረስን በኋላ በመሆኑ ኮንደሚኒየም ቤቱ የጋራ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ



www.chilot.me

ስህተት አለበት በማለት ሰኔ 8 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ከቤት የወጣሁት በስምምነት ጋብቻችንን በማፍረስ ሣይሆን አመልካች ስለሚደበድቡኝ የቀለብ ገንዘብ ሰጥተውኝ ነው፡፡ ኮንደሚኒየም ቤቱ የደረሰን ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት በመሆኑና አስር ፐርሰንት የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ከጋራ ንብረት በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መረምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በፍርድ ቤት ውሳኔ መሆኑንና ኮንደሚኒየም ቤቱ የደረሳቸው ጋብቻው በፍች ከመፍረሱ በፊት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ለኮንደሚኒየም ቤት የተመዘገብኩት ተጠሪን ከማግባቴ በፊት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክርም ቤቱን እዲገዙ እጣ የወጣበት ጊዜ ጋብቻው ፀንቶ እስካለ ድረስ ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት ስለተመዘገቡ ብቻ ቤቱ የግል ንብረት እንደማይሆን ከተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ለቤቱ ጋብቻው ከፈረሰ በኂላ የሚከፈለውን ክፍያ ከአመልካች ጋር አብረው የመጋራትና ግማሹን የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው ግልጽ በማድረግ አመልካችና ተጠሪ በኮንደሚኒየም ቤት ላይ ያለውን መብትና ግዴታ እኩል እንዲካፈሉ በማለት መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ ስላገኘነው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይኽ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47201

ጥቅምት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሒጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካቾች**፡- 1. በላቸው አስፋው ቀረበ

2. ሙክታር አሕመድ ቀረበ

3. ወ/ሮ ዙሪያሽ ወ/አረጋይ ቀረበች

4. አተረፈ ማሞ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ መኪያ አወል ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

በሰበር ችሎቱ ሊመረመር በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ የይርጋ መቃወሚያን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ጉዳዩ ያለአግባብ የተያዘው ቤት ይለቀቅልኝ በማለት ተጠሪ ባቀረበችው ክስ መነሻነት የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ይለቀቅልኝ የምትለው ቤት አመልካቾች ይዘውት የሚገኝ ሲሆን፣በተጠሪ ክርክር እንደተገለጸው ባለንብረት የሆኑት ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ የተባሉት ሴት ናቸው፡፡ ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ ቤቱን አቶ ማንደፍሮ ቸርነት እና ወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት ለተባሉት ሰዎች በስጦታ ውል እንዳስተላለፉት፣በኋላም ወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት ድርሻቸውን በፈቃዳቸው ለአቶ ማንደፍሮ ቸርነት እንደተው፣አቶ ማንደፍሮ ቸርነት ደግሞ የተጠሪ አውራሽ እንደሆኑ በተጠሪ ክስ ተገልጾአል፡፡ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ በየበኩላቸው ከአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ጋር ባደረጉት የሺያጭ ውል ቤቱን መግዛታቸውን፣ በገዙት መጠን ቤቱን ይዘው ከ11 እና ከ13 ዓመት በላይ ሲጠቀሙ መቆየታቸውን፣ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ ለአቶ ማንደፍሮ ቸርነት እና ለወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት አደረጉት የተባለው የስጦታ ውል በሕጉ አግባብ ፍፃሜ አላገኘም፤በዚህ አይነትም ከ21 ዓመት በላይ ቆይቶአል፣በመሆኑም ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚሉትን ነጥቦች በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ክርክሩን የመረመረ ሲሆን፣በመጨረሻም አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ በማድረግ ቤቱን ለተጠሪ እንዲለቁ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣በአመልካቾች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል



www.chilot.me

በመጨረሻም ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ በዚህ ደረጃም ክርክር የተሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ ይልቀቁ በማለት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካቾች ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ከግራ ቀኝ ወገኖች የቀረበውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመረው ጭብጥ አመልካቾች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ተደርጐ ቤቱን ይልቀቁ የተባለው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡ አመልካቾች በተለይ ከ1 እስከ 3 ያሉት ቤቱን የያዙት ከአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ጋር የሽያጭ ውል አድርገው በመግዛት እና የሺያጭ ዋጋውንም በመክፈል እንደሆነ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ቢሆን የሽያጭ ውል አልተደረገም አላለም፡፡ የሺያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 የተመለከቱትን መስፈርቶች አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው ውልን በማስመልከት አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ያደረገው 4ኛ አመልካችም ቦታውን በቃል በተደረገው ስጦታ ተላልፎልኝ ቤቱን በራሴ ወጪ ሰርቻለሁ በማለት ቢከራከርም፤ስጦታው በጽሑፍ አልተደረገም በሚል ክርክሩ ተቀባይነት ሳያገኝ እንደቀረ ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቤቱ በአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ስም አልተላለፈም (የስጦታ ውሉ ተፈፃሚ አልሆነም) የሚል ክርክር በአመልካቾች መነሳቱንና ተጠሪ ይህን በግልጽ አለማስተባበልዋን ተገንዝበናል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካቾች ቤቱን የያዙት ተጠሪ አውራሽ ነው የምትለው ሰው (አቶ ማንደፍሮ ቸርነት) በሕይወት በነበረበት ጊዜ ሆኖ ተጠሪ ክስ የመሰረተችው አመልካቾች ቤቱን ከያዙ ከ11 እና 13 ዓመታት በኂላ ነው፡፡ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበትም አመልካቾች ቤቱን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ አገኘሁ ከምትልበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ተጠሪ የወራሽነት ማረጋገጫ ያወጣችበትን ወይም አቶ ማንደፍሮ ቸርነት የሞቱበትን ቀን መነሻ በማድረግ በይርጋ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ መወሰኑ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካቾችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ በሕጉ አተረጓጐም ረገድ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲለቁ በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.31107 ሐምሌ 11 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይህን ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ. 43519 ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47889

ጥቅምት 04 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሒጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** እነ ወ/ሮ ሰላማዊት አስራት (አምስት ሰዎች) ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መሰረት ዘውዴ ከጠበቃ መስፍን እሸቱ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ጋብቻ በሞት መፍረስን ተከትሎ በሟች ወራሾችና በሕይወት በቀረው ተጋቢ መካከል የተነሣውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት አመልካች የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሲሆን በአቤቱታቸውም የአሁኗ ተጠሪ ባለቤት የነበሩት ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን፣ገለፀው የሟቹ ውርስ እንዲጣራላቸው የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ተጠሪን በመልስ ሰጪነት በመጥራት የውርስ አጣሪው እንዲሾም በማድረግ ውርስ አጣሪው የውርስ ሐብቱን በማጣራት ሪፖርቱን እንዲያቀርብለት አድርጐ ውርስ አጣሪው ሪፖርቱን ሲያቀርብለት ግራ ቀኙ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ ከዚህም በሁዋላ በአዲስ አበባ ከተማ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/03 ክልል ውስጥ ይገኛል የተባለውና ቁጥሩ 1539 የሆነ ቤት ሟች ማስተር ቴክኒሽያን አስራት መኮንን በግላቸው የነበራቸው ቤት በመሆኑ እና በቤተሰብ ሕጉም የጋብቻ ውል ሲደረግ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ መፃረር እንደሌለበት በመግለጽ ቤቱ የሟች የግል ቤት ነው በማለት ተጠሪ ቤቱ በጋብቻ ውል የጋራ ተደርጓል በማለት ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ አድርጐ ወስኗል፡፡ ከዚህ በሁዋላም የአሁኗ ተጠሪ ቤቱ የሟች የግል ነው ተብሎ በተወሰነው የውሳኔ ክፍል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ አመልካቾች በበኩላቸው በቤቱ ላይ ከተጠሪ በፊት ከሟች ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን ጋር ጋብቻ መስርተው የነበሩት የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ነው ሲሉ ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት መታለፉ ያላግባብ መሆኑን ገልጸው የመስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ አከራካሪው ቤት ላይ የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ድርሻ እንደሌላቸው በማረጋገጥ ቤቱ የሟች ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን የጋራ ንብረት እንዲሆን በጋብቻ ውል ስምምነት የተደረገበት በመሆኑ ቤቱ የጋራ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ



www.chilot.me

የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር ወስኗል፡፡ ከዚህ በሁዋላም አመልካቾች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አከራካሪው ቤት ግማሹ የአመልካቾች እናት ከሟች አስራት መኮንን ጋር በነበሩበት ጊዜ የተፈራ ሁኖ እያለና ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረትን በጋብቻ ውል የጋራ ንብረት ለማድረግ የማይቻል ሁኖ እያለ ቤቱን በጋብቻ ውል የጋራ አድርገውታል ተብሎ ግማሹን ተጠሪ እንዲወስዱ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ተጠሪ ቀርበው በጠበቃቸው አማካኝነት የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ የጋብቻ ውሉንና ሕጋዊ ውጤቱን መሰረት ያደረገ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካቾች አውራሽ ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የአመልካቾችን እናት ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻን አግብተው ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ መሆኑን፣ከፍቺው በሁዋላም የንብረት ክፍፍል ተደርጐ አሁን እያከራከረ ያለው ቤት ለማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን እንዲሆን በወቅቱ በተሰየመው የቤተዘመድ ጉባኤ ተወስኖ ይህ ውሳኔ ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቁን፣ከዚህም በኋላ ሟች አቶ አስራት መኮንን ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መስርተው ሐምሌ 27 ቀን 1972 ዓ.ም ባደረጉት የጋብቻ ውል አሁን እያከራከረ ያለውን ቤት የጋራ ማድረጋቸውን ነው፡፡ አመልካቾች የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ነው የሚሉት ሁለት ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አንደኛው ቤቱ ላይ የእናታቸው ግማሽ ድርሻ አለበት የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጋብቻ ውል የግል ንብረትን የጋራ ንብረት ለማድረግ አይቻልም በሚል ነው፡፡ እኛም እነዚህን ቅሬታዎች መሰረት በማድረግ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ፈትለወርቅ መነገሻ ከሟች አባታቸው ጋር የነበራቸውን ጋብቻ በፍቺ ካፈረሱ በሁዋላ ውጤቱን በተመለከተ ደግሞ በቤተዘመድ ጉባኤ ታይቶ ይኼው አካል የሰጠው የንብረት ክፍፍል ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ጸድቋል፡፡ በፍርድ ቤት በፀደቀው የቤተዘመድ ጉባኤ ውሳኔ ደግሞ አሁን እያከራከረ ያለው ቤት ለሟች ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን ተሰጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔ በየትኛውም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አልተለወጠም፡፡ እንዲህ ከሆነ ቤቱ የሟች አስራት መኮንን የግል ንብረት መሆኑ ከተረጋገጠ በሁዋላ ሟች አስራት መኮንን ከተጠሪ ጋር ጋብቻ የፈፀሙ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ቤቱ የሟች አስራት መኮንን የግል ንብረት ነው ተብሎ



www.chilot.me

መወሰኑ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ክርክሮችንና ማስረጃዎችን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍ ሁኖ ስላላገኘን በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

ሌላው በዚህ ችሎት አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ሟች አስራት መኮንን ከተጠሪ ጋር ሐምሌ 27 ቀን 1972 ዓ.ም የተደረገው የጋብቻ ውል አስገዳጅነት ያለውን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57 ስር የተደነገገውን የሚፃረር ነው የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57 ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸውን ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኂላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው የሚያገኟቸውን ንብረቶች በጋብቻ ዘመንም የግል ሁነው ይቀራሉ በማለት በአስገዳጅነት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ንብረቶቹ በጋብቻ ውል የጋራ እንዲሆኑ ስምምነት ከሌለ ብቻ ነው፡፡ የጋብቻ ውል ሲደረግ ደግሞ ሊከተለው የሚገባው ፎርማሊቲ ስለመኖሩ የተጠቀሰው ሕግ በአንቀጽ 44 ስር ደንግጓል፡፡ ይኸው ሕግ በአንቀጽ 42 ንኡስ ቁጥር አንድና ሁለት ስር ተጋቢዎች ንብረታቸውንና ግላዊ ግንኙነታቸውን በተመለከተ ለመወሰን እንደሚችሉ ይገልፃል፡፡ ሕጉ የጋብቻ ውል አስገዳጅ የሆኑ የሕጉ ድንጋጌዎችን መፃረር እንደሌለበትም በአንቀጽ 42/3/ ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የሕጉ አንቀጽ 47 እና 73 ድንጋጌዎች ሲታዩም የጋብቻ ውል የሚሻሻልበትን ሥርአት ያስገነዝባሉ፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው የጋብቻ ውጤት በጋብቻ ውል ሊቋቋም፣ሊቀር ወይም ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ሌላው ከድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ውጤት በጋብቻ ውል ከወሰኑ እና ውሉም አስገዳጅ ድንጋጌዎችን የማይቃረን መሆኑ ከተረጋገጠ የተጋቢዎች የንብረትም ሆነ ግል ግንኙነት ሊገዛ የሚባው በጋብቻ ውሉ መሆን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ሕጉ የባልና ሚስት የንብረትና የግል ግንኙነት ክርክር ሲቀርብ ተፈፃሚ የሚሆነው የጋበቻ ውሉ ያልሸፈነው ክፍተት ካለ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም "የጋብቻ ውል አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን እስካልተቃረነ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል…" የሚለው ሐረግ አስገዳጅነት ያላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ማለት የትኞቹ ናቸው? የሚለውን መመልከትን የግድ የሚል ነው፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የጋብቻ ውል ሲመሰረት ሊከተላቸው የሚገባቸው ፎርማሊቲዎች እና በጋብቻ ውሉ ስምምነት የሚደረግባቸው ግንኙነቶች ምን እንደሆነ በሕጉ ተመልክተዋል፡፡ የጋብቻ ውሉ ፎርማሊቲው ሲከተል ሊያሳካ የታሰበው ግብም ስምምነቱ የተጋቢዎችን ነፃ ፈቃድ አግኝቶ የመዋዋል ነፃነታቸው ተከብሮ የተገኘ መሆኑን ማረጋገጥ መሆኑ ይታመናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ሕጉ ከጋብቻ በፊት የተገኘ ንብረትን የግል ንብረት ነው በማለት ጥበቃ የሚያደርገው በሕጉ አግባብ በተደረገ የጋብቻ ውል መሰረት የጋራ ያልሆነውን ንብረት ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም አስገዳጅ የሆኑትን የሕግ ድንጋጌዎችን የጋብቻ ውሉ ሊፃረር አይገባም የሚለው የሕጉ አነጋገር ከጋብቻ ውል አደራረግ ጋር የተያዙትን የፎርማሊቲ ጉዳዮችንና ከተጋቢው ግላዊ ነፃነት ጋር የተገናኙት ጉዳዮች እንጂ ከንብረት ጋር የተያያዙትን አይደለም፡፡ ከጋብቻ በፊት የተፈራን ንብረት በሕጉ አግባብ በተደረገ የጋብቻ ውል የጋራ ማድረግ አስገዳጅ የሆኑ የቤትሰብ ሕግ ድንጋጌዎችን መፃረር ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አንድ ንብረት ከጋብቻ በፊት የተገኘ መሆኑ ንብረቱ የተጋቢው የግል ንብረት ሁኖ እንዲቀር ሕጉ ያስቀመጠው ሁኔታ ጠቅላላ ደንብ ሲሆን ይህ ጠቅላላ ደንብ ተፈፃሚ የሚሆነው ንብረቱን የጋራ የሚያደርግና ልዩ ደንብ የሆነው የጋብቻ ውል በሌለበት ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ የጋብቻ ውል ልዩ ደንብ (exception) ሲሆን በአንቀጽ 57 ስር የተመለከተው ሁኔታ ደግሞ መርህ ሊባል የሚችል ነው፡፡ በሕግ አተረጓጎም ደንብ ደግሞ ተፈፃሚነት ያለው ልዩ ሁኔታ የሆነው ሕግ ነው፡፡



www.chilot.me

ሲጠቃለልም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አከራካሪው  ቤት በጋብቻ ውል የአመልካቾች አባትና ተጠሪ የጋራ ሁኗል በሚል ምክንያት የቤቱ ግማሽ ድርሻ የተጠሪ ይሆናል በማለት መወሰኑ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 42፣44 እና 57 ድንጋጌዎችን ያገናዘበ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 73357 ግንቦት 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 46813 ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49171

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ዶ/ር ደስታ አቡኑ በለጡ

**ተጠሪ፡-** ሲስተር አስቴር ካሣ መልደየስ - ጠበቃ አየለ ማሞ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሣውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ነው፡፡ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ፍ/ቤቶቹ ከሰጡአቸው ውሣኔዎች ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ግራ ቀኝ ወገኖች በጋብቻቸው ወቅት ያፈሩዋቸው ናቸው ተብለው ለክፍፍል ከቀረቡት ንብረቶች መካከል ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆኑት በሁለት የተለያዩ ከተሞች የሚገኙት የመኖሪያ ቤቶች ናቸው፡፡ ክርክሩን በመጨረሻ ደረጃ የሰማው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በወላይታ ሶዶ ያለው ቤት ለአመልካች፤ በሃዋሣ ከተማ ያለው ቤት ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን ወስኖአል፡፡ የሃዋሣው ቤት በወላይታ ሶዶ ካለው ቤት ብልጫ ስላለው ተጠሪ ልዩነቱን በገንዘብ ለአመልካች እንድታካክስም በተጨማሪ አዞአል፡፡ አመልካች በዚህ መልክ የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ነው የአሁኑን የሰበር አቤቱታ ያቀረበው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገውም ግራ ቀኝ ወገኖቹ ባልተስማሙበት ሁኔታ የተሰጠው የንብረቶቹ ክፍፍል ውሣኔን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረት ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በጋብቻ ተሳስረው የቆዩ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በፍቺ ሲያፈርሱ በንብረት ረገድ የነበራቸው ግንኙነትም እልባት ማግኘት አለበት፡፡ ይህ የሚሆነው ንብረቱን በመከፋፈል ሲሆን፣ ክፍፍሉ የሚከናወነው አግባብ ባላቸው የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በፌዴራል መንግሥቱ የወጣውም ሆነ የአሁኑ ክርክር በተነሳበት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት የወጣው የቤተሰብ ሕግ በንብረቱ ክፍፍል ረገድ የሚከተሉት መርህ የእኩልነት መርህ ነው፡፡ የእኩልነት መርህ ድንጋጌዎቹ መሠረትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34/1/ የተቀመጠው ድንጋጌ



www.chilot.me

እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ሌላው በንብረቱ ክፍፍል ሂደት ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የባለጉዳዮቹ ስምምነት መኖር እንደሆነም በቤተሰብ ሕጎቹ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ቤቶቹን በሚመለከት በተደረገው የክፍፍል ሂደት ወይም ሁኔታ አመልካች አልተስማማም፡፡ ላለመስማማቱ የሰጠው ምክንያትም የክፍፍል ሂደቱ የእኔን የእኩልነት መብት ያስጠበቀ አይደለም የሚል እንደሆነ ከክርክሩ ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ ደግሞ እኔ የምኖረው በሃዋሣ ከተማ በመሆኑ እና አመልካች የሚኖረው ከሃዋሣ ወጪ ስለሆነ የሃዋሳው ቤት ለኔ ቢሰጥ የበለጠ ተጠቃሚ እሆናለሁ በማለት ነው የምትከራከረው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ቤቱ ለእስዋ እንዲሰጥ የወሰነውም ይህንኑ የበለጠ ተቃሚነት የሚለውን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

እንደምናየው አመልካችም ሆነ ተጠሪ በሁለቱም ቤቶች ላይ ያላቸው መብት የእኩል ነው፡፡ ክፍፍሉ መደረግ ያለበት ይህን መሠረት በማድረግ በመሆኑ ሁለቱም ከሁለቱ ቤቶች እኩል ድርሻ ሊያገኙ ይገባል፡፡ ቤቶቹ በተለያዩ ከተሞች /አካባቢዎች/ እንደመገኘታቸው መጠን የሚኖራቸው ዋጋም እንደዚሁ እንደሚለያይ መገመቱ አይከብድም፡፡ የቤቶቹ አሠራር እና ያሉበት ልዩ አካባቢም /ቦታም/ በሚያወጡት ዋጋ ላይ የራሱ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታወቃል፡፡ በእርግጥ እነዚህ ልዩነቶች ቢኖሩም ግራ ቀኝ ወገኖች ስምምነት ላይ ከደረሱ ያለምንም ችግር በስምምነቱ መሠረት ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡ ስምምነት ከሌለ ግን በሕጉ የተቀመጠውን የእኩልነት መርህ እና አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች የተቀመጠውን የክፍፍል ሥርዓት መሠረት በማድረግ ክፍፍሉ እንዲፈጸም መወሰን የግድ ይሆናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ለክፍፍሉ አፈፃፀም መሠረት ያደረገው የበለጠ በንብረቱ የመጠቀም ሁኔታ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ እንደ ትክክለኛ የክፍፍል ሥርዓት ተቆጥሮ ተቀባይነት የሚያገኝ አይደለም፡፡ በበኩላችን ትክክለኛ የክፍፍል ሥርዓት ሆኖ ያገኘነው በቅድሚያ ሁለቱም ቤቶች በገበያ ዋጋ መሠረት የሚያወጡት ዋጋ እንዲታወቅ ማድረግ፤ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች የገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ በዓይነት ለመከፋፈል ስምምነት ላይ ከደረሱ የበለጠ ዋጋ ያለውን ቤት የሚወስደው ወገን ገበያ ባስገኘው ዋጋ መሠረት ሌላኛውን ወገን ልዩነቱን በገንዘብ እንዲያካክስ፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ በሕጉ በተቀመጠው የመጨረሻው አማራጭ ቤቶቹ ተሸጠው ገንዘቡን እንዲከፋፈሉ ማድረግ ነው፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ክፍፍሉን በዚህ መሠረት እንዲከናወን ባለመወሰኑ ውሣኔው በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የሃዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በፍ/ብ/መ/ቁ. 14336 ሚያዝያ 8 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ፣ የአዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በፍ/ብ/መ/ቁ. 6945 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ 28643 ነሐሴ 7 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. በሃዋሣ ከተማ እና በወላይታ ሶዶ ከተማ ያሉት ቤቶች በቅድሚያ በገበያ ዋጋ መሠረት ተገምተው ዋጋቸው እንዲታወቅ እንዲደረግ፤ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች የሚስማሙ ቢሆን የቀረበውን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ቤቶቹን በዓይነት እንዲካፈሉ፤ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን የወሰደው ወገንም ሌላኛውን ወገን ልዩነቱን በገንዘብ እንዲያካክስ፤ በዚህ



www.chilot.me

መሠረት ተስማምተው መከፋፈል ካልቻሉ ግን ሁለቱም ቤቶች ተሸጠው ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49359

ጥቅምት 4 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች:-** ወ/ሮ ቀለሚ ወርቅነህ ሺበሺ

**ተጠሪ:-** ሻምበል ጌታሁን ገብሬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የሟች እህትዋ ወራሽ መሆንዋን መሠረት በማድረግ ያቀረበችው የውርስ ንብረት የመካፈል ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ውድቅ በመደረጉ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ከተጠሪ የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል እና በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000/1/ የተቀመጠውን የሦስት ዓመት የጊዜ ወሰን መሠረት በማድረግ ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ብታቀርብም፤ ውሣኔው ጉድለት የለበትም ተብሎ ይግባኙ ተሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 21 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበችበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱን የሚያርም ውሣኔ ይሰጥላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የተባለው በአግባቡ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን በማስመልከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ክስ የመሠረተችው የወራሽነት መብትን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት ባለሃብት ነበረች የተባለችው የአመልካች እህት የሞተችው መጋቢት 11 ቀን 88 ዓ.ም ሆኖ አመልካች የውርስ ንብረቱ እንዲሰጣት ክስ የመሠረተችው ደግሞ ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በመነሣት ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤቶችም ተመሣሣይ ምክንያት በመስጠት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ወስነዋል፡፡ አመልካች ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ትክክል አይደለም በሚል ክርክርዋን በመግፋት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡ በዚህ ረገድ የሰጠችው ምክንያት ሟች እህቴ



www.chilot.me

የተወቸልኝን ኑዛዜ በፍ/ቤት ሳላስፀድቅ በውርስ ንብረቱ ላይ ጥያቄ ማንሣት አልቻልኩም ነበር። ስለዚህም ኑዛዜው እንዲፀድቅልኝ ለፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቤ ስከራከር ከቆየሁ በኋላ ሲፀድቅልኝ በንብረቱ ላይ ክስ መሥርቻለሁ የሚል ነው። ተጠሪ ኑዛዜው መጽደቅ የለበትም በማለት ሲከራከራት እንደቆየም በአቤቱታዋ የገለፀች ሲሆን፣ ተጠሪም ይህ እውነት አይደለም የሚል መልስ ወይም ክርክር አላቀረበም።

ከቀረበው ክርክር እንደምንገነዘበው በእርግጥ አመልካች በንብረቱ ላይ ክስ የመሠረተችው ሟች ከሞተች ከአሥራ ሦስት /13/ ዓመት በላይ ቆይታ ነው። ነገሩ ከዚህ ሁኔታ ብቻ በመነሳት ሲታይ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ለማለት ይቻላል። ኑዛዜውን በፍ/ቤት ሣላስፀድቅ በውርስ ንብረቱ ላይ ክስ መመሥረት አልችልም ነበር የሚለው ክርክርም እንዳለ በቀጥታ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም። ኑዛዜው እስካለ ድረስ ወይም አመልካች የሟች እህት ነኝ እስካለች ድረስ በንብረቱ ላይ በቀጥታ መክሰስ እየቻለች ኑዛዜ በፍ/ቤት አስፀድቃለሁ በማለት ጊዜዋን ካሣለፈች ይርጋን በተመለከተ ለቀረበበት መቃወሚያ መከራከሪያ አድርጋ ልታቀርበው አትችልም። ኑዛዜው ዋጋ የሚኖረው በፍ/ቤት ስለፀደቀ ሣይሆን በሕግ የተቀመጡትን የኑዛዜ መሠረቶች ወይም መስፈርቶች ሲያሟላ ነው። ይህ የሰበር ችሎትም ከዚህ በመነሣት ኑዛዜ ለፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ በኑዛዜው ሕጋዊነት ላይ የሚጨምረው ነገር የለም በማለት ቀደም ሲል በሰጣቸው ውሣኔዎች ለሕጉ ትርጉም ሰጥቶአል። በመሆኑም ኑዛዜውን በፍ/ቤት ሳላስፀድቅ በውርስ ንብረቱ ላይ ክስ መመሥረት አልችልም ነበር የሚለው የአመልካች ክርክር በሕግ ረገድ ተቀባይነት ያለው አይደለም።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተነሣው ክርክር ከሌላም አቅጣጫ መታየት እንደለበት ከክርክሩ አመጣጥ እና ልዩ ባህርይ ለመገንዘብ ችለናል።

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው የኑዛዜውን መጽደቅ በተመለከተ በቀረበው አቤቱታ ተጠሪም ተካፋይ እንደነበረ የራሱ ምክንያት በመስጠት ኑዛዜው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ሲከራከር እንደቆየ ተገንዝበናል። የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 03103 ግንቦት 23 ቀን 98 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው አመልካች ኑዛዜ ይጽደቅልኝ የሚለውን አቤቱታ ለፍ/ቤቱ ያቀረበችው መጋቢት 17 ቀን 88 ዓ.ም ነው። ይህም ማለት ሟች ከሞተች /መጋቢት 11 ቀን 88 ዓ.ም/ በስድስት /6/ ቀን ውስጥ አቤቱታው ቀርቦአል ማለት ነው። ተጠሪ መልስ የሰጠው ሚያዝያ 3 ቀን 89 ዓ.ም ሲሆን፣ የኑዛዜው መደረግ አጠራጣሪ ነው፣ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ ከሟች ፊርማ ጋር አይመሳሰልም፣ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የኔም የጋራ ሐብት ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሮአል። ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክርክሩን ሲያይ ቆይቶ ውሣኔ የሰጠው ግንቦት 23 ቀን 98 ዓ.ም እንደሆነ ተመልክተናል። እነዚህን ሁኔታዎች ደምረን ስንመለከት አመልካች በጊዜው በንብረቱ ላይ ክስ ሣትመሠርት የቀረችው ተጠሪም ባደረገው አስተዋጽኦ እና ፍ/ቤቱ ባጭር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ባለመስጠቱ ነው ለማለት ችለናል። አመልካች እና ተጠሪ ሲከራከሩ የቆዩትም አመልካች በኑዛዜው መሠረት ንብረት ልትወርስ የምትችልበት አግባብ አለ ወይስ የለም ከሚለው ጋር በተያያዘ ሁኔታ እንደሆነ መመልከቱ የሚከብድ አይደለም። ከዚህ የተነሣም ይርጋው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1851/ለ/ በተመለከተው መሠረት ተቋርጦአል ለማለት የሚቻል ነው። ሲጠቃለል አመልካች ያቀረበችው ክስ በይርጋ ተቋርጦአል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ሕጉን በአግባቡ በማየት የተሰጠ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል።



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 26317 ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 0498 ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ//ሥ/ሥ/ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ አለመሆኑን በመገንዘብ ግራ ቀኝ ወገኖች በጉዳዩ ስረ- ነገር ላይ የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኂላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት ይመለስለት፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 53663

ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡** 1. አቶ ጊላጋብር ገብረህይወት

2. ወ/ሮ ለተሀዋርያት ገብረህይወት

3. ወ/ሮ ምፅላል ዓለም

ጠበቃ ስሜነህ ተክሉ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡** 1. ወ/ሮ አረጋሽ አብርሃ

2. አቶ በርሀ አርጋው

አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ከፍተኛ 20 ቀበሌ 29 የቤት ቁጥር 139 የሆነ መኖሪያ ቤትና የሰሌዳ ቁጥር 3-13285 ኢ.አ የሆነ ቦቴ መኪና በህይወት እስካሉ ድረስ አባታችን አቶ ገብረህይወት ሊያዙበት እሳቸው ሲሞቱ ወ/ሮ ብሬ እስከህይወታቸው ተጠቅመው ንብረቱ ለእኛ እንዲተላለፍ ስምምነት አድርገዋል፡፡ የሟች አቶ ገብረህይወት ባለቤት ወ/ሮ ንግስቲ ስምምነቱ የተደረገው በእኔ የጋራ ንብረት ነው በማለት ክስ አቅርበው ወ/ሮ ብሬና እኛ ግማሹን የቤትና የመኪና ግምት እንድንከፍል ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ወ/ሮ ብሬ በቤቱ ሲገለገሉ ቆይተው ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ.ም በሞት ተለይተዋል፡፡ በቤቱ መብት ያለን እኛ ስለሆን በሥር ተከሣሽ የነበሩት አንደኛ ተጠሪ አላግባብ የያዙ ስለሆነ ቤቱን ለቅቀው እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት አመልክተዋል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በሥር በተከሣሽነት ቀርበው በቤቱ ውስጥ የምኖረው ሟች ወ/ሮ ብሬ እየረዱኝ በጥገኝነት ነው ስለዚህ በቤቱ ላይ መብት የሌለኝና በሟች ወራሾች ፈቃድ የምኖር በመሆኑ ክሱ ተዘግቶ በነፃ እድሰናበት በማለት የተከራከሩ ሲሆን ሁለተኛው ተጠሪ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ በመሆን የሟች ወ/ሮ ብሬ ወራሽ መሆኑን ገልፆ ወ/ሮ ብሬና ሟች አቶ ገብረህይወት ያደረጉት ውል በህግ



www.chilot.me

ፊት የሚፀና ባለመሆኑና አመልካቾች /የሥር ከሣሾች/ የወ/ሮ ብሬ ወራሾች ባለመሆናቸው ውሉም በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ቤቱ የወ/ሮ ብሬ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ውሉ መኖሩ ባልተካደበት ሁኔታ የውሉ ፎርም መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36887 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ ጣልቃ ገቡ በወ/ሮ ብሬና በአቶ ገብረህይወት መካከል የተደረገው ውል ፎርሙን አላሟላም በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ አልተቀበልኩትም ቤቱ የሟች አቶ ገብረህይወት መሆኑ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 በሁለቱ በወ/ሮ ብሬና በአቶ ገብረህይወት መካከል የተደረገው ውል ስለሚያስረዳ ተከሣሹና ጣልቃ ገብ /የአሁን ተጠሪዎች/ ቤቱን ከሣሾች /አመልካቾች/ ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ውሉ የስጦታ ውል ነው የስጦታ ውል መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ ከሣሾች ቤቱ ከወ/ሮ ብሬ ጋር አባታችን ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲኖሩ የተገዛ የጋራ ንብረት ነው በማለት ከሚጠይቁ በስተቀር የስጦታ ውል መሠረት በማድረግ ቤቱን እንረከብ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 6 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የይግባኝ ማመልከቻ በመጀመሪያ በሠራተኝነት የገቡትና ኃላም ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩት ወ/ሮ ብሬ መሲሳና አባታችን አቶ ገብረህይወት ደበሣይ ወ/ሮ ብሬ እኛን ማሣደጋቸውንና ልጅ የሌላቸው መሆኑን ምክንያት በማድረግ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ውል ተዋውለዋል፡፡ በውላቸውም በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 20 ቀበሌ 29 ቁጥሩ 139 የሆነው መኖሪያ ቤትና ቦቴ መኪና ገዝተው ስሙ በሟች ብሬ መሲሳ ሆኖ ንብረቱን በሙሉ ባለሀብትነት የሚያዙበት አባታችን አቶ ገ/ሕይወት ደበሣይ እንደሆኑ አባታችን ሲሞቱ ወ/ሮ ብሬ በንብረቱ ህይወታቸው እስካለ ተጠቅመው በሟች አቶ ገብረህይወት ልጆች ንብረቱን ሊያስተላልፉ ተስማምተው የውል ግዴታ ገብተዋል ይኸ ውል ከተፈረመ ከሶስት ዓመት በኃላ ሟች አቶ ገብረህይወት በሞት የተለዩ ሲሆን ወ/ሮ ብሬ ከአስራ አምስት ዓመት በኃላ በሞት ተለይተዋል፡፡ ውሉ ስለንብረት ባለቤትነትና ንብረትን ስለመጠቀም በሟች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና በሟች ወ/ሮ ብሬ መሲሳ የተደረገ ሆኖ እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሉ ስጦታ ውል ነው ስጦታ ውሉ የህጉን ፎርም ባሟላ መልኩ የተደረገ አይደለም በማለት ግልፅ የሆነውን የውል ስምምነት ከተዋዋይ ወገኖቹ ፈቃድና ፍላጎት የራቀ ትርጉም በመስጠት ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ቤቱና መኪናው የተገዙት አቶ ገብረህይወት ጋር ሲኖር በተፈራ የጋራ ሀብት ነው ብለው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01302 በሟች ብሬ ሞሲሳና በእኛ ላይ ወ/ሮ ንግስቲ ገ/እግዚ ክስ አቅርበውብን መኪናውና ቤቱ የተገዙት በሟች ገብረህይወትና በወ/ሮ ንግስቲ የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሣኔ የተሰጠ በመሆኑ ሟች ብሬ ሞሲሳ ከሟች አቶ ገብረሕይወት ጋር ያደረጉት ውል ህጋዊ ነው ሊፀና ይገባል



www.chilot.me

በማለት በመዝገብ ቁጥር 01302 ከወ/ሮ ንግስቲ ጋር የተከራከሩበት ሆኖ እያለ የሟች ወ/ሮ ብሬ ወራሽ ነን የሚሉት ሁለተኛው ተጠሪ ውሉ ፈራሽ ነው ብሎ ያቀረበው ክርክር አውራሽ አምኖበት ለፍርድ ቤት ያረጋገጠውን ወራሹ መካዱ ተገቢ ባለመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይህንን ክርክር በመቀበል ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ንብረቱ የተገዛው በሟች አቶ ገብረህይወት ገንዘብ ነው ተብሎ በውሉ መጠቀሱ ንብረቱን የሟች አቶ ገብረህይወት ንብረት አያደርገውም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የሚረጋገጠው በአስተዳደሩ ክፍል በሚሰጥ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1195 ተደንግጓል፡፡ አመልካቾች ቤቱ የሟች ወ/ሮ ብሬ አይደለም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ይህን የህግ ግምት የማያፈርስ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 የተመለከተ ምክንያት ባለመሆኑ አቤቱታቸው የህግ መሠረት የለውም፡፡

አመልካቾች በአንድ በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሉ የስጦታ ውል ነው የህጉን ፎርም አላሟላም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት እያሉ በሌላ በኩል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01302 አቶ ገብረህይወት ለሟች ወ/ሮ ብሬ ያደረጉት የስጦታ ውል የወ/ሮ ንግስቲ የጋራ ንብረትና ድርሻ ያለበት ስለሆነ ግማሹን እንዲከፍሉ ብሎ የሰጠውን ውሣኔ በመከራከሪያነት ማንሣታቸው እርስ በርሱ የሚቃረን መከራከሪያ ነው በእርግጥ  ሟች ወ/ሮ ብሬ የወ/ሮ ንግስቲ ድርሻ ግማሹን እንዲከፍሉ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ሰጥቷል ሆኖም ውሣኔው አልተፈፀመም በአጠቃላይ የአመልካቾች ክርክር የህግ መሠረት የሌለውና ዕርስ በርሱ የሚቃረን በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ሟች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና ሟች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል የስጦታ ውል ማሟላት ያለበትን ፎርማሊቲ ያላሟላ ስለሆነ ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ቤት ለአመልካቾች የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ ሟች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና በሟች ብሬ ሞሲሳ መካከል የነበረውን ግንኙነት መሠረታዊ ባህሪ እንደዚሁም ሟች አቶ ገብረህይወትና ሟች ወ/ሮ ብሬ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል መሠረታዊ ይዘቱ እና በሕግ ረገድ የሚያስከትለውን ውጤት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሟች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና ሟች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት ለረዥም ጊዜ አብረው የኖሩ መሆናቸውንና ወ/ሮ ብሬ ሟች አቶ ገብረህይወት ደበሣይ ከሌሎች ሴቶች የወለዷቸውን ልጆች እንደ ወላጅ እናት ተንከባክበው ያሣደጉ መሆኑ በአመልካቾች የተገለፀና ተጠሪዎችም ያልካዱት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ለረጅም ጊዜ አብረው የኖሩት አቶ ገብረህይወትና ወ/ሮ ብሬ ባልና ሚስት የሚያሣዩአቸውን ሁኔታዎች የሚታዩባቸው የነበሩ መሆኑንና በመካከላቸውም የመተሣሠብ የመተማመን ሁኔታ የነበረ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ባልና ሚስት ከጋብቻቸው በፊት



www.chilot.me

ወይም ጋብቻ በሚፈፅሙበት ወቅት በንብረት ረገድ ስለሚኖራቸው ግንኙነት የጋብቻ ውል የሚያደርጉበት ሁኔታ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 42 የተደነገገ ሲሆን በተመሳሳይ መንገድ ባልና ሚስት ነን እየተባባሉ ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው የሚኖሩ ሰዎች በመካከላቸው ያለውን የንብረት ግንኙነት የሚመለከት ውል ቢዋዋሉ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ የሚያስነሳ ሲሆን የባልና የሚስት ሁኔታ እያሣዩ ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ስለግላዊ ግንኙነታቸውና በንብረት በኩል ስለሚኖራቸው ግንኙነት የመዋዋል ነፃነታቸውን በሚያሳጣና ውል እንዳይዋዋሉ የሚከለክል ግልፅ የህግ ድንጋጌ የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ህግ አውጭው የመዋዋል ነፃነታቸውንና የሚዋዋሉበትን መሠረታዊ ጉዳይ በህግ በግልፅ ክልከላ ካላደረገ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 መሠረታዊ ሁኔታዎች በማሟላት እንደባልና ሚስት የሚኖሩት አንድ ወንድና አንዲት ሴት ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ስለሚኖራቸው የግል ግንኙነትና የንብረት ግንኙነት ውል የመዋዋል ነፃነት ያላቸው መሆኑንና ይህም በውል ህግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚመራና ውጤት ያለው መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1676/1/ ውሎች አይነታቸውና ምክንያታቸው ማንኛውም ቢሆን በዚህ አንቀጽ ጠቅላላ ደንቦች ይመራሉ በማለት የደነገገውን ገዥ ድንጋጌ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ሟች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና በሟች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል እንደባልና ሚስት ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት ሲኖሩ በንብረት ረገድ የሚኖራቸውን ግንኙነት አንዳቸው በሞት ሲለዩ በተለይ አቶ ገብረህይወት በድንገት በሞት ሲለዩ በቀሪው እድሜ ወ/ሮ ብሬ በንብረቱ ላይ ስለሚኖራቸው መብት ውል አይደለም ሁለቱም ነፃ ሁነው ፈቃዳቸውን የሰጡበት የውል ሰነድ እንጅ፡፡ በዚህ በኩል ተጠሪዎችም በሆኑ ውሉ የፈቃድ ጉድለት ያለበት ነው በማለት ከሥር ጀምሮ ያቀረቡት ክርክር የሌለ መሆኑን በመዝገቡ ከተያያዙት የፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የውሉን ይዘት ስንመለከተው አምስት መሠረታዊ ነጥቦችን የያዘ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የመጀመሪያው ውሉ በአቶ ገብረህይወትና በወ/ሮ ብሬ መካከል ያለው ግንኙነት በምን መንገድ እንደተጀመረና ውሉን በሚዋዋሉበት ጊዜ በምን ሁኔታ ወይም ደረጃ እንደሚገኝ በስምምነታቸው የገለፁበት ነው፡፡ በውሉ ወ/ሮ ብሬ በመጀመሪያ በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው የገቡ ቢሆንም ከዚያ በኃላ ግንኙነታቸው ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነታቸው እንደ ባልና ሚስት አብረው የኖሩ መሆኑን በግልፅ ያመለክታል፡፡

ሁለተኛው ወ/ሮ ብሬ አቶ ገብረህይወት ከሌሎች ሴቶች የወለዷቸውን ልጆች በእናትነት በመንከባከብና በማሳደጋቸው ከአቶ ገብረህይወት ጋር ለረዥም ጊዜ አብረው በመኖራቸው የሰሌዳ ቁጥር 3-13285 የሆነ ቦቴ መኪናና በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ከፍተኛ 20 ቀበሌ 29 ቁጥሩ 139 የሆነው ቤት በወ/ሮ ብሬ ስም እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ ሶስተኛው ከላይ የተገለፁትና በወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ ስም የተመዘገቡት ንብረቶች የተገዙት ወ/ሮ ብሬና አቶ ገብረህይወት ሠርተው ባገኙት የጋራ ገቢ /የጋራ ሀብት/ ሣይሆን ሙሉ በሙሉ በአቶ ገብረህይወት የግል ገንዘብ የተገዙ መሆናቸውን በግልፅ የሚያብራራ ሲሆን አራተኛ ንብረቶቹ በወ/ሮ ብሬ ስም ያሉ ቢሆንም አቶ ገብረህይወት በህይወት እስካሉ ድረስ በንብረቶቹ ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ያላቸው መሆኑን በቤቱም ሆነ በመኪናው ገቢ የሚያዙበት አቶ ገብረህይወት መሆናቸውን በግልፅ የሚደነግግ መሆኑ ነው፡፡ አምስተኛው ወ/ሮ ብሬ ከአቶ ገብረህይወት በፊት በሞት ቢለዩ ንብረቱ ሙሉ በሙሉ



www.chilot.me

የአቶ ገብረህይወት እንደሆነ የሚያረጋግጥና ድንገት አቶ ገብረህይወት ከወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ በፊት በሞት ቢለዩ በንብረቶቹ ላይ ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ በህይወት እስካሉ የመጠቀምና አላባ የመሰብሰብ መብት ያላቸው መሆኑን "..... ሞት በሰው ላይ ያለ የተፈጥሮ ግዴታ ስለሆነ ከእሳቸው በፊት ህይወቴ ቢያልፍ ንብረቱ የራሳቸው ገንዘብ ስለሆነ የመኪናውም ሆነ የቤቱ ባለመብት ናቸው ከእኔ ህይወት በፊት የእሳቸው ህይወት ቢያልፍ ህይወቴ እስካለ ድረስ በመኪናውና በቤቱ ተጠቃሚ እኔ ሆኜ ከህይወት በኃላ እኔ ላሣደግኳቸው የሁለተኛ ተስማሚ ልጆች 1ኛ ህይወት ገ/ሕይወት 2ኛ ጊላ ገብረህይወት 3ኛ ለተሃዋሪያት ገብረህይወት እንዲተላለፍ በፈቀዱት መሠረት ለእነዚሁ ልጆች ቤቱና መኪናው የሚተላለፈው ባለመብት የሚሆኑት ልጆች መሆናቸውን በፊርማየ አረጋግጣለሁ በማለት ወ/ሮ ብሬ የተስማሙና አቶ ገብረህይወትም ስምምነቱን የተቀበሉ መሆኑን የሚያረጋግጥ የውል ሰነድ ነው፡፡

ይህ ውል ከተደረገ በኂላ አቶ ገብረህይወት በሞት ሲለዩ አመልካቾች የውሉን ድንጋጌ በመጣስ ወ/ሮ ብሬ ንብረት ያካፍሉን የሚል ክስ ያላቀረቡ መሆኑን በግራቀኙ በኩል ከተደረገው ክርክር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የአሁኑ ክርክር መነሻ ወ/ሮ ብሬ በህይወት እስካሉ ድረስ በንብረቱ የመጠቀም መብታቸውን ተጠቅመው ካለፉ በኃላ ሁለተኛ ተጠሪ ንብረቱን ልወርስ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ነው፡፡ በህግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋማቸው ሰው ላይ ህግ ናቸው በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731/1/ የሚደነግግ ሲሆን አንድ ሰው በሞት ሲለይ በሟች መሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆኑ በስተቀር በውርሱ ውስጥ የሚገኙት መብቶችና ግዴታዎች ለወራሾቹ ወይም የኑዛዜ ባለስጦታዎች የሚተላለፍ መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 826/2/ ተደንግጓል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ ሊወርስ የሚችለው በወ/ሮ ብሬ መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብቶችና ግዴታዎችን ነው፡፡ ሟች ወ/ሮ ብሬ አከራካሪው ቤት በስማቸው የተመዘገበ ቢሆንም ቤቱ በሟች አቶ ገብረህይወት የግል ገንዘብ የተገዛ የአቶ ገብረህይወት የግል ሀብት እንደሆነ ወ/ሮ ብሬ አብረው እስካሉ ድረስ በጋራ የመጠቀም ሟች አቶ ገብረህይወት ከወ/ሮ ብሬ በፊት በሞት ቢለዩ በህይወት እስካሉ ድረስ በንብረቱ የመጠቀምና አላባ የመስበሰብ መብት ብቻ ያላቸው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ በመግለፅ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ከአቶ ገብረህይወት ጋር ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት ሲኖሩ በንብረት ረገድ ስላላቸው መብትና ግዴታ በመዘርዘር ባደረጉት ውል ተስማምተዋል አቶ ገብረህይወት በሞት ከተለዩ በኃላ በዚህ ውል መሠረት ወ/ሮ ብሬ በንብረቶቹ ላይ ያላቸው መብት ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1309 በተደነገገው መሠረት በንብረቶቹ የመጠቀምና አላባ የመሰብሰብ መብት መሆኑ በውሉ በግልፅ ተገልፆል፡ በሚንቀሳቀስም ሆነ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ የአላባ የመጠቀም መብት /Usufruct Right / የአላባ ጥቅም ተቀባዩ ሲሞት ቀሪ የሚሆን መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1322/1/ የተደነገገ በመሆኑ ሟች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ በአከራካሪው ቤት ላይ ያላቸው የመጠቀምና አላባ የመሰብሰብ መብት በመሞታቸው ምክንያት የሚቋረጥና ለወራሻቸው ለሁለተኛው ተጠሪ የማይተላለፍ መብት መሆኑን ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች በማገናዘብ ለመረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሟች አቶ ገብረህይወትና ወ/ሮ ብሬ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል ከጋብቻ ውጭ እንዳባልና ሚስት ከግብረሥጋ ግንኙነት አብረው ሲኖሩ በንብረት ረገድ ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ያደረጉት ውል ሆኖ እያለ የስጦታ ውል ነው በማለት ከውሉ መሠረታዊ ይዘትና ባህሪ ውጭ የራሱን ትርጉም መስጠቱና ውሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 881 የተደነገገውን ፎርም አላሟላም በማለት የማይረጋ ነው ብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ

ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ወ/ሮ ብሬና አቶ ገብረህይወት ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል በንብረት ረገድ ያላቸውን ግንኙነትና ሁለቱም ያላቸውን መብትና ግዴታ በሙሉ ፈቃዳቸው የተስማሙበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ድንጋጌዎች መሠረት በተዋዋዬቹና በምስክሮች የተፈረመ ህጋዊ ውጤት ያለው ውል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በውሉ ሟች ወ/ሮ ብሬ በአከራካሪው ቤት ባለሀብት አለመሆናቸውና አቶ ገብረህይወት ከሞቱ በኃላ ወ/ሮ ብሬ በአከራካሪው ቤት ላይ የነበራቸው በንብረቱ የመጠቀምና ፍሬ የመሰብሰብ መብት እንደሆነ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ወ/ሮ ብሬ በቤቱ ላይ ያላቸው የአላባ ጥቅም መብት ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ምክንያት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1322/1/ መሠረት ቀሪ ስለሆነ ሁለተኛ ተጠሪ የአመልካቾች አባትና አውራሽ የአቶ ገብረህይወት ደበሣይ የግል ንብረት የሆነውን አከራካሪውን ቤት የሚወርሰበት ምክንያት የሌለው በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በውጤት ደረጃ ፀንቷል
3. አከራካሪውን ቤት ተጠሪዎች ለአመልካቾች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡
4. በሟች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳና በሟች አቶ ገብረህይወት ደበሣይ መካከል ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም የተደረገው ውል ህጋዊ አስገዳጅነትና ውጤት ያለው ውል ነው ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49831

ጥቅምት 2 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ሮማን ግዛው - ጠበቃ አቶ ግርማ

**ተጠሪ፡-** አቶ ግርማ አብርሃም - ጠበቃ አቶ አምዴ አበበ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስላመለከቱ ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ ሟች ወ/ሮ አስካለ ወልደየስ መስከረም 10 ቀን 1993 ዓ.ም. አመልካችን ኑዛዜ ወራሽና ተጠቃሚ የሚያደርግ ኑዛዜ አድርገዋል፡፡ የሟች የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ ይታወቅልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ በመመርመር አመልካች የሟች ወ/ሮ አስካል ወልደየስ የኑዛዜ ወራሽ መሆኗን በማረጋገጥ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካቲት 21 ቀን 1997 ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ይህንን ፍርድ በመቃወም የሟች የወንድም ልጅ የሆንኩት እኔ እያለሁ አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ነኝ በማለት በፍርድ ያስወሰነችው አላግባብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሟች በአመልካች ያደረጉትን ኑዛዜ ጥቅምት 9 ቀን 1997 ዓ.ም. ባደረጉት ኑዛዜ ተክተውታል በማለት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ በተጨማሪም ኑዛዜውን ሟች ያላደረጉት ነው የሚል መከራከሪያም አቅርበዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ተጠሪ ሟች ያደረጉትን ኑዛዜ ያውቃሉ በኑዛዜው መሠረት ለሌሎች ሰዎች ሲፈፀም በምስክርነት ተገኝተዋል፡፡ ፊርማው የሟች ነው፡፡ ዋናው የሚገኘው በሌላ ሰው እጅ በአደራ ተቀምጦ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የኑዛዜ ዋና ቅጂ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ የአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ማመልከቻ ተቀብሎ በሚያጣራበት ሰዓት ቀርቦ ከኮፒው ጋር የተገናዘበ መሆኑን ኮፒው ላይ ዳኛ አረጋግጦ የፈረመበት መሆኑን በመተቸትና በአሁኑ ወቅት ዋናው አለመቅረቡ የፖሊስ ምርመራ ባይደረግም ማስረጃ ተዓማኒነት ያለውና ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ነው፡፡ ሟች ጥቅምት 9 ቀን 1997 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ በፊት ካደረጉት ኑዛዜ የተለየና ሟች ለአመልካች ያደረጉትን ኑዛዜ ጋር የማይቃረንና የማይተካ ነው በማለት የተጠሪን የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡



www.chilot.me

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ኑዛዜውን በመቃወም የሚች ፊርማ እንዳልሆነ ገልፆ ሲከራከር ፊርማውን ለማስመርመር ዋናው ኮፒ ሲፈለግ አመልካች ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ አመልካች ዋናውን ኑዛዜ በማቅረብ ትክክለኛነቱን ማስረዳት ስላልቻሉ ኑዛዜው ሕጋዊ ተቀባይነት የለውም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች እኔ የሚች የኑዛዜ ወራሽ መሆኔን ባመለከትኩበት መዝገብ የኑዛዜው ዋና ኮፒ ከቀረበው ፎቶ ኮፒ ጋር ተገናዝቦ ትክክለኛነቱ ምልክት ተደርጎበት ምስክሮችን አስመስክሬ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡት ይህ ሁሉ ሂደት ሲከናወን እያወቁ ቆይተው ነው፡፡ ዋናው ኮፒ አንድ ጊዜ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ከታየ ከተረጋገጠ በኋላ መጥፋቱ ኑዛዜውን ለማስረዳት የሚችል ማስረጃ የለሽም የሚያስብል አይደለም፡፡ ኑዛዜው የሚች ኑዛዜ መሆኑ በሰው ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ለሕጉ የተዛባ ትርጉም በመስጠት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ያቀረቡት ፎቶ ኮፒ በሬጅስትራር ቀርቦ መረጋገጡን አያመለክትም፡፡ ዋናውን ሰነድ ለማስቀረብ የተሰጠውን ተደጋጋሚ ትዕዛዝ አመልካች ሊፈጽሙ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ አመልካች በሕግ በተደነገገው መሠረት የኑዛዜውን ዋና ኮፒ በማቅረብ ለማስረዳት ስላልቻሉ የበታች ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው በሕግ ፊት ውጤት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልሰ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ ከተማ የሰበር ችሎት አመልካች የኑዛዜ ወራሽና ተጠቃሚ መሆኗን የኑዛዜውን ዋናውን ሰነድ አቅርባ ባለማስረዳቷ ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ኑዛዜውን የማስረዳት ሸክም ስላለበት ወገንና ኑዛዜውን ለማስረዳት ሊቀርቡ ስለሚገቡ ማስረጃዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 896 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 የተደነገገውን ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ኑዛዜ መኖሩንና በኑዛዜው የሰፈረውን ቃል የማስረዳት ግዴታ ያለበት የኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ የሚለው ሰው መሆን እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 896 ይደነግጋል፡፡ የኑዛዜ ተጠቃሚው መብቱን ያገኘው በግልጽ ወይም በተናዛዥ ጽሁፍ በተደረገ ኑዛዜ በሆነ ጊዜ የኑዛዜውን መኖር ለማረጋገጥ የኑዛዜውን ጽሁፍ ዋናውን ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ዘንድ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ትክክለኛ ሆኖ የተመሳከረ ግልባጭ በማቅረብ እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 የሚደነግግ ሲሆን ኑዛዜዎቹን ለማስፈፀም በማናቸውም ሌላ መንገድ ማስረዳት እንደማይቻል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡



www.chilot.me

አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሟች ወ/ሮ አስካለ ወልደየስ መስከረም 10 ቀን 1993 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚና ወራሽ መሆኗን አረጋግጦ እንዲወስንላት ስታመለክት የኑዛዜው ዋና ሰነድ በወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ እጅ መሆኑን ገልፀው ፍርድ ቤቱ ዋናውን በማስቀረብ እንዲመለከተው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 223 መሠረት የካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ጠይቀዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤትም የኑዛዜው ዋና ሰነድ ለየካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም. እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም. የኑዛዜው ዋና ሰነድ ቀርቦ የታየና የተረጋገጠ መሆኑን በኮፒው ጀርባ የዳኛ ፊርማ የተፈረመበት ሲሆን ዋናው የኑዛዜ ሰነድ የቀረበውም ፍርድ ቤቱ የኑዛዜውን ዋና ሰነድ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በሰጠበት የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑን ይህ የሰበር ችሎት በትዕዛዝ ካስቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁ. 1185/97 ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኑዛዜው ዋና ሰነድ በእጃቸው የነበረው ወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ ለፍርድ ቤት በምስክርነት ቀርበው ሟች ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን የመሰከሩ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ባቀረበበት ጊዜ ወ/ሮ ትዕግሥት የኑዛዜውን ዋና ሰነድ ለፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆኑና ዋናው ሰነድ እንዳልተመለሰላቸው የገለጹ መሆኑን የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውሣኔው ገልፆታል፡፡

ከዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች የኑዛዜ ተጠቃሚና ወራሽ መሆኗን ለማስረዳት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት ዋናውን የኑዛዜ ሰነድ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም የተረጋጠውን በማቅረብ አስረድታለች ወይስ አላስረዳችም የሚለው ነው፡፡ ሟች ወ/ሮ አስካለ ወልደየስ ኑዛዜ ያደረጉት በሁለት ኮፒ እንደሆነና አንደኛው ኮፒ በወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ ሁለተኛው በአባ ማሞ አርጋው እጅ መቀመጥ እንዳለበት በኑዛዜው የገለጹ መሆኑን ሰነዱ ያሣያል፡፡ የኑዛዜው ዋና ሰነድ ወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ እጅ የነበረና በሌላ ሰው እጅ የካርቦን ኮፒው የነበረ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የኑዛዜ ወራሽነቷን የሚያረጋግጥላት ሰነድ በወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ እጅ እንደሚገኝ በማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ላይ በመግለጽ ወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ ዋናውን ሰነድ ለፍርድ ቤት የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም. እንድታቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የካቲት 17 ቀን 1997 ዓ.ም. ዋናው ሰነድ ቀርቦ ከዋናው ጋር የተረጋገጠ መሆኑ በኮፒው ጀርባ ዳኛ ጽፎ የፈረመበት በመሆኑ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት የኑዛዜውን ዋና ሰነድ በማቅረብ አላስረዳችም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎት የሰጡት የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች ዋናው የኑዛዜ ሰነድ በአደራ ይዘውት በነበሩት ሴት በኩል ቀርቦ ትክክለኛነቱ በዳኛ ከታየና ከተረጋገጠ በኋላ ተጠሪ ተቃውሞ ሲያቀርብ ይህ ሰነድ አለመቅረቡና መጥፋቱ አመልካች ኑዛዜ መኖሩን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አላስረዳችም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ተጠሪ ፊርማውን የካደ ቢሆንም በግልጽ ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩ ምስክሮች ኑዛዜው ላይ የሟች መሆኑን ገልፀው የመሰከሩና የኑዛዜ ሰነዱም በአመልካች እጅ ሣይሆን በሌላ ሰው እጅ በአደራ ተቀምጦ የቆየ መሆኑን በማገናዘብ ኑዛዜው የሟች ኑዛዜ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዛባ ትርጉም በመስጠት መሻራቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የአዲስ አበባ ከተማ የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል
3. አመልካች ሟች መስከረም 10 ቀን 1993 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚና ወራሽ ናት ብለናል፡፡
4. በትውስት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡
5. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 53223

ጥቅምት 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ አቶ ሐዲስ ዓለመስላሴ - ጠበቃ ጌታቸው ውብሸት ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** ወ/ሮ ብሌኔ ዓለመስላሴ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው ይግባኝ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘትም የአሁኑ አመልካቾች እናት ሐምሌ 30 ቀን 1986 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካቲት 27 ቀን 1990 ዓ.ም መጽደቁን ገልፀው ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም በማለት ኑዛዜው እንዲፈርስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም ለክሱ በሰጡት መልስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ተጠሪ ክስ ለመመስረት መብት ወይም ጥቅም የላቸውም ኑዛዜውን ለመቃወምም ይርጋ ያግዳቸዋል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲያቀርቡ በፍሬነገር ደረጃም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ተጠሪ ኑዛዜውን የተቃወሙት ኑዛዜው ከተደረገ ከአስራ ሁለት አመታት በሁዋላ ስለሆነና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 974(2) ድንጋጌ ተቀባይነት የሌለው ነው በሚል ምክንያት አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኗ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የተጠሪ ጥያቄ ኑዛዜው የተደረገው መብት በሌላቸው ንብረት ስለሆነ ይፍረስልኝ የሚል በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 974 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን በመሻር በሌሎች ነጥቦች ላይ አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት መልሶለታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

እኛም የአመልካቾች ጠበቃ የካቲት 18 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካቾች ከስር ጀምረው አቅርበው ሲከራከሩበት የቆዩት የይርጋ



www.chilot.me

መቃወሚያ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡በዚህ መሠረትም ይህ ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የስር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው አከራካሪው ኑዛዜ የተደረገው ሐምሌ 30 ቀን 1986 ሲሆን ተጠሪ ኑዛዜውን በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት ሕዳር 19 ቀን 1999 ኑዛዜ ከተደረገ ከ12 /አሥራ ሁለት/ አመት በኋላ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የኑዛዜው አድራጊ ወራሽ ስለሆንኩ ኑዛዜው መብቴን /ጥቅሜን/ ነክቷል ይስተካከልልኝ ሳይሆን ኑዛዜው የተደረገው በተናዛዡ ንብረት ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላ ሰው ሀብት (በተጠሪ አውራሽ ሀብት) ጭምር ነው ኑዛዜው ተፈጻሚነት የለውም በሚል ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ ተገልጾአል፡፡

ኑዛዜን በመቃወም የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ መታየት ያለበት አግባብነት ካላቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ ለጉዳዩ አግባብነት አለው በማለት ከሚጠቅሱት ድንጋጌዎች አንዱ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.973 የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል መቃወሚያ ያላቸው ኑዛዜው ሲነገር /ሲፈስ/ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም ወይም በኑዛዜው የተነገረ ቃል አይፀናም የሚሉትንና የመሳሰሉትን በመቃወም ክስ የሚያቀርቡ ሲሆን ይህን ማድረግ ያለባቸው ኑዛዜው ከተነበበት አንስቶ እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክስ የማቅረብ ሃሣብ መግለጫው በጽሑፍ ካልሆነና ለአጣሪው ወይም ለዳኞች ወይም በውርስ ላይ የተነሣውን ነገር ለመጨረስ ለተመረጡት የሽምግልና ዳኞች እንዲደርስ ካልተደረገ በቀር እንደማይፀና /መቃወሚያ አለ ለማለት እንደማይቻል/ በዚሁ ቁጥር 973/2/ ስር ተደንግጓአል፡፡ በመጨረሻም መግለጫው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ ሦስት ወር ድረስ ክስ ካልቀረበ መብቱ ከነጭራሹ እንደሚቀር በንኡስ ቁጥር /3/ ተመልክቶአል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 974/2/ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜው ከፈሰሰበት /ከተነበበት/ ጊዜ ከአምስት ዓመት በኋላ ስለኑዛዜው መጽናትም ሆነ ስለክፍያው ድልድል መቃወሚያ ማቅረብ አይቻልም፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያሳዩት ስለወራሾች መቃወሚያ አቀራረብና የጊዜ ገደቡ ነው እንጂ ወራሽ ያልሆነ ሰው ስለኑዛዜ የሚቃወምበትን የጊዜ ገደብ አይደለም፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ የኑዛዜ አድራጊ ወራሽ አይደሉም መቃሚያ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 973 በግልጽ የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ እንዳልሆነም ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 973 እና 974 ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡ ሲጠቃለል ተጠሪ የወ/ሮ የሽዋዘርፍ ዓለማየሁ ወራሽ ነኝ ኑዛዜ ሲነበብ /ሲፈስ/ አልነበርኩም ወይም አልሰማሁም በማለት ክስ ባላቀረቡበት ሁኔታ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 973 እና 974 ድንጋጌዎች መሠረት ሁነው ተቃውሞአቸው በይርጋ ቀሪ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ.ቁ 04142 ሕዳር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 06022 ሕዳር 19 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. ተጠሪ በኑዛዜው ላይ ያቀረቡት መቃወሚያ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54258

ህዳር 2 ቀን 2003ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘነበች በቀለ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዮናስ ፀጋዬ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጋብቻ መመስረት አለመመስረትን በተመለከተ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ከአሁኗ አመልካች ጋር ህዳር 03 ቀን 1998ዓ.ም በአገር ባህል መሰረት ጋብቻ ፈጽመው ሲኖሩ ልጅ አለመውለዳቸውን፣ የጋራ ንብረት ግን ያፈሩ ቢሆንም ተጠሪ የጋራ ንብረት እያሸሸች በመሆኑ አብሮ መኖር እንደማይችሉ ገልፀው ፍቺ ተወስኖ የጋራ ንብረት የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠብቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ ጋብቻው የተፈፀመው ተጠሪ በገለፁት ህዳር 3 ቀን 1998ዓ.ም ሳይሆን ታህሳስ 21 ቀን 2001ዓ.ም መሆኑን ገልጸው ያለምንም ማሰላሰያ ጊዜ ፍቺ ቢወሰን ግን ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ጋብቻው የተፈፀመው በተጠሪ በተገለፀው ህዳር 3 ቀን 1998ዓ.ም መሆኑን በመደምደም ጋብቻው እንዲፈርስ ወስኖ የግራ ቀኙን የጋራ ንብረት ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡ አመልካች ጋብቻው ህዳር 3 ቀን 1998ዓ.ም ተፈጸመ ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የውሳኔ ክፍል ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ምክንያት ጊዜውን ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት መጋቢት 20 ቀን 2002ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ03/03/1998ዓ.ም የባህል ጋብቻ መፈፀሙን ያረጋግጣል የተባለው አመልካች ያልተሳተፈችበት ሰነድ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 27 መሠረት የባህል ጋብቻ የተፈፀመ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ መሆን ያለመሆኑ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ



www.chilot.me

ተደርጎላቸው ቀርበው ሐምሌ 08 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሳቸውን የሰጡ ሲሆን አመልካችም መስከረም 10 ቀን2002ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሠረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የባህል ጋብቻ ህዳር 03 ቀን 1998ዓ.ም ስለመፈፀሙ ያረጋግጣል የተባለው ከድሬደዋ 02 ቀበሌ ስለመቅረቡና በ20/04/2001ዓ.ም ተጠሪ ብቻቸውን ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ስለመሰጠቱ የተረጋገጠው ሰነድ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ጋብቻው መፈፀሙን ያሳያል የሚሉት ሰነድ ደግሞ ግራ ቀኙ በተገኙበት በድሬደዋ አስተዳደር ከተማ ስ/አ/ጽ/ቤት በ21/04/2001ዓ.ም መመዝገቡን የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሠረት ለጋብቻ መኖር ቀዳሚና ዋናው ማስረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ሲሆን ይህ ሰነድ ጋብቻው በተፈፀመበት እለት ወይም ከዚያ በኂላ በክብር መዝገብ ሹም የሚሰጥ፣ ስለጋብቻው መፈፀም ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው፡፡ ሕጉ ምዝገባው በክብር መዝገብ ሹም ፊት ለተፈፀሙ ጋብቻዎች ብቻ ሳይሆን በሐይማኖት ወይም በባህል ስርዓት ለተፈፀሙ ጋብቻዎች ሁሉ ተፈፃሚነት እንዳለው ያሳያል፡፡ በመሆኑም በየትኛውም ስርዓት ጋብቻ ቢፈፀም የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የጋብቻ መፈፀሙ ምዝገባ ስርዓት በክብር መዝገብ የሚከናወነው በሕጉ በልዩ ሁኔታ ከተገለጹት ሁኔታዎች ውጪ ተጋቢዎች ባሉበት ጊዜና ቦታ ነው ተብሎም ይታሰባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ አመልካች ጋር ጋብቻ በባህላዊ መንገድ ስለመፈፀማቸው የሚያረጋግጠው እና በሕጉ አግባብ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ የሚያሳየው ጋብቻው ታህሳስ 21 ቀን 2001ዓ.ም መፈፀሙን ነው፡፡ ይህ ሰነድ ጋብቻው ከዚህ በፊት የተፈፀመ /ህዳር 3 ቀን 1998ዓ.ም/ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 30/ሐ/ ድንጋጌ አነጋገር መሠረት ይገልፃል፡፡ እንዲህ ከሆነ ጋብቻው ውጤት አለው የሚባለው ምዝገባ ከተወናወነበት ጊዜ ሳይሆን ከህዳር 03 ቀን 1998ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ይህም በአዋጅ አንቀጽ 28/3/ ድንጋጌ ስር በግልጽ የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካችና ተጠሪ በባህላዊ የፈፀሙት ጋብቻ ስለመኖሩ ታህሳስ 21 ቀን 2001ዓ.ም በተሰጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ በመሆኑ እና ይህንኑ የሚያስተባብል ማስረጃም አመልካች ያላቀረቡ መሆኑን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ ስለተገኘ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1/ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሶ/በ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56184

ሕዳር 02 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ኑን ስንታየሁ ጎዝ - ጠበቃ ሙሉቀን ልመንህ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክርን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩ ሲሆን የካቲት 07 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍቺ ውሳኔ ጋብቻው ፈርሷል፡፡ ከዚህም በሁዋላ አመልካች አይነቱንና መጠኑን በመለየት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲያቀርቡ ተጠሪም የጋራ ሊሆን የማይችለውን ንብረት አይነቱንና ብዛቱን በመለየት ለአመልካች ክስ መልስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ የጋራ ነው የሚሉትን ንብረትም ለይተው እንዲካፈሉ ይወሰን ዘንድ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና ተገቢ ነው ያለውን ሁሉ አጣርቶ ጉዳዩን በመመርመር በእያንዳንዱ ንብረት ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በአመልካች በኩል የጋራ እዳ ተብሎ በተጠቀሰው ገንዘብና አመልካች ከተጠሪ ከተለዩ በኋላ ፍቺው በፍርድ ቤት እስከሚወሰን ድረስ የወሰዱትን ደመወዝ ላይ እንዲሁም አንድ አንድ ንብረቶች ላይ አመልካች የግሌ ናቸው በሚል ካቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ፍቺ ከመፈፀሙ በፊት ያገኙ የነበሩትን ገቢ እኩል ይካፈሉ አመልካች ከመስሪያ ቤታቸው የተበደሩትን የብድር ገንዘብ ተጠሪን አይመለከታቸውም ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሲያፀናው የአመልካች የግል ንብረቶች መሆናቸውን ያረጋገጣቸውን ንብረቶችን ለይቶ ለአመልካች እንዲመለስላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች ፍቺ ከመፈፀሙ በፊት አመልካች ያገኙት የደመወዝ ገቢ ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ አመልካች ከመስሪያ ቤታቸው የተበደሩት እስከ ፍቺው ጊዜ ድረስ አለመከፈሉ የተረጋገጠው የብድር ገንዘብ ግን ተጠሪን አይመለከትም ተብሎ በተወሰነው የውሳኔ ክፍል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር



www.chilot.me

ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ተጠሪ እንዲቀርቡ ተደርጐ ሐምሌ 08 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም መስከረም 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በትዳር ተሳስረው በነበረበት ዘመን ብር 265,827.10 (ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ስምንት መቶ  ሃያ ሰባት ብር ከአስር ሳንቲም) የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ ከአስራ አንድ አመት በፊት አመልካች ከሚሰሩበት ከተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የብድርና ቁጠባ ሕብረት ሥራ ማህበር ላይ በተለያዩ ጊዜአቶችና በተለየዩ የወለድ መጠኖች ወስደው ለቤት መኪና መግዣ ለተጠሪው የግል መኪና የሞተር እድሳትን ጨምሮ ለሌሎች እድሳቶች፣ ለተለያዩ የቤት እቃዎች ማሟያ ለባለ አንድ ፎቅ መኖሪያ ቤት መስሪያና ለሌሎች የቤተሰብ ወጪዎች ማሟያ አገልግሎት እንደአዋሉ እዳው በትዳር ዘመን ከአመልካች ደመወዝ እየተቆረጠ ሲከፈል ቆይቶ የፍቺ ውሳኔ በተሰጠበት የካቲት 07 ቀን 1995 ዓ.ም ብር 147,852.10 (አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር ከአስር ሳንቲም) መቅረቱ በንብረት አጣሪዎቹ ትእዛዝ ከሕብረት ስራ ማህበሩ በቀረበ ማስረጃ መረጋገጡን አመልካች ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ተጠሪ የብድር ገንዘቡን እንደማያውቁት እና በአመልካች ለተጠቀሱት ነገሮች ያልዋለ ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ ያልተረጋገጠ መሆኑንና ቤቱ የተሰራውም ከባንኩ ያጠራቀሙትን ገንዘብ ወጪ አድርገው መሆኑን ገልፈፀሙ  ለእዳው ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ብድሩ በአመልካች ከመስሪያ ቤቻው ስለመወሰዱም ሆነ በትዳር ዘመን ከአመልካች ደመወዝ እየተቆረጠ ሲከፈል ቆይቶ እስከፍቺው ውሳኔ ጊዜ ድረስ ቀሪ ያልተከፈለ እዳ ያለ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነገር ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት እዳው የጋራ ሊባል የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አመልካች ከመስሪያ ቤታቸው የተበደሩትን ገንዘብ በስማቸው ወይም ከተጠሪ ጋር በጋራ በባንክ ስለማስቀመጣቸው አላስረዱም፣ በአቢሲኒያ  ባንክ ገነት ቅርንጫፍ እና ቦሌ ቅርንጫፍ ከሚገኘው ሂሳብ ከመጋቢት 04 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 27 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ 151,651.74 (አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ አንድ ብር ከሰባ አራት) ወጪ መደረጉ መረጋገጡ ቤቱ የተሰራውና ለተለያዩ አገልግሎት የሚውል ብድር ወስደናል በማለት አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እንዲሁም አመልካች በብድር የወሰዱትን ገንዘብ በአቤቱታቸው ለዘረዘሯቸው ነገሮች መግዣ መዋላቸውን አላስረዱም በሚል ምክንያት ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡ በዚህም መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 68(መ) ስር እንደተመለከተው በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከብር አምስት መቶ በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰው ዋስ ለመሆን የተጋቢዎች ስምምነት የግድ ያስፈልጋል፡፡ የስምምነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤትም ሕጉ በአንቀጽ 69 ስር ያስቀመጠ ሲሆን የተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ አንደኛው ተጋቢ በአንቀጽ 68 ስር የመለከተውን ባለማክበር የውል ግዴታ ገብቶ የተገኘ እንደሆነ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው ሊፈርስ እንደሚችል፣ በንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ የይፍረስልኝ ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መግባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ



www.chilot.me

ከስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ብድሩን ከተጠሪ ጋር ፈርመው ወስደዋል ባይባልም ብድሩ ትዳሩ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ከመስሪያ ቤታቸው ተወስዶ ከአስራ አንድ አመታት  በላይ ከአመልካች ደመወዝ እየተቆረጠ ሲከፈል የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ብድሩ ከአመልካች ደመወዝ እየተቆረጠ ሲከፈል የነበረ መሆኑ ሲታይ ደግሞ ተጠሪ ስለብድሩ እውቅና አልነበራቸውም ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ብድሩ ስለመኖሩ ተጠሪ ያወቁ እንደነበር የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ብድሩ ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆን አለመሆኑ ላይ ነው፡፡ ብድሩ በትዳር ወቅት የተወሰደ መሆኑ ከተረጋገጠ የሕግ ግምት ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይኸው የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚገባው ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም አልዋለም ብሎ በሚከራከረው ተጋቢ ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 71 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ቤት ለመስራት ወይም ለቤተሰቡ የተለያዩ ወጪዎች ብድሩ አለመዋሉን የማስረዳት ሸክም ባልተወጡበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች ለቤት መስሪያ በሌላ ባንክ ገንዘብ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ብቻ ተጠሪ ትዳር ከመፍረሱ በፊት  አስራ አንድ አመታት በፊት ከመስሪያ ቤታቸው የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ከወርሃዊ ደመወዝ እየከፈሉ ቆይተው ተጠሪ ምንም ተቃውሞ ባላነሱት ሁኔታ ብድሩ የጋራ ሊሆን አይገባም ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች ፍቺ በፍርድ ቤት ከመወሰኑ በፊትና ከተጠሪ ጋር አብሮ መኖር ትተው በግላቸው ሲኖሩ በነበሩበት ጊዜ ያገኙት ደመወዝ የጋራ ገቢ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተመልክተናል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62(1) መሠረት ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሃብቶቻቸው እንደሚሆኑ የተደነገገ ሲሆን ከግል ጥረት ከሚገኙት ገቢዎች አንዱ ደመወዝ መሆኑ ይታመናል፡፡ ሕግ አውጪው ደመወዝ የተጋቢዎች የጋራ ሀብት ነው በማለት የደነገገው የትዳርን ወጪ ለመሸፈን ሲሆን የትዳር ወጪን ደግሞ ተጋቢዎች እያንዳንዳቸው እንደ የአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ የማድረግ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 72 ስር ከመመልከቱም በላይ በገቢው መፈጠር በቀጥታ ወይም  በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላው ተጋቢም አስተዋጽኦ አለው ተብሎ የሚታሰብ መሆኑ እሙን ነው ለዚህም ምክንያቶች ደመወዝ የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው ተብሎ በሕጉ ከተመለከተ ምላሽ የሚያስፈልገው ጥያቄ  ፍቺው ከመፈፀሙ በፊት ተጋቢዎች ተለያይተው በኖሩበት ወቅት የተገኘ ደመወዝ የጋራ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይገባል ወይ የሚው ነጥብ ነው፡፡ የሕጉ ዓላማ ከላይ የተመለከተው ከሆነ ተጋበዎች ተለያይተው በነበሩበት ጊዜ የተጠሪ ደመወዝ ለቀለቡ ጥያቄ በሕጉ አግባብ ከሚስተናገድ በስተቀር እንደሌላው ሀብት የጋራ ነው ተብሎ የሚወሰድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔም መሠረታዊ የሆነ የሕግ  ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ ከአስራ አንድ አመታት በፊት ጀምሮ ንብረት ማፍሪያና ለትዳር ጥቅም የተወሰደውን ብድር ተጠሪው የጋራ እዳቸው መሆኑ ያውቁ የነበረ በመሆኑ እስከፍቺው ውሳኔ



www.chilot.me

ድረስ አለመከፈሉ የተረጋገጠውን ብር 147,852.10 (አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር ከአስር ሳንቲም) ግማሽ ብር 73,926.05 (ሰባት ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ስድስት ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም) ለአመልካች እንዲተኩ ብለናል፡፡

3. አመልካች ከተጠሪ ተለይተው ከቤት ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ካገኙት ደመወዝ ለተጠሪ ግማሹን የሚከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52569

ሕዳር 13 ቀን 2003 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሙሉወርቅ ዋቼ - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ ፡-** ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ሞገደገኝ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጡረታ ተጠቃሚነት የሚቋረጥበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች የሟች አቶ ጋቲሶ ሚስት ስለነበሩ የጡረታ አበል ተወስኖላቸው ሲቀበሉ ከቆዩ በሁዋላ ሌላ ባል አግብተውም ከሕግ ውጪ አበሉን መቀበሉን መቀጠላቸውን ገልጾ ባል ሲያገቡ መቋረጥ ሲገባው የተቀበሉትን መጠኑ ብር 5478.56 /አምስት ሺህ አራት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም/ የጡረታ አበል እንዲመልሱ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት ክርክርም በሌላ መዝገብ በቀረበ ክርክር ሟች አቶ ጋቲሶ አዲሶ ከሞቱ በሁዋላ ሌላ ባል ያላገቡ መሆኑ መረጋገጡን የሚገልጽ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ያቀረቡት ክርክርም የጡረታ አበሉን እየተቀበሉ ባሉበት ጊዜ ሌላ ባል ያላገቡ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመረ በሁዋላ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መልስ ሠጪን ሳይጠራ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥር 17 ቀን 2002 ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካች ሌላ ባል ያላገቡ መሆኑ በሌላ መዝገብ ተረጋግጦ ውሳኔ አግኝቶ እያለ ይኸው ታልፎና ተጠሪም አመልካች ሌላ ባል ስለማግባታቸው ሳያስረዳ ሌላ ባል አግብተዋል ተብሎ የጡረታ አበሉን እንዲመልሱ የተሰጠው ውሳኔ ያላግባብ



www.chilot.me

ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል; ወይስ አይቻልም; የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሌላ ባል ያገቡ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ይኸውም አመልካች ሌላ ባል ያገቡ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ይኸው ፍሬ ነገር በሕጉ አግባብ ተቀባይነት ባለው ማስረጃ ተረጋግጧል ተብሎ ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ ይኸውም አመልካች ሌላ ባል አግብተው የሚኖሩ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነጥብ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱን ነው፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ የቀረቡትን የተጠሪ ማስረጃዎችን ያላስተባበሉ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልፅ ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን መከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ ያደረገው ቃላቸው አመልካች ባል ማግኘቷን የሚገልፅ ቢሆንም ታአማኒነት የለውም በሚል ነው፡፡ ውሳኔው በግልፅ የሚያሳየው የአመልካች ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገው የግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል ክብደቱ ተመዝኖ መሆኑን ነው፡፡ አንድ ጡረታ አበል የሚቀበል ተጋቢ ሌላ ተጋቢ ማግባት አለማግባቱን በሰው ምስክር ለማረጋገጥ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ ይህ ሁኔታ በሰው ማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል ነው ከተባለ ደግሞ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እንጂ የሕግ አተረጓጎምን የሚመለከት አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ይህ ችሎት ጉዳዩን የሚመለከትበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች ባል ማግባታቸው በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው ከተባለ በአዋጅ ቁጥር 209/1955 አንቀጽ 21 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 35/2/ መሰረት ባል አግብተው እያለ የጡረታ አበል መቀበል ሕጋዊ ባለመሆኑ ገንዘቡን የማይመልሱበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 46726

ታህሣሥ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ነጋሲ አየለ ኢትቻ ጠበቃ ገመቹ ዱሬሣ ቀረበ

**ተጠሪዎች፡-** 1/ ሣሙኤል ዮሐንስ ገ/እግዚአብሔር /ጠበቃ ገ/ሚካኤል

2/ የሕፃን ዮሐንስ ሐጎስ ሞግዚት ወ/ሮ ማንአሰበሽ በየነ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውርስ ሐብት ክፍፍል ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የሟች እናታችን ወ/ሮ ዘነበች በየነ ወራሾች ስለሆንን የውርስ ንብረት ይጣራልን በማለት ነው፡፡ አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከከሣሾች እናት ጋር የጋብቻ ግንኙነት የለኝም፡፡ አብረን በጋራ ያፈራነው ንብረት የለም፡፡ ከሣሾች እኔን በመክሰስ የሚጣራላቸው ንብረት የለም በማለት ስለመከራከሩ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ከሣሾች የሟች እናታቸው ወራሾች እስከሆኑ ድረስ እናታቸው የተጠሪ ሚስት ብትሆንም ባትሆንም የአውራሻቸው ውርስ እንዲጣራ የመጠየቅ መብት አላቸው በማለት የሟች የውርስ ሐብት ይጣራ በማለት ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙ የቀረበው የመጨረሻ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ከተጠሪዎች አውራሽ /ሟች/ ጋር የጋብቻ ግንኙነት የለም የሚለው የአመልካች ክርክር አስቀድሞ ሣይወሰን ውርስ እንዲጣራ የመወሰኑን አግባብነት



www.chilot.me

ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው የክርክሩ መነሻ የሟች ውርስ ይጣራ የሚል ቢሆንም፤ አመልካች ግን ወደውርስ ማጣራቱ ከመገባቱ በፊት በእሱ እና በሟች /የተጠሪዎች እናት/ መካከል ስላለው ግንኙነት በሚመለከት ክርክር አንስቶአል፡፡ ክርክሩም ከሟች ጋር የጋብቻ ግንኙነት የለኝም፤ በጋራ ያፈራነው ንብረት የለም በሚል በግልጽ የቀረበ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሟች ውርስ ይጣራ በሚል ጥያቄ እኔ ተከሣሽ የምሆንበት ምክንያት የለም የሚል ክርክር ከአመልካች ቀርቦአል ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው በሞተ ጊዜ ትቶት የሄደውን ንብረት መካፈል የሚችሉት በሕጉ አግባብ ወራሾቹ እንደመሆናቸው የውርስ ሐብቱን ይዞ በሚገኝ ሰው ላይ ክስ በማቅረብ ሐብቱን ሊያገኙ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ውርስ ከመጣራቱ በፊት መከፋፈል ያልተቻለ በሆነ ጊዜም ወራሾቹ ወይም ከወራሾቹ አንዱ ውርሱ ይጣራ ዘንድ እንዲታዘዝላቸው ለፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ሕጉ ከፍ/ብሔር ህ/ቁ. 942 እና ቀጥለው ካሉት ድንጋጌዎች እንገነዘባለን፡፡ ውርሱ እንዲጣራ ሲጠየቅም ተከሣሽ መሆን ያለበት የውርሱን ሐብት የያዘ ወይም ወራሽ በሆነው ሰው ላይ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ በተጠሪዎች ክስ ይጣራ የተባለው ንብረት የሟች እናታቸው መሆኑ ቢገለጽም የተከሰሰው ግን አመልካች ነው፡፡ ተጠሪዎች አመልካችን በተከሣሽነት ያጣመሩት በእሱ እና በእናታቸው መካከል የጋብቻ ግንኙነት አለ /ነበረ/ በማለት እንደሆነ ከክርክራቸው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር በአመልካች ተክዶአል፡፡ የተጠሪዎችን እናት አላገባሁም አብረንም ያፈራነው ንብረት የለም በማለት እንደተከራከረም ተመልክተናል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በዚህ አይነት የቀረበን ክርክር ለመወሰን የሚያስችለውን የነገር ጭብጥ መሥርቶ ግራ ቀኝ ወገኖችን አላከራከረም፡፡

አመልካች አጥብቆ እንደሚከራከረው በተጠሪዎች እናት እና በእሱ መካከል በሕግ የሚታወቅ ግንኙነት ከሌለ በሟች ውርስ ማጣራት ሂደት እሱ ተከሣሽ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በእሱ እና በተጠሪዎች እናት መካከል በእርግጥም በሕግ የሚታወቅ ግንኙነት መኖሩ እና ንብረትም በጋራ ማፍራታቸው ከተረጋገጠ በቀረበው ክስ መሠረት ውርሱ እንዲጣራ ይደረጋል፡፡ አሁን እያየን ያለው ግን በተጠሪዎች እናት እና በአመልካች መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ ከመረጋገጡ ወይም በዚህ ረገድ የተነሣው ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 247/1/ በተደነገገው መሠረት ተገቢው ጭብጥ ተይዞለት ከመወሰኑ በፊት ወደውርስ ማጣራት እንዲገባ ነው የተበየነው በመሆኑም አካሄዱ የክርክር አመራር ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ክርክሩ በሥርዓት አልተመራም የሚል ይግባኝ ቀርቦለት እያለ ውርሱ እንዲጣራ በማለት የተሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 320/3/ እንደተመለከተው ጊዜአዊ አገለግሎት እንዳለው ትእዛዝ አድርጎ መቁጠሩ ትክክል አይደለም፡፡ ጉዳዩ እኔን በተከሣሽነት አስገብቶ ንብረቴን በውርስ ሐብትነት ተይዞ እንዲጣራ የሚያስደርግ አይደለም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር አለመቀበል ጊዜአዊ አገልግሎት ያለው ትእዛዝ እንደመስጠት የሚቆጠር አይደለም፡፡ ስናጠቃልለው አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 47254 መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 79397 ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ከተጠሪዎች እናት ጋር ግንኙነት የለኝም፡፡ ንብረትም በጋራ አላፈራንም በማለት ያነሣው ክርክር ተጠሪዎች ከሚያቀርቡት የመከራከሪያ ነጥብ ጋር በማገናዘብ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመመሥረት በቅድሚያ በዚህ ጭብጥ ላይ ውሣኔ ይሰጥ በማለት ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 50580

ታህሣሥ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፣** ዶ/ር አለሽኝ መኮንን ጠበቃ ኃይሉ ንጋቱ ጋር ቀረበ

**ተጠሪ፣** ወ/ሮ አስቴር አርአያ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአሁኑ አመልካች ጋር መስከረም 24 ቀን 1980 ዓ.ም በባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ፈፅመው አብረው በመኖር ንብረት ማፍራታቸውን ገልፀው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ሃብት ክፍፍል እንዲወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን በአማራጭም ከአመልካች ጋር ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረው በመኖር የተለያዩ የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ያፈሩ መሆኑን ዘርዝረው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጡት መከላከያ መልስም ከተጠሪ ጋር የመሠረቱት ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንዳባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የሌላቸው መሆኑንና በግልም ሆነ በጋራ ያፈሩት ንብረት አለመኖሩን፣ በህዳር ወር 1986 ዓ.ም ፈታሂ ቴክኒካል ኮርፖሬትድ ኢትዩጵያ ኃ.የተ.የግል ማህበር የተባለ የንግድ ድርጅት በባለአክሲዩንነት ከማቋቋም በስተቀር ሌላ ግንኙነት እንደሌላቸው ተጠሪ እስከ መጋቢት 28 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ አቶ አያሌው ተድላ የተባሉትን ግለሰብ አግብተው ይኖሩ እንደነበርና በተጠሪ በኩል የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎችም ይህንኑ የሚያስረዱና አመልካችም የሚያምኑባቸው መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ የነበረው ግንኙነት ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት መኖር ነው በማለት የደመደመ ሲሆን በዚህ ጊዜ መፈራቱ የተረጋገጠውና በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር በወረዳ 23 ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 1317 የሆነና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት የጋራ በመሆኑ እንዲካፈሉት በማለት የአከፋፈሉን ቅደም ተከተልና ሥርዓቱን ለይቶ ወስኗል፡፡ ሌሎች ንብረቶች ላይ የቀረበውን የተጠሪ ጥያቄ በማስረጃ አልተደገፈም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ



www.chilot.me

ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሕዳር 01 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ከአመልካች ጋር ጋብቻ እያላቸው ገልፀው ክስ ከመሠረቱ በኋላ ከስነ ሥርዓቱ መንፈስ ውጪ በአማራጭ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩን ጠቅሰው ዳኝነት መጠየቃቸው ያላግባብ መሆኑን በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነትም ተጠሪ ባላቸው የሕግ ሙያ የደምበኝነት እንጂ የባልና ሚስት አለመሆኑን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የቆጠሯቸው ምስክሮች ሕጋዊ ግንኙነት ስለመኖሩ ያላስረዱ መሆኑን ተጠሪ እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ ከሚች አቶ አያሌው ተድላ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ መስርተው ይኖሩ የነበረና ሚስትነታቸውም በፍርድ ቤት መረጋገጡን ገልፀው ከተጠሪ ጋራ የነበራቸው ግንኙነት ጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር እንዳልሆነ ምንም አይነት ንብረት ያላፈሩ መሆኑን ገልፆ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለ የመባሉን አግባብነትና አለ እንኳ ቢባል ከመቼ ጀምሮ የሚለው ጥያቄን አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ዳኝነት ማስረጃን ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የግራቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክስ የመሠረቱት ከአመልካች ጋር በባህላዊ ሥርዓት ብቻ ፈፅመው ይኖሩ የነበረ መሆኑና በግንኙነቱም ወቅት ንብረት ማፍራታቸውን ገልፀው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ እንዲወሰንላቸው ወይም ከአመልካች ጋር ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የነበራቸውንና ንብረት ያፈሩ መሆኑን ጠቅሰው የንብረት ክፍፍል ውሣኔ እንዲሰጥ ዳኝነት ጠይቀው ለማስረጃነትም የተለያዩ የሰነድና የሰው ምስክሮችን የዘረዘሩና የተሰሙላቸው መሆኑን አመልካች በበኩላቸው ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት የባለአክሲዩንነትና የጥብቅና አገልግሎት ውክልና ውል ከመሆኑ ውጪ ጋብቻ ወይም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለመሆኑን ጠቅሰው ይልቁንም አመልካች ከሚች አቶ አያሌው ተድላ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ የነበራቸው መሆኑ የሚታወቅ መሆኑን ገልጸው መከራከራቸውን ለማስረጃነትም የተለያዩ በተጠሪ የተቆጠሩ ሰነዶችና የሰው ምስክሮችን የቆጠሩና የተሰሙላቸው መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ክስ ሲመሠርቱ ሁለት የተለያዩ የግንኙነት አይነቶች ከአመልካች ጋር የነበራቸው መሆኑን እየገለጹ ይህንንም ክስ ላሻሽል በሚል ምክንያት ከአንዴም ሶስት ጊዜ የጠቀሱ መሆኑንም ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ የተመለከትን ሲሆን ተጠሪ ለማስረጃነት ከቆጠሯቸው እና አመልካችም ለመከላከያነት ይጥቀሙኛል ብለው ከጠቀሷቸው የሰነድ ማስረጃዎች መካከል ተጠሪ ከአቶ አያሌው ተድላ ጋር ሐምሌ 12 ቀን 1960 ዓ.ም ጋብቻ ፈፅመው ሲኖሩ አቶ አያሌው ተድላ ከዚህ አለም መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም በሞት መለየታቸውን በግንኙነቱ ወቅትም ልጆችን የወለዱ መሆኑን ገልፀው የሚች ሚስትነታቸው ልጆቹ ደግሞ የሚች የመጀመሪያ ደረጃ



www.chilot.me

ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አጣርቶ ተጠሪ ከሐምሌ 12 ቀን 1960 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ የሟች አቶ አያሌው ተድላ ሕጋዊ ሚስት የነበሩ መሆናቸውን ገልፆ ሚስትነታቸውን የልጆችን የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነታቸውን አረጋግጦ ማስረጃ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት ባሰሙት የቃል ክርክር ይኸው ማስረጃ በራሳቸው ጥያቄ የተሰጠ መሆኑን ሳይክዱ ማስረጃውን የጠየቁበት ዓላማ የልጆችን ወራሽነት በማረጋገጥ የሟችን ንብረት ለልጆች ጥቅም ለማስከበር አስበው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንግዲህ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ከላይ የተመለከቱት ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አዛምደን በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ከአመልካች ጋር ተጠሪ የነበራቸው ግንኙነት እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰ ሲሆን ይህ ችሎትም እንዲመለከተው የተያዘው አንዱ ጭብጥ ይኸው ግንኙነት አለ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆኑን አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ሁለት የተለያዩ ግንኙነቶችን በመጥቀስ የቀረበ መሆኑ በራሱ ከክስ አመሠራረት መርህ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ሥነ ስርዓታዊ መሆን ያለመሆኑ ጥያቄ የሚያስነሳ ቢሆንም ይህንኑ ከመመልከት በማለፍ በስር ፍርድ ቤት አለ የተባለው ግንኙነት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ያገናዘበ መሆኑን ያለመሆኑን መመልከቱ የተሻለ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሠረቱ ጋብቻ ስለመፈፀሙ በቀዳሚነት ሊቀርብ የሚገባው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94 ድንጋጌ ሲያስቀምጥ ጋብቻ ስለመኖሩ ይኸው ማስረጃ ከሌለ የጋብቻ ግንኙነት ስለመኖሩ በትዳር ሁኔታ ማረጋገጥ ስለመቻሉም የተጠቀሰው ሕግ በአንቀጽ 95 ደንግጓል፡፡ ይህ የጋብቻ መኖር አለመኖርን በተመለከተ ሊቀርብ የሚገባው የማስረጃ አይነትና ቅደም ተከተሉ ነው፡፡ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ግን ጉዳዩን ለማስረዳት የሚቀርበውን ቀዳሚ የማስረጃ አይነት በሕጉ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃ የፍሬ ነገር ጉዳይ በመሆኑ ግንኙነቱን በማሳየት ብቻ ማስረዳት ይቻላል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 106/2/ ድንጋጌ ሲታይም ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ለሚኖሩ ሰዎች የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትዩዋ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆኑን ማሳየት እንደአለበት ያመለክታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ራሳቸው ለፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 92 መሠረት እውነትነቱን አረጋግጠው ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ከሟች አቶ አያሌው ተድላ ጋር ከሐምሌ 12 ቀን 1960 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስረው ጋብቻው በሞት እስከ ፈረሰበት እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ይኖሩ የነበሩ መሆኑ የተጠቀሰ ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ የቀረበውን አቤቱታ አረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጥ የተጠየቀው ፍርድ ቤትም ይህንኑ አረጋግጦ ተጠሪ እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ የሟች አቶ አያሌው ተድላ ሚስት የነበሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መስጠቱን የሚያሳይ ውሣኔ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ይህ የፍርድ ቤት ውሣኔ የማስረጃ ዋጋ ሳይሰጠው የሚታለፍበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያሰሟቸው በርካታ ምስክሮችም ቢሆኑ እንደተጠሪ የክስ አመሰራረት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ በባህላዊ ሥርዓት የፈጸሙ መሆኑን እናውቃለን በማለት ጊዜውን ቦታውንና የአፈፃፀሙን ሥርዓት አልመሰከሩም፡፡ በምስክሮቹ ቃል የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ በጥቅሉ ሲታይ ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደባልና ሚስት የሚገምቷቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ



www.chilot.me

ከሟች ጋር ጋብቻ ፈጽመው ይኖሩ የነበረ መሆኑን ራሳቸው እያረጋገጡና ምስክሮቻቸውም ከአመልካች ጋር እንደባልና ሚስት ይኖሩ የነበሩ ስለመሆኑ ሳያረጋግጡ በፍርድ ቤት የሚስትነት ማስረጃ ጥያቄ ያቀረብኩት ከሟች ለተወለዱት ልጆች የውርስ ጥያቄ መብት ለማስከበርና ለንብረት አስተዳደር ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ምክንያት ሆኖ አግኝተናል፡፡ አንዲት ሴት ከአንድ ወንድ ጋር በሕግ አግባብ ጥበቃ የሚደረግለትን ጋብቻ በመሰረተችበት ጊዜ ከሌላ ወንድ ጋር እንዳባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አላት ተብሎ ይኸው ግንኙነት በሕግ ጥበቃ የሚደረግበት በቂና ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከ1980 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1987 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ከአመልካች ጋር ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ ሲኖሩ ነበር በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ጋብቻ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ተቋም መሆኑንና ከጋብቻ ውጪ እንዳባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በሕጉ ጠበቃ የሚደረግለትን ሁኔታ ባግባቡ ያላገናዘበ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 25 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ መስርቼ ነበርኩ የሚሉት ግንኙነት በሕጉ አግባብ ጥበቃ የማይደረግለት መሆኑን ከላይ በተመለከተው ምክንያት ድምዳሜ ከያዝን ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ የነበረው ግንኙነትን አይነቱንና ውጤቱን መመልከቱ የግድ ይሆናል፡፡ አመልካች በዚህ ጊዜ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ሲታይ ተጠሪ ከሟች አቶ አያሌው ተድላ ጋር የመሠረቱት ጋብቻ በሞት የፈረሰበት ወቅት ነው፡፡ አመልካች በተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችም ተጠሪን በሚስትነት የሞሉ መሆኑ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን በአመልካች ስም በተከፈቱ መዝግቦች ላይ ተረጋግጧል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች በስር ፍርድ ቤቶች ታይተው ሊሰጣቸው የሚገባው ክብደት ተሰጥቷቸው አመልካች ሊያስተባብሉ አለመቻላቸው ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ያለው የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ነው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የተደመደመው የውሣኔ ክፍል የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የነበረው ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም በኃላ እስከ 1996 ዓ.ም ነው ብለናል፡፡

ውጤቱን በተመለከተ ተጠሪ ከአመልካች ጋር አፍርተናል የሚሉት መኖሪያ ቤት የተፈራው ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም በፊት ቦታው በ1975 ዓ.ም በአመልካች ተገኝቶ የቤቱ ግንባታ ፈቃድም በ1979 የተሰጠ መሆኑ እንዲሁም ቤቱ የተሰራው በ1980-1984 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ መኖሪያ ቤቱን ከአመልካች ጋር የሚካፈሉበት ምክንያት የለም፡፡ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በንብረት ላይ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው እንደባልና ሚስት አብሮ የሚኖሩት ሰዎች ከሶስት አመታት ላለነሰና ከዚያ በላይ አብሮ ሲኖሩና ንብረቱ በዚህ ጊዜ የተፈራ መሆኑ መረጋገጡ ሲታወቅ መሆኑን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 102 ያሳያል፡፡ በመሆኑም በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር በወረዳ 23 ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 1317 የሆነው በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ በኖሩበት ጊዜ ውስጥ ሳይሆን ቀድሞ የተፈራ በመሆኑ ተጠሪ ሊካፈሉ የሚገባበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

# ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 37094 የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁጥር 78790 ጥቅምት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አልነበረም ብለናል፡፡
3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የነበረው ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም በኃላ ሆኖ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ነው ብለናል፡፡
4. በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር በወረዳ 23 ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 1317 የሆነና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ሊካፈሉ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54385

ጥር 27 ቀን 2003

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ፍቃዱ ሽፈራው - ቀረቡ

**መልስ ሰጪ፡-** አቶ ግሩም ኤርሚያስ - ጠበቃ ወርቅነህ በረደድ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ስለውርስ ንብረት ክፍፍል የተደነገጉትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አተረጓጎምን የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ነገር ሟች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየሱስ ሚያዚያ 08 ቀን 1998 ዓ.ም የተውት ኑዛዜ ነው፡፡ አመልካች የሚቿ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ፣ተጠሪ ደግሞ የሚቿ የልጅ ልጅና የኑዛዜም ወራሽ መሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ሟች የተውት ኑዛዜ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሟች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየሱስ የተውት ኑዛዜ የሕጉን ፎርማሊቲ ያልጠበቀና ከውርስ የነቀለኝ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል፣ ተጠሪ የሚቿ የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 360 መሠረት ሊሰረዝ የሚገባው ነው በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ኑዛዜው በሕጉ የሚፈለገውን ፎርማሊቲ ያሟላ ከመሆኑም በላይ ሟች ለአመልካች ብር 100.00 /አንድ መቶ / እንዲሰጣቸው በኑዛዜው ላይ የተገለፀ በመሆኑ አመልካችን ከውርስ ነቅሏል ሊያስብል የሚችል አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ኑዛዜው ፎርማሊቲውን ያሟላ ነው፣ አመልካች ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ እንዲሰጣቸው ሟች የተናዘዙ መሆናቸው ደግሞ ከውርስ ነቅለዋል ለማለት የሚያስችል አይደለም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ተጠሪ የሟች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው በማለት የሰጠውን ውሣኔ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ሲሆን የአቤቱታው መሠረታዊ ነጥብም ሟች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየሱስ የተውት ኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የሆኑት አመልካች ከውርስ የነቀለና የጎዳ በመሆኑ ሊፈርስ የሚገባው ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም የሰበር አቤቱታውን



www.chilot.me

በመመርመር አመልካች በኑዛዜው ላይ ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ ብቻ ያገኛል ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ድንጋጌ አንፃር ተገቢነቱ ሊታይ የሚገባ መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ከአዘዘ በሁዋላ ለተጠሪ ጥሪ አድርጎላቸው ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከውርስ ሕጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ወ/ሮ በላየነሽ ገ/እየሱስ ሚያዚያ 08 ቀን 1998 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በፎርማሊቲ በኩል ፈራሽ ሊያደርገው የሚገባ ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ እና አመልካችም በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊ አይደለም በማለት ያቀረቡት የሰበር ክርክር የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ ኑዛዜው የሕጉን ፎርማሊቲ ያሟላ ነው ከተባለና በኑዛዜ አንድ ወራሽ አለአግባብ ተነቀለ የሚባል ቢሆን በውርሱ አከፋፈል ላይ የሚታይ እንጂ በአግባቡ የተሰጠን ኑዛዜ ፈራሽነት የሚያስከትል የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ የኑዛዜ ስጦታው የፀና መሆን በውርስ ክፍፍሉ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይህን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ተያያዥነት ያላቸውን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መመለከት ያስፈልጋል፡፡ አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 913 ሲሆን ይህ ድንጋጌ የኑዛዜው ቃል የተናዛዡን ተቃራኒ ሐሣብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር ከውርስ ሃብት አንድ ድርሻን ወይም አንድ ንብረትን ሟቹ ለወራሾች መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ ደንብ እንጂ እንደ ኑዛዜ ስጦታ ነው ተብሎ አይቆጠርም በማለት ያስቀምጣል፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ ሟች አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኘውንና ብቸኛ ንብረት የሆነውን ቤታቸውን በኑዛዜው ይሰጥልኝ ያሉት የእህት የልጅ ልጅ ለሆነው ለአሁኑ ተጠሪ ሲሆን ልጅ ለሆነው የአሁኑ አመልካች ደግሞ በተጠሪ ብር 100.00/ አንድ መቶ/ ብቻ እንዲሰጣቸው ነው፡፡ ተጠሪ የሟች እህት ልጅ ልጅ በመሆናቸው ክርክሩ የሚያረጋግጥ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ስር የተመለከተው ድንጋጌ መሠረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1117 በመሆኑ በዚህ አግባብ የሚታይ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም አሁን የቀረበው ክርክር በተወላጆች መካከል አይደለምና፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በዚህ ረገድ የተያዘውን ጭብጥ አልፈነዋል፡፡ በጭብጥነት ተይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካችን ሟች ከውርስ ነቅለዋል ሊባል ይቻላል? ወይስ አይቻልም?፣ ነቅለዋል ከተባለስ ተግባሩ በሕግ ፊት ተቀባይነት አለው? ወይንስ የለውም? የሚሉት ነጥቦች ሁነው አግኝተናል፡፡

ከቀረበልን ጉዳይ ለመገንዘብ እንደቻልነው ሟቿ ኑዛዜአቸው ላይ ያሏቸውን ንብረቶች በሙሉ የሰጡት ለተጠሪ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ክፍፍል ሕጉ የሚደግፈው ቢሆንም አንድ ወላጅ ተወላጅን ከውርሱ ያለሕጋዊ ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሲነቅል ግን ተቀባይነት ሊኖረው የማይችል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 937፣938 እናና 939 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ /ነጥብ/ ነው፡፡ ሟች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየስ ልጃቸው የሆኑትን አመልካችን ካላቸው ንብረታቸው ብር 100.00 /አንድ መቶ/ ብቻ እንዲሰጣቸው በኑዛዜው ላይ ገልፀዋል፡፡ ሟች ተጠሪ እንዲወስዱ የተናዘዙት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሣቀስ ንብረት ነው፡፡ ከዚሁ ንብረት አይነትና ካለው ዋጋ አንፃር ሲታይ ሟች በኑዛዜው ላይ ለአመልካች ብር 100.00



www.chilot.me

ብቻ እንዲሰጣቸው መጥቀሣቸው ከውርሱ በተዘዋዋሪ ነቅለዋቸዋል ከሚባል በስተቀር ሌላ ምክንያት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ሟች አመልካችን በተዘዋዋሪ ነቅለዋል ከተባለ ደግሞ የነቀሉበት ምክንያት በቂና ሕጋዊ መሆን ሊታይ የሚገባው ሲሆን ሟች በዚህ ረገድ በኑዛዜው ላይ ያስቀመጡት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በተዘዋዋሪ መልኩ በዝምታ ከሟቿ ውርስ የነቀሉ መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ወላጅ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ወይም በዝምታ ከነቀለም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሁነው የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ወደዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በወላጅ የተደረገ የኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አለበት፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912 ስር እንደተመለከተው የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ሲባልም ተናዛዡ ሀብቱን ጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በሙሉ ሀበትነት ወይም በሌጣ ርስትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912/1/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ማንኛውም ሌላ የኑዛዜ ቃል ሁሉ እንደ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡ አንድ ኑዛዜ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014 ድንጋጌ ቅደም ተከተል መሠረት የሚከፈል ይሆናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየስ የነበራቸውን አንድ መኖሪያ ቤት ለአሁኑ ተጠሪ እንዲሆን በኑዛዜ ስጦታ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ሌሎች ንብረቶች ያላቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት አያሣይም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር ተናዛዧ ያደረጉት ኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ሲታይ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ እንጂ ልዩ የሆነ የኑዛዜ ስጦታ አይነት አይደለም ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014/ሠ/ ስር በተመለከተው መሠረት እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ ለልዩ ኑዛዜ ተቀባዩ የሚከፈል ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ድንጋጌዎች ታይቶ ተወላጅ ከውርስ ተነቅሏል፣ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊካፈል ይገባል ሊባል የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየስ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካችን በተዘዋዋሪ መንገድ ከውርስ የነቀለ መሆኑን በመለየት የኑዛዜ ስጦታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912፣ 915፣937፣938 እና 939 አንፃር በማየት መወሰን ሲገባቸው የአመልካችን ጥያቄ ሙሉ ሙሉ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51/2001 መጋቢት 09 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09721 መጋቢት 23 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ፡ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 10029 ጥር 28 ቀን 2002 ዓ.ም በውሣኔ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአጠቃላይ ፍርስ ባይሆንም ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተጠቀሰው መሠረት አመልካችና ተጠሪ የሟችን ንብረት እኩል የመውረስ መብት አላቸው ብለናል፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት ውሣኔው መሻሻሉን እንዲያውቀው የውሣኔው ኮፒ ይላክለት፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

**ዳኞች፣** ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፣** 1. ወ/ሮ ጸሐይ ተሰማ
2. ወ/ሮ አለምነሽ ተሰማ } ጠበቃ ታደሠ ወ/ጊዮርጊስ ቀረበ

**ተጠሪ፣** ህፃን አማኑኤል ወንድወሰን ሞግዚት ወ/ሮ ብርሃኔ ባየህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋብቻ ውል አንዱ ተጋቢ ለሌላው ተጋቢ የማይንቀሳቀስ ንብረት አጠቃቀምን የሚመለከት መብት በሕይወት ለሚቀረው ተጋቢ እስከ እለተሞት ድረስ እንዲጠቀምበት በማለትና በሕግ አግባብ ተወላጅ ያልሆነውን ሰው የድርሻ ንብረቱ ተጠቃሚ በማድረግ ውል ገብቶ ሲገኝ ስለሚኖረው ውጤት የሚመለከተውን ክርክር መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ሞግዚት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አቶ ታፈሰ ተፈራ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን የአቶ ታፈሰ ተፈራ ልጅና የህፃን አማኑኤል እናት የሆኑት ወ/ሮ ትዕግስት ታፈሰም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን ህፃኑ የወላጅ እናቱ ወራሽ መሆኑና ሞግዚትም የተሾመለት መሆኑን ህፃኑ ወላጅ እናቱን በመተካት አያቱን መውረስ እንደሚገባው አቶ ታፈሰ ተፈራ በሕይወት እያሉም በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ውስጥ ቁጥሩ 1011 የሆነና በስማቸው የተመዘገበ መኖሪያ ቤት ያፈሩ መሆኑን ይህን ቤት የአሁኑ አመልካቾች ይዘው በማከራየት እየተጠቀሙ እንደሚገኙና ለማካፈልም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልፀው የቤቱን ግምት ግማሽ 50,000.00 /ሃምሳ ሺህ ብር/ እንዲያካፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስም አከራካሪው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ መሆኑን ሳይክዱ ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ እና 1ኛ አመልካች የጋብቻ ውላቸውን ሲያድሱ ቤቱን 1ኛ አመልካች በሕይወት እስካሉ ድረስ እንዲጠቀሙና ከሣሽ ሞግዚት አድራጊ እናትና 2ኛ አመልካች ከ1ኛ አመልካች ሕይወት ፍጻሜ በኂላ የሟች ድርሻን እንዲተላለፍላቸው መስማማታቸውን ይህንኑ በመገንዘብና የጋብቻ ውሉን በማክበርም የሕጻኑ እናት በሕይወት እያሉ ጥያቄ ሳያቀርቡ የቆዩ መሆኑን 2ኛ አመልካችም በቤቱ ውስጥ ያሉት በቤተሰብነት መሆኑንና ቤቱ የሚከራየውም በብር 550.00 ሳይሆን በብር 350 መሆኑን በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ



www.chilot.me

የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር በመመርመር የጋብቻ ውሉ በሶስተኛ ወገን ላይ ግዴታ ሊጥል የሚችል ሊሆን አይገባም በሚል ምክንያት የ1ኛ አመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገ ሲሆን 2ኛ አመልካችን በተመለከተ ደግሞ ልጅ ስላልሆኑ ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራን ሊወርሱ አይገባም፣ ተጠሪ ሟችን እናታቸውን ተክተው መውረስ የሚችሉ ናቸው በማለት አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ግማሹ የተጠሪ በመሆኑ ከተቻለ በአይነት ለሁለት ተከፍሎ ግማሹ ለተጠሪ ግማሹ ደግሞ ለ1ኛ አመልካች ይሰጠው ካልተቻለ ግን ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ የሽያጭ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 46ን የተረጎመው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826/2/ ጋር አዛምዶ ባለመመልከት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ቀርበው የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ ሕጋዊነት በመግለፅ ሊፀና ይገባል ሲሉ ሕዳር 08 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች ታህሣሥ 08 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤተታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ 1ኛ አመልካች ከሟች ታፈሰ ተፈራ ጋር በጋብቻ ተሳስረው ሲኖሩ አከራካሪ የሆነውን ቤት በጋራ ያፈሩ መሆኑን ሟች አቶ ተፈራ ታፈሰ በህይወት በነበሩበት ጊዜ ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም ከ1ኛ አመልካች ጋር ባደረጉት "የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት" በሚል ሰነድ 1ኛ አመልካች ዋናውን ሶስት ክፍል ቤትም ሆነ ሰርቪሶቹን ከአቶ ታፈሰ ተፈራ ሞት በሁዋላ እድሜዋ እስከፈቀደላት ድረስ የግልዋ ሆኖ ለመሸጥም ሆነ ለመለወጥ ከፈለገች ግን የአሁኑ ተጠሪ እናት የሆኑት ሟች ትዕግስት ታፈሰና የአሁኗ 2ኛ አመልካችን በመያዝ መለወጥም ሆነ መሸጥ ትችላለች ልጆቹም እናታቸው እስካሉ ድረስ ንብረቱን በሙሉ የእናታቸው የግልዋ መሆኑን አውቀው መቀመጥ አለባቸው በማለት መግለፃቸውን ነው ይህ ሰነድ ስለመኖሩም የተካደ ነገር አይደለም ተጠሪም ሟች አያቱን በተተኪነት መውረስ የሚችል ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የሰነዱን መኖርና በሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ መደረጉን በመቀበል ሕጋዊ ውጤት የለውም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 46/1/ን በዋቢነት በመጥቀስ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታ ሊጥል አይችልም በሚል ምክንያት ስለመሆኑም ከውሣኔው ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ ይህንኑ ግንዛቤ በመውሰድም የሰነዱን ይዘት ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ሊኖረው የሚገባውን ውጤት መርምረናል፡፡



www.chilot.me

የጋብቻ ውል ሕጋዊ ድርጊትና ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል መሆኑን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 40 እና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባሉ የጋብቻ ውል ከሚያስከትላቸው ሕጋዊ ውጤቶች መካከል አንዱ በተጋቢዎች የንብረት ግንኙነት ላይ ስለመሆኑ የተጠቀሰው አዋጅ በአንቀጽ 42/1/ ድንጋጌ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ በጋብቻ ውል የተቋቋሙ አንዳንድ ውጤቶችም በውል ሊቀሩ ወይም ሊሻሻሉ እንደሚችሉ ተጠቃሹ ሕግ በአንቀጽ 40 ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን ይህ ተግባር በሕግ ፊት ውጤት የሚኖረው በአንቀጽ 73 አግባብ ሲደረግ ነው እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 46/1/ ድንጋጌ ሲታይም ተጋቢዎች በጋብቻቸው ውል ውስጥ በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ አይችሉም በሚል ተቀምጧል የስር ፍ/ቤት የጋብቻ ውል አፈፃፀሙንና ውጤቱን በተመለከተ ሊኖረው ስለሚገባ ሥርዓት ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ከተገነዘበው በሁዋላ በአሁኗ 1ኛ አመልካችና በሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ መካከል ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም የተደረገ የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት ውጤት ሊኖረው አይገባም በማለት ውድቅ ያደረገው በሶስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታ በሚያስከትል መልኩ ስምምነቱ ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሶስተኛ ወገን የተባለው በጉዳዩ ላይ ክርክር ያቀረበው የአሁኑ ተጠሪ የሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ተተኪ ወራሽ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826/2/ መሠረት ተተኪ ወራሽ ሊተላለፍለት የሚችለው አውራሽ የነበረው ግዴታና መብት ሆኖ አውራሽ በመሞቱ ምክንያት ሊቋረጡ የማይችሉ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ወራሽ ሊሰራበት የሚችለው መብትና ግዴታ አውራሽ በሚኖረው መብትና ግዴታ መጠን ነው ይህም የሚያሳየው ወራሽ አውራሹ በሚያደርጋቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ውስጥ አውራሹን ተክቶ የሚሰራ ከአውራሹ ጋር ተመሳሳይ አቋም ያለው መሆኑን እንጂ አውራሹ ለፈጸማቸው ድርጊቶች ሶስተኛ ወገን ሊባል የሚገባ አለመሆኑን ነው በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 46/1/ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826/2/ እና 842 ጋር በማዛመድ ሳይመለከተው ተጠሪን እንደሶስተኛ ወገን መቁጠሩ ያላግባብ ሆኖ ተገኝቷል ይህ ሰነዱ የጋብቻ ውል አይደለም እንጂ ነው እንኳ ቢባል ሊደርስበት የሚችለው ድምዳሜ ነበር፡፡

ከሁሉም በላይ በሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ እና በአሁኗ 1ኛ አመልካች መካከል ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም የተደረገው "የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት" የሚል ርዕስ የተሰጠው ሰነድ ይዘቱ መታየት ያለበት እና የውሉ አይነት ተለይቶ በየትኛው የሕግ ክፍል መገዛት አለበት? የሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የጋብቻ ውል ሕጋዊ ድርጊትና ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል ሲሆን ውጤቱ በተጋቢዎች የግል ወይም የንብረት ግንኙነት ላይ መሆኑን በዚህ ረገድ የተደነገጉት የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የጋብቻ ውል ውጤት የሚኖረውም ተጋቢዎች በጋብቻ ላይ ፀንተው ባሉበትና ጋብቻም ከፈረሰ በኋላ ሊሆን እንደሚችል በስምምነቱ ሊወሰን የሚችል መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ግን ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ጋር የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት የሚል ሰነድ ያደረጉት የጋራቸውን የሆነውን ቤት ከራሳቸው ሕልፈተ ሕይወት በኃላ 1ኛ አመልካች በግላቸው እንዲጠቀሙበት ነው፡፡ በስምምነቱ መሠረት 1ኛ አመልካች ላይ ወይም በሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ላይ ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ስለቤቱ አጠቃቀም 1ኛ አመልካች ያገኙት ልዩ መብት የለም በሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ላይም የተጣለ ገደብ የለም፡፡ አቶ ታፈሰ ተፈራ በቤቱ ካላቸው ሰፊው የባለቤትነት መብት ለ1ኛ አመልካች ከራሳቸው ፍፃሜ ሕይወት በኃላ የሰጡት የመጠቀም መብታቸውን ብቻ ነው፡፡ በስምምነት ሰነዱ ላይ 1ኛ አመልካች ቤቱን ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ከፈለጉ የአሁኗን 2ኛ አመልካችንና የህፃን አማኑኤል ወንድወሰን እናት



www.chilot.me

የሆኑትን ሟች ትዕግስት ታፈሰን በመያዝ ስለመሆኑ መጠቀሱ 1ኛ አመልካች የተሰጣቸው በቤቱ የመጠቀም መብት ብቻ ስለመሆኑ አስረጂ ነው በመሆኑም የስምምቱ ይዘት ሲታይ በሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ላይ በሕይወት እያሉ የሚጥለው ግዴታ የሌለ መሆኑና 1ኛ አመልካችም በቤቱ ላይ የመጠቀም መብታቸው የሚኖረው አቶ ታፈሰ ተፈራ ከሞቱ በኃላ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲህ ከሆነ ስምምነቱን የሚገዛው የትኛው የህግ ክፍል ነው? የሚለው ጥያቄ ተያይዞ የሚነሳ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2427 ድንጋጌ ሲታይ ስጦታ ማለት አንድ ወገን ተዋዋይ ማለትም ሰጪው ተቀባይ ተብሎ ለሚጠራው ለሌላ ሰው ችሮታ በማድረግ አሳብ ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት ወይም ግዴታ የሚገባበት ውል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ስጦታ ደግሞ ሰጪው ሲሞት ይፈፀማል ተብሎ ሊደረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል ይህንኑ መሠረት አድርገን ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ እና 1ኛ አመልካች ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም ያደረጉትን ስምምነት ይዘት ስንመለከተው በሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ላይ በሕይወት እያሉ ምንም ግዴታ የማይጥል ከሕልፈተ ሕይወታቸው በኃላም ቢሆን 1ኛ አመልካች ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ካላቸው ንብረቱን የማውደም የመጠቀምና የማስተላለፍ ሰፊ የባለቤትነት መብታቸው ውስጥ ቤቱን የመጠቀም መብታቸውን ብቻ ተግባራዊ ሲያደርጉ በ1ኛ አመልካች ላይ ግዴታ የማይጥል ችሮታ ላይ የተመሠረተ እንዲሁም 1ኛ አመልካች የሟች አቶ ታፈሰ ተፈራን ድርሻ የመጠቀም መብት ተግባራዊ የሚያደርጉት ከአቶ ታፈሰ ተፈራ ሕልፈተ ሕይወት በኃላ መሆኑ የተጠቀሰበት በመሆኑ ሰነዱ የስጦታ ሰነድ ሊባል የሚገባ እና ስለስጦታ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የሚገዛ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የሰነዱን ይዘት በአግባቡ ሳያገናዝብ የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት በሚል በአርእስትነት በመቀመጡ ብቻ ሰነዱ የጋብቻ ውል ነው ወደሚለው ድምዳሜ መደረሱም ተገቢ ሆኖ አለገኘነውም፡፡ እንግዲህ ስምምነቱ ሲታይ የስጦታ ውል ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደረሰን ሲሆን ውሉ የሚኖረው ውጤት በዚህ ረገድ የተደገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መልስ የሚያገኝ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ሰጪው ሲሞት ይፈፀማሉ ተብለው በተወሰኑት ስጦታዎች ላይ ስለኑዛዜ የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚዎች እንደሚሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 ስር በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በመሠረቱ ኑዛዜ የሟቹ ጥብቅ የሆነ ራሱ የሚፈፅመው ስራ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 857/1/ ስር የተመለከተ ሲሆን ኑዛዜው የሚሻርበትንና በሕግ ፊት ውድቅ የሚሆንበትን ምክንያት ሕግ አውጪው አስቀምጧል፡፡ ኑዛዜ ሰጪ ኑዛዜ ሊያደርግ የሚችልበት ሥርዓትም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881፣ 882 እና 884 ስር ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜ አድራጊ በሕጉ በተመለከቱት መንገዶች መሠረት ንብረቱን ለስጋ ዘመዱ ወይም የስጋ ዘመድ ላልሆነው ሊያስተላልፍ የሚችልበት አግባብም በሕጉ ጥበቃ የተደረገለት ተግባር ነው፡፡ ከዚህም በላይ ኑዛዜ ገደብ ያለበት ሆኖ ሊደረግ እንደሚችልም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 916 ስር ተመልክቷል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ እና 1ኛ አመልካች ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 መሠረት በኑዛዜ ድንጋጌዎች የሚገዛ ሆኖ በአፃፃፍ ሥርዓቱም ሆነ በውጤቱ ሕጋዊ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም 1ኛ አመልካች እስከ እለተሞታቸው ድረስ ቤቱን የመጠቀም መብታቸው የሚያጡበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ 2ኛ አመልካች ደግሞ ከሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ የማትወለድ ቢሆንም ሟች ከድርሻቸው እንዲሰጣት ሕጋዊ ስጦታ እስካአደረጉላት ድረስ ከተጠሪ ጋር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 እና 915 ድንጋጌዎች መሠረት እንደአንድ ወራሽ ተቆጥረው እኩል ተጠቃሚ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረት የ1ኛ አመልካችን የመጠቀም መብት የ2ኛ አመልካችን ደግሞ በስጦታ የተሰጣቸውን የሟች ድርሻ ግማሽ የማግኘት መብታቸውን ማሣጣቱ የስምምነት ሰነዱን ይዘት



www.chilot.me

ከሕጉ ጋር ባላገናዘበና ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

***<u>ው ሣ ኔ</u>***

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 63108 ሰኔ 03 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 82805 ሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ከ1ኛ አመልካች ጋር ግንቦት 06 ቀን 1986 ዓ.ም ባደረጉት የስጦታ ውል መሠረት 1ኛ አመልካች ወ/ሮ ፀሐይ ተሰማ በአከራካሪው ቤት የሟች ድርሻ ላይ እስከእለተሞታቸው ድረስ የመጠቀም መብት አላቸው 1ኛ አመልካች ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በሁዋላ ደግሞ 2ኛ አመልካች /ወ/ሮ አለምነሽ ታፈሰ/ ከተጠሪ /ህፃን አማኑኤል ወንድወሰን/ ጋር የሟች አቶ ታፈሰ ድርሻን የመውሰድ መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 62041

የካቲቲ 11 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ጥሩወርቅ ወርዶፋ - ጠበቃ ብርሃኑ ወልደዮሐንስ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ጥሩነሽ ወርዶፋ - ጠበቃ ደጀኔ አባተ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ልጅነትን የሚመለከት ክርክርን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ የሟች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅነት ይረጋገጥልኝ በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ የሰጠው የልጅነት ማስረጃ በሐሰት የተሠጠ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ በአቤቱታቸው ላይም የአሁኑ ተጠሪ ከሟች አቶ ወርዶፋ በዳሳ እና ከወ/ሮ አፀደ ወ/ጊዮርጊስ ተወልጃለሁ ያሉት ሐሰት ነው፣ ሕጋዊ ግንኙነት አልነበራቸውም፣ የአቶ ወርዶፋ በዳሳ ብቸኛ ልጅ አመልካች ነኝ፣ ተጠሪ የሟች ልጅ ነኝ የሚሉ ከሆነ የደም ምርመራ(DNA) ሊደረግ ይገባል በማለት ገልፀው ለተጠሪ የተሰጣቸው የልጅነት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለአሁኗ አመልካች የመቃወም አቤቱታ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎም ባቀረቡት መከራከሪያ የሟቹ ልጅ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆኑንና የደም ምርመራም የመቃወም አመልካች ሊጠይቁ እንደማይችሉ ገልፀው የመቃወም አመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የ“DNA” ምርመራ ጥያቄን አልፎ የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የአመልካችን መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ አድርጎ ተጠሪ የሟች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅ ናቸው በማለት የሰጠውን ውሳኔ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ የሟች ወርዶፋ ልጅ ናቸው ተብሎ የተሰጠው የልጅነት ማስረጃ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ የተወሰነው በተገቢው ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሲሆን የ“DNA” ምርመራ ጥያቄም የታለፈው ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ የሟች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅ ናቸው ተብሎ መወሰኑም ሆነ



www.chilot.me

የ“DNA” ምርመራ ጥያቄ የመታለፉን ተገቢነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ያቀረቡት በሳይንሳዊ መንገድ የደም ምርምራ ጥያቄ ታልፎ ተጠሪ የሟች አቶ ወርዶፋ ልጅ ናቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሟች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅ እና ወ/ሮ የሺመቤት አየነው በጋብቻ ተሳስረው የተወለዱ ስለመሆናቸው የተረጋገጠ ሁኖ በተጠሪ በኩል የቀረበ ማስተባበያ ክርክር የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ የሟቹ ልጅ ነኝ በማለት የሚከራከሩት ሟች እንደአባት በመሆን ሲንከባከቧቸው የነበረ በመሆኑና ይህም በማስረጃ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የተጠሪን ማስረጃዎች ለማስተባበል በማስረጃነት እንዲቀርብላቸው ከሚፈልጉት ማስረጃዎች አንዱ ደግሞ ሳይንሳዊ የደም ምርመራ ዘዴ ነው፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የማስረጃ ይቅረብልን ክርክር ሳያጠናቅቅ ማለፉን መዝገቡ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ የተጠሪ የሟች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅነት ተረጋግጧል የተባለው በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 143(ሠ) መሰረት ሲሆን በአንቀጽ 143 ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚገባቸው ሁኔታዎች መሆኑ፣ ከእነዚህ ሁኔታዎች ውጪ አባትነት በፍርድ ሊነገር የማይችል ስለመሆኑ የተጠቀሰው አዋጅ በአንቀጽ 145 ስር በግልፅ ደንግጓል፡፡ አዋጁ አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚችልባቸው ሁኔታዎች ላይ ማስተባበያ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለው በአንቀጽ 144 ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች ስለመሆኑ በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ደግሞ “ሣይንሣዊ” ደም ምርመራ አንዱ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ጥያቄ ያልተቀበለበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ በውሳኔው ላይ የገለጸው ነገር የለም፡፡ ይህ ደግሞ የፍርድ አካሄዱን የተሟላ ሳያደርግ ፍርድ የሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ሟቹ በሕጋዊ ጋብቻ ውስጥ የወለዷቸው ስለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ከተጠሪ ጋር የደም ምርመራ ይደረግልኝ ብለው ያቀረቡት ክርክር የሚታለፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች የደም ምርመራ ጥያቄ የታለፈው ያላግባብ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 27962 ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 97440 ጥቅምት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡



www.chilot.me

2. በአመልካች ወጪ የአመልካችና የተጠሪ የ"DNA" ምርመራ እንዲካሄድ በማድረግ የሚቀርበውን ውጤት መሰረት አድርጎ ጉዳዩን እንደገና በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ እንዲሠጥበት ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁጥር 50971

የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች:- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሀመድ

**አመልካች:-** አቶ ኃይሌ ስሙጋ - ጠበቃ አቶ መኸዲ ሁሴን ቀረቡ

**ተጠሪ:-** ሠላማዊት ተኮላ - ጠበቃ አቶ አንተነህ ተካልኝ ቀረቡ

መዝገቡን የቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ማየት የተሳነው ሰው የሚያደርገውን የኑዛዜ አደራረግ ሥርዓት በሚመለከት ግራ ቀኙ ያደረጉትን ክርክር ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሚች ወ/ሮ መሠረት መንገሻ ሚያዚያ 6 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት የኑዛዜ ሰነድ ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ ይኸው የኑዛዜ ሰነድ በፍ/ቤት እንዲፀድቅላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጉዳዮን ተመልክቶ በን/ላ/መ/ቁ/ 1806/99 ሚያዚያ 05 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተቀብሎ አፅድቆታል፡፡

ከዚህ በኂላ የአሁኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሠረት የሚች ወ/ሮ መሠረት መንገሻ አባት ነኝ ሚች ልጅ የላትም ዓይነስውርና የስኳርና HIV/AIDS በሽተኛ የነበረች ስለሆነ በአዋዋይ ፊት ያልተደረገው የኑዛዜ ሰነድ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ስለሆነም ቀደም ሲል ኑዛዜው ፀድቋል በሚል የተሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም ዓይነ ስውር፣ የስኳር እና የ HIV/AIDS በሽተኞች ኑዛዜ ማድረግ አይችሉም የሚል ህግ የለም ኑዛዜውን ሲያደርጉ አእምሯቸው ጤነኛ እንደነበር ይኸው ፍ/ቤት በምስክሮች አረጋግጦታል፡፡ ውሳኔው ሊሰረዝ አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የመቃወም አመልካችን ምስክሮች ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ

ድዳ፣ ደንቆሮ፣ ዕውር የሆኑና ነዋሪ በሆነ ደዌ ምክንያት እራሳቸውን ችለው ለመተዳደር ወይም ንብረታቸውን ለማስተዳደር ችሎታ ለሌላቸው ሰዎች ስለ አእምሮ ጎደሎዎች የተነገሩትን እርዳታዎች ለመጠየቅ ይችላሉ ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 ተደንግጓል፡፡ ሚችም አይነ ስውር እንደመሆናቸው መጠን የኑዛዜ ሰነዱን በእገዛ አይተውና ለይተው የፈረሙበት መሆኑ



www.chilot.me

አልተረጋገጠም። ስለሆነም የኑዛዜ ሰነዱ ፀድቋል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 360(2) መሠረት ተሽሯል። በማለት ወስኗል።

የአሁን ተጠሪ ሟች ኑዛዜውን ሲያደርጉ አእምሯቸው ደህና የነበረ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ ኑዛዜውን ሳያፀድቅ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፣ ዓይነስውር በአዋዋይ ፊት ኑዛዜ ማድረግ አለበት የሚል ህግ የለም የኑዛዜ አደራረግ ሥርዓት በልዩ የህግ ክፍል የተደነገገ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1728 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም የሚሉትን ነጥቦች መሠረት አድርገው ውሳኔው በይግባኝ እንዲታረም የይግባኝ አቤቱታ በማቅረባቸው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባለበት ጉዳዩን ተመልክቷል።

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 ድንጋጌ ዓይነስውራን ድጋፍ ሊጠይቁ እንደሚችሉ እንጂ በአዋዋይ ፊት ያልተደረገ ኑዛዜ ፈራሽ ነው ብሎ በአስገዳጅነት አላስቀመጠም።

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1728 ተፈፃሚነቱ ውሎች ላይ እንጂ ይህንን ጉዳይ አይመለከትም፤ በዚህ ጉዳይ የኑዛዜው አደራረግ የፎርማሊቲ ጉድለት አለት፣ አልተባለም። ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜውን ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው ያላደረጉት ስለሆነ አጠራጣሪ ነው በሚል ምክንያት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል ሲል ዳኝነት ሰጥቷል። የከተማው ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ የህግ ስህተት አልተገኘበትም የሚል የመጨረሻ ዳኝነት ስለሰጠበት ይህ የሰበር ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ችሏል።

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከዚህ በፊት በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ከቀረቡት በይዘቱ የተለዩ አይደለም።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነውም ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸው የኑዛዜ ሰነድ በህግ ፊት የፀና ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው።

ኑዛዜ አድራጊዋ ሟች ወ/ሮ መሠረት መንገሻ ኑዛዜ ባደረጉበት ጊዜ ማየት የተሳናቸው የነበሩ ስለመሆኑም በግራ ቀኙ የተካደ ጉዳይ አይደለም።

ማየት የተሳነው ሰው ኑዛዜ የማድረግ ተግባር ሲፈፀም ይህ ተግባር በህግ ፊት የፀና፤ ማናቸውንም ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል እንደሆነ በህግ መሟላት የሚገባቸው ነጥቦች ምን ምን ናቸው? በሚለው ነጥብ ላይ ነው የተለያዩት።

ይህን አከራካሪ ነጥብ ለማስረዳት በግራ ቀኙ የቀረቡት የፍሬ ነገር ክርክሮች እና ጉዳዩን ለመወሰን የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዳኝነት የጠቀሱት ትንታኔ በህግ ፊት የፀና ተግባር ለመፈፀም አስፈላጊ ሁኔታዎች ናቸው በሚል ህጉ በየቅል ያስቀመጣቸውን ማሟያ ሁኔታዎች አንዱን ከሌላው በማቀላቀል እየተጠቀሱ የቀረቡ እና የተተቹ መሆኑን ከውሳኔዎች ግልባጭ ተገንዝበናል።

ይኸውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 ድውዮች በሚል ርዕስ በተቀመጠው ድንጋጌ ማናቸውንም ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ተግባር ለመፈፀም ችሎታ አስፈላጊ ነው። ችሎታ አለ ወይስ የለም? ማለት



www.chilot.me

የሚቻለው መቼ እና እንዴት ነው የሚለውን በዝርዝር በሚደነግገው ክፍል የሚገኝ ነው፡፡ ችሎታ ከዕድሜ፣ ችሎታ በከባድ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት፣ ችሎታ ከአእምሮ በሽታ ጋር በተያያዘ የእያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ በያዘው የህግ ክፍል የሚገኝ ሆኖ በተለይም በአእምሮ መጎደል ወይም በድውይነት የተነሣ አንድ ሰው የሚሠራው ተግባር ምን ውጤት እንደሚያስከትል የማያውቅ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ይህ ሰው ማናቸውንም ተግባር እንዳያከናውን በማድረግ በፍርድ በመከልከል በህግ ጥበቃ ከሚደረግበት ክፍል ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች በፍርድ ሊከልከሉ የሚገባቸው ስዎች የትኞቹ ናቸው የሚለውን ለመለየት በመሠረትነት ለተቀመጠው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 339 ቀጠሎ የሚገኝ ድንግጌ ነው፡፡ ድውዮችም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የአእምሮ ጎደሎነት እንዳለባቸው ሰዎች ተቆጥረው የፍርድ ክልከላ እንደሚደረግባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 351(3) መመልከቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 ድንጋጌ ይዘትና አስፈላጊነት አንድ ሰው ተግባሩን ለመፈፀም ችሎታ ነበረው ወይስ አልነበረውም የሚለውን ለመለየት እንጂ አካላዊ ጎዶለነት ያለባቸው ሰዎች ህጋዊ ተግባር ለመፈፀም በፈለጉ ጊዜ የአደራረጉ ሥርዓት በምን አኳኋን ሊፈፀም ይገባል ከሚለው ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት የለውም የሚሠሩት ሥራ ምን ውጤት እንደሚያስከትል የማያውቁ ሰዎች ስለሆኑ የፈፀሙት ተግባር ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? በማለት ያደረጉትን ተግባር ህጋዊነት (Validity) ለመመርመር መሠረት የሚሆን ድንጋጌ እንጂ እነዚህ ስዎች ተግባራቸውን የት? እና እንዴት ማከናወን አለባቸው ከሚለው የውል አደራረግ ሥርዓት ጋር የተዛመደ አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 368(1) የተከለከለ ሰው ክልከላው በፍርድ ከተነገረ በኋላ ኑዛዜ ለማድረግ አይችልም በሚል የተደነገገውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 እና 351(3) ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው ይህንኑ የትርጉም መስመር፣ ይበልጥ የሚያጠናክር ሆኖ ይገኛል፡፡

እንደዚሁም ኑዛዜ ዋጋ እንዲኖረው የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች በሚለው ክፍል ችሎታ አስፈላጊ ከሆኑ የሥራ ነገር ሁኔታዎች አንዱ ሆኖ ኑዛዜ ለማድረግ ችሎታ ከዕድሜ አንፃር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 860፣ ችሎታ ለአእምሮ መጓደል ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 861 — 864 በዝርዝር መደንገጉና የኑዛዜ አደራረግ ሥርዓትን በማመልከት ግን እራሱን በቻለ የኑዛዜ ፎርምና ማስረጃ በሚል ንዑስ ክፍል መቀመጡ ኑዛዜ የሚያደርጉ እነማን ናቸው? ኑዛዜ የሚደረግበት ሥርዓት እንዴትና በምን አኳኋን ነው? የሚሉት ነጥቦች በየቅል የሚታዩና ጉዳዮቹን የሚገባው የህግ ክፍል በየነጥቦቹ አግባብ የተቀመጠ መሆኑ እየታወቀ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 የተመለከተውን ድንጋጌ ከውል አደራረግ ሥርዓት ጋር በማያያዝ የሰጠው ትንታኔ እና ትችት አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህም አንፃር ሟች ወ/ሮ መሠረት መንገሻ ማየት የተሳናቸው መሆኑ ከመረጋገጡ በቀር በዚህ አካላዊ ጉድለት ምክንያት ለእራሳቸውም ሆነ ሌሎች መብታቸው የሚያከብሩላቸው ሰዎች ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በፍርድ የተከለከሉ አይደሉም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 343(2) መሠረት በፍርድ ባይከላከሉም ድውይነታቸው አከራካሪ የሆነውን ተግባር ለመፈፀም የሚያስችላቸው ነበረ ብሎ ከችሎታ ጋር በማያያዝ ለመተርጎምም መነሻ የሆኑ ፍሬ ነገሮች አላገኘንም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 አንፃር በማየት አከራካሪ የሆነው ኑዛዜ ህጋዊ ውጤት አያስከትልም በሚል የሰጠው ውሳኔ ከተሳሳተ መነሻ የመነጨ በመሆኑ አተረጓጉሙ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



www.chilot.me

በሁለተኛ ደረጃ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ማየት የተነሳው ሰው ኑዛዜ የሚያደርግበትን የአደራረግ ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡

የአሁን አመልካች ከሥር ጀምሮ አንስቶ የተከራከረበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1728(3) ድንጋጌ ስለውሎች አደራረግ ሥርዓት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678(ሐ) የተመለከተውን መሪ ድንጋጌ በሚያብራራው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1719(2) እስከ 1730 በተመለከተው የውል አደራረግ ሥርዓት ከሚደነግጉት ዝርዝር ድንጋጌዎች አንዱ በመሆኑ ክርክሩ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ የሚገኘው ስለውሎች በጠቅላላው ክፍል እንደ መሆኑ መጠን ስለውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ደንቦች ከውሎች ባሻገር ስለሌሎች ጉዳዮች ያላቸው አግባብነትና ተፈፃሚነት በመሸጋገሪያ ድንጋጌው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1676 በተመለከተው መሠረት ነው፡፡ በዚህም ድንጋጌ አነጋገር የኑዛዜ አደራረግ ሊከተል የሚገባውን ሥርዓት በተመለከተ ስለኑዛዜ በሚያወራው ልዩ ህግ የኑዛዜዎች ፎርምና ማስረጃ በሚለው ርዕስ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 880 ጀምሮ የተደነገገ በመሆኑ ገዥው ህግ ይህ የልዩ ሕግ ክፍልእንጂ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1719 — 1730 የተመለከቱት ድንጋጌዎች አንዱ የሆነው ቁጥር 1728(3) ሊሆን አይችልም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 881 በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡና ምስክሮች በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረግ እንዳለባቸው እንጂ አካላዊ ጉድለት፣ ያለበትን ተናዛዥ አካሉ ከተስተካከለው ለይቶ ያስቀመጠው መስፈርት የለም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1728(3) መሀይማን የጣት ምልክት ፊርማቸውን በአዋዋይ ፊት ማድረግ እንደሚገባ ሲደነግግ ኑዛዜን አስመልክቶ በተቀመጠው በዚህ ልዩ ድንጋጌ 881(3) ማሀይማን የጣት ምልክታቸውን ወዲያውኑ ማስቀመጥ ያለባቸው መሆኑን እንጂ በተለይ በአዋዋይ ፊት እንዲያደርጉ አልደነገገም፡፡ ይህም በአንድ ጉዳይ ላይ በተለያዩ መንገድ በተለያዩ የህግ ክፍል መደንገጉ ጉዳዮች እንደየ አግባብነታቸው ሊታዩ የሚገባ መሆኑን ስለሚያስገነዝብ ለዚህ ለተያዘው ጉዳዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1728(3) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸው ምክንያቶች አንፃር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሆነ ሰበር ሰሚው የሰጡት ዳኝነት መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 እንደተደነገገው የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት በተፈፀመባቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

(1) የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/መ/ቁ 12033 በ17/03/2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

(2) የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡

በዚህ የሰበር ጉዳይ ግራ ቀኙ ላወጡት ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57114

ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፣** ወ/ሮ ሃና ፀጋዬ ጠበቃ አሰፋ ዝቅአርጋቸው ቀረበ

**ተጠሪ፣** ወ/ት ጣዕሙ ደስታ ጠበቃ ገመቹ ሮሮ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ይጣራ ጥያቄን መነሻ ያደረገን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሾች የነበሩት ዳዊት ፀጋዬ የተባለው የአሁንዋ አመልካች ወንድም እና አመልካች ናቸው፡፡ ክሱ በተጠሪ ላይ ሊቀርብ የቻለው የውርስ ንብረት ልታካፍል ይገባል በመባሉ ነው ተጠሪ ለክሱ በሰጠችው መልስ ክሱ የቀረበው የከሣሾች አባት ከሞቱ ከአሥር ዓመት በላይ ቆይቶ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ተከራክራለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የዳዊት ፀጋዬ ሞግዚት በመሆን ያሳደገችው መሆንዋን ከመረጋገጡም በላይ እስዋም ይህን መሠረት በማድረግ በዳዊት ላይ አንስታው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያም መተዋን እንደገለጸች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ተመልቶአል፡፡ ክሱ የቀረበለት ይኸው ፍ/ቤት ሁሉም ወገኖች ያሰሙትን ክርክር ከመረመረ በኃላ የአሁንዋ አመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ጥያቄዋን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው ተጠሪ የአመልካች እንጀራ እናት መሆንዋ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦ እያለ ይርጋው በአመልካች ላይ ተፈጻሚነት አለው የመባሉን አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጠውን ውሣኔ ይዘት ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በዋናነት ለመገንዘብ የቻልነው ተጠሪ የአመልካችም የእንጀራ እናት መሆንዋን ነው፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ሞግዚት የነበረችው ለዳዊት ፀጋዬ ብቻ እንጂ አመልካች በተጠሪ ሞግዚትነት ሥር



www.chilot.me

አልነበረችም። ይህም ሆኖ ግን አመልካችም እንደወንድምዋ /ዳዊት ፀጋዬ/ በወቅቱ ለአካለመጠን ያላደረሰች የነበረች ስለመሆንዋ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል። ፍ/ቤቱ በተጠሪ የተነሳው የይርጋ መቃወሚያ በአመልካች ላይ ብቻ ተፈጻሚነት አለው ለማለት ከበቃበት አንደኛው ምክንያትም አመልካች የሞግዚትነት እና የአሳደሪነት ሥልጣን በነበራቸው ስዎች አማካይነት መብትዋን በወቅቱ ማስከበር ነበረባት የሚል ነው። ይህን ምክንያት መነሻ በማድረግም የአመልካች አባት የሞቱበትን ጊዜ ለይርጋው ጊዜ አቆጣጠር እንደሁለተኛ ምክንያት አድርጎ ወስዶአል። በሌላ በኩል ግን ፍ/ቤቱ የተጠሪን የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት አለው ለማለት እነዚህን ምክንያቶች መሠረት ቢያደርግም አመልካች ከሞግዚት አስተዳደር መቼ ነፃ እንደወጣች በውሣኔው ላይ አላመለከተም ተጠሪም ብትሆን የአመልካች አባት የሞቱበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ የአሥር ዓመትን የይርጋ ጊዜ /የፍትብ/ሕግ ቁ 1845/ በመጥቀስ ከመከራከር አልፋ አመልካች ጊዜውን ያሳለፈችው ለአካለ መጠን ከደረሰች በኃላ /ከሞግዚት አስተዳደር ከወጣች በኃላ/ ነው የሚል መከራከሪያ አላነሳችም።

በበኩላችን እንደምናየው የተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ በዳዊት ፀጋዬ ላይ ተፈጻሚነት የለውም ከተባለ በአመልካችም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የማይታይበት ሕጋዊ ምክንያት የለም። የአመልካች ሞግዚት ነበሩ የተባሉት ሰዎች በወቅቱ መብትዋን አላስከበሩላትም የሚለው አካሄድም እንደዚሁ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም። ዋናው መለየት ያለበት አመልካች የሟች አባትዋ ወራሽ መሆንዋን እና ለማስከበር የተነሳችውም የወራሽነት መብትዋ እንደሆነ ነው። የይርጋው ጊዜ ሊቆጠርባት የሚገባውም በመብትዋ መጠቀም ከቻለችበት /አካለመጠን ከደረሰችበት/ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል። በመሆኑም የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል። በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል።

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 14168 መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 79963 ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል።
2. አመልካች ያቀረበችው የውርስ ይጣራልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል። ስለዚህም የአመልካች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄም ከዳዊት ፀጋዬ ጥያቄ ጋር አብሮ ይታይ በማለት ወስነናል።
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቶአል። ይመለስ።

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

*የሰ/መ/ቁ 57607*

*ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም*

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ኤርሚያስ ኬስታንትኖስ ግሊፐትስ -ወኪል ጸሐይ መለሰ - ቀረበር

**ተጠሪ፡-** ሰለሞን ከስታንቲኖስ ግሊፐትስ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወቀረቀት ይሰጠኝ በሚል በቀረበው ጥያቄ መነሻነት የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን መዝገቡ የተከፈተው አሁኑ አመልካች ባቀረበው የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠን ጥያቄ መሠረት ነው፡፡ ፍ/ቤትም ጥያቄውን በመቀበል የምስክር ወረቀቱን ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ የምስክር ወረቀቱ የሚሰጥበት ህጋዊ ምክንያት የለም፤ ኤርሚያስ የሟች ኬስታንቲኖስ ግሊፐትስ ልጅ አይደለም በማለት መቃወሚያ በማቅረቡ መዝገቡ እንደገና ተንቀሣቅሶ ሁለቱ ወገኖች እንዲከራከሩ ተደርጕአል፡፡ በመጨረሻም የአሁኑ አመልካች የሟች ኪስታንቲኖስ ግሊፐትስ ልጅ ስለመሆኑ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት /የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት/ አረጋግጦ ማስረጃ አልመጣም በማለት ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል ሰጥቶት የነበረውን ማስረጃ ሰርዞአል፡፡ በየደረጃው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የቀረበላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰር ችሎትም በመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰረዘው በአግባቡ ነው ወይ በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡

በዚህ መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን በማስመልከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡



www.chilot.me

ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የሰማው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ መገንዘብ እንደቻልነው ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተጠሪ ባቀረበው መቃወሚያ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አመልካች በሚመለከተው /ስልጣን ባለው/ ፍ/ቤት ልጅነቱን አረጋግጦ ይቅረብ የሚል ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ውጤቱን ለመጠበቅ በሚልም ቀጠሮ ተይዞ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የልጅነት ይረጋገጥ ጥያቄ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ልጅነት አረጋግጦ የሰጠው ውሣኔ የለም የሚል ምክንያት በመስጠት ፍ/ቤቱ የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል ውሣኔ እንደሰጠ ተመልክተናል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ሆነ የይግባኝ ሰሚው ሰበር ችሎትም ይህን መስመር ተከትለው ነው የወሰኑት፡፡

በበኩላችን እንዳየነው የልጅነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ /አቤቱታ/ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ በእርግጥ አመልካች የሟች አቶ ኬስታንቲኖስ ግሊፐስ ልጅ ነው፡፡ ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ ፍ/ቤቱ ከአመልካች ካቀረበው አቤቱታ /ማመልከቻ/ ይዘት በመነሣት ብቻ መዝገቡን እንደዘጋው እና የሰጠው ምክንያትም በጋብቻ ውስጥ ተወልጃለሁ ካልክ በህጉ ልጅ መሆንህ ስለሚገመት ጥያቄህ በፍ/ቤት የሚረጋገጥ አይደለም የሚል እንደሆነ በመዝገቡ ተያይዞ ከቀረበው ውሣኔ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የአመልካችን የይግባኝ ክርክር ያልተቀበለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ከምትጠይቅ ውጪ በዚህ በኩል የሚደረግ የለም በማለት እንደሆነም ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው አመልካች የሟች ልጅ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ አከራካሪ ሆኖአል፡፡ ተጠሪ ቀደም ሲል የተሰጠው የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሚከራከረው አመልካች ሟች እና እናቴ በጋብቻ ተሳስረው ይኖሩ በነበሩበት ጊዜ የተወለድኩ ልጅነኝ የሚል መከራከሪያ ይዞ ነው የምስክር ወቀረቱን እንዲሰጠው የጠየቀው በእርግጥ አመልካች በጋብቻ ውስጥ ስለመወለዱ ከመግለጽ አልፎ ይህ ሁኔታ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ የለም፡፡ በዚህ ምክንያትም ነው አመልካች አቤቱታውን ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ የተጠየቀው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት አመልካች የሟች ልጅ ነኝ የሚለውን ክርክር አለመቀበሉ ትክክል ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን የልጅነት ማረጋገጫ ውሣኔ መስጠት ያለበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ በአግባቡ ሣያስተናግድ በመቅረቱ ብቻ አመልካች ፍትህ የሚያገኝበትን መድረክ እንዲያጣ ማድረጉ አግባብ አይሆንም፡፡

በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ያለው ማንኛውም ሰው ጉዳዩን ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሣኔ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገመንግስት አንቀጽ 37 /1/ ተደንግጐአል፡፡



www.chilot.me

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች በጋብቻ ውስጥም ይወለድ ከጋብቻ ውጪ ልጅነቱን ይረጋገጥላት ዘንድ ለፍርድ ቤት አቤቱታ /ጥያቄ/ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ጥያቄው በፍርድ ሊወሰኑ ከሚገባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ስለዚህም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ በመደበኛው የክርክር አመራር ስርዓት መሠረት አለማስተናገዱ ወይም ከወዲሁ መዝጋቱ ትክክል አይደለም፡፡ በጋብቻ ውስጥ ተወልጃለሁ የሚል ሰው ልጅ መሆኑን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻለው ሰውየው በእርግጥም በጋብቻ ውስጥ ስለመወለዱ በቅድሚያ በፍሬ ነገር ረገድ ሲረጋገጥ እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በእኛ ግንዛቤ እና እምነት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተያዘው ጉዳይ እልባት ከማግኘቱ /ከመወሰኑ/ በፊት አመልካች ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው የልጅነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ /አቤቱታ/ ውሣኔ ማግኘት አለበት፡፡ አመልካች ፍትህ እንዲያገኝ ማድረግ የሚችለውም በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሲሰራ ነው ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመ/ቁ. 1803/96 ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13497 ሰኔ 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13689 ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. በአመልካች አቤቱታ /ጥያቄ/ አቅራቢነት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተው ቁጥር 43257 የሆነው መዝገብ እንዲንቀሣቀስ እና ፍ/ቤቱም የአመልካችን ጥያቄ መሠረት በማድረግ እንደዚሁም ለጉዳዩ አወሣሰን ተገቢ የሆነውን ጭብጥ በመያዝ ውስጥ ይስጥ ብለናል፡፡

3. ተጠሪም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠቃሚ ነኝ የሚል ከሆነ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረውን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሊቀጥል ይችላል ብለናል፡፡

4. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57836

ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አስናቀች ደለለኝ ጠበቃ ዘውዴ ተሰማ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን ጠበቃ በርናባስ ደስታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ የድርሻ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ታህሣሥ 14 ቀን 1993 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ በወረዳ 08 ቀበሌ 05 ቁጥሩ 145/ለ/ የሆነ ፣ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ቁጥር 8/02601 የተሠጣቸውን መኖሪያ ቤት ለተጠሪ እንዲሆን በኑዛዜ መስጠታቸውን ገልጾ በኑዛዜ መሠረት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣት ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ስታቀርብ የአሁኗ አመልካች ይኸው የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄ ተገቢነት የለውም የሚሉባቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት በስር ፍርድ ቤት ያቀረቧቸው ምክንያቶች ሟች ትተውታል በተባለው ኑዛዜ የባለቤታቸውን የአቶ ደለለኝ ስሻን ድርሻ ንብረትን የሚያካትት በመሆኑ ኑዛዜው ሕጋዊነት ያለውም፣ በኑዛዜው ላይ የሰፈረው ፊርማም የሟቿ አይደለም፣ ኑዛዜውን ባደረጉበት ወቅትም በእድሜ መግፋት ምክንያት የሚሰሩትን አያውቁም ነበር ከውርስ ንብረቱም ያለ በቂ ምክንያት ነቅለውኛል የሚሉ ናቸው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ፊርማውን በተመለከተ በተገቢው አካል ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብለት በማድረግ ፊርማው የሟች ማርታ ዳኛቸው መሆኑን ውጤቱን አረጋግጦ ከቀረበለት በሁዋላ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ በሌሎች ነጥቦች ላይ የቀረቡትን የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ኑዛዜውን ያደረጉት ከባላቸው ጋር ባፈሩት የጋራ ንብረት ላይ በመሆኑና ይህም ሕጋዊነት የሌለው መሆኑን እንዲሁም አመልካችን ያለሕጋዊና በቂ ምክንያት ከውርስ የነቀሏቸው መሆኑን ዘርዝሮ ኑዛዜው እንዲፀድቅ የቀረበውን አቤቱታ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኟን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርባ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ባደረጉት ኑዛዜ መሠረት ተጠሪ ወራሽ ናት በማለት የስር



www.chilot.me

ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ኑዛዜውን ያደረጉት ከነባለቤታቸው ድርሻ ጭምር ሁኖ እያለና አመልካችን ከውርሱ ያለሕጋዊና በቂ ምክንያት የነቀሉ መሆኑ ተረጋገጦ እያለ ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽ ናት ተብሎ መወሰኑ ከሕጉ ውጪ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ጠበቃው ቀርበው መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ አመልካችን ሟች ከውርስ የነቀሏት ምክንያት ጠቅሰው በመሆኑ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ እንዲፀና ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ/ም በጻፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ታህሣሥ 14 ቀን 1993 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም አመልካችንስ ከሟች ውርስ ነቅሏል ወይስ አልነቀለም? ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባቸው ሁነው አግኝቷቸዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የቻለው ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ታህሣሥ 14 ቀን 1993 ዓ.ም ግልፅ ኑዛዜ የተው መሆኑን አመልካች የሟቿ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ/ልጅ/ ተጠሪ ደግሞ የሟች የኑዛዜ ወራሽ መሆኗን ሟች ይኖራቸዋል ተብሎ የተጠቀሰው ንብረት መኖሪያ ቤትና የቤት ቁሣቁስ ሁኖ ለአመልካች ብር 1000 እና የቤት ቁሳቁስ እንዲሰጣቸው የገለፁ መሆኑን ይህንን ለማድረግ በምክንያትነት የጠቀሱት ደግሞ አመልካች ትዳር ከያዘች ጊዜ ጀምሮ ተገቢውን እንክብካቤ አላደረገችልኝም ስታመምም እናቴ ብላ አላስታመመችኝም የሚል መሆኑን ነው፡፡ አከራከሪው ቤት የተናዛዧ እና የአቶ ደለለኝ ስሻን የጋራ ሃብት ስለመሆኑ አከራካሪ አለመሆኑንም በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ጭምር ተገንዝበናል፡፡

የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ኑዛዜው ሕጋዊ ነው በማለት የወሰኑት ሟች ለአመልካች ድርሻቸውን ሰጥተዋል፣ የድርሻ ማነስ ደግሞ የውርስ መነቀል ነው ሊባል የሚችል አይደለም የሚል እንድምታ ያለውን ምክንያት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች <u>የኑዛዜ ስጦታ</u> /legacy/ ወይም <u>የክፍያ ደንብ</u> /Rule of partition/ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመህር ደረጃ ደግሞ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያሰኘውም፡፡ ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ /legacy/ አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /partition/ በመከተል የሚከናውን ይሆናል፡፡ ሆኖም በኑዛዜው ላይ የሚሰጠውን ክፍያ መጠን በመገለፁ ብቻ ሁል ጊዜ የክፍያ ደንብ ነው ሊባል የሚችል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተሰጠው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት ግምት ጋር ታይቶ ውጤቱም በዚህ ረገድ መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡



www.chilot.me

በሌላ አገላለፅ ሟች በኑዛዜው ላይ የሚያስፍረው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት መጠን ጋር እየታየ የመነቀል ጉዳይ ነው ወይስ የክፍያ ማነስ ነው? የሚለው ነጥብ የሚለይ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ከሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ለመገንዘብ እንደቻልነው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በወረዳ 8 ቀበሌ 05 ክልል ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 145/ለ/ በሚል የተመዘገበውና በ343 ካ.ሜትር ስፋት ቦታ ላይ የሰፈረው መኖሪያ ቤት የባለቤትነት ደብተር ስሙ ተመዝግቦ የሚገኘው በአቶ ደለለኝ ስሻን ስም መሆኑን ንብረትነቱም የአቶ ደለለኝ ስሻን እና የወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው የጋራ ሃብት መሆኑን የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ለስር ፍርድ ቤት በፃፈው ደብዳቤ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑ ያላከራከረ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሟቿ የተናዘዙት የራሳቸው የግል ንብረት ብቻ ባልሆነ ንብረት ነው ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በራሱ ባልሆነና ሙሉ በሙሉ ሊያዝበት በማይችል ንብረቱ የተናዘዘ እንደሆነ ኑዛዜው የሚኖረው ሕጋዊ ሁኔታ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በውርስ ሕግ በግለጽ ምላሹ ያገኘ ነው፡፡ የውርስ ሕግ ውስጥ ይህንን ጉዳይ የሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1047 እንዲህ ይነበባል፡፡

1. "በኑዛዜው የተደረገው ስጦታ በተለየ ነገር እንደሆነና ሟቹ በሞተበት ቀን በዚህ ነገር ላይ አንዳችም መብት የሌለው እንደሆነ የኑዛዜው ስጦታ ፍርስ ነው፡፡
2. ስለሆነም ሟቹ ይህን ሁኔታ እያወቀ በኑዛዜው ሰጥቶ እንደሆነ ስጦታው ዋጋ ያለው ይሆናል፡፡
3. እንደዚህ በሆነ ጊዜ አጣሪው በኑዛዜ የተሰጠውን እቃ ዋጋ መስጠት አለበት"

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው በመርህ ደርጃ ማንም ሰው ምንም መብት በሌለው ንብረት ላይ የተናዘዘ እንደሆነ የተሰጠው ኑዛዜ ዋጋ አይኖረውም፡፡ በሕግ ፊት የሚፀና ኑዛዜ ለመስጠት ሟቹ ኑዛዜ በተደረገበት ንብረት ላይ መብት ሊኖረው ይገባል በሌላ በኩል በንዑስ አንቀጽ /2/ በግልጽ እንደሰፈረው ሟቹ ኑዛዜ በሚያደርጉበት ንብረት ላይ ምንም መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ ስጦታ የሰጠው እንደሆነ በስጦታው ሕጋዊነት የፀና ይሆናል፡፡ በመሆኑም ኑዛዜ አድራጊው መብት ያለው መሆን አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ስለዚህ ጉዳይ የነበረው ግንዛቤ በኑዛዜው ፍረስ መሆን አለመሆን ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ኑዛዜው ፍርስ የሚሆነው ተናዛዡ ስጦታ ባደረገበት ንብረት ላይ መብት እንደሌለውና ይህንም ያውቅ እንዳልነበረ ሲታወቅ ብቻ ነው ፡፡ ይህ መደምደሚያ የሚገኘው ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ አንድና ሁለት ንዑስ ቁጥሮችን አጣምሮ በማንበብ ነው፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ ተናዛዧ በአከራካሪው ቤት ለአሁኗ ተጠሪ በስጦታ በሰጡት ቤት ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት አልነበራቸውም፡፡ ቤቱ በጋብቻ የተፈራ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑና ከአቶ ደለለኝ ስሻን ሞት በሁዋላ ይዘውት ይጠቀሙበት ስለነበር ሟቿ ቤቱ ላይ ሙሉ መብት እንደሌላቸው ሳያውቁ ኑዛዜ ማድረጋቸው ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው የተሰጠበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ 1047/1/ ን መስፈርት የሚያሟላ ነው፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ቤቱ የጋብቻ የጋራ ንብረት በመሆኑ ምክንያት ሟቿ በቤቱ ላይ ሙሉ መብት ባይኖራቸው የኑዛዜ ስጦታውን ያደረጉት ይህ መብት እንደሌላቸው ሳያውቁ በመሆኑ በሟች አቶ ደለለኝ ስሻን ድርሻ ላይ የተደረገው ኑዛዜ ሊፈርስ የሚገባው ነው፡፡ ኑዛዜው ፍርስ ሊሆን አይችል የነበረው ሟቿ በቤቱ ላይ ሙሉ መብት እንዳላቸው የሚያውቁና ከሟች ደለለኝ ስሻን የተላለፈላቸው መብት ያለ መሆኑ ማስረጃ ቢቀርብ ነበር ፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበችው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም በአቶ ደለለኝ ስሻን ድርሻ ላይ የተደረገው የኑዛዜ ክፍል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1047/1/ መሠረት ፈራሽ



www.chilot.me

ሊሆን የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሆኖም ይህ ምክንያት በሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ድርሻ ላይ የተደረገውን ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ፈራሽ የሚያደርገው አይደለም፡፡

ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው አመልካችን ከድርሻ ንብረታቸው ውርስ ነቅለዋል ወይስ አልነቀሉም? የሚለውን ነጥብም ተመልክተናል፡፡ በመሰረቱ አንድ ተናዛዥ/ወላጅ/ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለህጋዊና በቂ ምክንያት እንዲሁም በዝምታ ከውርስ ለመንቀል እንደማይችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎች ይዘት በግልፅ ያሳያል፡፡ ወላጅ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ወይም በዝምታ ከነቀለም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂ ሕጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሁነው የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በወላጅ የተደረገ የኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አለበት፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912 ስር እንደተመለከተው የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ሲባልም ተናዛዡ ሀብቱን ጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በሙሉ ሀብትነት ወይም በሌጣ ርስትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቀጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ማንኛውም ሌላ የኑዛዜ ቃል ሁሉ እንደ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እንደሚቆጠር ይነደገጋል፡፡ አንድ ኑዛዜ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014 ድንጋጌ ቅደም ተከተል መሠረት የሚከፈል ይሆናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ሀብታቸውን ሙሉ በሙሉ ተጠሪ እንድትወርስ ለአመልካች ደግሞ ብር 1000 እና የቤት ቁሳቁስ የሰጡ መሆኑ ከኑዛዜው ሰነድ ይዘት ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ሟች አላቸው ከተባለው የማይንቀሳቀስ የውርስ ንብረት አንፃር አመልካች እንዲወስዱ በማለት የተናዘዙት የንብረት መጠን ሁኔታ ሲታይ እግምት ውስጥ የሚገባ ወይም የድርሻ ጥያቄ አነሰ የሚል ክርክር የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችል ሳይሆን በውጤቱ የመነቀል ውጤትን ያስከተለ ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡ ሟች ለአመልካች ብር 1000 እና የቤት ቁሣቁስ እንዲሰጥ በማለት የተናዘዙት “ትዳር ከመሰረተች በሁዋላ አልተንከባከበችኝም ፣ ስታመምም እናቴ ነች ብላ አልጠየቀችም ” በሚል ምክንያት ነው፡፡ የዚህ ሐረግ አገላለፅ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938/2/ መሠረት እንደእውነት የሚወሰድ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከውርስ ለመንቀል የሚያስችል ሕጋዊ እና በቂ ምክንያት መሆኑን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938/3/ መሠረት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር በሟች የተሰጠው ምክንያት አመልካችን ከውርስ ለመንቀል ሕጋዊና በቂ ምክንያት ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፎርማሊቲ ረገድ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የሌለ ሲሆን ሟች የአቶ ደለለኝ ስሻንን ድርሻ አጠቃልለው መናዘዛቸው ግን ሕጋዊ አይደለም፡፡ ሟቿ አላቸው ከተባለው ጠቅላላ የውርስ ንብረት መጠን አንፃር ሲታይ ለአመልካች የተሰጠው የገንዘብ መጠን በውጤት ደረጃ አመልካችን ነቅሏል ከሚባል በስተቀር ድርሻቸውን አግኝተዋል፣ ውጤቱም በፍ/ብ/ሕቁጥር 1123 ሊታይ የሚችል ነው ሊባል የሚችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንጻር ተናዛዧ ያደረጉት ኑዛዜ ስጦታ ሲታይ በውጤቱ አመልካችን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ከውርስ የነቀለ ሁኖ ዓይነቱ ልዩ የሆነ የኑዛዜ ስጦታ ሳይሆን



www.chilot.me

ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ አይነት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕቁጥር 1014/ሠ/ ስር በተመለከተው መሠረት እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ ለልዩ ኑዛዜ ተቀባዩ የሚከፈል ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ድንጋጌዎች ታይቶ ተወላጅ ከውርስ ተነቅሏል ፣ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊከፈል ይገባል የሚባልበት ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ የክፍያ ማነስ አለማነስ ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር ጉዳዩ እንዳይስተካከል ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1117 የተቀመጠው መርህ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ጋር ተዛምዶ ሲታይ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የሟች ተወላጅ ወይም ወደ ላይ የምትቆጠር ወላጅ አይደለችምና፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ድርሻ ላይ በፍ/ሕ/ቁጥር 915 መሠረት እንደጠቅላላ ኑዛዜ ወራሽ ተወስዳ ከአመልካች ጋር እኩል ተካፋይ ናት ተብሎ ሊወሰን ሲገባው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከውርስ ንብረት ክፍያ ማነስ ጋር በማያያዝ የሰጡት ውሣኔ የኑዛዜውን ውጤት ሟች አላቸው ከተባለው ንብረት ግምት መጠን ጋር ባለማገናዘብ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 05380 መጋቢት 23 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 13512 ግንቦት 18 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1178/96 ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ/ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
3. ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ታህሣሥ 14 ቀን 1993 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በውጤቱ ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት አመልካችን የነቀለ በመሆኑ በአመልካች ላይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፤ ኑዛዜው ተጠሪን በሟቿ /ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው/ ድርሻ ንብረት ላይ አንድ ወራሽ የሚያደርግ በመሆኑ አመልካች የሟችን ድርሻ ንብረት ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡
4. የአቶ ደለለኝ ስሻን ድርሻ ላይ ተጠሪ በኑዛዜው ተጠቃሚ የምትሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59268

ግንቦት 03 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ዝባድ ታዬ ጠበቃ አማረ ጋሻው ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡-1. ብፁአን ታዬ ሞግዚት አሰለፈች ለገሠ ቀረቡ፡፡

2. ዳኛቸው ታዬ

3. አቶ አቤል ታዬ } ጠበቃ ዘለቀ ደሬሣ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኑዛዜ ተጠቃሚነት ይሰረዝልኝ ጥያቄን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ባጭሩ ፡- ተጠሪዎች የሟች አቶ ታዬ ድንቅነህ ኑዛዜ ወራሾች ነን በማለት ያቀረቡት ሰነድ በሟች ያልተደረገና ፊርማውም የሟች ባለመሆኑ ፊርማው ሊመረመር ይገባል በማለት ዘርዝረው ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች የሟች ታዬ ድንቅነህ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው ሲል የሰጠውን ማስረጃ ሊሰርዝ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም በፍርድ ቤቱ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው ኑዛዜው የሟች ነው፣ ፊርማውም የሟች ነው፣ ኑዛዜው የተደረገውም ምስክሮች ባሉበት ነው በማለት ገልፀው በፍርድ ቤቱ የተሰጣቸው የኑዛዜ ወራሽነት ሊሰረዝ እንደማይገባ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በኑዛዜው ላይ አለ የተባለውን ፊርማ በፎረንሲክ እንዲመረመር አድርጎ በኑዛዜው ላይ ነበሩ ተብሎ ስማቸው የጠቀሰውን ሰዎች በምስክርነት ሰምቶና ፊርማውን በተመለከተ ፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱ የሟች ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመለየት መቸገሩን የሚመለከተው አካል ከገለፀለት በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለጉዳዩ በምስክርነት የቀረቡት ሰዎች ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩበት ሁኔታ እርስ በራሱ ሊጣረስ በሚችል ሁኔታ የመሰከሩ ስለሆነ ቃላቸው ታዓማኒነት የለውም የሚል ምክንያት በመያዝ የአመልካቾችን የኑዛዜ ወራሽነት በማረጋገጥ የተሰጠውን ማስረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 360/2/ መሠረት ሰርዞታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች አይደለም የሚል ሆኖ እያለ



www.chilot.me

የምስክሮችን ቃል በመመርመር ስለኑዛዜው መነበብ መሠረት ተደርጎ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም ተብሎ መወሰኑ በመቃወሚያነት ከተጠቀሱት ነጥቦች ውጪ የተሰጠ ውሳኔ ነው የሚል ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር የተጠሪዎችን የኑዛዜ ወራሽነት ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም ፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ነሐሴ 05 ቀን 2002 ዓ/ም በተጻፈ ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የሻረው በቂና ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረውና በፍ/ብ/ሕ/ቁ/881 - 883 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ባግባቡ ባላገናዘበ ሁኔታ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ስህተቱ እንዲታረምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 881 እስከ 883 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ በፁሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ታዬ ድንቅነህ ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ/ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ አይነቱ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ዓይነት መሆኑን ነው፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትና ይህም ችሎት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲጣራ ያደረገበት ነጥብ ሟች አቶ ታዬ ድንቅነህ ያደረጉት ኑዛዜ በሕጉ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ያሟላል? አያሟላም ? የሚለው ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልጽ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባው ስርዓቶች በፍ/ሕ/ቁ/881 ሥር ተዘርዝረዋል፣፡ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ ይህም ስርዓት መፈፀሙና በተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ ፣ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡ በሟች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ሰነዱ ሲታይ አራት ምስክሮች የፈረሙበት ፣ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚገልጽ እና ተናዛዡ የጣት አሻራቸውን ፣ምስክሮቹ ደግሞ ፊርማቸውን ያኖሩበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ሕ/ቁ/ 881 ሥር የተመለከቱትን ስርዓቶች የሟላ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ኑዛዜው ፈራሽ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የሕጉን ሥርዓት አልተከተለም በሚል ግልጽ ምክንያት ሳይሆን በኑዛዜው ላይ የተጠቀሱት ምስክሮች ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩትን ምስክሮችንና ተጠሪዎችን እንዲሁም ኑዛዜውን ያነበበውን ሰው ማንነት በሚጣረስ መልኩ መስክረዋል በሚል ምክንያት ሲሆን ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በአመልካች በኩል ከቀረበው መቃወሚያ ይዘት ውጪ ነው በሚል ነው፡፡ በመሠረቱ የምስክሮች ዋና አስፈላጊነት ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜ ቃሉም



www.chilot.me

የእርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሕግ ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች ኑዛዜው ፈራሽ ነው ብለው እስከተከራከሩ ድረስ የሕጉን ሥርዓት ያሟላ መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ተገቢውን መወሰን የፍርድ ቤት የስራ ድርሻ ከሚሆን በስተቀር በየትኛው ሕጋዊ ምክንያት ኑዛዜው ፈራሽ እንደሆነ ተከራካሪ ወገን ለይቶ ሊከራከር ይገባል የሚባልበት ሕጋዊ አካሄድ የለም፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ አለመሆኑን፣ አመልካች ተጠሪዎች የሟች ታዬ ድንቅነህ የኑዛዜ ወራሽ አይደሉም፣ ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መሻሩ በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 881— 883 የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 11876 መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 13442 ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/938/2001 በ19/02/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት ፀንቷል፣ሟች አደረጉት የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያላሟላ በመሆኑ ተጠሪዎች የሟች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ሊባሉ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

እ/ብ



www.chilot.me

*የሰ/መ/ቁ. 49713*

*ሚያዚያ 3 ቀን 2003 ዓ.ም*

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- የወ/ሮ ጥሩነሽ አያለ ወራሾች

1. ወ/ሮ የምሥራች ግርማ
2. አቶ ዘላለም ግርማ
3. አቶ ሚሊዮን ግርማ
4. አቶ አዲስ ግርማ

} ጠበቃ አቶ በለው አብዲ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አመልካቾች የአዲሰ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት ማመልከቻ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት የመዝገብ ቁጥር 310198 በማስቀረብ ለመረዳት እንደቻልነው በሥር ፍርድ ቤት የአመልካቾች አውራሽ ወ/ሮ ጥሩነሽ አየለ የፍርድ ተቃዋሚ ተጠሪ ደግሞ የመቃወም ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት የአመልካቾች አውራሽ በመቃወም አመልካች ሆነው በመቅረብ በመዝገብ ቁጥር 0068/96 ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን የሚች የወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3680 ጥር 23 ቀን 1995 የወሰነ በመሆኑ የመቃወም ተጠሪዋ የሟች የወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የልጅ ልጅና ተተኪ ወራሽ ናት በማለት የሰጠውን ውሣኔ ይሰርዝልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት የመቃወም ተጠሪ ሆነው ቀርበው ወንድ አያቴ ታፈሰ በላቸውን ታህሣሥ 7 ቀን 1968 ዓ.ም ከዚህ ዓለም



www.chilot.me

በሞት ተለይተዋል፡፡ ሴት አያቴ ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የካቲት 24 ቀን 1994 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ የአቶ ታፈሰ በላቸውና የወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ልጅ አባቴ አቶ ሰለሞን ታፈሰ ታህሣሥ 28 ቀን 1977 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የሁለቱ ሟቾች ተተኪ ወራሽ ናት በማለት የሰጠውን ውሣኔ የሚሠርዝበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ተጠሪን ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ከውርስ የነቀሏት መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሟች አቶ ታፈሰ እና የወ/ሮ እታለማሁ ያልጅ ልጅ ናት፡፡ ተጠሪ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 በሚደነግገው መሠርት ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል የፈፀመች መሆኑ በፍርድ አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተጠሪዋ የመግደል ሙከራ እንደፈፀመችባቸው በኑዛዜያቸው የገለፁ ቢሆንም የመቃወም ተጠሪ ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን በመግደል ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ያልተባሉ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 መሠረት የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ተቀባይነት የለውም ስለሆነም የመቃወም ተጠሪ ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተተኪ ወራሽ ናቸው በማለት የሰጠሁት ውሣኔ የሚሠርዝበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአምልካቾችን ይግባኝ ውድቅ በማድረግ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለከተማው ሰበር ችሎት አቅረበዋል፡፡ የከተማው ሰበር ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 9 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ አባት ከሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ በፊት የሞተ በመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 830 በሚደነግገው መሠረት ሟችን የመውረስ ችሎታ የለውም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ አባቱን በመተካት ሟችን እወርሳለሁ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ሟች ወ/ሮ እታፈራሁ ተጠሪ በተኙበት ቦታ ሌሊት ልትገድላቸው በዱላ ስትደበድባቸው ጎረቤት ደርሶ ህይወታቸውን እንዳተረፋቸው በኑዛዜቸው በመግለጽ ከውርስ የነቀሏት ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ተተኪ ወራሽ ናት በማለት የሰጠውን የተሣሣተ ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ መልስ እኔ የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ተተኪ ወራሽ መሆኔን በማረጋገጥ የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካቾች ተጠሪን ሟች በኑዛዜ ነቅለዋታል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ህጋዊ መሠረት የለውም፡፡ መከራከሪያም በሰበር ደረጃ የቀረበ ነው፡፡ ሟች የተናዘዘችው በራሷ ንብረት ላይ ብቻ ሣይሆን በወንድ አያቴ ንብረት ላይ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት ተጠሪ የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተተኪ ወራሽ ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም; የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ

ቤት በመዝገብ ቁጥር 0068/96 መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ሊሠረዝ አይገባውም በማለት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ነው በማለት የደረሡበትን መደምደሚያ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ መሠረት የተሰጠ መሆኑንና በውሣኔው ይዘት ተገቢ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ፡- የአመልካቾች አውራሽ ወ/ሮ ጥሩነሽ አየለ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ግልፅ ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን በመግለፅ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚች ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ወራሽ መሆኑን አረጋግጦ እንዲወሰንላቸው ባቀረቡት ማመልከቻ መሠረት ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩ ምስክርና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ የህጉን መስፈርት ያሟላ ነው፡፡ ወ/ሮ ጥሩነሽ አየለ የሚች የወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ወራሽ ናቸው በማለት በመዝገብ ቁጥር 3680 ጥር 23 ቀን 1995 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ በህይወት ዘመናቸው ያደረጉት ኑዛዜ የሌለ መሆኑን በመግለፅ ተጠሪ የሚች የልጅ ልጅና ተተኪ ወራሽ እንደሆኑ እንዲወሰንላቸው ለአዲስ አበባ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጥያቄ አቅረበዋል፡፡ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪን ማስረጃ በመዝገብ ቁጥር 0068/96 በመስማት ተጠሪ የሚች የልጅ ልጅና ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካቾች አውራሽ ተጠሪ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ በህይወት ዘመናቸው ኑዛዜ አላደረጉም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የተሣሣተ ነው፡፡ የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን የተሣሣተ አቤቱታ በመቀበል መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበትና የእኔን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ነው፡፡ ሚች ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን እና የሚች ኑዛዜ ህጋዊ መስፈርት የሚላ መሆኑ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስቀድሞ በፍርድ የተወሰነ ነው በማለት ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ መሠረት ሲጣራ ሚች ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑንና ኑዛዜው ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟላና ህጋዊ ውጤት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥር 23 ቀን 1995 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚች ወ/ሮ እታለማሁ በነፃ ፈቃዳቸው በህግ የተደነገገውን መስፈርት በሚሟላት ያደረጉትና ህጋዊ ውጤት ያለው ኑዛዜ መሆኑን በማረጋገጥ ጥር 23 ቀን 1995 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠበት ሚች ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በይዘቱ ተጠሪን ከውርስ የሚነቅልና የአመልካቾችን አውራሽ የሚች ወ/ሮ እታለማሁ የኑዛዜ ወራሽ የሚያደረግ መሆኑን ለማስረዳት የአመልካቾች አውራሽ በማስረጃነት ካቀረቡት የኑዛዜ ሰነድ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ የቀረበለት የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ህጋዊነቱ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ ጥር 23 ቀን 1995 ዓ.ም የተሰጠውን ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 በሚደነግገው መሠረት ውሣኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት የፍርድ መቃወሚያ በማቅረብ ካላሻሩት በስተቀር በመዝገብ ቁጥር 0068/96 መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በተሣሣተ ፍሬ ጉዳይ ላይ የተመሠረተና በሌላ ፍርድ ቤት አስቀድሞ ውሣኔ በተሰጠበት ጭብጥ ላይ የተሰጠ መሆኑ የአመልካቾች አውራሽ ካቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ጋር አያይዘው ባቀረቡት የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ



www.chilot.me

ቤት ውሣኔና ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ባደረጉት የኑዛዜ ሰነድ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0068/96 መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ያደረጉት ኑዘዜ የለም በማለት ተጠሪ ያቀረቡትን የተሣሣተ ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ የተሰጠና ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ያደረጉት ኑዛዜ የህጉን መስፈርት ያሟላና ህጋዊ ውጤት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ አስቀድሞ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን ባለማወቅ መሆኑን ገልፆ ውሣኔውን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 360/2/ መሠረት መሠረዝ ነበረበት፡፡ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5/1/ መሠረት አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ መሆኑንና ተጠሪ የኑዛዜውን ህጋዊነትና የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት አስመልክቶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3680 ጥር 23 ቀን 1995 የሰጠውን ውሣኔ ላይ የፍርድ መቃወሚያ በማቅረብ ሣያስርዙ ከውርስ የተነቀሉ መሆኑን የሚገልፅ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ያደረጉት ኑዛዜ መኖሩን በማረጋገጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ እያለ ተጠሪ የሚች ወ/ሮ እታለማሁ ተተኪ ወራሽ ናቸው በማለት የሰጠሁትን ውሣኔ የምሰርዝበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ መስጠቱ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5/1/ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊ መስፈርቱን የሚያሟላና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው በማለት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ይዘት እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመመርመር ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ በኑዛዜቸው የገለፁት ምክንያት ተጠሪን ከውርስ ለመንቀስ የሚያበቃ አይደለም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የሆኑትን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5/1/ ፣ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 እና የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 360/2/ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ሚያዚያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የሥነ ሥርዓት ህግ ግድፈት ብቻ ሣይሆን በይዘቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ አተረጓጎም ችግር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ምክንያቱም ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ከተራ ቁጥር 2 "ያሣደጓት የአቶ ሰለሞን ታፈሰ ልጅ ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን ከልጅነት ጀምሮ አሣድጌ ለቁም ነገር ከአደረስኳት በኋላ እኔ ሣላስበው ከተኛሁበት ቦታ ልትገለኝ በዱላ ደብድባኝ ጎረቤት ደርሶ ህይወቴን ያተረፍኩት ስለሆነ ከልጅነት ጀምሮ በማሣደጌ ብር 1,000/አንድ ሺ ብር/ ተሰጥቷት ከምንም ንብረቴ እንዳትደርስ በዚህ ኑዛዜ ቃል አውግዥ አግዳታለሁ" በማለት የተናዘዙ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ከተያያዘው የነዛዜ ሰነድ ተረድተናል፡፡

የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች አውራሽ ይህንን የኑዛዜ ሰነድ በመጥቀስ ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ተጠሪ የመግደል ሙከራ የፈፀመችባቸው መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ተጠሪ በመግደል ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ያልተባሉ በመሆኑ ኑዛዜው የፍታብሔር ህግ 838 ድንጋጌ መስፈርት አያሟላም በማለት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ለውሣኔ መሠረት በማድረግ የጠቀሰው እና የተረጉመው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 ከተዘረዘሩት ወንጀሎች አንደኛውን መፈፀሙ በፍርድ ተረጋግጦበት



www.chilot.me

ጥፋተኛ የተባለ ወራሽ ሟችን እንዳይወርስ በውርስ ህግ ክልከላና ማዕቀብ ይደረግበታል፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 የሚደነግገው በሟች ወይም በሟች ሚስት ወይም ባል ወይም በሟች ወላጆችና ተወላጆች ላይ በህጉ ከተመለከቱት አንደኛውን ወንጀል የፈፀመ መሆኑ በወንጀል ችሎት ተረጋግጦ የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 830 መሠረት ሟችን የመውረስ ችሎታ እንዳይኖረው በህግ ክልከላና ማዕቀብ የሚደረግበትና ሟችን ለመውረስ ያልተገባ /unworthy/ በመሆኑ በህግ ክልከላ /ማዕቀብ/ ይደረግበታል፡፡ ሟች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 841 በተደነገገው መሠረት ይቅርታ ካላደረገለት በስተቀር በፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 ከተዘረዘሩት ተግባራቶች አንደኛውን መፈፀሙ ተረጋግጦ በፍርድ ጥፋተኛ የተባለ ወራሽ በሟች ወርስ እንዳይካፈል ክልከላ የሚያደርግበትና ማዕቀብ የሚጥልበት ሟች ሣይሆን በውርስ ህግ ድንጋጌ ህግ አውጭው በደነገገው የፍታብሔር ቅጣት /civil sanction/ መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 830 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 ድንጋጌዎች ይዘትና ህጋዊ ውጤት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የአመልካቾች አውራሽ የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡት ተጠሪ ሟች ለመውረስ ያልተገባች ናት በማለት አይደለም፡፡ የአመልካቾች አውራሽ የተከራከሩት ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰን ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ባደረጉት ኑዛዜ ከውርስ ነቅለዋታል በማለት ነው፡፡ ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ስለመሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 በተደነገገውና አንድ ሰው በግልፅ በሚያደርገው ኑዛዜ ተወላጆቹን ከውርስ ለመንቀል ስለሚችልበት ሁኔታ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 937 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 938 በተደነገገው መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ ከውርስ መንቀል "Dishersion" የሚባለው ተናዛዡ የውርስ ህግ በሚደነግገው መሠረት ባደረገው ኑዛዜ ውስጥ ምክንያቱን በመግለጽ ወይም በዝምታ ከወራሾቹ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑት ወራሾቹ በውርሱ እንዳይካፈሉ ያደረገውን ኑዛዜ በውርስ ህግ ዕውቅናና ውጤት የሚሰጠው በሆነ ጊዜ ከውርሱ እንዳይሣተፍ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡ ተናዣዡ ከወራሾቹ አንደኛውን ከወራሽነት ለመንቀል የሚችል መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 937/1/ የሚደነግግ ሲሆን ተናዣዡ ልጅን ወይም ወደታች የሚቆጠረውን በኑዛዜ ለመንቀል የደረሰበትን ምክንያት በኑዛዜው ውስጥ ካልገለፀ በቀር ልጅን ወይም ተወላጅን ለመንቀል ያደረገው ኑዛዜ እንደማይፀና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 938/1/ ተደንግጓል፡፡

ተጠሪ የሟች እታለማሁ ታፈሰ የልጅ ልጅ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተጠሪን ከውርስ ለመንቀል የደረሱበትን ምክንያት ተጠሪ አደረገቸው ያሉትን ተግባር በኑዛዜያቸው ገልፅዋል፡፡ ሟች በኑዛዜ ፈፀመችው በማለት የገለፁት ተግባር ማለትም ሟች "ሣያስቡት ሌሊት ከተኙበት የደበደበቻቸው መሆኑንና ጎረቤት ደርሶ ህይወታቸውን ያተረፋቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሟች በኑዛዜያቸው የገለፁት ምክንያት ሙሉ በሙሉ ዕውነት ነው የሚል የህግ ግምት ያለ ሲሆን ህጉ ተጠሪ ተቃራኒ ማስረጃ ሊያቀርቡበት የማይችሉና /የማይስተባበል የህግ ግምት/ መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 938/3/ ተደንግጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ተወላጆቻቸውን ተጠሪን ከውርስ ለመንቀል በኑዛዜቸው የገለፁትን ምክንያት ዕውነት ነው ብሎ በመቀበል ሟች የሰጡት ምክንያት ተጠሪን ከውርሰ ለመንቀል በቂ ነው ወይስ አይደለም; የሚለውን ነጥብ መርምሮ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 938/2/ መሠረት መወሰን ነበረበት፡፡ ሟች በኑዛዜቸው የገለፁት ምክንያት ከባድና ተጠሪውን ከውርስ ለመንቀል የሚያስችል በቂ ምክንያት መሆኑ ሟች በኑዛዜቸው ከገለፁት ምክንያት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 937/1/ እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 938 ድንጋጌዎች መሠረት መርምሮ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 በመጥቀስ ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 መሠረት በሟች ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል

የፈፀመች መሆኑ በፍርድ ጥፋተኛ የተባለችበት ማስረጃ አልቀረበም በማለት የአመልካቾችን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 310/98 ሚያዚያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት 07155 የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 10061 ሀምሌ 17 ቀን 2001 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ለተጠሪ ከተናዘዙት ብር 1,000/አንድ ሺህ ብር/ ውጭ በውርሳቸው እንዳይሳተፉ በኑዛዜ የነቀሏቸው ስለሆነ ተጠሪ የሟች ተተኪ ወራሽ አይደሉም ብለናል፡፡
3. አመልካቾች የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3690 ጥር 23 ቀን 1995 የሰጠው ውሣኔ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት አለው በማለት ወስነናል፡፡
4. ተጠሪ የሟች አቶ ታፈሰ በላቸው ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት አለው በማለት ወስነናል፡፡
5. ከሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የውርስ ንብረት አመልካቾች ለተጠሪ ብር 1,000/አንድ ሺ ብር/ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

*ቅ/መ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55648

መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቶች፡-** 1- ወ/ሮ እቴቱ ሽፈራው
2- አቶ አሸናፊ ሽፈራው } ጠበቃ አቶ ግርማቸው ይላላ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1- ወ/ሮ መንበረ ሽፈራው
2- አቶ ይድነቃቸው ሽፈራው } ጠበቃ አቶ ሀይሉ ነጉ ቀረቡ
3- አቶ ዮናስ ሽፈራው

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካቾች የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ጭብጥ ተይዞ ለሰበር ችሎት የቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች አመልካች አመልካቶች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት የአንደኛ ተጠሪ ወላጅ አባት አቶ ሽፈራው ወልደማርያም ህዳር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ምንም አይነት ኑዛዜ ሣይተው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ እንደዚሁም የአንደኛ ተጠሪ ወላጅ እናትና የሁለተኛና የሶስተኛ ተጠሪዎች አያት የሆኑት ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ፊንታ ጥር 17 ቀን 2000 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩና ጥር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ተጠሪዎችን የኑዛዜ ተጠቃሚ የሚያደርግ ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን በመግለፅ አንደኛ ተጠሪ የሟች ሽፈራው ወልደማርያም ያለኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲሰጣቸውና ተጠሪዎች የሟች የወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው እንዲረጋገጥላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካቶች በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ በመሆን ገብተው የሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ልጆችና ህጋዊ ወራሾች ነን፡፡ ጥር 7 ቀን 2000 ዓ.ም እናታችን ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ አደረጉት የተባለው ኑዛዜ ሟች ካላቸው ንብረት እኛ ብር 500/አምስት መቶ ብር / እንዲሰጠን የሚልና እኛን ከውርስ የመንቀል ያህል ውጤት ያለው ነው፡፡ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉት በትክክለኛ አእምሮ አለመሆኑን ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች የልጅ ልጆቻቸው ሆነው እያለ ልጆቼ



www.chilot.me

በማለት ያደረጉት ኑዛዜ ያስረዳል ስለዚህ ኑዛዜው ውድቅ ሊደረግልን ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ኑዛዜ አድራጊዋ ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ አንድ ሚሊዮን ከሚያወጣው የውርስ ሀብት ውስጥ አመልካቾች ብር 500 /አምስት መቶ ብር / እንዲወስዱ ኑዛዜ ሲያደርጉ የሰጡት ምክንያት በቂ ምክንያት ባለመሆኑ ኑዛዜው እንዲሻሻል በማድረግ አመልካቶች ጣልቃ ገቦች የሚችን የውርስ ሃብት እኩል ይካፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሟች በኑዛዜ የፈለጋችውን ያህል ሀብት ለወራሾች በኑዛዜ የመስጠት ስልጣን እንዳላቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 913 የተደነገገ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ኑዛዜ እንዲሻሻል የሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር በሟች ኑዛዜ መሠረት ተጠሪዎች ይወርሳሉ በማለት ወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለፅ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የከተማው የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ለአመልካቾች ብር 500/አምስት መቶ ብር/ የሰጡበትን ምክንያት በኑዛዜው የገለፁ ስለሆነ የአመልካቾች ተቃውሞ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 913 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123/1/ ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች ሚያዝያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ከተማ የሰበር ችሎት ሟች እናታችን ያደጉት ኑዛዜ ከሟች ውርስ ከሚደርሰን አንድ አራተኛ በላይ ጉዳት እንደሚያደርስብን ካረጋገጠ በኋላ ሟች በኑዛዜያቸው ምክንያት የገለፁ መሆኑን ብቻ በማየት የሟች ምክንያት በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ሣይመዝን የፍታብሔር ሀግ ቁጥር 1113/1/ በመጥቀስና በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሟች የአመልካቾችን ድርሻ ዝቅ በማድረግ ብር 500/አምስት መቶ ብር/ እንዲወስዱ ያደረጉት ኑዛዜ ተገቢ ነው አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123ን በመጥቀስ ያልተከራከሩ በመሆኑ በሰበር ደረጃ ማንሣታቸው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329ን የሚጥስና በሰበር ያቀረቡት አዲስ ክርክር ነው የከተማው የሰበር ችሎት ለፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123/1/ የሰጠው ትርጉም ተገቢ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ታህሣሥ 8 ቀን 2003 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ የስር ፍርድ ቤት ሟች ያደረጉትን ኑዛዜ ያሻሻለው በህግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው የተጠሪዎች ክርክር የህግ መሠረት የለውም የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካቾች እናትና አውራሽ የሆኑት ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ አመልካቾች ከውርስ ከሚደርሳቸው አንድ አራተኛ /ሩብ/ በላይ ጉዳት እንደደረሰባቸው በማሰብ ጥር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል በማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123 ንዑስ አንቀፅ 1 በስጦታው አከፋፈል ውስጥ ተቃራኒ ቃል ከሌላ በቀር ወደ ታች

ከሚቆጠሩ ተወላጆች አንዱ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ የስጦታ አከፋፈሉ እንዲቀር ለመጠየቅ እንደሚችል ይደነግጋል። የበታች ፍርድ ቤቶች ሟች ካላቸው የውርስ ንብረት አመልካቾች እያንዳንዳቸው ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ ብቻ እንዲሠጣቸው ያደረጉት ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል ከሚለው መደምደሚያ ላይ ያደረሱት ሟች በኑዛዜው ውስጥ ይህንን ያደረጉበትን ምክንያት ገልፀዋል በማለት ነው።

ሟች አመልካቾች የአብራካቸው ክፋይ ልጆቻቸው መሆናቸውን ገልፀው እነርሡ ግን ያልጠየቁኝ ያልረዱኝ በመሆኑ ከውርሱ ንብረት ብር 500/አምስት መቶ ብር / እንዲወስዱ በማለት በኑዛዜው ገልፀዋል። ሆኖም ሟች በኑዛዜው ውስጥ የገለፁት ምክንያት እውነት ነው ብለን ወስደን ምክንያቱ አመልካቾችን ከሟች ውርስ ከሚደርሳቸው ድርሻ ከሩብ በላይ ለማሣጣት በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ መወሰን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። ከዚህ አንፃር ሲታይ ሟች ወ/ሮ ዳርቻ በኑዛዜው ውስጥ የሰጡት ምክንያት አመልካቾች ከውርሱ ንብረት ከሚደርሳቸው ድርሻ ከሩብ /አንድ አራተኛ/ በላይ ለማሳጣት የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመሆኑ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የከተማው የሰበር ችሎት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 913 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123 ንዑስ አንቀፅ 1ን በመጥቀስ የሟች ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም።

ስለሆነም ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ አመልካቾች ብር 500/አምስት መቶ ብር/ ብቻ እንዲወስዱ ያደረጉበትን ምክንያት የገለፁ ቢሆንም ሟች በኑዛዜቸው የገለፁት ምክንያት ዕውነት እንደሆነ በመውሰድ ምክንያቱ በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ዳኞች መመዘን የሚችሉ ስለመሆኑ የፍትብሔር ህግ ቁጥር 1123 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 938 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ጋር በጣምራ በመተርጎም ለመረዳት የሚቻል በመሆኑ ወ/ሮ ዳርቻ አመልካቶች ስላልረዷቸውና ስላልጠየቋቸው ከውርሱ ከሚደርሳቸው ድርሻ ከአንድ አራተኛ /ሩብ/ በላይ እንዲያጡ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመሆኑ ኑዛዜው አመልካቾች የሚያጡት መብት ከድርሻቸው አንድ አራተኛ /ሩብ/ በላይ መሆን አይገባውም። ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል በማለት የሰጠት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል።
2. ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾች ከውርሱ ንብረት ከሚደርሳቸው ከሩብ /አንድ አራተኛ/ በላይ ሊያሳጣቸው የሚችል አይደለም በማለት ወስነናል።
3. ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾች ከውርሱ ከሚደርሳቸው ድርሻ እስከ አንድ አራተኛ /ሩብ/ ድረስ ብቻ የሚያሳጣቸው በመሆኑ ኑዛዜው በዚሁ መንገድ ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው ተደርጎ ሊተገበር ይገባዋል በማለት ወስነናል።
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ሃ/ዲ                                                  የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 61677

ሚያዚያ 18 ቀን 2003ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ፈቃደ መክብብ ጠበቃቸው አቶ አምዴ አበበ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዳንኤል ብሥራት ጠበቃቸው ወ/ሮ አበባ መንግስቱ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት በስር አመልካች ወይም በአሁን ተጠሪ ዳንኤል ብሥራትና በስር ተጠሪ ሞገስ ብሥራት መዝገብ የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

በሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ያሁን ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ ሟች አባታችን አቶ ብሥራት ኪዳኑ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ምድብ የመ/ደ/ፍ/ቤት ከተጠሪ /ሞገስ ብሥራት/ ጋር ወራሽ ነኝ የሚል ግለሰብ እኔን ያሁን አመልካችን ወራሽ አይደለም በማለት ውሳኔ በማሰጠቱ አመልካች በይግባኝ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሳይሽር ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ልጅነት አረጋግጬ ስቀርብ ከውርስ ልነቀል አይገባም በሚል መከራከር እንደሚችል ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የሟች ብሥራት ኪዳኑ ልጅ ስለመሆኔ ይረጋገጥልኝ ብሏል፡፡

የስር ተጠሪ የነበረው አቶ ሞገስ ብሥራትም በሰጠው መልስ አመልካች ከሟች አቶ ብሥራት ኪዳኑ እና ከወ/ሮ ውድነሽ ይደግልኝ ህዳር 25 ቀን 1959ዓ.ም የተወለደ በአባትም በእናትም የምንገናኝ ወንድሜ ነው፣ ልጅነቱም እውነት ስለሆነ በጥያቄው መሠረት ቢረጋገጥለት ተቋውሞ የለኝም ብሏል፡፡

የሥር አመልካችን አቤቱታና የተጠሪን መልስ የመረመረው የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤትም አመልካች ከሟች ብሥራት ኪዳኑ ስለመወለዱ ተጠሪ ወይም የአመልካች ወንድም ያልተቃወመ በመሆኑ አመልካች የሟች ብሥራት ኪዳኑ ልጅ ነው በማለት በቤተሰብ ህግ ቁጥር 143 መሠረት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የስር የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የአሁኑ የሰበር አመልካች ቅር በመሰኘት ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ እንዲታረምለት ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤቱ በ25/01/2003 ዓ.ም



www.chilot.me

በዋለው ችሎት መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

የሰበር አመልካችም በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ጥቅምት 22ቀን 2003ዓ.ም የተጻፈ ቅሬታ አቅርቧል፡፡ በሰበር አቤቱታ የተጠቀሱት ዋና ዋና የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- ሟች አጐቴ አቶ ብሥራት ኪዳኑ በሕይወት ዘመናቸው ያደረግኩላቸውን ውለታ በመግለጽ በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 04/06/07 ክልል የሚገኘውን ቁጥሩ 288 የሆነውን የግል መኖሪያ ቤታቸውን በታህሳስ 15 ቀን 1994ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት 4 ምስክሮችን ይዞ በመቅረብ የተናዘዙልኝ በመሆኑ ይህንኑ መሠረተ በማድረግ የኑዛዜ ወራሽነቴን በቦሌ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 373/2000 እንዲረጋገጥ ያደረግኩ ሲሆን ያሁኑ ተጠሪና አቶ ሞገስ ብሥራት ኑዛዜውን ተቃውመው የሟች ኑዛዜ በፎረንሲክ ላብራቶሪ ተመርምሮ የሟች ፊርማ መሆኑ በመረጋገጡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወራሽነቴን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኋላ ተጠሪው እንደገና ሳያገኝ አቶ ሞገስ ብሥራት የተባለውን በተጠሪነት መዝግቦ በቀጥታ አቤቱታ በማቅረቡ የሥር መ/ደ/ፍ/ቤትም አመልካቹን የሟች ልጅ ነው ሲል ውሳኔ በመስጠቱ ያሁን አመልካችም በዚሁ ውሳኔ መቃወሚያ ባቀረብም የሥር ፍ/ቤት በቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/1-3/ መሠረት የመቃወም መብት የለህም ማለቱ የህግ ስህተት ነው፣
- በሥር ፍ/ቤት በተጠሪነት የተመዘገበው አቶ ሞገስ ብሥራት በቦሌ ምድብ የመ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ፣ ሰሚው ፍ/ቤት የተከራከረኝ ሲሆን እንደ ህጉ ዓላማ ከሆነ በተጠሪነት መመዝገብና መጠራት የሚገባኝ እኔ ያሁኑ አመልካች ነበርኩ፡፡ ይህ ታልፎ ከዚህ በላይ በስም የተጠቀሰውን ግለሰብ ተጠሪ ማድረጉ የህግ ስህተት ነው፣ የሚሉ ሲሆኑ ተጠሪው የሟች ብሥራት ኪዳኑና የወ/ሮ ውድነሽ ይደግልኝ ልጅ ሳይሆን የአቶ መኮንን በላይና የወ/ሮ ሰማያት ይደግልኝ በመሆኑ ተጠሪው ፍ/ቤቱን ሳያስፈቅድና ፍ/ቤቱም ሳይፈቅድለት ከሟች የተወለደ ልጅ ነው በሚል የተሰጠ ውሳኔ ይሻርልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

ለቀረበው የሰበር ቅሬታ ተጠሪው በሰጠው መልስ፡- አባትነትን መቃወም ለማንም የተለቀቀ ሳይሆን ለቅርብ የቤተሰብ አባላት የተሰጠ መብት ነው፡፡ አመልካች የሟች ወንድም በመሆኑ በቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/1-3/ ሥር ከተመደቡት የዘር እርከን ውስጥ አይሸፈንም፡፡ ተጠሪን የሟች ብሥራት ኪዳኑ ልጅ አይደለም በማለት የሚከራከረውም ሟች ንብረታቸውን በኑዛዜ ሰጥተውኛል በሚል ሲሆን በቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/3/ ከጥቅም ግጭት የተነሳ አባትነትን ለመቃወም ከተገለጹት ወራሽና ወኪል አንዱ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሟች አቶ ብሥራት ኪዳኑ ለአመልካች በኑዛዜ ንብረታቸውን የሰጡ መሆኑንና ይህንኑ ተጠሪና ወንድሜ ተቃውመን ኑዛዜው የሟች ነው በሚል በመረጋገጡ አሁን ለዚህ ችሎት ከቀረበው የልጅነት ጥያቄ ጋር የሚያናኝ ነገር የለም፡፡ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ይጽናልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

ተጠሪው ላቀረበው መልስ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ የተጠሪው መልስ በሥር ፍ/ቤቶች የተፈፀመውን የህግ ስህተት የሚያስተባብል ባለመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ ይሻርልኝ በሚል ክርክሩን አጠናክሯል፡፡



www.chilot.me

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የቀረበ ሲሆን እኛም የሰበር አመልካች ተጠሪው የሟች ብሥራት ኪዳኑ ልጅ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ያቀረበውን የመቃወሚያ አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው ክርክሩን መርምረናል፡፡

አመልካች የፍታብሐር ሥ/ሥ/ህግ ቁጥሮችን 35/፣359 እና 360 በመጥቀስ ባቀረበው የፍርድ መቃወሚያ በ29/8/2002ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ የሟች ብሥራት ኪዳኔ ልጅ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ይሻርልኝ በማለት ሲሆን ለዚህም እንደምክንያት የጠቀሰው ተጠሪ ከሟች ብሥራት ኪዳኔና ከወ/ሮ ውድነሽ ይደግልኝ አልተወለደም የሚል ነው፡፡ እንደ አመልካች አባባል የተጠሪ አባት አቶ መኮንን በላይ እናቱ ደግሞ ወ/ሮ ሰማያት ይደግልኝ ናቸው፡፡ ከተጠሪ በኩል ከቀረቡት የመከራከሪያ ሐሳቦች ምላሽ ማግኘት ያለበት አመልካች ተጠሪው የሟች ብሥራት ኪዳኔ ልጅ አይደለም በማለት የመከራከር ህጋዊ መብት የለውም የሚል ነው፡፡ ለዚህም ተጠሪው ጠቅሶ የሚከራከረው የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 177 /1-3/ ያሉ ድንጋጌዎችን ነው፡፡

በመሠረቱ በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ሲሆን ክሱንም የሚያቀርበው የልጅ አባት ነህ የተባለ ሰው ነው፡፡ ሆኖም በህግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አባት ነህ የተባለው ሰው ችሎታያጣ እንደሆነ ከተወላጆች አንዱ በርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክስ ማቅረብ እንደሚችል የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/1/ ይደነግጋል፡፡

ነገር ግን ተወላጆች የሌሉ እንደሆነ አባት እና እናት የመካድ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው ሲሆን እነዚህም በሌሉ ጊዜ ደግሞ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች አንዱ መብቱን ሊሠራበት እንደሚችል ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ህግ አንቀጽ 177/2/ ተጠቅሷል፡፡ በመጨረሻም ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች የሌሉ እንደሆነ በመካድ መብት ሊሠራበት የሚችለው ከወንድሞቹ ወይም ከእህቶቹ አንዱ እንደሆነ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/3/ ይናገራል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይም አመልካች የሟች ወንድም በመሆኑ የሟች ተወላጆች ወይም ወላጆች (Descendants or Ascendants) በሕይወት አለመኖራቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 177/3/ መሠረት የመካድ ክስ ወይም ሟች ብሥራት ኪዳኑ የተጠሪ አባት አይደለም በማለት ሟች የተጠሪ አባት ነው ተብሎ የተሰጠውን ፍርድ እንዲነሳ መቃወሚያ ማቅረብ አይችልም፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡



www.chilot.me

## ው ሳ ኔ

1. የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 169057 በቀን 29/8/2002ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 96603 በ25/01/2003ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ አጽንተናል፡፡
2. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ም/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59539

ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች**፡-1. አቶ ስዩም ወ/መሰቀል - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ዘነቡ ወ/መስቀል

3. ወ/ነት ጠግባቸው ወ/መስቀል

4. ወ/ሮ ጽዮሐና ወ/መስቀል

**ተጠሪ**፡- ወ/ት አምሣለ ሙሉነህ - ጠበቃ ዳንኤል ገ/ጊዮርጊስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ አውራሻችን ሟች ወ/ሮ ሙሉሸዋ ወ/መስቀል ከሟች አቶ አበበ ተክሉ ግር ጋር ጋብቻ ፈጽመው በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 14/15 የቤት ቁጥር 1654 እና የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን በጋራ አፍርተዋል፡፡ ተከሣሽ የሟች አውራሻችንን ንብረት ይዘው እየተጠቀሙ ሲሆን እንዲለቁ ቢጠየቁ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በህግ ተገደው ንብረቱን እንዲያካፍሉን ወይም ንብረቱ ተሸጦ የድርሻችን ክፍያ እንዲፈጸምልን የሚል ነበር፡፡

ተከሣሽ /የአሁን ተጠሪ/ በሰጡት መልስ የተጠቀሰው ቤት የባልና ሚስት ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረቡም እና ቤቱም በተከሣሽ ስም የተመዘገበ በመሆኑ የመክሰስ መብት የላቸውም፤ አውራሻቸው ከሞቱ ከመጋቢት 04/1990 ጀምሮ ከ10 ዓመት በኋላ የቀረበ ክስ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት የተነሣውን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ ቢያልፈውም ይርጋን በተመለከተ ግን ተቀባይነት ያለው ተቃውሞ መሆኑን በመግለጽ የቀረበውን ክስ በዚሁ በይርጋ ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካቾች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡



www.chilot.me

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ነሐሴ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በ4 ገጽ በተጻፈ አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃቸውን ከያዙ በጥቂት ወራት ውስጥ ያቀረቡት ክስ በመሆኑ ተጠሪ ተሰጠኝ የምትለው በስጦታ በመሆኑ የተደረገው ደግሞ መጋቢት 04 ቀን 1993 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋ ጊዜ ከዚህ ጀምሮ ሲቆጠር 10 ዓመት ያልሞላው በመሆኑ እና ተጠሪም በይዞታቸው ስር አደረጉ እንኳ ቢባል ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በ2 ገጽ የተጻፈ የመልሣቸዉ ፍሬ ሃሣብ የአመልካቾች አውራሽ ከሞቱ ከ10 ዓመት በኋላ የቀረበ ክስ በመሆኑ በይርጋ ውድቅ ይሆናል፡፡ የስጦታው ውል ለውርስ ጥያቄ የይርጋ መቁጠሪያ መነሻ ጊዜ ሊሆን አይችልም እና ወራሽነታቸውን ያረጋገጡበት ቀንም እንደ ይርጋ መቁጠሪያ መነሻ ሊያገለግል ስለማይችል የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካቾች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡ በግራቀኙ መካከል የነበረው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን ከተነሱት ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ፡-

አመልካቾች ያቀረቡት የውርስ ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም የሚለው ጭብጥ ተይዞ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የአመልካቾች አውራሽ የሞቱት መጋቢት 04 ቀን 1990 ዓ.ም እንደሆነ፣ አመልካቾች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት በ2000 ዓ.ም ውስጥ እንደሆነና ክስ ያቀረቡት ደግሞ መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም እንደሆነ አላከራከረም፡፡

የአመልካቾች አውራሽ በሞቱበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው የቤተሰብ ህግ በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 683 እስከ 689 ጋብቻ ከተጋቢዎቹ በአንዱ መሞት ሊፈርስ እንደሚችልና መብት አለን ባዮች የድርሻቸውን መጠየቅ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም እስከ መቼ ድረስ መጠየቅ እንደሚገባቸው ስለማያመለክት ክርክሩም ደግሞ በወራሾች መካከል ባለመሆኑ በፍ/ብሔር ህግ ኑንቀጽ 1677/1/ እና 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ መታየት እንዳለበት ከዚህ በፊት በመዝ.ቁ. 17937 እና ሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ጊዜው መቆጠር ያለበት አውራሻችን ነው የተባለው ሰው ከሞተበትና ጋብቻውም በዚያው ምክንያት ከላይ እንደተመለከተው ከፈረሰበት ጊዜ ጀምሮ መሆን እንዳለበት ከላይ የተመለከተው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች እና የይርጋ ዘመን አቆጣጠርን የተመለከቱ የህግ ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም የይርጋ ዘመን አቆጣጠርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ከመቼ መቆጠር እንደሚጀምሩ በምንመለከትበት ጊዜ በአንደኛው ተጋቢ መሞት ምክንያት ከፈረሰ ጋብቻ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ጋብቻው በሞት ከፈረሰበት ዕለት ጀምሮ መሆን እንዳለበት ከመውረስ መብት አኳያ ሲታይም በፍ/ብ/ህግ ቁ. 826/1/ መሠረት ውርሱ የሚከፈተው የአመልካቾች አውራሽ በሞቱበት ቦታና ቀን እንደሆነ ስለሚደነግግ እና የይርጋ ዘመን መቀጠር የሚጀምረው በፍ/ብ/ህግ ቁ. 5 እና 1846 መሠረት መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ የይርጋው ዘመን መቆጠር ያለበት የአመልካቾች አውራሽ ከሞቱበት ቀን ጀምሮ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቱም የአመልካቾች መብት ሊበስል ወይም መጠየቅ ይችላሉ የሚባለው ወይም ንብረቱ በዕጅ ይገኛል የተባለው ሰው የማስረከብ ግዴታ አለበት የሚባለው አውራሻቸው ከሞቱበት ቀን ጀምሮ ስለሚሆን ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የአመልካቾች አውራሽ ከሞቱ ከ10 ዓመታት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ከመሆኑም በላይ አመልካቾች የይርጋው ዘመን መቆጠር ያለበት ወራሽነታችንን ካረጋገጥንበት ቀን ጀምሮ ነው



www.chilot.me

ወይም ደግሞ ለተጠሪ ስጦታ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የህግ መሠረት የላቸውም ብለናል፡፡
በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 50871 ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 65579 በቀን 16-2-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት የውርስ ክስ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ከፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የመጣው የመ/ቁ. 65579 ወደ መጣበት ይመለስ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60725

ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አቶ አብርሀ የኒላሽት - ጠበቃ ፍሰሀ ሐጐስ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አበባ ዘመን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የተጀመረው በግራ ቀኙ የቀረበውን የንብረት ክፍፍል ጥያቄን በሚመለከት ነው፡፡ ለአሁኑ ቅሬታ መሠረት የሆነው በአመልካች ስም ያለው በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 የቤቱ ቁ. 708 የሆነ መኖሪያ ቤት ሲሆን ተጠሪ የጋራ ንብረታችን ነው በማለት የተከራከረች ሲሆን አመልካች በበኩሉ በቀን 05-11-80 ዓ.ም በስሜ የተመዘገበና የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት አሁን ያለውን ቤት ሰርቶ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የምኖርበት በመሆኑ ከተጠሪ ጋር ደግሞ በ1993 ዓ.ም በባህላዊ ጋብቻ የተገባን መሆኑና በዚህ ጋብቻ ውልም የጋራ ንብረት ያልተደረገና በድጋሚ ተደርገ የተባለው የጋብቻ ውል እኔ ታምሜ በአማኑኤል ሆስፒታል በነበርኩበት ወቅት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሏ የተባለው ቤት ከጋብቻ በፊት 3 ክፍል ጭቃ ቤት የነበረ መሆኑ ከተጋባን በኋላ የኮርኒስ ስራ በር ቀለም እንዲሁም 10 ቅጠል ቆርቆሮ ጨምረን በጋራ እድሣት ሰርተናል፣ አንድ መኝታ እና አንድ ሣሎን ክፍል እንዲሁም አንድ 4x5 ክፍል ቤት ሰርተናል ፣ በኋላም በ1999 ዓ.ም በተደረገ የጋብቻ ውል የጋራ ንብረት ያደረግንና ይሄው የጋብቻ ውል በክብር መዝገብ ሹም ቀርቦ የተመዘገበ በመሆኑ የጋራ ንብረታችን ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ ለዚህ ቅሬታ መነሻ የሆነውን ቤት እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ የጠየቀ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡



www.chilot.me

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደተመረመረውም ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ /ጭብጥ/ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት ግራ ቀኙ ከመጋባታቸውም በፊት በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በተመሣሣይም በግራ ቀኙ መካከል ቀድሞ የተደረገው የጋብቻው ውል ማለትም በቀን 18-12-1992 ዓ.ም የተደረገ ስለመኖሩና በዚህም የጋብቻ ውል የተመለከተው መኖሪያ ቤት የጋራ ንብረት ያልተደረገ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በግራ ቀኙ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ታህሣስ 12 ቀን 1999 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የጋብቻ ውል ሲሆን የተጠሪ ክርክር በዚህ ጋብቻ ውል መሠረት በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 19/20 የቤት ቁጥሩ 708 የሆነ ቤት የጋራ ንብረት እንዲሆን ተስማምተናል የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ደግሞ ከላይ በድጋሚ ተደረገ የተባለውን የጋብቻ ውል የማያውቁ መሆናቸውን ፣ በወቅቱ የአዕምሮ በሽተኛ ሆኖ አማኑኤል ሆስፒታል ሲታከም የነበረ መሆኑን ፣ ተጠሪ ራሷ አዘጋጅታ ያቀረበችው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የተነሳውን የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸው ከፌዴራል የቤተሰብ ህግ ጋር ስንመረምር በእርግጥ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992 አንቀጽ 47/1-3/ ስንመለከት ቀድሞ የተደረገውን የጋብቻ ውል ማሻሻል እንደሚቻል የሚደነግግ ሲሆን ለፍ/ቤት ቀርቦ የተደረገው የጋብቻ ውል መሻሻል የቤተሰብን ጥቅም የማይጐዳ ከሆነ ሊጸድቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይሄ የተሻሻለው የጋብቻ ውል ለፍ/ቤት ቀርቦ ማጽደቅ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል በዚህ አንቀጽ ስር መልስ የሚሰጥ ባይሆንም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 73 ጋር አያይዘን ስንተረጉም ፍ/ቤት ካላጸደቀው በስተቀር ተቀባይነት የለውም የሚለውን ትርጉም ይሰጠናል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ከላይ የተመለከተው በግራ ቀኙ መካከል በድጋሚ ተደርገ የተባለው የጋብቻ ውል በክብር መዝግብ ሹም ፊት ቀርቦ የተመዘገበ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ቢሆንም ከላይ በተመለከተው አግባብ ለፍ/ቤት ቀርቦ የጸደቀ ስለመሆኑ ተጠሪ ያስረዳች ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ታህሣስ 12 ቀን 1999 ዓ.ም በድጋሚ ተደርገ የተባለው የጋብቻ ውል ከላይ በተመለከተው ምክንያት ሊጸና አይችልም ቢባልም በተጠሪ በኩል ተነስቶ የነበረው ሌላው ክርክር መኖሪያ ቤቱ በተጠሪ ስም የነበረና ሶስት ክፍል ጭቃ ቤት የነበረበት መሆኑን ሆኖም ከተጋቡ በኋላ ለዚሁ ቀድሞ ለነበሩት ክፍሎች አጠቃላይ እድሣት ያደረጉ ከመሆኑም በላይ በተጨማሪ ከሶስት የማያንሱ ክፍሎችን ጨምሮ የሰሩ መሆናቸዉን የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ደግሞ ውጪ አገር ሆኖ በላከው ገንዘብ እንደተሰሩ ተከራክሯል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ የሚያነሷቸው ክርክሮች ባላቸው ማስረጃ ተጣርተው ያልተወሰነ በመሆኑ እና የግራ ቀኙ በመኖሪያ ቤቱ ላይ ያላቸው መብት ተገቢው መጣራት ከተደረገ በኋላ መወሰን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም ግራ ቀኙ ሲጋቡ የተጠቀሰው መኖሪያ ቤት የሚገኝበት አጠቃላይ ይዘት እንዴት እንደነበር ፣ አብሮ ባሉበት ጊዜ የተደረገው መሻሻል ምን ያህል እንደሆነ እና ክሱ ሲቀርብ የመኖሪያ ቤቱ አጠቃላይ ይዘት በግራ ቀኙ ማስረጃ ተጣርቶ በቤቱ ላይ የግራ ቀኙ መብት ምን ይሆናል? የሚለውን የበታች ፍ/ቤቶች መወሰን ሲገባቸው ማለፋቸው መሠረታዊ የሆነ የሙግት አካሄድ መርሆቹን የተከተለ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁ መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 92430 ነሐሴ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 155334 በቀን 29-7-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 የቤት ቁ. 708ን በተመለከተ የተሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው በተመለከተው መሠረት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰናል፤ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ.መ.ቁ 61788

ሰኔ 14 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለማ

**ተጠሪ፡-** ታፈሰ ተሰማ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን ፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተደረገውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሃዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ሲሆን ፣ ፍ/ቤቱ በሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከተመለከተ በኋላ የንብረት ክፍፍሉ በዕጣ እንዲሆን በማዘዝ አከፋፍሎአል በወጣው ዕጣ መሠረት ለአመልካች የደረሰው ቤት ለተጠሪ ከደረሰው ቤት በዋጋ የሚበልጥ ነው በማለትም አመልካች ብር 31,585.65 ለተጠሪ ትክፈል ብሎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሣኔው ባለመስማማት ለሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረብዋ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን ፣ ችሎቱ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የንብረት ክፍፍሉ የተመራው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ለክፍፍል የቀረቡት ንብረቶች በፍቺ የተለያዩት ባልና ሚስት /ተከራካሪዎች/ የጋራ ሃብት ናቸው፡፡ ከዚህ ደግሞ በቅድሚያ መገንዘብ የሚቻለው ሁለቱም በሃብቶቹ ላይ እኩል የሆነ መብት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመብት ረገድ አንደኛው ከሌላኛው አያንስም ወይም አይበልጥም ከተባለ ደግሞ የክፍፍሉ ሥርዓትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው



www.chilot.me

መከናወን ያለበት፡፡ የእኩልነት መርሁ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 35/1/ እና/2/ የተቀመጠ ሲሆን ፣ ቀጥለው በወጡት የፌዴራል እና የክልል ቤተሰብ ሕጎችም እንደዚሁ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የቤተሰብ ሕግ "የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 " ሲሆን የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ለሁለቱም እኩል እንደሚከፋፈል በአንቀጽ 101/1/ ደንግጎአል፡፡ በእርግጥ ባልና ሚስቱ ሃብታቸውን በስምምነት ለመከፋፈል ከፈለጉና ከቻሉ ሕጉ ይህን ስምምነታቸውን እንደሚያከብርላቸውም ተመልክቶአል፡፡ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ በስምምነት መከፋፈል ካልቻሉ/ካልፈለጉ / የክፍፍሉ ሥርዓት እንዴት ሊከናወን ይችላል? የሚለው ነው፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሰው የቤተሰብ ሕግ የክፍፍል ሥርዓቶቹን በቅደም ተከተል በዝርዝር አስቀምጦአል /በአንቀጽ 102/2/ እና በአንቀጽ 103/1/ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በአይነት ሊከፋፈሉ የሚችሉ ናቸው አልተባለም፡፡ ችግሩ የተፈጠረው በአይነትም ለመከፋፈል ሁለቱም ወገኖች ስምምነት ላይ ባለመድረሳቸው ነው፡፡ አመልካች እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ እየተከራከረች ያለችው በእጣ ደርሶሻል የተባልኩት ከስምምነቴ ውጪ ነው፡፡ በዕጣ የደረሰኝ ነው የተባለውን ንብረት ብወስድ እጎዳለሁ፡፡ ተጠሪ አልተጎዳሽም የሚል ከሆነ ለኔ ደርሶአል የተባለውን ንብረት ብር 31,585.65 በመክፈል ጠቅልሎ ይውሰድ ፤ እኔ ደግሞ ለእሱ የደረሰውን ልውሰድ በማለት ሲሆን፣ ተጠሪ ግን በዚህ አይስማማም ፡፡ እየተከራከረ ያለው አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ነው፡፡ ከዚህም በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው በንብረት ክፍፍሉ ግራ ቀኝ ወገኖች አለመስማማታቸውን ነው፡፡ እጣ እንዲወጣ ያዘዘውም ፍ/ቤቱ /በራሱ አነሳሽነት / እንጂ ተከራካሪ ወገኖቹ ክፍፍሉ በዕጣ ይሁን ብለው ስለተስማሙ እንዳልሆነም ከተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት ጭምር ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ፍ/ቤቱ ወደ ዕጣ አማራጭ የሄደው ግራ ቀኝ ወገኖች በስምምነት ለመከፋፈል ባለመቻላቸው እና ንብረቱም በአይነት የማይከፋፈል በመሆኑ እንደሆነ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰጠው ውሣኔ ተመልክቶአል፡፡

በንብረቱ ክፍፍል ረገድ ችግር ሲያጋጥም ማለትም ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሳይቻል የቀረ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን እንዲከፋፈል እንደሚደረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 103/1/ ግልጽ ባለሁኔታ ተመልክቶአል፡፡ ይህ ድንጋጌ ንብረቱ በዕጣ የሚከፋፈልበትን የክፍፍል ሥርዓት በአማራጭ አላስቀመጠም፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ከሕጉ በመውጣት ውሣኔ መስጠት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ሕጉ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው /አንቀጽ 103 / ቀደም ሲል የተመለከትነውን የእኩልነት መርህን ግንዛቤ ውስጥ በማግባት እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በመሆኑም የንብረቱ ክፍፍል በዕጣ እንዲሆን በማለት የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሃዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ 20692 በ28/10/2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፣ የሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 08513 በ8/11/2002 ዓ.ም የሰጠው



www.chilot.me

ትዕዛዝ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ 44349 በ27-1-2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች እና ተጠሪ ንብረቱን መከፋፈል ያለባቸው በቤተሰብ ሕጉ በተዘረጋው የክፍፍል ሥርዓት መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60691

ሐምሌ 12 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ገዛችን ገብሩ - ከጠበቃቸው ከአቶ ተክለ አብ ስዩም ጋር ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ዓለምነሽ በየነ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የተጀመረው በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኗ የሰበር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ፍሬ ቃልም ከሟች አቶ ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ጋር ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ እንደ ባልና ሚስት አብረን ለአምስት ዓመታት ስንኖር ህፃን ገሊላ ፀጋዬ የተባለችውን ልጅ የወለድን ሲሆን በጋራ ከሟች ጋር የነበረንን ኮድ 3.03110 የሆነውን የጭነት መኪና የሟች ሚስት ነኝ የሚሉት 2ኛ ተከሳሽ ይዘው ስለሚገኙ ድርሻዬን እንዲያካፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር 2ኛ ተከሣሽም /ያሁኗ አመልካች/ በክሱ በሰጡት መልስ ከሳሽ ከሟች ጋር እንኳን ለአምስት ዓመታት ቀርቶ ለወራት እንኳን እንደ ባልና ሚስት አልኖሩም፡፡ ከሳሽ ለመካፈል የጠየቁትን መኪና እኔና ባለቤቴ የነበረንን ኮድ 3.50133 የሆነውን አይሱዙ መኪና ሸጠን የገዛነው በመሆኑ ከሳሽን የሚመለከት አይሆንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም ከሳሽ በማስረጃነት ያቀረቡትን በመ/ቁ 20488 ሰኔ 09 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠውን ውሳኔ ከመረመረ በኋላ በዚህ በማስረጃነት በቀረበው ውሳኔ ከሳሽ ከ1991 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ከሳሽና ሟች ፀጋዬ ተክለሀይማኖት በተከራዩት ቤት እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ እንደነበር ሆኖም ግን ጋብቻ ይፈጽሙ አይፈጽሙ እንደማያውቁ ምስክሮች ያስረዱ ስለሆነና ከሳሽ የጋራ ሀብት ነው በሚል የጠየቁት ኮድ 3.03110 የሆነው መኪና የተገዛው ጥቅምት 21 ቀን 1993 ዓ/ም መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በማረጋገጡ መኪናው ከሳሽና ሟች እንደ ባልና ሚስት አብረው በነበሩበት ጊዜ የተገዛ ነው በማለት በመኪናው ከሳሽ እና 2ቱም የሥር ተከሳሾች እያንዳንዳቸው 1/3ኛ ድርሻ አላቸው ብሏል፡፡

በዚህ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሥር 2ኛ ተከሳሽ ይግባኝ ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ከፍተኛው ፍ/ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት መልስ ሰጪዋን መጥራት ሳያስፈልግ የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት ይግባኝ ባይዋን አሰናብቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ሲሆን በዋናነት አመልካች ያቀረቡት ቅሬታም ተጠሪዋ ክርክር ባስነሳው መኪና መብት ሳይኖራቸው የአመልካች ድርሻ ከመኪናው 1/3 ብቻ እንዲሆን መወሰኑ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ጋር እንደ ባልና ሚስት በኖሩበት ወቅት አከራካሪው መኪና የተገዛ መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ባቀረቡት ክርክር ተጠሪዋ ከመኪናው መብት የላቸውም ሲሉ የተከራከሩት የህግ መሠረት የለውም ብለዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ተጠሪዋና ሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት እንደ ባልና ሚስት ኖረዋል? ወይስ አልኖሩም? የሚለው ጭብጥ በሥር ፍ/ቤት በአግባቡ ተረጋግጧል? ወይስ አልተረጋገጠም የሚለውን ነጥብ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኗ የሰበር ተጠሪ ከሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ጋር እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ እንደነበር በመግለጽ የጋራ ሀብት ነው የሚሉት የጭነት መኪና ድርሻቸው እንዲሰጥ ሲጠይቁ አመልካች ባቀረቡት መልስ ካነሷቸው ነጥቦች አንዱና ዋናው ከሳሽ /ያሁን ተጠሪ/ ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት አልኖሩም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ በዚህ መልኩ ክርክር እስከቀረበ ድረስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተቀበለው የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤትም ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች የተለያዩበትን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ መስጠት ሲገባው በመቃወም አመልካች /የአሁኗ አመልካች/ እና በመቃወም ተጠሪ /ያሁኗ ተጠሪ/ በመዝገብ ቁጥር 20488 የአሁኗ ተጠሪ የሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ሚስት ናቸው ተብሎ በ11/10/96 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ እንዲሰረዝ ክርክር ባቀረቡበት ወቅት የቀረቡት ምስክሮች የአሁኗ ተጠሪና ሟች እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ እንደነበር አረጋግጠዋል በማለት በመ/ቁ 20488 ለተያዘው ጉዳይ ውሳኔ ለማሰጠት የቀረቡትን ማስረጃዎች በዚህ መዝገብ /60691/ በተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንዳላቸው በመቁጠር ፍ/ቤቱ የምስክሮቹን ቃል ለውሣኔው መሠት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘንም፡፡ ይኸውም በመ/ቁ 20488 የክርክሩ ጭብጥ የአሁኗ ተጠሪ የሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ሚስት ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ከተረጋገጠ በኂላ ሚስት አለመሆናቸው ተረጋግጦ በ11/10/96 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተጠሪዋ ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠ ውሣኔ እንዲሰረዝ የተደረገበት ሲሆን በዚህ መዝገብ በተያዘው ጉዳይ ግን ክሱ የቀረበው ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት በመኖራችን የጋራ ሀብት የሆነው መኪና ተካፍሎ ድርሻ ይሰጠኝ በሚል ነው፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪዋ ላቀረቡት ክስ አግባብነት የሌለውን በመ/ቁ 20488 የተሰጠውን የምስክርነት ቃል መሠረት በማድረግ በተጠሪና በሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት መካከል እንደ ባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ መኖር አለመኖሩን በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሠረት ተገቢውን ማጣሪያ ሳያደርጉ ተጠሪዋ ከመኪናው 1/3ኛውን ድርሻ ያግኙ ሲሉ የወሰኑት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡



www.chilot.me

## ው ሳ ኔ

1. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 68308 በቀን 22/8/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 95917 በቀን 29/10/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. በተጠሪዋና በሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት መካከል እንደ ባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ የነበረ መሆኑንና አለመሆኑን የግራ ቀኙን ማስረጃዎች የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሰማ በኋላ ለቀረበው የጋራ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ በተሻሻለው የፌ/የቤተሰብ ሕግ መሠረት ተገቢውን እንዲወስን ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ቤ/መ



www.chilot.me

የሠ/መ/ቁ. 63195

ሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ገረመው ሙሜቻ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አሰፉ ነበበ - ጠበቃ አልማዝ አሰፋ ቀረበች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በአሁንዋ ተጠሪ ክስ አቅራቢነት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካችን የከሰሰችው በቤት ሰራተኛነት ተቀጥሬ በነበረበት ጊዜ አስገድዶ ደፍሮኝ በማርገዜ ልጅ ወልጃለሁ፡፡ ልጅቷን አምኖ ሊቀበለኝ አልቻለም፡፡ ስለዚህም የህፃን መታደል ወላጅ አባት መሆኑ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሳሽ ክሱን የመሰረተችው ተደፈርኩ ካለችበት ጊዜ ከአሥር ዓመት በላይ ቆይታ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ በኔ ቤት የቆየችው ለአንድ ወር ተኩል ያህል ከመሆኑም በላይ፣ በ85 ዓመት ዕድሜዬ ለመድፈር የአካልም ሆነ የሞራል ብቃትም የለኝም /አልነበረኝም/፡፡ ከሣሽ በእኔ ስለመደፈርዋ ማስረጃ የላትም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም በዚህ መልክ የቀረበለትን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች ህፃን መታደል አባት ነው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 8 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የሥር ፍ/ቤቶች ወደ ውሳኔው ለመድረስ የተከተሉት አካሄድ /የክርክር አመራር/ አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች እና ተጠሪ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡



www.chilot.me

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ ክስ ስትመሰርት ሰዎችን በምስክርነት የቆጠረች ሲሆን፣ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራ እንዲደረግለትም ስለመጠየቅዋ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ከተደረገበት መዝገብ ጭምር ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ አመልካችም በበኩሉ ሰዎችን በመከላከያ ምስክርነት ቆጥሮ ማሰማቱን ተመልክተናል፡፡ ክሱን የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ምስክሮች ከመስማት አልፎ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራ እንዲደረግ አላዘዘም፡፡ በዚህ ረገድ የሰጠው ምክንያትም አመልካች የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ማድረግ እንደማይችል እና እንደማይገደድ ገልጾ መልስ ሰጥቶአል የሚል እንደሆነ ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ /ክርክር/ በዋነኛነት የተመሰረተውም በዚሁ ነጥብ ላይ ነው፡፡ ከሣሽ ተጠሪ ሆኚ ሳለ በአስረጂነት የጠቀሰችው የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ በኔ በተከሣሽ ወጪ ይደረግ መባሉ ትክክል አይደለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ተጠሪ በበኩልዋ ለአቤቱታው በሰጠችው መልስ አባትነቱን በምስክር ያስረዳሁ ስለሆነ እና አቅምም ስለሌለኝ የምርመራው ወጪ መሸፈን ያለበት አባት አይደለሁም የሚለው አመልካች ነው በማለት ተከራክራለች፡፡

ተጠሪ ከሣሽ እንደመሆንዋ እንደ ክሱ ያስረዱልኛል ያለቻቸውን ምስክሮች እና የሕክምና ማስረጃ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 223 በተደነገገው መሠረት በዝርዝር ስለማቅረቧ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ከተደረገበት መዝገብ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰማው ምስክሮችን ብቻ እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ከማስረጃዎችዋ አንዱ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራ እንደሆነ በማስረጃ ዝርዝር መግለጫዋ ገልፃ ሳለ ፍ/ቤቱ ግን በዚህ ረገድ የተጠየቀውን ማስረጃ አልሰማም፡፡ ማስረጃውን ያልሰማበትን ሕጋዊ ምክንያት ያለው ስለመሆኑም አልገለፀም፡፡ ምክንያት ያደረገው አመልካች /በወቅቱ ተከሣሽ/ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለሁም ወይም አልገደድም ብሎአል የሚል ነው፡፡ ክርክር የተደረገበት መዝገብ አስቀርበን እንዳየነው ፍ/ቤቱ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ ወይም የምርመራው ውጤት ይቀርብለት ዘንድ የሰጠውን ትዕዛዝ አላገኘንም፡፡ አመልካች ለክሱ የሰጠው መልስ እንዳየነው ደግሞ በራሴ ገንዘብ /ወጪ/ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ለማድረግ አልገደድም የሚል ግልጽ የመከራከሪያ ነጥብ ያለው ነው፡፡ አመልካች ይህን የመከራከሪያ ነጥብ ሊያነሳ የቻለው ተጠሪ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራው በተከሣሽ /በአሁኑ አመልካች/ ወጪ ይደረግልኝ በማለት በማስረጃ ዝርዝር መግለጫዋ ላይ በመግለጽዋ /በመጠየቅዋ/ እንደሆነም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ፍ/ቤቱ አመልካች የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ የደረሰውም ከዚህ በመነሳት ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ አካሄድ የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው ተጠሪ ከሣሽ እንደመሆንዋ እንደ ክስ አቀራረብዋ የሚያስረዳላትን ማስረጃ አቅርባ የማሰማት ግዴታ /ሸክም/ አለባት፡፡ የዲ.ኤን.ኤ /የህክምና ማስረጃ/ እንደ ሌሎቹ ማስረጃዎች አንዱ የተጠሪ ማስረጃ ሆኖ በመቆጠሩ ማስረጃው ቀርቦ ይሰማ ዘንድ የማድረግ ግዴታ የተጠሪ እንጂ ማስረጃውን በመከላከያነት ያልቆጠረው የአመልካች ግዴታ ሊሆን አይችልም፤ አይገባምም፡፡ ከሣሽ የሆነው ወገን የከሣሽነት ቃሉን በመስጠት መመሥረት የሚገባውን ጭብጥና ያቀረበውን ክስ የሚደግፍለትን ማስረጃ እንደሚያቀርብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 259/1/ መመልከቱን መገንዘቡም ተገቢ ነው፡፡ የሕክምና ማስረጃው የተቆጠረው በኔ ቢሆንም፤ መቅረብ ያለበት በአመልካች ወጪ ነው የሚለው የተጠሪ ክርክር ሲታይ ከመሠረታዊ የማስረጃ ሕግ መርህ የወጣ እና ከሳሽ እንደሚያቀርብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 259/1/ የተቀመጠውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላም በኩል የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ የሕክምና ዘዴን /ሳይንሳዊ/ መሠረት

በማድረግ የሚከናወን በመሆኑ የአስረጂነት ዋጋው ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ ፍ/ቤቱም በሂደቱ መጨረሻ እውነት ላይ መድረስ ሲገባው ማስረጃውን ሳይሰማ የሚያልፍበት በቂ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወደ ውሳኔ ያመራው የክርክሩ እና የማስረጃ አሰማም ሂደቱን በሕጉ አግባብ ሳያጠናቅቅ ነው ለማለት ችለናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሣሣይ መንገድ በመከተል ውሳኔውን ከማፅናት አልፎ ማስረጃውን አልሰማም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በክርክር አመራር እና ማስረጃ አቀባበል ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 16229 ሚያዝያ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 94681 ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የሆነችው እና ማስረጃውን የቆጠረችውም ተጠሪ በመሆንዋ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራው መደረግ ያለበት በተጠሪ ወጪ ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራውም በተጠሪ ወጪ እንዲደረግ ትዕዛዝ በመስጠት ውጤቱን ካስቀረበ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳይ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343/1/ መሠረት ወስነናል፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 43988

መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

ዓልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሰኒያ ሼካ ተማም - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ በላይነሽ ማቴቦ

2. አቶ ሽሪፍ አህመድ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ ወንድ ከሁለት ሴቶች ጋር ጋብቻ ፈጽሞ ሲኖር ከቆየ በሁዋላ ከአንደኛዋ ጋር በፍቺ ሲለያይ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚስተናገድበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ በጉራጌ ዞን መስቃን ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የመሠረቱት ክስ ይዘት ባጭሩ ሲታይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሲኖሩ በእንሲኖ ከተማ ውስጥ አንድ ክፍል ቆርቆሮ ቤት ማፍራታቸውንና የገጠር መሬት አራት ጥማድ የነበራቸው መሆኑን ገልፀው እነዚህን ንብረቶች 2ኛ ተጠሪ እንዲያካፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም 1ኛ ተጠሪ ጋር የተጋቡት በ1988 ዓ.ም ሆኖ እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ቆይታ መሄዷንና በ1994 ዓ.ም ሌላ ጋብቻ አለኝ በማለቷ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ፈጽማ የነበረችው ጋብቻ እንዲፈርስ መወሰኑን በጋራ ያፈሩት ንብረት አለመኖሩን ንብረቶቹ የተፈሩት ከአሁኗ አመልካች ጋር መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ወደ ክርክሩ በጣልቃ ገብነት ለመግባት ማመልከቻ አቅርበውና የስር ፍርድ ቤት ፈቅዶላቸው ባቀረቡት ክርክር ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ ፈጽመው ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ያፈሩት አመልካች እንጂ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ያለመሆናቸውን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የገጠር መሬትን በተመለከተ የጋራ ባለይዞታዎች የአሁኗ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ መሆናቸውን የቆርቆሮ ቤቱን በተመለከተ ግን የጋራ ባለሀብቶች ተጠሪዎች ስለሆኑ እኩል ሊካፈሉ የሚገባቸው መሆኑን ገልፆ ወስኗል፡፡ በዚሁ የቆርቆሮ ቤቱን በተመለከተ በተሰጠው የውሣኔ ክፍል አመልካች ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉት ፍ/ቤቶች ይግባኝና የሰበር



www.chilot.me

አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ በ1980 ዓ.ም በመመስረት አከራካሪውን ቤት ስለማፍራታቸው ማስረጃ አቅርበውና አረጋግጠው ባለበት ሁኔታ ንብረቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የአመልካችና 2ኛ ተጠሪ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ በእንሲኖ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት የተሰራ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ እንዳለ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል ስለሆነም ቤቱ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ጋብቻ ፀንቶ እያለ የተሰራ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ንብረቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካችና የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ሕጋዊ ጋብቻ በ1980 ዓ.ም መሥርተው እስካሁንም አንድ ላይ ያሉ መሆኑን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ከአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ጋር በ1988 ዓ.ም ጋብቻ መሥርተው እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ከኖሩ በኂላ 1ኛ ተጠሪ ጥለው በመሄድ በሌላ ቦታ ቆይተው በ1994 ዓ.ም የፍቺ ጥያቄ አቅርበው መለያየታቸውን በእንሴኖ ከተማ ውስጥ ይገኛል በተባለው ቦታ ቀድሞውንም የሳር ቤት የነበረና ይህ ቤት ፈርሶ 2ኛ ተጠሪና አመልካች አንድ ላይ ሁነው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት መስራታቸው በማስረጃ መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት አይገባቸውም በማለት ሊወስን የቻለው ቤቱ የተሰራበትን ቦታ የያዙበትን መንገድና መቼ እንደያዙ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን አላስረዱም፣ ንብረቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የጋራ ስለማድረጋቸውም የሚያሣይና በፍርድ ቤት የተመዘገበ የፅሑፍ ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ከሣሽ ክስ ሊመሠርት የሚገባው ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ለክሱ ምክንያት በሆነው ነገር ላይ ከሣሹ መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ የከሣሽ እንጂ የተከሣሽ ሊሆን አይገባም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት መብት የላቸውም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የተወሰነው 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት የሌላቸው ስለመሆኑ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ ምስክሮች አልተመሰከረም በሚል ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ቤቱ የተሰራው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በጋብቻ ፀንተው በነበሩበት ጊዜ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን የአመልካችን ክርክር ውድቅ ሊያደርግ የቻለው ቦታው በምን መልኩ እንደተያዘና መቼ እንደተያዘ እንዲሁም ቤቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የጋራ ስለመደረጉ በፍርድ ቤት የተመዘገበ ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባዶ ቦታ ባለቤትነቱ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝቦች

ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገመንግሥትና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተረጋገጠ ሲሆን አንድ ሰው በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት በሕጉ አግባብ የተሰጠው የባለይዞታነት መብቱ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው በተገቢው መንገድ ባለይዞትነቱን ሲያረጋግጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ የነበራቸው ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን አከራካሪው ንብረት ግን በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ የተሰራ እንጂ በ1ኛ ተጠሪና በ2ኛ ተጠሪ የተሰራ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም ጋብቻቸውን በ1990 ዓ.ም ትተው መሄዳቸውና አከራካሪው ቤትም በዚሁ ወቅት ስለመሰራቱ መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያሣያል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ጋብቻቸውን በተገቢው መንገድ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያፈረሱት በ1994 ዓ.ም ቢሆንም ለአከራካሪው ቤት መሰራት ግን ያደረጉት አስተዋጽኦ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ በእርግጥ ጋብቻው በሕጉ አግባብ ሣይፈርስ የተፈራ ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ነጥብ ነው፡፡ ሆኖም ጋብቻው በተገቢው መንገድ ሣይፈርስ ጋብቻውን ትቶ የሄደ ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት ሌላው ተጋቢ ያፈራውን ንብረት የጋብቻ ውጤት ነው በማለት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ ንብረቱ በዚህ ሁኔታ የተፈራ ስለመሆኑ የተረጋገጠ የሆነ እንደሆነ ጋብቻውን ትቶ የሄደ ተጋቢ ንብረቱ የጋራ ነው የሚለውን የሕግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም፡፡ ለንብረቱ መፈራት ምክንያት የሆነው ተጋቢ የንብረቱ የግል ባለሀብት ይሆናል እንጂ ምንም አስተዋጽኦ ያላደረገ ተጋቢ እንዲካፈል ማድረግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/1/ስር የተቀመጠውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚጥስና የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ የቤተሰብ ሕጉ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ ንብረት የጋራ ነው የሚል ሕጋዊ ግምት የወሰደውም ተጋቢዎች ለንብረቱ መፈራት የየራሣቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ታሣቢ በማድረግ ነው ተብሎም ይገመታል፡፡ ይህ ግምት ግን በተቃራኒ ማስረጃ የማይስተባበልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ጋብቻው በሕጉ አግባብ ሣይፈርስ አንደኛው ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት ቀሪው ተጋቢ ሌላ ሰው አግብቶ ንብረቱን ማፍራቱ በሚገባ እስከተረጋገጠ ድረስ ጋብቻውን ትቶ የሄደ ተጋቢ በሌላ ጊዜ በመምጣት በሌለበት የተፈራውን ንብረት ልካፍል በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ በሕገ መንግሥቱ ስለንብረት ማፍራት መብት የተደረገውን ጥበቃ እና በቤተሰብ ሕጉም ስለባልና ሚስት የጋራ ንብረት የተዘረዘረትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መሠረት ያደረገ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች አከራካሪውን ንብረት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት ሁኖ እያለ ድርሻ የላቸውም የተባለው ያላግባብ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በእንሴኖ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቆርቆሮ ቤት እኩል ሊካፈሉ የሚገባቸው ተጠሪዎች ናቸው በማለት የሰጡት የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እኩል መብት ያላቸው አመልካች እንጂ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ /ወ/ሮ በላይነሽ ማተቦ/ አይደሉም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ተ.ወ የማየነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

*የሰ/መ/ቁ. 65621*

*ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም*

**ዳኞች**፡- ሐጕስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች**፡- 1. ወ/ሮ ታደለች መንግስቱ - ቀረበች

2. ኢሣያስ ሐለፎም - ቀረበ

3. ወ/ሪት ረድኤት ሐለፎም

4. ወ/ሮ ገነት ሐለፎም

5. ያዕቆብ ሐለፎም

**ተጠሪ**፡- - የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የሚስትነት እና የወራሽነት ማረጋገጫ ይሰጠን በማለት የቀረበውን አቤቱታ /ጥያቄ/ የሚመለከት ነው፡፡ አቤቱታው የቀረበው በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፣ ፍ/ቤቱ ሟች /የ1ኛ አመልካች ባለቤት እና የሌሎቹ አመልካቶች አባት/ ከዘጠኝ አመት በፊት ወደኤርትራ ተመልሶ የኤርትራ ነዋሪ መሆኑን አረጋግጫለሁ /ተገንዝቤአለሁ/ በማለት አቤቱታውን ሣያስተናግድ ቀርቶአል፡፡ በዚህ ብይን ላይ አቤቱታ የቀረበላቸው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠ/ፍ/ቤትም ብይኑ ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካቾችን ይግባኝ ሰርዘዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካቾች የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን አቤቱታው ከቀረበበት ብይን እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ በሰበር ችሎቱ ሊመረመር ይገባል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ ሟች የኤርትራ ነዋሪ ናቸው በማለት የአመልካቾች ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት የሰጠው ብይን እንዳየነው የአመልካቾች ጥያቄ ማስረጃ ይሰጠን የሚል ነው ቢባልም ፣ የጠቀሱት ድንጋጌ /ህግ/ ግን በፍ/ብ/ህግ ቁ. 826/1/ የተመለከተው ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የአመልካቾች ኀላፊነት ከሟች ጋር ያላቸውን ግንኙነት /ዝምድና/ ተረጋግጦ ውርሱ እንዲከፈትላቸው መሆኑን ነው፡፡ በእርግጥም ሟች የሞተው



www.chilot.me

ኤርትራ ውስጥ እንደሆነ በአቤቱታቸው ላይ ገልጸዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህን መሠረት በማድረግ ብቻ ሟች ዋና መኖሪያው ስፍራ ኤርትራ ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በበኩላችን እንደምናየው ግን ሟች ወደ ኤርትራ ሄዶ ሣይመለስ እዛው በመሞቱ ብቻ ዋና መኖሪያው ስፍራ ኤርትራ ነው ወደሚለው ብቸኛ መደምደሚያ መድረሱ ትክክል አይደለም፡፡

ከአመልካቾች አቤቱታ መገንዘብ እንደቻልነው ሟች በመደበኛነት ሲኖር የነበረው በሐረር ከተማ ውስጥ ከአመልካቾች /ሚስቱ እና ልጆቹ/ ጋር ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ወታደር እንደነበር ፣ ከወታደርነት በጡረታ ከተገለለ በኋላም በመካኒክነት ስራ በግሉ ተሰማርቶ ከቦታ ወደቦታ እየተዘዋወረ ሲሰራ እንደነበር ወደ ኤርትራ የሄደውም በዚሁ የመካኒክነት ስራ ለመስራት ሲሆን ፣ ጊዜውም በየካቲት ወር 1990 ዓ.ም እንደሆነ ፣ በኋላ ወደቤተሰቦቹ /ሐረር/ ሊመለስ ያልቻለው በግንቦት ወር 1990 ዓ.ም በተነሣው የድንበር ግጭት /ጦርነት/ ምክንያት መውጣት ባለመቻሉ እንደሆነ ፣ ዜግነቱም ኢትዮጵያዊ እንደሆነ አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት ገልጸዋል፡፡

የስር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታ እውነት ስለመሆን አለመሆናቸው ለማጣራት ስለመሞከራቸው በብይኑ አልተገለጸም፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው ለሰጡት ብይን ዋና መሠረት ያደረጉት ሟች ወደ ኤርትራ ከሄደ በኋላ ሣይመለስ እዛው ሞቶአል የሚለውን ፍሬ ነገር ብቻ እንደሆነም ነው ለማየት የቻልነው፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድ እንዳለ ተቀባይነት ይኑረው ቢባል ለስራ ወይም ለተለያዩ ምክንያቶች ከአገራቸው ወጥተው ሣይመለሱ ሊሞቱ በሚችሉት ኢትዮጵያውያን የውርስ አከፋፈት ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል መገመቱ አይከብድም፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁ. 826/1/ የተመለከተው ድንጋጌ፤ በተለይም "…ዋና መኖሪያው ስፍራ…" የሚለው ሐረግ መተርጐም ያለበትም ከዚህ አንጻር እየታየ ሊሆን እንደሚገባ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህን ታስቢ በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ብይን ስናየው ለጉዳዩ አወሣሰን አግባብነት ያላቸው ፍሬ ነገሮች በአግባቡ ሣይጣሩ የተሰጠ ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሐረር ህዝብ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 33899 ህዳር 21 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ የሐረር ህዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 07698 ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና በሐረር ህዝብ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01792 ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የሐረር ህዝብ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካቾች ያቀረቡለትን አቤቱታ በተከፈተው መዝገብ ማሰማቱን እንዲቀጥል ፣ ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያላቸው ናቸው ያላቸዉን ሁኔታዎች እና ሌሎችም ፍ/ቤቱ አግባብነት አላቸው የሚላቸዉን ፍሬ ነገሮች እንዲያጣራ በመጨረሻም ፍሬ ነገሮችን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ.ከ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52407

ኀዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ ውልታ ደስታ ወ/ማሪያም - ወ/ኤያስ እጅጉ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ደጅይጥኑ ደስታ ወ/መሪያም አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እቴቴ ደስታ ጠ/መታሰቢያ ፈቃዱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት አጣሪ እንዲሾም አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በይርጋ ታግዷል ተብሎ መወሰኑን በመቃወም ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት መረዳት እንደተቻለው የመልካቾች እና የተጠሪ አውራሽ ሟች ወ/ሮ በቀለች ደስታ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በ1977 ዓ.ም ሆኖ አመልካቾች የውርስ ንብረት አጣሪ ተሹሞ በተጠሪ እጅ ያለ የውርስ ንብረት ተጣርቶ እንዲቀርብ ለፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም በመሆኑ አቤቱታው ከ22 ዓመታት በኂላ የቀረበ ነው ስትል ተጠሪ ያቀረበችው መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677/1/ እና 1845 መሰረት የ10 ዓመት ጊዜ አልፎበታል ሲል አቤቱታውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት ወደ ስማቸው ያዛወሩት በ1997 ዓ.ም ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ይርጋ አቆጣጠርን በሚመለከት በሥር ፍ/ቤቶች ግምት ውስጥ ያለመግባቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት የሰጡት መልስ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ሟች ከሞቱበት ጊዜ እንጂ ስመ ሐብቱ በተጠሪ ከተዛወረበት ጊዜ ሊሆን እንማይገባ ገልፀው የስር ችሎቱ የሰጠውን ውሳኔ መዝገብ በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡



www.chilot.me

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካቾችም ሆኑ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ በቀለች ደስታ ወራሾች መሆናቸው አላከራከረም፡፡ ሟች ወ/ሮ በቀለች ደስታ የሞቱት በ1977 ዓ.ም ስለመሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ ሆኖ ሳለ የሟች የውርስ ንብረት በተጠሪ ተይዟልና የውርስ ንብረት አጣሪ ይሾምልኝ ሲል አመልካቾች ሥር ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡

እንግዲህ ግራ ቀኙ የሟች ወራሾች መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ የውርስ ንብረት በአንደኛው ወራሽ እጅ ነውና ውርስ አጣሪ ተሾሙ ይጣራልን የሚለውን ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው እስከመቼ ጊዜ ድረስ ነው? የሚለው ጉዳይ ምላሽ የሚያሻው ነው፡፡ በዚህ ረገድ ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ የሰበር መዝገቦች የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 17937 የሰጠው የሕግ ትርጉም እንደሚያስገነዝበው በወራሾች መካከል የሚነሳ የውርስ ንብረት ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ በተደነገገው አግባብ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ሲሆን ወራሽ በሆነ እና ወራሽ ባልሆነ ተከራካሪ ወገን መካከል የሚቀርበው የውርስ ንብረት ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677 እና 1745 መሰረት በአሥር /10/ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በፌዴራልም ሆነ በክልል ፍ/ቤቶች ተፈፃሚነት እንደሚኖረው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ በሥር ፍ/ቤት የተጠቀሰው 10 ዓመት ጊዜ ሳይሆን 3 ዓመት ጊዜ ገደብ ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች አጥብቀው የተከራከሩት ተጠሪ ቤቱን እንድትጠቀም የተደረገው በግራ ቀኙ መካከል በተደረገ ስምምነት እና ተጠሪ ታላቅ እህታችን በመሆኗ በአዘኔታና በአክብሮት ስለሆነ ይርጋ ሊቆጠርብን አይገባም የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1853/1/ እንደሚያመለክተው በግራ ቀኙ መካከል ያለው ዝምድና ወይም ታዛዥነት፣ የመፍራት ወይም የማክበር ስሜት መኖር ሲታመን የይርጋ መቃወሚያ ቀጣይነት ሊያጣ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር በስምምነትና በአክብሮት ስሜት እንድትኖር ፈቅደናል ብሎም ፍ/ቤቱን ሊያሳምን የሚችል ማስረጃ እንዳላቀረቡ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በግልጽ ያመላክታል፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች ክርክር ለመቀጠል አልተቻለም፡፡ ከዚህም ሌላ የይርጋ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ተጠሪዋ የቤቱን ስመ ሐብት ወደ ራሷ ካዛወረችበት ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ሊሆን ይገባል የሚል አማራጭ ክርክር በአመልካቾች በኩል ቀርቧል፡፡ በዚህ ረገድም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ. 36975 በሰጠው ውሳኔ እንደተመለከተው የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ቤቱን በእጅ ካደረገበት ጊዜ እንጂ ስመ ሃብቱን በስሙ ካዞረበት /ካደረገበት/ ጊዜ ስላለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ እንደቅድመ ሁኔታ እንዳልተቀመጠ ጠቅሷል፡፡ በዚህም አግባብ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ /እንዲሁም የሰበር መ/ቁ. 44932 ይመልከቱ፡፡/

በአጠቃላይ የውርስ ንብረት አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1000/1/ መሰረት ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ ይህ



www.chilot.me

ሰበር ችሎት በተለያዩ የሰበር ችሎቱ መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰጠቱን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በማገናዘብ የሥር ፍ/ቤት በአሥር ዓመት ይርጋ የአመልካቾች ጥያቄ ቀሪ ሆኗል የሚለው ምክንያት ከሰበር ችሎቱ ትርጉም የሚጣጣም ባይሆንም በውጤት ደረጃ ግን የአመልካቾች ጥያቄ በ3 ዓመት ይርጋ ቀሪ መሆኑን ስለተረዳን ውሳኔውን በውጤቱ ተስማምተን አጽንተነዋል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29647 ሰኔ 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83973 ኅዳር 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በውጤቱ ብቻ በመስማማት አጽንተነዋል፡፡
2. የአመልካቾች ጥያቄ በ3 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 45905

ጥቅምት 03 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሚስስ ሚላን ፒሲጂ ማልጂ

ሚስስ ሲልቪ ፒሲጂ ጠበቃ የሽጥላ አስፋ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ሐንድሬ ፒስ ማልጂ

2. ወ/ሪት ሞኒካ ፒስጂ ማልጂ ወኪል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍርድን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ከሣሽ የነበሩ ሲሆን ተከሣሽ ሚስተር ጆርጅ ፔስልዲ ማልጂ ነበሩ፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች የአያታቸውን የማዳም ፔግሩሂ ፔስጂ ማልጂ ወራሾች መሆናቸው እንዲጣራላቸው ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ውርስ አጣሪው ተሹሞ ውርስ ተጣርቶ ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ከመዘገበው በሁዋላ ይህንኑ በመያዝ የውርስ ሐብት ከፍፍል ድርሻ ይገባናል በማለት በስር ተከሣሽ ሚስተር ጆርጅ ፔስጂ ማልጂ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ክርክሩ ከተካሄደ በኂላም የውርስ ሐብቱን የአሁኑ ተጠሪዎች እና ሚስተር ጆርጅ እንዲካፈሉት ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ያቀረቡትም ከዚሁ የውርስ ሐብት ክፍፍል በኂላ ነው ፡፡ የአሁኑ አመልካች የመቃወሚያ አቤቱታ ይዘትም የሟች እናታችንና የሟች እህታችን ወራሾች በመሆናችን በተወላጅነት ከእናታችን፣ በተተኪነት ደግሞ የእህታችንን ድርሻ ስለሚገባን የተሰጠው የውርስ ሐብት ክፍፍል ውሣኔ መብታችን ስለሚነካ ፍርዱ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአሁኑ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ለስር ከሣሾችና ተከሣሽ እንዲደርስ አድርጎ አቤቱታቸውን ከሰማ በሁዋላ ውርሱ የተጣራው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሾመው የውርስ አጣሪ መሆኑን ይህ የውርስ ሪፖርት ደግሞ የአሁኑን አመልካችን የማያውቃቸው መሆኑን በመግለጽ የፍርድ መቃወሚያው ሪፖርቱን ለአፀደቀው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሚቀርብ በስተቀር የውርስ ሐብት ክፍፍል ውሣኔ ለሰጠው ፌዴራል



www.chilot.me

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ምክንያት የአመልካችን ጥያቄ ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 05 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የውርስ አጣሪ ሪፖርት አመልካችን ያላካተተ ከመሆኑም በላይ ከማስረጃነት አልፎ እንደፍርድ የማይቆጠር በመሆኑ ተቃውሞው ሪፖርቱን ለአፀደቀው ፍርድ ቤት ይቅረብ መባሉ ያለአግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ የተጠሪዎች ጠበቃ ቀርበው ህዳር 03 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ህዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካች መቃወሚያ ማቅረብ መደረጉ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በመሠረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ የክርክሩ ተሣታፊ ያልሆነ ወገን አንድ በሕግ አግባብ የተሰጠ ፍርድ የሚቃወምበትን ሥርዓት የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ የአቤቱታው አቀራረብን በተመለከተም ሥነ ሥርዓት ሕጋችን በቁጥር 359 ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው የክርክሩ ተሣታፊ ያልሆነ ወገን መብቱን ወይም ጥቅሙን የሚነካ ፍርድ ከተሰጠ ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት መቃወም የሚችል መሆኑንና ፍርድ ቤቱም የመቃወሚያ አቤቱታው በተገቢው ሥርዓትና በተገቢው ማስረጃ የተደገፈ ሁኖ ከአገኘው ቀድሞ የሰጠውን ፍርድ ማረም የሚችል መሆኑን ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች አቤቱታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌን መሠረት አድርጎ የቀረበ መሆኑን ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያለመሆኑን ከመመርመራችን በፊት በውርስ ሕጋችን ስለውርስ አጣሪ ስልጣን የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መመልከት ለጉዳዩ አወሳሰን አስፈላጊ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ውርስ አጣሪ በሟች ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉትን ወገኖችን ወይም ወራሾችን የመወሰን፣ የሟች ኑዛዜ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥና በኑዛዜው ተጠቃሚዎችን የመለየት ውርሱን የማስተዳደር የውርሱን ተከፋይ ገንዘብ መሰብሰብና እዳዎችን መክፈል፣ የሟች ንብረት ማጣራትና ማፈላለግ እንዲሁም የኑዛዜ ስጦታዎችን የመክፈል ሥልጣን ያለው መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 944፣ 946 እና 956 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 960 ድንጋጌ ሲታይም የውርስ አጣሪው የማጣራቱን ተግባር ከአከናወነ በኋላ ሪፖርቱ ለወራሾችና ለፍርድ ቤት ማቅረብ እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ በዚሁ መሠረትም ተገቢው ክርክር ከተደረገ በኋላ የውርስ ማጣራቱ ተግባር ሲጠናቀቅ በአጣሪው ሪፖርት መሠረት ወራሾች የወራሽነት ምስክርነት ወረቀት /Certificate of Succession/ ከፍርድ ቤቱ እንደሚሰጥ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 996 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የውርስ



www.chilot.me

አጣሪ ስልጣኑና ተግባሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የማጣራቱ ውጤትም እያንዳንዱ ወራሽ ከውርሱ የሚደርሰውን ድርሻ ተለይቶ የወራሽነት የምስክር ወረቀት የሚሰጥ መሆኑ በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌዎቹ የሚያስገነዝቡት ውርሱ ተጣርቶ ለወራሽ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ወራሹ የምስክር ወረቀቱን መሠረት በማድረግ የውርስ ሀበት ክፍፍል መፈፀም፣ በወራሾች መካከል አለመግባባት ከአለ የክፍፍሉን ጥያቄ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት የሚያቀርብ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍርድ ቤት መጽደቅ በራሱ ፍርድ ሁኖ ለአፈፃፀም የሚቀርብ ሣይሆን እንደማስረጃ የሚያገለግል ነው፡፡ በመሆኑም ሪፖርቱ የማስረጃነት ዋጋ አለው ከተባለ ደግሞ የክፍፍሉ ክርክር ሲቀርብ በማስረጃነቱ ላይ ክርክር ቢቀርብ ክርክሩ መቅረብ ያለበት በውርስ አጣሪና ሪፖርቱን በአፀደቀው ፍርድ ቤት ነው ተብሎ ውድቅ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በውርስ ሐብት ድርሻ ያላቸው መሆኑንና የድርሻቸው መሠረትም ከሟች ጋር ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ እና የተተኪነት ወራሽነት መሆኑን ይህ ሁኖ እያለ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑን ገልፀው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበው የክፍፍል ጥያቄ የተሰጠው ውሣኔ መብታቸውን ሊነካ የሚችል መሆኑን ጠቅሰው መብታቸው እንዲጠበቅ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ አቀራረብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌን መሠረት ያደረገ ሲሆን የአመልካችን መብት ይነካል የተባለው እና ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የተሰጠው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ከማስረጃነት ዋጋ ውጪ ሌላ ዋጋ የሌለውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ሊቃወሙ ይገባል የሚባልበት አግባብ የለም፡፡ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍርድ ቤት መጽደቁ ሪፖርቱን ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የሚያደርገው አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ የተደረገው የውርስ አጣሪ ኃላፊነትና ተግባር እንዲሁም የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍርድ ቤት መጽደቅና ውጤቱ ምን እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ መንፈስና ይዘት ጋር ባልተገናዘበ መልኩ ሁኖ ስለአገኘነው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 44715 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁጥር 42272 መጋቢት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉት በውርስ ሐብት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ውሣኔ ለሰጠው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን ለአፀደቀው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አይደለም ብለናል፡፡
3. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀብሎና የግራ ቀኙን ቀሪውን ሁሉን ክርክር በመመርመር ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53814

ጥቅምት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች፣*** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፣*** 1. አቶ ነስሩ ሰማን ቀረቡ

2. አቶ አብዱራህማ ሰማን ቀረቡ

***ተጠሪ፣*** ወ/ሮ ሙህሊሣ ኒጋኒ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች በአቶ ሰማን መሐመድ ላይ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ጋብቻቸው በፍች የፈረሰ መሆኑን ገልፀው በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 የቤት ቁጥር 808 የጋራ ንብረት ስለሆነ እንዲያካፍለኝና ሌሎች ንብረቶችንም እንዲያካፍለኝ በማለት ክስ መሥርተዋል አመልካቾች ወላጅ አባታቸው አቶ ሰማን መሐመድ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን ገልፀው በክርክሩ ጣልቃ ገብተው ባቀረቡት ክርክር በኮልፌ ቀራንዩ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 የቤት ቁጥር 808 አመልካቾች ሟች አባታችን ከመጋባታቸው በፊት የነበረ ስለሆነ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው የቃል ክርክር የአመልካቾች ወላጅ አባትና ተጠሪ ከተጋቡ በኃላ ከዋናው ቤት ውጭ ያሉት ሰርቪስ ቤቶችና ሸንት ቤቶች የተሠሩ መሆኑንና ዋናው ቤት ተጠሪ ከሟች ጋር ከመጋባታቸው በፊት 1949 ዓ.ም የተሰራ መሆኑን ምስክሮች ያረጋገጡ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው ካሰፈረ በኃላ 1949 ዓ.ም የተሰራ ቤት እስካሁን ይኖራል ተብሎ አይገመትም በማለት ደምደሟል በውሣኔው ማጠቃለያ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቁጥር 808 ተመዝግቦ የሚገኘው ከዋናው ቤት ውጪ ያሉ ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤቶች ተጠሪና የሟች የጋራ ንብረት ነው የቤቶቹን ግማሽ ተጠሪ ወስደው ግማሹን አመልካቾች ይካፈሉት ካልተቻለ ዋናው ቤት በመሀንዲስ ተገምቶ ከተሸጠ በኃላ ይከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ



www.chilot.me

አፅንቶታል፡፡ አመልካቾች ለሰበር ባቀረቡት አቤቱታ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቁጥር 808 የሟች አባታችን የግል ንብረት ነው፡፡ ተጠሪ በዋናው ቤት ላይ ድርሻ አላቸው ሣይባል ዋናው ቤት በመሀንዲስ ተገምቶ እንዲሸጥ በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው እኔ ሟች አቶ ሰማን መሐመድና ወ/ሮ መህድያ መሐመድ ያፈሩትን ንብረት በማመን ተከራክሬለሁ የሰርቪስ ቤቶቹ እኔና አቶ ሰማን መሐመድ በጋብቻ ባለንበት ጊዜ የተሰሩ ስለሆነ የጋራ ንብረቴ ናቸው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በኮልፌ ቀራንዮ ቀበሌ 16 ቁጥሩ 808 የሆነው ዋናው ቤት ሟች ሰማን መሐመድ ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የተሰራ መሆኑን ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የቃል ክርክር ያመኑ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው የተመዘገበ ሲሆን የቤት ቁጥር 808 የሆነው ዋናው ቤት ተጠሪ ከሟች አቶ ሰማን መሐመድ ጋር ከመጋባታቸው በፊት የተሰራ መሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በኮልፌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 የሚገኘው የቤት ቁጥር 808 ዋናው ቤት የተጠሪ የጋራ ንብረት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ሟች ጋር ጋብቻ ከመሠረቱ በኃላ ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤት የተሰራ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የቤት ቁጥር 808 ይዞታ ሥር የተሰሩት ሰርቪስ ቤቶች እና ሽንት ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ናቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪ የጋራ ንብረቶች ሰርቪስ ቤቶቹና ሽንት ቤቱ መሆኑን ካረጋገጡ በኃላ የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 የሚገኘው 808 ዋናው ቤት በመሀንዲስ ተገምቶ እንዲሸጥና በሟች ወራሾችና ለተጠሪ እንዲከፋፈል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና የተሻሻለውን የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ የሚጥስ ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቁጥሩ 808 የሆነው ዋናው ቤት የተጠሪ የጋራ ንብረት አይደለም ብለናል፡፡
3. በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቁጥሩ 808 ከሆነው ዋና ቤት ውጭ የተሰሩ ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤት የተጠሪና የሟች አቶ ሰማን መሐመድ የጋራ ንብረት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. የሟች አቶ ሰማን መሐመድ ወራሾችና ተጠሪ ከዋናው ቤት ውጭ ያሉትን ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤት በአይነት ይከፋፈሉ፡፡ ሰርቪስ ቤቶቹንና ሽንት ቤቶቹን በአይነት ለመከፋፈል የማይቻል ከሆነ ሰርቪስ ቤቶቹና ሽንት ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ግማሹ ለተጠሪ ቀሪውን ደግሞ የሟች ወራሾች ይውሰዱ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡ ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 54013

ጥር 12 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አስመረት ነጋሲ በይን አቶ ግርማቸው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ጽጌረዳ ስዩም ከነጠበቃቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው ጉዳይ መነሻ ሆኖ የተገኘው ሟች አቶ ወልደማርያም ወልደጋብር ሐምሌ 29 ቀን 1996 ዓ.ም በፍታብሄር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት አድርገዋል የተባለው ግልጽ ኑዛዜ እንዲፀድቅ ተደርጐ በዚሁ በፍትሐብሄር ሕጉ ቁጥር 996(1) መሠረት የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ይሰጠኝ በሚል ቀርቦ የነበረ ጥያቄ ነው፡፡

ሟች ኑዛዜውን አድርገዋል የተባለው ለአሁኗ አመልካች ሲሆን የአሁኗ አመልካችም የኑዛዜ ይጽደቅልኝ ጥያቄውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ በኑዛዜው ሰነድ በምስክርነት ፈርመዋል የተባሉት ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ካደረገ በኋላ ምስክሮቹ በአቤቱታው መሠረት አስረድተዋል የኑዛዜው የሰነድ ማስረጃም ቀርቧል፡፡ ስለዚህ ኑዛዜው ፀድቋል አመልካችም የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጧል የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁኗ ተጠሪ ወ/ሮ ጽጌረዳ ስዩም በዝምድና የዘር ሐረግ የሟች ወራሽ እኔ ነኝ፤ አመልካች ሟች ኑዛዜ አድርገውልኛል ያሉት ሀሰት ነው የቀረበው የሟች ኑዛዜ አይደለም በኑዛዜው ላይ የሰፈረው ፊርማ የሟች አይደለም በሚል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረባቸው የኑዛዜው ጉዳይ እንደገና እንዲንቀሳቀስ ተደርጓል፡፡ ፍ/ቤቱ በኑዛዜው ጉዳይ ላይ ሁለቱን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በመቃወሚያ አቅራቢ በኩል በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው ፊርማ የሟች አይደለም ተብሎ ስለተካደ በሰነዱ ላይ በጣት አሻራ የተፈረመው የሟች መሆን አለመሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ተጣርቶ ውጤቱ ይቅረብ ብሎ አዞ የቴክኒክ ባለሙያው ፊርማውን ከሌሎች ፊርማዎች ጋር ለማመሳከር አልተቻለም የሚል መልስ በመስጠቱ ሌላ የሰማው ማስረጃ ሣይኖር ወደ ውሣኔ መስጠት አምርቷል፡፡ በሰጠው ውሣኔም መቃወሚያ አቅራቢዋ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች አይደለም ቢሉም የሟች ፊርማ ስላለመሆኑ ለማስረዳት አልቻሉም በሚል ምክንያት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 360(2) መሠረት አጽድቆታል፡፡ በዚሁ ውሣኔው



www.chilot.me

መቃወሚያ አቅራቢዋ የአሁኗ ተጠሪም የሟች ህጋዊ ወራሽ መሆኔ ይረጋገጥልኝ ብለው ያቀረቡትን ጥያቄም አብሮ በማየት የሟች ወራሽ ናቸው ብሏል፡፡

በአሁኗ ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ቀርቦለት የተመለከተው የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም መርምሮ ይግባኙ አያስቀርብም ብሎታል፡፡

በእነዚህ ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ አቤቱታ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ሰበር ችሎት ደግሞ በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ በመጨረሻም መርምሮ ኑዛዜው ይጽደቅልኝ ብለው ያቀረቡት የአሁኗ አመልካች በኑዛዜው ላይ ያለው የሟች ፊርማ ስለተካደ የሟች ፊርማ ስለመሆኑ በሕጉ የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ ነገር ግን አመልካች የሟች ፊርማ ስለመሆኑ ለማስረዳት ያሰሙት ማስረጃም ሆነ ለማሰማት ያዘጋጁት ምስክር የለም፣ ስለዚህ የሟች ፊርማ ስለመሆኑ ስላላስረዱ የሟች የኑዛዜ ወራሽ መሆን አለብኝ በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ይኼው ሣይረጋገጥ ወ/ሮ አስመረት ነጋሲ የሟች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት ተሽሯል የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም በከተማ ነክ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል ምክንያት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ በመባሉ ማመልከቻው ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮላቸው እንዲቀርቡ ተደርጐ የግራ ቀኙ ጠበቆች በተገኙበት ክርክሩ ተሰምቷል፡፡

የአመልካች ጠበቃ አመልካች በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው የጣት አሻራ ፊርማ የሟች ስለመሆኑ አስቀድመው ምስክሮች አቅርበው በማረጋገጥ ውሣኔ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ መቃወሚያ ካቀረቡ በኂላም ቢሆን በሰነዱ ላይ ያለው የጣት አሻራ የሟች ስለመሆኑ በምርመራ ይጣራ ተብሎ ሲላክ ቀለም የበዛበት ስለሆነ ከሌሎች ፊርማዎች ጋር ማመሳከር አይቻልም ተብሎ ተመለሰ እንጂ የሟች ፊርማ አይደለም አልተባለም፣ ስለዚህ ተጠሪዋ የሟች ፊርማ አይደለም ካሉ የማስረዳት ሸክሙ የተጠሪዋ እንጅ የአመልካች ሊሆን አይችልም የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን የተጠሪዋ ጠበቃ ደግሞ በቀረበው መቃወሚያ መነሻ በሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ የሟች መሆን አለመሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ተጣርቶ እንዲቀርብ ታዞ ተልኮ ቀለም የበዛበት በመሆኑ የሟች ፊርማ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አይቻልም ተብሎ ስለተመለሰ በተጠሪዋ በኩል የሟች ፊርማ ስላለመሆኑ አስረድተናል የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው የጣት ምልክት ፊርማ የሟች ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት የትኛው ተከራካሪ ወገን ነው በሚል የተነሣውን ክርክር በተመለከተ በኑዛዜው የሰፈረውን ቃልና ኑዛዜው መኖሩን ማስረዳት ያለበት በዚሁ ኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ የሚለው ሰው መሆኑን የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 896 ያስረዳል፡፡

የአስረጂውን አይነት በሚመለከት በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 897(1) ላይ እንደተመለከተው በግልጽ ወይም በተናዛዡ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜ ስለመኖሩ የሚረጋገጠው የኑዛዜውን ጽሑፍ



www.chilot.me

ዋናውን በማቅረብ ወይም ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ዘንድ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ሹም ትክክለኛ ሆኖ በተመሰከረ አንድ ግልባጭ በማቅረብ ነው፡፡

እንዲህ አይነቱን ኑዛዜ አድርጓል የተባለው ሰው ህጋዊ ወራሽ መሆኑ የታወቀ ሰው በኑዛዜው ላይ የሚያቀርበውን የተቃውሞ ክርክር በተመለከተም በፍትሐብሄር ሕግ አንቀጽ 1677(1) ላይ ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም ስለውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ደንቦች በማሚያነት ይፈፀሙባቸዋል ተብሎ በተደነገገው መሠረት ስለውል ጉዳይ ማስረጃዎች በሚመለከተው ምዕራፍ ሥር የሚገኘው የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2007(2) ለኑዛዜም ጉዳይ ስለሚያገለግል ወራሹ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ ወይም ጽሑፍ የአውራሹ ስለመሆኑ አላውቅም ማለቱ ብቻ ይበቃል፡፡ ፊርማው ወይም ጽሕፈቱ የሱ ነው የተባለው ሰው ስለመሆን አለመሆኑ ለማረጋገጥ ደግሞ ዳኞች እንዲመረመር ሊያዙ እንደሚችሉ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 208 ላይ ተገልጿል፡፡

በዚህም ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ሟቹ አቶ ወልደማርያም ወልደጋብር ሐምሌ 29 ቀን 1996 ዓ.ም ያደረጉልኝ ግልጽ ኑዛዜ አለ ብለው የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን እንዲረጋገጥ የኑዛዜውን ጽሑፍ በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ የአሁኗ አመልካች በመጀመሪያ የኑዛዜውን ጽሁፍ ብቻ ሣይሆን ኑዛዜው ሲደረግ በምስክርነት ተገኝተው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል የተባሉትን አራት ምስክሮች ጭምር ፍ/ቤት በማቅረብ አስመስክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ማስረጃውን መርምሮ ኑዛዜው በሕጉ መሠረት የተደረገ ነው በማለት በጥያቄአቸው መሠረት በማጽደቅ የአሁኗ አመልካች የሟች የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ውሳኔ በኋላ የአሁኗ ተጠሪ በዝምድና የዘር ሐረግ የሟች ህጋዊ ወራሽ እኔ ነኝ፣ አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ የተወሰነው የወራሽነት መብቴን የሚያሳጣ ነው፣ ሟች አድርገዋል የተባለው ኑዛዜ ሀሰት ነው፣ ፊርማው የሟች አይደለም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረብ እንደገና በኑዛዜው ጉዳይ ላይ ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ የአሁኗ ተጠሪ የሟችን ኑዛዜ የመቃወም መብት የላቸውም ህጋዊ ወራሽ አይደሉም በሚል የተነሣ ክርክር የሌለና ህጋዊ ወራሽ ነኝ ብለው ባቀረቡት መሠረት እንዲቀጥል የተደረገ ስለሆነ ከፍሲል እንደተገለፀው በመቃወም አመልካችዋ የአሁኗ ተጠሪ በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው የጣት ምልክት ፊርማ የአውራሼ የሟች ስለመሆኑ አላውቅም ማለታቸው ብቻ በሕጉ በቂ ይሆናል፡፡ ተጠሪዋ ግን ከዚህ አልፈው በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የሟች አይደለም በማለት በግልጽ በመካድ ተከራክረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው የጣት ምልክት ፊርማ የሟች መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ ለመወሰን እንዲቻል በፎረንሲክ ምርመራ እንዲጣራ ያዘዘ ቢሆንም የተላከለት የቴክኒክ ምርመራ ክፍል በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው የጣት ምልክት ፊርማ ቀለም የበዛበት ስለሆነ ከሌሎች ማመሳከሪያዎች ጋር በማመሳከር ለመመርመር አይቻልም ብሎ መልሶታል፡፡

በኑዛዜው ጽሑፍ ላይ ያለው ፊርማ ቀለም የበዛበት በመሆኑ ምክንያት የሟች ፊርማ ነው አይደለም የሚለው በፎረንሲክ ምርመራ ሊረጋገጥ ባልቻለበት ሁኔታ የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የሚሉት የአሁኗ አመልካች የተጣለባቸውን የማስረዳት ሸክም አልተወጡም የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይቻልም፡፡ አመልካች የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ በማንሣት ከመቅረባቸው በፊት በኑዛዜው ላይ ተገኝተው ፈርመዋል የተባሉትን አራት ምስክሮች

ጭምር በማስረጃነት ቆጥረው ቀርበው እንዲሰሙ አድርገው የነበረ ሲሆን ተጠሪዋ መቃወሚያውን ካቀረቡ በኋላ ግን ምስክሮቹ እንደገና ቀርበው እንዲመሰክሩ ሣይደረግ ታልፏል፡፡ የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ላይ ያለው የጣት ምልክት ፊርማ የሟች አይደለም ተብሎ የተረጋገጠበት መንገድ ሣይኖር እና በኑዛዜው ላይ ያሉት አራት ምስክሮች መቃወሚያው ከቀረበ በኋላ እንደገና ቀርበው እንዲመሰክሩ ሣይደረግ የአሁኗ አመልካች የማስረዳት ግዴታቸውን አልተወጡም ያለው ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው የሟች ፊርማ ነው የተባለው ቀለም ስለበዛበት በፎረንሲክ ምርመራ ለማጣራት አይቻልም ተብሎ ሲመለስ ፊርማው የሟች ስላለመሆኑ ማስረዳት ያለባቸው የሟች ወራሽ ነኝ ብለው መቃወሚያ ያቀረቡት የአሁኗ ተጠሪ ናቸው ያለውም ትክክል አይደለም፡፡

በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 881 መሠረት ግልጽ ኑዛዜ ተደርጓል ተብሎ በቀረበው የኑዛዜው ጽሑፍ ላይ ተናዛዡ በጣት ምልክት ፈርመዋል የተባለው በቀለም መብዛትም ሆነ ቆይቶ በመደብዘዙ ምክንያት በፎረንሲክ ተመርምሮ ሊረጋገጥ የሚችል አይደለም የሚባል ሆኖ ከተገኘ ምን ሊደረግ ይችላል? ሟች ኑዛዜውን ሲያደርጉ በምስክርነት ተገኝተው በኑዛዜው ሰነድ ላይ ፈርመዋል የተባሉት አራት ምስክሮች በማስረጃነት በቀረበው የኑዛዜ ሰነድ መሠረት ስለኑዛዜው መደረግ እና ሟች በኑዛዜው ሰነድ ላይ በጣት ምልክት ፈርመዋል ተብሎ በቀረበው መሠረት ስለመፈረማቸው ለማስረዳት ይችላሉ አይችሉም? የሚለው ሲመረመር በሕጉ በኩል የሚከለክል ነገር የለም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ችሎት በውሣኔው ላይ የአሁኗ አመልካች ስለኑዛዜው ጉዳይ ለማስረዳት ያሰሙትና ለማሰማትም ያዘጋጁት ምስክር እንደሌለ አድርጐ ይግለጽ እንጂ አመልካች ከመጀመሪያው የኑዛዜ ይጽደቅልኝ ጥያቄውን ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ በኑዛዜው ሰነድ ላይ ፈርመዋል የተባሉትን አራት ምስክሮች ቆጥረው ቀርበው እንዲሰሙ ማድረጋቸውን የመጀመሪያው የፍ/ቤቱ ውሣኔ ያስረዳል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርበው የኑዛዜው ጉዳይ እንደገና ተንቀሳቅሶ ክርክሩ በሚደረግበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ ነበሩ የተባሉት ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ መደረግ ሲገባው ፍ/ቤቱ አልፎታል፡፡ የተቆጠሩት ምስክሮች በመጀመሪያ ያልነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ባሉበት እንደገና ቀርበው እንዲሰሙ ማድረጉ የፍ/ቤቱ የሥራ ድርሻ ስለሆነ የተከራካሪዋ የአሁኗ አመልካች ጉድለት ተደርጐ የሚታይ አይደለም፡፡ ሰበር ችሎቱ ይህንን ከመዝገቡ ተመልክቶ በመቃወሚያው የክርክር ሂደት ሣይሰሙ የታለፉትን የአሁኗን አመልካች አራት ምስክሮች የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንደገና ምስክሮቹን ሰምቶ በኑዛዜው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት መመለስ ሲገባው አመልካች ያሰሙትና ለማሰማት ያዘጋጁት ምስክር ስለሌለ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም በማለት የወሰነው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ችሎት በመ/ቁ 07902 የካቲት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮ በኑዛዜው ሰነድ ላይ ፈርመዋል የተባሉት አራት ምስክሮች ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ቀርበው በጽሑፍ ማስረጃነት በቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ላይ በተገለፀው መሠረት ስለኑዛዜው መደረግ እና በኑዛዜው ሰነድ ላይ



www.chilot.me

ሟች በጣት ምልክት ፈርመዋል ስለተባለው ተጠይቀው የሚሰጡት ምስክርነት ከተሰማ በኋላ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን እንዲወሰን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት ተመልሷል፡፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መሠረት እንዲፈጽም ታዟል፡፡ ይተላለፍ፡፡

3. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 54024

ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፣** አቶ ገብረሊባኖስ ረዳ ጠበቃ ከበደ መንገሻ ቀረበ

**ተጠሪ፣** ወ/ሮ አዜብ አሰፋ ጠበቃ አዲሱ ሽባባው ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው አባትነትን ስለማስረዳት ዳኝነት በተጠየቀ ጊዜ አባትነትን የማስረዳት ጉዳይ እና የውሣኔ አሰጣጥ አስመልክቶ በግራቀኙ ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ መነሻ በማድረግ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ እንደሚከተለው ነው፡፡ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ባለው በሰበር መ/ቁ 54062 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተሰጠው የሰበር ውሣኔ ላይ እንደተገለፀው የአሁን ተጠሪ ከሟች አቶ መዝሙር አፈወርቅ ጋር በጋብቻ እየኖሩ እያለ ህፃን ሜሮን እንደተወለደች ገልፀው አባቷ አቶ መዝሙር አፈወርቅ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ስለሆነም የህፃን ሜሮን ወራሽነት ይረጋገጥልኝ በማለት ለአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ህፃን ሜሮን የሟች አቶ መዝሙር አፈወርቅ ወራሽ ናት በሚል ከተወሰነ በኃላ የአሁን አመልካች ይህቺ ህፃን የተወለችው ከአሁን ተጠሪ ጋር በትዳር እያሉ መሆኑን የጋብቻውን ዘመን እና ህፃኗ የተወለደችበትን ቀን በመጥቀስ ካስረዱ በኃላ አባት እኔ ሆኜ እያለ ሟች አቶ መዝሙር አፈወርቅ አባት እንደሆኑ ተደርጎ የተሰጠው ውሣኔ የእኔን መብት ይነካል ይሰረዝልኝ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ጥያቄ አቅርበው ይኸው ጉዳይ እስከ ከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የህፃን ሜሮን አባት ማን ነው? የሚለውን የልጅነት ጉዳይ ያስነሳ ክርክር ሆኖ በመገኘቱ ይህ ዓይነት ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቅ እንጂ የአ/አበባ ፍ/ቤቶች ተመልክተው ለመዳኘት ሥልጣን የላቸውም ስለሆነም የህፃን ሜሮን አባት ማን ነው? የሚለው ሥልጣን ባለው የፌዴራል ፍ/ቤት ተወስኖ እስከሚታወቅ ድረስ ህፃን ሜሮን የአባቷ የአቶ መዝገሙር አፈወርቅ ወራሽ ናት በሚል ቀደም ሲል በአ/አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሰጥቶት የነበረውን የውሣኔ ክፍል ለጊዜው አግዶ ግራቀኙን አሰናብቷቸዋል፡፡



www.chilot.me

ይህም የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ፍርድ ምክንያት የሆነው በዚህ መሠረት የሜሮን አባት ማን ነው? የሚለው አከራካሪ ነጥብ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ታይቶ ዳኝነት እንዲሰጥበት የአሁን አመልካች አቶ ገ/ሊባኖስ ረዳ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።

የአቤቱታቸውም ይዘት ከተጠሪ ጋር ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ በፍቺ እስከተለያየንበት እስከ 1994 ድረስ በጋብቻ ላይ እያለን ከወልድናቸው ሌሎች ልጆች በተጨማሪ ህፃን ሜሮን ገ/ሊባኖስን ግንቦት 13 ቀን 1989 ዓ.ም ተወልዳለች ተጠሪ ከእኔ ጋር በጋብቻ ተሳስራ እየኖረች እያለ ይህቺ ህፃን ተወልዳ እያለ ተጠሪ ይህንን በመካድ ከሚች ከአቶ መዝሙር አፈወርቅ ጋር ከጥር 28 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ እያሉ ሜሮን ከአቶ መዝሙር አፈወርቅ እንደተወለደች አድርገው የወራሽነት ማስረጃ ለማግኘት ጥረት ማድረጋቸውን ስለተረዳሁ የእኔ አባትነት በፍርድ ይረጋገጥልኝ የሚል ነው።

ተጠሪም የህፃን ሜሮን አባት ሚች አቶ መዝሙር እንጂ አመልካች እንዳልሆነ በሚያስረዳ አኳኋን ክደው በመከራከራቸው ክሱ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 42739 ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በክስ አቤቱታቸው የገለፁት ሜሮን የተወለደችው ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በሚኖሩበት ጊዜ ነው በጋብቻ ጊዜ ለተወለደ ህፃን አባቱ በጋብቻው ያለው ሰው እንደሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 126 ላይ የህግ ግምት ተቀምጧል። በዚህ የህግ ግምት አመልካች የሜሮን አባት ናቸው ይህንን የህግ ግምት ተጠሪ እናቲቱ አባቷ ሌላ ሰው ነው በማለት ውድቅ ማድረግ አይችሉም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 በፍርድ ቤት ውሣኔ አባትነት የሚታወቀው የልጅ አባት ያልታወቀ ወይም አባቱ ልጁን የካደው እንደሆነ ነው አመልካችም ሜሮን ልጄ አይደለችም ብለው የመካድ ክስ አላቀረቡም በሕግ ግምት ደግሞ አመልካች የሜሮን አባት ናቸው ስለሆነም የሜሮን አባት የታወቀ በመሆኑ አባቷ ለታወቀ ሰው ልጅነቷ በፍርድ ቀርቦ የሚረጋግጥበት አግባብ የለም ክሱ ለፍርድ የሚቀርብ አይደለም በማለት የፍርድ ሐተታ አስፍሮ የአመልካች አቤቱታ ለፍርድ የሚቀርብ ባለመሆኑ የክስ አቤቱታው ተሰርዟል በማለት ተወስኗል።

ይህም ፍርድ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ስህተት የሌለበት መሆኑ ተገልፆ የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነትን ሳያገኝ በመቅረቱ ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ ችሏል።

የሰበር አቤቱታው ፍሬ ቃልም የህፃን ሜሮን አባት ማን ነው? የሚለው ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሊረጋገጥ ካልቻለ እንዴት ፍትህ ማግኘት ይቻላል? የሚለውን የሚያብራራ ነው።

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል እንደመረመርነውም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኙን ያከራከረው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው አይደለም ከሚል መደምደሚያ ሊደርስ የቻለው በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 በአንቀጽ 126 እና 143 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና ትርጉም አዛብቶ በመተርጎሙ የተነሳ እንደሆነ ተገንዝበናል ይኸውም አባትነት የሚረጋገጥባቸው ሶስት መንገዶች ያሉ ሲሆን እነዚህም መንገዶች በቀደም ተከተል ተደንግገዋል። በቅድሚያ የተቀመጠው ጋብቻ መኖርንና ክርክር የተነሳበት ህፃን በዚህ ጋብቻ ጊዜ የመወለድን ሁለት መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ የልጅ አባት ወይም አባቷ ባል የሆነው ሰው ይሆናል የሚል ግምት ህጉ የወሰደበት ነው ይህ የህግ ግምት ነው ይህ የህግ ግምት መረጋገጥ በሚገባቸው ፍሬነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው እነዚህን ፍሬ ነገሮች ማረጋገጥ የቻለ ወገን ሌላ የተለየ ማስረጃ ማቅረብ ሳይጠበቅበት ህግ በእራሱ ግምት የወሰደለት መሆኑን የሚያሳይ ነው።



www.chilot.me

የህግ ግምት ህግ አውጭው ከተለያዩ መነሻ ሀሳቦች በመነሳት ህጉ የሚገመተው ነገር እንደማስረጃ ሆኖ እንዲያገለግል ያስቀመጠው እንጂ በህጉ የተቀመጠው ግምት ያለ ፍርድ ቤት ዕውቅና በእራሱ ተፈፃሚ እንዲሆን አይደለም የህግ ግምት እንደማስረጃ ከሚወሰዱት እንደ ሰነድ፣ የሰው ምስክርነት ቃል፣ የእምነት ቃል ገላጭ ማስረጃ ወዘተ ሆኖ ሊያገለግሉ ከሚችሉት የማስረጃ ዓይነቶች የሚመደብ እንጂ በእራሱ እንደፍርድ ሊቆጠር የሚችል አይደለም፡፡

የህግ ግምት ተጠቃሚ የሆነው ወገን በቅድሚያ በህጉ ግምት መነሻ የሆኑትን መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ከሌላው ወገን ተከራካሪ መብት አንፃር እነዚህን መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ማረጋገጡና አለመረጋገጡ ክርክሩን በሚያየው ፍ/ቤት ዳኝነት የሚያስፈልገው ነው አረጋግጦ የህግ ግምት በማስረጃነት እንዲያለግለው ወይም እንዲጠቀመው ከማድረግ ደረጃ እንኳ ቢደርስ እንደ ግምቱ ዓይነት ሁኔታ ሊስተባበል የሚችል ከሆነም ሌላው ተከራካሪ ወገን በተራው እነዚያ የህግ ግምት መነሻ የሆኑት ፍሬነገሮች ያልተሟሉ ያልተረጋገጡ መሆኑን በፍ/ቤት በማስረዳት የህጉን ግምት የማፈረስ መብት አለው ይህ ሁሉ ተግባር በክርክር ሂደት በፍርድ ቤት ሊረጋገጥ የሚችል የዳኝነት ሥራን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ እየታወቀ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በክስ አቤቱታው የገለፃቸው ፍሬ ነገሮች እንዳሉ እውነት አድርጎ በመያዝ እና በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 126 እንደተነገረው የህፃን ሜሮን አባትነት በህግ ግምት ተረጋግጧል ሌላ የፍርድ ቤት ተጨማሪ ሥራ የሚያስፈልገው አይደለም ከሚለው መደምደሚያ የደረሰው ከላይ በዝርዝር እንዳሰፈረው የህግ ግምት የሚቋቋምበትንና የህግ ግምት እንደማስረጃ ሊወሰድ የሚችል መሆኑን ካለማገናዘብ በስህተት መተርጉሙን የሚያሳይ በመሆኑ በአተረጓጐም ረገድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በፈፀመው ስህተት መነሻነትም ለተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 ተፈፃሚነት ውስጥም በስህተት እንዲተረጎም አድርጎታል /አብቅቶታል/፡፡

አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚችልበት ሁኔታ በአንቀጽ 143 ሲቀመጥ በቅድሚያ አባትነት ከህግ ግምት የሚመነጭ በህግ ግምት የሚረጋገጥ ከሆነ በዚህ አኳኋን በጋብቻ ጊዜ የመወለድ ሁኔታ ካለ በአንቀጽ 126 በተመለከተው በህግ ግምት የሚረጋገጥ እንጅ አንቀጽ 143 ሥራ ላይ የማይውል መሆኑን እንዲሁም የጋብቻ ግንኙነት ወይም በህግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖር የተወለደን ልጅ አንድ ሰው አባት ነኝ በሚል በፅሑፍ ያወቀ እንደሆነ በዚሁ ሥርዓት አባትነትን ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑን ከላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች በማይሸፈኑት በቁጥር 143 የተዘረዘሩት ምክንያቶች ባጋጠሙ ጊዜ እንደ ሶስተኛ የአባትነት ማረጋገጫ መንገድ አባትነት በፍርድ የሚነገርበትን አግባብ የደነገገ በመሆኑ የአሁን አመልካች አባትነቱ በአንቀጽ 126 መሠረት ታይቶ ይረጋገጥልኝ በማለት ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ልክ በአንቀጽ 143 አባትነት በፍርድ ይረጋገጥልኝ በማለት እንደቀረበ የዳኝነት ጥያቄ አድርጎ መተርጎሙ ከመጀመሪያው ስህተት የመነጨ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የግራቀኙ ክርክር በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው በየፊናቸው ያቀረቡት የህግና የፍሬ ነገር ክርክር በየተራቸው በሚያቀርቡት የማስረጃ አግባብነት ጥንካሬ ታይቶ ፍርድ ሊያርፍበት የሚችል ሆኖ እያለ በተሳሳተ የህግ ትርጓሜ መነሻ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ሆኖ አልተገኘም በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ 42739 በ14/5/2002 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ እና በመ/ቁ 89823 በ18/6/2002 የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በግራቀኙ መካከል የተነሳውን ክርክር በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ስለሆነ በፍርድ ሀተታው እንደተገለፀው በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮን ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡
3. ግራቀኙ እዚህ ሰበር ድረስ ክርክር ለማድረግ የበቁበት የሥር ፍ/ቤቶች በፈፀሙት የህግ ስህተት ሳቢያ በመሆኑ ግራቀኙ የየራሳቸውን ወጭና ኪሣራ ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54827

ሚያዝያ 21 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቶች፡-** 1- የሮም ወርቅ ተስፋዬ በራስዋ እና ሞግዚት በሆነችላቸው ኤልሲ ተስፋዬ ፣ ፋሲል ተስፋዬ እና ደረጀ ተስፋዬ ፣ ወ/ሮ የሮም ወርቅ ቀረበች

2- አሸናፊ ተስፋዬ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አሰግድ ሽነገለኝ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው ክርክሩ በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ አመልካቾችን የከሰሰው ከእናታቸው ጋር በመሆን በውል የሸጡልኝን ቤት ያስረክቡኝ፣ የባለቤትነት መብቱንም በስሜ ያዛውሩልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ በመሃከላችን የተደረገ ሕጋዊ ውል ስለሌለ እንድንፈጽም አንገደድም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ክርክሩን ከመረመረ በኋላ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ ግራ ቀኝ ወገኖች ከውሉ በፊት ወደ የነበሩበት እንዲመለሱም አዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ በመሻር አመልካቾች በውሉ መሠረት ለመፈጸም ይገደዳሉ በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካቾች ሚያዝያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በሕግ ረገድ ያለው አግባብነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡



www.chilot.me

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው የሽያጭ ውሉ ተደረገ የተባለው በ5/9/93 ዓ.ም ሆኖ ተጠሪ ክስ ያቀረበው ደግሞ በ27/9/99 ዓ.ም ነው፡፡ በክሱ እንደገለጸው ኤልሲ/ኤልሳቤት/ ፣ ፋሲል እና ደረጀ በወቅቱ አካለመጠን ያላደረሱ/ ክሱ ሲቀርብም/ በመሆናቸው የተወከሉት በሞግዚታቸው በሮምወርቅ ተስፋዬ ነው፡፡ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ውሉን አደረግሁ የሚለው ከእነዚህም ህፃናት ጋር ጭምር ነው፡፡ ቤቱን ገዛሁ የሚለው በብር 200,000 እንደሆነ እና ውሉ በተደረገበት ጊዜም ብር 57,285 ብቻ እንደከፈለ ቤቱን ግን እንዳልተረከበም በክሱ አመልክቶአል፡፡ ከላይ እንዳመለከትነው አመልካቾች በፍሬ ነገር ረገድ የተከራከሩት ከውሉ ሕጋዊነት ጋር በማያያዝ ሲሆን፣ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ውሉ ተከሣሾችን /አመልካቾችን/ የማስገደድ ሃይል የለውም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው ክሱን ሳይቀበል የቀረው ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው ፍ/ቤት ደግሞ ውሉ መደረጉ እስከ ታመነ ድረስ የማይፈጸምበት ምክንያት የለም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡

በበኩላችን እንደምንገነዘበው በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ውሣኔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ሊያዝ የሚገባው ጭብጥ በውሉ መደረግ አለመደረግ ወይም በመታመን አለመታመን ላይ የሚመሠረት ሳይሆን፣ ውሉ ሊያስከትለው በሚችለው ሕጋዊ ውጤት ላይ የሚመሠረት ነው አመልካቾች እንደውሉ እንዲፈጽሙ በፍርድ ሊገደዱ የሚችሉት ውሉ በሕጉ አግባብ ውጤት ሊሰጥ የሚችል ነው ለማለት የሚቻል ከሆነ ነው ፡፡ ደጋግመን እንዳመለከትነው አመልካቾች ውሉ በሕግ ረገድ ውጤት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ውሉ ተደረገ በተባለበት ጊዜ ኤልሲ /ኤልሳቤት/ ፣ ፋሲል እና ደረጀ እንደቅደም ተከተላቸው የ12 ፣ የ14፣ እና የ10 ዓመት ህፃናት እንደነበሩ ተጠሪው ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ ጭምር ተረጋግጦአል፡፡ ይህም ማለት የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው በሞግዚታቸው አማካይነት ነው ማለት ነው ቤቱ የሁሉም አመልካቾች የጋራ ሃብት በመሆኑ ሊሸጥ ወይም ለሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችለው የሁሉም አመልካቾች የጋራ ስምምነት ሲኖር እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1226 ተደንግጎአል፡፡ ለዚህም ነው ተጠሪ አመልካቾች አንድ ላይ በመሆን ቤቱን ሸጠዉልኛል በማለት ክስ የመሠረተው ይሁንና ከጋራ ባለሃብቶቹ ከፊሎች ለአካለ መጠን ያላደረሱ ህፃናት በመሆናቸው /ውሉ ተደረገ በተባለበት ጊዜ/ እና ውሉ ሕጋዊ ውጤት የለውም የሚል ክርክርም ስለተነሳ ሕጉ ለአካለ መጠን ያላደረሱ ልጆችን /ህፃናት/ ንብረት አጠባበቅ በሚመለከት ያደረገውን ጥበቃ በዝርዝር ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ክርክር የተነሳው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/በመሆኑ የተሰማውም በክልሉ ፍ/ቤቶች ነው፡፡ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የራሱ የሆነ የቤተሰብ ሕግ በአዋጅ ቁ 69/1995 /በአዋጅ ቁ 83 /1996 የተሻሻለው / አውጥቶአል፡፡ ይህ የቤተሰብ ሕግ አካለ መጠን ስላላደረሱ ሰዎችን በሚመለከት በአዋጅ ምዕራፍ አሥራ ሁለት ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቶአል፡፡ አካለ መጠን ያላደረሰውን ሰው አሳዳሪ እና ሞግዚት ሥልጣን በሚመለከትም በክፍል ሶስት ሥር የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ሲኖሩ ከእነዚህም መካከል ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያለው በአንቀጽ 294 የተመለከተው እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ እንደተቀመጠው ሞግዚቱ መሸጥ የሚችለው አካለ መጠን ያላደረሰውን ሰው ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን አክሲዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ነው፡፡ ሞግዚቱ አካለ መጠን ያለደረሰውን ሰው ንብረት የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ እንደሚችል በዚህ ድንጋጌ አልተመለከተም፡፡ ይልቁንም ሕጉ የመረጠው /የተከተለው/ ሞግዚቱ ሊሸጣቸው የሚችላቸውን ንብረቶች በግልጽ አስቀምጦ /ደንግጎ / ማለፍ ነው ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ በተቃራኒው አስተሳሰብ ሲታይ ሞግዚቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ



www.chilot.me

በሕጉ በቀጥታ ያልተፈቀደለት መሆኑን ነው፡፡ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግም እንደዚሁ በአንቀጽ 277/1/ ተመሣሣይ ድንጋጌ አስቀምጦአል፡፡

እንደምንመለከተው ሕጉ አካለመጠን ላላደረሱ ሰዎች ልዩ ጥበቃ ይኖር ዘንድ ግልጽ ድንጋጌዎችን በቤተሰብ ሕጉ አካቶአል፡፡ እንኳንስ አካለመጠን ባላደረሰው ሞግዚት የተደረገው ቀርቶ በራሱ አካለ መጠን ባላደረሰው ሰው ወይም ልጅ የተደረገው ውልም ፈራሽ እንደሆነ በኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 316 እንደዚሁም በተሻሻለው የፌዴራል መንግስት የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 299 ተደንግጎአል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎችን ቀደም ሲል ከተቀጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ስናየው በዚህ መዝገብ ለቀረበው ክስ መነሻ የሆነው የቤት ሽያጭ ውል በሕጉ ረገድ ተፈጻሚነት ያለው ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት እና የጠ/ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት የደረሱበት መደምደሚያ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሕጉን በአግባቡ በመተርጎም የተደረሰ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 31454 ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 100903 መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነው በ5/9/93ዓ.ም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈጸም አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ መሠረትም የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 16777 በ5/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54129

ኀዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ከፍያለው በቀለ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወጣት ሶፊያን አብዱልቃድር - ቀረበ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ አካለ መጠን ያላደረሰን ልጅ ንብረት በሞግዚትነት ሲያስተዳድሩ የነበሩት ወላጆች በሽያጭ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ባስተላለፉ ጊዜ አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ይኸው ተግባር የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለውን የሕግ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

የነገሩ መነሻ የአሁን አመልካች ከተጠሪ ወላጆች የማይንቀሳቀስ ንብረት ቤት በውል ገዝቻለሁ፤ ውል ሊፀድቅልኝ ይገባል የሚል አቤቱታ አቅርቦ፣ ከሻጮች ጋር ከተከራከረ በኋላ እንደ ጥያቄው ምላሽ የሚሰጥ ውሣኔ አግኝቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁን ተጠሪ የተሸጠው ንብረት ስመሃብትነት በእኔ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ነው በተሸጠበት ጊዜ በወላጆቼ የሞግዚትነት ሥልጣን ሥር የምተዳደር አካለ መጠን ያልደረስኩ ልጅ ነበርኩ፡፡ ወላጆቼ የሽያጭ ተግባሩን ለመፈፀም የሚያስችል ከሕግ የመነጨ መብት የላቸውም፡፡ በዚህ በሕግ ረገድ ተቀባይነት በሌለው ተግባር መነሻ እኔ በሌለሁበት ገዢና ሻጭ ናቸው ተብሎ በተነሣው ክርክር የሽያጭ ውል ይጽደቅ በሚል የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ስለሚነካ ውሣኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360 መሠረት ሊሰረዝ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት እራሱን በቻለ መዝገብ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ከዚህ ቀደም በአሁን አመልካችና በተጠሪ ወላጆች መካከል የተነሣውን ክርክር ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠው የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ነጥብ ላይ አመልካችና ተጠሪን ካከራከረ በኋላ በአሁን ተጠሪ ከላይ በተገለፀው አኳኋን የቀረበውን ክርክር መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀደም በሌላ መዝገብና የሽያጭ ውል ይጸድቃል በማለት የሰጠው ውሣኔ ውጤት እንደማይኖረው አድርጎ ሰርዞ ወስኗል፡፡



www.chilot.me

በዚህ መነሻ በተሰጠው ውሣኔ ሁለቱም ወገኖች በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተጠሪ የአቤቱታ አቀራረብ የተፈፀመው ሥነ ሥርዓታዊ ጉድለት መሠረታዊ ሆኖ በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በመሰረዝ የሰጠውን ዳኝነት ለማስለወጥ የሚያበቃ አይደለም፡፡

አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ የማይንቀሳቀስ ንብረት በሞግዚትነት ሥልጣን ወላጆቹ በማናቸውም መንገድ ቢሆን ለማስተለለፍ ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በክልሉ ሕግ አልተደነገገም፤ ስለሆነም በዚህ ረገድ የወረዳው ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ሻጮች ለገዢው የሽያጭ ውል ሊያፀድቅ ይገባል በሚል አስቀድሞ ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ ተሰርዟል ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም የሚለውን ጠቅሶ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መጓደልን ምክንያት በማድረግ የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር በየደረጃው ባሉት የሥር ፍ/ቤቶች በየፊናቸው አቅርበውት ከነበረው የተለየ አይደለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፣ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ በሆነው የሽያጭ ውል ላይ ተሸጧል የተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት /ቤት/ ስመ ሃብትነቱ በአሁን ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ አይደለም የአሁን አመልካች አጠንክሮ ከሚከራከርበት ነጥብ አንዱ ምንም እንኳ ስመ ሃብትነቱ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ ይገኝ እንጂ በተሸጠበት ጊዜ ተጠሪ ንብረት ለማፍራት በሚችልበት የዕድሜ ክልል ስላልነበረ ንብረቱንም በውርስ አግኝቻለሁ ስለማይል ሀብትነቱ የሻጮች በመሆኑ በፈፀሙት ሕጋዊ ተግባር ሊገደዱ ይገባል የሚለው ነው፡፡ ሆኖም የተሸጠው ንብረት ባለቤት ማን ነው? የሚል እንደ አሁኑ ያለ ጥያቄ በተነሣ ጊዜ አከራካሪ ከሆነው ንብረት ዓይነት አንፃር የንብረት ምዝገባን መሠረት በማድረግ ሕጉ ምላሽ የሚሰጥበት በመሆኑ በአመልካች በኩል በፍሬ ነገር ላይ ተመርኩዞ የቀረበው ክርክር ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ንብረቱን በግዢ አግኝቼ ለ14 ዓመታት በእጄ አድርጌ ከቆየሁ በኋላ በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በሚል ጊዜን መነሻ በማድርግ የቀረበውን ክርክር በሚመለከት ገዝቻለሁ ካለ በኋላ እንደጠቀሰው ለዓመታት ያሕል በእጁ ይዞ የቆየ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጡት ውሣኔዎች ላይ ያልተረጋገጠ የፍሬ ነገር ክርክር ከመሆኑም በላይ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው አንድ ተከራካሪ መሆን ይገባው የነበረ ሰው የክርክር ተካፋይ ሳይሆን የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ይነካል ብሎ በቀረበ ጊዜ አቤቱታው መቼ መቅረብ አለበት ለሚለው የጊዜ ማሟያ እንደ ውሣኔው የሚፈፀም እና ያለመፈፀም ጉዳይ ብቻ በመሆኑ ክርክሩ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህም አንፃር እንደ ውል ይጽደቅልኝ ብሎ ካስወሰነ በኋላ እንደ ውሉ ያልፈፀመ ስለመሆኑም ገልፆ አልተከራከረም ስለሆነም ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላውና ከሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ጋር በተያያዘ የተነሣው ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን አቤቱታ ወይም መዝገብ ያልከፈተበት አግባብነት ነው፡፡ ለአቤቱታው መሠረት አድርጎ ያቀረበው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ እንደሚያስረዳውና የነገሩ አመጣጥ እንደሚያስገነዝበው የተጠሪ የአቤቱታ አቀራረብ እኔ የክርክር ተካፋይ ባልሆንኩበት ተሰጠ



www.chilot.me

የተባለውን ውሣኔ በያዘው መዝገብ ላይ በመቅረቡ የተዘጋውን መዝገብ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ ሲገባው እራሱን የቻለ አዲስ መዝገብ ማስከፈቱ እንደ ሥርዓት አነጋገር ግድፈት የተፈፀመበት ሆኖ ቢገኝም መብቱን ለማስከበር አንኳር የሆኑ ማሚያ ምክንያቶች ተሟልተው እስከተገኙ ድረስ በየትኛው መዝገብ ክርክሩ መካሄድ ነበረበት የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ የሕግ ጉዳይ ሆኖ የጉዳዩን ውጤት ለማስለወጥ የሚያበቃ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመ መሆኑን አያሳይም፡፡

የሞግዚትነትን የሥልጣን ውልን በሚመለከት የተነሣው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች ትርጉም የሰጡበት አንድ የሕግ ክርክር እንደሆነ ከመዝገቡ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው የሕግ ትርጉም ላይ እንደተተቸው የሞግዚቶች ንብረትን ወደ ሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ ሥልጣን አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ የሚንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተያያዘ እንጂ የማይንቀሳቀስን ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚያስችል ሥልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ ይኸው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የክልሉ ሕግ ግልባጭ ንባብ አስረጂ ነው፡፡ ይህንኑ በሕግ የተገደበ ሥልጣን ተላልፈው ንብረት ባስተላለፉ ጊዜ ንብረቱ የተላለፈለት ወገን ሊኖረው የሚችለው ማስተካከያ ምን እንደሆነ በሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ ጥበቃው አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ከመሆኑ በቀር ከዚህ የተለየ ውጤት ለገዢው የተደረገ ጥበቃ ስለመኖሩ በሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም ሻጮች በሌላቸው ሥልጣን የፈፀሙት ተግባር መሆኑን መነሻ በማድረግ ሻጮች የሽያጭ ውሉን ሊያፀድቁ ይገባል፣ በውጤት ደረጃ ስመሃብትነት ሊያዛውሩ ይገባል በሚል ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ምክንያቶች ውጤት እንዳይኖረው በማድረግ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በዚህ ጉዳይ የወረዳው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04306፣ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05885 እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 81290 የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ የፀና ሲሆን በተቃራኒው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 71141 የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፤ ሆኖም ሻጮችን የሚጠይቅበት አግባብ የተጠበቀ ነው፡፡

ይህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58338

ሚያዝያ 06 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1- አቶ ዳንኤል ጽጌ
2- ወ/ሮ ጽዮን ጽጌ } ጠበቃቸው ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** ህፃን አሳለፈ ጽጌ ሞግዚት ኢ/ር ታምራት ብሩ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ የድርሻ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ሟች አቶ ፅጌ ዘገኑ ሐምሌ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ለሕፃን አሳለፍ ፅጌ ያደረጉትን ኑዛዜ መሠረት በማድረግ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የሕፃኗን የኑዛዜ ወራሽነት በማረጋገጥ ማስረጃ ከሰጠ በሁዋላ የአሁኑ አመልካቾች ይኸው የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ አመልካቾች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት መቃወሚያ የሟች አቶ ፅጌ ዘገኑ ልጆች ሁነው እያለ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ አመልካቾች በህይወቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለአደረሱብኝ ከመጡ ለእያንዳንዳቸው ብር 5/ አምስት / እንዲሰጥ በማለት መግለፃቸው ከውርስ ንብረቱ ያለምክንያት የነቀሏቸው መሆኑን ዘርዝረው ለተጠሪ የተሰጠው የኑዛዜ ወራሽነት ተሰርዞ አመልካቾች የሟች ወራሾች ናቸው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የሟች ኑዛዜ አመልካቾችን ያለምክንያት ከውርስ የነቀለ ነው በሚል ምክንያት ለተጠሪ የሠጠውን የኑዛዜ ወራሽነት በማሻሻል አመልካቾችና ተጠሪ የሟችን ውርስ እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ የአመልካቾችን ድርሻ ከማሳነስ ውጪ ከውርስ አልነቀሏቸውም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ ኑዛዜው የጸና ነው በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በሁዋላ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ጉዳዩ ተመርምሮ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡



www.chilot.me

የአመልካቾች ጠበቃ ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ/ም በጻፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ሟች ባደረጉት ኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾቻቸው ለሆኑት አመልካቾች ግምቱ ብር 600 ሺህ በላይ ከሆነው ንብረታቸው ለእያንዳንዳቸው ብር 5/አምስት ብር / ብቻ እንዲሰጣቸው መናዘዛቸው አመልካቾችን በውጤት ከውርስ የነቀሏቸው መሆኑን የሚያሳይ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የውርስ ንብረት ድርሻ አንሷል ከሚባል በስተቀር ከውርስ መነቀል አይደለም በማለት መወሰናቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎችና ይዘትና መንፈስን ያላገናዘበ ነው፣ ይኸው እንኳ ቢታለፍ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ድንጋጌ አንፃር መታየት ሲገባው መታለፉ ያላግባብ ነው በማለት ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻሻል ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርመሮም ለሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በይዘቱ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ካቀረቡት ጋር ተመሳሳይ የሆነ መልሰ ሠጥተዋል፡፡ የአመልካቾች ጠበቃም ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት አንድ ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ሟች አቶ ጽጌ ዘገኑ ሐምሌ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾችን ነቅሏል አልነቀለም?፣ ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባቸው ሁነው አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች አቶ ፅጌ ዘገኑ ሐምሌ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ግልፅ ኑዛዜ የተው መሆኑን አመልካቾች የሟቹ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች/ ልጆች/ ፤ ተጠሪ ደግሞ የሟች ወንድም ልጅ መሆኑን ፣ ሟች ይኖራቸዋል ተብሎ የተጠቀሰው የንብረት ግምት ከብር 600 ሺህ በላይ ሁኖ ለአመልካቾች ለእያንዳንዳቸው እንዲሰጣቸው የገለፁት ገንዘብ ብር 5/አምስት ብር / ብቻ መሆኑን ይህንን ለማድረግ በምክንያትነት የጠቀሱት ደግሞ በሕይወቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለፈጠሩብኝ የሚል መሆኑን ነው፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ኑዛዜው ሕጋዊ ነው በማለት የወሰኑት ሟች ለአመልካቾች ድርሻቸውን ሰጥተዋል የድርሻ ማነስ ደግሞ የውርስ መነቀል ነው ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች የኑዛዜ ስጦታ /legacy/ ወይም የክፍያ ደንብ / Rule of partition/ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመርህ ደረጃ ደግሞ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያሰኘውም፡፡ ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ / legacy/አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /partition/ በመከተል የሚከናወውን ይሆናል፡፡ ሆኖም በኑዛዜው ላይ የሚሰጠው ክፍያ መጠን በመገለፁ ብቻ ሁል ጊዜ የክፍያ ደንብ ነው ሊባል የሚችል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተሰጠው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት ግምት ጋር ታይቶ ውጤቱም በዚሁ ረገድ መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ሟች በኑዛዜው ላይ የሚያስፍረው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት መጠን ጋር እየታየ የመነቀል ጉዳይ ነው ወይስ የክፍያ ማነስ ነው? የሚለው ነጥብ የሚለይ ይሆናል፡፡



www.chilot.me

በሌላ በኩል አንድ ተናዛዥ/ ወላጅ/ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለህጋዊና በቂ ምክንያት እንዲሁም በዝምታ ከውርስ ለመንቀል እንደማይችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎች ይዘት በግልፅ ያሳያል፡፡ ወላጅ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ወይም በዝምታ ከነቀለም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሁነው የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በወላጅ የተደረገ የኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አለበት፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912 ስር እንደተመለከተው የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ሲባልም ተናዛዡ ሀብቱን ጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በሙሉ ሀብትነት ወይም በሌጣ ርስትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ማንኛውም ሌላ የኑዛዜ ቃል ሁሉ እንደ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡ እንደ ኑዛዜ ላይ የኑዛዜ ስጦታ መሆኑ የተረጋገጠ ደግሞ እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014 ድንጋጌ ቅደመ ተከተል መሠረት የሚከፈል ይሆናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ሟች አቶ ፅጌ ዘገኑ ሀብታቸውን ሙሉ በመሉ ተጠሪ እንዲወርስ ለአመልካቾች ደግሞ ለእያንዳንዳቸው ብር 5/ አምስት/ የሰጡት መሆኑ ከኑዛዜው ሰነድ ይዘት ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ሟች አላቸው ተብሎ ከተገመተው የብር 600 ሺህ ብር የውርስ ንብረት አንፃር ለአመልካቾች እያንዳንዳቸው ብር 5/አምስት ብር/ እንዲወስዱ በማለት የተናዘዙት ሁኔታ ሲታይ እግምት ውስጥ የሚገባ ወይም የድርሻ ጥያቄ አነሰ የሚል ክርክር የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችል ሳይሆን በውጤቱ የመነቀል ውጤትን ያስከተለ ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡ ሟች ለአመልካቾች ለእያንዳንዳቸው ብር 5/ አምስት / እንዲሰጥ በማለት የተናዘዙት **"በሕይወቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለፈጠሩብኝ"** በሚል ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም በሕይወቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለፈጠሩብኝ የሚለው ሐረግ ዝርዝር ይዘቱ ግን በኑዛዜው ላይ አልተገለጸም፡፡ የዚህ ሐረግ አገላለፅ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938/2/ መሠረት እንደእውነት የሚወሰድ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከውርስ ለመንቀል የሚያስችል **ሕጋዊ እና በቂ ምክንያት** መሆኑን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938/3/ መሠረት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር በሕይወት ላይ ችግር መፍጠር የተለያየ ደረጃና መንገድ ያለው በመሆኑ ሟች አመልካቾችን በዚህ ምክንያት ብቻ መንቀሉ ሕጋዊና በቂ ምክንያት ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፎርማሊቲ ረገድ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የሌለ ሲሆን ሟች አላቸው ከተባለው ጠቅላላ የውርስ ንብረት መጠን አንፃር ሲታይ ለአመልካቾች የተሰጠው የገንዘብ መጠን በውጤት ደረጃ አመልካቾችን ነቅሏል ከሚባል በስተቀር ድርሻቸውን አግኝተዋል ውጤቱም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ሊታይ የሚችል ነው ሊባል የሚችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር ተናዛዡ ያደረጉት የኑዛዜ ስጦታ ሲታይ በውጤቱ አመልካቾችን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ከውርስ የነቀለ ሁኖ ዓይነቱ ልዩ የሆነ የኑዛዜ ስጦታ ሳይሆን ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ አይነት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014/ሠ/ ስር በተመለከተው መሠረት እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ ለልዩ ኑዛዜ ተቀባዩ የሚከፈል ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ድንጋጌዎች ታይቶ ተወላጅ ከውርስ



www.chilot.me

ተነቅሿል፣ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊካፈል ይገባል የሚባልበት ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በፍ/ሕ/ቁጥር 915 መሠረት እንደጠቅላላ ኑዛዜ ወራሽ ተወስደው ከአመልካቾች ጋር እኩል ተካፋይ ናቸው ተብሎ ሊወሰን ሲገባው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከውርስ ንብረት ክፍያ ማነስ ጋር በማያያዝ የሰጡት ውሣኔ የኑዛዜውን ውጤት ሟች አላቸው ከተባለው ንብረት ግምት መጠን ጋር ባለማገናዘብ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12988 መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 13364 ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 137/02 የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ/ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ሟች አቶ ጽጌ ዘገኑ ሐምሌ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በውጤቱ ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት አመልካቾችን የነቀለ በመሆኑ በአመልካቾች ላይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፣ ኑዛዜው ተጠሪን በሟቹ ድርሻ ንብረት ላይ አንድ ወራሽ የሚያደርግ በመሆኑ አመልካቾች የሟችን ድርሻ ንብረት ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 66727

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ዝናሽ ዘውዱ - ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድምአገኘሁ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የወ/ሮ መድኃኒት ካሳ ወራሽ - እነ ወ/ሮ ደብሪቱ ስዩም አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲሆን የአመልካች አባት አቶ ዘውዱ አበበና የተጠሪዎች ልጅ እህት የሆኑት ወ/ሮ ሰናይት ስዩም በጋብቻ አብረው ሲኖሩ ወ/ሮ ሰናይት ስዩም ታህሳስ 25 ቀን 1995 ዓ/ም ከዚህ አለም በመለየታቸው ምክንያት ጋብቻው በሞት መፈረሱን ገልጸው ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብላቸው ተጠሪ ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም አመልካችን አስቀርቦ አመልካች የይርጋ ክርክር ቢያነሱም ይኸው ታልፎ የውርስ ንብረቱ ተጣርቶ እንዲቀርብ የውርስ አጣሪ ሹሞ የውርስ አጣሪውም ሀብቱን አጣርቶ ለፍርድ ቤቱ ሪፖርቱን ሲያቀርብ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ፍርድ ቤቱ የውርስ አጣሪው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 የቤት ቁጥር 497 ግቢ ውስጥ ከዋናው ቤት ትይዩ የሚገኝ ሁለት ክፍል ቤቶችና አንድ ክፍል እቃ ቤት በአጠቃላይ ሶስት ክፍል ቤት የአመልካች የግል ቤት ነው በማለት የውርስ አጣሪ የደረሰበት መደምደሚያ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 መሰረት የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ባልቀረበበት ሁኔታ ነው በማለት ውድቅ አድርጎ ዋናው ቤትና ሰርቪስ ቤቶች በሙሉ የውርስ ሀብት ናቸው በማለት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት አሻሽሎ አፅድቆታል፡፡ አመልካች የሰሩት ቤት ካለ ግምቱን ጠቅሰው ዳኝነት ከፍለው የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለትም ትእዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የውርስ አጣሪው በ23/04/2002 ዓ.ም ያቀረቡት ሪፖርት በአግባቡ የቀረበ ሁኖ እያለ ፍርድ ቤቱ አከራካሪው ቤት የግል አይደለም ማለቱ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የውርስ አጣሪው ከሟች ሞት በኋላ የተሰራውን ሶስት ክፍል የአመልካች የግላቸው ነው በማለት ያቀረበው ሪፖርት በፍርድ ቤቶቹ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ ንብረት አጣሪውን ሪፖርት በሰርቪስ ቤቶችና በእቃ ቤት ላይ ተቀባይነት የለውም በማለት ውደቅ ያደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነውም የውርስ አጣሪው ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ሪፖርት ቁጥሩ 497 በሆነው ዋና ቤት ከወ/ሮ ሰናይት ስዩም ሞት በሁዋላና ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶችና አንድ ክፍል እቃ ቤት መሰራቱን በምስክሮች ቃል መረጋገጡን የገለፁ ሲሆን ይህ ድምዳሜ በበታች ፍርድ ቤቶች ቤቶቹን የአመልካች የግል አያደርጋቸውም ተብሎ ውሳኔ የተሰጠው



www.chilot.me

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 1195 መሰረት ከአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አልቀረበም፣ ባለሀብትነቱ በሰው ማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 956 እንደተደነገገው የአጣሪው ሥራ ሟቹ አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግና በመጨረሻም ውርሱ የሚደርሳቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣ የውርሱን ሃብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸው የደረሰውን የውርስ እዳዎች መክፈል እና ሟቹ ኑዛዜ ያደረገባቸውን ስጦታዎች መክፈልና የኑዛዜውን ቃል ለመፈፀም ማንኛቸውም ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎች ማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በሚያከናውንበት ጊዜ ደግሞ በኑዛዜው የውርስ ንብረት መሆናቸውን ጠቅሶ የክፍፍል ስርዓትም የተቀመጠላቸውና ወራሾች በሙሉ የተስማሙባቸው ንብረቶችና መክፈያቸው የደረሰው የውርስ እዳዎች ሲኖሩ በወራሾቹ ስምምነት መሰረት ንብረቶቹን ሊያከፋፍልና እዳዎችንም ሊከፍል ይችላል፡፡ በኑዛዜው ላይ በተጠቀሱትና ባልተጠቀሱት ንብረቶች የውርስ ሃብት መሆን ያለመሆን ላይ ወራሾቹ ያልተስማሙና ክርክር ያነሱ ከሆነ የአጣሪውሥራና ኃላፊነት ወራሾች የተስማሙባቸውን ንብረቶች የውርስ ሃብት መሆናቸውን መመዝገብ፣ ወራሾች ያልተስማሙባቸው ንብረቶችና እዳዎች ካሉ ደግሞ ማስረጃ በመስማት ማስረጃው ምን እንደሚያስረዳ ሪፖርቱ ላይ በማስፈር እንዲያጣራ ላዘዘው ፍ/ቤት ማቅረብ እንጂ ንብረት አጣሪው ይህ ንብረት የውርስ ሐብት አይደለም የሚሉ ወራሾች ቢኖሩም ማስረጃ በመስማት የውርስ ሃብት መሆኑን ስለተገነዘብኩኝ ንብረቱ የውርስ ሃብት ነው በማለት ወስኛለሁ ወይም ደግሞ ማስረጃውን እንደተመለከትኩት ንብረቱ የውርስ ሐብት ያለመሆኑን ስላረጋገጥኩኝ የውርስ ሐብት አይደለም ወይም የእገሌ የግል ንብረት ነው በማለት ወስኛለሁ ለማለት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም፡፡

በዚህ ጉዳይ የውርስ አጣሪው ያደረጉትን የማጣራት ሥራ ስንመለከተው ወራሾቹ የውርስ ሐብት ናቸው በሚሉዋቸው ዋና ቤት እና በሰርቪስ ቤቶች ላይ ገና ከጅምሩ አንስቶ ያልተስማሙና ክርክር ያነሱ በመሆኑ አጣሪው ማስረጃ መስማታቸው በአግባቡ ነው፡፡ ሆኖም አጣሪው በወራሾች መካከል የተደረገው ክርክር እንደነበረ፣ የኑዛዜ ወራሾችና የሕግ ወራሾች እነማን እንደሆኑ፣ የግራ ቀኙ ማስረጃ ምን እንደሚመስል፣ እንዲሁም ወራሾች የተማመኑባቸውና ያልተማመኑባቸው የውርስ ንብረቶችና እዳዎቹ ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ሪፖርት ማዘጋጀት ሲኖርባቸው ከዚህ አልፈው ወራሾችን አከራክረው ማስረጃ ከሰሙ በኂላ ክርክሩንና ማስረጃውን ከሕግ ጋር በማገናዘብ ይህ ንብረት የአመልካች እንጂ የሟች የወ/ሮ ሰናይት ስዩምና የሟች ዘውዱ አበባ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት መወሰናቸው ከተሰጣቸው የውርስ አጣሪነት ሥልጣን በላይ በመሄድ መደበኛ ፍ/ቤት በሚያከናውነው የዳኝነት ሥራ ውስጥ መግባት መሆኑንና ይህም ተገቢ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ውርስ አጣሪው አዘጋጅተው ያቀረቡት ሪፖርት ውሳኔም ጭምር ያዘለ በመሆኑ ሪፖርቱ በቀረበለት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በውርስ አጣሪ ውሳኔ መሰጠት እንደማይገባ ሊገለፅና ሂደቱ ሕጋዊ አይደለም ተብሎ ውድቅ መደረግ ሲገባው መታለፉ ያላግባብ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ የባለቤነት ክርክር በውርስ ማጣራት ሂደት ከተነሳ ጉዳዩ መታየት ያለበትና እልባት ሊያገኝ የሚገባው በመደበኛው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሰረት ተገቢው ጭብጥ ተይዞ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ተሰምተው ሊሆን ይገባል፡፡ ፍርድ ቤት የባለሀብትነት ክርክር ሲቀርብ ሊያረጋግጥ የሚገባው ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን ሁሉ ሰምቶና ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ ተከትሎ ነው፡፡

በመሰረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለቤትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የዚሁ ንብረት ባለሃብት ሁኖ እንደሚቆጠር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያሳየው የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሃብት እንደሆነ ሕጉ ግምት የሚወስድ መሆኑን ነው፡፡ ይህ የሕጉ ግምት ሊስተባበል



www.chilot.me

የሚችል ስለመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው የሕጉ ግምት ባለሃብትነት በሌላ መንገድ የማይረጋገጥ አይደለም በሚል የተቀመጠ አይደለም፡፡ በዚህ መሰረትም አንድ ንብረት በአንድ ሰው ስም ስለመመዝገቡ በአስተዳደር መስሪያ ቤት ታውቆለት የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት ከተሠጠውና ይኸው ምስክር ወረቀት የተገኘበትን መንገድ ሕጋዊ አለመሆኑን ክርክር ከቀረበ ፍርድ ቤቱ ንብረቱ በማን እንደተፈራ፣ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሰው ስም እንዴት ሊመዘገብ እንደቻለ ከተገቢው አካል የቤቱ ማህደር ቀርቦ ወይም ሌሎች ማስረጃዎች ቀርበው እንዲታዩ የቀረበውን ክርክር በመመልከትና ጉዳዩን በማስረጃ በማንጠር ወደ እውነት የሚደርስበት ይሆናል እንጂ ስመ ሀብቱ የተመዘገበው ሰው የንብረቱ ባለሃብት ነው ወይም ስመ ሀብቱ ካልተመዘገበ አንድ ሰው የንብረት ባለቤት ሊሆን አይችልም፣ ወይም በሰው ማስረጃ ሊያስረዳ አይችልም በሚል ደምድሞ ከወዲሁ ክርክሩን ወይም ክሱን ውድቅ የሚያደርግበት አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱን ራሳቸው ያፈሩት ስለመሆኑና በግራ ቀኙ ማስረጃዎቻቸው ሳይነጥርና ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ በመከተል ሳይመዘኑ ከአስተዳደር አካል የተሰጠ የምስክር ወረቀት የለም ተብሎ የሰው ምስክሮች ቃል ከወዲሁ ውድቅ የተደረገው የአመልካችን የክርክር ይዘት ባለገናዘበና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት አከራካሪውን ቤት የሰራው ማን ነው? የሚለው ጭብጥ ተይዞ በዚህ ረገድ የሚቀርቡት የግራ ቀኙ ማስረጃዎች በፍርድ ቤት ፊት ቀርበው ተሰምተው ምስክሮቹ የሚሠጡት ቃል ከንብረት ባለቤትነት መብት ሕግጋት ጋር ተዛምዶ ውሳኔ መሰጠት ሲገባው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባለሀብትነት ሊረጋገጥ የሚገባው በአስተዳደር አካል በሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው በሚለው ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር የሠጠው ውሳኔ አመልካች ንብረቱን ያፈሩት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው የፍትሐብሔር ድንጋጌዎችና የህገ መንግስት ድንጋጌዎች ጋር ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች የቤቶችን ግምት ጠቅሰው ዳኝነት ከፍለው በሌላ መዝገብ ይጠይቁ ተብሎ መወሰኑም የፍትሐ ብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ መሰረታዊ አላማ ጋር አብሮ የማይሄድ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195(1) ድንጋጌ የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሀብት እንደሆነ ሕጉ ግምት ይወሰዳል ከማለት ውጪ ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በሌላ መንገድ አይረጋገጥም የማይል ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 36322 ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66774 የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ/ም በጉለሌ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ በሚገኝ የቤት ቁጥር 497 ግቢ ውስጥ ከዋናው ቤት ተይዩ የሚገኝ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች እና አንድ ክፍል እቃ ቤት በአጠቃላይ ሶስት ክፍል ቤቶች የውርስ ሀብት ናቸው ተብሎ ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 91243 መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ/ም የጸናው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 የቤት ቁጥር 497 ግቢ ውስጥ ከዋናው ቤት ትይዩ የሚገኝ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች እና አንድ ክፍል እቃ ቤት በአጠቃላይ ሶስት ክፍል ቤቶች በማን እንደተሰሩና ሕጋዊ ባለሀብት ማን እንደሆነ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66774 በሆነው ቀጥሎ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይጻፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 45207

ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡** ወ/ሮ አየለች ከበደ - ቀረበች

**ተጠሪ፡** በላቸው ዋለ ከጠበቃ ውብሥራ ሹመቴ ጋር - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የጋራ ናቸው ያለቻቸውን ንብረቶች በመዘርዘር ድርሻዋን ትወስድ ዘንድ እንዲወሰንላት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ የሚክደውን በመካድ የሚያምነውን ደግሞ በማመን ክርክሩን አቅርቦአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የቀረበለትን ክርክር መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሳኔው ባለመስማማትዋ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው፡፡ የብሎኬት ማምረቻና የገበያ ማዕከል እንዲሁም በሱልልታ ከተማ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ሥራዎች የግምቱን ግማሽ ለአመልካች ሰጥቶ ተጠሪ ያስቀረው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራቀኙ ወገኖች የተያዘውን ጭብጥ በሚመለከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከሥር ጀምሮ በግራቀኝ ወገኖች የተደረገውን ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ እንደምናየው በግራ ቀኝ ወገኖች አከራካሪ ሆነው ከቀረቡት ነጥቦች አንደኛው የመኖሪያ ቤቱን የሚመለከት



www.chilot.me

ነው፡፡ አመልካች ከሥር ጀምራ የተከራከረችው የመኖሪያ ቤቱን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ከሥር ጀምራ የተከራከረችው ቤቱ በሞት ከተለየው ከቀድሞ ባለቤቴ ጋር በትዳር ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ የተሠራ የቀድሞ ባለቤቴ እና የኔ የጋራ ሃብት ነው፡፡ ባለቤቴ ከሞተ በኋላም በእኔ እና በልጆቻችን ስም ተመዝግቦና ካርታ ወጥቶለት ይዘነው ቆይተናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በዚህ ቤት ላይ የጋራ ባለሃብት ነኝ ሊል አይችልም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ በእርግጥ ቤቱ አመልካች እንደምትለው እሱ እና ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት የነበረ፣ በእስዋ እና በልጆችዋ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ አይክድም፡፡ ቤቱ የኔም የጋራ ሃብት ነው በማለት የሚከራከረው ከአመልካች ጋር ከተጋባን በኋላ ፈርሶ እንደ አዲስ ተሠርቶአል የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤትም ይህንኑ የተጠሪ ክርክር በመቀበል ነው ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት ነው ሲል የወሰነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ቤቱ የታደሰው አመልካች እና ከቀድሞ ባለቤትዋ የወለደቻቸው ልጆችዋ በጋራ በመሆን የእድሳት ፈቃድ ለሚሰጥ አስተዳደር /በጉለሌ ክ/ከተማ የቀበሌ 13/14 አስተዳደር ጽ/ቤት/ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት እንደሆነ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አረጋግጦአል፡፡ በእርግጥ በዚህ ጊዜ የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ አልፈረሰም ነበር፡፡ ተጠሪም ይህን መሠረት በማድረግ ነው እየተከራከረ ያለው፡፡ በቤቱ ላይ የተደረገው እድሳት አዲስ ቤትን እንደመሥራት የሚቆጠር በመሆኑ እና ይህ የሆነው ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ስለሆነ ቤቱ የጋራ ሀብቴ ነው በማለትም ነው ክርክርሩን ያሰማው፡፡

እንደምናየው ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ ከመመሥረቱ በፊት የነበረ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የቤቱ ባለሃብቶች አመልካች እና ከሟች የተወለዱ ልጆችዋ እንደሆኑ ተረጋግጦ ከሚመለከተው የመንግሥት አስተዳደር ክፍል ማስረጃ የተሰጠ ስለመሆኑ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤት አረጋግጦአል፡፡ እነዚህ የቤቱ የጋራ ባለሃብቶች ቤቱን እንዲያድሱ እንዲፈቀድላቸው ቀበሌውን በጋራ የጠየቁትም የተረጋገጠላቸውን የባለሃብትነት መብታቸውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱ የታደሰው የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ስለሆነ ብቻ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት /በጋብቻ ጊዜ የተፈራ/ ነው ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የግል ንብረቶች ሆነው እንደሚቀሩ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 57 መመልከቱንም እዚህ ላይ ማንሳቱም ተገቢ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጋቢዎች ጋብቻቸው ንብረታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት በውል መወሰን እንደሚችሉ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 42/1/ የተደነገገ ቢሆንም፣ አመልካች እና ተጠሪ ግን በዚህ ድንጋጌ መሠረት ያደረጉት ውል ስለሌለ አመልካች ቤቱን የተጠሪም የጋራ ንብረት እንዲሆን ፈቅዳለች የሚባልበት አግባብ የለም፡፡ ስለዚህም ቤቱ የኔም የጋራ ሃብት ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበው ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን ክርክር በመቀበል የሰጡት ውሳኔ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ የተመለከትነው የቡሎኬት ማምረቻና ሱፐር ማርኬት/ የገበያ ማዕከል/ እንዲሁም በሱሉልታ ከተማ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን በሚመለከት የተነሳውን ክርክር ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ እንዳየነው መሠረት ያደረገው ንብረቶቹ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት አይደሉም የሚል አይደለም፡፡ ንብረቶቹ የጋራ ሃብት እንደሆኑ ፍ/ቤቱ አረጋግጦአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የንብረቶቹን

ግምት ግማሽ ለአመልካች በመስጠት ያስቀራቸው በማለት ወስኖአል፡፡ አመልካች የተቃወመችው ይህን ውሳኔ ነው፡፡ ንብረቶቹ የጋራችን እስከሆኑ ድረስ መካፈል ያለብን እኩልነታችን ተጠብቆ ነው በማለትም ነው የተከራከረችው ተጠሪም ቢሆን ንብረቶቹ የጋራ አይደሉም የሚል መከራከሪያ የለውም፡፡ ክርክሩ አመልካችም በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘውን ቤት ለኔ ድርሻዬን ግምት ከፍላ እንድታስቀር ስለተወሰነላት ይህንኑ ለማቻቻል ተብሎ የተደረገ ነው የሚል ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት የአመልካች እና የልጆችዋ ብቻ በመሆኑ ተጠሪ የዚህ ቤት እኩል ድርሻ አለኝ የሚልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በሌሎች ንብረቶች የተሰጠው ውሳኔ ከመኖሪያ ቤቱ ጋር የሚያያዝበት ሁኔታ እንዳለ በማድረግ ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ እዚህ ላይ በአግባቡ መታየት ያለበት ጉዳይ ሌሎቹ ንብረቶች የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት መሆናቸው ከተረጋገጠ ክፍፍሉ መፈጸም ያለበት በምን አይነት ሁኔታ ነው የሚለው ነው፡፡ ባልና ሚስት በጋራ ያፈሩአቸው የጋራ ሃብቶች መከፋፈል ያለባቸው በእኩልነት መርህ ላይ በመመሥረት እንደሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35/2/ እና በተሻሻለው የቤተሰብ አንቀጽ 90 ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የእኩልነት መርህ መጠበቅ አለበት ከተባለ ደግሞ አንዱ ከሌላው ያነሰ ወይም የበለጠ አይወስድም ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብቶች ናቸው የተባሉት የቡሎኬት ማምረቻ እና የገበያ ማዕከል እንዲሁም በሱሉልታ ከተማ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ስራዎች በባለቤትነት /በተግባር/ እንዲረከብ ወይም እንዲወስድ የተባለው ተጠሪ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተቀባይነት ይኑረው ከተባለ አመልካች ልታገኝ የምትችለው የንብረቶቹ ግምት/ገንዘብ/ ግማሽ ብቻ ነው፡፡ አመልካች ግን አልተስማማችም፡፡ ገንዘቡን የምትወስደው በፍርድ ስለተገደደች እንጂ ፈቅዳ አይደለም ማለት ነው ተጠሪ ንብረቱን መውሰድ አለብኝ እንደሚለው ሁሉ አመልካችም የንብረቱን ግምት ግማሽ በገንዘብ ተለውጦ እንድትወስድ አልገደድም የማለት ከእኩልነት መርህ የሚነሳውን ክርክርዋ ከሕግ አግባብ ውጪ እንዳለመቀበልም ነው የሚቆጠረው፡፡ በእኛ እምነት እና ግንዛቤ የንብረት ክፍፍሉ መከናወን ያለበት ሕጉ ባስቀመጠው የእኩልነት መርህ እና በቤተሰብ ሕጉ በተመለከተው የክፍፍል ሥርዓት መሠረት ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች እና ተጠሪ ንብረቶቹን በስምምነት ሊከፋፈሉ አልቻሉም፡፡ ከዚህ የተነሣም ሕጉ ወደአስቀመጠው የክፍፍል ሥርዓት መሄዱ የግድ ነው፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 91 እንደተመለከተው ሃብቱን በአይነት መከፋፈል የሚቻል ከሆነ ከንኡስ አንቀጽ /1/ እስከ ንኡስ አንቀጽ /3/ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት እንዲፈጸም የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ለማከፋፈል የማይቻል ከሆነ ደግሞ ቀጥሎ ባለው አንቀጽ 92 መሠረት ንብረቱን በመሸጥ ከሺያጩ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ማድረግ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የንብረት ክፍፍሉ በዚህ ሥርዓት መሠረት እንዲፈጸም አላደረጉም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው በሕጉ አተገባበር /አተረጓጐም/ ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

በመጨረሻም ያየነው በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት ሲታደስ እኔም ገንዘብ አዋጥቻለሁ የሚለው የተጠሪ ክርክር በምን አግባብ ሊታይ ይገባል የሚለው ነው፡፡ የሥር



www.chilot.me

ፍ/ቤቶች ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት ነው ብለው በመደምደማቸው ሌላውን አማራጭ አላዩም፡፡ በበኩላችን እንደተገነዘብነው ቤቱ የአመልካች እና የልጆችዋ የጋራ ሃብት ነው ቢባልም፤ ሲታደስ በጥቅም ላይ ከዋለው የእድሳት ወጪ/ገንዘብ/ ውስጥ ግማሹ የአመልካች መሆኑ የሚታመን ሲሆን ይኸው ገንዘብ የአመልካች የግል ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ከተጠሪ ጋራ የጋራ ሃብት ነው ተብሎ የሕግ ግምት የሚወስድበት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ያለው መብት አመልካች ለእድሳት ካወጣችው ወጪ ግማሽ ገንዘብ ውስጥ ግማሹን ማለትም የቤቱን መቶ ፐርሰንት ሃያ አምስት ከመቶ /ፐርሰንት/ መውሰድ ነው፡፡ ይህ መጠን ደግሞ በሥር ፍ/ቤት ሊረጋገጥ የሚገባው ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/54406 ነሐሴ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.72805 ሚያዝያ 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14 ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 1005 በሆነው የመኖሪያ ቤት ላይ ተጠሪ የጋራ ባለሃብትነት መብት የለውም ብለናል፡፡
3. የቡሎኬት ማምረቻው እና የገበያ ማእከሉ /ሱፐርማርኬት/ እንዲሁም በሱሉልታ ከተማ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ሥራዎች/የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ በተራ ቁጥር 6 የተመለከቱት/ በአይነት ለማከፋፈል የሚቻል ከሆነ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 91 መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም፤ በዚህ መሠረት ማከፋፈል ካልተቻለ ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሠረት ተሸጠው አመልካች እና ተጠሪ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
4. ተጠሪ ለቤቱ እድሳት ከወጣው ወጪ ውስጥ ሊያገኝ /ሊመለስለት/ የሚገባው መጠን ምን ያህል እንደሆነ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲወስን በዚህ ነጥብ ብቻ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣ ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራቀኝ ወገኖች ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47917

ግንቦት 05 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች፣*** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፣** 1. ወ/ሮ መልካምስራ አለበል

2. አቶ ጌትነት አለበል

3. አቶ ሁልጊዜ አለበል

4. ወ/ሮ ማንእንዳንቺ አለበል

(1–4) ከጠበቃ ደመቀ ዘነበ ቀረቡ

***ተጠሪ፣*** ወ/ሮ አንለይ ሊበን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ የውርስ ይጣራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ወራሾች መሆናቸውንና የሟች ሀብት የሆነው ቤት በተጠሪ ይዞታ ስር የሚገኝ ቢሆንም ተጠሪ የውርስ ሃብቱን ለመካፈል በመፈለጋቸው ውርስ አጣሪ እንዲቋቋም ይታዘዝላቸው ዘንድ ለደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም በተከሣሽነት ቀርበው ሟች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ኑዛዜ የተው መሆኑን ኑዛዜው እንዲፀድቅ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ የአሁኑ ተጠሪ የሚያውቁትና ያልተቃወሙት ጉዳይ መሆኑን ገልፀው ቤቱን ለመካፈል ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆንላቸው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር መርምሮ ኑዛዜው ሕጉ የሚጠይቀውን የአፈፃፀም ስርዓት የተከተለ መሆኑን ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ሲፀድቅ ተጠሪ እያወቁ



www.chilot.me

ያልተቃወሙና ከውርስ ተነቅዬአለሁ የሚል ክርክርም ስለሌላቸው የተጠሪ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ምንም እንኳ ኑዛዜው በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተደረገ ቢሆንም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው በምስክርነት ያልተጠቀሰ በመሆኑ ኑዛዜው ዋጋ የለውም ዋጋ አለው ቢባል እንኳን ተጠሪን ከውርስ የነቀለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚሉ ምክንያቶች በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔን ሽሮ ውርስ አጣሪ እንዲቋቋም ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለዚሁ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ መሠረታዊ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ ኑዛዜው በፍርድ ቤት ሲፅድቅ የነበሩና ሁኔታውን እያወቁ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ ውርስ አጣሪ እንዲቋቋም አቤቱታ ማቅረባቸው ከስነሥርዓት ውጪ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ በሶስት አመት ይርጋ ጊዜ ገደብ የሚታገድ ነው የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረነገር ስልጣን የላቸውም ክርክሩ የቀረበው አንድን ቤት ለመካፈል ስለሆነ ውርስ አጣሪ ሊቋቋም የሚገባው ጉዳይ አይደለም ኑዛዜው ሕጋዊ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኑዛዜ አፃፃፍ ፎርምን አስመልክቶ ለፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 882 ድንጋጌ የሰጠው ትርጉምና ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን የመነቀል ክርክር መሠረት በማድረግ ውሣኔ የመስጠቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮላቸው መጥሪያውን ለመቀበል ፍቃደኛ አልሆኑም በሚል ቃለመሃላ በአመልካቾች በኩል በመቅረቡ ይህ ችሎት ጉዳዩ ተጠሪ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩን በመመርመር በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ሚያዚያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ ሰጥቶ ነበር፡፡ ከዚህ በኃላ ተጠሪ ጉዳዩ በሌለሁበት እንዲታይ የተደረገው ከሕግ ውጪ ነው በማለት በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሣኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት ታይቶ እንዲወሰን ጥያቄ አቅርበው ይህ ችሎትም በዚህ ረገድ በቀረበው አቤቱታ ግራቀኙን አከራክሮ ተጠሪ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው ያላግባብ መሆኑ አረጋግጦ ሚያዚያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠውን ውሣኔ በማንሳት ጉዳዩ ተጠሪ ባሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ላይ በሰጡት መልስ አመልካቾች አለ የሚሉትን ኑዛዜ የማያውቁት መሆኑና በሕጉ የተመለከተውን አፃፃፍ ሥርዓት ያላሟላና ጥቅማቸውን የጎዳ እንዲሁም ሟችም ቀድመው ከውርስ ያልነቀሏቸው መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በሌሎች የበላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ እንዲጸናላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም በተጠሪ በኩል በዋናው ጉዳይ ላይ የቀረበው የሰበር አቤቱታ መልስ ይዘት በጉዳዩ ላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሰጥቶት የነበረውን ውሣኔ የሚለውጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረውና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት የመልስ መልሳቸው ላይ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ጽጌ ዘገኑ ሐምሌ



www.chilot.me

07 ቀን 1998 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾችን ነቅሏል አልነቀለም? ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባቸው ሆነው አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች አቶ ፅጌ ዘገየ ነሀሴ 07 ቀን 1991 ዓ.ም ኑዛዜ የተው መሆኑን አመልካቾችም ሆኑ ተጠሪ የሚቿ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች /ልጆች/ መሆናቸውን ሲሆን ተጠሪ ውርስ አጣሪ እንዲቋቋምላቸው አቤቱታ ሲያቀርቡ አመልካቾች በአከራካሪው ቤት ላይ ኑዛዜ በሟች መደረጉንና የውርስ ማጣራት ለዚህ አንድ ንብረት ሲባል ሊቋቋም እንደማይገባ እና የተጠሪ ድርሻም በቤቱ ላይ በኑዛዜ ቀሪ የሆነ መሆኑን ገልፀው መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡ ሌላው ከመዝገቡ የተረዳነው ዋናው ቁምነገር አከራካሪው ኑዛዜ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተደረገ መሆኑን ኑዛዜው ላይ ሁለት ምስክሮች መፈረማቸውን በኑዛዜው ላይ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው በምስክርነት በሟች ኑዛዜ ላይ አለመፈረማቸውን ነው፡፡ ተጠሪ ኑዛዜው ላይ ያለውን ቀንና ኑዛዜው ፀደቀ የተባለበትን ጊዜ መሠረት አድርገው ኑዛዜው ሐሰተኛ ነው የሚል ክርክር ያቀረቡ ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም ይኸው በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያላረጋገጡት ነጥብ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ// እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት ከተሰጠው የመሠረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር በዚህ የክርክር ደረጃ ተቀባይነት የሚያገኝበትን የሕግ አግባብ ያላገኘን በመሆኑ እንደተረጋገጠ ፍሬ ነገር አድርገን የምንወሰደው አይደለም፡፡ እንግዲህ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡት ነጥቦች ከላይ የተመለከቱት ከሆኑ ኑዛዜው በሕጉ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን ያለመሆኑን መመርመር የግድ ይሆናል፡፡

ተጠሪ ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ነሐሴ 07 ቀን 1991 ዓ.ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ሕጋዊ አይደለም የሚሉበት ምክንያት በአራት ምስክሮች ፊት አልተደረገም በሚል ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው የሕጉን ፎርማሊቲ ያሟላ አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ግን ኑዛዜው በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ቢሆንም አዋዋዩ በምስክርነት አልተጠቀሱም በማለት ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባቸው ስርዓቶች በፍ/ሕ/ቁ 881 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በሟች ተሰጠ  የተባለው ኑዛዜም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ ሁለት ምስክሮች የፈረሙበት ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ኑዛዜውን አረጋግጦ ማህተም ያሰፈረመበት ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚገልጽ እና ተናዛዥዋ የጣት አሻራቸውን ምስክሮቹ ደግሞ ፊርማቸውን ያኖሩበት መሆኑን ተገንዝብናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ሕ/ቁ 881 ሥር የተመለከቱትን ስርዓቶች ያሟላ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው የህጉን ሥርዓት አልተከተለም ያለው በኑዛዜው ላይ ከተመለከቱት ምስክሮች ውስጥ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ሰው በምስክርነት አልተጠቀሱም ወይም ምስክር አይደሉም በማለት ነው በእርግጥ ምስክሮች ተብለው የተፃፉት ሁለት ሰዎች ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ለመሆኑ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው የተደረገው ከሁለቱ ምስክሮች በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ፊት ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ነው፡፡ ምንም እንኳን እኚህ  ሰው ምስክር ተብለው ባይገለፁም ሟች ኑዛዜውን በነፃ ፈቃዳቸው ሲሰጡና ኑዛዜውም ሲነበብ አይተው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል፡፡



www.chilot.me

የምስክሮች ዋና አስፈላጊነትም ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜ ቃሉም የእርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው አረጋግጠው ፊርማቸውን ያኖሩ በመሆኑ ምስክር ተብለው ስማቸው ባለመገለፁ ብቻ ምስክር አልነበሩም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ከምስክሮቹ አንዱ ደግሞ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ከሆነና ኑዛዜው ይኸው ሰው ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ከሆነ ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ መሆናቸው በፍ/ሕ/ቁ 882 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ አይደለም የተባለው ምክንያት ሕጋዊ ባለመሆኑ የምንቀበለው አይደለም፡፡ ኑዛዜው በሕጉ የተመለከተውን አጻጻፍ ስርዓት የተከተለ መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያምንበት ሲሆን ተጠሪ በጠቅላላው የሚከራከሩት ኑዛዜው መብቴን የጎዳኝ በመሆኑ ፈራሽ ነው በሚል የሕግ ጥያቄ በማንሳት በመሆኑ የኑዛዜው ውጤት አግባብነት ባለው የውርስ ድንጋጌዎች መሠረት ሊታይ የግድ የሚል ይሆናል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜውን ውድቅ ያደረገበት ተጨማሪ ምክንያትም ኑዛዜው ተጠሪን ከሟች ውርስ ነቅሏቸዋል በሚል ሲሆን አመልካቾች ይህንኑ ክርክር ተጠሪ ሳያነሱት ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ማንሳቱ አግባብነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት አጠቃላይ ክርክር ማንሳታቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ኑዛዜው ፈራሽ የሚሆንበትን የሕግ አግባብ ፍርድ ቤቱ ለይቶ መወሰኑ በተጠሪ ያልተነሳን ክርክር አንስቷል ለማለት የሚያስችል አይደለም ምክንያቱም የሕጉን ጥያቄ ለይቶ የመወሰን ተግባር የፍርድ ቤቱ የስራ ድርሻ እና የዳኝነት አካሄዱ የግድ የሚለው ጉዳይ ነውና፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከሟች ውርስ ተነቅለዋል አልተነቀሉም የሚለውን ጉዳይ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ተናዛዥ /ወላጅ/ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለህጋዊና በቂ ምክንያት እንዲሁም በዝምታ ከውርስ ለመንቀል እንደማይችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎች ይዘት በግልፅ ያሳያል፡፡ ወላጅ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ወይም በዝምታ ከነቀለም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ አንድ ልጅ ከውርስ ተነቅሏል ሊባል የሚችለው ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ለሌሎች ልጆቹ ወይም ሰዎች ሲደረግ እንደሆነ ስለመነቀል የተደነገጉት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች /ከቁጥር 937-939 ድረስ ያሉት/ ያሳያሉ፡፡ በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች የኑዛዜ ስጦታ /legacy/ ወይም የክፍያ ደንብ /Rule of partition / ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመርህ ደረጃ ደግሞ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያሰኘውም፡፡ ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ /legacy/ አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /Partition/ በመከተል የሚከናወን ይሆናል፡፡ ሆኖም በኑዛዜው ላይ የሚሰጠው ክፍያ መጠን በመገለፁ ብቻ ሁል ጊዜ የክፍያ ደንብ ነው ሊባል የሚችል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተሰጠው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት ግምት ጋር ታይቶ ውጤቱም በዚሁ ረገድ መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ሟች በኑዛዜው ላይ የሚያሰፍረው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት መጠን ጋር እየታየ የመነቀል ጉዳይ ነው ወይስ የክፍያ ማነስ ነው? የሚለው ነጥብ የሚለይ ይሆናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ባደረጉት ኑዛዜ አንድ መኖሪያ ቤታቸውን ነው፡፡ ተጠሪዎች የውርስ ንብረቱ ይጣራ ጥያቄ በአንድ ቤት ላይ የቀረበ በመሆኑም ግምቱ ተቀምጦ ክሱ ከሚቀርብ በስተቀር የውርስ አጣሪ እንዲቋቋም የሚደረግበት አግባብ የለም



www.chilot.me

የሚል ክርክር ከስር ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩበት ጉዳይ ሲሆን ሟች ከዚህ ንብረት ውጭ የውርስ ንብረት ያለስለመሆኑም በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን ከአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት ተገንዘበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያላቸው ንብረት ይኸው በተጠሪ ይዞታ ስር ይገኛል የተባለ ቤት ብቻ ከሆነ አመልካቾች እንደጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ ሊወስዱ የሚገባቸው ሲሆን በውጤት ደረጃ ደግሞ ተጠሪ በኑዛዜው በዝምታ የተነቀሉ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 939/2/ መሠረት ተቀባይነት የሌለው ሲሆን በውጤት ደረጃ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 842/2/ እና 915 ድንጋጌዎች ይዘት አንፃር ሲታይ ተጠሪን ከአመልካቾች ጋር እኩል እንዲካፈሉ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂ ሕጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሆነው የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በወላጅ የተደረገ የኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አለበት፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912 ስር እንደተመለከተው የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ሲባልም ተናዛዡ ሀብቱን ጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በሙሉ ሀብትነት ወይም በሌጣ ርስትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ማንኛውም ሌላ የኑዛዜ ቃል ሁሉ እንደ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡ አንድ ኑዛዜ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014 ድንጋጌ ቅደም ተከተል መሠረት የሚከፈል ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ቤቱ ለአመልካቾች የተሰጠበት አግባብ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014/ሠ/ ስር በተመለከተው መሠረት እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ ለልዩ ኑዛዜ ተቀባዩ የሚከፈል ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ድንጋጌዎች ታይቶ ተወላጅ ከውርስ ተነቅሏል ከኑዛዜ ተቀባዮች ጋር እኩል ሊካፈል ይገባል የሚባልበት ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በፍ/ሕ/ቁጥር 915 መሠረት እንደጠቅለላ ኑዛዜ ወራሽ ተወስደው ከአመልካቾች ጋር እኩል ተካፋይ ናቸው ተብሎ ውርሱ እንዲጣራ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ በበላይ ፍርድ ቤቶቹም መፅናቱ ህጋዊ እንጂ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19946 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273/2001 ጥር 13 ቀን 2001 ዓ.ም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01275 ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ነሐሴ 07 ቀን 1991 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በውጤቱ ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ተጠሪን የነቀለ በመሆኑ በተጠሪ ላይ ተፈፃሚት የለውም ብለናል ኑዛዜው አመልካቾችንና ተጠሪን በሟቹ ድርሻ ንብረት ላይ እኩል ወራሽ የሚያደርግ በመሆኑ ውርሱ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ የሚገኘው ውጤት አመልካቾች የሚችን ድርሻ ንብረት ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡
3. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ መዝገብ ሚያዚያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተፈፃሚት የሌለው ነው ብለናል፡፡



www.chilot.me

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡*

*ም.አ* *የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*



www.chilot.me

# አሠሪና ሠራተኛ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54451

መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልድ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡-የፊንጫአ ስኳር ፋብሪካ - ጠበቃ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ መ/ሰ/ማህበር - ነ/ፈጅ ኤልያስ አበበ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሠረት አድርጐ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቋሚ ቦርድ ሲሆን አመልካች የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 131 መሠረት መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም ከአሁኑ አመልካች ተወካዮች ጋር በሕብረት ስምምነት ላይ ድርድር ጀምሮ በዓመቱ ማለትም መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም መጨረሱን፣ ሆኖም የአሁኑ አመልካች የሕብረት ስምምነቱን የተደራደሩት ወኪሎቹ ከውክልና ስልጣናቸው ውጪ ተደራድረዋል በሚል ምክንያት ሕብረት ስምምነቱን ልቀበል አልችልም በማለት መግለፁን በመዘርዘር ሕብረት ስምምነቱ ቀርቦ እንዲመዘገብና ሰራተኛውም በድርድሩ መሠረት የተገኙትን መብቶችና ጥቅማ ጥቅሞችን እንዲያገኝ እንዲወስንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የአመልካች ወኪሎች ከተሰጣቸው ስልጣናቸው ውጪ በተወሰኑት ነጥቦች ላይ መደራደራቸውንና የተወሰኑት ነጥቦችም በሕብረት ስምምነቱ የማይሸፈኑ መሆናቸው በመረጋገጡ አስፈላጊው ማሻሻያ እንዲደረግ ለአሁኑ ተጠሪ ምላሽ መስጠቱን በመግለጽ ክሱ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ቋሚ ቦርድም በጉዳዩ ላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር አስማሚ አስተያየቱን እንዲሰጥበት ከአደረገ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ሕብረት ስምምነቱ ድርድሩ ያለቀለት ስለሆነ በሁለቱ ወገኖች ተፈርሞ አስፈላጊው ቅጂ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 131 መሠረት ለመዝጋቢው አካል ተልኮ ይመዝገብ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃው መጋቢት 23 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት



www.chilot.me

ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የአመልካች ተወካዮች በተወሰኑት ነጥቦች ላይ ከስልጣናቸው ውጪ የፈፀሙት ድርድር መሆኑን የአመልካች ማኔጅመንት አረጋግጦ እነዚህ ነጥቦች እንዲወጡ ያቀረበው ሐሣብ በተጠሪ ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቶ ክሱ ተቀባይነት ማግኘቱ ከውክልና ሕግ ድንጋጌዎችና ከሕብረት ስምምነት ድርድር ሐሣቦች ጋር በማይዛመድ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የአመልካችን መስሪያ ቤትን በመወከል ከተጠሪ ጋር የሕብረት ስምምነት ድርድር ያደረጉት ግለሰቦች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ስለመሆኑ መጣራት ያለበት ነው በሚል ምክንያት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ጠበቃው ቀርበው ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከተጠሪ ጋር የሕብረት ስምምነት ለማድረግ ግለሰቦችን በመወከል ድርድር ሲያካሂድ የቆየ ሲሆን ድርድሩ ተጠናቅቆ ጉዳዩን የአመልካች የማኔጅመንት አካል ሲመለከተው አመልካች የወከላቸው ግለሰቦች ድርድሩን ያካሄዱት ከተሰጠቸው ሥልጣን ውጪ እና የህብረት ስምምነት በማይሸፍናቸው ጉዳዮች ሁኖ በማግኘቱ ይህንኑ ለተጠሪ እንዳሣወቁ እና ማሻሻያ እንዲደረግ ጥያቄ ማቅረቡን ነው፡፡ ተጠሪ የሚከራከረው ደግሞ ድርድሩ ላይ የተሣተፉት የአመልካች ወኪል ግለሰቦች ከስልጣናቸው ውጪ የሰሩት ነገር አለመኖሩንና በሕብረት ስምምነት የማይሸፈን የመብት ወይም የጥቅማ ጥቅም ጥያቄ የለም በሚል ስለመሆኑም ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ አዋጅ ቁጥር 377/96 “አንቀጽ” 124 እስከ አንቀፅ 135 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለህብረት ስምምነት ትርጉም ስለህብረት ስምምነት ድርድር የህብረት ስምምነት ድርድር፣ የህብረት ስምምነት ድርድር ሥነ ሥርዓት፣ ስለህብረት ስምምነት አመዘጋገብ፣ የሕብረት ስምምነት የሚፀናበት ሁኔታ እና የሕብረት ስምምነት ተፈፃሚነት ወሰን ደንግጎ እናገኛለን፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 124/2/ እና የአዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ሲታዩ ተደራዳሪ ወገኖች በስራ ላይ ያለውን ህብረት ስምምነት የስራ ዘመኑ ከማለቁ ወይም ቀደም ብሎ ሕብረት ስምምነቱን እንዲሻሻል ወይም በሌላ እንዲተካ መወሰን ያለባቸው መሆኑን የሚያስገነዝቡን ሲሆን በዚሁ መልክ በሚደረስበት ውሣኔ መሠረት ተደራዳሪዎች የህብረት ስምምነቱን ድርድር ተቀራርበው መስራት ያለባቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 3 በግልጽ ያሣያል፡፡ አዋጁ የሕብረት ስምምነት ድርድር ሊደረግ የሚችልባቸውን ነጥቦችና ድርድሩን ለማድረግ የሚችሉ ወገኖች እነማን እንደሆኑም በአንቀጽ 124/2/ እና 126 ስር ደንግጎ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም ድርድሩ ስለስራ ሁኔታዎች ወይም ስለህብረት ስምምነት ወይም የሕብረት ስምምነትን ለማደስና ለማሻሻል በአሰሪዎችና በሰራተኞች ማህበር ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻቸው መካከል የሚደረግ ክርክር (NEGOTITON) ስለመሆኑ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች አስፈላጊነት ሲታይም የአሰሪና ሰራተኛ ወገኖች የመደራደርና ሕብረት ስምምነት የማድረግ መብታቸው በአግባቡና በቀና መንፈስ እንዲጠቀሙ ማስቻል ስለመሆኑ በአዋጁ ማሻሻያ ላይ የተደረገው የውይይት ሰነድ / ሀተታ ዘምክንያት/ ያሣያል፡፡ የሕብረት ስምምነት ከተፈረመ በሁዋላ የስምምነቱ አስፈላጊ ቅጅ በተዋዋይ



www.chilot.me

ወገኖች አማካኝነት ለሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር ለምዝገባ እንደሚላክ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 131 ስር ሰፍሯል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 133/2/ ድንጋጌ ሲታይም በህብረት ስምምነቱ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር አንድ የሕብረት ስምምነት ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና እንደሚሆን ያስገነዝባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የሕብረት ስምምነት ድርድር አመልካች ውክልና በሠጣቸው ወኪሎችና በተጠሪ መካከል ስለመከናወኑ የተረጋገጠ ሲሆን አከራካሪው የሕግ ጥያቄ አመልካች ሰነዱ በሕብረት ስምምነት ሊፀድቅ አይገባም በማለት ተቃውሞ አቅርቦ እያለ ወኪሎቹ ስለፈረሙ ብቻ በሕግ ፊት የፀና ይሆን ዘንድ የድርድሩ ውጤት በሚመለከተው አካል እንዲመዘገብ ዳኝነት ሊያርፍበት የሚገባው ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የሕብረት ስምምነቱ እንዲመዘገብ የሚደረገው ከተፈረመ በሁዋላ ነው፡፡ አመልካች በድርድሩ ወቅት የተሣተፉ ወኪሎቹ ሰነዱ ህብረት ስምምነት እንዲሆን ስምምነት የደረሱና የፈረሙ ስለመሆኑ ሣይክዱ የወኪሎቹን ተግባር የሕብረት ስምምነቱ በሚመለከተው አካል ከመመዝገቡ በፊት ተቃውሞታል፡፡ የሕብረት ስምምነት ድርድሩ በሕጋዊ ወኪሎቹ እንዲከናወን ያደረገ አሰሪ በድርድሩ መሠረት የተደረሰን ስምምነት ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ከመመዝገቡ በፊት ቢቃወመው ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ አዋጅ ቁጥር 377/96"ም" ሆነ የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ የሆኑት አዋጅ ቁጥር 466/97 እና 494/98 ድንጋጌዎች ምላሽ አይሰጡም፡፡ ይሁን እንጂ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድርድሩ በሕጋዊ ወኪሎች የሚደረግበትን አግባብ የዘረጋ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ ስለእንደራሴነት የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ማየቱ አግባብነት ያለው ይሆናል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2190 ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ከስልጣኑ ውጭ ወካይ የተወካይነት ተግባር ለማጽደቅ ወይም ለማፍረስ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወኪሎቹ በሕብረት ስምምነት ድርድር ላይ ክርክር ሲያደርጉ ቆይተው ሰነዱ የሕብረት ስምምነት እንዲሆን በፊርማቸው ያረጋገጡበትን ሁኔታ ያልተቀበለው መሆኑን ምክንያቱን ገልጾ እንዲመዘገብ ፍላጎት የሌለው መሆኑን መግለፁ ከመነሻውም ስምምነቱ ገና ወደሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ ያልፀደቀ ከመሆኑ በድርድር ደረጃ ያለ በመሆኑና በወካይነት ስልጣኑም የወኪሎቹ ተግባር ሕጋዊ ግዴታ እንዳይጥልበት የማድረግ ሕጋዊ መብት ያለው በመሆኑ የሕብረት ስምምነቱን በፍርድ ኃይል እንዲያስመዘግብ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በሕጉ አግባብ የሕብረት ስምምነት የፀና ነው የሚባለው በተገቢው መንገድ በአሰሪው መፈረሙና የወኪሎቹን ተግባር ማጽደቁ ሲረጋገጥ ነውና፡፡

ተጠሪ ድርድሩ የበረሃ አበልን የማይመለከትና በአመልካች ተገቢ ባለሥልጣን ተፈርሞ እንዲመዘገብ የሚል ሃሣብ መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የቀረበ ሁኖ እያለ የአመልካች ጠበቃ የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም በሚል ያቀረበው ክርክር ሲታይም በሕጉ አግባብ አመልካች የሰበር አቤቱታውን የተወው መሆኑ እስካልተረጋገጠ እና ጉዳዩን አይተው ዳኝነት ባሣረፉት አካላት ፊትም ተጠሪ ይህንኑ ክርክር አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ስለመሆኑ የሚያመለክት ሁኔታ በሌለበት ይህ ችሎት የሚቀበለው የክርክር ነጥብ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች ተገቢ ባለሥልጣን ሰነዱ የሕብረት ስምምነት እንዲሆን የበርሃ አበልን በተመለከተ የተቀመጠው ጉዳይ እንዲወጣ ሀሣብ አቅርቦ እያለ ሰነዱ በወኪሎቹ ተፈርሟል በሚል ምክንያት ብቻ በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ እንዲመዘገብ የተደረገው ያላግባብ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁጥር 383/ቀወ1/2001 ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 90031 መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ወኪሎቹ ያደረጉትን ድርድር ያለመቀበል ሥልጣን ያለው በመሆኑ በተገቢው ባለስልጣን ያልተፈረመ ሰነድ የሕብረት ስምምነት ሁኖ እንዲመዘገብ እንዲያስደርግ የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48945

ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፣* ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

*አመልካች፣* አቶ አየለ አበበ ቀረቡ

*ተጠሪ፣* የፊንፊኔ የደን ድርጅት ነገረፈጅ ጋንገና ገብረሚካኤል ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ አመልካች የድርጅቱ ንብረት ዲ 7 ኤች ተብሎ በሚጠራው ዶዘር ላይ ጉዳት በማድረሱ ብር 227,594.18 ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች ማሽኑን ለሥራ ከማንቀሳቀሱ በፊት ቅባት ዘይትና ውሃ ማየት የነበረበት ቢሆንም ይህንን ሳይፈትሽ በመንዳት እንዲሰባበር በማድረጉ ለጥገና ብር 227,594.18 /ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አምስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአስራ ስምንት/ ሣንቲም ወጭ አድርገናል፡፡ ስለዚህ አመልካችና የአመልካች ወኪል ይህንን ገንዘብ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ማሽኑ የተሰበረው በእኔ ችሎታና ሙያ ሊፈተሹ የሚችሉ የሞተር ቅባት ዘይትና ውሃ ሣልፈትሽ ስለነዳሁት አይደለም፡፡ ማሽኑ የተሰበረው በቴክኒክ ባለሙያ ስሌትና ክትትል ሊደረግበት የሚገባው የመጨረሻ ክፍሎች /Final Drive/ በደረሰበት ጉድለት ነው፡፡ የፋይናል ድራይቭ ዘይት መፈተሽና መፍታት የእኔ ሥራ ድርሻ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኃላ ሬይስ ኢንጀነሪንግ የሰጠውን ሙያዊ አስተያየት በመመርመር ለማሽኑ ብልሽት አመልካች ፋይናል ደራይቭ ዘይት ሣይፈትሽ በመንዳቱ ነው በማለት አመልካች ብር 227,594.18 /ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አምስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአስራ ስምንት ሣንቲም/ የመክፈል ሃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ



www.chilot.me

ችሎት ያቀረበ ቢሆንም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታቸውን አልተቀበላቸውም፡፡

አመልካች መስከረም 4 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተበላሸው የዶዘር ክፍል /ፋይናል ድራይቭ/ በኦፕሬተር በቀላሉ የማይፈታና ሰርቪስ የማይደረግ መሆኑ ከሬስ ኢንጅነሪንግ የተላከው ባለሙያ በማረጋገጡ ወደ ሥራዬ ተመልሼ እየሠራሁ እገኛለሁ፡፡ በወንጀልም ተከሣሼ በነፃ ተሰናብቻለሁ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ማስረጃ ሣይመረምርና ስህተቱ የእኔ አለመሆኑን ሳያገናዝብ አለአግባብ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በሥራ ክርክር ችሎት የሰጠው ውሣኔም ሆነ በወንጀል ችሎት የሰጠው ውሣኔ የጉዳት ካሣ ከመጠየቅ የሚገድበን አይደለም፡፡ ማሽኑ የተበላሸው በአመልካች ጥፋት መሆኑን አስረድተናል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በቃል ክርክር መልስ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኃላ ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰበር ችሎቱ ባቀረባቸው ጥያቄዎች አመልካችና ተጠሪ በቃል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በፅሑፍና በቃል የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል መዝገቡን እንደመረመርነው የተጠሪ ንብረት የሆነው ዲ. 7 ኤች ተብሎ የሚታወቀው ዶዘር ላይ ጉዳት ያደረሰው አመልካች በሥራው ሂደት ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ሣያደርግ ዶዘሩን በማንቀሳቀሱ ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረትና ድጋፍ አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የዶዘሩ ኦፕሬተር መሆኑና የአመልካች የሥራ ድርሻና ሃላፊነት ማሽኑን ኦፕሬት በማድረግ መስራት የሚገባውን ሥራ መሥራት መሆኑ በግራቀኙ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ የአንድ የዶዘር ኦፕሬተር ጠቅላላ የሥራ ሃላፊነት የሞተር የመሪ ዘይትና ሌሎች በቀላሉ ሊፈተሹ የሚችሉ የዶዘሩን አካላት ዶዘሩን ከማንቀሳቀሱ በፊት መፈተሽና የተጓደሉ ነገር ቢኖር እንዲሟላ ማድረግ እንደሆነ በአመልካችና በተጠሪ በኩል ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አሁን ዶዘሩን ለብልሽት የዳረገውና ተጠሪውን ለጥገና ከፍተኛ ወጭ ያስወጣው /ፋይናል ድራይቭ/ የሚባለው የማሽኑ ክፍል እንደሆነ ይህንን ክፍል ለመፈተሽ የተለየ መፍቻና የተለየ ሥልጣና የሚያስፈልግ መሆኑን አንድ የዶዘር ኦፕሬተር የፋይናል ድራይቭ ልዩ መፍቻ ከተሰጠው ፋይናል ድራይቭ እንዴት እንደሚፈታና እንደሚፈተሽ ሥልጠና ከተሰጠውና ይኸው በሥራ መዘርዝሩ በግልፅ ከተካተተ ፋይናል ድራይቭ ዘይት መፍታት የሚችል መሆኑና የመፈትሽም ግዴታ እንዳለበት በማብራራት ሬስ ኢንጅነሪንግ በፅሑፍ የሰጠውን መግለጫ እንድያብራራ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 64587 አስቀርቦ የሙያ ምስክርነታቸውን የሰማቸው የሬስ ኢንጅነሪንግ ባለሙያ በሰጡት ምስክርነት ያረጋገጡ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሀምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ገልፆል፡፡

ምንም እንኳን በሥራና አሠሪ ክርክር ችሎት የተሰጠ ውሣኔ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5/1/ መሠረት የአሠሪውን የፍታብሔር ክስ የማቅረብ መብት የማይገድብ ቢሆንም የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ችሎት ውሣኔ ለፍታብሔር ክርክር በማስረጃነት አንዳይቀርብ የሚከለክል ግልፅ የህግ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ውሣኔውን ሠራተኛው በአሠሪው የቀረበበትን ክስ ለመከላከል



www.chilot.me

በማስረጃነት ቢያቀርበው በህግ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ የፍታብሔር ክሱን የሚያየው ፍ/ቤት ይህንን ማስረጃ ተቀብሎ የመመዘን ግዴታና ሃላፊነት አለበት፡፡

በያዝነው ጉዳይ ሬስ ኢንጅነሪንግ በፅሑፍ የሰጠው ሙያዊ አስተያየት ጥቅልና ግልፅነት የጎደለው በመሆኑ የሬስ ኢንጅነሪግ ባለሙያ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አሠሪና ሠራተኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጣሪያ ምስክርነት ቀርበው አንድ ኦፕሬተር "ፋይናል ደራይቭ" የተባለው የዶዘር ክፍል በመፍታት ዘይት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ለመፈተሽ የሚችለው ሶስት መሠረታዊ ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ መሆኑን አሰረድቷል፡፡ ሶስቱ መሠረታዊ ሁኔታዎችም ፋይናል ድራይቭ ለመፍታትና ለመግጠም የሚያስችል ልዩ ስልጠና ለሠራተኛው በአሠሪው የተሰጠ ሲሆን ፋይናል ደራይቭ ለመፍታት የሚያስችል ልዩ መፍቻ ለሠራተኛው  የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥና በሠራተኛው የሥራ መዘርዝር ፋይናል ደራይቭ የመፍታትና የመፈተሽ ሃላፊነት የኦፕሬተሩ መሆኑ በግልፅ ተፅፎ የተሰጠው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የፋናል ደራይቭ መፈተሽ የሞተር ዘይት የራዲያተር ውሃና የሀይድሮሊክ ዘይትና የትራንስሚሽን ዘይት እንደመፈተሽ አመልካች ሊፈፅመው የሚገባው ሥራ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም ተጠሪ አመልካች የዶዘሩን ፋይናል ደራይቭ ለመፈተሽ የሚያስፈልገውን ልዩ ሥልጣና የሰጠ መሆኑንና ይህንን የዶዘሩን ክፍል ለመፍታት የሚያስችል ልዩ መፍቻ ተጠሪ ለአመልካች የሰጠው ስለመሆኑ በማስረጃ ሣይረጋገጥ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለጉዳቱ ሃላፊ ነው በማለት የወሰነ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ለአመልካች ፋይናል ደራይቭ ለመፍታትና ለመፈተሽ አስፈላጊ የሆነውን ልዩ ሥልጠና ያልሰጠና ይህንን የማሽን ክፍል ለመፍታት የሚያስችለው ልዩ መፍቻ ያልሰጠው መሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክሩን በይግባኝ ሰምቶ በወሰነው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካችን ለጉዳቱ በኃላፊነት ለመጠየቅ በመጀመሪያ ማሟላት ያለባቸው ሶስት ሁኔታዎች መሞላታቸውን ሣያረጋግጥ አመልካች የዶዘሩን ፋይናል ድራይቭ ዘይት ሣይፈትሹ ማሽኑን አንቀሣቅሰዋል በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎት ማፀናታቸው አሠሪው ግዴታና ሃላፊነቱን በአግባቡ የተወጣ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ /1/ሀ የተደነገገውን የሚጥስ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ዶዘር ላይ ለደረሰው ጉዳት በሃላፊነት አይጠየቅም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡት ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53985

ህዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ዳሽን ባንክ አ.ማ ነ/ፈጅ የሺ.ወርቅ ይመር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዘነበ ድንቄሣ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአመልካች ድርጅት ውስጥ ላይ በማገልገል ላይ እያሉ በጋዜጣ ላይ አስተያየት ሰጥተሃል በሚል ሰበብ አመልካች ድርጅት ከታህሳስ 14 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ያላግባብ ከሥራ ያገዳቸው መሆኑን በመግለጽ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የታህሳስ ወር ደመወዝ ከተለያዩ ወጪና ኪሳራዎችጋር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ተጠሪ በአመልካች ላይ ከባድ ጉዳት እያደረሱ በመሆኑ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ከስራ መታገዳቸውን ገልፆና እግዱም በአግባቡ የተሰጠ መሆኑን ጠቅሶ እግዱ ሊነሳ አይገባውም ሳልሰሩበት ጊዜ ደመወዝ ሊከፈላቸው እንደማይገባ ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዮን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካች ተጠሪን ከስራ ያገዳቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 18 መሠረት ለማገድ የሚያበቁ ሕጋዊ ምክንያቶች በሌሉበት ሁኔታ መሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአዋጅ አንቀጽ 27(4) ድንጋጌ ሲታይም እግድ የሚፈቀደው በሕብረት ስምምነት ላይ በተመለከተው መሰረት መሆኑን ገልፆ ሕብረት ስምምነቱ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪን አመልካች ከሥራ ማገዱ ሕገ ወጥ ነው በሚል ድምዳሜ ተጠሪን የታህሳስ ወር 2002 ዓ.ም ደመወዝ በመክፈል አመልካች ወደ ሥራ እንዲመለስ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) ድንጋጌ ጥፋት መኖሩን አሰሪው



www.chilot.me

እስከሚያጣራ ድረስ ሰራተኛን ከስራ በማገድ ጉዳዩን ለማጣራት የሚችል መሆኑን ፈቃጅ በሆነ አገላለጽ ደንግጎ እያለ የሕብረት ስምምነት ከሌለ ተፈጻሚነት የለውም በሚል የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው መስከረም 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ጥቅምት 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ተጠሪን ከስራ እና ደመወዝ ያገዳቸው ተጠሪ በድርጅቱ ላይ ጉዳት እያደረሱ ነው በሚል ጉዳዩን እስከሚያጣራ ድረስ ሲሆን ለእርምጃው ህጋዊነት በዋቢነት የሚጠቅሰውም አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/(4) ስር የተመለከተውን መሆኑን ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ሕብረት ስምምነት ሳይኖር በአዋጁ አንቀጽ 27(4) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የለውም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነጥብ የሕብረት ስምምነት የሌለው አሠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) መሠረት የማገድ እርምጃ መውሰድ አይችልም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ የቅጥር ውል ባይቋረጥም አሰሪውና ሰራተኛ ከግዴታዎቻቸው ለተወሰነ ጊዜ ነፃ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች ያሉ ስለመሆኑ አዋጁ ቁጥር 377/96 ከአንቀጽ 17 እስከ 22 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የቅጥር ውል ሲታገድ ምክንያቶቹ የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎችና ከአንቀጽ 27(4) እና 184 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ለአሁኑ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የእገዳ አይነት በአዋጁ አንቀጽ 27(4) ስር የተመለከተው ከዲስፕሊን ጋር ተያይዞ የሚፈፀምና የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችሉ ጥፋቶችን ለማጣራት የሚደረግ እገዳ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በአንቀጽ 27 ስር በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ እንዲቋረጥ ከመደረጉ በፊት ሰራተኛውን ለአንድ ወር ያህል ከስራ አግዶ ማቆየት ስለሚቻልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን ይችላል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ የድንጋጌው ዓይነት ዓላማ አሰሪው በአስተዳደራዊ ሥልጣኑ ሰራተኛው ለሚፈጽመው ጉድለት ተገቢውን የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችል ዘንድ ሠራተኛው ፈፀመ የተባለውን የሥነ ምግባር ጉድለት በተገቢው መንገድ ለማጣራትና ለመመርመር እንዲችል ማድረግ ነው፡፡ ሕጉ ይህንን አላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ እገዳ ማድረግን የሚፈቅድ ሲሆን እገዳው የሚቆይበትን የጊዜ ገደብም ከአንድ ወር መብለጥ እንደሌለበት ያስቀምጣል፡፡ ሕጉ አሰሪው እገዳውን ሲፈጽም ከድርጅቱ ሰራተኛ ማህበር (በህብረት ስምምነት መሠረት) ጋር በመስማማት ለመወሰን እንደሚችል ያሳያል፡፡ ሆኖም የህብረት ስምምነት የሌለው ድርጅት ሰራተኛውን ቢያግድ እገዳው ሕገ ወጥ ሊባይ ሚችል ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ አያሳይም፡፡ የእገዳው አላማ በሰራተኛው ተፈፀመ የተባለውን የስነ ምግባር ጉድለት በተገቢው መንገድ ማጣራትና ለመመርመር አሰሪውን ለማስቻል ነው ከተባለ የሠራተኛ ማህበር የሌለው (የሕብረት ስምምነት (የሌለው) ድርጅት ሰራተኛው ፈፀመ ለተባለ ጉድለት እገዳ በማድረግ የዲስፕሊን ግድፈቱን ለማጣራት ወይም ለመመርመር እይችልም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት

የለም፡፡ ድንጋጌው በይዘቱ ሲታይ ፈቃጅ እንጂ ክልከላ ያበጀ አይደለም፡፡ አገዳው የሚደረግበት አላማ ሲታይ እውነቱ በትክክል እንዲወጣ በሕጋዊ ምክንያት የስራ ውል እንዲቋረጥ ለማድረግ፣ ሰራተኛውም ለአሰሪው ታማኝ በመሆን አገልግሎቱን እንዲሰጥ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሰላምን ማስፈን ነው፡፡ ሕግ ሲተረጎምም ይህንን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን እንዳለበት ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስገነዝቡን ሐቅ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሕግ ሊተረጎም የሚገባው የሕጉን አላማ በሚያሳካ መልኩ ስለመሆኑ የሕግ አተረጓጎም መርሆዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም አንድ የሕብረት ስምምነት የሌለው አሰሪው ሰራተኛው የዲስፕሊን ጉድለት ፈጽሟል የሚልበትን ጉዳይ ለማጣራትና ለመመርመር ሰራተኛውን ከአንድ ወር ጊዜ ላልበለጠ ጊዜ ቢያግድ እርምጃው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(4) የሚሸፈን አይደለም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ መሠታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 48933 ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 89046 መጋቢት 01 ቀን 2002 ዓ/ም በትእዝዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የህብረት ስምምነት ባይኖረውም ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉትን ድርጊት ለማጣራት ወይም ለመመርመር በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) መሠረት ለአንድ ወር ጊዜ ያህል ማገድ ይችላል ብለናል፣ እገዳው ተነስቶ ተጠሪን ወደ ስራ ይመልስ ተብሎ ሊገደድ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54326

ኀዳር 03 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**:- አንበሳ ጫማ አ/ማህበር -የቀረበ የለም

**ተጠሪ**:- ወ/ሮ እትሁን አያሌው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት አድርጐ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በምእራብ አማራ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር የግል ስራ ክርክር ሲያደርጉ ከቆዩ በሁዋላ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በሰ/መ/ቁ. 44515 የቅጥር ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው በማለት ውሳኔ ከሰጠ በሁዋላ ታህሣሥ 16 ቀን 2002 ዓ.ም በቁጥር 11/መ/485/2-3 በተፃፈ ደብዳቤ ከባህር ዳር ሽያጭ መደብር ወደ ሃዋሳ ሽያጭ መደብር ያለበቂ ምክንያት ያዛወራቸው መሆኑን በመግለጽ ዝውውሩ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ክሱ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ በቋሚ ቦርድ ሊታይ የማይገባው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከሩ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ግን ድርጅቱ ዝውውሩን ለማድረግ የወሰነው ድርጅቱ ያለበት ቦታ ለኢንቨስትመንት የተሰጠ በመሆኑ በህብረት ስምምነቱ መሰረት መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ቋሚ ቦርድም ጉዳዩን መርምሮ ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውጪ የተፈፀመ መሆኑን በማረጋገጥ ዝውውሩ ተገቢ አይደለም በማለት ሰርዞታል፡፡ ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ድርጅት ወኪል መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ቦርዱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን አይችልም፣ዝውውሩም የተከናወነው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት ነው የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ



www.chilot.me

ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የተጠሪ ዝውውር ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐአል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ቀርበው የፁሁፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ላይ የግል የስራ ክርክር አቅርበው በዚህ ሰበር ችሎት ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረች ሰራተኛ ነች ተብሎ ውሳኔ ጥቅምት 25 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ አመልካች ድርጅት ታህሣሥ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ዝውውሩን መፈፀሙን፣ ዝውውሩን ለመፈፀም አመልካች በምክንያትነት የጠቀሰው ድርጅቱ ያለበት ቦታ ለኢንቨስትመንት በመፈለጉ ቦታውን እንዲለቅ ከሚመለከተው አካል ትእዛዝ የደረሰው መሆኑን፣ሆኖም ዝውውሩ በሁሉም ሰራተኛ የተከናወነ ሳይሆን በተጠሪ ላይ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ቋሚ ቦርድም ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረት የተደረገ ሳይሆን ከሕጋዊ ምክንያቶች ውጪ መከናወኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጡን ከቦርዱ ውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው ቦርድና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ ስለመፈፀሙ በፍሬ ነገር ደረጃ የተስማሙበት ከሆነ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የፍሬ ነገር ወይም የማስረጃ ምዘና እንጂ የሕግ ትርጉም ጥያቄ አይደለም፡፡ ፍሬ ነገርና ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ደግሞ የዚህ ሰበር ችሎት ሥልጣን አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው የተባለው ተጠሪ ከአመልካች ላይ የነበራቸው ክስና ከዚህ በሁዋላ የተከናወኑትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤ማስረጃዎቹም ተመዝነው በመሆኑ የመሰረታዊ የሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ እና በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችል ሁኖ አላገኘውም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 06880 መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም የቦርዱን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57068

ሕዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ማህሌት ዓለሙ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ ሰናይት መጫ (3 ሰዎች) - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በስራ ላይ ስለሚደርስ የሞት ጉዳትና የካሳ አከፋፈሉን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በግልግል ጊዜ ቁጥር II ሣሊኒ ኮንስትራቶሪ ኤስ.ፒ.ኤ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አቶ ሙላቱ ገብረ ማርያም በተከሳሽ ድርጅት ተቀጥሮ ሚያዚያ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በዋሻ ውስጥ ስራ ላይ እያለ የኦክስጅን እጥረት ገጥሞት ከዋሻው ወደ ውጪ በባቡር ፉርጐ ሲወጣ ከፉርጐው ተንሸራቶ በመውደቅ በኩላሊቱና በጎን አጥንት መቀጥቀጥ አደጋ ደርሶበት ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን ገልፀው በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ካሳ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ተከሳሽ ለክሱ በሰጠው መልስም ሟች በአደጋ ምክንያት ሕይወቱ ለማለፉ ከሳሾች ማስረጃ አለማቅረባቸውን በተቃራኒው ሟች እንደታመመ የፉፋ ጤና ጣቢያ በካርድ ቁጥር 760 የጻፈው ሪፈራል የሟች በሽታ ታይፎይድ እና የሽንት ቧንቧ ኤንፌክሽን የሚል ስለሆነ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ ተወስዶ ካሳ የሚከፈልበት ምክንያት የለም በማለት መልሱን ከሰጠ በሁዋላ ባለው የመድን ውል መሠረት የአሁኑ አመልካች ድርጅት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከርለት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለስር ተከሳሽ ሠራተኞች የስራ ላይ ጉዳት የመድን ሽፋን የሠጡ መሆኑን በመግለጽ ሟች በስራ ላይ አደጋ አልደረሰበትም፣ የሞተው በወባና በታይፎይድ ስለሆነ በስራ ምክንያት የመጣ አደጋ ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ ካሳ የሚያስከፍል አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የስር ተከሳሽን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(2) እና 110(3) ድንጋጌዎች መሠረት የሞት ጉዳት ካሳ ለሟች ጥገኛ ለሆኑት ተጠሪዎች እንዲከፈል የአመልካች የኃላፊነት መጠንም በሰበር ተከሳሽ ጋር ባለው የመድን ውል መሠረት እንዲሆን እንዲሁም ክፍያው ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፈል ገልፆ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች



www.chilot.me

ባለመስማማት ይግባኙን ለየም ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፣ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩ የፌዴራል በመሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚገባ አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሰኔ 7 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ሟች ሕይወቱ ያለፈው በስራ ላይ በመጣ አደጋ ሳይሆን በታይፎይድ በሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽንና ወባ ስለመሆኑ የሕክምና ማስረጃ እየገለፀ የሰው ምስክሮች የሰጡት ቃል መሠረት ተደርጐ አደጋው በስራ ላይ የደረሰ ነው ተብሎ የሟች ጥገኞች ካሳ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 97፣ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005፣ 2011 እና 2012 ድንጋጌዎች ውጪ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሞት መንስኤው በስራ ላይ በመጣ ጉዳት ሳቢያ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ስድስት ገጽ የአመልካችን ቅሬታ ነጥቦችም በመንቀፍ፣ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ህጋዊነት በመዘርዘር መልሳቸውን የሰጡ ሲሆን አመልካችም ጥቅምት 07 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ምላሽ ያስፈልጋል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ ሟች አቶ ሙላቱ ገ/ማሪያም የሞቱት በስራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ ነው? ወይንስ በሌላ ምክንያት? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ (Occupational injury) ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ (occupational disease) እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 95(2) ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 97 ደግሞ በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ማለት ማንኛውም ሰራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ስራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ የሚያቀርበው ወገን ጉዳቱ የደረሰው በአንቀጽ 97 በተመለከተው አኳኋን በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት መሆኑንና እንደዚሁም በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ቅርብና ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖሩን (Proximate cause and effect relationship) ማስረዳት እንደሚጠበቅበት ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል የአሰሪው ኃላፊነት በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ (strict) ስለሆነ ካሣ ጠያቂው ወገን ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማሳየት ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ የጉዳት አድራሹን ወይንም የአሰሪውን የአእምሮ ሁኔታ (State of Mind) ማስረዳት እንደማይጠበቅበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ሟች ሙላት ገ/ማሪያም በስር ተከሳሽ ድርጅት ተቀጥሮ ሚያዚያ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በዋሻ ውስጥ ስራ ላይ እያለ የኦክስጅን እጥረት ገጥሞት ከዋሻው ወደ

ውጭ በባቡር ፉርጎ ሲወጣ ከፍርጎው ተንሸራቶ በመውደቅ አደጋ ደርሶበት ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን ተጠሪዎች ገልፀው በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ካሳ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብኝም የሚለው ሟች በስራ ላይ በደረሰ አደጋ መክንያት ሕይወቱ ለማለፉ ተጠሪዎች ማስረጃ አለማቅረባቸውን በተቃራኒው ሟች እንደታመመ የፉፋ ጤና ጣቢያ በካርድ ቁጥር 760 የጻፈው ሪፈራል የሟች በሽታ ታይፎይድ፣ ወባ እና የሽንት ቧንቧ ኤንፌክሽን የሚል ስለሆነ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ የሚቆጠር አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን ምስክሮችን አቅርቦ የሰማ ሲሆን የተጠሪዎች ምስክሮች በክሱ በተገለፀው መሠረት መመስከራቸውን ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍ/ቤቶች የተቀበሉት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ይኸው የተጠሪዎች ምስክሮች ቃል ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚለው የሕክምና ማስረጃው ከሚገልፀው ይዘት ውጪ ነው በማለትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005፣ 2011 እና 2012 ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሟች ጉዳቱ ደረሰ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ በሕክምና ሲረዳ የቆየ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የሕክምናው ማስረጃ በሟች ላይ ምርመራ በተደረገበት ወቅት ታዩ የተባሉ ሁሉም ምልክቶች ከመነሻ የተከሰቱና ለሞቱ ምክንያት መሆናቸውን የሚገልጽ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልጽ የሚያሳየው ደግሞ በተጠሪዎች በኩል የቀረቡት የሰው ምስክሮች ከመነሻው የነበረውን ሁኔታና በሟች ላይ የደረሰውን ጉዳት ገልፀው ለሞቱ ምክንያት የሆነው ነገር የተከሰተው ሟች በስራ ላይ እንዳለ ስለመሞቱ ማስረዳታቸውን በመቀበል የህክምና ማስረጃው ደግሞ የተጠሪዎችን ምስክሮች ቃል ሊያስተባብል አለመቻሉን በመግለጽ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች መመዘናቸውን ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የቀረቡትን ማስረጃዎች በማመዛዘን ውሳኔ የሰጡ ሲሆን የሕክምና ማስረጃው ይዘት ሲታይም ተጠሪዎች በሟች ላይ በደረሰው አደጋ የኩላሊት መቀጥቀጥ የደረሰ መሆኑን የገለጹትን የህክምና ማስረጃ ሟች የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን ደርሶበት የነበረ መሆኑ የሚገልጽ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የሕክምናው ማስረጃ በይዘቱ ከሰው ምስክሮች ቃል ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው ለማለትም የሚያስችል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘን አደጋው በስራ ቦታ ላይ የደረሰ ስለመሆኑ የደመደመ በመሆኑ ክብደቱ ለሕክምና ማስረጃ የግድ መሰጠት አለበት ሊባል የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ፍሬ ነገርን የጣራና ማስረጃዎቹን የመዘነ ከሆነ ይኸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑ መሠረት ተደርጐ ጉዳዩ በዚህ ሰበር ችሎት የሚታይበት አግባብ የሌለ መሆኑን በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሟች በስራ ቦታ ላይ በደረሰው አደጋ መሞታቸውን በሕጉ አግባብ መረጋገጡን መሠረት አድርጐ የተሰጠ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57541

ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፡-* ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፣*** የቻይና መንገድና ድልድይ ሥራ ድርጅት

***ተጠሪ፣*** ግርማ ቡሽራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የሥራ ውሌን ያለአግባብ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለው እንዲወሰንለት ጠይቆአል አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ እራሱ ሥራውን ትቶ ሄደ እንጂ እኔ አላባረርኩትም ሥራውን ትቶ የሄደው በብድር የወሰደውን ገንዘብ ላለመክፈል ነው በማለት ተከራክሯል ክሱን የሰማው የባህር ዳር ወረዳ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር አልተቀበለም፡፡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለትም አመልካች የተጠየቀውን ክፍያ ለተጠሪ ይከፍል ዘንድ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ያፀና ሲሆን በመጨረሻ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረውን የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራቀኙ ወገኖች ጭብጡን መሠረት በማድረግ ያሰሙት ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከተሰሙት ውሣኔዎች ይዘት መገንዘብ እንዳቻልነው ተጠሪ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ ነው በማለት ሲከራከር፤ ተጠሪ ደግሞ በኔ በኩል ተጠሪን አላሰናበትኩም ሥራውን ትቶ የሄደው እራሱ ነው ይህን ያደረገውም በብድር የወሰደውን



www.chilot.me

ብር 2000 አጠቃሎ ሳለመክፈል ለመሸሽ በማሰብ ነው በማለት ተከራክሮአል ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤትም በእርግጥ ተጠሪ በአሠሪው ድርጅት የበላይ ሃላፊ ወይም ሠራተኛን የማሰናበት /የሥራ ውል እንዲቋረጥ የመወሰን/ ሥልጣን ባለው ሃላፊ ስለመሰናበቱ ወይም ሥራውን እንዲለቅ ስለመደረጉ አላረጋገጠም በውሣኔው እንዳመለከተው አመልካች ይሰራው በነበረው የአስፓልት መንገድ አካባቢ ተጠሪ እና አንድ ቻይናዊ ሲጣሉ አይተናል የሚሉ መንገደኞች የሰጡትን ምስክርነት ብቻ በመያዝ ነው ወደውሣኔው ያመራው ይህ ማለት ግን ተጠሪ በድርጅቱ ከሥራው ስለመሰናበቱ ያመለክታል ማለት አይደለም ከፍ ሲል እንዳመለከትነው አመልካች እኔ ተጠሪን አላሰናበትኩም በማለት እስከተከራከረ ድረስ በእርግጥ በአመልካች ስለመሰናበቱ ተጠሪ የማስረዳት ግዴታ ነበረበት፡፡ እንደምንመለከተው ግን ተጠሪ የማስረዳት ሸክሙን /ግዴታውን/ አልተወጣም በሌላ አነጋገር በእርግጥ በአመልካች ኃላፊዎች የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ስለመሆኑ ሊያስረዳለት የሚችል ማስረጃ ከነጭራሹ አላቀረበም፡፡ ከዚህ የተነሳም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት ያለው ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የሕግ መሠረት የሌለው ውሣኔ ደግሞ ትክክለኛ ውሣኔ ሊባል ስለማይችል አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>***ው ሣ ኔ***</u>

1. የባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18489 መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 39337 ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 09846 ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ተቋርጦአል በማለት የጠየቃቸው ክፍያዎች ሊከፈሉት አይገባም ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

*መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡*

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

*ም.አ*

የሰ/መ/ቁ. 46075

ታህሣሥ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፣** አቶ ንጉስ ሐዱሽ አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፣** የመቀሌ ዩንቨርሲቲ የተማሪዎች ዲን አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የግራቀኙን ከሥራ ቅጥር የመነጨን ክርክር የሚገዛው የትኛው ህግ ነው የሚለውን ለይቶ ዳኝነት ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በተጠሪ ጽ/ቤት በሻሂ ማሽን ሠራተኝነት በደመወዝ ተቀጥሮ ሲሰራ የቆየ ለመሆኑ እና በመጨረሻም ተጠሪ በሰጠው ምክንያት ከሥራ የተሰናበተ ለመሆኑ ተጠሪ የካደው ጉዳይ አይደለም፡፡

በዚህ መነሻ በተጠሪ በኩል የተፈፀመው የሥራ ስንብት የአሠሪና ሠራተኛ ህግ ከደነገገው ውጭ ስለሆነ ልዩ ልዩ ክፍያ ይገባኛል በማለት የአሁን አመልካች ለቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት በጥሪው መሠረት የበኩሉን መልስ ለማቅረብ አልቻልም በሚል ምክንያት ክሱ የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን የክስ አቤቱታ እና እንደ አቤቱታው ለማስረዳት ያቀረበውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ ተመልክቶ በግራቀኙ መካከል የሥራ ቅጥር ግንኙነት እንዳለ እና ከዚህ የቅጥር ግንኙነት የተነሳው ክርክር የሚዳኘው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት መሆኑን ገልፆ ሠራተኛው ለቀጣሪው ከሰጠው የአገልግሎት ዘመን አንፃር ሊሰጠው የሚገባው የአንድ ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ብቻ ሆኖ አልተገኘም የማስጠንቀቂያ አሰጣጥ ሥርዓቱ የተሟላ ሆኖ አልተገኘም ስለሆነም ከአዋጅ አንቀጽ 35/1/ለ/ አንፃር ሲታይ ስንብቱ ህግ ከደነገገው ውጭ ሆኖ ተገኝቷል በማለት ልዩ ልዩ ክፍያ እንዲከፈለው ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ የአሁን ተጠሪ በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሯል፡፡

ዋነኛ የይግባኝ አቤቱታውም የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የሚተዳደረው በአዋጅ ቁጥር 515/99 እና በደንብ ቁጥር 61/99 መሠረት በመሆኑ ዩኒቨርቲው ተከራካሪ የሆነበትን ይህን መሰል ጉዳይ

በሚተዳደርበት አዋጅ መሠረት እንጂ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚገዛ አይደለም የሚለው ይገኝበታል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የአሁን ተጠሪ እንደሚለው ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚዳኝ አለመሆኑን የሥር ፍ/ቤት ተገናዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 9 እና 231/1/ለ/ መሠረት መዝገቡን መዝጋት ነበረበት በሚል ምክንያት ተችቶ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አለማግኘቱን ገልፆ ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት የሆነውን የሰበር አቤቱታ የአሁን አመልካች አቅርቧል፡፡

የሰበር ቅሬታው ይዘትም የሥር ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የወሰነው የአሁን ተጠሪ በሌሉበት ስለሆነ ይህ ተጠሪ በዚያው ጉዳይ ተከራካሪ ለመሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78 መሠረት በክርክሩ እንዲገባ ካልተደረገ በቀር በቀጥታ የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ መብት የለውም ይህን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አላየውም እኔን የቀጠረኝ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ሲሆን የተቀጠርኩትም ለሻሂ ክብብ በሻሂ ማሽን ሠራተኛነት ነው የምሰራበት ክበብ በእራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደር በተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ቁጥጥር የሚንቀሳቀስ በመሆኑ በቀጥታ በአዋጅ ቁጥር 515/99 ሆነ በደንብ ቁጥር 6199 የሚገዛ የሚሸፈን አይደለም የሚለውን በግራቀኙ መካከል ለተነሳው የህግ ጥያቄ መነሻና አንኳር የሆነውን ክርክር አቅርቧል፡፡

በዚህ የሰበር አቤቱታ ላይ የአሁን ተጠሪ ቀርቦ የበኩሉን ክርክር ማቅረብ ይችል ዘንድ መጥሪያ ተልኮለት መጥሪያው የደረሰው ለመሆኑ በእራሱ ማህተም ካረጋገጠ በኃላ እንደ ጥሪው የመደመጥ መብቱን ሊጠቀም አልቻለም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች በተጠሪ በኩል የተጠቀሱት አዋጆች ለግራቀኞችን የቅጥር ሁኔታ ተፈፃሚነት የላቸውም በማለት ለቀረበው ክርክር በተጠሪ በኩል ሊቀርብ የሚችል ማስተባበያ ካለ በአከራካሪ ነጥብነቱ ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት መስጠት አልተቻለም የተለየ ማስተባበያ እስካልቀረበ ድረስም አመልካች እንዳለው እንዲያገለግል የተቀጠረበት የሻሂ ክበብ በእራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደር ከሆነ ከዚህ መሰል ቁጥር የመነጨን ክርክር ተጠሪ የጠቀሳቸው ህጎች የማይገዙ ይልቁንም ክፍተቱ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ስለተገኘ ወይም ለዩኒቨርሲቲው የህ/ሰብ ክፍል አገልግሎት ስለሰጠ ብቻ በደፈናው በሲቪል ሠራተኛ አስተዳደር ህግ ይገዛል ለማለት የሚያበቃ አለመሆኑ እየታወቀ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙ ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚገዛ አይደለም በዚህም ሳቢያ የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 7229 በ19/6/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 29531 በ30/7/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከሥራ ቅጥር የመነጨውን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሥልጣን ባለው የወረዳ ፍ/ቤት ታይቶ ዳኝነት የተሰጠበት ስለሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ ስልጣን የመ/ቁጥር 7229



www.chilot.me

አንቀሳቅሶ በሌላው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጠበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት መልሰናል፡፡ ግልባጩ ይድረሰው፡፡

አመልካች ለዚህ ክርክር ያወጣውን ወጭ በእራሱ ይሽፍን ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60685

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ በዛብህ እሸቴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሳሊኒ ኮንስትራክሽን - ጠበቃ አቶ አሥራኤል ተክሉ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ተቀብሎ በማስተናገድ የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው? የሚለውን አስመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች አሠሪዬ የአሁን ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ይህ ካልሆነ ያለአግባብ በመሰናበቴ ምክንያት ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ይፈፅምልኝ በማለት ባቀረቡት ክስ በማስረጃነት የቀረቡት ግራ ቀኙ ያደረጉትን የሥራ ቅጥር ውል ነው፡፡

የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ከዚህ የቅጥር ውል በመነሳት የሥራ ቅጥር ውሉ የተደረገው በተባበሩት አረብ ኤምሬት የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ነው፡፡ የሥራ ቦታውም በዚሁ ሀገር በሚገኘው የተጠሪ ቅርንጫፍ መ/ቤት መሆኑ ተረጋጋጧል፡፡ ይህም ከሆነ ጉዳዩ በዓለም አቀፍ የግል ሕግ መሠረት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ አስረጂ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11/2/ መሠረት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባለመሆኑ ሥልጣን የለኝም በማለት አመልካችን አሰናብቷል፡፡

የአሁን አመልካች የቅጥር ውል የፈፀምኩት ኢትዮጵያ ከሚገኘው የተከሳሽ መ/ቤት ጋር ነው፤ ይህ አልታየልኝም በማለት ክርክር በማቅረቡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክርክሩን እንደ አዲስ የቀረበ መሆኑን ተገንዝቦ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲረዳ ለዚሁ ክርክሩ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቀጠሮ ቢሰጠውም ይህንኑ መፈፀም አለመቻሉን አይቶ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው ክርክርም በሥር ፍ/ቤት አንስቶ ከተከራከረበት በይዘቱ የተለየ አይደለም፡፡

አመልካች የሥራ ቅጥር ውል የተፈፀመው ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኘው ቅርንጫፍ መ/ቤት ጋር ነው የሚለውን ክርክር በሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለማረጋገጥ የተሳነው መሆኑ የተገለፀ ስለሆነና የዚሁ ክርክር ይዘት በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችልን ፍሬ ነገር ጉዳይ የሚመለከት በመሆኑ በሰበር ደረጃ ሊታይ የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ግራ ቀኙ ያደረጉት የሥራ ቅጥር ውል ጋር በተያያዘ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን የሚገዛው የተባበሩት አረብ ኢምሬት ሀገር ሕግ ስለመሆኑና የሥራ ቦታውም በዚሁ አገር ውስጥ ለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

ይህም ከሆነ ክርክሩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ቢነሳ በየትኛው ሀገር ሕግ ታይቶ ዳኝነት ማግኘት የሚገባው ስለመሆኑና የሥራ ቦታውስ ኢትዮጵያ ውስጥ ሳይሆን በውጭ ሀገር መሆኑን ሁሉ ጠቅሰው በውል ለይተው አስቀምጠውታል፡፡ ይህም ከሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች የየትኛው ሀገር ነው? ጉዳዩስ የሚታው በየትኛው ሀገር ሕግ ነው የሚሉትን ጥያቄዎች ስለሚያስነሳ ይህን መሰል የሕግ ጥያቄ ያካተተ ጉዳይ ደግሞ በዓለም አቀፍ የግል ሕግ መሠረት ታይቶ የሚዳኝ ነው፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ለማቋቋም በወጣው ሕግ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11/2/ መሠረት በክርክሩ ውስጥ የተካተተው የገንዘብ መጠን ይብዛም ይነስም ክርክሩ የዓለም አቀፍ የግል ሕግን የሚመለከት ሆኖ ከተገኘ ከጉዳዩ ዓይነት አንፃር ብቻ በማየት ጉዳዩ ለመጀመሪያ ጊዜ አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

የሥር ፍ/ቤትም የክርክሩን ባህሪ በማየት በዚሁ ሕግ መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም፡፡ ጉዳዩ መታየት ያለበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው በማለት የሰጡት ትርጉም በአግባቡ የተሰጠ እንጂ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በየትኛው ደረጃ በሚገኘው ፍ/ቤት ነው? የሚለውን ለይተው ዳኝነት ሰጡበት እንጂ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የሚያስችላቸው ሥልጣን የላቸውም ከሚል ትርጉም ላይ አልደረሱም፡፡ ዳኝነት በዚህ አኳኋን የተሰጠ መሆኑ እየታወቀ የአሁን ተጠሪ ጉዳዩ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ሊታይ የሚችል አይደለም የሚለው የሰበር ክርክሩ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ እንደ ሥርዓቱ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዳኝነት ለማሳረም ቀርቧል እንኳ ቢባል ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የሥራ ክርክር ለመዳኘት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/3/ መሠረት እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት በሰበር ሊታረም የሚገባው የመጨረሻ ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው በዚህም መሠረት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት በየትኛው ደረጃ የሚገኘው የፌዴራል ፍ/ቤት ነው የሚለውን አስመልክቶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ. 45888 ታህሣስ 12 ቀን 2002 ዓ.ም. እና በኮ/መ/ቁ. 87855 ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጡት ብይን እና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት ያቀረበው የሰበር ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም

ይህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59320

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፣* ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

***አመልካች፡-*** ጊዮን ሆቴሎች ድርጅት ነገረፈጅ እሱባለው ዋለልኝ ቀረቡ

***ተጠሪ፡-*** አቶ ስለሺ አምዴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው ተጠሪ አመልካች ህዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም አላግባብ ከሥራ አግዶትና አሰናብቶት በፍርድ ቤት ውሣኔ ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም ወደሥራ የተመለሰ መሆኑን ገልፆ በጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም የሰራሁበት የሃያ ቀን ደመወዝ የ2001 ዓ.ም የበጀት ዓመት ቦነስና የሰርቪስ ቻርጅ እንደዚሁም ከሀምሌ 2001 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም አስር ፐርሰንት የደመወዝ ጭማሪ እንዲከፍል ውሣኔ ይስጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ የሃያ ቀን የደመወዝ ክፍያ በይርጋ ይታገዳል፡፡ ከሣሽ /ተጠሪ/ የ2001 ዓ.ም የበጀት ዓመት ቦነስ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ በህግም ሆነ በህብረት ስምምነቱ የማይገባቸው ክፍያ በመሆኑ ክሱ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ አመልካች ትርፍ በተገኘበት 2001 ዓ.ም የበጀት ዓመት ስድስት ወር ያልሰሩ በመሆኑ ያቀረቡት የቦነስ ክፍያ ህግንም ሆነ በህብረት ስምምነቱን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ ተከሣሽ /አመልካች/ ለከሣሽ /ተጠሪ/ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪን አላግባብ ከሥራ ያባረረው አመልካች በመሆኑ አመልካች ተጠሪ የጠየቀውን የቦነስና ሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ የመክፈል ሃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አስራአንድ ወራት እንዳልሰሩ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ባልሰሩበት ወቅት ለተገኘው ትርፍ የሚከፈለው የቦነስ ክፍያ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ እንድንከፍል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ



www.chilot.me

የህብረት ስምምነቱን ግልፅ ድንጋጌ የሚጥስና የህግ መሠረት የሌለው ነው። ስለሆነም በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል። ተጠሪ በበኩላቸው የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በትምህርት ዝግጅቴና በሥራ ልምድ ከሌሎች ሠራተኞች በተሻለ ሁኔታ ላይ ነበርኩኝ በ2001 ዓ.ም ያልሰራሁትና የሥራ አፈፃፀም ያልተሞላልኝ አመልካች ከህግ ውጭ ከሥራ ስላሰናበተኝ በመሆኑ ጥፋቱ የተጠሪ ሣይሆን የአመልካች ነው። ስለዚህ አመልካች በህብረት ስምምነቱ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዳላሟላ ከህግ ውጭ ከሥራ አሰናብቶኝ የቆየ በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገቢና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል። አመልካች መጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለተጠሪ የ2001 ዓ.ም የበጀት ዓመት ቦነስ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ እንዲከፍል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

አመልካች የቦነስ ክፍያ የሚከፍለው የሥራ አፈፃፀሙ ተመዝኖ በአማካኝ ከሃምሳ ፐርሰንት በላይ መሆኑ ሲረጋገጥና ሠራተኛው በበጀት ዓመቱ ከስድስት ወር በላይ የሠራ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ በአስረኛው የህብረት ስምምነት በአንቀጽ 34/5/ለ እና አንቀጽ 356/ሐ/ ተደንግጓል። የሰርቪስ ቻርጅ የሚከፈለውም በወቅቱ ሥራ ላይ ለነበሩና አገልግሎት ለሰጡ ሠራተኞች እንደሆነ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 28/4/ የተመለከተ ሲሆን የደመወዝ ጭማሪ የሚደረገው የሠራተኛው የሥራ አፈፃፀም ከተመዘነ በኃላ እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል። አንድ ሠራተኛ አሠሪው ጥቅም እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚችለው በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የሥራ ውል የህብረት ስምምነቱን ወይም የአሠሪና ሠራተኛ ህግን መሠረት በማድረግ ነው። በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሥራ ውል አመልካች ተጠሪን አላግባብ ከሥራ ያገደ ወይም ያሰናበተ መሆኑ ተረጋግጦ በፍርድ ሲወሰን ተጠሪ ባልሰራበት የበጀት ዓመት የሚከፈል የቦነስ ክፍያ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ የሚከፍል ስለመሆኑ እንደማይገልፅ ግራቀኙ በሰበርና በሥር ፍርድ ቤት ካደረጉት ክርክር ለመገንዘብ ችለናል። አመልካች ተጠሪን ከሥራ ሲያግደውና ሲያሰናብተው ሥራ ላይ የነበረው አስረኛው የህብረት ስምምነት ተጠሪ ከሥራ ታግዶ ወይም ከሥራ ተሰናብቶ በነበረበት ጊዜ የተገኘ የቦነስ ክፍያ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ አመልካች እንዲከፍል የማያስገድደው መሆኑን ከላይ ከጠቀስናቸው የህብረት ስምምነቱ ድንጋጌዎች ይዘት ተገንዝበናል።

አሰሪው አላግባብ ከሥራ የተሰናበተ መሆኑ ተረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ወደ ሥራው እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ በመጀመሪያ ደረጃ የሥራ ክርክር ችሎት ከስድስት ወር ያልበለጠ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ፍርድ ቤቱ የሚወስንለት መሆኑንና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ሥራ የመመለስ ውሣኔው ከፀና ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ውዝፍ ደመወዝ እንደከፈለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንደሚወሰንለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 5 ተደንግጓል። "ደመወዝ" ማለት አንድ ሠራተኛ በሥራ ውሉ መሠረት ለሚያከናውነው ሥራ የሚከፈለው መደበኛ ክፍያ ማለት እንደሆነ በአዋጅ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ ከአሠሪው የሚሰጥ ጉርሻ /ቦነስ/ እንደ ደመወዝ ክፍያ የማይቆጠር መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ በግልፅ ተደንግጓል። ከላይ ከተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች አመልካች ተጠሪን አላግባብ ከሥራ አሰናብቶ በመገኘቱ ተጠሪን ወደ ሥራ እንዲመልስ የአሠሪና ሠራተኛ የመጀመሪያ ደረጃ የሥራ



www.chilot.me

ክርክር ችሎትና የይግባኝ ችሎት ሲወስኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት እስከ ስድስት ወር ወይም እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፍል ከሚወሰን በስተቀር ተጠሪ ባልሠራበት ዓመት ለሌሎች ሠራተኞች የተከፈለው ቦነስ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ እንዲከፍል ለመወሰን የሚያስችል የህግ መሠረት የለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከህግ ውጭ አሰናብቶት በፍርድ ቤት ውሣኔ የተመለሰ በመሆኑ ባልሠራበት ዓመት የተገኘው ትርፍ ለሠራተኞች የተከፈለውን የቦነስ ክፍያ የደመወዝ ጭማሪና የሰርቪስ ቻርጅ ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ የሚጥስና የህብረት ስምምነቱን መሠረት ያላደረገ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

***ው ሣ ኔ***

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሠ/መ/ቁ 64079

ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ ጌትነት መኮንን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የጅማ ወረዳ ፍርድ ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ተጣርቶ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች አላግባብ ከሥራ አሰናብቶኛል ወደ ሥራ እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የመብራት ቢል ሰብሳቢ ሆኖ ሲሰራ ብር 11,177.01 /አስራ አንድ ሺ አንድ መቶ ሰባ ሰባት ብር ከዜሮ አንድ ሣንቲም/ ለግል ጥቅሙ ያዋለ መሆኑ በኦዲተር ተረጋግጧል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ጥፋቱ መፈፀሙን በአወቀ በሰላሣ ቀን ውስጥ ከሥራ አላሰናበተኝም፡፡ ስለዚህ በአዋጅ ቁጥር 277/96 አንቀፅ 37/3 በመተላለፍ የፈፀመው የሥራ ስንብት ህገወጥ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከላይ የተገለፀው ገንዘብ ዋጋ ያላቸውን ቢሎች ወስዶ ለግል ጥቅሙ ያዋለ መሆኑ ከህዳር 21 ቀን 2002 ዓ.ም እስከ ህዳር 29 ቀን 2002 በተደረገው የኦዲት ምርመራ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከሥራ የተሰናበተው ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ነው፡፡ ስለዚህ ስንብቱ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 3 የሚጥስ በመሆኑ ህገ ወጥ ነው በማለት አመልካች የተጠሪን የስድስት ወር ደመወዝ ከፍሎ ወደ ሥራ እንዲመልሰው ወስኗል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት በማድረግ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ 11,177.01 ብር ቢል ለግል ጥቅም ያዋለ መሆኑን ኦዲተሮች ሪፖርት ያደረጉት ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ነው አመልካች ተጠሪን በማገድ በህብረት ስምምነቱ መሠረት የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ ተጠሪ ከሥራ እንዲሰናበት የካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ተወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት



www.chilot.me

ደብዳቤው ውጭ የሆነበትንና ተጠሪ የወሰደበትን ጊዜ ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም በማየት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ጥር 4 ቀን 2003ዓ.ም በተፃፈ መልስ ከሥራ ለማሰናበት የፃፈው ደብዳቤ ወጭ የሆነው ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን በሰበር ማመልከቻው አምኗል፡፡ አመልካች በእኔ በፃፈልኝ የስንብት ደብዳቤ የኦዳተሮች ሪፖርት የደረሰው ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑና ከሥራ ያገደኝ ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑንና ከሥራ ያሰናበተኝ ሚያዚያ 1 ቀን 2002 መሆኑን በግልፅ ካሰፈረ በኋላ ዕውነታውን የሚሸፋፍን የሰበር አቤቱታ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ እንዲያቀርብ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ የመልስ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ወደ ሥራ እንዲመልስ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ተጠሪ በስህተት በተደራቢነት ከተሰጠው የደንበኞች የሒሳብ መሰብሰቢያ ቢል ለግል ጥቅሙ በማዋል ብር 11,177.01 ሣንቲም ያጎደለ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ ይህንን ጥፋት ያጠፋ መሆኑ በኦዲተሮች ሪፖርት የተደረገለት በህዳር ወር መጨረሻ እንደሆነ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው በወረዳው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ለተጠሪ የፃፈው የስራ ስንብት ደብዳቤ ወጭ የሆነው ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ እንዲሰናበት የተወሰነው የካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ነው፡፡ ደብዳቤው ወጭ ሣይሆን የቀረው የተጠሪን መምጣት ስንጠብቅ ነው በማለት በሰበር አቤቱታው የገለፀ ቢሆንም አመልካች ለተጠሪ የሥራ ስንብት ደብዳቤ ወጭ አድርጎ የሰጠው ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም እንደሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች የተጠሪን ጥፋት ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሣ ቀን ውስጥ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሥራ ስንብት ደብዳቤ ያልፃፈ በመሆኑ የአመልካች እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 3 በተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል በማለት የወረዳውን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

2. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ በመሆኑ ህገወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪ የሥራ ስንብት ህገወጥ ነው የሚባል ከሆነ ተጠሪ ወደ ሥራ ቢመለስ መልካም የሥራ ግኑኙነት ስለማይኖረን በአማራጭ በአዋጅ ቁጥር 43 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለውት ተጠሪ እንዲሰናበት ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን አማራጭ የዳኝነት ጥያቄ ማለፋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ የሥራ ውሉን ባለማቋረጡ እንጅ ተጠሪ ከባድ የዕምነት ማጉደል ተግባር የፈፀመ መሆኑ በአመልካች ኦዲተሮች ተረጋግጧል፡፡



www.chilot.me

አመልካች የደንበኞች ቢልና ክፍያ ሰብሳቢ የነበረ መሆኑ አመልካችና ተጠሪ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል፡፡ ተጠሪ ሲሰራበት የነበረው የሥራ መደብ ከፍተኛ የሆነ ዕምነት የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ በኋላ ተጠሪ ወደ ሥራ ቢመለስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የመተማመን መንፈስ እና የመልካም የሥራ ግኑኝነት ይኖራቸዋል ብሎ ለመደምደም የማይቻል በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በአማራጭ ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 3 በሚደነግገው መሠረት ለተጠሪ ካሣ ከፍሎ እንዲያሰናብተውና ክፍያውም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት ታስቦ እንዲከፍለው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የጅማ ወረዳ ፍርድ ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ወደ ሥራ ቢመለስ ከአመልካች ጋር መልካም የሥራ ግኑኝነት ሊኖረው የማይችል በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ካሣ ከፍሎ እንዲያሰናብተው በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43/4/ መሠረት ወስነናል፡፡ የክፍያው መጠን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43/4/ መሠረት ተደርጎ ሊሰላ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60464

መጋቢት 8 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን

**ተጠሪ፡-** አቶ ግርማ ወዮሳ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ የተቀጠረበትን የአሠሪውን ሥራ በመሥራት ላይ እያለ ድንጋይ ወድቆበት ሁለት የእግሮቹ ጣቶች ተቆርጠው ዘላቂ የአካል ጉዳት ደርሶበታል ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(3) መሠረት ካሣ ብር 57,442.66 እንዲከፈለው በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

የጉዳት ካሣውን ክስና ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ውሣኔውን የሰጠው የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ቀጥሎም የኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ክርክሩን ከሰማ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት አጽንቶታል፡፡ በመጨረሻም የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው ዘላቂ የአካል ጉዳት ደርሶበታል ተብሎ ካሣ እንዲከፈለው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን አቅርቦ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ በወረዳው ፍ/ቤትም ሆነ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ሊያፀናው ችሏል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ በዚህ ምክንያት የቀረበ ሲሆን የአመልካች ነገረ ፈጅ በ13/1/2003 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የካሣውን ጉዳይ በየደረጃው ያዩት የክልሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡



www.chilot.me

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ተብሎ በመወሰኑ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በ23/5/2003 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በእኔ ላይ ጉዳት ስለመድረሱ እያየና በህክምና ማስረጃም ተረጋግጦ እያለ ሊከፈለኝ የሚገባውን ካሣ እንዳይከፈል ለማድረግ ለሰበር ችሎት አቤቱታ ማቅረቡ ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም፣ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፣ ኪሣራ ተቆርጦልኝ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም በተጠሪው በኩል በቀረበው መልስ ላይ በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥቶበታል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ አጥብቆ የሚከራከረው የቀረበው የሕክምና ማስረጃ በአሁኑ ተጠሪ አካል ላይ ስለደረሰው ጉዳት መጠን የሚያረጋግጥ ስላልሆነ ቋሚ ሙሉ የአካል ጉዳት ደርሶበታል ተብሎ ካሣ ሊወሰንለት አይገባም፤ የጉዳቱ መጠን ባልተገለፀበት ሁኔታ ካሣ እንዲከፈለው መወሰን ስለማይቻል እንደገና ወደ ሆስፒታል ተልኮ የጉዳቱ መጠን ተገልጾ መቅረብ አለበት በማለት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም በአሁኑ አመልካችና በተጠሪው መካከል የአሠሪና ሠራተኛ የሥራ ውል ግንኙነት መኖሩና ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ በአሠሪው የተቀጠረበትን ሥራ በማከናወን ላይ እያለ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ የሚያከራክር ሆኖ የተገኘው የአካል ጉዳት መጠን ደረጃው የሚመደበው በጊዜያዊ የአካል ጉዳት ነው ወይንስ ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ወይንም ደግሞ በዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መሆን አለመሆኑ እና የካሣው መጠን እንዴት ይወሰናል የሚለው ነው፡፡

በሠራተኛው /በአሁኑ ተጠሪ/ ላይ ጉዳት የደረሰው በየትኛው አካሉ ላይ ነው? በቀረበው የሕክምና ማስረጃስ የተረጋገጠው ምንድነው? የሚለውን በተመለከተ፡-

ተተርጉሞ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዞ በቀረበው የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ተጽፎ የሚገኘው እና ቀጥሎ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው  የኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔ ላይ የገለፀው ፍሬ ነገርም ሆነ የማስረጃ ሁኔታ የተምታታ ከመሆኑም በላይ በዚህ መዝገብ በነበረው የክርክር ሂደት ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ በግንባር በችሎት ተገኝቶ ስለደረሰበት የአካል ጉዳት ተጠይቆ ከገለፀውና ካሣየው ጋር የማይገናኙ ነገሮች ያሉበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ላይ የፃፈው ነው ብሎ ያሰፈረው በእግሩ ላይ ድንጋይ ወድቆበት እግሩ የተሰበረና ሲሰራ የነበረውን ግንበኝነት ለመሥራት የማያስችለው ዘላቂ የአካል ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑ የሚገልጽ ሲሆን የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በውሣኔው ላይ በክሱ የተገለፀ ነው ብሎ የፃፈው ለድልድይ የሚሆን ድንጋይ እየጠረበ እያለ ድንጋይ ወድቆበት ሁለት የእግር ጣቶቹ ተቆርጠው እግሩም ተሰብሯል የሚል ነው፡፡ የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤትም በውሣኔው ላይ የፍቼ ሆስፒታል የሃኪሞች ቦርድ የፃፈው የህክምና ማስረጃ በአሁኑ ተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰበት በእግር ጣቱ ላይ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ነው በሚል መንገድ ገልጾታል፡፡ ሆኖም ከሣሹ የአሁኑ ተጠሪ በአካል ቀርቦ ሲጠየቅ የተቆረጡት የእግር ጣቶቹ ሣይሆኑ የግራ እጁ ሁለት ጣቶች እንደሆኑ አሣይቷል፡፡ ሲታይም የግራ እጅ ሁለት የመሀል ጣቶች ተጉምደዋል፡፡ እግሬም ተሰብሯል ብሏል፡፡ በእርግጥ የአሁኑ ተጠሪ ለወረዳው ፍ/ቤት የቀረበው የፍቼ ሆስፒታል የሀኪሞች ቦርድ የሰጠው የሕክምና ማስረጃ ነው በማለት ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ አድርጐት የተገኘው በእንግሊዘኛ የተፃፈው ሲታይ፡-



www.chilot.me

………. Patient Girma Weysswa Boru ……

…. X-ray showing fracture of the femur, and amputation of tip of two fingers from left hand for which reason referred to Tukur Anbassa Hospital.

But he developed mal union and shortening of the high and difficulty in using his leg as previously.

Thus the board decided the above named patient can't work as carpainter.

በሚል የሚነበብ ሲሆን ይህም ተጠሪው ቀርቦ የደረሰብኝ ጉዳት ነው ብሎ ያሣየውን የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሕክምና ቦርድ ጽፏል ብሎ የጠቀሰው የሕክምና ማስረጃ በሚመለከት ተጠሪው ተጠይቆ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሂዶ አለመታከሙን ስላረጋገጠ ፍ/ቤቱ ከየት አምጥቶ በውሣኔው ላይ ሊጽፈው እንደቻለ ለመረዳት አልተቻለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄጄ አልታከምኩም እያለ በውሣኔው ላይ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄዶ የታከመበት ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጐ የህክምና ቦርድ በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂነት ያለው በፊት ሲሰራ የነበረውን የአናጺነት ሥራ ለመሥራት እንደማይችል አረጋግጧል ተብሎ የተፃፈውን ለመቀበል አይቻልም፡፡

ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ የተቀጠረበትን የአሠሪውን ሥራ በመሥራት ላይ ሳለ ጉዳት የደረሰበት ሆኖ ከተገኘ አሠሪው የአሁኑ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ መሠረት ኃላፊነት አለበት፡፡

በሠራተኛው /በአሁኑ ተጠሪ/ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት መጠን በተመለከተም፡-

የአዋጁ አንቀጽ 99(1) "የአካል ጉዳት" ማለት የመሥራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡

በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "2" ሥር በሥራ ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት ውጤቶች፡-

- ጊዜያዊ የአካል ጉዳት
- ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት
- ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት እና
- ሞት

መሆናቸው ተዘርዝሯል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 100 "ጊዜያዊ የአካል ጉዳት" የሚለውን ሠራተኛው ሥራውን ለተወሰነ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን እንዳይችል የሚያደርገው የአካል ጉዳት እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን አንቀጽ 101 ደግሞ ዘላቂ ከፊል ወይም ሙሉ የአካል ጉዳት የሚባለው እንዴት እንደሆነ የሚያብራራ ነው፡፡ በዚህ የሕጉ ትርጓሜ መሠረት ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ማለት ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛን የመሥራት ችሎታ የሚቀንስ የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡



www.chilot.me

ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ማለት ደግሞ ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ በሠራተኛው ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት የሚለውን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑ ከዚሁ ከአዋጅ አንቀጽ 101(2) አንፃር ሲመረመር የፍቼ ሆስፒታል የሕክምና ቦርድ የሰጠው የሕክምና ማስረጃ በአሁኑ ተጠሪ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን የአካል ጉዳት ስለመሆኑ የሚያሳይ ባለመሆኑ በሕጉ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪው የፍቼ ሆስፒታል የህክምና ቦርድ በፃፈው የሕክምናው ማሥረጃ ላይ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሂዶ እንዲታይ ባለው መሠረት ሣይሄድ መቅረቱን ራሱ ያረጋገጠ ሲሆን አመልካች ተጠሪው እንደገና በሌላ ሆስፒታል ታይቶ የጉዳቱ መጠን ተረጋግጦ እንዲቀርብ የጠየቀውንም ከሰጠው መልስ እንደሚታየው የሚስማማበት ሣይሆን ባለው ታይቶ እንዲወሰን የሚጠይቅ በመሆኑ የደረሰበት የአካል ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ስለ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው ተብሎ ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

አሁን ባለው ሁኔታም ሲታይ በተጠሪው ላይ የደረሰው ጉዳት በሕጉ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት የሚባል ሆኖ ባይገኝም የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሕክምናው ማስረጃም የደረሰበት የአካል ጉዳት ተቀጥሮ ሲሰራ የነበረበትን ሥራ ለመሥራት እንደማያስችለው ተገልጿል፡፡ አመልካችም በክርክሩ ላይ ተጠሪ ተቀጥሮ ሲሰራ የነበረበትን ሥራ ተመልሶ መሥራት ይችላል አላለም፡፡ አመልካች በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ካሣ ሊከፈለው አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 109(3)(ለ) በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ከዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መጠን በታች ሆኖ ከተገኘ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) ክፍያ መሠረት ሆኖ ከአካል ጉድለት ደረጃው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ እንደሚሰጠው የሚደነግግ ነው፡፡

በአሁኑ ተጠሪም ላይ የደረሰው ጉዳት ከዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መጠን በታች ነው ለማለት ስለተቻለ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ የጉዳት ካሣ እንዲያገኝ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ሕጉ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የካሣውን መጠን በርትዕ መሠረት አይቶ መወሰን ስለሚፈቅድ በዚሁ መሠረት በማመዛዘን ታይቶ የአሁኑ አመልካች ለሠራተኛው ለአሁኑ ተጠሪ ብር 24000 (ሃያ አራት ሺህ) ካሣ ሊከፍለው ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በአሁኑ ተጠሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት በአዋጅ አንቀጽ 109(3)(ለ) መሠረት አይተው የካሣውን መጠን መወሰን ሲገባቸው የደረሰበት ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መሆኑ ሣይረጋገጥ የደረሰበት ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው በማለት በአዋጅ አንቀጽ 109(3)(ሀ) መሠረት የአመት ደመወዙ በአምስት ተባዝቶ ካሣ እንዲከፈለው በሚል የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 108579 በ10/01/2003 የሰጠው ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 28436 በ30/09/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 08697 በ16/06/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሎ አሠሪው የአሁኑ አመልካች ለሠራተኛው /ለአሁኑ ተጠሪ/ የጉዳት ካሣ ብር 24000 (ሃያ አራት ሺህ) እንዲከፍለው ተወስኗል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው የሰበር ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ መዝገብ በ26/01/2003 ዓ.ም በግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት የተከፈተው አፈፃፀም እንዳይቀጥል ተብሎ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 63635

ሰኔ 27 ቀን 2003

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ጉልላት ወልዴ ጠበቃ ሰይፈ ረታ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ነገረ ፈጅ ገ/ማርያም ዋዴሮ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ሲሆን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ከሣሽነት የተጀመረ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ከሣሽ በተከሣሽ ድርጅት በወር ብር 2847 እየተከፈላቸው ሲሰሩ ቆይተው ያላቸው የሥራ ውል በጡረታ ምክንያት ከሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም የተቋረጠ መሆኑን ገልፀው ከሥራ ከመገለሌ ጋር ተያይዞ ሊከፈለኝ ከሚገባው የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ብር 7051.49 ስላስቀሩብኝ ለዚህ ክስ ያወጣሁት ወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ ለቀረበው ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር መልስ የሠጡ ሲሆን ቀርቦ የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ከሣሽ ከሥራ የተሠናበቱበትና ክስ ያቀረቡበት ጊዜ መካከል ከ6 ወራት በላይ ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል ነው፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ከካራከረ በኋላ ከሣሽ ከሥራ በጡረታ ከተገለሉበት ቀን ሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም መካከል ያለው ጊዜ በአዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 162/4/ የተደነገገውን የይርጋ ዘመን ደንብ የሚፃረር በመሆኑ እና በወቅቱ የቀረበ ክስ ባለመሆኑ በይርጋ ውድቅ ይሆናል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 337 መሠረት አፅንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን አመልካች ታህሣሥ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በ2 ገፅ ጽፈው ያቀረቡት የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ተጠሪ ያለበትን የክፍያ ጥያቄ ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ያመነ ሲሆን በአሁኑ አመልካች መተማመኛ ያልተደረገበትን ዕዳ ተቀናሽ በማድረግ ክፍያ የፈፀመው ደግሞ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በመሆኑ ይርጋው የተቋረጠ መሆኑን እየተከራከርኩ ውድቅ መደረጉ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል



www.chilot.me

በመባሉ ተጠሪ የካቲት ቀን 2003 ዓ.ም በ2 ገፅ ፅፎ መልስ የሠጠ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ አመልካች ይርጋ ቀሪ ስለሚሆንበት አግባብ በሥር ፍርድ ቤት ያልተከራከረ በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አዲስ ክርክር ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረቡትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም የቀረበው የክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች ለቀረበበት የይርጋ ተቃውሞ ይርጋው ሊቋረጥ ይገባል የሚለውን መከራከሪያ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቧል ወይስ አላቀረበም? የሚለውን ነጥብ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ አመልካች ይርጋውን ሊያቋርጥ ይችላል ብሎ የሚከራከረውን በተጠሪ የተፃፈ ደብዳቤ ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረበ በመሆኑ ፣ ከዚያ በመቀጠል የይርጋ ተቃውሞ በተጠሪ ሲቀርብበት ተጠሪ ያለበትን ክፍያ በማረጋገጥ የፃፈው ደብዳቤ ይርጋን ያቋርጣል በማለት የተከራከረ መሆኑን ችሎቱ ተረድቷል፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክር እያቀረበ ነው የሚባል አይደለም፡፡ ይልቁንም በበታች ፍርድ ቤት ሲያነሣው የነበረ እና ፍርድ ቤቱ ሣይመለከተው ያለፈው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑ በሰበር ሰሚ ደረጃ የተነሣ አዲስ ክርክር ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል የአመልካችን ክርክር አግባብነት ስንመለከት በእርግጥ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162/4/ መሠረት ከሥራ ውሉ መቋረጥ ጋር ተያይዞ ሊከፈለኝ የሚገባ ክፍያ አለኝ በማለት የሚቀርበው ክስ በ6 ወር ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ተጠሪም እየተከራከረ ያለው አመልካች በጡረታ የተገለለበት ጊዜ እና ክስ ያቀረበበት ጊዜ መካከል ያለው ጊዜ ከ6 ወራት በላይ ሆኖአል የሚል ነው፡፡ ይሄንን የይርጋ ተቃውሞ በተመለከተ አመልካች ከበታች ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ እየተከራከረ ያለው ተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ የይርጋ ዘመኑ ይቋረጣል በሚል ነው፡፡ ይሄንን በተመለከተ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጠሪ ተፃፈ በማለት የተነሳው ነጥብ ስለመፃፍ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ በዚህም ደብዳቤ ለአመልካች የሚከፈል ክፍያ እንዳለና ሆኖም የሚቀናነሱ ክፍያዎች በዚሁ ደብዳቤ የተገለፁ መሆኑን ችሎቱ ተረድቷል፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 164/3/ መሠረት ይርጋን ለማቋረጥ ከሚችሉት ምክንያቶች አንዱ በመሆኑ ይርጋው በዚሁ ደብዳቤ ይቋረጣል ብለናል፡፡ ይርጋ ዘመን ከተቋረጠ ደግሞ አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ ስለዚሁ የሚደነግግ የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1852/1/ ሥር የተደነገገ በመሆኑ ከጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ጊዜውን ስንቆጥር ክስ እስከቀረበበት ሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ 6 ወራት ያላለፈው በመሆኑ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም ብለናል፡፡

በዚሁ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው መወሰን ሲገባው የቀረበው ክስ በይርጋ ውድቅ ነው በማለት መወሰኑና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይሄንን ሣያስተካክል ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ 96677 በቀን 02/03/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 33762 በቀን 07/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ስለማይሆን በፍሬ ጉዳይ ተገቢውን ማጣራት ከተደረገ በኂላ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲሠጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ላይ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ከፌ/የመ/ደ/ፍቤት የመጣው የመዝ.ቁ . 33762 ወደ መጣበት ይመለስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

**ሃ/ዲ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64758

ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** እነ ተመስገን ገ/እየሱስ ጠበቃ ግርማ ዓለሙ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ኮከብ ስለሺ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቦነስ ክፍያ ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካቾች የተጠሪ ድርጅት ሠራተኞች ሁነው ካገላገሉ በሁዋላ በራሳቸው ፈቃድ ከባንኩ በቅርቡ የለቀቁ መሆኑን ፣ ተጠሪ በ2001 የበጀት አመት አትራፊ በመሆኑ በዚሁ የበጀት አመት ላገለገሉ ሰራተኞች የሁለት ወር ደመወዝ ቦነስ የሠጠ ቢሆንም አመልካቾችን ግን ሕጋዊ ባልሆነ ምክንያት የከለከለ መሆኑን ገልጸው የአንድ ወር ደመወዛቸው በቦነስነት ፣ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ደግሞ የድጎማ ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካቾች የቦነስ ክፍያው ያልተከፈላቸው ሕብረት ስምምነቱን መሠረት አድርጎ በወጣው መመሪያ ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ስለማያሟሉ ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በ06/12/2001 ዓ/ም የወጣው የቦነስ አከፋፈል መመሪያ የተጠሪ ባንክ ሠራተኛ ማህበር ፕሮዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሁም የተጠሪ ባንክ ሰራተኛ ማህበር ጸሐፊን ጨምሮ የባንኩ የተለያዩ ክፍል ኃላፊዎች በተገኙበት ስምምነት የተደረሰበት መሆኑን እንደሚያስረዳ በማረጋገጥ በመመሪያው ሕጋዊነት ላይ የተነሣውን የአመልካቾች ክርክር ውድቅ ያደረገ ሲሆን የቦነስ ክፍያ ጥያቄውን ደግሞ በተጠቃሹ መመሪያ ቁጥር 2/ለ/4/ መሠረት አንድ ሠራተኛ ወይም የስራ መሪ ለቦነስ ክፍያው ብቁ የሚሆነው ይህ ቦነስ ክፍያ ተፈቅዶ ክፍያ እስከተፈጸመበት እለት ድረስ ድርጅቱን በማንኛውም ምክንያት ከለቀቀ ወይም ለመልቀቅ ማመልከቻ ያላስገባ ሲሆን ብቻ መሆኑን ፣ በእድሜ ጣሪያ ምክንያት በጡረታ የተገለሉ በመመሪያው ላይ የሰፈሩትን መስፈርቶች ያሟሉ ከሆነ ክፍያ የሚከፈላቸው መሆኑን መደንገጉን በመመልከትና አመልካቾች ከስራ የተሰናበቱት በዕድሜ ጣሪያ ምክንያት በጡረታ ስለተገለሉ ሳይሆን እያንዳንዳቸው አመልካቾች ከመመሪያው ተግባራዊነት



www.chilot.me

በፊት ስራ ለመልቀቅ ባቀረቡት መልቀቂያ ማመልከቻ መሆኑን እንዲሁም የድጎማ ክፍያ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የሚከፈለውም በእድሜ ጣሪያ ከስራ ለተገለለ ሰራተኛ መሆኑን በማረጋገጥ የአመልካቾችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ተጠሪ የአመልካቾችን መብት በሚያጣብብ መልኩ ያወጣው የቦነስና የድጎማ ክፍያ መመሪያና የህብረት ስምምነት ተቀባይነት ማግኘቱ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 134/2/ ድንጋጌ ጋር የማይሄድ ከመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 20869 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለአመልካቾች የቦነስ ክፍያው አይገባቸውም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት በመቅረብ የሰበር ችሎቱ አስገዳጅ ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑና የተጠሪዎች ጥያቄ ውደቅ የተደረገው ባግባቡ መሆኑን ጠቅሶ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

በክርክሩ ሂደት አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ተቀጥረው ሲያገለግሉ ቆይተው እድሜያቸው የጡረታ ጣሪያ ሳይደርስ በገዛ ፈቃዳቸው ስራውን የለቀቁ ፣ ተጠሪ መስሪያ ቤትም የቦነስና የድጎማ ክፍያ ለአመልካቾች አይገባም በማለት የሚከራከረው ሕብረት ስምምነቱንና ይህንኑ መሠረት አድርጎ የወጣውን መመሪያ በመመርኮዝ መሆኑን ነው፡፡ አመልካቾች የሕብረት ስምምነቱ ህጋዊነት ተፈፃሚነት ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር የታለፈው ሕብረት ስምምነቱ የወጣው ሥርአቱን ተከትሎ እና የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ስምምነት ተደርሶበት መሆነና በሕብረት ስምምነቱ ላይም የቦነስ አከፋፈል መመሪያና ማውጣት እንደሚቻል ፣ ሰራተኛ ስራ ሲለቅ ድጎማ የሚከፈልበት አግባብ በሕብረት ስምምነቱ መመልከቱ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ ሲሆን በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃም አመልካቾች የሚከራከሩት የህብረት ስምምነቱ የተሻለ መብት የማይጠብቅ በመሆኑ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ በተመሣሣይ ጉዳይ በሕግ ከተደነገገው ይልቅ የሕብረት ስምምነቱ ለሰራተኞች የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሆኖ ሲገኝ ስምምነቱ ተፈፃሚ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 134/2/ ሥር ተደንግጓል፡፡ ለጉዳዮቹ የተደነገገው ሕግ ለሰራተኞቹ የበለጠ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ግን ሕጉ በስራ ላይ ሊውል የሚገባ መሆኑን ይኸው ድንጋጌ በኃይለ ቃል አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም ህብረት ስምምነቱ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የተሻለ ሁኖ ሲገኝ ሲሆን ከሕጉ ተቃራኒ ወይም ያነሰ ጥቅም የሚያስገኝ ሁኖ ከተገኘ ደግሞ ስራ ላይ የማይውል መሆኑን ከድንጋጌው መንፈስ ፣ ይዘትና ቅርፅ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካቾች ጥያቄ የቦነስና የድጎማ ጥያቄ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ ቦነስ ወይም ድጎማ ሊያገኝ የሚገባው ከአሰሪው ጋር በሚኖረው ስምምነት እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ለሰራተኛው አሰሪው በአሰሪነቱ የግድ እንዲከፍል ተለይቶ የተቀመጠ ጉዳይ አለመሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 4፣ 12፣ 13፣ እና 53 ድንጋጌዎች ቅርጽ ፣ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የሕብረት ስምምነቱ ከአሰሪና ሠራተኛ ሕግ የተሻለ ጥቅም የማይጠብቅ በመሆኑ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይችልም በማለት ያቀረቡት ክርክር በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ የተጠበቀ መብት ባለመሆኑ አግባብነት ያለው ክርክር ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ ሕብረት ስምምነቱ



www.chilot.me

ተፈጻሚ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ሕብረት ስምምነቱ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ከተባለ ደግሞ የቦነስ ክፍያ ጥያቄ የሚፈፀምበት አግባብ በመመሪያ ሊወጣ እንደሚችል በህብረት ስምምነቱ የተመለከተ ሁኖ ይህንኑ መሠረት አድርጎ ተጠሪ ነሐሴ 06 ቀን 2001 ዓ/ም መመሪያ አውጥቶ ስራ ላይ አውሏል፡፡ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 4 ላይ ከስራ በጡረታ የተገለሉና ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟሉ ቦነስን እንደሚያገኙ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ በመመሪያው ተራ ቀጥር 4 የቦነስ ክፍያ ተፈቅዶ እስከ ተፈጸመበት እለት ድረስ በማንኛውም ምክንያት ከሰራ ሰራተኛው ከለቀቀ ወይም ለመልቀቅ ማመልከቻ ያላስገባ ሲሆን ብቻ ቦነሱ እንደሚከፈል መመልከቱን የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካቾች ይህንኑ የመመሪያውን ይዘት ትክክል አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር የሌለ ሲሆን አመልካቾች ስራቸውን ለመልቀቅ ማመልከቻውን ያስገቡትና ከስራ የተሰናበቱት መመሪያው ነሐሴ 06 ቀን 2001 ዓ/ም ከመውጣቱ በፊት መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ የድጎማ ክፍያን በተመለከተ ደግሞ የሕብረት ስምምነቱ በአንቀፅ 34/1/ እና /4/ መሠረት ሊከፈል የሚችለው ሰራተኛው በእድሜ ብቁነት በጡረታ ከስራ ሲገለል መሆኑን የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በእድሜ ብቁነት ሳይሆን በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን የለቀቁ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ሕብረት ስምምነቱም ሆነ የቦነስ ክፍያ መመሪያው የሚከለክሏቸው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ አመልካቶች አጥብቀው የሚከራከሩት የሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 20869 የሰጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈጻሚነት አለው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ አንድ ሰራተኛ በበጀት አመቱ ለሚገኘው ትርፍ አስተዋጽኦ ማድረጉ እስከተረጋገጠ ድረስ ስራውን ቢለቅም ቦነሱ ሊከፈለው እንደሚገባ ሰበር ችሎቱ በተጠቃሹ መዝገብ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ መዝገብ የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ከሰ/መ/ቁጥር 20869 ከተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ጋር ሙሉ ሙሉ ተመሳሳይነት አለው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ቦነስ ከአሰሪው ለሰራተኛው የሚሰጥ ጉርሻ /የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 53/2/ሐ/ ይመለከቷል/ እንደመሆኑ መጠን አከፋፈሉን በተመለከተ ተጠሪ ሥርዓቱን ዘርግቷል፡፡ በዚህ ስርዓት መሠረት ደግሞ አመልካቾች የቦነሱና የድጎማ ተጠቃሚ ለመሆን ሁኔታዎችን የሚያሟሉ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች ክርክርም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካቾች የቦነስና የድጎማ ክፍያ አይገባቸውም ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 45679 የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 90211 ጥር 17 ቀን 2003 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች የቦነስና የድጎማ ክፍያ አይገባቸውም ተብሎ የተወሰነው ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁጥር 66242

ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሙሉ ደምሴ - ጠበቃ ከበደ ወርቁ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሼራተን አዲስ - ጠበቃ ግርማ ሀይሌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በምግብ ዝግጅት የስራ መደብ ተቀጥረው የሰሩ መሆናቸውን ገልጸው ተጠሪ የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው በማለት ለሌሎች ሰራተኞች የሚሰጠውን ጥቅማጥቅም የማግኘት መብት ነፍጉኛል፡፡ ስለሆነም ከመስከረም ወር 2002 ዓ.ም ጀምሮ የቲፕ ክፍያ ቦነስ የሁለት ወር ደመወዝ የደመወዝ ጭማሪ አስር ፐርሰንት በየዓመቱ የስድስት ወር ፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከሣሽ የመድን ሽፋን እንዲሰጠኝ የህክምና ወጭ እንዲሸፍንልኝ የደመወዝ መክፈያ ጊዜ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር እንዲያስተካክልልኝና የስራ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ ይወስንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ /አመልካች/ ከዚህ በፊት ክስ አቅርበው የቲፐና ዓመታዊ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በድጋሚ የቀረበችው ክስ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 መሠረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከሣሽ ሌሎቹን ጥያቄያቸውን ከዚህ በፊት ካቀረቡት ክስ ጋር ዘርዝረው ያላቀረቡ በመሆኑ አሁን ማቅረባቸው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 የሚጥስ ነው፡፡ ከሣሽ የጠየቋቸው ጥቅማጥቅሞች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ነው፡፡ ከሣሽ ለተወሰነ የስራ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኛ በመሆናቸው ያቀረቡት የጥቅማጥቅም ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ቲፕ እንዲከፈላቸው በመዝገብ ቁጥር 18403 ጠይቀው ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በዚህ መዝገብ ክስ መልሰው መጠየቃቸው በፍርድ የመጨረሻ ውሣኔ ባገኘ ጉዳይ ያቀረቡት ስለሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 የሚታገድ ነው፡፡ እንደዚሁም በመዝገብ ቁጥር 22230 አመልካች /ከሣሽ/



www.chilot.me

አስር ፐርሰንት የደመወዝ ጭማሪና የህክምና ክፍያ አልጠየቁም፡፡ ከሣሽ የሰርቪስ ቻርጅ በቀጣይነት እንዲከፈላቸው ነው ክስ ያቀረቡት ስለሆነም ከሣሽ ክሣቸውን ነጥለው ያቀረቡ ስለሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት የአመልካች የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው ተጠሪ የሁለት ወር ቦነስ ሊከፍል ይገባል፡፡ የመድን ሽፋንና የደመወዝ መክፈያ ጊዜ ይስተካከልኝ ጥያቄ ግልጽነት የጐደለው ነው፡፡ ተጠሪ የስራ ምስክር ወረቀት ይሰጣት በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል መሆኑን ከወሰነ በኋላ አመልካች ያቀረቡትን የመብትና የጥቅማጥቅም ጥያቄዎች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 216 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ስለሆነም ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች የከፈላቸውን መብቶችና ጥቅማጥቅሞች እንዲያከብር ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካች በሶስት መዝገቦች ማለትም በመዝገብ ቁጥር 18403 በመዝገብ ቁጥር 22230 እና ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሣኔ በተሰጠበት የመዝገብ ቁጥር 33375 የተለየዩ ጥያቄዎችን አቅርበው በፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገ በመሆኑ አሁን የሚያቀርቡት ክርክር የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 የሚቃረን ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሰኔ 6 ቀን 2003 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቧቸውን የጥቅማጥቅምና የመብት ጥያቄዎች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተነዋል፡፡

አመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ተወስኗል፡፡ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል ላይ የተመሰረተ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት በህግ አግባብ እስከሚቋረጥ ድረስ ቀጣይነት ያለው ግንኙነት እንደሚሆን የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ልዩ ባህሪ የስራን ውል መነሻ በማድረግ ሊቀርቡ ከሚችሉት የመብት ጥያቄዎችና እነዚህ የመብት ጥያቄዎች ላይ ተፈጻሚነትና ገዥነት ካለው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ማንኛውም አሰሪ በስራ ውሉ ከተስማማባቸው ልዩ ግዴታዎች በተጨማሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 12 የተዘረዘሩት በህግ የተጣለበት ግዴታዎች እንዳሉበት ከህጉ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ለሰራተኛው ደመወዙንና ሌሎች ክፍያዎችን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ወይም በህብረት ስምምነት መሠረት የመክፈል ግዴታ አሰሪው እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

ይኸም የሚያሣየው ሰራተኛው አሰሪው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ መሠረት ሊከፍለው የሚገባውና ያልከፈለው ክፍያ መኖሩን ወይም በህብረት ስምምነቱ መሠረት ሊከፍለው የሚገባው



www.chilot.me

ክፍያና ሊያከብርለት የሚገባው መብት እንዳለ በተረዳ ጊዜ አሰሪውን የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ካለው ቀጣይነትና ዘላቂነት አንጻር ስንመለከት ሰራተኛው በአንድ ወቅት ሊጠበቅልኝ ወይም ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበው የመብት ወይም የክፍያ ጥያቄ በፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በሌላ ጊዜ መብቱን ወይም ክፍያውን ለመጠየቅ የሚያስችለውን የስራ ውል የህግ ድንጋጌ ወይም የህብረት ስምምነት ዋቢ በማድረግ እንዳይጠይቅ የሚገድበው አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሰራተኛው በአንድ ወቅት ክስ ሲያቀርብ ክፍያዉን ለመጠየቅ የሚያስችለው የስራ ውል፣ የህግ ድንጋጌ ወይም የህብረት ስምምነት ባለመኖሩ ያልጠየቀውን ክፍያ ወይም የመብት ጥያቄ በሌላ ጊዜ እንዲከፈለው ከመጠየቅ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 ይገድበዋል የሚል መደምደሚያና ትርጉም ላይ መድረስ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነትን እና የስራ ውል አስመልክቶ የሚነሱ የመብት ጥያቄዎችና ክርክሮች ከሌሎች ጉዳይ ከሚደረጉ ክርክሮች አንፃር ያላቸውን ውስብስብና ልዩ ባህሪ ያላገናዘበና የአሰራና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማና ግብ የማያሳካ የህግ አተረጓጐም ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ ለተደረጉ የስራ ውል ላላቸው ሰራተኞች የሚያከብራቸውን መብቶችና የሚጠብቃቸዉን ጥቅማጥቅሞች ተጠሪ እንዲያከብርላቸው ያቀረቧቸውን ጥያቄዎች ከፊሎቹን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ ላይ ከተገለጸው በተጨማሪ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18403 እና በመዝገብ ቁጥር 22230 ክስ አቅርበው ከተጠሪ ጋር የተከራከሩበት መሠረታዊ ጭብጥ ለዚህ ክርክር መነሻ ከሆነውና ለስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33375 ካቀረቡት ክርክርና ጥያቄ በባህሪውም ሆነ በይዘቱ የተለየ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በተለይም አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 22230 የተከራከሩት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የስራ ውል መቋረጥና ከስራ መሰናበቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው መሠረታዊ ጭብጥ ላይ ሆኖ እያለ ይህንን መዝገብ በመጥቀስ አመልካች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ ሰራተኛ ስለሆንኩ ለቋሚ ሰራተኞች የሚከበረው መብትና የሚከፈላቸው የጥቅማጥቅም ጥያቄ ለእኔም ይከፈለኝ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ ለሌሎች ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች የሚያሟላውን መብትና የሚከፍላቸውን የጥቅማጥቅም ክፍያዎች ለእኔም እንዲያከብር ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 5/1/ እና አንቀጽ 216 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኛ ስለሆኑ ተጠሪ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍል በማለት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የውሣኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. በድርጅቱን የህብረት ስምምነትና ደንብ መሠረት ተጠሪ ላልተወሰኑ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች የሚያከብረውን መብትና የሚከፍለውን የጥቅማጥቅም ክፍያ ለአመልካች ሊያከብርላትና ሊከፍላት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59579

ቀን 16/9/2003

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ወልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አሞኘስ ገብሬ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** በአቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎች የእጅ መሥሪያዎች አ/ማ የሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ነገረ ፈጅ አዳነ አረጋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን በበታች ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ስትሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ በአሰሪ መስሪያ ቤቷ ላይ ባቀረበችው ክስ ተከሳሽ መስሪያ ቤቷ ባቀረበው ተቃውሞ ከሳሽ የስራ መሪ እንጅ ሰራተኛ አይደሉም፡፡ የከሳሽና ተከሳሽ ክርክር መዳኘት ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ሳይሆን የራሱ የሆነ ሕግ ስለአለ በአዋጅ ቁ. 147/91 እና 402/96 መሠረት መሆን አለበት በማለት ተከራክሯል፡፡

በእነዚህ በቀረቡት መቃወሚያዎች ላይ ፍርድ ቤቱ ካከራከረ በኋላ ከሳሽ የስራ መሪ ናቸው በማለት የቀረበውን ተቃውሞ በተመለከተ ከሳሽ የሂሳብ ሰራተኛ ባለሙያ እንጂ ለአሰሪ መስሪያ ቤት የምታቀርበው የውሣኔ ሃሳብ ባለመኖሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ሲወስን ሁለተኛውን የተቃውሞ ነጥብ /ተፈፃሚነት ያለውን ህግ በተመለከተ/ እንደዚህ አይነት የህብረት ሥራ ማህበራት ተቋም ሂደታቸው የሚመራው በአዋጅ ቁ. 147/91 አንቀጽ 49/3/ እና 52 እና አዋጅ ቁ. 402/96 አንቀጽ 8 መሠረት መሆኑን በማብራራት አለመግባባቶች ሲከሰቱ መጀመሪያ በእርቅ፣ በእርቅ ካልተቻለ ደግሞ በሽምግልና ዳኝነት መታየት እንዳለበትና እነዚህ አካላት በሚወስኑት ውሣኔ ላይ ቅሬታ ካለ ወደ ሚመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችሉ ስለሚደነግግ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ጉዳዩን ለሽማግሌዎች አስፈላጊውን መመሪያ በመስጠት እንዲያዩት እንዳዘዘና መዝገቡን እንደዘጋ ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

የአሁኑ ይግባኝ ሊቀርብ የቻለው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሲሆን በ18/12/2002 ዓ.ም የተፃፈ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሬ ስሰራ የቆየሁ ሲሆን ተጠሪ ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሌን አቋርጦ ከስራ ስላሰናበተኝ



www.chilot.me

የተቋረጠብኝ ጥቅም ተጠብቆ ወደ ስራዬ እንድመለስ ትዕዛዝ እንዲሰጠኝ የበታች ፍርድ ቤት ብጠይቅም ጉዳዩ መታየት ያለበት በእርቅ ወይም በሽምግልና ዳኛ ነው በማለት መዝገቡን ዘግተውብኛል፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የስራ ውል እንደመሆኑ መጠን በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መታየት ሲገባው በመጀመሪያ በእርቅ ይሄም ካልተቻለ በሽምግልና መታየት አለበተ በማለት መዝገቡ መዘጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤት በህጉ አግባብ ዳኝነት እንዲያዩልን ውሣኔ እንዲሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ በመታዘዙ በተወካያቸው አማካኝነት በ27/382003 ዓ.ም በ2 ገጽ ጽፈው ባቀረቡት መልስ የበታች ፍርድ ቤት ይሄ ጉዳይ በህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ 147/91 መታየት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ ምንም ዓይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም በ20/4/2003 ዓ.ም በ2 ገጽ ባቀረቡት የመልስ መልስ ቅሬታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆኑ እኛም የቀረበውን ቅሬታ የበታች ፍርድ ቤት ከሰጡት ውሣኔ ከተያዘው ጭብጥና ጉዳዩ ከሚመለከተቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት ክስ መቅረብ ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 396/96 ነው ወይስ በህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁ. 147/91 ነው የሚለው ጭብጥ ተይዞ መፍትሄ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ጉዳዩን ስንዳስሰው በእርግጥ በአዋጅ 147/91 አንቀጽ 49 ስር አለመግባባቶች ሲኖሩ እንዴት ሊፈቱ እንደሚገባቸው ይደነግጋል፡፡ ይሄውም በመጀመሪያ ደረጃ በእርቅ መታየት እንዳለበት በእርቅ ካልተቻለ ደግሞ በሽምግልና ታይቶ በዚህ አካል በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው አካል በይግባኝ ወደሚመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ መሄድ እንደሚቻል ይዳነግጋል፡፡ ሆኖም ምን አይነት ጉዳዮች ናቸው በእንደዚህ አይነት ሂደት መታየት ያለባቸው የሚለውን በምናይበት ጊዜ በዚሁ አንቀጽ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ለሽምግልና ዳኝነት የሚቀርቡት ጉዳዮች በዝርዝር ስለአንድ ማህበር አቋም ስለስራው አካሄድ ወይም ስለስራው አፈፃፀም እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ የዚሁ አንቀጽ መግቢያ የእንግሊዝኛ ትርጉም “The arbitrators shall have the power to hear disputes not settled by arbitration regarding the organization, management or operation of a society…” ይላል፡፡ የዚህን አንቀጽ አቀራረጽ ስናይ አጠቃላይ የህብረት ስራ ማህበሩን እንቅስቃሴ ወይም ህልውና የሚመለከቱ በተለይም አደረጃጀቱን አመራሩና የስራ እንቅስቃሴን መሰረት ያደረገ አለመግባባት እንጅ ማህበሩ እንደማንኛውም ህጋዊ ሰውነት እንዳለው ተቋም ሊቀጥራቸውና ሊያሰራቸው ወይም በስሩ የሚተዳደሩትን ሠራተኞች በዚሁ የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ለመምራት ያሰበ ስለመሆኑ የሚያመለከት ነገር የለም፡፡ የአንቀፁን መንደርደሪያ ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው ከአሰራተኞቹ ጋር ሊፈጠር የሚችለውን የስራ ክርክር ሂደት ከላይ በተጠቀሰው የሙግት አመራር ስርዓት ለማስኬድ የህግ አውጪው ሃሳብ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነገር የለም፡፡

የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁ. 147/91 አጠቃላይ ትኩረት ተመሳሳይ ፍላጐት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የህብረት ስራ ማህበራትን በመፍጠር ገንዘብን፣ እውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ቁጠባንና እርስ በርስ መደጋገፍ የሚጐለብትበትና



www.chilot.me

የሚመራበትን የህግ ማዕቀፍ መፍጠር እንደሆነ ከዚሁ አዋጅ መግቢያ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአዋጁ አንቀጽ 4/1-9/ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ስንመለከት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለየብቻቸው ሆነው ሊከብዳቸው የሚችለውን ጉዳይ በመተባበር ሊደርሱባቸው የሚችሉበትን የአደረጃጀት ማዕቀፍ ከመዘርጋት አኳያ እንጅ እንደማንኛውም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም አሰሪ የሚሆንላቸውን ሠራተኞች በዚህ አዋጅ መሠረት ሊፈጠሩ የሚችሉትን አለመግባባቶች ለማስኬድ የታሰበ ስለመሆኑ የሚያሳይ አይደለም፡፡

በተጨማሪ መነሳት ያለበት ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የስራ ክርክርን በተመለከተ የተለየ ህግ በመሆኑና በህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ሊተዳደሩ አይገባም ሊባል የሚችልበት አጋጣሚ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/2/ /ሠ/ መሰረት የሚተዳደሩበት የራሳቸው ዝርዝር ህግ ወጥቶላቸው ቢሆን ኖሮ ነበር፡፡ ከዚህ አኳያም የወጣ ነገር የለም፡፡ እንደማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት እንዳለው ተቋም ሰራተኛ ሊቀጥርና ሊያስተዳድር የሚችል ተቋም መሆናቸው ቢታመንም ባላቸው የስራ ግንኙነት ምክንያት ወይም የስራ ውል መሰረት ያደረገ አለመግባባት ሲፈጠር የሚመራበት የተለየ ህግ በሌለበት ሁኔታ፣ የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ቢባል እንኳ የትኛውን ህግ መሰረት ያደርጋል? ሠራተኛው ከሚያነሳው የመብት ጥያቄ አኳያ የሚሰጠው መፍትሔ (remedy) ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በአዋጁ መልስ አላገኘም፡፡ በሌላ በኩል በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚነሱትን የስራ ውል ተያያዥ ክርክሮችን ለምሳሌ የሥራ ስንብት፣ የካሳ አከፋፈል እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መፍትሔ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ሕግ አውጪው ጉዳዩን በአዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት ተፈፃሚ እንዲሆን ያሰበ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በግልጽ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ተፈፃሚነት የለውም ባልተባለበት ሁኔታ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አይመራም መባሉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ውስጥ እየተጠቀሰ ያለው የቅሬታ አፈታት ስርዓት ከላይ በተመለከተው ምክንያት ለሌላ ዓላማ የተቀመጠ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁ. 377/96 ይሆናል ብለናል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በአንድ ወጥ በሆነ የህግ ማዕቀፍ ለማስተዳደር መሠረታዊ የሆነ የህግ አውጭው ሐሳብ እንደሆነ ከወጣው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መግቢያ ንባብ ከመረዳታችን በላይ በህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ ላሉት ሰራተኞች የተለየ ህግ ማስፈለጉን በግልጽ ባልተደነገገበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የወሰዱት አቋም አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይሄንን ሳያገናዝቡ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለንም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ያለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 44428 በ21/5/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይንና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 90023 ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ መታየት ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበውን ክስ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ፍርድ እንዲሰጥ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለደረሰው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰበር መዝገብ 65427

ቀን 15/9/2003

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ሜታ አቦ ቢራ አ/ማ ነገረ ፈጅ አቶ ሰለሞን ዘውዴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ወ/መድህን ቢረዳ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የአሁኑ ተጠሪ ለሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ በተከሳሽ ድርጅት /የአሁን አመልካች/ በዩቲሊቲ ክፍል ሃላፊ ሆኜ ስሰራ ቆይቼ ማያዝያ 26 ቀን 2001 ዓ.ም በሥር ላይ በደረሰብኝ አደገ በህክምና የተረጋገጠ 7% ጉዳት የደረሰብኝ ስሆን ተከሳሽ ክፍያ የፈፀመልኝ ካደረሰብኝ ጉዳት ባነሰ በመሆኑ ቀሪውን ገንዘብ ከነ ወለዱ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽም በሰጠው መልስ ተከሳሽ በገባው የመድን ዋስትና መሰረት ለከሳሽ የሚገባውን የካሣ ገንዘብ ከፍሏል፡፡ ስለሆነም ቀሪ የሚከፈለው ካሣ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በበኩሉ ወደ ክሱ ጣልቃ በመግባት የተከራከረ ሲሆን የሥር ተከሳሽ በገባው የመድን ሽፋን መሠረት ክፍያ መፈፀሙን ገልጿል፡፡ የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም በሰጠው ፍርድ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/2/ መሠረት ለከሣሽ ተገቢውን ካሣ የከፈለ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

የሥር ከሣሽም በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብይ መልስ ሰጪው ቀደም ሲል ከከፈለኝ ገንዘብ ብር 7500 በተጨማሪ ብር 8649 ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረብኩትን ክስ የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ከፍተኛ ፍ/ቤትም የመልስ ሰጪዎችን መልስ ከቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ጋር ከመረመረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/1/ ድንጋጌ መሠረት ለሠራተኛ የሚከፈል የጉዳት ካሣ አሠሪው በገባበት የመድን ዋስትና ተፈፃሚ ይሆናል ተብሎ የተገለፀው የመንግስት ሠራተኞችን የሚመለከት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በ1ኛ መልስ ሰጪ /የአሁን አመልካች/ እና 2ኛ መልስ ሰጪ /የኢት/መድን ድርጅት/ መካከል የተደረገው የመድን ሽፋን ውል ህግ ሆኖ የሚገዛው ሁለቱን ተዋዋይ ወገኖችን



www.chilot.me

እንጂ ይግባኝ ባይ /ያሁን ተጠሪን/ የውሉ ተገዢ ለማድረግ ሙሉ በሙሉ የሚያስገድድ አይደለም በማለት 1ኛ መልስ ሰጪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ መሠረት ከደረሰው የአካል ጉዳት ጋር ተያይዞ ቀሪ የካሣ ክፍያ ብር 8649 የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት ፈርዷል፡፡

በሥር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም አመልካች የመንግስት የልማት ድርጅት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ የመንግስት ሠራተኛ ነው፡፡ በመሆኑም አሰሪው ካሣ መክፈል ያለበት በአዋጅ አንቀጽ 109/1/ መሠረት አሰሪው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ መሠረት ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም አመልካች በገባው የመድን ዋስትና መሠረት ከሚገባው ካሣ በላይ ለተጠሪው ከፍሏል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ን ለውሣኔው መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህ አንቀጽ ከ109/2/ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው በጡረታ ህግ ላልተሸፈኑ ሠራተኞች አሰሪው በአንድጊዜ ስለሚከፍለው ካሣ ሲሆን ተጠሪ ግን የጡረታ ሽፋን ያለውና እንደማንኛውም ሠራተኛ ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ መብት የሚከበርለት ነው፡፡ ስለሆነም የስር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳይ በተጠቀሰው ህግ አንቀጽ 109/3/ለ/ ሥር የሚሸፈን ነው በማለት ተጠሪው በተጨማሪነት እንዲከፈለው የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ያለአግባብ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ አመልካች ለሠራተኛው የገባው የመድን ዋስትና የሚያስገኘው ጥቅም አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ ለሠራተኛው የሚሰጠው ጥቅም ያነሰ ነው፡፡ የህብረት ስምምነቱም የካሣ ክፍያን አስመልክቶ ለሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ካስቀመጠው ያነሰ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ተፈፃሚነት የለውም ተጠሪም እንዲከፍለኝ የጠየቅኩት የህብረት ስምምነቱ ያስቀረብኝን ጥቅም በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ሲል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው ብሏል፡፡

አመልካችም ለተጠሪ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን እኛም አመልካች በቀሪነት የሚፈለግበትን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ለተያዘውን ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት ስለ ጉዳት ካሣ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109 የተደነገገውን መመልከት ተገቢነት ያለው ነው፡፡ የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 109/1/ የሚናገረው በመንግስት ድርጅቶች ሠራተኞች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ካሣ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ሲሆን አከፋፈሉም አሠሪው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ መሠረት መሆኑን ይገልፃል፡፡ አንቀጽ 109/2/ ደግሞ ተፈፃሚ የሚሆነው በጡረታ ህግ ላልተሸፈኑ ሠራተኞች ሲሆን የጉዳት ካሣውም የሚከፈለው በጡረታ ህግ መሠረት ሳይሆን በአንድ ጊዜ ክፍያ ነው፡፡ የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ ከንዑስ ቁጥር 2 ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ ስለ ጉዳት ካሣው መጠን ስሌት የሚናገር ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በደንብ ቁጥር 64/85 የተቋቋመ ሲሆን ተጠሪውም የመንግስት ሠራተኞች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪው የደረሰበት ጉዳት 7% እንደመሆኑ መጠን መደበኛ ሥራውን እያከናወነ ያለና በጡረታ ህግ የተሸፈነና



www.chilot.me

ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አበል ጭምር የሚያገኝ መሆኑን አመልካች ያስረዳ ሲሆን ተጠሪው ግን ይህን በሚያስተባብል መልኩ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡

ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪው ክርክር መወሰን ያለበት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደጠቀሰው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ ሳይሆን በአንቀጽ 109/1/ መሠረት ነው፡፡ በዚህ በተጠቀሰው አንቀጽ ማለትም 109/1/ መሠረት አንድ የመንግስት ድርጅት በሰራተኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የሚከፍለው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ ሲሆን ይህ ሊቀየር የሚችለው አሠሪውና ሠራተኛው በህብረት ስምምነታቸው በተቃራኒ ተስማምተው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በህብረት ስምምነት በተቃራኒ የተወሰነ ወይም የተደረገ ስምምነት ስለመኖር በሥር ፍ/ቤት በአስረጂነት የቀረበ ነገር የለም፡፡

አመልካችም የጉዳት ካሣውን ገንዘብ የከፈለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/1/ መሠረት ለተጠሪው በገባለት የመድን ዋስትና ሲሆን የዋስትና ሽፋኑም ብር 7500 በመሆኑና ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪው መክፈሉን ገልጿል፡፡ በአንቀፁ የጉዳት ካሣው አሰሪው በገባበት የመድን ዋስትና ሊሆን እንደሚችል ከተደነገገው በተጨማሪ በአመልካች እና በሜታ አቦ ቢራ አክስዮን ማህበር መሠረታዊ የሠራተኞች ማህበር መካከል በ2000 ዓ.ም በተደረገው የህብረት ስምምነት አንቀጽ 32 ድርጅቱ /አመልካች/ ለማንኛውም ሰራተኛ በሥራውና ከሥራው ውጪ ለሚደርስበት አደጋ የሕይወት መድን ዋስትና ይገባለታል የተባለ ሲሆን ለአካል ጉዳትና የሕይወት መድን ዋስትና ድርጅቱና ሠራተኛው በጋራ በሚያዋጡት አረቦን ዓመታዊ የህይወት ዋስትና እንደሚገባለት አንቀፁ ይናገራል፡፡

በመሆኑም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና በ2000 ዓ.ም በተደረገው የህብረት ስምምነት መሠረት ለሠራተኞች /ተጠሪን ጨምሮ/ የመድን ዋስትና ገብቶላቸው ተጠሪውም ዓመታዊ አረቦን ማዋጣቱን እያወቀ ለደረሰበት ጉዳት አመልካች ለተጠሪው በገባለት የመድን ሽፋን መሠረት የከፈለውን የጉዳት ካሣ አንሶኛል በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መርምሮ የጉዳት ካሣ በአግባቡ ተከፍሏል በማለት የወሰነውን የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/ለ/ በመጥቀስ ቀሪ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል ሲል የወሰነው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 99288 በቀን 02/05/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16634 በቀን 03/02/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ውሣኔውም የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ስ/ረ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ/62370

ታህሣስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ዕዮብ መሰለ

2. አቶ ደምመላሽ አበዬ

3. አቶ ወንድማገኝ ይርጉ

4. አቶ ፍቃዱ ደጀኔ

} ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች ሥር ፍ/ቤት ከሣሽ ነበሩ፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን የሥራ ውል ከሕግ አግባብ ውጪ አቋርጧል በሚል ወደ ሥራ እንዲመልሳቸው ወስኗል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የ6 ወር ደመወዝ ከፍሎ ተጠሪዎችን ወደ ሥራ ይመለስ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ታህሣስ 1 ቀን 2003 ዓ.ም. የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በአመልካች በተያዘው የፕሮጀክት ሥራ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያየ ቦታና የሥራ መደብ ሲሠሩ መቆየታቸውን ገልፀው የሥራ ውል ማደስ አስፈላጊ ነው ከተባለም ይሠሩ ከነበሩበት ሙያ ጋር በሚጣጣም መልኩ ባለመቅረቡ እንጂ ውል ለማደስ ፈቃደኛ መሆናቸውን ዘርዝረው በዚህም ምክንያት የሥራ ውል ማቋረጥ ከሕግ ውጭ ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ፍርድ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡



www.chilot.me

አመልካች አቤቱታውን ከጠናክሮ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንፃርና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ ምክንያት ያደረገው ተጠሪዎች የውል እድሳት ውል ለመፈረም አልፈቀዱም አዲስ የውል ሁኔታን አቅርበዋል በሚል ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንደተረጋገጠው ተጠሪዎች በአመልካች በተያዘው የፕሮጀክት ሥራ ውስጥ በነዳጅ ቀጅነትና በብየዳ ሥራ ላይ ይሠሩ እንደነበር እና የሥራ ውል ሊታደስ የሚገባ ከሆነም በዚሁ አግባብ እንጂ ጫኝ እና አውራጅ በሚለው የሥራ መደብ መሆን የለበትም የሚል ነው፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዎች ለውል እድሳት ያቀረቡት ሁኔታ ቀድሞ አልነበረም ተጠሪዎች የተቀጠሩት በዩኒቨርሳል ኤሌክትሪፊኬሽን አክሰስ ፕሮጀክት ውስጥ የተወሰነ ሥራ ለመሥራት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10/1/ሀ መሠረት ነው፡፡

በመሠረቱ የሥራ ውል ባህሪ የሚወሰነው በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 9 እና 10 በተደነገገው አግባብ መሆኑ እሙን ነው፡፡ አሠሪው የሥራ ውል በአዋጅ አንቀጽ 10 ሥር በተደነገገው አግባብ የተፈፀመ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ማስረዳት ከቻለ ደግሞ የሥራ ውል ታደሰም አልታደሰ ሥራው ሲያልቅ ወይም ጊዜው ሲያበቃ የሥራ ውል ሊቋረጥ እንደሚችል አዋጁ በግልፅ ደንግጓል፡፡

በተያያዘው ጉዳይ አመልካች ተጠሪዎች የተቀጠሩበት የፕሮጀክት ሥራ ተጠናቋል የሚል ክርክር በአመልካች በኩል አልቀረበም፡፡ ስለሆነም የፕሮጀክት ሥራው አሁንም ቀጥሎ ያለ ስለመሆኑ መረዳት አዳጋች አይደለም፡፡ ስለዚህም ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ አመልካች እንደሚለው በአንቀጽ 10/1/ሀ ሥር የሚሸፈን ነው እንኳ ቢባል የፕሮጀክቱ ሥራ ተጠናቋል፡፡ እስካልተባለ ጊዜ ድረስ የሥራ ውል አድሰዋል ወይም አላደሱም አሊያም ለማደስ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል ምክንያት ብቻ የሥራ ውልን ለማቋረጥ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን መከራከሪያ ነጥብ ውድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ በሕግ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

ስለዚህም ውሣኔው ባለበት እንዲፀና ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 50103 ሰኔ 25 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 98347 በ30/02/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡



www.chilot.me

2. በዚህ መዝገብ ላይ ህዳር 17 ቀን 2003 ትዕዛዝ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55731

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ መልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ማህበር - አቤነዘር በወንጌል ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የሕግ ተወካይ

አቶ ፈቃዱ ደጀኔ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ተቋቁሞና ሕጋዊ ዕውቅና እና ሕልውና አግኝቶ የኖረ ማህበር መሆኑን ገልያ ከታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 377/96 እንደማይተዳደርና በልዩ ሕግ የሚታዳደር መሆኑ በሕግ የተደነገገ በመሆኑ ማሕበሩ እንዲፈርስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ዓላማዬን ማሣካት አልቻልኩም ብሎ የመፍረስ ጥያቄ ማቅረብ የማሕበሩ እንጂ የከሳሽ (ተጠሪ) መብት አይደለም ማሕበሩ የሚፈርስበት ምክንያት የለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ሠራተኛው ከአዋጅ ቁጥር 377/96 ውጭ በተለየ ደንብ መታዳደሩ ማሕበሩን ለማፍረስ ያማያስችል አይደለም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የብሔራዊ ባንክ ሠራተኞች በደንብ ቁጥር 157/2001 የሚተዳደሩ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3/1/ሠ/ የሚሸፈኑ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ማሕበሩ ሊፈርስ አይገባም ሲል የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ አመልካች ማሕበር እንዲፈርስ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ግንቦት 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ማሕበሩ ለሰላሣ ሦስት ዓመት ያሕል ዕውቅና አግኝቶ የሠራተኛውን መብትና ጥቅም ሲያስጠብቅ የኖረ ነው፡፡ ሠራተኛው



www.chilot.me

በደንብ ቁጥር 157/2001 የሚተዳደር መሆኑ ማህበሩ ያለውንና ቀደም ሲል የነበረውን ህልውና ለማስጣት የሚቻል አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 120 ድንጋጌና የአገሪቱን ሕገ መንግስት አንቀፅ 31 እንደዚሁም ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት በኩል ያፀደቁትን ስምምነቶች በተለይም ቁጥር 87 እና ቁጥር 98 የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ታሕሣሥ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር መልስ የብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ. 591/2000 የባንኩን ሠራተኞችና የአስተዳደር አካላትን በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንድያወጣ ሥልጣን ይሰጣል፡፡ በዚህ መሠረት ደንብ ቁጥር 157/2001 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ የባንኩ ሠራተኞች በዚህ ልዩ ሕግ የሚተዳደሩና በአዋጅ ቁጥር 377/96 የማይተዳደሩ በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2/ሠ/ መሠረት በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ያቋቋመው አመልካች ሕልውና ኖሮት ተግባሩን ሊያከናውን አይችልም ፡፡ አመልካች የአዋጅ ቁ/ 377/96 አንቀፅ 120ን በመጥቀስ ያቀረበው አቤቱታ ከተያዘው ክርክር ጋር አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 31 እና ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት ስምምነቶች ቁጥር 87 እና ቁጥር 98ን በመጥቀስ ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በልዩ ሕግ የሚተዳደሩ እንደ ፖሊስ ዐቃቢያነ ሕግ ዳኞች የመንግስት ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የተደራጀ ማሕበር እንደማይኖራቸው ሁሉ አመልካች የተለየ የሚሆንበት ምክንያት የሌለ በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያስናብተን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ በሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች እንዲፈርስ ተጠሪ ያቀረበው ጥያቄና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው ጭብጥ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 31 ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ የመደራጀት መብት እንዳለው የተደነገገ መሆኑን ገልፆ በተጠሪ የተመዘገበውን የምስክር ወረቀት የተሠጠው የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ማሕበር የሚፈርስበት ሕጎዊ ምክንያት የለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች በሕገመንግስቱ አንቀፅ 31 እና ሌሎች የሕግ ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ እንደተቋቋሙት ሌሎች የሙያ ማሕበራት የሚቆጠር ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

የሠራተኛ ማህበር የማቋቋም መብት በህገመንግስቱ አንቀፅ 31 ከተደነገገው በተለየ ሁኔታ በህገመንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች ገበሬዎች የእርሻ ሠራተኞች ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግስት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚውን ሁኔታ ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው ይህ መብት የሠራተኛ ማሕበራትን ሌሎች ማሕበራትን በማደራጀት ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብት ያካትታል በማለት ይደነግጋል፡፡ በህገመንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚቋቋም የሠራተኛ ማህበር በህገመንግስቱ አንቀፅ 31 እና በሌሎች የህግ ማዕቀፎች ከሚቋቋሙ ማህበራት በአደረጃጀቱ በዓላማውና በተግባሩ የሚለይበት ሁኔታ እንዳለ በህገመንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 1/ለ/ እና በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 42 የንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ



www.chilot.me

ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሠራተኛ ማሕበር የሚመዘገበበትና የምስክር ወረቀት የሚያገኝበት መንገድ ሌሎች ማሕበራት ከሚመዘገቡበትና ዕውቅና ከሚያገኙበት የተለየ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 118 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ "የሠራተኛ ማህበር" በህገ መንግስቱ አንቀጽ 42 መሠረት የመመሥረት መብት ያላቸው "ሠራተኞች" ሲሆኑ ማንኛውም ሰው ዓላማውን እደግፋለሁ በሚል ምክንያት የአንድ ሠራተኛ መሕበር አባል መሆን አይችልም ፡፡ የሠራተኛ ማሕበር የመመስረት የሠራተኛ ማሕበር አባል መሆንና የመሣተፍ መብት ያላቸው "ሠራተኞች" ብቻ መሆናቸውን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የሠራተኛ ማሕበር ማለት ሠራተኞች በአንድነት ሆነው የሚያቋቁሙት ማህበር እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ ተደንግጓል፡፡

"ሠራተኛ ' ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ከአሠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው በማለት አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 2/4/ ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም በአንድ ተቋም ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች የሠራተኛ ማህበር ለማቋቋም የሚችሉት ወይም ቀደም ሲል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አቋቁመውት የነበረው ማህበር ህጋዊ ህልውና ኖሮት በሠራተኛ ማህበርነቱ ሊቀጥል የሚችለው የተቋሙ ሠራተኞችና የማህበሩ አባላት በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና በህገመንግስቱ አንቀጽ 42 መሠረት የሠራተኛ ማህበር የማደራጀት መብት ያላቸውና "ሠራተኛ ' የሚለውን ትርጓሜ የሚያሟሉ ሁነው ሲገኙ እንደሆነ ከላይ በዝርዝር ከገለፅናቸው ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ተቋቁሞ በተጠሪ ተመዝግቦና የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት የተደረጀና ሕጋዊ ህልውናውን ይዞ የሚቆይ የሠራተኛ ማህበር ከሌሎች ማህበሮች የተለየና "ሠራተኞች'ን ብቻ በአባልነት የያዘ መሆን እንደሚገባው ስለ ሠራተኛ ማህበር አመሠራረት በሚደነግገው አንቀፅ 114፣ ስለሠራተኛ ማሕበር ተግባር ከሚደነግገው አንቀፅ 115 ስለ ማሕበራት ምዝገባና ሕጋዊ ሕልውና ከሚደነግገው አንቀፅ 118 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የሠራተኛ ማሕበር የመመስረት መብት በአዋጅ ቁጥር 377/96 "ሠራተኛ ' የሚለውን ትርጉም የሚያሟሉ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደሩ ሠራተኞች መብት ብቻ መሆኑን ከሕገመንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 3 እና ከአሥሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ዝርዝር ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች አባላቱ በአዋጅ ቁ. 377/96 በሚተዳደሩበት ጊዜና ከዚህ የሕግ ማዕቀፍ በፊት በነበረው አዋጅ ቁጥር 42/68 መሠረት ተደራጅቶ የነበረ መሆኑ ከክርክሩ ለመገንዘብ ችለናል፡፡በአዋጅ ቁጥር 42/1968 እና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አባላቱ "ሠራተኛ' የሚለውን የሕግ ትርጓሜን በሚያሟሉበት ወቅት የተደራጀ የሠራተኛ ማሕበር ተቋሙ የሚተዳደርበት የሕግ ማዕቀፍ ከተቀየረና አባላቱ "ሠራተኛ' የሚለውን የሕግ ትርጉም የማያሟሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ "በሠራተኛ ማህበርነቱ' ተሰጥቶት የነበረው ምዝገባና እውቅና እንዲሁም የምስክር ወረቀት ለሚመለከተው ክፍል እንዲመልስ ተጠሪን ከመጠየቅ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 120 ድንጋጌዎች የሚከለክል አይደሉም፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 120 በባህሪው የአመልካች ክርክር (Indicative) የህግ ድንጋጌ እንጂ "Exhaustive" አሳሪ ወይም አሚጣጭ የህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነም አባላቱ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ጥር 377/96 በሚተዳደሩበትና ሠራተኛ የሚለውን ትርጓሜ በሚያሟሉበት ወቅት በሠራተኛ ማህበርነት ተመዝግቦና ከተጠሪ የምስክር



www.chilot.me

ወረቀት ወስዶ በህገመንግስቱ አንቀፅ 42 እና በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 115 የተመለከቱትን ተግባራት ሲፈፅም የቆየው አመልካች የተቋሙ ሠራተኞች በደንብ ቁጥር 157/2001 መተዳደር ከጀመሩበትና "ሠራተኞች' የሚለውን ትርጓሜ የሚያሟሉ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) ከተዘረዘሩት መካከል የሚመደቡ በመሆናቸው ከተጠሪ የተደረገለትን ምዝገባና የምስክር ወረቀት ይዞ በሠራተኛ ማሕበርነት የሚቀጥልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካችን በአዋጅ ቁጥር377/96 በአንቀጽ 118 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በመመዝገብ የሰጠው የምስክር ወረቀት እንዲሠረዝለት ማመልከቱ ተገቢና ሕጋዊ መሠረት ያለው ሲሆን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል የሰጠው ውሣኔ የህገመንግስቱን አንቀፅ 42 ድንጋጌዎችና በአዋጅ ቁጥር 377/96 ከላይ የተገለፁትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59666

ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ሠላማዊት ኃይሉ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ አቡ ጉበና ከጠበቃቸው ከአቶ ተካልኝ ነጋሣ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በአሁኑ የሰበር ተጠሪ አቅራቢነት ለሥር ወረዳ ፍ/ቤት ነሐሴ 27 ቀን 1999 ዓ/ም የቀረበው ክስ በተከሣሽ /በአሁኑ አመልካች / መ/ቤት ከ1989 እስከ የካቲት 1999 ዓ/ም በተለያዩ የሥራ መደቦች በወር ብር 2110 ደመወዝ እየተከፈለኝ ከቆየሁ በኋላ ተከሣሹ ከሥራ ሲያስናበተኝ የአገልግሎት ካሣ እና የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ ብር 13,187.50 ካሰበልኝ በኋላ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ ታክስ ብር 2,203.87 ከቀነሠ በኋላ በሥልጣኑ ለት/ቤት የከፈልኩት ነው በማለት ብር 6,792.57 ቆርጦብኝ ብር 4,191.04 ብቻ ከፍሎኛል፡፡ የከፈለኝን ገንዘብም ቢሆን መክፈል ከሚገባው ጊዜ 2 ወር በማዘግየት የሚያዝያ ወር 1999 በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 337/96 በአንቀጽ 36 በተደነገገው መሠረት በ7 ቀን ውስጥ አልከፈለም፡፡ የት/ቤት ክፍያም ቢሆን በህብረት ስምምነታችን አንቀጽ 25 ከ12ኛ ክፍል በላይ ለሆነ ትምህርት የት/ቤት ክፍያ ተከሣሽ መ/ቤት 50% እንደሚከፍል ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ተከሣሽ መ/ቤት ያለ አግባብ የቆረጠብኝ ገንዘብና ክፍያ ባዘገየበት የ3 ወር ደመወዜን እንዲከፍለኝ ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሹም በነገረ ፈጁ አማካይነት በሰጠው መልስ ከሳሽ ለ11 ዓመት አገልግያለሁ የሚለው ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ከሣሽ ከመስከረም 1 ቀን 1989 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1992 ድረስ የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ሰራተኛ ነበር፡፡ የመንግስት ሠራተኛ ከሆነ ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 ጥቅማጥቅም ማግኘት አይችልም፡፡ ከሣሽ በተከሳሽ መ/ቤት የተቀጠረው ከሐምሌ 1 ቀን 1992 ጀምሮ ስለሆነ የአገልግሎት ካሣ ማግኘት ያለበት ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከሣሽ በየጊዜው የትምህርት ቤት ክፍያ እየጠየቀ ተከሳሽ መ/ቤት ሲከፍል የቆየ በመሆኑ በመካከላችን ውል የለም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/ለ/ ሥር የተጠቀሰውን ግዴታ አልተወጣም በማለት የከሣሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡



www.chilot.me

የሥር ወረዳ ፍ/ቤትም ዕዳን አንድ ሠራተኛ ከሚያገኘው የአገልግሎት ካሣ ማቻቻል አይቻልም፡፡ ተከሣሽ አለኝ የሚለው መብት ካለ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት መጠየቅ እንጂ ከደመወዙ ጋር ተያይዞ የሚገኝ ነገር ላይ ማቻቻያ ሊደረግ አይገባም፡፡ ይህ ሆኖ ሣለ ተከሣሽ ከከሣሽ ደመወዝ መቁረጡ በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 1833 /11/ የተደነገገውን የሚፃረር ነው በማለት ተከሣሽ ከከሣሽ የቆረጠውን ገንዘብ ብር 6,792.57 ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝና ኪሣራ ብር 500 እንዲሁም የጠበቃ አበል 10% እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ይግባኝ ባይ /የሥር ተከሣሽ/ የ11 ዓመት የአገልግሎት ካሣ ለመልስ ሰጪው ከከፈለ በኋላ የ11 ዓመት አገልግሎት በተከሣሽ መ/ቤት የለውም ሲል የተከራከረው ያለአግባብ ነው፤ ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪውን ያስተማረ ቢሆንም ምን ያህል እንደሚያገለግል የተማረው መቼ እንደሆነና ግዴታውን ተወጥቷል የሚባለው መቼ ነው የሚሉትን ነጥቦች ያላስረዳ በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ የሚነቀፍ ነገር የለም በሚል ውሣኔውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካች ለሥር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል በማመልከቱ የሥር ሰበር ሰሚው ችሎትም የግራቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ ከአገልግሎት ካሣ ክፍያ ውስጥ ለትምህርት የተከፈለውን በሚመለከት ተመላሽ የሚደረግ ስለመሆኑ ውል መኖር አለበት፡፡ ውል በሌለበት አስተማርኩ በሚል ብቻ ከአገልግሎት ካሣ ቆርጦ ማስቀረት ተቀባይነት የለውም፡፡ ክፍያ ለዘገየበት አመልካች ያመነውን ከፍሎ ያላመነውን ያልከፈለ ስለሆነ በክፉ ሀሳብ ተጠሪን ለመጉዳት አዘግይቷል ለማለት አይቻልም በማለት አመልካች ለተጠሪ የ3 ወር ደመወዝ መክፈል የለበትም ሲል የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር የተሰኘው የሰበር አመልካችም ለዚህ ችሎት ባቀረበው ቅሬታ ተጠሪው ከመስከረም 01 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ወር 1992 ዓ/ም ድረስ በአመልካች መ/ቤት ያገለገለው በአሠሪና ሠራተኛ ህግ መሠረት ሳይሆን በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ በመሆኑ የሶስት ዓመት ከአሥር ወር የአገልግሎት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈለው አይገባም፡፡ ተጠሪው ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀው የ2ኛ ዲግሪውን ትምህርት መንግስት እየከፈለ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ የሚፈለግበትን አገልግሎት ሳይፈጽም በመሆኑ በተሻሻለው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ መሠረትና አንቀጽ 39/ሸ/ የውል ግዴታ ስላለበት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ የለም፣ ገንዘቡም ለመንግስት ተቆርጦ ገቢ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ ምንም ዓይነት ስምምነት ከአመልካች ጋር የለኝም በሚል ያቀረበው ክርክርም ቢሆን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 26 በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ ባለመፈረሙ ብቻ ግዴታውን የሚያስቀርለት አይሆንም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ እስከአሻሸለው ድረስ የጠበቃ አበል 10% እና ኪሣራ ብር 500 አሻሽሎ መወሰን አሊያም መሠረዝ ይገባው ነበር በማለት ከመስከረም 1 ቀን 1989 - ሰኔ 30 ቀን 1992 ያለው የ3 ዓመት ከ10 ወር የአገልግሎት ካሣ አመልካች ለተጠሪው ይከፍላል የተባለው እንዲሠረዝ አመልካች ከተጠሪው የአገልግሎት ካሣ ውስጥ ለትመህርት የከፈለውን ቆርጦ ማስቀረቱ ያለአግባብ ነው የተባለው ተሽሮ ገንዘቡ ለአመልካች ገቢ እንዲሆን እንዲወሰን፣ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነበት የጠበቃ አበልና ኪሣራ እንዲሠረዝ ጠይቋል፡፡



www.chilot.me

አመልካች ላቀረበው የሰበር ቅሬታ ተጠሪው በሰጠው መልስ ከመስከረም ወር 1989 ዓ/ም ጀምሮ ያለውን የአገልግሎት ካሣ አስቦ የከፈለኝ ራሱ የአሁኑ አመልካች ስለሆነ ተጠሪ ክስ ከመሠረትኩበት በኋላ የአገልግሎት ካሣው የተከፈለው በስህተት ነው ብልም ከመስከረም 01 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ ሠራተኛ ስለመሆኔ በሥር ፍ/ቤት በቀረበው የፅሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የህብረት ስምምነት አንቀጽ 26/2/ ከትምህርትና ሥልጠና ጋር በተያያዘ የውል ግዴታ መግባት እንደሚያስፈልግ ይናገራል፡፡ ተጠሪም የውል ግዴታ ገብቼ የፈረምኩት ሠነድ የለም፡፡ አመልካችም በማስረጃነት ያቀረበው ሠነድ የለም፡፡ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 39/1/ሸ/ ከሥልጠና ጋር በተያያዘ ለአሠሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሠራተኛው ሲለቅ የአገልግሎት ካሣ እንደሚከፈለው ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም የሰበር ተጠሪ ከአሠሪው መ/ቤት ጋር የገባሁት የትምህርት ውል ስለሌለ የአገልግሎት ካሣ ከማግኘት የሚከለክለኝ ነገር የለም፡፡ ስለሆነም በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የቀረበ ሲሆን እኛም በሥር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ለተጠሪ ሊከፈለው ይገባል በሚል በተወሰነው ገንዘብ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚለው በአገልግሎት ካሣ፣ በጠበቃ አበል እና በኪሣራ ገንዘብ አከፋፈል ነው፡፡

የአገልግሎት ካሣን በሚመለከት ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸው ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠርና የአግልግሎት ካሣ ለተጠሪው ይገባል በማለት አመልካች ከወሰነው ገንዘብ ውስጥ አመልካች ለተጠሪው የትምህርት ቤት ክፍያ ፈጽሜአለሁ በማለት የቀነሰው ገንዘብ ነው፡፡

ተጠሪው ከመስከረም 1989 እስከ የካቲት 1999 ዓ/ም ለአሥራ አንድ ዓመት በአመልካች መ/ቤት ማገልገሉን በመጥቀስ ሲከራከር አመልካች ግን ተጠሪው ከ1989 መስከረም ወር ጀምሮ እስከ 1992 ሰኔ ወር ድረስ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 377/96 የማይተዳደርና የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ሠራተኛ ነበር በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ የተነሣም የ3 ዓመት ከ 10 ወር የአገልግሎት ካሣ አይገባውም ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች መ/ቤት ቀደም ሲል በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ የሚተዳደር የነበረና ከዚያም በአዋጅ ቁ. 377/96 ማለትም ስለ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በወጣው አዋጅ እንዲተዳደር መደረጉን ነው፡፡ ተጠሪም ቢሆን ቀደም ሲል በአመልካች መ/ቤት የመንግስት ሠራተኛ የነበረ ሲሆን አመልካች መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 እንዲተዳደር ሲደረግ ተጠሪውም በተመሳሳይ ሁኔታ በተጠቀሰው አዋጅ የሠራተኛን ትርጉም በማሟላት በአመልካች መ/ቤት ሲሠራ ቆይቷል፡፡ አመልካች መ/ቤትም ተጠሪው ለ11 ዓመት ያህል በአመልካች መ/ቤት ማገልገሉን በማመን የ11 ዓመት የአገልግሎት ካሣ በማስላት አጠቃላይ የሚከፈለው የአገልግሎት ካሣ መጠን ከታወቀ በኋላ ለትምህርት ቤት የከፈለውን በመቀነሥ ለራሱ አስቀርቷል፡፡ ይሁን እንጂ አሠሪው ማለትም ያሁን አመልካች የተጠሪው የአገልግሎት ዘመን 11 ዓመት መሆኑን ተቀብሎ ምን ያህል የካሣ መጠን እንደሚከፈለው ካረጋገጠ በኋላ በፍ/ቤት በተጠሪ ከሳሽነት ክስ ሲቀርብ የተጠሪውን ቀደም ሲል የመንግስት ሠራተኛ ነበር በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የአገልግሎት ካሣ ማግኘት



www.chilot.me

ያለበት ከሐምሌ 1992 ጀምሮ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ህጋዊ ውጤት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪን የአገልግሎት ዘመን በሁለት በመክፈል ካሣ ሊከፈለው የሚገባ ው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መተዳደር ከጀመረበት ጊዜ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤት ያልተቀበለው በአግባቡ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪው 11 ዓመት አገልግሎት አለው ተብሎ በዚሁ መጠን የ11 ዓመት የአገልግሎት ካሣ ሊከፈለው አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤት ውድቅ በማድረጉ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ከዚህ ከካሣ አከፋፈል ጋር ተያይዞ የሚነሣው አመልካች ለተጠሪው የሚገባውን የካሣ መጠን በስሌት ካረጋገጠ በኂላ የተጠሪው 2ኛ ዲግሪ ሲማር አመልካች የት/ቤት ክፍያ ከፍሏል በማለት ብር 6,792.57 ከካሣው ገንዘብ መቁረጡ ነው፡፡፡ አመልካች ለት/ቤት የከፈለውን ገንዘብ የቀነሠው ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኂላ በአመልካች መ/ቤት ማገልገል ሲገባው ግዴታውን አልተወጣም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለት/ቤት ያወጣውን ወጪ ከተጠሪው ለመቀበል በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሸ/ መሠረት መብት አለው ምክንያቱም በአመልካችና ተጠሪ መካከል የውል ግዴታ አለ የሚል ነው፡፡ የውል ግዴታውም ሊመሠረት የቻለው ተጠሪው የትምህርት ቤት ክፍያ እንዲከፍልለት በየጊዜው እየጠየቀ አመልካችም ይከፍልለት ነበር በማለት ነው፡፡ ሆኖም ከአመልካች አለ የሚለውን የውል ግዴታ ተጠሪው የፈረምኩት ሠነድ የለም በማለት ይከራከራል፡፡

እዚህ ላይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የትምህርት ቤት ክፍያን በሚመለከት ውል አለ ወይስ የለም? የሚለውን ነጥብ ሳይሆን አመልካች ለተጠሪው ከሚገባው የአገልግሎት ካሣ የትምህርት ቤት ክፍያ ቆርጦ ማስቀረት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ነጥብ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተገለፀው አመልካችና ተጠሪ የሚተዳደሩት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ሲሆን የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች በአዋጁ የተቀመጡትን መብትና ግዴታ ማክበር ይጠበቅባቸዋል ፡፡ በአዋጁ ከተጠቀሱት መብቶች አንዱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ደመወዙንና ከደመወዙ ጋር የተያያዙትን ክፍያዎችን በህጉ በተወሠነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ክፍያው አከራካሪ ሆኖ ከተገኘ የሕጉን አካሄድ መከተል የግድ ይላል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ የመንግስት ግብር ተቀንሶ ተጠሪው የአገልግሎት ካሣ ማግኘት ያለበት ብር 10,983.63 መሆኑን ሲገልጽ ይኸንኑ የገንዘብ መጠን አመልካችም ትክክል መሆኑን ያምናል፡፡ ይሁን እንጂ የት/ቤት ክፍያ ብር 6,792.57 መቀነሱ አግባብ ነው ይላል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 የደመወዝ ቅነሣን በሚመለከት በአንቀጽ 59 የተደነገገ ሲሆን ይኸው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ደመወዝ የሚቀነሰው በህግ በህብረት ስምምነት ወይም በሥራ ደንብ በተወሰነው ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ መሠረት ካልሆነ ወይም ሠራተኛው በጽሁፍ ካልተስማማ አሠሪው ከሠራተኛው መቀነሥ እንደማይችል ወይም በዕዳ ሊይዝ ወይም ሊያቻችል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ የአገልግሎት ካሣም ቢሆን ለዕዳ የሚያዝ ወይም የሚቀነሥ ከሆነም በተጠቀሰው የህግ አንቀጽ መሠረት መቀነስ ወይም ሊያዝ ከሚችል ውጪ አሠሪ በራሱ ውሣኔ ሊቀንስ ሊይዝ ወይም ለዕዳ እንዲቻቻል ማድረግ አይችልም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የሰበር አመልካች ቆርጦ ያስቀረው የአገልግሎት ካሣ ገንዘብ ለተጠሪ እንዲመልስ በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡



www.chilot.me

ሌላው አመልካች እንደመሠረታዊ የህግ ስህተት የጠቀሰው የጠበቃ አበል 10% አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ተጠሪው ክርክር ያካሄደው በግሉ ስለመሆኑ አልተከራከረም፡፡ ነገር ግን 10% ለጠበቃው አበል መወሰኑ አለአግባብ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ጠበቃው ሙያዊ አገልግሎት መስጠቱ እስካልተካደ ድረስ ደግሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 42 በተደነገገው መሠረት ተገቢና ሚዛናዊ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ተገቢና ሚዛናዊ ክፍያ ነው የሚባለው ደግሞ በተጠቀሰው የህግ ቁጥር ከንዑስ ቁጥር 1-8 የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች መሠረት በማድረግ የተወሰነ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች ግን የሥር ፍ/ቤት 10% የጠበቃ አበል ሲወስን በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 42 ሥር የተዘረዘሩ መመዘኛዎች የተጣሱ ስለመሆናቸው ያቀረበው የህግ ክርክር የለም፡፡ ይህ ችሎትም የቀረበውን የጠበቃ አበል ቅሬታ ከተጠቀሰው ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 42 እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 462ና 463 ድንጋጌ ጋር እንዳገናዘበው በደንቡ የዘረዘሩት መመዘኛዎች የተጣሱ ስለመሆናቸው አመላካች የሚሆን ነገር አላገኘም፡፡ በመሆኑም በጠበቃ አበል አወሣሠን ላይ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የለም፡፡

አመልካች ያቀረበው ሌላው ክርክር የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በማሻሻል እስከወሰነ ድረስ የብር 500 /አምስት መቶ / ኪሣራ መቀነስ ወይም መሰረዝ ነበረበት የሚል ሲሆን ይህ ችሎት ተጠሪ በክርክር ወቅት ከብር 500(አምስት መቶ) ያላነሠ ኪሣራ እንደሚደርስበት ያምናል፡፡ የኪሣራው መጠን ከዚህ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ያንሣል ቢባል እንኳ የአመልካችን ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን በጎላ መልኩ የሚጉዳ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አሻሽሎ በመወሠኑ ብቻ ኪሣራ መቀነሥ አለበት ወይም ሙሉ በሙሉ መሠረዝ አለበት ለማለት ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ፡፡ በመሆኑም የሥር ሰበር ሰሚው ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔን አሻሽሎ ሲወስን ኪሣራውን ግን በማጽናቱ የተጣሰ ህግ የለም፡፡ ስለሆነም በኪሣራ አወሣሠን ረገድም የሥር ፍ/ቤት የፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 90368 በቀን 14/10/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፣ በውሳኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ተብሏል፡፡
2. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ፡፡
3. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን ፡፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64821

ግንቦት 1 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - አንበሴ መኵንን /ነገረ ፈጅ/ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አያሌው ሕብስት ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሣውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ መሠረት በተደረገው ምደባ ከደረጃ 11 ወደ ደረጃ 14 አድጌ እንድሠራ የተደረገ ቢሆንም ለቦታው የተመደበው ደመወዝ ግን አልተከፈለኝም በማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ያለአግባብ ሳይከፈለኝ ቀርቶአል የሚለውን የሁለት እርከን ጭማሪ ምደባው ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ታስቦ እንዲከፍለው ይወሰንለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የሥረ ነገር ክርክር አቅርቦአል፡፡ በሥረ ነገር ረገድ ያቀረበው ክርክር ከሣሽ ደረጃውን ያገኘው በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አጠቃላይ ምደባ እንጂ በእድገት አይደለም፡፡ እድገት የሚሰጠው ወይም የሚገኘው በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 11 መሠረት ነው፡፡ በዚህ አግባብ የተሰጠ የደረጃ እድገት ስለሌለ ክሱ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ የአመልካችን ክርክር በመቀበል የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ የጠየቀው የሁለት እርከን የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ የጠየቀው የሁለት እርከን የደመወዝ ጭማሪ የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጭብጥ ግራቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የተሰጡትን ውሳኔዎች በዝርዝር ተመልከተናል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የቻልነው ተጠሪ ተመድቤበታለሁ የሚለው በደረጃ 14 የሚታወቀው (የተሰየመው) የሥራ መደብ በኮርፖሬሽኑ (አመልካች) ባለው የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት እና ሂደት መሠረት የተገኘ አለመሆኑ በፍሬ ነገር መረጋገጡን ነው፡፡ በእርግጥ ኮርፖሬሽኑ አጠቃላይ የሆነ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በማካሄድ ከሥራ ሂደት ለውጡ መካሄድ በፊት የነበረው አደረጃጀትና የሥራ መደቦች ስያሜ ተለውጠዋል፡፡ ይህ ደግሞ የኮርፖሬሽኑ የሥራ አደረጃጀትን በተመለከተ የተደረገ አጠቃላይ ለውጥ እንጂ ሠራተኞችን ለማሳደግ (በእድገት ለማስቀመጥ) በሚል የተደረገ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው የደረጃ እድገት ሊገኝ የሚችለው እራሱን በቻለ የአሠራር ሥርዓት እና ደንብ መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ማካሄድ እና የደረጃ እድገት መስጠት ወይም አሰጣጥ በዓላማም ሆነ በውጤት ረገድ የተለየዩ የየራሳቸውን ግብ ይዘው የሚነሱ እንደሆኑ መገንዘቡ ተገቢ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው በአመልካች ኮርፖሬሽን የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት እና ደንብ መሠረት ተጠሪ የደረጃ እድገት አግኝቶአል አልተባለም፡፡ የደመወዝ ጭማሪ ሊገኝ የሚችለው በእድገት ወይም አሠሪው የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ የሚችልበት አግባብ ኖሮት ሲጨምር ነው፡፡ ተጠሪ የጠየቀው የሁለት እርከን የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኝ በፍ/ቤት ሊወሰን የሚችለውም ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሁለት እርከን ደመወዝ ጭማሪ ሊያሰጥ የሚችል የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሠረት አልነበረውም፡፡ ሲጠቃለል ተጠሪ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 95369 ጥር 12 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው የሁለት እርከን የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠኝ ጥያቄ የሕግ መሠረት የለውም ብለናል፡፡ በዚህ መሠረትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 33360 ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53527

መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ፖስታ አግልግሎት ድርጅት ነ/ፈጅ ማስረሻ በለጠ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ በዳሶ መልካቶ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ታይቶ የተወሰነውን ውሳኔ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዳማ ቱሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በዚሁ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የፍርድ ይፈፀምልኝ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 07667 ላይ ቀርቦ የተወሰነውን ውሳኔ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በዋናው ጉዳይ ላይ የአሁኑ ተጠሪ የስራ ውላቸው ያላግባብ የተቋረጠባቸው መሆኑን በመግለጽ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም ተገቢ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች የአሁኑን ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመለስ ወይም ተገቢ ክፍያዎችን እንዲከፍል ሲል ተወስኗል፡፡ እንዲፈፀም የቀረበው ውሳኔውም ይህ ሲሆን ዋናውን ፍርድ ተጠሪ ከአገኙና ከመፈፀሙ በፊት ግን ተጠሪ የመንግስት ገንዘብ አጉድለው ተገኝተዋል በሚል ምክንያት በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው ጥፋጽ በመፈጸሙ ጥፋተኝነታቸውም በፍርድ ተረጋግጦ በአንድ አመት ጽኑ እስራት እና በብር 1000.00(አንድ ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኖባቸዋል፡፡ ይህንኑ ቅጣት ጨርሰው ከወጡ በኂዋላ በአስሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እንዲፈጸምላቸው የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርቡም የአሁኑ አመልካች ተጠሪ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው ተረጋጋጦባቸው ቅጣቱን ጨርሰው ከወጡ በሁላ ሊፈጸምላቸው የሚገባ ፍርድ የለም በማለት እንደ ፍርዱ የማይፈጽምበትን ምክንያት ቀርቦ አስረድቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ፍርዱ የማይፈፀምበት ምክንያት የለም በማለት ተጠሪን አመልካች ወደስራው እንዲመልሰው ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትእዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 377 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 01 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ትእዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት



www.chilot.me

ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ በእምነት ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ተገቢው ቅጣት ተላልፎ ቅጣቱን ጨርሰው ከወጡ በሁዋላ ቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ወደ ስራ የሚመለሱበት ምክንያት የለም በማለት ዘርዝረው ትእዛዙ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የፍርድ አፈፃፀም ሂደቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የተመለከተውን ከፍተኛ የይርጋ ጊዜ መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓአል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮላቸው ተጠሪ ቀርበው በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ፍርድ ባልተለወጠበት ሁኔታ ፍርድ ሊፈጽም አይችልም ሊባል የሚችልበት ምክንያት የሌለ መሆኑንና አመልካች ከፈለገ በአማራጭ የተለያዩ ክፍያዎችን በመክፈል ሊያሰናብታቸው የሚገባ መሆኑን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ሲሉ ግንቦት 23 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገር ፈጅም ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የመንግስት ገንዘብ አጉድለው በመገኘታቸው በወንጀል ተፈርዶባቸው የእስራት ጊዜውን አጠናቅቀው ከወጡ ከአንድ አመት በሁዋላ በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት ቀደም ብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም አቤቱታ አቅርበው የስር ፍርድ ቤት ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚከለክለው ነገር የለም በሚል ምክንያት አመልካች ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ትእዛዝ መስጠቱን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ ስልጣን ባለው አካል እስካልተሻረ እና በሕጉ የተመለከተውን የይርጋ ጊዜ መሰረት አድርጐ ለአፈፃፀም እስከቀረበ ድረስ እንዲሁም የማይፈፀምበት ሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስከሌለ ድረስ የማይፈፀምበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉም ሆነ በሌሎች ተፈፃሚነት ባላቸው ሕጐች የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ የሚመራበት ሁኔታም እንደጉዳዩ አግባብነት መታየት ያለበት ስለመሆኑ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ልዩ ሕግ ካለ ተፈፃሚነት የሚኖረው ይኸው ልዩ ሕግ ነው፡፡ ጠቅላላ ሕግ ተፈፃሚነት የሚኖረው ጉዳዩን የሚገዛው ልዩ ሕግ በሌለበት ሁኔታ ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጐም መርሆዎች የሚሳዩት ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ጉዳዩ መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" ሲሆን ይህ ሕግ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚነሳን ክርክር የሚገዛ ነው፡፡ በዚህ ሕግ ውስጥ የተለያዩ የመብት ጥያቄዎች የሚቀርቡበት የዳኝነት አካልና የመብት ጥያቄዎች የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ ተመልክቷል፡፡ ሕጉ ግልጽ የሆነ የይርጋ ጊዜ ያልተቀመጠለት እና ምንጩ የአሰሪና ሰራተኛ የሆነ ማናቸውም የመብት ጥያቄ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እስካልቀረበ ድረስ የማይስተናገድ ስለመሆኑ በአንቀጽ 162 ስር አስቀምጧል፡፡ አዋጁ በግልጽ ላልተመለከቱ ጉዳዮች ከፍተኛውን የይርጋ ዘመን በተመለከተ አንድ አመት ስለመሆኑ ከማስቀመጡም በተጨማሪ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጐች ስር የተመለከቱት የይርጋ ጊዜያት ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአንቀጽ 162/5/ ድንጋጌ ስር አስፍሯል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ለሚቀርቡ ክርክሮች አግባብነት ካላቸው ሕጐች መካከል



www.chilot.me

አንዱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ነው፡፡ ይህ ስነ ሥርአት ከያዛቸውና ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንዱ ደግሞ በቁጥር 384 ስር የተመለከተው የአፈፃፀም ይርጋ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ፍርድ ለአፈፃፀም ሊቀርብ የሚገባው በአስር አመት ጊዜ ውስጥ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ አንድ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክር ሰሚ አካል የተሰጠ ውሳኔ ለአፈፃፀም ሊቀርብ የሚገባው ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ በስንት ጊዜ ውስጥ ነው የሚለው? ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 በዚህ ረገድ ያስቀመጠው ግልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ ሆኖም ግን አዋጁ በግልጽ ባያስቀምጥም ተገቢውን የሕግ ትርጉም መስጠት የግድ የሚል ነው፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ተገቢውን የሕግ አተረጓጐም መንገዶችን መከተል አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ሕግ ሲተረጐምም ሕጉ ሊፈፀም የሚችል ውጤት እንዲኖረው በማድረግ ስለመሆኑም ጠቅላላ የሕግ አተረጓጐም ደንቦች የግድ የሚሉት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ አይነተኛ ዓላማ ሲታይ የኢንዱስትሪ ሰላምን በማስፈን አጠቃላይ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለአገር ኢኮኖሚ አዎንታዊ ሚና መጫወት ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ ላይ የተገለፀ ጉዳይ ነው፡፡ የሕጉ አይነተኛ አላማ ይህ ከሆነ ደግሞ በአዋጁ የተካተቱት ድንጋጌዎች ሊተረጐሙና ሊፈፀሙ የሚገባው ይህንኑ የሕጉን አላማ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰራተኛ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕጉ ስር በተመለከተው የአስር አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ የአፈፃፀም መዝገብ ማስከፈት ይችላል ከተባለ አዋጅ ቁጥር 377/96 ሊያሳካ ያሰበውን ግብ ችግር ውስጥ የሚከተለው ይሆናል፡፡ ሰራተኛው በጊዜውና በቦታው ተገኝቶ ስራውን ካልሰራ አሰሪው ምርትና ምርታማነትን ያሳድጋል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት የሚኖረው በአዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የተመለከተው ከፍተኛው የአንድ አመት የይርጋ ጊዜ ለአፈፃፀም ማመልከቻም ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረጉ የአዋጁ አላማ ግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ አፈፃፀም የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም የፍርድ ይፈጸምልኝ ጥያቄው በዚህ ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የፍርድ ይፈጽምልኝ ጥያቄውን በአንድ ጊዜ ውስጥ ያለማቅረባቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይርጋውን ለማቋረጥ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የነበራቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ ሁኔታም የለም፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 377/96 ከአንድ አመት በላይ የረዘመ ክርክርን የማያስተናግድ ሁኖ እያለ ተጠሪ ይህንኑ ጊዜ ያሳለፈ ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ የአዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" አይነተኛ አላማና በዚሁ አዋጅ መሰረት የተወሰኑት ውሳኔዎች የፈጸሙበትን አግባብ ያላገናዘበ በመሆኑ አመልካች ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመልሳቸው የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአዳሚ ቱሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0925 ጥር 03 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 23879 የካቲት 18 ቀን 2002 ዓ.ም የጸናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት የአፈፃፀም ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/1/ መሰረት በአንድ አመት ይርጋ የታገደ ነው ብለናል፡፡



www.chilot.me

3. አመልካች ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመልስ ወይም በአማራጭ የተለያዩ ክፍያዎች ከፍሎ እንዲያሰናብት አይገደድም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 61872

የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፣* ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

*አመልካች፣* የኢትዮጵያ ፕልፕና ወረቀት አ/ማ ታፈሰ አበበ ቀረበ

*ተጠሪ፣* ዓብዱልቃድር አደም ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በአመልካች ፋብሪካ ለ38 /ሰላሳ ስምንት/ ዓመት ካገለገልኩ በኃላ ለጡረታ አራት /4/ ዓመት ሲቀረኝ በራሴ ፍላጎት ሥራውን የለቀቅሁ በመሆኑ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ነው አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ ሊሟላ የሚገባው ሁሉ ተሟልቶለት ጡረታ የወጣ በመሆኑ የስንብት ክፍያ ሊከፈለው አይገባም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ አይፈቅድለትም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤት ክርክሩን የመረመረ ሲሆን በመቀጠልም የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ተጠሪ የሥራ ስንብት ይከፈለው በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ ከተሰማ በኃላ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻው የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት አይደለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈለው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ 377/96ን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ 494/98 በአንቀጽ 2 ከተመለከተው ድንጋጌ አንፃር ሊመረመር የሚገባው ነው በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ በራሱ ፍላጎት የሥራ ውሉን ያቋረጠው /ከሥራ የተሰናበተው/ 38 /ሰላሳ ስምንት/ ዓመት ካገለገለ በኃላ እንዲሁም ዕድሜው 60 /ስድሳ/ ዓመት ሊሞላ 4 /አራት/ ዓመት ሲቀረው እንደሆነ አላከራከረም የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፈለኝ ይገባል የሚለው በእርግጥም በአሁኑ ጊዜ



www.chilot.me

የጡረታ አበል አላገኝም /አይከፈለኝም/ በማለት ሳይሆን ሥራውን በራሴ ፍላጎት በመለቀቄ እና በሕጉ የተመለከተውን የመጨረሻ የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት ስላልሞላኝ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አለኝ በማለት እንደሆነም ከክርክሩ ይዘት ተገንዝበናል አመልካች ደግሞ ተጠሪ ሥራውን የለቀቀው /የተሰናበተው/ ሊሟላለት የሚገባው ሁሉ ተሟልቶለት በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የጡረታ አበል እየተከፈለው ነው፡፡ የጡረታ አበል የሚያገኝ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያም እንዲከፈለው ሕጉ አያዝም ይልቁንም ሁለቱ ክፍያዎች በአንድ ጊዜ እንዳይከፈሉ ሕጉ በግልፅ ይከለክላል በማለት ተከራክሮአል፡፡

እንደምንመለከተው አከራከሪው ጭብጥ የሕግ ነጥብ በመሆኑ ሊፈታ የሚችለው አግባብ ባለው የሕጉ ድንጋጌ ነው፡፡ ክርክሩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳ በመሆኑም በቅድሚያ መታየት ያለበት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 ነው በዚህ አዋጅ ስለሥራ ስንብት ክፍያ በሚመለከት ተደንግጎ የሚገኘው በአንቀጽ 39 ሲሆን ይህ ድንጋጌ አዋጁን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 494/98 ተሻሽሎአል፡፡ በዚህ ማሻሻያ አዋጅ አንቀጽ 2/ሰ/ እና /ሸ/ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲታዩ አንድ ከሥራው የተሰናበተ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከሥራው በሚገለልበት ጊዜ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ሲሆን ወይም ደግሞ ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ በሕመም ወይም በፈቃዱ ሲለቅ /ሥራው ላይ የሚያስቀይ ከሥልጠና ጋር የተያያዘ የውል ግዴታ ሳይኖርበት የለቀቀ ሲሆን/ እንደሆነ ነው በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ሥራውን የለቀቀው በገዛ ፈቃዱ ሲሆን እንደለቀቀም በጡረታ መብት ተጠቃሚ ሆኖአል፡፡ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 13/3/ እንደተመለከተው ቢንያስ ሃያ አምስት ዓመት ያገለገለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ያልሆነ የመንግስት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕድሜ ልኩ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡ ተጠሪ ሥራውን በራሱ ፈቃድ የለቀቀው 60 ዓመት ሊሞላው 4 ዓመት ሲቀረው በመሆኑ በዚህ ሕግ መሠረት አበሉን እያገኘ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡

ከፍ ሲል በዝርዝር እንዳመለከትነው የጡረታ አበል እና የሥራ ስንብት ክፍያ አንድ ላይ እንዲከፍሉ ሕጉ አልፈቀድም፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ከሕጉ መውጣት የሚቻል አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንደምናየው ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ ይልቁንም ሕጉን በግልጽ በሚቃረን መልክ የተሰጠ ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ ከዚህ የተነሳም አቤቱታው የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39748 ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 25367 ጥቅምት 17 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 116497 ጥቅምት 25 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡
2. ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚያገኝበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

ም.አ                    *የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64988

ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች - ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ዳሽን ባንክ አ.ማ - ነገረ ፈጅ ዓለማየሁ ገበየሁ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሀይሉ ሽመልስ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ የካቲት 01 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ከሐምሌ 15 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረዉ በመስራት ላይ ከቆዩ በኋላ አመልካች ድርጅት ከታህሳስ 28 ቀን 2002 ዓ/ም ያለአግባብ ከስራ አግደዋቸው ቆይቶ ከታገዱበት ቀን ጀምሮ የተሰናበቱ መሆኑን ጥር 25 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ ደብቤ የገለፀላቸው መሆኑን ገልፀው ከህግ ውጭ የተከናወነ ስንብት በመሆኑ ወደ ስራ እንዲመለሱ እና ያልተከፈላቸው ደሞዝ ከኪሳራ ጋር እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠቀዋል፡፡ የአሁን አመልካች በክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ ባንኩን በተመለከተ ማንኛውንም መግለጫ የመስጠት ስልጣን ሳይኖራቸው በጋዜጣ የሰጡት አሉታዊ መግለጫ በባንኩና በሰራተኞች ላይ መረብሽን፣በደንበኞች ላይ ደግሞ መደናገጥን፣ለወደፊቱ የባንኩ ደንበኞች ሊሆኑ የሚችሉት ላይም ጥርጣሬን እና የህዝብ አመኔታን የሚያሳጣ በመሆኑ መሰናበታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/ መሰረት ባግባቡ ነዉ በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ማስረጃዎችን በመመርመር አመልካች ለጉዳዩ ማስረጃዎችን ያለማቅረቡንና ጥር 25 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ የስንብት ደብዳቤ የገለፀላቸው ድርጊቶችም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1/ስር ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት ከተጠቀሱት ህጋዊ ምክንያቶች ውስጥ የሚወድቁ አይደሉም የሚሉ ምክንያቶችን በመያዝ ስንብቱ ከህግ ውጭ የተከናወነ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች ተጠሪን የስድስት ወር ደመወዝ እና በእገዳ ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ከፍሏቸው ወደ ስራቸው ሊመልስ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡



www.chilot.me

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 02 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ በጋዜጣ ላይ የሰጡት መግለጫ ሀሰተኛ ሆኖ በባንኩ ክብርና እና ዝናው ላይ የተፈፀመ ሆኖ ይህም በባንኩ ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን የሚያረጋግጥ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27/1//ሸ ስር የሚወድቅ ሆኖ እያለ በበታች ፍርድ ቤቶች የታለፈው ያለአግባብ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው ግራቀኙ በፁሁፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የስራ ውሉ የተቋረጠው በህገወጥ መንገድ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ስለአመልካች ባንክ ጋዜጣዊ መግለጫ የመስጠት ሃላፊነት የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ሐሰተኛ የሆነ መግለጫ በመስጠት በባንኩ ሰራተኞች ላይ መደናገጥ፣በደንበኞቹ ላይ ጥርጣሬንና በህዝቡ አመኔታ እንዳይኖረው አድርገዋል በሚል ምክንያት መሆኑ ሲሆን ተጠሪ የሰጡት መግለጫ ሀሰተኛ ስለመሆኑ ሳይክዱ ለስንብቱ ምክንያት ነው በማለት የሚከራክሩት በስንብት ደብዳቤ ጥር 25 ቀን 2002 ዓ/ም የተፃፈው ሳይሆን በሪፖርተር ጋዜጣ የካቲት 03 ቀን 2002 ዓ/ም ወጣ የተባለውን መግለጫ በሚል መሆኑን ተረድተናል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው ተጠሪ የሰጡት ሀሰተኛ መግለጫ የለም በሚል ሳይሆን ሀሰተኛ መግለጫ መስጠታቸው መረጋገጡን ተቀብሎ ይኸው ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/ ስር አይወድቅም፣ በባንኩ ሰራተኞች ላይ መረበሽን፣በባንኩ ደንበኞች ላይ ደግሞ ጥርጣሬን መፈጠሩን አመልካች በማስረጃዎቹ አላስረዳም በሚል ነው፡፡

እንግዲህ ለስራ ስንብቱ ምክንያትነት የተጠቀሰው የተጠሪ ስለባንኩ ሀሰተኛ መግለጫ በጋዜጣ መስጠትና ይኸውም ድርጊታቸው በባንኩ ሰራተኞችና ደንበኞች የፈጠረውንና ሊፈጥር የሚችለው ችግርን ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የሀሰተኛ መግለጫ ፍሬ ጉዳይ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ተገንዝቦ ምክንያቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ስር የሚወድቅ አይደለም ሲል ነው የስራ ስንብቱ ህገወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው፡፡ በርግጥ የስር ፍ/ቤቱ በስራ ስንብቱ ላይ የተመለከተው የተጠሪን ጥፋት ይዘቱን በተፃፈው መልክ ከተመለከትነው ጥፋቱ በአዋጁ መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት ከሚያስችሉ ምክንያቶች ውስጥ ሊካተት የማይችል መሆኑን መገንዘብ ይቻል ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በተጠቃሹ አዋጅ ስር የተመለከቱት ምክንያቶች በክርክሩ ወቅት የሚረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮችንና የአዋጁን አጠቃቀም አላማና አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ በመመርመር ሊተረጎም የሚችሉ ስለመሆናቸው መገንዘብ አያዳግትም፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ የሰጠው ሀሰተኛ መግለጫ በባንኩ ስምና ክብር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ሆኖ በባንኩ ንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ሊቆጠር የሚገባው ነው በማለት ነው፡፡ ጉዳት ደረሰ የተባለውም የባንኩ መልካም ስም ጠፍቷል በሚልም ጭምር ሲሆን አመልካች ለዋቢነት የሚጠቅሰው ድንጋጌም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27/1//ሸ/ ስር የተመለከተውን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በአሠሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸዉም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ

ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሰራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ነው፡፡ ንብረት ለሚለው ቃል በአዋጁ ስር የተመለከተ ትርጓሜ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከአዋጁ አላማና ከአሠሪው ድርጅት ባህርይ እንዲሁም ከንብረት ህግ ፅንሰ ሀሳቦች ጋር በማዛመድ ለቃሉ ትርጉም መስጠት ህጋዊነት ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ንብረት ለሚለው ፅንሰ ሀሳብ ሁሉንም የሚያስማማ ትርጉም መስጠት የሚቻል አይደለምና፡፡ በመሆኑም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን አጠቃላይ አላማም ሆነ አጠቃላይ የንብረት ህግ ፅንስ ሀሳቦች ባህርያት እንዲሁም በንግድ ህጉ ስለመልካም ስም(Good Will) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ ንብረት ማለት ዋጋው ኢኮኖሚያዉ ጠቀሜታ ያለው እንዲሁም በአብዛኛው ሀብትነት ሊያዝ የሚችል ነገር መሆኑን ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ዋጋው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ በባለሀብትነት ሊያዝ የሚችል ነገር ላይ ሆን ብሎ ወይም  በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ያደረሰ ሰራተኛ ከሆነ በአሠሪው ንብረት ላይ በህጉ አነጋገር ጉዳት አድርሷል ለማለት የማይቻልበት ምክንያት የለም፡፡

እጃችን ወዳለዉ ጉዳይ ስንመለስ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት የተጠሪ አድራጎት ለአመልካች ዋጋው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባለው ነገር ላይ ጉዳት አላደረሰም የሚል ግልፅ ምክንያት በመያዝ ሳይሆን በሀሰተኛ መግለጫ ምክንያት በባንኩ ሰራተኞች ላይ መረበሽ በባንኩ ደንበኞች ላይ ደግሞ ጥርጣሬ ስለመድረሱ አመልካች ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአመልካች በኩል የቀረበው የፅሁፍ ማስረጃ የተጠሪን ጥፋቶች በግልፅ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችም ተጠሪ በሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 21.6 መሰረት ሀሰተኛ ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት የማይችሉ መሆኑን የሚያሳዩ ሲሆን ሐሰተኛ መግለጫ በባንኩ መልካም ስም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊኖረው አይችልም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አንድ ሰው ሀሳቡን የመግለፅ ህገመንግስታዊ መብት ያለው ቢሆንም ሀሰተኛ ቃል በመስጠት ግን በሌላ ሰው መልካም ስምና ክብር ላይ ወዲያውኑ ወይም ወደ ፊት ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ተግባር ሊፈፅም አይገባም፡፡ የባንክ ስራ በተለይ ሲታይም የህዝብ ጥቅም የበለጠ የሚንፀባረቅበት በመሆኑ መልካም ስም ሊጠበቅለት የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከህጉ መንፈስ ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሌላው የስር ፍ/ቤት የአመልካችን እርምጃ ህገ ወጥነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አንድ ሰራተኛ ከስራ የሚታገደው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ/18 መሰረት ነው፣የአመልካች እርምጃ ግን ይህንኑ ድንጋጌ የተከተለ አይደለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድን ሰራተኛ ጥፋት ፈፅሟል የሚል አሠሪ ሰራተኛውን ከስራው አግዶ ለማቆየት የሚችል መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/4/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያሳይ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜም የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤት በተጠሪ የስንብት ደብዳቤ ላይ የተገለፀውን ምክንያት እንዳለ በመውሰድ የደረሰበት ድምዳሜ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ ባለመምረጥና አጠቃላይ ይዘቱንና መንፈሱን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሳ ኔ

1. በፌደራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁ 50691 ሕዳር 06 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 99417 ጥር 25 ቀን 2003 በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ወጪና ኪሳራ የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሂ/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 61843

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሰይፋ ናስር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ እና ህግ ጉዳዮች ነ/ፈጅ ዓለም ቱፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 515/99 "ን" መሠረት አድርጎ የቀረበን የዲሲኘሊን ክርክርንና ይህንኑ መሠረት አድርጎ የተሠጠውን የቅጣት ውሣኔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አመልካችን የዲስኘሊን ግድፈት ፈፅሟል በማለት ከስራ እንዲሰናበቱ የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይኸው ፍርድ ቤት ተጠሪ መስሪያ ቤት አመልካችን ከስራ ያሰናበተው በአዋጅ ቁጥር 515/99 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 77/94 መሠረት ጉዳዩ በዲስኘሊን ኮሚቴ ተጣርቶ የውሣኔ ሀሣብ ሳይቀርብ ከባድ የዲስኘሊን ግድፈት ተፈጽሟል በሚል ምክንያት ነው፣ ይህ ደግሞ ሥነ ስርዓቱን ያሟላ አይደለም በማለት ጉዳዩ በዲስኘሊን ኮሜቴ ከታዩና ከተጣራ በሁዋላ ተገቢውን ውሣኔ ሊያገኝ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ መስሪያ ቤት ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይህ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በሁዋላ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የቢሮ ኃላፊ የሰጡትን ውሣኔ አፅንቶ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል በፍሬ ጉዳዩ ላይ የቀረበውን የአሁኑ አመልካች ቅሬታ ተገቢነቱ ሳይመረመር የቢሮው ኃላፊ ውሣኔ መጽናቱ ስነ ሥርዓታዊ አይደለም በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር ተጣርቶ ተገቢው እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ለአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት መልሶለት ይኸው ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ የቢሮው ኃላፊ በአመልካች ላይ ያስተላለፋት ቅጣት ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ አመልካች የሶስት ወር ደመወዝ ተቀጥተው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በሁዋላ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ



www.chilot.me

አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ ተብሎ በተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የተሠጠው ውሣኔ ሕጋዊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱን አስመልክቶ የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በችሎቱ ላይ የተሰየሙት ዳኞች ጉዳዩን ገለልተኛ ሁነን ለማየት አንችልም በማለት መዝገቡን ዘግተውታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው የይግባኝ ጊዜ ከአለፈ በሁዋላ ከመሆኑም በላይ በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠው ውሣኔም በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ ውሣኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው ፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታመኑም ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሑፍ መልሱ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ከአላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአንድ ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ ማረም የሚችለው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ሲሰጥና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ቀርቦለት ዋናውን ጉዳይ ሳይመለከት የቀረው ጉዳዩን ዳኞቹ ገለልተኛ ሁነው ሊመለከቱ አይችሉም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ያልሰጠበት ቢሆንም ችሎቱ ካለው የመሰረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አኳያ እና ጉዳዩ ከዚህ በፊት ከወሰደው ጊዜ እንዲሁም ከጉዳዩ ባህርይ አንጻር ይህ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎትም መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ሥልጣኑ በመሆኑ ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት ያለበት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ጠብቆ ቀርቦለት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ የሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሰጠው ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ/ም ነው፡፡ ይህ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ፣ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜም ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ የሚታሰቡ ሰላሳ ቀናት መሆናቸውን የአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 76/2/ እና የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 አንቀጽ 77/2/ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሰጠው ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ/ም ሲሆን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኙ የቀረበው ደግሞ ሐምሌ 21 ቀን 2002ዓ/ም ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ስለማለፋ የአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 76/2/ ን በመጥቀስ ያረጋገጠው ሲሆን በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ያደረገው አዋጅ ቁጥር 515/99 ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ነው፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ



www.chilot.me

ፍርድ ቤት ይግባኙን የሚያየው በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43/3/ መሠረት ሁኖ የሚመራውም በ1958ቱ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ነው፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ስልሳ ቀናት ነው፣ አዋጅ ቁጥር 515/99 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አለው ቢባል እንኳ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት ማመልከቻ ወደያውኑ ለአመልካቹ በመዝገብ ቤት ሹሙ እንደሚመለስለትና በአስር ቀናት ጊዜ ውስጥ የይግባኝ ማስፈቀጃ እንዲያቀርብ የሚደረግ በመሆኑ በመዝገብ ቤት ሹም ተከፍቶ ወደ ችሎት የቀረበ የይግባኝ መዝገብ በችሎት የሚታረም አይደለም የስነ ስርዓት ግድፈቱ በችሎት ሊስተካከል የሚገባው አይደለም በሚሉ ምክንያቶች ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች አዋጅ ቁጥር 515/99 እና አዋጅ ቁጥር 6/2000 ሲሆኑ ጉዳዩ የሚመራበትን ሥርዓትም በእነዚህ ሕጎች የተመለከተው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43/3/ መሠረት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ቢኖረውም ከዚህ አዋጅ በሁዋላ የወጡት አዋጅ ቁጥር 515/99 እና 6/2000 ጉዳዩ የሚመራበትን ሥርዓት በግልጽ ዘርግተው ይገኛሉ፡፡ እንዲህ ከሆነ በሕግ ተዋረዳዊ አቀማመጥ/ hierarchy of Laws / በሁዋላ የወጣ ሕግ ቀድሞ የወጣውን ሕግ በመቀደም ስራ ላይ የሚል መሆኑን ተቀባይነት ያለው የሕግ አተረጓጎም መርህ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43/3/ እና በፍትሓ ብሔር ስነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከተው የይግባኝ ማቅራቢያ ጊዜ ነው በማለት የሠጠው ምክንያት ከሕግ አተረጓጎም መርህ አንፃር ሲታይ ሕጋዊ አይደለም፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 515/99 እና አዋጅ ቁጥር 6/2000 ሲሆኑ እነዚህ አዋጆች በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ውሣኔ በተሰጠ በሰላሳ ቀናት መሆኑን ይደነግጋሉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አዋጆቹ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት አላቸው ቢባል እንኳ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 324/1/ ስር በተመለከተው ሁኔታ ችሎት የሥነ ሥርዓት ግድፈቱን ሊያስተካክል የሚችለው አይደለም በማለት ደምድሟል፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 324/1/ መሠረት ለአንድ ፍርድ ቤት መዝገብ ሹም የተሰጠው ሥልጣን ይግባኝ ማቅራቢያ ጊዜ ማለፍ አለማለፋን በመመልከት ይግባኝ መዝገቡ እንዲከፈት ማድረግ ሲሆን ይግባኙ ጊዜውን ጠብቆ ያልቀረበ ከሆነ ማመልከቻውን መመለስ፣ ማመልከቻው የተመለሰበት ወገን የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ሕጋዊ ምክንያት ካለው ማስፈቀጃ አቤቱታውን በማቅረብ ይኸው ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ራሱን የቻለ አቤቱታ አቅርቦና ይህ መዝገብ ተከፍቶ ጉዳዩ ለችሎት ቀርቦ ችሎቱ የይግባኝ ማስፈቀጃውን በመመርመር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 325 እና 326 መሠረት ተገቢ ነው ያለውን ትእዛዝ የሚሰጥበት ነው፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 324/1/ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 325 እና 326 ድንጋጌዎች ጋር አንድ ላይ ሲነበቡ የመዝገብ ቤት ሹም ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ለችሎት እንዲቀርብ የመፈቀድ ስልጣን የሌለው መሆኑን የሚያሳዩ ሲሆን ፋይሉ ተከፍቶ ቀርቦ ከሆነም ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ይግባኙ የቀረበው ጊዜው ከአለፈ በሁዋላ ነው በማለት መዝገቡን ከመዝጋት የሚከለክለው አይደለም፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 324/1/ ድንጋጌን ይዘቱንና መንፈሱና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 325 እና 326 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር አዛምዶ ሳይመለከት የመዝገብ ቤት ሹም የይግባኝ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ መዝገብ ከፍቶ ከአቀረበ ችሎቱ ሊያስተካክለው የሚችለው አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ሕጋዊ መሠረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያላቸው የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 515/99 ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 በመሆናቸውና በእነዚህ አዋጆች መሠረት በሚታይ ጉዳይ ላይ ውሣኔ ሲሰጥ ይግባኙ የሚቀርበው በሰላሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ መሆኑ



www.chilot.me

የተደነገገ በመሆኑና የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ሁኔታ በስርዓቱ መሠረት የማስፈቀጃ አቤቱታ ለችሎት ቀርቦ የሚታይ ከሚሆን በስተቀር በመዝገብ ቤት ሹም የሚታይ ባለመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ የይግባኝ ጊዜው አልፎበት እያለ ተቀብሎ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የስነ ስርዓት ሕግ ግድፈት በመፈፀም ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13951 ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ/ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ/ም በሰጠው ውሣኔ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበው የሰላሳ ቀናት የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜያት ከአለፉ በሁዋላ በመሆኑና በሥርዓቱ መሰረትም ተገቢውን የማስፈቀጃ አቤቱታ ያላቀረበ በመሆኑ ይግባኙ የሚስተናገድበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. የአዲሰ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 158/02 ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ/ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገበ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57337

ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አድቬንቲስት የልማት የተረድኦ ድርጅት - ጠበቃ ዶ/ር ዘወድነህ በየነ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ገበየሁ ወ/ሚካኤል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የቀረበው ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ሲሆን የቀረበው በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው በመስራት ላይ እንዳሉ ያለአግባብ ከስራ የተሰናበቱ መሆኑን በመግለጽ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲወሰንላቸው የጠየቁ ሲሆን በማስረጃም የጽሁፍ የሰው ምስክሮች ዝርዝር አቅርቧል የሚል ነው፡፡ ተከሣሽ ድርጅት ቀርቦ በሰጠው መልስ ከሣሽ የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ይኼው ሲያበቃ ያሰናብተዋል፤ ከሣሽ ለረሃብተኞች እንዲከፋፈል ተብሎ የተሰጣቸውን ስንዴ እንዲበላሽ በማድረጋቸው በስራ ቦታ ላይ አለቃቸውን በመሳደባቸው እንደሁም የስራ ሰዓት ባለማክበራቸዉ ተሰናበተዋል በማለት በአማራጭ የተከራከረ ሲሆን ከማስረጃም አኳያ የጽሁፍ ሰነድና የሰው ምስክሮች ዝርዝር ቀርቧል የሚል ነው፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ በግራቀኙ መካከል የነበረው የስራ ውል ለተወነ ጊዜ ሆኖ የሚቆየው ከሰኔ 2000 ዓ.ም እስከ ታህሣስ 2001 ዓ.ም ድረስ በመሆኑ ይሄ ጊዜ ሲያልቅ የሚቋረጥ በመሆኑ ስንብቱ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/1/ መሠረት የተፈጸመ በመሆኑ ህጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ክፍያን በተመለከተ የፕሮቪደንት ፈንድ ብር 5086,96 ተከሣሽ ድርጅት ለከሣሽ በአንድ ዓመት የአገልግሎት ዘመን ውስጥ ለተሰራ የአራት ወር ከ20 ቀን የአመት ፍቃድ ክፍያ እንዲከፍለው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁን ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ካከራከረ በኋላ የቅጥር ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም የተቀጠሩት ለፕሮጀክቱ ስራ እስከ ሆነ ድረስ ፕሮጀክቱ ደግሞ የሚጠናቀቀው የስራ ዘመኑና የበጀት ዘመኑ አንድ ዓመት ነው በመባሉ ፕሮጀክቱ ስለመጠናቀቁ ደግሞ ተጠሪ /የአሁን አመልካች/ ያቀረበው ማስረጃ ባለመኖሩ ከስራ ተጠሪን ያሰናበተው ያለአግባብ ነው በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር አመልካች ለአሁን ተጠሪ ፕሮጀክቱ እስከሚጠናቀቅ ቢቆየ ኖሮ ሊከፈላቸው የሚችል የነበረው ደግሞ ማለትም ከታህሣስ 22 እስከ ሰኔ 30/01 ድረስ ያለውን ደሞዛቸው ታስቦ እንዲከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡



www.chilot.me

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ተጽፎ በቀረበው ቅሬታ ተጠሪ በሙሉ ፍቃድ ተቀብሎ የስራ ውል የገባው ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ይሄ ጊዜ ደግሞ የሚያበቃው ታህሣስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በመሆኑ ስራውም የፕሮጀክት ስራ ሆኖ እያለ ስንብቱ ህጋዊ ነው መባል ሲገባው ተጠሪ ያልሰራበትን ደሞዝ እንዲከፈለው መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የተጠሪ ጠበቃ ታህሣስ 04 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ፡- የቀረበው ቅሬታ ግልጽነት የለውም የተቀጠርኩበት የውል ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ ቢልም ተፈጻሚነት ያለው ግን የተቀጠርኩበት የስራ ጸባይ በመሆኑ የተቀጠርኩት ለፕሮጀክት ስራ ስለመሆኑ በመ/ደ/ፍ/ቤት ያልቀረበ በመሆኑ የስራ ውሉ የተቋረጠው ያለአግባብ ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃ ታህሣስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ የቀረበውን ቅሬታ በማጠናከር የሰጠ ሲሆን በተጨማሪ ፕሮጀክቱ በአሜሪካ አለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት የሚታገዝ በመሆኑ ጊዜው የሚጠናቀቀው ማለትም የበጀት ዓመቱ ታህሣስ 2001 ዓ.ም ሆኖ ሣለ ሰኔ 30 /2000/ ያልቃል በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲሻርልን በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራቀኙ የቀረበው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በተጠሪና በአመልካች መካከል የነበረው የስራ ውል ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪ ፈጽሚቸዋል በማለት አመልካች ያቀረበችውን ጥፋቶች በተመለከተ ደግሞ ከስራ ለማሰናበት በቂ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የበታች ፍርድ ቤት ማጣራት ውስጥ ያልገባ በመሆኑ ይሄ ችሎትም ወደዚህ ጭብጥ የሚያስመጣ አግባብ ካለ ከላይ በተያዘው ጭብጥ ውጤት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ለጊዜው እናልፈዋለን፡፡

ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የስራ ውል በውላቸው ውስጥ በግልጽ እንደተቀመጠው ከሰኔ /2000 ዓ.ም እስከ ታህሣስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም የሚመለከት መሆኑ አላከራከረም፡፡ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የውሉ ቃል ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ መሆኑ ሣይሆን መታየት ያለበት ከተቀጠርኩበት የስራ ጸባይ አኳያ መሆን ይገባዋል የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ደግሞ ውሉ ግልጽ ከመሆኑም በላይ ስራው የፕሮጀክት በመሆኑ የሚጠናቀቀው በታህሣስ ወር 2001 ዓ.ም ሆኖ ተገምግሞ ይቀጠል አይቀጥል የሚለው ውሣኔ ሲያገኝ ብቻ የሚቀጥል በመሆኑ ፕሮጀክቱ የአንድ ዓመት ነው የበጀት ዓመቱ ደግሞ የሚያልቀው ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ነው በማለት ፍርድ ቤቱ የደረሰበት መደምደሚያ አግባብነት የለውም የሚል ነው፡፡

የቀረበውን ክርክር ስንመለከት በእርግጥ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 10 አንድ ላይ ስናዬው አንድ የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ መደረጉ ብቻ የተወሰነ ጊዜ የስራ ውል እንደማያሰኘውና እንደስራው ባህሪ እየተየ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ ያስገነዘበናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ግን የስራ ውሉ ተጠሪ እንደሚከራከረው ለተወሰነ ጊዜ ስለመሆኑ ማስረዳት ብቻ ሣይሆን ስራው የፕሮጀክት ስራ መሆኑና በውጪ ድርጅት የሚደገፍ በመሆኑ የዓመት ስራ እንቅስቃሴው

ታይቶ ፕሮጀክቱ ይቀጥል ሲባል ብቻ የሚቀጥል እንደሆነ የበጀት ዓመቱም የሚጠናቀቀው ታህሣስ 2001 ዓ.ም እንደሆነ ከመከራከሩም በላይ በዚህ ነጥብ ላይ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ማስረጃ ሰምቶ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

የፕሮጀክቱ የበጀት ዓመት በታህሣስ ወር ላይ እንደሚጠናቀቅ ማስረጃን የመቀበልና የመመዘን ስልጣን ያለው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ያረጋገጠው ሲሆን ተጠሪ ይሄንን የሚያስተባብል ማስረጃ ባልቀረበበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የበጀት ዓመቱ የሚጠናቀቀው ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ነው ወደሚለው መደምደሚያ መድረሱ ወደዚህ መደምደሚያው ያደረሰውን በቂ ምክንያት ሣይገልጽ በመሆኑ መሠረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆዎችን የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም በተጠሪ እና በአመልካች መካከል የነበረው የስራ ውል ግንኙነት በተወሰነ ጊዜ በመሆኑ የውል ጊዜያቸው ከማለቁ በፊት በስራ ላይ ትብብር እንዲያደርግላቸው የድጋፍ ደብዳቤ ለሚመለከተው ክፍል አመልካች መጻፋ እንደዚሁም የስራ ውሉ ከተቋረጠ በኋላ ሌሎች ሰዎችን ድርጅቱ መቅጠሩ የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው የሚያሰኝ አግባብ የለም ብለናል፡፡ ከስራም የተገለለው በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/1/ መሠረት ነው ብለናል፡፡

በዚሁ መሠረት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ለተጠሪ በስራ ላይ ቢቆይ ኖሮ ይከፈለው የነበረው ደሞዝ ከታህሣስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ይከፈለው ማለቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሣኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 86989 በቀን 26-09-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56140 ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64734

ሰኔ 16 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ካንትሪ ክለብ ዴቨሎፐር የረር ቪው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት - ነገረ ፈጅ ታማኝ የበነ - ቀረበ

**ተጠሪዎች**፡- 1. አቶ በቀለ ለማ - ቀረቡ

2. አቶ ተሾመ አጫሉ - ቀረቡ

3. አቶ ባህሩ አበራ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ሲሆን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበው በአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ በአናጢነት ሙያ ተቀጥረን 1ኛ ከሣሽ በቀን ብር 36 ፣ 2ኛ ከሣሽ ብር 39 እና 3 ከሣሽ ብር 20 እየተከፈለ በመስራት ላይ እያለን ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም ያለአግባብ ከስራ ላይ ያሰናበተን ስለሆነ ወደ ምድብ ስራችን እንድንመለስ ወደ ስራ የማይመልሰን ከሆነ ደግሞ በህጉ መሠረት ሊከፍለን የሚገባውን ክፍያዎች እንዲከፍለን የሚል ነው፡፡ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ መጥሪያ ደርሷቸው በሰጡት መልስ ከሣሾች ከስራ የተሰናበቱት ድርጅቱ ከመዝገብ ቤት የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ አንቀበልም በማለታቸው በህብረት ስምምነቱ መሠረት ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክር በመስማት የተከሣሽ ምስክሮች ከመዝገብ ቤት ወጪ ሆኖ ለከሣሾች የተጻፈውን ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ አንቀበልም ማለታቸውን አረጋግጫለሁ በሌላ በኩል የተከሣሾች ምስክሮች ቃል እርስ በርስ የሚቃረን በመሆኑ ማስተባበል አልቻሉም፤ ከድርጅቱ መዝገብ ቤት ተጽፎ የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ አልቀበልም ማለት ደግሞ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 58/10/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብት የሚችል በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአሁን አመልካች እየሰጠ የነበረው ማስጠንቀቂያ ሣይሆን ቀደሞ በቅጥር ውላቸው



www.chilot.me

ውስጥ የተጠቀሰውን በቀን 5 ካ.ሜ የአሁን ተጠሪዎች ለመስራት የገቡትን ግዴታ ወደ 10 ካ.ሜ. ለማሻሻል የተደረገ በመሆኑ የአሁን አመልካች በራሱ ተነሳሽነት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የስራ ውል ስምምነት መጣሱን እንጂ በጥፋት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ባለመሆኑ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡ የተጠየቀውን ክፍያ በተመለከተም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ፣ የስራ ስንብት እና የካሣ ክፍያ እንዲከፍላቸው አመልካች ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 23-5-03 ዓ.ም በነገረፈጅ በኩል በተጻፈ 4 ገጽ አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ ከድርጅቱ መዝገብ ቤት ወጪ ሆኖ ለሰራተኞች የሚሰጠውን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ አልቀበልም ማለት በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 58/10/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ሆኖ እያለ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይሄንን በማለፍ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ታዘው የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ ፍሬ ሃሣብ ያቀረብኳቸው የሰው ምስክሮች የተባለው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተሰጠ ለተባለበት ያልነበርና እንቢ ያላልን መሆኑን መስክሮልናል ፤ አንፈርምም ያልነው ደግሞ ቀድሞ የተስማማንበት የስራ ውል በቀን 5 ካ.ሜ ሆኖ እያለ አሁን ደግሞ 10 ካ.ሜ እንድንሰራ ያዘዘን በመሆኑ ከአቅማችን በላይ በመሆኑ እምቢ ማለታችን እንጂ በጥፋተኝነት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ባለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረቡትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት በህጋዊ መንገድ ወይስ በህገ-ወጥ መንገድ ነው? በሚል ጭብጥ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27 ስር ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉ ጥፋቶችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ 5 አንቀጽ 27/1/ ስር ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰብቱ የሚችሉትን ጥፋቶች በህብረት ስምምነታቸው መደንገግ እንደሚችሉና በዚሁ መሠረት በድርጅቱ ውስጥ ስራ ላይ ያለው የህብረት ስምምነት አንቀጽ 58/10/ ከመዝገብ ቤት የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ አልቀበልም ማለት እንደ አንድ በቂ ምክንያት የተቀመጠ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የአሁን አመልካችም የሚከራከሩት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ይሄ የህብረት ስምምነት አንቀጽ እንደሆነና የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ያለመቀበል በራሱ ከስራ ለማሰናበት በቂ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የሚከራከሩት የተጻፈው ደብዳቤ ባጠፋነው ጥፋት የተሰጠ ሣይሆን በስራ ውላችን ውስጥ የተስማማንበትን በቀን 5 ካ.ሜ ለመስራት ውል የገባንበትን በመለወጥ በቀን 10 ካ.ሜ እንድንሰራ የታዘዘንበት ነው በማለት የተጠቀሰው የህግ አንቀጽ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምር የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1/ መግቢያን በምናይበት ጊዜ በሌላ አኳኋን በህብረት ስምምነቱ የተካተተ ካልሆነ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉ ነገሮች በዚሁ አንቀጽ ስር የተዘረዘሩት ብቻ እንደሆኑ ያመለክታል፡፡ ለህብረት ስምምነቱ መውጣት መሠረት የሆነው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/ተ/ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ ይችላሉ ተብለው በህብረት ስምምነት የሚደነገጉት ሌሎች ጥፋቶች እንደሆኑ ያመለክታል፡፡



www.chilot.me

ይሄ ማለት ደግሞ በህብረት ስምምነት እንደምክንያት ሊደነገጉ የሚችሉት ነገሮች ጥፋትን መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡፡

አሁን ለተጠሪዎች ከስራ መሰናበት መሠረት የሆነውን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 58 ስንመለከትም የአንቀፁ ርዕስ ከስራ የሚያሰናብቱ ከባድ ጥፋቶች በሚል ከመደንገጉም በላይ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 10 በተያያዘ መልኩ "ድርጅቱ ከመዝገብ ቤት የሚሰጠውን የማስጠንቀቂያ ወረቀት አልቀበልም ካለ" በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሄንን ሁሉ አንድ ላይ ጠቅለል አድርገን ስንመለከት የስራ ስንብቱ የሰራተኛውን ጥፋት መሠረት ያደረገና የሚሰጠውም ማስጠንቀቂያ ጥፋትን መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች እንዲቀበሉ የታዘዙትን ደብዳቤ አንቀበልም ማለታቸው በመጀመሪያ ጉዳዩን ባየው ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ ቢታመንበትም እየተሰጣቸው ያለው ደብዳቤ ከላይ እንደተብራራው የህግ ድንጋጌዎች ጥፋትን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም ከሚለው አኳያ መታየት አለበት፡፡

በዚህ መሠረት ተጠሪዎች እንዲቀበሉ እየታዘዙ ያሉት ቀድሞ በስራ ውላቸው ውስጥ በቀን ተጠሪዎች 5 ካ.ሜ ለመስራት የተስማሙበትን አመልካች በቀን 10 ካ.ሜ እንዲሰሩ የጻፈባቸውን ደብዳቤ ስለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው በመሆኑ የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና በአዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የህግ ስህተት ሲኖር ማረም በመሆኑ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሠረቱ አመልካችም የሚከራከረው የተጻፈው የደብዳቤ ይዘት ከዚህ የተለየ ስለመሆኑ ሣይሆን ደብዳቤውን ያለመቀበላቸው ብቻ ከስራ ለማባረር በቂ ነው ከሚለው ነጥብ አኳያ በመሆኑ አልፈነዋል፡፡

የተጻፈባቸው ደብዳቤ ይዘት ከላይ የተመለከተው በመሆኑ አመልካችም ተጠሪዎች ሲቀጠሩ የነበረው ውል በቀን 5 ካ.ሜ ለመስራት እንደተስማሙ ባላስተባበሉበት በራሱ ተነሣሽነት በውላቸው ውስጥ የተቀመጠውን የቀን የስራ መጠን በመተላለፍ በቀን 10 ካ.ሜ እንዲሰሩ ማለቱና ቀድሞ የነበረውን የስራ ውል የሚያስቀይር ጉዳይ መኖሩን እንኳ ባላስረዳበት በራሱ መጻፍና አንቀበልም ብሏል በማለት ከስራ ማሰናበቱ ከተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ/ቁ. 99340 በቀን 09-05-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎችን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበተው ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ተያያዥ ክፍያዎች ለተጠሪዎች እንዲፈጸሙ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀን 01-06-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ.ከ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 66306

ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች** ፡- እምላሉ ወረዳ ክንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ጠበቃ ሲሳይ ታደሰ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ መሐመድ ሰይድ አልቀረቡም

2. ሲሳይ ተስፋዬ ቀረቡ

3. መላኩ እውነቱ ቀረቡ

4. አበባ ጉዲሳ ቀረቡ

5. ስብአት አለማየሁ ቀረቡ

6. በሐይሉ ደምሴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ አመልካች በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች ነበሩ፡፡ ክሱም በተከሣሽ ድርጅት ተቀጥረን እየሠራን እያለ ተከሣሽ በራሱ አነሳሽነት የሥራ ውላችንን ያቋረጠብን ስለሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሳሾች የተቀጠሩት ተከሣሽ ተስፋ የነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ከተባለው ጋር የሱቆች ህንፃ ግንባታ ለማድረግ በገባነው ውል መሠረት የሱቆች ህንፃ ለመገንባት ቢሆንም ከማህበሩ ጋር የተደረገው የሱቆች ህንፃ ግንባታ ውል በመቋረጡና ከሳሾችም የተቀጠሩት ለዚሁ ኘሮጀክት ለተወሠነ ጊዜ በመሆኑ የሚገባቸውን ክፍያ ማለትም የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እና የስንብት ክፍያ እንዲሁም የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶአቸው የሥራ ውሉ ተቋርጧል ብሏል፡፡



www.chilot.me

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም ተከሣሽ ከከሣሾች ጋር የነበረውን የቅጥር ውል ያቋረጠው ተስፋ ነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ጋር የነበረው የሱቆች ግንባታ ውል በመቋረጡ ነው ቢልም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ላይ የተመለከተውን ግዴታ አልተወጣም ፡፡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው የፕሮጀክቱ ሥራ (የሱቆች ሕንፃ ግንባታ) በመጠናቀቁ አይደለም፡፡ ተከሣሽ ከማህበሩ ጋር ያደረገው የሱቆች ህንፃ ግንባታ ውሉ መቋረጡ ከ3ኛ ወገኖች (ከሳሾች) ጋር የነበረውን ውል እንዲቋረጥ አያደርገውም በማለት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህገወጥ መንገድ ነው ሲል ተከሣሽ ለከሳሾች ቀደም ብሎ ከከፈላቸው ክፊያዎች በተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና ካሣ የ6 ወር ደመወዘ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የሥር ተከሣሽም በዚህ በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች ካከራከረ በኂላ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋነኛነት አመልካች የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ተጠሪዎች ሙያቸው አናጢነትና ግንበኝነት ሲሆን የተቀጠሩትም ተስፋ የነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር አባላት ሱቆችን ለመገንባት አመልካች ከማህበሩ ጋር በገባው ውል መነሻ ሲሆን ይኸው የግንባታ ሥራ የማህበሩ አሠሪ እንዲቋረጠ በማዘዙ ተቋርጧል፡፡ የተጠሪዎችም የሥራ ውል በዚሁ ምክንያት ተቋርጦ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/2/ሀ/ ሠራተኞቹ በተሠማሩበት ሥራ በሙሉና በቀጥታ የሚያስቆም ሁኔታ የተከሰተ አንደሆነ አስሪው ለማሠናበት የሚችል መሆኑ ተደንግጐ እያለ ይኸንኑ ድንጋጌ በማለፍ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው ሲሉ መወሰናቸው ያለአግባብ ነው የሚል ሲሆን የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል መነሻም አመልካቾች ለተጠሪዎች እንዲከፍል የተባሉትን ክፍያዎች ይህ ችሎት ውድቅ እንዲያደርግ ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎች ለአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰጡት መልስ አመልካች በተለያዩ ክፍሎች ሠራተኞችን እየመደበ የሚያሠራ እንጂ የግንባታ ሠራዎችን ከአሠሪዎች እየተቀበለ የተቀበለውን ህንፃ ግንባታው እስከሚጠናቀቅ ብቻ ሠራተኞችን ውል በማስገባት የሚይሠራ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ሙያችን አናጢነት ሲሆን አመልካች የቀጠረን ከተስፋ ነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር የተቀበለው የህንፃ ግንባታ ሥራ እስከሚጠናቀቅ በሚል ብቻ አይደለም ስለሆነም በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 4/1/ መሠረት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሠሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመሥራት በሚያደርገው ስምምነት የሥራ ውል ይመሠረታል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 10 ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ በሚል መዋዋል የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች የሚዘረዝር ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች በቀር የሚመሠረቱ ውሎች በአዋጁ አንቀጽ 9 በተጠቀሰው መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረጉ የሥራ ውሎች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

ወደተያዘው ጉዳዩ ስንመለስ በሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ተጠሪዎችን የቀጠራቸው አመልካች ተስፋ የነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ለተባለው የሱቆች ህንፃ ግንባታ ሲሆን ሥራው ሲጠናቀቀም ውሉ የሚያበቃ ነበር፡፡ በመሆኑም ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል በአዋጁ አንቀጽ 10 ሥር ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ ተብሎ የሚደረጉ ውሎች ውስጥ የሚሸፈን ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሱቆች ህንፃ ለመገንባት ከተስፋ ነጋዴዎች ማህበር ጋር የገባው ውል የግንባታ ውሉ ፕሮጀክት ከመጠናቀቁ በፊት ተቋርጧል፡፡ ይህ አመልካች ከተስፋ የጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ጋር የገባው የሱቆች ህንፃ ግንባታ ውል መቋረጡ የሥራ ውሉ በሌላ ምክንያት ድርጅቱ ለዘለቀታው ሲዘጋ በህግ የሚቋረጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24/4/ የተደነገገውን የሚያሟላ ነው፡፡

ይህ ሆኖ ሣለ የሥር ፍ/ቤቶች በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል የተቋረጠው በአመልካችና በተስፉ ነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ተደርጐ በነበረው ውል መሠረት የተጀመረው የፕሮጀክት ሥራ ሳይጠናቀቅ ነው፡፡ በማህበሩና በአመልካች መካከል የነበረው ውል መቋረጥ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አይሆንም በማለት ውሉ የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው ሲሉ የወሰኑት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/67044 በቀን 20/11/2002 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጠር 96791 በቀን 22/6/2003 የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለተጠሪዎች የስንብት ክፍያና የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ በመክፈል እንደሁም የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት በመስጠት ተጠሪዎችን ያሰናበታቸው በአግባቡ ነው፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59906

የካቲት 09 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት - ነገረ ፈጅ አቶ ፈለቀ እንግዳሸት ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ኃ/ማርያም ሻረው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር ክርክር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውም የአሁን ተጠሪ የሥራ ውሉ ተቋርጦ እንዲሰናበት የተደረገው ከሕግ ውጭ ስለሆነ አሠሪው ድርጅት ወደ ሥራው እንዲመልሰው ይገባል፣ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅሞች ሊከፈሉት ይገባል በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ መሠረት የቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሹ ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ሆኖ ክሱ አሠሪው ድርጅት የሆነው የአሁኑ አመልካች ከሕግ ውጭ እኔን በወንጀል በመጠርጠር አግዶኝ እንዳልሠራ ስላደረገ ወደ ሥራ እንዲመልስ ይወስንልኝ በሚል የቀረበ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው ከሥራው እንዲታገድ የተደረገው የመንግሥት ቼክ በሀሰት ፈርሞ ከባንክ ገንዘብ ስላወጣ ነው፣ ከሥራ የሚያሰናብተው ከፍተኛ የዲሲፕሊን ጥፋት ስለፈፀመ የተወሰደው እርምጃ ትክክል ነው የሚል ክርክር ቢያቀርብም የወረዳው ፍ/ቤት ሠራተኛው በተጠረጠረበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በሕግ የተሰጠ ውሣኔ የለም፣ በመጠርጠሩ ብቻ ከሥራ ታግዷል የሚለው በሕጉ ተቀባይነት የለውም በማለት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛውን ወደ ሥራው እንዲመልሰው፣ ደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅሞች ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊከፍለው ይገባል በሚል ወስኗል፡፡



www.chilot.me

የአሁኑ አመልካች በዚህ የወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በየደረጃው ላሉ የኦሮሚያ ፍ/ቤቶች ቢያቀርብም ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች በ28/12/2002 በነገረ ፈጁ አማካኝነት በተጻፈ ማመልከቻ ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመባሉ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪው በ23/03/2003 የተጻፈ መልስ ሲያቅርብ የአመልካች ነገረ ፈጅም የመልስ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩም ተመርምሯል፡፡

አሠሪው ድርጅት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው የድርጅቱን ቼክ በሀሰት በመፈረም ከባንክ ገንዘብ አውጥቶ በመውሰድ ከፍተኛ ጥፋት በመፈፀሙ ነው በማለት አጥብቆ የሚከራከር ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ከጥርጣሬ በቀር ወንጀሉን ስለመፈፀሜ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላልቀረበ የአመልካች ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም ባይ ነው፡፡

በመጀመሪያ ከሥራ ዕገዳ ሆኖ በመጨረሻ ከሥራ ስንብት ሆኗል የተባለው የአሁኑ አመልካች እርምጃ ከሕግ ውጭ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተ ወረዳው ፍ/ቤት ሠራተኛው በወንጀል ተጠርጥሯል ከመባል በቀር በሕግ ጥፋተኛ ስለመሆኑ ተወስኖበት የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ማስረጃው የፍርድ ቤት የወንጀል ውሣኔ ብቻ እንደሆነ አድርጐ በመውሰድ አሠሪው ሠራተኛው ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በማስረጃ አላስረዳም ወደሚል ድምዳሜ ያመራ ሆኖ ይገኝ እንጂ አሠሪው ድርጅት ሠራተኛው ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በፍርድ ቤት የተሰጠ የወንጀል ውሣኔ በማስረጃነት ማቅረብ ሣያስፈልግ የሰው ወይም ሌላ የጽሑፍ ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይችላል፡፡ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ጉዳዩ ተጣርቶ ከሥራ የሚያስወጣው ጥፋት ፈጽሟል የተባለበት የዲሲፕሊን ውሣኔ መኖሩ ከታወቀ በጽሑፍ ማስረጃነት የማይቀርብበት ምክንያት የለም፡፡ በወንጀል ምርመራ የተጣራበት ማስረጃም ካለ በማስረጃነት ቀርቦ ሊታይና ሊመዘን የሚችል ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች እነዚህን ሁሉ ማስረጃዎች እንዲያቀርብ አድርጐ አጣርቶ መወሰን ሲገባው ሠራተኛው በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተባለበት የፍርድ ቤት ውሣኔ በማስረጃነት ካልቀረበ ከሥራ የሚያሰናብተው ጥፋት ስለመፈፀሙ ማስረዳት እንደማይችል አድርጐ የወሰነው ትክክል አይደለም፡፡

ሌሎች ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተደርጐ ሣይጣራ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>**ውሣኔ**</u>

1. የገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት በፋይል ቁጥር 04168 በ23/09/2002 የሰጠው ብይን፣ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09309 በ30/10/2002 የሰጠው ትዕዛዝ እና



www.chilot.me

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 109450 በ13/12/2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረው የገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በፍርድ ላይ በተዘረዘረው መሠረት አሉኝ የሚላቸውን ሌሎች ማስረጃዎች እንዲያቀርብ አድርጐ በተገቢው መንገድ በማጣራት ከሥራ እገዳው ወይም ማሰናበቱ በሕጉ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም በሚለው ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ተመልሷል፡፡

2. የገደብ አሰሳ ወረዳ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መሠረት እንዲፈጽም ታዟል፡፡
3. በዚህ መዝገበ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተጠሰው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 18495

መጋቢት 18/99 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች**፡- የኢት/መንገዶች ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ አስመላሽ ገሠሠ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አሚናት ገበየሁ - በሌለችበት የሚታይ

**ፍ ር ድ**

አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 6083 ኀዳር 7/1997 በዋለው ችሎት የኮምቦልቻ ወረዳ ፍ/ቤት በቁ. 633/96 ጥቅምት 22/97 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ክሱን ያቀረቡት ሟች ሀሰን ዓሊ የተባለው ልጄ በተከሣሽ መ/ቤት ከ1978 ዓ.ም. ጀምሮ በወር ብር 285 እየተከፈለው በሠራተኛነት ሲያገለግል ቆይቶ በአደረበት ሕመም በ20/8/96 ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ የሟች ወራሽ በመሆኔ የልጄን የ18 ዓመት የአገልግሎት ካሣና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ይክፈሉኝ የሚል ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39/2/3/ እና አንቀጽ 110/2/ሐ/፣ 3/ሐ/ መሠረት የሠራተኛው የዓመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ ተከሣሽ ለከሳሽ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ የዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቶታል፡፡

አቤቱታው የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለበት ምክንያትም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 መሠረት የአገልግሎት ካሣ እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው፡፡

ከሥር ክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው ለሥራ ውሉ መቋረጥ ምክንያት የሆነው የአመልካች ሠራተኛ የነበረው ሟች በአደረበት ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ከአሠሪው የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሚኖረው በአዋጁ አንቀጽ 39/1/ ሥር ከ/ሀ/ እስከ/ረ/ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ነው፡፡

በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት ሠራተኛው በሞት ምክንያት የሥራ ውሉ ቢቋረጥ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚጠየቅበት አይደለም፡፡ ሕጉ መብት አይሰጥም፡፡

የሥር ፍ/ቤቱ ክፍያው ይፈፀም ያለው በአዋጁ አንቀጽ 39/1/ መሠረት በቅድሚያ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ስለመኖር አለመኖሩ ሳያረጋግጥ በአንቀጽ /2/ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያው በአንቀጽ 110/2/ ለተመለከቱት ጥገኞች ይከፈላቸዋል የሚለውን በማየት ብቻ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 39/2/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ግን በአንቀጽ 39/1/ መሠረት የስንብት ክፍያ የማግኘት መብት መኖሩ የተረጋገጠ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቱ የሥራ ስንብት ክፍያው እንዲከፈል የወሰነው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39/1/ እና /2/ ድንጋጌን በአግባቡ ባለማገናዘብ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የኮምቦልቻ ወረዳ ፍ/ቤት በቁ. 633/96 ጥቅምት 22/97 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና ይህንኑ በማጽናት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 6083 ኀዳር 7/97 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የተሻረ መሆኑንም እንዲያውቁት የዚህ ውሣኔ ቅጂ ይተላለፍላቸው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 20869

ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ከማል በድሪ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ጌታቸው ምህረቴ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡-** አቶ ፋንታሁን አባተ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ - ቀረቡ (ነ/ፈጅ እስክንድር)

**ፍ ር ድ**

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሣኔ የሰጠው የፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በስራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ የተከፈለው የሁለት ወራት ቦነስ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የቦነስ ክፍያ ዋና አላማው ሠራተኛ በስራ ላይ በነበረበት ወቅት የሠራው ስራ ለአሠሪው ጥሩ ውጤት አስገኝቶ ከሆነ በስራ ላይ ያለው ሠራተኛ ለወደፊት ውጤታማ እንዲሆን ለማበረታታት እንጂ ስራውን የለቀቀ ሠራተኛ እንደመብት የሚጠይቀው አይደለም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም የቀረበውን ይግባኝ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች በስራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ የተከፈለውን የቦነስ ክፍያ ለአመልካቹ ስራ በመልቀቃቸው ሊከፈላቸው አይገባም የተባለበትን ህጋዊ ምክንያት በመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ተጠሪ ተጠርቶ ቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው አመልካች ስራ ላይ በነበሩበት ወራት ለተሰራ ስራ የተከፈለው ቦነስ አመልካች ከሥራ ከተሰናበቱ በኋላ ሊከፈላቸው የሚገባ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች የተጠሪ መ/ቤት ሠራተኛ የነበሩና በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን ከለቀቁ በኋላ አመልካቹ በሥራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ለተሰራ ሥራ የቦነስ ክፍያ ለተጠሪ መ/ቤት ሠራተኞቹ መክፈሉ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ ፍ/ቤቶቹ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት የአመልካች የሥራ ውል በተቋረጠበት ጊዜ የተፈቀደ የቦነስ መብት ካለመኖሩም በላይ የቦነስ አላማው ሠራተኛው በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት የሠራው ሥራ ለአሠሪው ጥሩ ውጤት አስገኝቶ ከሆነ ለወደፊትም



www.chilot.me

በተመሳሳይ መልኩ በርትቶ ውጤታማ እንዲሆን ለማበረታታት እንጂ ስራውን የለቀቀ ሠራተኛ እንደመብት የሚጠይቀው አይደለም በማለት ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው ቦነስ የሚከፈለው በስራ ላይ ያለ ሰራተኛ ወደፊት በርትቶ እንዲሰራ ለማበረታታት ብቻ ሳይሆን ሠራተኛው በስራ ላይ በነበረበት ወቅት የሰራው ሥራ ለአሠሪው ትርፋማ ውጤት በማስገኘቱ የትርፉ ተጠቃሚ እንዲሆንም ጭምር የሚሰጥ የጥቅም ክፍያ ነው፡፡ በመሆኑም የቦነስ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ለቦነስ ክፍያ ምክንያት ለሆነው ትርፍ ሠራተኛው አስተዋጽኦ ማድረግ አለማድረጉ ሊታይ ይገባል፡፡ በእርግጥ የሠራተኛው ሥራ ትርፋማ መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው የበጀት አመቱ ሂሳብ ከተሠራ በኋላ በመሆኑ የቦነስ መብት የሚፈቀደው ይኸው ውጤት ከታወቀ በኋላ ነው፡፡ የሂሳቡ ውጤት የአሠሪውን ትርፋማነት ካረጋገጠ ግን ለትርፋማነቱ አስተዋጽኦ ያደረገው ሠራተኛ የቦነስ ጥቅም ተካፋይ ሊሆን ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቹ በስራ ላይ በነበሩበት ጊዜ የተሰራው ሥራ ለመ/ቤቱ ትርፋማነት ምክንያት ሆኗል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የቦነሰ መብት የተፈቀደው አመልካቹ ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ቢሆንም የቦነስ መብቱ የተፈቀደው የአመልካች በስራ ላይ በነበሩበት ወቅት ለተሠራ ሥራ በመሆኑ አመልካች የጥቅሙ ተካፋይ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ቦነስ በስራ ላይ ያለን ሠራተኛ ለማበረታታት ብቻ የሚሰጥ ነው በማለት የአመልካች የቦነስ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ሥህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16632 በ29/6/97 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37603 በ25/09/97 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በስራ ላይ ለነበሩበት ከሰኔ 24 ቀን 1995 እስከ ሰኔ 23/1996 ላለው ጊዜ ለሌሎች ሠራተኞች የተሰጠው ቦነስ እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

# ንብረት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48217

ጥቅምት 03 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች -** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፣** ወ/ሮ አባዲት ለምለም የቀረበ የለም

**ተጠሪዎች፣** 1. የዛለአንበሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ወኪል አለምፀሐይ ግርማይ ቀረቡ

2. አቶ ብርሃን ዘረፈ በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ቤትና ቦታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአግባቡ በዛላንበሳ አስተዳደር የታደልኩትን በራሴ ተጨማሪ ገንዘብ ደግሞ የሰራሁትን በስሜ በርዕስተ መዝገብ የተመዘገበውን ቤትና ቦታ አስተዳደሩ ነጥቆ ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የሰጣቸው መሆኑን ገልፀው ገንዘቡና ቤቱ እንዲመለስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበውም አመልካች ቦታና ገንዘብ የተሰጣቸው በጦርነት ምክንያት ቤት ስለወደመባቸው መንግስት ምትክ ቦታና ገንዘብ እንዲሰጥ በአስተላለፈው አስተዳደራዊ ውሣኔ በመሆኑና ይህም ውሣኔ ፖለቲካዊ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ እንደማይችል በመግለፅ አመልካች ክስ ለመመስርት የሚያስችላቸው ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ያሳያል በማለት ያቀረበው ክርክር ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም የአመልካች ጥያቄ በአስተዳደሩ ተጣርቶ ቤትና ገንዘብ ከመንግስት ሊያገኙ የማይችሉበት ምክንያት በመገኘቱ ውድቅ የሆነ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪም ቤትና ገንዘቡን የመንግስት አስተዳደር አካላት በሰጡት ውሣኔ መሠረት የተሰጣቸውና የተረከቡት በመሆኑ ሊከሰሱ እንደማይገባ ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤትና ገንዘብ ለአመልካች ሊመለስላቸው እንደሚገባ ገልፆ ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ጉዳዩ ተመርምሮ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚያልቅ እንጂ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ

ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የአመልካች ጥያቄ ቤትና ገንዘብ ያላግባብ ተነጠቅሁ የሚል ሁኖ እያለ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና በሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ አስተዳደራዊ ስለሆነ በፍርድ ቤት መዳኘት የለበትም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪዎች መጥሪያ ተልኮላቸውና መድረሱም ተረጋግጦ ሊቀርቡ ስላልቻሉ ጉዳዩ ተጠሪዎች በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በበታች ፍርድ ቤቶች ግራቀኙ ያደረጉትን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በዛላንበሳ አካባቢ በጦርነት ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለነበሩት ዜጎች ማቋቋሚያ የሚሆን መሬትና የብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሺህ/ ቤት መስሪያ እርዳታ ለመስጠት የተለያዩ አካላት ተወካዮች ያሉበት ኮሚቴ ማቋቋሙን መንግስት ባወጣው የችግረኛ ተረጂዎች መለያ መስፈርት መሠረት በጦርነቱ ተፈናቅለው በፕላስቲክ ዳስ የሚኖሩ 969 ተፈናቃዮች በዕዳ መሬት ተሰጥቷቸው ገንዘቡም በየደረጃው በሶስት ጊዜ እንዲሰጥ ተወስኖ ብር 7,500.00 በማቋቋሚያ ኮሚሽን መስጠቱን አመልካችም በጦርነቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በፕላስቲክ ዳስ የሚኖሩና ለተረጂነት የሚያሟሉ መሆኑ ተረጋግጦ መሬት ተሰጥቷቸው በስማቸው በማዘጋጃ ቤት ተመዝግቦ የመሬት ኪራይ ካርታ የፅዳት የቤት ስራ ፈቃድ የቴክኒክ አገልግሎት የችካል የይዞታ ማረጋገጫ ክፍያዎችን በሙሉ ከፍለው ከመንግስት በእርዳታ የተሰጣቸውን ብር 7,500.00 እና ከራሳቸው ብር 7000.00 ጨምረው በብር 14,500.00 የቆርቆሮ ክዳን እስኪቀረው ቤቱን ሰርተው ከጨረሱ በኃላ ኤርትራዊ ነሽ በሚል ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ነጥቆ ለሁለተኛ ተጠሪ እንዲሰጥ ማድረጉን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የተቻለው አመልካች የሚከራከሩት በመንግስት በተሰጣቸው ቦታና ገንዘብ የራሳቸውን ገንዘብ ጨምረው የገነቡት ቤትና ቦታ ያላግባብ የተነጠቁ በመሆኑ በፍርድ ኃይል እንዲመለስላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን ነው፡፡

በመሠረቱ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79/ለ/ ተደንግጓል፡፡ የሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ ፍ/ቤቶች በማናቸውም ጉዳይ ገደብ የለሽ ስልጣን የሌላቸው መሆኑም ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሕገመንግስቱ አንቀጽ 79/ለ/ እና 37 አንድ ላይ ሲታዩ ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን የሚኖራቸው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው /Justiciable matter/ ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 “ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት



www.chilot.me

ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡" በሚል ከተደነገገው "…. ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል….." የሚለው እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 4 በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በህግ ካልተገለፀ ክሱን ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ብቻ ነው በሚል መደንገጉ በፍርድ ሊወሰን በሚችለው ጉዳይ ፍ/ቤቶች ብቸኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ማየት የሚችሉት ጉዳዩ በፍርድ የሚያልቅ ሲሆንና በሌላ አኳኋን እንዲታይ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካች ጥያቄ ቤትና ቦታዬን ያላግባብ ተነጠቅሁ የሚልና በፍርድ ኃይል የንብረት መብቻው እንዲከበርላቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ጉዳይ በፍርድ እንዳያልቅ የሚከለክል ሕግ የሌለ ሲሆን ጉዳዩ አስተዳደራዊ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ ጉዳዩን እንዲዳኝ በሕግ ተለይቶ ስልጣን የተሰጠው አካልም የለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው /Justiciable matter/ ጉዳይ እንጂ በአስተዳደር የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በአስተዳደር የሚያልቅ ነው በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መሻሩና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ውሣኔ ማጽደቁ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 23281 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 25845 ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም በአብላጭ ድምጽ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ጥያቄ ያላግባብ ቤትና ቦታዬን ተነጠቅሁኝ የሚል በመሆኑ በፍርድ ሊወሰን የሚችል እንጂ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚያልቅ አይደለም ብለናል፡፡
3. ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚችል በመሆኑ የስር የዞን ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ የግራቀኙን ማስረጃዎችንና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ሥሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52496

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ ከድር ኃሌጅንሶ /አስራ ሁለት ሰዎች/- ጠበቃ አማን ቡልቡላ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመሬት ይዞታ ካሣ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሣሥ 13 ቀን 1998 ዓ.ም በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ በክሱ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው 6666 ካሬ ሜትር የሆነው የእርሻ መሬት ይዞታ የነበራቸው መሆኑን፣ አመልካች በዚሁ የእርሻ መሬት ላይ ጥቅምት 05 ቀን 1997 ዓ.ም ካምፕ ያሰፈረበት መሆኑን፣ እያንዳንዳቸው በመሬቱ ላይ በሄክታር ሰላሣ ኩንታል ስንዴ የሚያገኙ መሆኑን፣ በወቅቱ የአንድ ኩንታል ስንዴ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ መሆኑን ገልፀው የአምስት ዓመት ምርት በጠቅላላው ብር 240,000.00 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ እንደሚያወጣ ጠቅሰው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 7 እና 8 መሠረት ካሣውን እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ተጠሪዎች የመሬቱን ባለይዞታ መሆናቸውን የሚያሣይ ማስረጃ ስላላቀረቡ ለመክሰስ የማይችሉ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ካምፑ የሰፈረበትን መሬት የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት የተረከበ መሆኑን፣ ካምፑ ከሰፈረሰበት መሬት ውስጥም 20794.5 ካ.ሜትር ላይ ብቻ መኖሩን የሚመለከተው አካል አረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 80/89 እና 401/96 መሠረት ተገቢው ካሣ መከፈሉን፣ በቀሪው 79,205.5 ካ.ሜትር ላይ ግን መሬቱ ባዶ ስለሆነ የወረዳ አስተዳደርም ሆነ የቀበሌ አስተዳደር ያነሱት የካሣ ጥያቄ ሣይኖር መሬቱን የተረከቡ መሆኑንና በዚሁ ይዞታ ላይ የቀረበው ክስ በተጨባጭ ማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ምስክሮችን ከሰማ እና መሬቱ እህል የሚያበቅል መሆን ያለመሆኑን ከሚመለከተው አካል ማጣራት ከአደረገ በኋላ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ለካሣው በአዋጅ ቁጥር 401/96 መሠረት ኃላፊነት አለበት የሚል ምክንያት በመስጠት ለክሱ መሠረት የሆነውን የገንዘብ መጠን አመልካች እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ



www.chilot.me

የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ የካቲት 03 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች በአከራካሪው የመሬት ይዞታ መብት ያላቸው ስለመሆኑ ሣያረጋግጡ እና መሬቱ በተወሰደበት ሰዓትም በይዞታው ላይ ምንም ሰብል በሌለበት ሁኔታ የአምስት ዓመት ካሣ ይከፈላቸው ተብሎ የተወሰነው ከሕጉ ውጭ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪዎች በይዞታው ላይ መብት ወይም ጥቅም የነበራቸው ስለመሆኑ የተረጋገጠ መሆን አለመሆኑ እና ከአዋጅ ቁጥር 401/96 አኳያ ካሣ ይከፈል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በዚህም መሠረት ተጠሪዎች በወኪሎቻቸው አማካኝነት ሐምሌ 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የጽሑፍ መልስ የሰጡ ሲሆን የአመልካች ነገረፈጅ በበኩላቸው ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ክሱን የመሠረቱት የእርሻ መሬት ይዞታችን በአመልካች ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ተወስዶ ካሣ ስላልተከፈለን ሊከፈለን ይገባል በሚል መሆኑን፣ አመልካችም ተጠሪዎች ክስ ለመመሥረት የሚያስችላቸው መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና ለክሱም በአጠቃላይ ሕጋዊ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመጥቀስ የተከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች ተጠሪዎች ክስ ለመመሥረት መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በሚል ያቀረበው ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉበትን አግባብ ይህ ችሎት ለመመርመር የሚችል መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች በይዞታው ላይ መብት የነበራቸው መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጣቸውን መሠረት በማድረግ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አመልካች የማስተባበያ ማስረጃም ከሚመለከተው አካል አላቀረበም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ይዞታውን ተጠሪዎች ቀበሌ አስተዳደሩ በፃፈው አንድ ደብዳቤ እና የግብር ካርኒዎች ብቻ ሊያረጋግጡ አይገባም የሚል እንድምታ ያለውን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቀበሌ አስተዳደሩ የፃፈው ደብዳቤና የግብር ካርኒ ይዞታን ለማረጋገጥ አግባብነት የሌለው ማስረጃ ነው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሠረት የለም፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤት ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግሥት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ ፍሬ ጉዳዩን ለማጣራት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር አልፈነዋል፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ሌላውና ዋናው ነጥብ ተጠሪዎች ካሣ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 401/96 መንፈስና ይዘት ውጪ ነው የሚለው ሲሆን ይህ ችሎት ይህንኑ

የክርክር ነጥብ ከሕጉ ጋር አዛምዶ ተመልክቷል፡፡ አመልካች የተጠሪዎች የእርሻ መሬት ይዞታ ወሰደ ተብሎ የተረጋገጠው ጥቅምት 05 ቀን 1997 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪዎች ክሱን የመሠረቱት ታህሣሥ 13 ቀን 1998 ዓ.ም ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች ወሰደ የተባለው መሬት በወቅቱ እህል ማብቀል የሚችል መሆን ያለመሆኑ በሚመለከተው አካል ከመረጋገጡ ውጪ በአመልካች ሲወሰድ የስንዴ አዝመራ የነበረበት አለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በባዶ የእርሻ ይዞታ መሬት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት የተባለው መሬቱ ወደፊት ሊዘራበትና ሊመረትበት የሚችል ነው በሚል ምክንያት መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ እና ከአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ እንግዲህ ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ አግባብነት ያለው ሕግ የትኛው ነው? በዚሁ ሕግ መሠረትስ አመልካች ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት? ወይንስ የለበትም? የሚለው ጥያቄ መታየት ያለበት ነው፡፡

አመልካች የተጠሪዎችን የእርሻ ይዞታ መሬት መወሰዱ በተረጋገጠበት ጥቅምት 05 ቀን 1997 ዓ.ም ስራ ላይ የነበረውና ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 401/96 ነው፡፡ ተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት ታህሣሥ 13 ቀን 1997 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ወቅት ስራ ላይ ያለው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ ስለሚለቀቅበትና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/97 መሠረት ነው፡፡ ተጠሪዎች ከጉዳዩ አግባብነት አለው በማለት የሚከራከሩትም ክስ በመሠረቱበት ወቅት ተፈፃሚ የሆነውን ይህንኑ ሕግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አዋጅ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የተደረገው ከሐምሌ 08 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን በመሸጋገሪያ ድንጋጌም አዋጅ ቁጥር 401/96 ተፈፃሚነት በነበረበት ወቅት የተወሰዱ የመሬት ይዞታ ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር 455/97 መሠረት የሚታዩበት አግባብ ስለመኖሩ አላስቀመጠም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ መታየት ያለበት መሬቱ ተወሰደ በተባለበት ወቅት ስራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 401/96 መሠረት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9/1/ መሠረት መሬት የሚወሰድበት ባለይዞታ በገንዘቡ፣በጉልበቱ፣ ወይም በፈጠራ ችሎታው ላፈራውና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እንዲሁም ላደረገው ቋሚ ማሻሻል ካሣ ይከፈለዋል በሚል የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ከባለይዘታው በሚወሰደው መሬት ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል ካሣ ንብረቱን ለመተካት ከሚያስፈልገው ወጪ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል ሲል ደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የምንገነዘበው አቢይ ነጥብ የካሣ መሠረትና መጠን የሚወሰነው በይዞታው ላይ ንብረት ያለ መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም መሬቱ ሲወሰድ ንብረት ያልነበረ ከሆነ ካሣ ሊከፈል ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚያገኘው በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የመሬት ይዞታው በቋሚነት የሚወሰድበት ሰው በመሬቱ ላይ ሰብል ወይም ተክል ቢኖርም ባይኖርም ተመሣሣይ መሬት ያለው ሰው የሚያገኘው አማካይ ገቢ በአዋጁ አንቀጽ 9 ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ የሚከፈለው ስለመሆኑ በመርህ ደረጃ በንዑስ ቁጥር አንድ ስር ያስቀመጠ ሲሆን ዝርዝሩም በደንብ እንደሚወሰን ያሣያል፡፡ የተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌም የመሬቱ ይዞታው ለተወሰነ ጊዜ ለሚወሰድበት ሰው ወይም ለወል መሬት ባለይዞታዎች በመሬቱ ላይ ሰብል ወይም ተክል ቢኖርም ባይኖርም መሬቱ ባይለቀቅ ኖሮ ከመሬቱ ሊገኝ ይችል የነበረው ገቢ መሬቱ እስከሚመለስ ድረስ ላለው ጊዜ ታስቦ በአዋጁ አንቀጽ ዘጠኝ መሠረት ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ እንደሚከፈል፣ በአንቀጽ አስር ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ከሚከፈለው ክፍያ መብለጥ እንደሌለበትና ዝርዝሩም በደንብ እንደሚወሰን ደንግጓል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ አስር ንዑስ ቁጥር አንድ እና ሁለት የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት የመሬት ባለይዞታው ለተወሰደበት ሰው ተተኪ መሬት ያልተገኘለት መሆኑን አግባብ ያለው የመስተዳድር አካል ሲያረጋግጥ ብቻ እንደሆነ ተጠቃሹ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሦስት ስር



www.chilot.me

በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ለተጠሪዎች ካሣ እንዲከፈል የስር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት ደንቡን መሠረት በማድረግ ባይሆንም ይዞታው ምን አይነት ሰብል እና ምን ያህል መጠን ሊያስምርት እንደሚችል ከሚመለከተው የክፍሉ አካል የስር ፍርድ ቤት ማረጋገጫ እንዲቀርብለት አድርጎ ባጣራው መሠረት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለተወሰደባቸው መሬት ይዞታ ተተኪ መሬት የተገኘላቸው ወይም የተሰጣቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፣ አመልካችም በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የለም፣ በስር ፍርድ ቤትም የሚመለከተው አካል ለተጠሪዎች ተተኪ መሬት የተገኘላቸው ስለመሆኑ የገለፀው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በአዋጁ አንቀጽ  አስር ንዑስ አንቀጽ አንድ፣ ሁለት እና ሶስት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መሰረት የመፈናቀያ ካሣ የማያገኙበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመጨረሻ የተወሰነው የመፈናቂያ ካሣ መጠን ሲታይም የተጋነነ ወይም ከክፍሉ አካል ከቀረበው ማረጋገጫ ይዘት ውጪ ነው ለማለት የሚያስችልም አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ባለይዞታ ስለመሆናቸው ተረጋግጧል እስከተባለ ድረስ በቦታው ላይ ሰብል ሣይኖር ቦታውን አመልካች መውሰዱ የመፈናቂያ ካሣ ለተጠሪዎች እንዲከፈል የሚያደርግ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 401/96 አንቀጽ 9 እና 10 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/7/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ሆኖ ስለአገኘን በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

በዚህ ችሎት የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55081

ጥቅምት 18 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ራሔራ ሥነፀሐይ - ጠበቃ አስረስ ባያው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ መስፍን ታምራት - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የፍርድ ባለመብት የሆኑበትን እዳ ለማስከፈያ እንዲሆን የፍርድ ባለእዳው የተጠሪው ንብረት የሆነ ቤት እንዲሸጥላቸው አመልካች አመልክተዋል፡፡ ቤቱ በፍርድ ባለእዳው ልጅ ተማሪ ማራማዊት መስፍን ስም ስሙ ተዛውሮና ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ ቤቱን የእዳ መክፈያ እንዳይሆን ለማሸሽ ያደረጉት ድርጊት በመሆኑ በልጃቸው ተማሪ ማራማዊት መስፍን ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ንብረት ተሸጦ ፍርዱ እንዲፈፀምልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዲውል የጠየቁት ቤት በፍርድ ባለ እዳው ስም ሳይሆን በተማሪ ማሪማዊት መስፍን ስም የሚገኝ በመሆኑ አፈፃፀሙን በቤቱ ላይ ማስቀጠል አይቻልም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች የፍርድ ባለእዳ የሆነው ተጠሪ ቤቱን ለእዳ መክፈያ እንዳይሆን ለማሸሽ በማሰብ ምንም አይነት ሐብት ለሌላት አካለ መጠን ላልደረሰች ልጁ የቤቱን ስመ ንብረት በማዛወር የፈፀመው ተግባር መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የማራማዊት መስፍን ነው፡፡ ለዚህም ቤቱ የማራማዊት መስፍን መሆኑን የሚያረጋግጥ ውልና የቤቱ ክፍያ የተከፈለባቸው ወርሀዊ ደረሰኞች ስላሉ ቤቱ የፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡



www.chilot.me

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ የሆነበትን ገንዘብ ለመክፈል ጥረት በሚደረግበት ጊዜ ቤቱ የተጠሪ ልጅ በሆነችው ህፃን ማራማዊት መስፍን ስም የተዛወረ መሆኑ የስር ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተረጋግጧል፡፡ የቤቱ ባለቤት ናት ቤቱም በስሟ ተመዝግቧል የምትባለው ማራማዊት መስፍን ህፃን መሆኗን የስር ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተረጋግጧል፡፡

አንድ ሰው የንብረት ባለቤት የሚሆነው በጉልበቱ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንብረቱን ያፈራው ሲሆን እንደሆነ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ በተጠሪና በተጠሪ ባለቤት በወ/ሮ አለም ዘውዱ ዘርፉ ስም ተመዝግቦ የነበረው ቤት በህፃን ልጃቸው በህፃን ማራማዊት መስፍን ስም አዛውረው ቤቱን በህፃን ማራማዊት ስም አስመዝግበው መገኘታቸው ብቻውን ህፃን ማራማዊት መስፍን የቤቱ ባለሐብት ናት ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ በፍርድ የተወሰነበትን እዳ መክፍያ እንዳይሆን ቤቱን በራሷ መንገድ ሰርታ ባገኘችው የገቢ ምንጭ የገዛችው ስለመሆኗ ሳያረጋግጥ የንብረቱ በህፃን ልጅ ስም በማዛወር ለፍርድ ማስፈፀሚያነት ንብረቱ እንዳይውል ለማሸሽ የሞከረ መሆኑን የሚያመለክት ተግባር ነው፡፡

የፍርድ ባለእዳ የሆነ ሰው ንብረቱ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እዳይውል አካለ መጠን ባልደረሰ ህፃን ልጁ ስም እያዛወረ መልሶ ንብረቱን በሞግዚትነት የሚያስተዳድርበት የሚሸጥበትና የሚለውጥበትን ሁኔታን ህጋችን አይፈቅድም፡፡ ባለእዳው መክፈል የሚገባውን እዳ ባለመክፈል በአጭበርባሪነት የሚፈጽማቸውን ተግባራት የፍርድ ባለመብት ወይም ገንዘብ ጠያቂው የመቃወምና እዳውን ላለመክፈል ያደርገው ተግባር መሆኑን ለማሳየት በማጭበርበር የተሰራው ስራ ዋጋ እንዳይኖረውና ባለእዳው እዳውን እንዲከፍል ማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1895 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1896 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መዝገብ በተጠሪና በአመልካች ስም የነበረውን ቤት ተጠሪ በህፃን ልጁ ለማራማዊት መስፍን ስም ማዛወሩ ንብረቱ የፍርድ ማስፈፀሚያ እንዳይሆን ለማድረግ የተፈፀመ የማጭበርበር ተግባር ነው በማለት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. በመጀመሪያ በተጠሪና በባለቤታቸው ወ/ሮ ዓለም ዘውድ ዘርፉ በአሁኑ ጊዜ በህፃን ማሪማዊት መስፍን ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት አመልካች በፍርድ ያስወሰኑትን ገንዘብ ማስፈፀሚያ እንዲሆንና የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በሐራጅ በማሸጥ እንዲያስፈጽም ጉዳዩን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ሶ/በ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. *50810*

ጥቅምት *30* ቀን *2003* ዓ.ም

***ዳኞች -*** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካቾች፣***

1. አቶ ፀጋዬ መሠረት
2. ወ/ሮ አስናቀች ሞላ
3. አቶ ታደሰ ተንሱ
4. ወ/ሮ እቴቱ አስፋው
5. ወ/ሮ ከበደች ባሕታ
6. አቶ ሀይለሚካኤል ወልደገብርኤል
7. አቶ ፀጋዬ ዋቄ
8. ወ/ሪት ፍቅርተ ፔትሮ
9. አቶ ሀይሌ ካሣይ
10. አቶ አስናቀ እጅጉ
11. አቶ ባልቻ ያህያ
12. አቶ አሉባ ዘሪሁን
13. አቶ ንጉሴ አለሙ
14. ወ/ሮ ቅድስት አበበ
15. አቶ ብርቄ ፈቃዱ
16. አቶ ከተማ ተክሉ
17. አቶ ገብሩ ገብርሥላሴ
18. አቶ አሰፋ መልካ
19. አቶ ግርማ ገብረስላሴ
20. አቶ ደበበ ደምሴ
21. ወ/ሮ እቴነሽ ያደቴ
22. አቶ ገረመው ቦጋለ
23. አቶ ሙዘይን መሐመድ
24. አቶ ክንፈ ገብሩ
25. አቶ ጌታቸው በቀለ
26. ወ/ሮ ጣይባቸው ደግፌ



www.chilot.me

27. አቶ ሰይፈ ተሾመ
28. አቶ ጌቱ ሀይሉ
29. አቶ ጌታቸው ደምሴ
30. ወ/ሮ አበራሽ ዲባባ
31. አቶ ተስፋዬ ሀይለጊዮርጊስ
32. አቶ ፍቅሬ መላ
33. አቶ አብርሃም ሀይሉ
34. ወ/ሮ ሙንትሀ አወል
35. አቶ ባርክልኝ ኑር
36. አቶ ዋናው ሀይለማርያም
37. አቶ ገብረዩሐንስ ሰባኔ
38. አቶ እንዳለው በየነ
39. ወ/ሮ ሉባባ ይልማ
40. ወ/ሪት ሙለዓለም ዳመጠው
41. የአስር አለቃ ክብረት ቱሉ
42. መቶ አለቃ ሳሙኤል ክብረት
43. አቶ ሙሉ በረዳ
44. አቶ ጌታቸው ደፍሰህ
45. አቶ ማዕረጉ ሽፋ
46. ወ/ሮ አለም ሲሳይ
47. አቶ ኤርካ ጉርሙ
48. ወ/ሮ አሰለፈች ደስታ
49. ወ/ሮ ባዩሽ ስጠኝ
50. አቶ አብራ መላ
51. አቶ ጌታቸው ካሣዬ
52. አቶ አወጣሽኝ አማረ
53. አቶ አረጋይ ቤኛ
54. ወ/ሮ አለም ተፈራ
55. አቶ ታምራት ቱሉ
56. አቶ ሀይሉ ታችበሌ
57. አቶ አበበ ተካ
58. ወ/ሮ ድጌረዳ መንግስትአብ
59. ወ/ሮ አስናቀች እሸቴ
60. አቶ አማረ ፀጋዬ
61. አቶ ተስፋዬ አበበ
62. ወ/ሮ አሰገደች ክብረት
63. ወ/ሮ ግምጃ ጉርሙ
64. አቶ ከበደ ባራኪ
65. ወ/ሮ አሰገደች ቱሉ
66. አቶ ገረመው ይርዳ



www.chilot.me

67. አቶ ጫኔ ተፈራ
68. አቶ መኮንን አሰፋ
69. አቶ ሲሳይ ግርማይ
70. ወ/ሮ ዘነበች ገብረህይወት
71. ወ/ሮ ልዑል ገባኢ
72. ወ/ሮ ጋዲሴ ሞላ
73. አቶ ካሣሁን አለሙ
74. አቶ ጣሰው ፈይሳ
75. አቶ ብርሃኑ ገብሬ
76. ወ/ሮ ቀነኔ ደባ
77. አቶ ሀብታሙ ወልደማርያም
78. ወ/ሮ ለተ ትንሣኤ
79. ወ/ሮ አስቴር ቀለታ /ወ/ሮ አስናቀች ተፈራ/

*ተጠሪ - የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን - ነገረፈጅ አወቀ ታረቀኝ ቀረቡ*

*መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡*

***ፍ ር ድ***

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የመጨረሻ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት በጠበቃቸው አማካኝነት ህዳር 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ የአሁን አመልካቾችና ሌሎች ሰዎች በድምሩ 151 ሰዎች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ አሁን ላለው የአሽከርካሪዎችና መካኒኮች የሥልጠና ማዕከል ለማስፋፋት በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስትር 130,777 ካሬ ሜትር ቦታ የካቲት 7 ቀን 1982 ዓ.ም የተሰጠው መሆኑን ገልፀው በወቅቱ በቦታው ላይ የነበሩት ሰላሣ ዘጠኝ ሰዎች የቤታቸውን ግምት ተቀብለው በተዘጋጀላቸው ቦታ እንዲዛወሩ ተወስኗል፡፡ በዚህ መሠረት ግምት የተቀበሉት ቦታውን እንዲለቁ ወይም የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ሌሎቹም በህገወጥ መንገድ በቦታው የሰፈሩ በመሆኑ ቦታውን ለቅቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካቾች የተጠሪ ክስ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በቦታው ላይ የሰፈርነው መንግስት እያወቀው በህጋዊ መንገድ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ቤታችን የተገመተው በዝቅተኛ ዋጋ ነው ስለዚህ እንደገና ተገምቶ ካሣ ሊሰጠን ይገባል የሚል ዝርዝር የመከራከሪያ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ቦታውን ተጠሪ በህዝብ አገልግሎት ስም ተቋም ለማስፋፋት በህጋዊ መንገድ የያዘው በመሆኑና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149/1/ ለእንደዚህ አይነት ሁኔታ የሚያገለግል ባለመሆኑ ተገቢነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ስማቸውን ከአንደኛ ተራ ቁጥር እስከ ስልሣ ዘጠነኛ ተራ ቁጥር የጠቀሳቸው ተከሣሾች በወቅቱ የንብረታቸው ግምት ተገምቶ ግምቱን እንዲቀበሉ በመሆኑና ምትክ



www.chilot.me

ቦታ ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው በመሆኑ የተጠሪን የይዞታ መሬት የማያስረክቡበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ቦታውን ለተጠሪ ያስረክቡ ስማቸው ከተራ ቁጥር 40 እስከ 151 የተዘረዘሩት ተከሣሾች የቤታቸው ግምት ያልወሰዱ ስለሆነ ቤቱ በፊት በነበረው ግምት መጠን በቅድሚያ በመክፈል ወይም ተመሳሳይ ቤት እንዲሰጣቸው አድርጎ ይዞታውን ማስለቀቅ ይችላል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ስልሣ ዘጠኝ የሚሆኑ አመልካቾች ይግባኝ ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ሰዎቹ በቦታው ላይ የሠፈሩት በህገወጥ መንገድ ሆኖ እያለ ካሣ እንድከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሥር ተከሣሽ የነበሩና አሁን ይግባኝ ባይ የሆኑ ሰዎች በአስተዳደር አካላት ህጋዊ ነዋሪዎች መሆናቸውና የተለያዩ ማስረጃዎች የተሰጣቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት ለሚፈርሰው ቤታቸው ተጠሪ ግምት እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው በማለት የተጠሪን መስቀለኛ ይግባኝ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የካሣውን መጠን በተመለከተ ይግባኝ ባዮችም ሆኑ ሌሎች ግለሰቦች ቤታቸው ተጠንቶ ለተወሰኑት ካሣና ምትክ ቦታ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በወቅቱ በቤቶቹ ግምት ላይ የቀረበ መቃወሚያ አልቀረበም ካሣው ለይግባኝ ባዩች ሣይከፈል የዘገየው ይግባኝ ባዮች በስምምነቱ መሠረት የክፍሉ ማዘጋጃ ቤት ወደአዘጋጀው ቦታ ለማዛወር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እና አከራካሪውን ቦታ ይዘው ለመቆየት በመፈለጋቸው በመሆኑ ጥፋቱ የይግባኝ ባዩች ነው ጥፋቱ የይግባኝ ባዩች ከሆነ መልስ ሰጭ/ተጠሪ/ በወቅቱ በነበረው ግምት መሠረት እንጂ አሁን ባለው የገበያ ዋጋ ለቤቶቹ ግምት የሚከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አቤቱታውንም ሰርዞታል፡፡ አመልካቾች ለሰበር ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አመልካቾችና ሌሎች በቦታው /ስፍራው/ የሚገኙ ከሶስት መቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ከሰላሣ አንድ ዓመት በላይ የያዙትን ይዞታ እንዲለቁ ክስ የቀረበው የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስትር ፈቅዶልኛል በማለት ነው፡፡

መንግስት አንድ ንብረት የሚወሰደው ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውና ተመጣጣኝ ካሣ ሲከፍል ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቦታው ለህዝብ ጥቅም የሚፈለግ ስለመሆኑ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሰጠው ውሣኔ አልቀረበም፡፡ ቦታው በሊዝ የተወሰደ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሰነው ውሣኔ የለም፡፡ ስለዚህ ቦታው ለህዝብ ጥቅምና አገለግሎት የሚውል መሆኑ በተገቢው የመንግስት አካል ሣይወሰን ተጠሪ ይዞታን ለማስፋፋት በማቀድ ያቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም ተጠሪ በዚህ አይነት ሁኔታ ከንብረታችንና ከይዞታችን ለማስነሣት የሚያደርገው እንቅስቅሴ የህገመንግስቱ አንቀጽ 40/8/ ና አዋጅ ቁጥር 272/1994 ድንጋጌ ውጭ በመሆኑ ካሣውም እነዚህን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የተሰራ ባለመሆኑ የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በይግባኝ የተከራከሩት ስልሣ ዘጠኝ ሰዎች ብቻ ሲሆኑ ሰባ ዘጠኝ ሰዎች ለችሎቱ የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም የማሰልጠኛ ተቋሙ በአገራችን የትራፊክ አደጋን ለመቀነስና የትራፊክ ደህንነትን ለማጎልበት አስፈላጊ መሆኑ በመንግስት ታምኖበት በከፍተኛ በጀትና ወጭ የተቋቋመ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡ ተቋሙን ለማስፋፋት በአቅራቢያው ያለውን ምቹ ቦታ እንዲንወሰድ ሥልጣን ባለው አካል ውሣኔ ተሰጥቶበት የቦታው ባለይዞታ የሚያደርገን ካርታና ፕላን ተሰጥቶናል ስለዚህ አመልካቾች ቦታውን ላለመልቀቅ የሚያቀርቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት በቃል ክርክር መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች



www.chilot.me

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሣይወሰን ቦታውንና ንብረታችንን እንድንለቅ መደረጉ ህጋዊ አይደለም በማለት በጠበቃቸው አማካኝነት በቃል ክርክር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ በፅሑፍና በቃል ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካቾች ቦታውንና ንብረቱን ለተጠሪ እንዲለቁ እንደዚሁም ተጠሪ በፊት በተሠራው ግምት መሠረት ለተጠሪዎች ካሣ እንዲከፍል በአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ከማየታችን በፊት ተጠሪ በይግባኝ ተከራካሪ የነበሩት ስልሣ ዘጠኝ ሰዎች ነበሩ አሁን ለሰበር ሰባ ዘጠኝ ሰዎች አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበውን ተቋውሞ መርምረናል፡፡ አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ ጋር ከተያያዘው የአዲስ አበባ አስተዳደር የሰበር ችሎት የውሣኔ ግልባጭ በከተማው ሰበር ችሎት አመልካች የነበሩት ስልሣ ዘጠኝ ሰዎች ሣይሆኑ ሰባ ዘጠኝ ሰዎች መሆናቸው በግልፅ ተመዝግቧል፡፡ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በአንድ መዝገብ ይግባኝ አቅርበው የተከራከሩት ስልሣ ዘጠኝ ሰዎች ሲሆኑ አሰሮቹ ሰዎች በይግባኝ የብቻ መዝገብ አስከፍተው በይግባኝ ሲከራከሩ ቆይተው ወደ ከተማው ሰበር አቤቱታ ያቀረቡና መዝገባቸው ተጣምሮ የታየ መሆኑን ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ለከተማ ሰበር ችሎት ያቀረቡትን አቤቱታ የተቀበላቸው ስለመሆኑ ለመለየት የማይቻል ቢሆንም ተጠሪ ተቃውሞ ከማቅረብ ውጭ እንዴትና በምን ምክንያት የከተማ ሰበር ችሎት ሰባ ዘጠኝ ሰዎች አመልካቾች የሆኑበትን አቤቱታ ተቀብሎ ትዕዛዝ ሰጠ የሚለውን ያላስረዳ በመሆኑ ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልተቀበልነውም፡፡

ወደ መሠረታዊ ጉዳዩ ስንመለስ ተጠሪ ያቋቋመውን የአሽከርካሪና የቴክኒክ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም ለማስፋፋት ክርክር ያስነሣውና ስፋቱ 137,777 ካሬ ሜትር ቦታ በወቅቱ በነበረው ከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የተሰጠ መሆኑንና ተጠሪ የይዞታ የምስክር ወረቀት፣ ካርታና ፕላን በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል የተሰጠው መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ መንግስት ለህዝብ ጥቅም ተመጣጣኝ ካሣ በመክፈል የግለሰብ ሀብትና ንብረት መውሰድ የሚችል መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ መንግስት በህግ በኩል እንደአንድ ሰው የሚቆጠር መሆኑንና በመሥሪያ ቤቶቹ አማካኝነት ከተፈጥሮው ጋር የሚስማሙትን መብቶች ሁሉ ሊሠራባቸውና ሊያገኝ እንደሚችል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 394 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ የመንግስት መሥሪያ ቤት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ለህዝብ ጥቅምና አገልግሎት ያቋቋመውን ተቋም ለማስፋፋት ጥያቄውን ለጉዳዩ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ላለው የከተማው ልማትና ቤት ሚኒስቴር አቅርቦ ቦታው ተሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም ቦታው ለህዝብ ጥቅም የተፈለገ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 394 ንዑስ አንቀጽ 2 ተጠይቆ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 396 አንቀጽ 2 መሠረት ታምኖበት በወቅቱ ሥልጣን ባለው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የተፈቀደ በመሆኑ አመልካቾች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሣይወሰን ቦታና ንብረታችንን እንድንለቅ መደረጉ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 የሚጥስ ተግባር ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡



www.chilot.me

አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 272/1994 በመጥቀስ ከቦታው እንድንለቅ የተሰጠው ውሣኔ የአዋጁን ድንጋጌ የሚቃረን ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከት አመልካቾች በቦታው ላይ ያለውን ንብረት በማንሣት እንዲለቁ የተወሰነው ቦታው በህዝብ ጥቅምና ግልጋሎት የሚሰጥ ተቋም ማስፋፊያነት ለመጠቀም ነው፡፡ መንግስት አንድ የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚወስድበት ጊዜ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓት ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1460 እስከ ፍታብሔር ህግ ቁጥር 1488 ተደንግጓል፡፡ አመልካቾች የሚከራከሩበት ቦታና ንብረት ለህዝብ ጥቅም እንዲለቁ የተወሰነው በ1982 ዓ.ም በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መብታቸውን በማስከበር ከሚጠይቁ በስተቀር ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 272/1994 በመጥቀስ ክርክር ማቅረባቸው ተገቢ ሆኖ አላኘነውም፡፡

አመልካቾች የህገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 በሚደነግገው መሠረት ለንብረታቸው ተመጣጣኝ ካሣ ተጠሪ እንዲከፍል አልተወሰነልንም በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ አመልካቾች ንብረት ተጠንቶና ግምቱ ተለይቶ አመልካቾች ማዘጋጃ ቤት ወደአዘጋጀው ቦታ ተዛውረው የንብረታቸውን ግምትና ዋጋ እንዲወስዱ ተጠየቀው የነበሩ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በወቅቱ ለንብረቱ የተሰጠው ግምት ከንብረቱ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ አይደለም ብለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1477/2/ በሚደነግገው መሠረት በሶስት ወር ለፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ እንደሌለ የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

አመልካቾች ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ በሚደነግገው የጊዜ ገደብ ውስጥ በወቅቱ ለንብረታቸው የተወሰነላቸውን የካሣ ገንዘብ በመቃወም ለፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ የለም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች በቦታው ላይ ያለውን ንብረት እና ይዞታውን እንዲለቁ የሚመለከተው የመንግስት አካል ወስኖ ካሣወቃቸው በኃላ ወደ ተዘጋጀው ቦታ ላለመዛወርና ቦታውን ላለመልቀቅ የተለያየ ምክንያት እየፈጠሩ እስካሁን እንዳለቀቁ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በወቅቱ ተገምቶ ተጠሪ ያሣወቃቸውን የካሣ መጠን በመቃወም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1477 ድንጋጌዎች መሠረት አቤቱታ ለፍርድ ቤት በማቅረብ እንዲሻሻል መከራከር ወይም ቦታውን በመልቀቅ ግምቱን መውሰድ ሲገባቸው እስካሁን በቦታው ላይ መቆየታቸው ተገቢ አለመሆኑና ጥፋቱ የተጠሪ ሣይሆን የአመልካቾች መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የህጉን ሥርዓት ተከትለው ቅሬታቸውን ማቅረብና ቦታውን በመልቀቅ ቦታውን ለተሰጠው የህዝብ ጥቅምና ግልጋሎት እንዲውል ማድረግ ሲገባቸው ይህንን ሣያደርጉ በመቅረታቸውን በመዘግየታቸው ምክንያት ንብረቱ በፊት ከተገመተው ግምት በላይ የሚጠየቁበት የህግ መሠረት የለም በማለት የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎት መወሰናቸው ንብረቶቹ በወቅቱ በግምታቸው ካሣ ሣይከፈል የቀረው በማን ጥፋት ነው የሚለውን ነጥብ ለማስረዳት ያቀረቡ ማስረጃዎችን በመመዘን የደረሱበት መደምደሚያ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውና ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

***ው ሣ ኔ***

1. የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47139

ኅዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ የሱፍ ሁሴን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አደን አብደላ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሱማሌ ብሔራዊ ክልል የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለጅጅጋ ዞን ያቀረበው ክስ ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ካሀ አብደላ የተባለችው እህቱ የአፈር ቤቶችና የከተማ ቦታ የነበራት መሆኑንና እህቱ ካሀ ከተጠሪ ውጭ ሌላ ወራሽ የሆነ የሥጋ ዘመድ የሌላት መሆኑን ገልፆ ሚች ካሀ ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ አክስቷ ወ/ሮ ከድጃ ሰምታ መጥታ ለተከሳሽ (አመልካች) ቤቶቹን እኔ እስክመጣ ድረስ በአደራ እየጠበቀ እንዲቆይ ለተከሳሽ (አመልካች) አባት ሁሴን አሰን ሰጥታዋለች፡፡ አቶ ሁሴን አሰን (የአመልካች አባት) በቀበሌ 02 ክልል ውስጥ ያሉትን የሚች ወ/ሮ ካሀ ቤትና ቦታ ይዟል፡፡ የቦታው አዋሳኝ በምስራቅ የአመኑር ቤት፣ በምእራብ መንገድ በሰሜን የአህመድ ሽፋው ቤተሰቦች በደቡብ መንገድ ሲሆን የሚች ወ/ሮ ካሃ ቤቶች ብዛት ሁለት ክፍል በአፈር ክዳን የተሰራ ቤት፣አምስት ክፍል በቆርቆሮ ክዳን የተሰራ ቤትና ስድስት መፀዳጃ ቤት ያካተተ ነው፡፡ አቶ ሁሴን አሰን ቤቶቹን እንዲያስረክበኝ ስጠይቀው ለረዥም ጊዜ ቤቶቹን ስንከባከብና ስጠብቅ ስለቆየሁ ገንዘብ ይክፈለኝ በማለቱ በሽማግሌ ብር 8000 (ስምንት ሺህ ብር) ልከፈለው ከተስማማን በኋላ የቤቱ ባለሐብት ለመሆኔ ካርታና ፕላን አለኝ በማለት ቤቱን ለመሸጥ እያስማማሁ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ቤቱን የሠራችው ሚች ወ/ሮ ከሃ አብደላ መሆኗን፣እና ተከሳሽ የያዘው ትክክለኛ ያልሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ትክክለኛ አለመሆኑ በማስረጃ ተጣርቶ እንዲወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፣የሥር ተከሳሽ የአሁን አመልካች በበኩሉ ቀደም ሲል ሚች ወ/ሮ ከሃ የግል ይዞታና ቤት የነበራት ቢሆንም በሕይወት እያለች ቤቱንና ቦታውን ለእኔ ወላጅ አባት ሁሴን ሐሰን ሰጥታዋለች ወ/ሮ ከሃ ቤቱን ለወላጅ አባቴ የሰጠች ስለመሆኑ ማስረጃ አለን፡፡ ከሳሽ (ተጠሪ) ገንዘብ እንዲከፍለኝ ያደረግሁበት



www.chilot.me

ስምምነት የለም በማለት የይዞታ ማረጋገጫ የባለቤትነት የምስክር ወረቀትና ሌሎች ምስክሮችን ዘርዝሮ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልስ ሰጥቷል፡፡

የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካችን የቃል ክርክር ሲሰማ ቤቱና ቦታው በመጀመሪያ የሟች የወ/ሮ ካሀ አብደላ መሆኑንና በአቅራቢያው ሟች ወራሽ ያልነበራት መሆኑን የተስማሙበት ፍሬ ጉዳይ እንደሆነ በውሣኔው የገለፁ ሲሆን፣ወ/ሮ ካሃ አብደላ በህይወት እያለች ቤቱን ለአመልካች አባት ሰጥታለች ወይስ አልሰጠችም የሚለው ነጥብ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት መሆኑን በመለየት ጭብጥ መሥርቷል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በጽሑፍ በተደረገ የስጦታ ውል ቤቱን ለአመልካች አባት የሰጠች ስለመሆኗ የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረበና አመልካች ያቀረበው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በአሁኑ ወቅት ቤቱ የአመልካች ንብረት መሆኑን የሚያስረዳ እንጅ ቤቱ የቀድሞ ባለሐብት ከሆነችውና የቤቱ ባለንብረት መሆኗ አከራካሪ ካልሆነው ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ እንዴት ወደ አመልካች አባት እንደተዛወረ አያስረዳም፡፡ በሌላ በኩል ከሳሽ/ተጠሪ/ የሟች ካሃ አብደላን ቤት ከድጃ የተባለችው ሴት ለአመልካች አባት ተጠሪ የሟች ወራሽ እስኪመጣ በአደራ ይዞ እንዲቆይ የሰጠችው መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ የተደራደሩና አመልካች ብር 8000/ስምንት ሺህ ብር/ ከተጠሪ ለመቀበል ተስማምቶ ተጠሪ ገንዘብ የሌለው በመሆኑ መክፈል እንዳልቻለ አስረድቷል በማለት የአመልካች አባት ቤቱን የያዙት በአደራ በመሆኑ ለተጠሪ (ለሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ) ወራሽ እንዲያስረክብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታቸውን አልተቀበለውም፡፡ አመልካች ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ወላጅ አባቴ አቶ ሁሴን አው ሐሰን 1986 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡ ወላጅ አባቴ በጅጅጋ 02 ቀበሌ የቤት ቁጥር 123-01 ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበረ ሲሆን እኔም አባቴ በሞት ከተለዩ በኋላ እየኖርኩበት እገኛለሁ፡፡ ተጠሪ ቤቱ የእህቴ ወ/ሮ ካሃ ስለሆነ ይልቀቅልኝ በማለት ክስ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦብኝ እኔም አባቴ ለአርባ ስድስት ዓመት በቤቱ ውስጥ የኖረና በሶማሊያ ጦርነት ሰነዱ /ካርታና ፕላኑ/ በመቃጠሉ ወ/ሮ ካሃ በሕይወት እያሉ ሌላ ካርታና ፕላን አውጥተው የኖሩበት ነው በማለት ተከራክሬአለሁ፡፡ ቤቱ የአባቴ አክስት የሆነውንና የአባቴ አክስት ለአባቴ በሕይወት እያለ የሰጡት ቤት መሆኑን በህይወት ያሉት የአባቴ አክስት ባል አሊ ባድል ሣይጠየቁና ሣይመሰክሩ ለተጠሪ እንዲያስረክብ የተሰጠው ውሣኔ አባቴ የቤቱ ባለሐብት መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ እያለ አላግባብ የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህ ውሣኔው በሰበር እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የእህቴ የሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች ሟች ወ/ሮ ካሃ ቤቱን ለአባቷ እንደሰጡ በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም ሟች ወ/ሮ ከሃ ቤቱን በስጦታ ያስተላለፉበትን ሰነድ በማቅረብ አላስረዳም፡፡ በእኔ በኩል የሟች ወ/ሮ ካሃ ወንድምና ወራሽ መሆኔን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቤአለሁ፡፡ የአመልካች አባት ቤቱ ከቀድሞ ባለንብረቷ ከወ/ሮ ካሃ በሕጋዊ መንገድ ሣይተላለፍላት የወጣው የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት አመልካችን የቤቱ ባለሐብት ሊያደርገው አይችልም፡፡ ስለሆነም በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት ኀዳር 10 ቀን



www.chilot.me

2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ኅዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የአባቴ አክስት ከሆኑት ከወ/ሮ ከሃ አብደላ ለሚች አባቴ እንዲተላለፍና በሚች አባቴ ስም ካርታ ወጥቶበት እንደሚገኝ በአቤቱታዬ በሰፊው ዘርዝሬ አቅርቤያለሁ፡፡ ቤቱ በአባቴ ስም ካርታ ያለው በመሆኑ ተጠሪ ከዚህ የበለጠ የቤቱ ባለሐብት ለመሆን ማስረጃ ያላቀረቡ ስለሆነ ክርክራቸው ተገቢ አይደለም የሰነድ ማስረጃ በምስክር ማቅረብ እንደማይቻል የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2005 ይደነግጋል የሚል ሰፊ ክርክር አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ክርክር የተደረገበትን ቤትና ቦታ ለተጠሪ እንዲያስረክብ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመመስረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትና ቦታ የሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በህይወት እያሉ ያፈሩት ንብረት መሆኑን አመልካችና ተጠሪ ያልተካካዱበት ፍሬ ጉዳይ እንደሆነ የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በመጀመሪያ ያፈሩት ሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ መሆናቸውን አመልካች ለዚህ ችሎት በሰጠው የመልስ መልስ ገልጿል፡፡ ስለሆነም የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትና ቦታ ሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በህይወት እያሉ ያፈሩት ሀብት መሆኑ አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡

አከራካሪው ጭብጥ አመልካች ወ/ሮ ካሃ አብደላ ቤቱንና ቦታውን በህይወት በነበሩበት ጊዜ ለአባቴ ለአቶ ሁሴን አው ሐሰን በስጦታ አስተላልፋለት የቤቱ ባለሃብትነት ካርታና ፕላን በአባቴ ስም ሆኗል በማለት አመልካች የሚያቀርበውን ክርክር ተጠሪው በግልጽ በመካድ የአመልካች አባት አቶ ሁሴን አው ሐሰን ቤቱን ከወ/ሮ ከድጃ እኔ እስክመጣ ድረስ በአደራ እንዲጠብቅ ነው የተረከበው፣የቤቱን ባለሃብትነት ማስረጃ ያወጡት ቤቱ በስጦታ ለሺያጭ ወይም ለውርስ ከሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ ሣይተላለፍላቸው በተሣሣተ መንገድ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ስለሆነም ቤቱ በአሁኑ ወቅት በአመልካች አባት ስም ተመዝግቦ መገኘቱና የአመልካች አባት የቤቱ ባለሐብት መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለሐብትነት ማስረጃ ካርታና ፕላን ያለው መሆኑ ቤቱ የቀድሞ ባለንብረት ከነበሩት ወ/ሮ ከሃ አብደላ በህጋዊ መንገድ የተላለፈለት ለመሆኑ የሚያረጋግጥና ሊስተባበል የማይችል ማስረጃ ነው ወይስ አይደም? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአንድ የማይንቀሣቀሥ ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማረግገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ማስረጃ የያዘ ሰው የማይንቀሣቀሰው ንብረት ባለቤት ነው ተብሎ እንደሚገመት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1195/1/ የሚደነግግ ሲሆን ይኸ የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1195 ንኡስ አንቀጽ 2 በግልጽ ይደነገጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በአሁኑ ወቅት በአመልካች አባት ሚች አቶ ሁሴን አው ሃሰን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን የአመልካች አባት የቤቱ ባለሐብት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማስረጃ ያላቸው መሆኑ ቤቱ የአመልካች አባት አቶ ሁሴን አው ሐሰን ሐብት ነው ብሎ የህሊና ግምት ለመያዝ የሚያበቃ ማስረጃ ነው፡፡ ነገር ግን ይኸ ማስረጃ ጥቅሜና መብቴ ተነክቶብኛል የሚል ሌላ ሰው ቤቱ የሚች አቶ ሁሴን አው ሐሰን አለመሆኑንና የተሰጠው የባለቤትነት ማስረጃም ትክክለኛ ማስረጃ አለመሆኑን ሌላ ማስረጃ በማቅረብ ሊያፈርሰውና ሊያስተባብለው የሚችል መሆኑ በፍታብሔር ሕጉ አንቀጽ 1195 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ንብረቱ በአባቴ ስም የተመዘገበና የአባቴ ንብረት መሆኑን የሚያረጋግጥ ካርታና ፕላን



www.chilot.me

እያለ ተጠሪ ይህንን እንዲያስተባብልና በሰው ማስረጃ እንዲያፈርስ የበታች ፍርድ ቤቶች መፍቀዳቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የሕግ መሰረት የለውም፡፡

ተጠሪ ቤቱ በመጀመሪያ አውራሹ የሆነችው የሟች ካሃ አብደላ መሆኑን በማስረጃ ከማረጋገጡ በተጨማሪ ቤቱን በሕይወት እያሉ ያፈሩት ሟች ወ/ሮ ካሃ መሆናቸውን አመልካች በሥርና በዚህ ፍርድ ቤት አምኖ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ከዚህ በተጨማሪ የአመልካች አባት አቶ ሁሴን አው ሐሰን ቤቱን በአደራ ጠባቂነት ወ/ሮ ከድጃ ከተባሉ የሟችና የተጠሪ ዘመድ የተረከቡ መሆኑና አመልካች ቤት በአደራ የጠበቁበትን የድካም ዋጋ ብር 8000 (ስምንት ሺ ብር) ለመቀበል ተስማምተው የነበሩ መሆኑን ጉዳዩን በሽምልና በማየት አመልካችና ተጠሪን ያስማሙ ምስክሮች እንዳረጋገጡ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ተረጋግጧል፡፡ የአመልካች ወላጅ አባት ቤቱ ከሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በሽያጭ ውል በውርስ ወይም በስጦታ ሣይተላለፍላቸው ቤቱን በአደራ ጠባቂነት ከወ/ሮ ከድጃ ከተረከቡ በኋላ የቤቱን ስመ ሐብት ማዞራቸውንና የባለቤትነት ማስረጃ የተሰጡ መሆኑን ተጠሪ በበቂ ማስረጃ ካረጋገጠ የአመልካች አባት የቤቱ ባለሐብት ናቸው የሚለውን ግምት ለማፍረስና ለማስቀረት የሚችል ምክንያት መሆኑ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1196/ሀ/ እና /ለ/ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ አመልካች በዚህ በኩል ያቀረቡት ቅሬታ የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

ቤቱ በአመልካች አባት ስም መመዝገቡና የአመልካች አባት የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1195/1/ መሰረት የቤቱ ባለሃብት ናቸው የሚል ግምት ሊያሣድር የሚችል ማስረጃ ቢሆንም ተጠሪ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1196 /ሀ/ እና /ለ/ የተደነገጉትን ሁኔታዎች በማስረዳት የባለቤትነት ማስረጃው ትክክል አለመሆኑን በበቂ ሁኔታ እንዳስተባበሉ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ለሟች አባቴ አቶ ሁሴን አው ሐሰን ወ/ሮ ከሃ አብደላ የቤቱን ባለሐብትነት በስጦታ አስተላልፋላቸዋለች የሚል ክርክር ከሥር ጀምሮ እስከ ሰበር ችሎት ያቀረበ ቢሆንም አመልካች ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ቤቱን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 881 ወይም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 882 በሚደነግገው መሰረት በስጦታ የሰጧቸው መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ እንዳላቀረቡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካች አባታቸው ቤቱን ከሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ ከላይ የተገለፁት የሕግ ድንጋጌዎች በሚደነግጉት መሰረት በስጦታ ያስተላለፉላቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴትና ኃላፊነታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ ቤቱን ለአባቴ የሰጠችው መሆኑን አቶ አሊ ባድል የተባሉ ሰው በሚሰጡት የምስክርነት ቃል ለማስረዳት ያቀረብኩትን ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች አላግባብ ውድቅ አድርገውብኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ ድጋፍና መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም አከራካሪው ቤትና ቦታ ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በሕይወት እያሉ ያፈሩት ንብረት መሆኑና ተጠሪም የሟች ወ/ሮ ካሃ ወራሽ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑና ለክርክር መነሻ የሆነው ቤትና ቦታ በአመልካች አባት በአቶ ሁሴን አው ሐሰን ስም ተመዝግቦ የሚገኝና አቶ ሁሴን የቤቱ ባለሐብት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማስረጃ ያላቸው ቢሆንም አቶ ሁሴን የቤቱን ባለሐብትነት በስማቸው ያስመዘገቡትና የባለሐብትነት ማስረጃ የወሰዱት ቤቱ በሕጋዊ መንገድ ከባለሐብቷ ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በሽያጭ፣ በውርስ ወይም በስጦታ ሣይተላለፍላቸው ይልቁንም ወ/ሮ ከድጃ የተባሉ የሟች ወ/ሮ ካሃና የተጠሪ ዘመድ በአደራ እየጠበቁ እንዲቆዩ ካስረከቧቸው በኋላ



www.chilot.me

ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የቤቱን ስመ ሐብት በስማቸው ያዛወሩና የባለቤትነት ማስረጃ የወሰዱ መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1196/ሀ/ ና /ለ/ በሚደነግጉት መሰረት ተጠሪ በማስረጃ ያረጋገጠና ያስረዳ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡትን ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማጽደቁ ተገቢና የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሱማሌ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ሰኔ 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የካቲት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡት ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48086

ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- 1/ወ/ሮ አሰለፈች ወልደሚካኤል አልቀረበም

2/ ወ/ሮ ቀለመወርቅ ወልደሚካኤል አልቀረበም

**ተጠሪ**፡- ቶታል ኢትዮጲያ አክሲዮን ማህበር ጠበቃ አቶ ወንድየ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአሁን አመልካች አባታችን ሟች አቶ ወልደሚካኤል ወልደማርያም በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 1 ቀበሌ 07 የቤት ቁጥር 142 የሚታወቀውንና በተለመደ አርበኞች ቶታል ኩባንያ ለኮትንትራክት አስረክበዋል፡፡ የአባታችን የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ስለሆንን የነዳጅ ማደያው ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት ስለሆነ ቢሮውንና የነዳጅ ማደያውን እንዲያስረክቡን በማለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፣ከሣሾች ወራሽነታቸውን አላረጋገጡም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ አርበኞች መንገድ ተብሎ የሚጠራው የቶታል ቤንዚን ማደያ ቢሮ ግምት ያነሰ ነው፡፡ በተከሣሽ /ተጠሪና/ በከሣሾች አውራሽ አቶ ወልደሚካኤል ወልደማርያም መካከል ተደርጎ የነበረው ውል የነዳጅ ማደያ ኪራይ ውል አይደለም፡፡ ከሟች አቶ ወልደሚካኤል ጋር የነበረን ውል የመሬት ኪራይ ውል ነው፡፡ ከአቶ ወልደሚካኤል በተከራየው ቦታ ላይ የቤንዚን ማደያውንና ጽ/ቤቱን የሠራው ተከሣሽ /ተጠሪ/ ነው፡፡ ኪራዩ ከ1967 ዓ.ም በፊት የተደረገ በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 47/1967 የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት እንዲሆን የታወጀ በመሆኑ እንደዚሁም በየነዳጅ ማደያው ከመንግሥት ቦታና ቤት ተከራይተው ይሰሩባቸው የነበሩ ይዞታዎች የሚኒስትሮች ቤት መጋቢት 10 ቀን 1968 ዓ.ም ቁጥር 411/68 በተፃፈ ደብዳቤ ግንኙነቱ ከመንግሥት ጋር እንጅ ከቀድሞ አከራዬች ጋር እንዳልሆነ የደነገገ በመሆኑ ክሱ ሕጋዊ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡



www.chilot.me

የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል የተከራይ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ አመልካች በነዳጅ ማደያውና በጽ/ቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎችና የሕግ ድንጋጌዎች እንደዚሁም ከአመልካች አውራሽ ጋር ከተደረገው የመሬት ኪራይ ውል ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪና በአመልካች አውራሽ መካከል የተደረገው የመሬት ኪራይ ውል እንጅ የነዳጅ ማደያና የጽ/ቤት ኪራይ ውል አይደለም፡፡ የኪራይ ውሉ የተደረገው ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 በፊት በመሆኑና በዚህ አዋጅ የከተማ ቦታ የመንግሥት ሀብት የሆነ በመሆኑ እንደዚሁም የሚንስትሮች ምክር ቤት መጋቢት 10 ቀን 1968 በቁጥር 411/68 ዲፖዎች ባሉበት እንዲቀጥሉ የወሰነ ስለሆነ አመልካች ተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ተገቢ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የተከራየው መሆኑ ብቻ አይደለም፡፡ የነዳጅ ማደያውንና ቤቱን የተከራየ መሆኑን የሚያሣይ ማስረጃ አቅርበናል፡፡ በሚንስትሮች ምክር ቤት ተፃፈ የተባለው ደብዳቤ ታዓማኒነቱ ሣይረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች መቀበላቸው ስህተት ነው፡፡ ውሉ የተደረገው 1954 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ውል መሠረት የውሉ ዘመን ሲጠናቀቅ ተጠሪ የነዳጅ መቅጃ መሣሪያዎቹን ቤቱቹን አስረክቦ ለመሄድ ተዋውሏል፡፡ ተጠሪ ቦታውን ተረክቦ ቤት ሠርቷል ስለዚህ በውሉ ምዕራፍ አስር መሠረት የቤቱ ባለመብቶች እኛ ሆነን እያለ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1731/11/ በመጣስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ የመሬት ኪራይ ውል የተፈፀመው አዋጅ ቁጥር 47/1967 ከመታወጁ በፊት ሣይሆን ውሉ ከዚህ አዋጅ በኋላ ሕጋዊ አስገዳጅነት የሌለው በመሆኑ የተከራየነው የነዳጅ ማደያ ቢሮ ሣይሆን መሬት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም በአመልካwች አውራሽና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል መሠረት ተጠሪ እንዲፈጽም አይገደድም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በአውራሻችን አቶ ወልደሚካኤልና በተጠሪ መካከል በ1954 ዓ.ም የተደረገው ውል የመሬት ኪራይ ውል ሣይሆን የነደጅ ማደያና ለጽሕፈት ቤት የሚሆን ቤት ኪራይ ውል ነው በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በተጠሪና በአመልካች አውራሽ መካከል በ1954 ዓ.ም የተደረገው ውል የመሬት ኪራይ ውል መሆኑን በማረጋገጥ ወስነዋል፡፡ አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የማስረጃ ተዓማኒነት እና ክብደት ሲመዝኑ ስህተት ሠርተዋል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የሰበር ችሎት ለሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባና የሰበር ችሎት ማስረጃ ታዓማኒነትና ክብደት እንዲመዝን የሚጠይቅ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በአመልካች አውራሽና አቶ ወልደሚካኤል መካከል የመሬት ኪራይ ውል የተደረገው በ1954 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ጊዜ መሬት የግለሰቦች ሀብትና ርስት እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን አቶ ወልደሚካኤል የነበረችውን ርስት መሬት ላይ ተጠሪ የነዳጅ ማደያ ድርጅትና ጽ/ቤት ገንብቶ ኪራይ እየከፈለ እንዲኖር በመጨረሻም የኪራይ ዘመኑ ሲጠናቀቅ ድርጅቱንና ግንባታውን ለቆ እንዲሄድ ተስማምተው የነበሩ መሆኑን ግራ ቀኙ በሥርና በሰበር ካደረጉት ክርክር ተገንዝበናል፡፡



www.chilot.me

ሆኖም የኪራይ ውል ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት የውሉን አይነተኛ ጉዳይ በተለይም የአመልካች አውራሽ ባለመብት ሆነው የኪራዩን መሬት መንግሥት የሕዝብ ሀብት የሚያደርግ የሕግ ማዕቀፍ አዋጅ ቁጥር 47/1967 ታውጇል፡፡ በአዋጁ በባለርስትና በጭሰኛ መካከል ያለውን ግንኙነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የተቋረጠ በመሆኑ ከነሐሴ ወር 1967 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች አውራሽም ሆነ በአመልካች እንዲፈጽም የሚገደድበት ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል ውል የለም፡፡ አንድ ውል በተዋዋዮች መካከል እንደ ሕግ ሆኖ አስገዳጅነት የሚኖረው ውሉ የሚቻልና የተደረገውም ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የሆነ እንደሆነ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ይደነግጋል፡፡ የአመልካች አውራሽና ተጠሪ  በ1954 ዓ.ም ሲዋዋሉ የውርስን መሬት ማከራየት፣ መሸጥና መለወጥ የሚቻል ቢሆንም ይህ ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 የተቋረጠና በግለሰብ ደረጃ መሸጥ ፣መለወጥ የተከለከለ በመሆኑ የውሉ መሠረታዊ ጉዳይ የማይቻልና በሕግ ያልተፈቀደ ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቀድሞ የመሬት ባለርስት ከነበሩ ሰዎች መሬት ተከራይተው የነደጅ ማደያ ያቋቋሙ ድርጅቶች ግንኙነታቸው ከመንግሥት ጋር እንደሆነና መንግሥት አይቶ ውሣኔውን የሚያሣውቃቸው መሆኑን የሚኒስትሮች ምክር ቤት መጋቢት 10 ቀን 1968 በቁጥር 411/68 በፃፈው ደብዳቤ  ያሣውቀ መሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ በመንግሥት የተደረገ ክልከላ ከተዋዋይ አቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካች አውራሽና በተጠሪ መካከል በ1954 ዓ.ም የተደረገው የመሬት ኪራይ ውል በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ተፈፃሚነቱ የተቋረጠ በመሆኑና የሚንስትሮች ምክር ቤትም ተጠሪ የመሬቱን ኪራይ በተመለከተ ግንኙነቱ ከመንግሥት ጋር እንጅ ከቀድሞ አከራይ ጋር አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን በማጣራት ተጠሪ የነደጅ ማደያውንም ሆነ በቦታው ላይ የሠራቸውን ቤቶች ለአመልካች ለማስረከብ አይገደድም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
3. ለውሣኔ አሰጣጥ እንዲጠቅም ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በትውስት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49985

ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሻለቃ አሰፋ አየለ ደምሴ ጠበቃ አቶ ግርማ አይታገድ

**ተጠሪ፡-** ፍቃዱ ሙሉኔታ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ ተለይቶ የታወቀ ንብረት ተወስዶብኛል ይመለስልኝ በሚል በሁከት ይወገድልኝ ስም ክስ በቀረበ ጊዜ ለዚህ ዓይነቱ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(2) የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ልንከተል የሚገባውን አተረጓጐም የሚመለከት ነው፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሰኔ 22 ቀን 1991 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ በወረዳ 17 ቀበሌ 20 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 23803 የተሰጠኝን ስፋቱ 250 ካ.ሜትር የሆነውን ቦታ ከእነ ጅምር ቤቱ በመያዝ አለቅም ስላለ ለቆ እንዲያስረክበኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪም በተከሳሽነቱ ክርክር ያስነሳውን ንብረት ከያዝኩበት ጊዜ ጀምሮ ከሳሽ ቦታው ተወሰደብኝ በማለት ክስ እስካቀረቡበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ 13 ዓመት ያለፈው ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡

ቦታውን ተረክበው ግንባታ ባለማከናወናቸው በመንግስት መመሪያ ከተወሰደባቸው መንግስትን እንጂ እኔን አይጠይቁም ቦታውን በክፍሉ ቀበሌ አመልክቼ በ1978 ዓ.ም ተሰጥቶኝ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ የንግድ ፈቃድ አውጥቼ በይዞታ ሥር አድርጊያለሁ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር መልስ አቅርበዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የቀረበውን የሰነድና የሰው ማስረጃ ከተመለከተ በኋላ ክርክር ያስነሳውን ቦታ የአሁን ተጠሪ ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ያዙት የሚለውን ነጥብ በሚመለከት የተጠሪ ማስረጃዎች ከአመልካቹ በተሻለ ሚዛን በሚደፋ መልኩ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ በተጠሪ ይዞታ ሥር ንብረቱ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው (ከ1978-1991) ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲታሰብ ከ2 ዓመት

በላይ ስለሚሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(2) መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች በመፅናቱ ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ ችሏል፡፡

በሰበር ቅሬታቸውም ላይ ለይርጋ ጊዜ መነሻ ሆኖ የሚያዘው ጊዜ የትኛው ሊሆን ይገባል የሚለውን አስመልክቶ የፍሬ ነገር ዝርዝር ክርክር ካቀረቡ በኋላ የእኔ ክስ የሥረ-ነገር ጥያቄ በሚል አገላለፅ ይጥቀሱት እንጂ የባለቤትነት ጥያቄ ነው በማለት ሁከት ይወገድ በሚለው አይወድቅም ስለሆነም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት የለውም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ተጠሪም በጊዜው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ለመመልከት ሥልጣን ለነበረው ፍ/ቤት ክሱን ማቅረባቸው ክሳቸው የሁከት ይወገድልኝ የሚል እንደነበረ በእራሱ አስረጂ ነው እንዲሁም ክሱ የመፋለም ሳይሆን የይዞታ ስለመሆኑ ብር 2000.00(ሁለት ሺህ) መገመታቸው ክሳቸው በሁከት ይወገድልኝ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመለክታል በማለት ለተያዘው አከራካሪ ጉዳይ አግባብነት ያለውን መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአመልካች የክስ ምክንያት ተለይቶ የታወቀ ንብረት ተወስዶብኛል፤ ይመለስልኝ የሚል እንደመሆኑ የክሱ አቀራረብ ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 226(3) እንደተመለከተው ትክክለኛ ዋጋው ተገምቶ ነገሩን አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት ሊቀርብ እንደሚገባ አመላካች ነው፡፡ በዚህ መሠረት መቅረብ ሲገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 1149(1) ሁከት የተነሣበት ሰው ሁከት እንዲወገድለት መጠየቅ ይችላል ከሚለው የህግ አነጋገር "ሁከት ይወገድልኝ" የሚለውን ለይቶ በገንዘብ ሊገመት እንደማይቻል ተደርጎ መቅረቡን ያሳያል፡፡

ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(1) ላይ ሁከት የተፈጠረበት ሰው ሁከት እንዲወገድለት፤ ይዞታው የተወሰደበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ሁለቱንም ዓይነት ሁኔታዎች ለያይቶ የደነገገ በመሆኑ የተወሰደን ነገር ለማስመለስ በሚል ዳኝነት ለመጠየቅ በተፈለገ ጊዜ ከላይ በተመለከተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 16፣ 226(3) መሠረት ትክክለኛ ዋጋው ተገምቶ ተገቢው ዳኝነት ተከፍሎበት የሥረ ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት የሚቀርብ እንጂ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድ ("cessation of interference") እንደሆነ ተቆጥሮ በገንዘብ የማይገመቱ አቤቱታዎች በሚቀርቡበት ሁኔታ ሊስተናገድ የሚችል እንዳልነበር ተገንዝበናል፡፡

ይህ ዓይነቱ በክስ አቀራረብ ረገድ የሚታየው ሥነ ሥርዓታዊ ግድፈት የሥረ ነገር ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ ጉዳዩ እንዳይታይ በማድረግ ብቻ ውጤቱ የተንፀባረቀ ሳይሆን በይርጋ ደንቦች አፈፃፀም ላይ ችግርን አስከትሏል፡፡

ከክርክሩ ዓይነት አንፃር ጉዳዩ በሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሥር ሊሸፈን የሚችል ባለመሆኑ ለዚህ ለተያዘው ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(2) የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ አግባብነት የሌለው መሆኑ እየታወቀ የክሱን ይዘት ሳይሆን የክሱን አርዕስት ብቻ በመመልከት የሥር ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌለውን የይርጋ ዘመን ተፈፃሚ በማድረጋቸው የህግ ስህተት መፈፀማቸውን ተረድተናል፡፡

በተጠሪ ክርክር ላይ እንደተገለፀው አከራካሪ የሆነው ንብረት በተጠሪ እጅ ከገባ 13 ዓመት አልፎታል የሚል ክርክር ስለቀረበ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(2) ተጠቅሶ ሁለት ዓመት አልፎታል ቢባልም ከ10 ዓመት (ከአስር ዓመት) በላይ ያለፈው መሆኑ ከተረጋገጠ በይርጋ ቀሪ መሆኑ ስለማይቀር የተለየ ለውጥ አያመጣም እንዳይባል የተወሰደ ንብረት ለማስመለስ እና የመፋለም መብትን ለማስከበር የሚቀርቡ ክሶች (petitory actions) በይርጋ ዘመን ቀሪ ሊሆን የማይገባበትን የህግ ትንታኔ በመስጠት ከዚህ ቀደም በዚህ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 43600 በሆነው ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677 እና 1845 መሠረት የተቀመጠው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜም ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሆኖ አይገኝም፡፡

በሌላ በኩል የክሱ አቀራረቡ ግድፈት በሥረ ነገር ሥልጣን ረገድ ያስከተለውን ሥነ-ሥርዓታዊ ስህተት በማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የማይታለፍ የመርህ ጉዳይ እንደመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ በየትኛውም ደረጃ ሊታረም ይገባል የሚለውን መሠረት በማድረግም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ በቀረበበት ዘመን በ1991 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ይህንን መሰል የባለቤትነት ጉዳይ ተቀብለው ለማስተናገድ የሚያስችላቸው ስልጣን ያልነበራቸው መሆኑ ቢታወቅም፤ እንዲሁም ክርክሩ የተነሣው በሁለት ግለሰቦች መካከል እንደመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/95 መሠረት ሥልጣን የሌላቸው ቢሆንም በክርክር ላይ የነበሩ ጉዳዮች በምን አኳኋን መስተናገድ እንደሚኖርባቸው በሚደነግገው የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ለማሻሻል በወጣው በአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 2(3) በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 66 ሥር የሚከተለው አንቀጽ 10 ተጨምሯል ካለ በኋላ በአንቀጽ 10 ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት በመታየት ላይ የነበሩና በአዋጅ ቁጥር 361/95 በከተማ ፍ/ቤት ዳኝነት ሥልጣን ሥር የማይወድቁ ጉዳዮች በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት መታየታቸው ይቀጥላል በሚል ምላሽ ስለተሰጠው ይህም ጉዳይ ከላይ በዝርዝር እንደህን አነጋገር ሁከት ይወገድልኝ በሚል ሥር የማይወድቅ በመሆኑ ከጅምሩም ቢሆን በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ባይሆንም ክርክሩ ሳይቋጭ በክርክር ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ ከላይ በተመለከተው አዋጅ መሠረት አሁንም በተጀመረበት ፍ/ቤት የሚታይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 00257 በ3/2/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ 08247 በ15/7/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የከተማው ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/መ/ቁ 09744 በ06/2/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ዘመን ቀሪ ሊሆን የሚችል ባለመሆኑ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀሪው ጉዳይ ላይ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ይስጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡

በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ራ/ታ　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49200

ህዳር 1 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ጋሻው በጎሰው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አለበል መከተ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው በአማራ ክልል የላይ ጋይንት ወረዳ ፍርድ ቤት የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ወሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የቦታና የባህር ዛፍ አትክልት ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ከሳሽ ሆኖ የቀረበው የአሁን ተጠሪ ሲሆን የከሰሰውም አቶ ሲሳይ በጎሰውንና አቶ ጋሻው በጎ ሰውን ነው፡፡ ተጠሪ ከሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ሲሳይ በጎ ሰው ብር 1900 (አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር) ተበድሮ ቆይቶ ገንዘቡን ለመክፈል ባለመቻሉ ቦታውን ከእነ አትክልቱ በብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) ግምት አስረክቦኛል፡፡ ይህ ቦታ ለመንገድ ሲቀየስ ሁለተኛው ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ቦታውና ባህር ዛፍ የእኔ ነው በማለት 4,400 የባህርዛፍ ግምት እንዳይከፈለኝ ቦታው የእኔ ነው በማለት በቀበሌ አስተዳዳር በማመልከት ገንዘቡ እንዲያዝ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የባህርዛፉን አላባ እንዳልቀበል ቦታውም የእኛ ነው በማለት ሁከት የፈጠሩብኝ ስለሆነ በይዞታዬ ላይ የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተከሳሾች በበኩላቸው ተከሳሽ ብር 1900 ለሲሳይ በጎ ሰው ያበደረ መሆኑን በክሱ ገልጿል፡፡ ሆኖም የብድር ገንዘቡን ከሰጠኝ አስር ዓመት ያለፈ በመሆኑ ሊጠይቀኝ አይችልም የብድር ውሉ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በወቅቱ የዕዳ መክፈያ እንዲሆን የተዋዋልኩት ቦታና ባህርዛፍ አትክልት የተበዳሪው የአቶ ሲሳይ በጎ ሰው ሣይሆን የወንድሜ የጋሻው በጎ ሰው በመሆኑ ውሉ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሲሳይ በጎ ሰው መልስ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካች በበኩሉ በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ሆኖ ቀርቦ ቦታውም ሆነ ይዞታው የእኔ እንጅ የአንደኛ ተከሳሽ የሲሳይ በጎ ሰው አይደለም፡፡ ወንድሜ በተዋዋለውና እኔ ባልተስማማሁበት ሁኔታ እኔ የይዞታ መሬቴንና የባህርዛፍ አትክልቴን ለከሳሽ የምለቅበት ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ የቀረቡት ምስክሮችም ቦታውና ባህርዛፍ አትክልቱ የጋሻው በጎሰው ነው ነገር ግን አንደኛ ተከሳሽ ሲሳይ በጎሰው ለአሁን ተጠሪ ለሥር ከሳሽ



www.chilot.me

አለበል መከተ ሽጦለታል በማለት የመሰከሩ መሆናቸውን በውሣኔው ገልጿል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ሁከት ፈጥሮአል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅረቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርቦ የሰበር ችሎቱ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የባህር ዛፍ አትክልቱና ቦታው የእኔ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ካረጋገጠ በኋላ የእኔን አትክልት ግምት ወንድሜ ሲሳይ በጎሰው በተዋዋለው ውልና በተበደረው ገንዘብ መነሻ የአሁን ተጠሪ እንደወሰደ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ይዞታው የአቶ ሲሳይ በጎ ሰው ነበር፡፡ በብር 1900 /አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር/ ተበድሮ ባለመክፈሉ ቦታውንና አትክልቱን ተረክቤዋለሁ፡፡ የይዞታ የምስክር ወረቀትም አውጥቼበታለሁ ፡፡ አሁን ግን የባህርዛፍ ግምት ለእኔ ነው የሚገባው በማለት አመልካች ሁከት የፈጠረ በመሆኑ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ክስ አቅርቤ የተወሰነው በአግባቡ ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረባቸው ምስክሮች ይዞታው የማን እንደሆነ አናውቅም ገዝቶታል ሲባል ሰምተናል በማለት የመሠከሩ ሲሆን የእኔ ምስክሮች የእኔ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የላይ ጋይንት ወረዳ መሬት አስተዳደር ይዞታው የእኔ መሆኑን በማረጋገጥ ጽፏል ስለሆነም ይዞታው የእኔ እንጅ የሲሳይ በጎ ሰው ባለመሆኑ ተጠሪ ቦታውን በዕዳ መክፈያነት በውል ተቀብዬ ይዥዋለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላኘነውም፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠረ ስለሆነ ሁከቱ ይወገድ በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የወረዳው ፍርድ ቤት በአንድ በኩል የተጠሪ ጥያቄ የቦታ ባለቤትነት ጥያቄ ባለመሆኑ የቦታ ውሉን ማጣራቱ አስፈላጊ አይደለም በማለት በውሣኔው የገለፀ ሲሆን በሌላ በኩል ቦታው የጋሻው በጎሰው ነው ነገር ግን ሲሳይ በጎሰው ለተጠሪ ለመከተ ደምሴ በገንዘብ ሲሸጠው እናውቃለን በማለት የመሰከሩ መሆኑን በውሳኔው ገልፆል፡ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ሁከት ፈጥረዋል ወይም አልፈጠሩም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመያ ተጠሪ የቦታው ህጋዊ ባለይዞታ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ማጣራት አስፈላጊ ነው፡፡

ተጠሪ ቦታውን አገኘሁ የሚለው የአመልካች ወንድም አቶ ሲሳይ በጎሰው ብር 1900 /አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር/ ተበድሮኝ ይህንን ገንዘብ ባለመክፈሉ ቦታውንና የባህርዛፍ አትክልቱን በብር 1500 /አንድ ሺ አምስት መቶ ብር/ ተገምቶ በእዳ መክፈያነት በውል አግኝቸዋለሁ በማለት የሚከራከር ሲሆን አመልካች ከሲሳይ በጎ ሰው ጋር የእዳ መክፈያ እንዲሆን የተስማማሁበት ቦታና አትክልት የእኔ ይዞታ በመሆኑ ከውል የመነጨ መብት በቦታውና በባህርዛፍ ላይ ሊኖርህ አይችልም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

ተጠሪ ቦታውን አገኘሁ የሚለው ከማን እንደሆነ በራሱ አከራካሪ ቢሆንም ተጠሪ የቦታውን ባለይዞታ ሆንኩበት የሚለው ውል በቦታው ላይ ባለይዞታ ሊያደርገው የሚችለው ነው ወይስ



www.chilot.me

አይደለም? የሚለው መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ቦታውን የፍታብሔር እዳ መክፈያነት ተረክቤአለሁ የሚለው ክርክር በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሀብት ነው ተብሎ ከተደነገገው ድንጋጌ አንፃር ስናየው መሬትን ለዕዳ በመክፈያነት በውል በማስተላለፍ መሸጥና መለወጥ የማይቻልና በዚህ አይነት መንገድ ህጋዊ የመሬት ባለይዞታ መሆን የማይቻል በመሆኑ ተጠሪ የመሬቱ ባለይዞታ ሆኘበታለሁ የሚለው ውል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ህጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የተደረገ ባለመሆኑ ውሉ ህጋዊ ውጤት የሌለውና መብት የማያስገኝ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ምስክሮች ይዞታው የአመልካች መሆኑን ነገር ግን ወንድሙ ለተጠሪ አባት የሸጠ መሆኑን እናውቃለን በማለት የመሰከሩ መሆኑን በውሣኔው ገልጿል፡፡ ይዞታውና የባህርዛፍ አትክልቱ የአመልካች መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች ወንድሙ ሲሳይ በኀ ሰው ባደረገው ውል ሊገደድ የሚችለው አመልካች እሱን ወክሎ ውል እንዲዋዋል የሰጠው የውክልና ሥልጣን ካለና ወንድሙ ሲሳይ በኀ ሰው በዚህ በውክልና ሥልጣኑ መሠረት ውል የተዋዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አቶ ሲሳይ በኀ ሰው ውሉን የተዋዋለው ከአመልካች ባገኘው የውክልና ሥልጣን መሆኑን አላስረዳም፡፡ ስለዚህ አመልካች ባልተስማማበትና በቦታው ላይ ያለው የባህር ዛፍ አትክልት ለወንድሙ ዕዳ መክፈያ እንዲሆን ስምምነቱን ባልገለፀበት ሁኔታ ወንድሙ በተዋዋለው ውል መነሻ ቦታውንና አትክልቱን ለተጠሪ እንድለቅና በተጠሪ ላይ ሁከት እንዳይፈጥር ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በቦታዬና በንብረቴ ላይ ሁከት ተፈጥሮብኛል ብሎ ክስ ለማቅረብ በመጀመሪያ የቦታውና የንብረቱ ህጋዊ ባለይዞታ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ምስክሮች ይዞታው የአመልካች መሆኑን እንደመሠከሩና ቦታውን ከነባህርዛፉ ለተጠሪ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሲሳይ በኀሰው በገንዘብ ሸጦለታል የሚል የምስክረነት ቃል እንዳስመዘገቡ የወረዳው ፍርድ ቤት በውሳኔው ገልፆታል፡፡ ይኸም ተጠሪ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገውን የሚጥስ ተግባር በመፈፀምና የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታ ካልሆነው አቶ ሲሳይ በኀሰው መሬቱን በዕዳ መክፈያነት በውል ይዣለሁ በማለት የሚከራከሩ መሆኑንና የቦታው ህጋዊ ባለይዞታ የማያደርጋቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ አመልካች በተጠሪ ህጋዊ ይዞታ ላይ ሁከት ፈጥሯል በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል የላይ ጋይንት ወረዳ ፍርድ ቤት የደቡብ ጐንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በዚህ ክርክር ተሣታፊ ካልሆነውና በሥር አንደኛ ተከሳሽ በነበረው አቶ ሲሳይ በኀ ሰው በብድር ሰጥቸዋለሁ የሚለውን ገንዘብ እንድከፍለው ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ ይህ ውሣኔ አያግደውም ብለናል፡፡



www.chilot.me

3. አመልካች የቦታውና የአትክልቱ ሕጋዊ ባለይዞታ በመሆኑ በተጠሪ ላይ የፈጠረው ሁከት የለም በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57271

ታህሣሥ 27 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች፣*** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች -*** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - መላኩ ነገሡ ቀረበ

***ተጠሪ -*** ጃዳ ብሩ ከጠበቃ ደጀኔ ፋይሳ ጋር ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በመንገድ ሥራ ምክንያት ለተወሰደ ንብረት ካሣ ይከፈል ዘንድ በመጠየቅ የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች እና በሞጆ ከተማ አስተዳደር ላይ ክስ የመሠረተው በሞጆ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ በ400 ካ.ሜትር ቦታ ላይ ያለኝን የንግድ ቤት በሚሠራው መንገድ ምክንያት እንደሚነሳ ነግረውኝ የንብረቱን ግምት ብር 46614 እንድወሰድ ያዘዙልኝ ቢሆንም ግምቱ ትክክል ባለመሆኑ አልወሰድኩም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ንብረቱን በግል ባለሙያ አስገምቼ ብር 119,367 ዋጋ እንዳለው አረጋግጫለሁ፡፡ በመሆኑም ንብረቱ በሶስተኛ ወገን ባለሙያ እንዲገምትልኝ እና በዚሁ መሠረት ካሣው እንዲከፈል ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ከዚሁ በተጨማሪም በተወሰደው ቦታ ምትክ ሌላ ቦታ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄም አንስቶ እንደነበር ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ፍ/ቤቱ የሁሉንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኃላ ንብረቱን እንደገና አስገምቶ ተገኘ ባለው ውጤት መሠረት ካሣ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የካሣው ክፍያ ጥያቄ በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት የሚቀርብበት አግባብ አለ ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ጭብጡን በማስመልከት ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ ባጭሩ እንዳመለከትነው አመልካች ለተጠሪ የሚከፈለውን ካሣ በማስገመት ገንዘቡን እንዲወስድ አስቀድሞ አስታውቆታል፡፡ ተጠሪ ደግሞ የካሣው መጠን አንሶአል የሚል እምነት በመያዙ በቀጥታ ለፍ/ቤት ክሱን አቅርቦአል፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የሕግ ጥያቄ የተነሳውም እዚህ ላይ ነው፡፡ ተጠሪ የካሣው መጠን አንሶአል የሚል እምነት ወይም ተቃውሞ ካለው ይህን

ተቃውሞውን ማቅረብ የነበረበት በምን አግባብ ነው የሚለው ጭብጥ ነው በሰበር ችሎቱ ውሣኔ የሚያሻው ሆኖ የተገኘው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ግልጽ የሆነ የመከራከሪያ ነጥብ አቅርቦአል፡፡ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብ ያለው ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁ 455/97 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ካሣን በሚመለከት ስለሚቀርብ አቤቱታ እና ይግባኝ ተደንግጓአል፡፡ የከተማ መሬት ይዞታውን እንዲለቅ የሚደረግ ባለይዞታ በተወሰነለት የካሣ መጠን ላይ ካልተስማማ ወይም በካሣው መጠን ላይ ቅሬታ ካለው አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት በከተማው አስተዳደር ለተቋቋመው የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አስተዳደራዊ አካል ስለመሆኑም በዚሁ አንቀጽ 11/2/ ተመልክቶአል፡፡ የካሣውን መጠን በሚመለከት ለመደበኛ ፍ/ቤት ክርክር ወይም አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው በንዑስ አንቀጽ /4/ በተደነገገው መሠረት በይግባኝ ብቻ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ጉዳዩ የተነሳው በከተማ ክልል ውስጥ እንደመሆኑ ይህን በሚመለከት በተቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ክርክሩ መታየት እንዳለበት የሚያከራክር አይደለም፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዋጁ መሠረት እንደሆነ መገንዘቡን ከውሣኔው ተመልክተናል፡፡ ይህን እየተገነዘበም ነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ ሊሰጥ የቻለው በመሠረቱ ፍ/ቤቶች ሊመሩ የሚገባቸው በሕጉ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ሕጉን መሠረት ያላደረገ ውሣኔ እንዲሰጡ አይጠበቅም፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው ግን ሕጉን በመተው ነው ውሣኔ የተሰጠው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

***<u>ው ሣ ኔ</u>***

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22818 መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 53814 ሰኔ 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በካሣው መጠን ላይ በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ማቅረብ በሕጉ አልተፈቀደም ብለናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47526

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ዛፍኮ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ዜና ደባሱና አቶ

ታምሩ ወንድምአገኘሁ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ብሔራዊ መሐንዲሶች ስራ ተቋራጭ ድርጅት - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ ሆነው የተከራከሩ ሲሆን በሌላ በኩል አመልካች የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በማቅረቡ አመልካች የተከሣሽ ከሣሽ ተጠሪ የከሣሽ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጉዳይ የግንባታ ስራ ውል አፈጻጸምና ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡

1. ጉዳዩ የተጀመረው ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ መጋቢት 4 ቀን 1984 ዓ.ም በተደረገና ሐምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም በተሻሻለ ውል ለተከሣሽ የግንባታ ስራ የሰራ መሆኑንና በግንባታው ሂደት በአሰሪው የተሰጠ የስራ ለውጥ ትዕዛዝና ተጨማሪ ስራ ምክንያት ሶስት ስምምነቶችን በመፈራረም ስራውን የሰራ መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪ /ከሣሽ/ ጥር 1 ቀን 1988 ዓ.ም የምድር ቤቱንና ቤዝመንቱን ለተጠሪ ያስረከበ መሆኑንና ከአንደኛ ፎቅ እስከ አምስተኛ ፎቅ ያለውን ስራ በማጠናቀቀ መጋቢት 20 ቀን 1988 ዓ.ም ማስረከቡንና የተከሣሽ /አመልካች/ አማካሪ መሐንዲስ ብር 644,216.37 /ስድስት መቶ አርባ አራት ሺ ሁለት መቶ አስራ ስድስት ብር ከሰላሣ ሰባት ሣንቲም/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ለመጨረሻ የክፍያ ሰርተፊኬት ጽፏል፡፡ አመልካች የእሱ ተቀጣሪ በሆነው አማካሪ መሀንዲስ የተሰጠውን የክፍያ የምስክር ወረቀት በመቃወም በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተከሣሽ አማካሪ

መሀንዲስ በክፍያ የምስክር ወረቀት የገለጻቸው ክፍያዎች ለከሣሽ ሊከፍሉት የሚገባ ክፍያዎች መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠውን የመጨረሻ ክፍያ ከነወለዱና ለመያዣና ለመልካም ስራ አፈጻጸም የተያዘውን ገንዘብ ከነ ወለዱ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ተከሣሽ ብር 2,144,107.60 /ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ አራት ሺ አንድ መቶ ሰባት ብር ከስልሣ ሣንቲም/ እንዲከፍለው ጠይቋል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ጉዳዩ በሽምግልና ሣይታይ ለፍርድ ቤት መቅረብ አይገባውም የሚል መከራከሪያ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሣሽ 589 ቀናት የዘገየ በመሆኑ መቀጫ ገንዘብ የመክፈል ሃላፊነት አለበት ከሣሽ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ የግንባታ ስራውን አልሰራም፡፡ ከጊዜዊ እርክክብ በኋላ የተለያዩ ጉድለቶችን ለማስተካከል ወጭ አውጥቻለሁ፡፡ አማካሪ መሐንዲስ የመጨረሻ ክፍያ የማጽደቅ ስልጣን ያሌለው በመሆኑ የከሣሽ /ተጠሪ/ ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

2. አመልካች በበኩሉ አሻሽሎ ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የከሣሽ ተከሣሽ /ተጠሪ/ የግንባታ ስራውን ሐምሌ 6 ቀን 1986 ዓ.ም በማጠናቀቅ ማስረከብ ሲገባው አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ቀናት ግንባታውን አዘግይቷል፡፡
   ስለሆነም የከሣሽ ተከሣሽ የግንባታ ስራ ውሉን ላዘገየበት 10% ቅጣት ብር 662,679.59 /ስድስት መቶ ስልሣ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ብር ከሀምሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ ሊከፍል ይገባዋል፡፡ የህንጻ ስራው በመዘግየቱ ህንጻውን በማከራየት አገኘው የነበረውን ገቢ ቀርቶብኛል፡፡ እንዲሁም ለባንክ የተከፈለው ወለድ የከሣሽ ተከሣሽ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡ የከሣሽ ተከሣሽ ስራውን በሚፈለገው ጥራት ደረጃ ባለመስራቱ ጉድለቱን ለማስተካከል የወጣውን ወጭ መሸፈን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም የከሣሽ ተከሣሽ /ተጠሪ/ ብር 5,823,704.26 /አምስት ሚልዮን ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ሺ ሰባት መቶ አራት ብር ከሃያ ስድስት ሣንቲም/ ለተከሣሽ ከሣሽ /ለአመልካች/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡
   ተጠሪ የከሣሽ ተከሣሽ በመሆን የህንጻ ስራው ማጠናቀቂያ ጊዜ የተራዘመው በስምምነት በመሆኑ ከህንጻ ስራው ማጠናቀቂያ ጊዜ ጋር በማያያዝ የተከሣሽ ከሣሽ ያቀረቡት የቅጣት ክፍያና የጉዳት ካሣ ክፍያ የህግ መሠረት የለውም፡፡ የከሣሽ ተከሣሽ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ስራውን ሰርቶ አስረክቧል፡፡ አለ የተባለውን ጉድለት ለማስተካከል ተገቢውን ጥረት አድርጐ በተከሣሽ ከሣሽ እንቢተኛነት የቀረ በመሆኑ በሀላፊነት ልጠየቅ አይገባም፡፡ የተከሣሽ ከሣሽ ጉድለትን ለማስተካከል አወጣሁ የሚሉትን ወጭ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ክሣቸው ሙሉ በሙሉ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን ለማጠናከር በቃልና በጽሁፍ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች /ተከሣሽ/ የከሣሽ /የተጠሪ/ ክስን በመቃወም የቀረበውን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ በብይን ውድቅ አድርጐታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሣሽ /ተጠሪ/ ህንጻውን በአግባቡ ሰርተው ያስረከቡ መሆኑን በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ /አመልካች/ ከሣሽ የጠየቀውን የመጨረሻ ክፍያ ብር 644,216.37 /ስድስት መቶ አርባ አራት ሺ ሁለት መቶ አስራ ስድስት ብር ከሰላሣ ሰባት ሣንቲም/ ከነወለዱ የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡ ነሐሴ 29 ቀን 1984 ዓ.ም የተደረገው የግንባታ ስራ ውል ስምምነት ሀምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም በተደረገው ውል ተሻሽሏል፡፡ ከዚህ በኋላ የተከሣሽ ከሣሽ /አመልካች/ መስከረም 26 ቀን 1987 ዓ.ም ግንቦት 28 ቀን 1987 ዓ.ም እና ጥር 9 ቀን 1988 ዓ.ም በሰጠው የስራ ለውጥ ትዕዛዝና ተጨማሪ የግንባታ ስራ ትዕዛዝ መሠረት የስራ ውል ማጠናቀቂያ ጊዜ ግራ ቀኙ ቃለጉባኤ በመያዝ የተስማሙ በመሆኑና የከሣሽ ተከሣሽ ስራውን በተሻሻለው የጊዜ ገደብ ውስጥ

ስላጠናቀቁ የከሣሽ ተከሣሽ የተከሣሽ ከሣሽ የጠየቀውን መቀጫና የጉዳት ካሣ ክፍያ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም፡፡ ከሣሽ ለተከሣሽ ስራውን ሰርቶ ካስረከበ በኂላ የእምነበረድ ስራው የረገፈ መሆኑን የተከሣሽ ከሣሽ በተሻለ ማስረጃ አስረድቷል፡፡ ስለሆነም ጉድለት ያለበት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠው የዕምነበረድ ስራ በካሬ ሜትር ብር 238 ታስቦ የ2040.64 ካሬ ሜትር እንደገና ለመስራት የሚያስፈልገው ብር 485,672.32 /አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰላሳ ሁለት ሣንቲም/ የከሣሽ ተከሣሽ /ተጠሪ/ ለከሣሽ ተከሣሽ /አመልካች/ የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም የከሣሽ ተከሣሽ ለመልካም ስራ አፈጻጸምና መያዣ ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ የእምነበረድ ስራውን ለማስተካከል የሚያስፈልገው ብር 485,672.32 ቀንሶ የተከሣሽ ከሣሽ ብር 28, 663.68 /ሀያ ስምንት ሺ ስድስት መቶ ስልሣ ሶስት ብር ከስልሣ ስምንት ሣንቲም/ ለከሣሽ ተከሣሽ ሊከፍል ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

4. አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የአመልካችና የተጠሪ ክርክር በሽማግሌ እየታየ እያለ በፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን በግልጽ ያቀረብኩትን ተቃውሞ የስር ፍርድ ቤት ማለፋ የሥነ ሥርዓት ህግ ግድፈት ነው፡፡ በህግና በውል የተደነገገውን የግንባታ ስራ ውል ማጠናቀቂያ ጊዜ በተለያየ ጊዜ በተያዙ ቃለ ጉባኤዎች ተራዝሟል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የአመልካች አማካሪ መሀንዲስ በግንባታ ስራዎች መመሪያ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ የመጨረሻ ክፍያ ሰርተፍኬት ያለአመልካች ፈቃድና ስምምነት ለተጠሪ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡

የስር ፍርድ ቤት አማካሪ መሀንዲስ ከስልጣኑ ወጭ ባጸደቀው የመጨረሻ ክፍያ የምስክር ወረቀት መሠረት አመልካች ለተጠሪ ክፍያ እንዲፈጽም መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የልዩ አዋቂ ምስክርነት ቃል ሣይመዝነው ማለፋ ተገቢነት የለውም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ የተዘረዘረው ጉድለት ያለበትን ውሣኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የራሱ ወኪል የሆነው አማካሪ መሀንዲስ ያዘጋጀውን የክፍያ የምስክር ወረቀት በመቃወም ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አቤቱታ አቅርቦ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአማካሪ መሀንዲሱ ያዘጋጀው የክፍያ የምስክር ወረቀት ጉድለት ያሌለበት መሆኑን በመግለጽ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈጸምለት የአፈጻጸም ክስ አቅርቦ አመልካች ጉዳዩ መወሰን ያለበት በፍርድ ቤት ነው የሚል መቃወሚያ በማቅረቡ የአፈጻጸም መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ አመልካች ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ ጉዳዩ በሽምግልና ሊታይ ይገባል በማለት ያቀረቡት ተቃውሞ የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካችና ተጠሪ ውል የተዋዋሉበት መሠረታዊ ጉዳይ የማይንቀሣቀስ ህንጻ ስራ ግንባታ ውል ነው፡፡ አመልካች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ልዩ የህግ ክፍል ሣይሆን ስለ ውሎች በጠቅላላው የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 24 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የግንባታው ማጠናቀቂያ ጊዜ የተለወጠ መሆኑን አምኖ መልስ ከሰጠ በኂላ አመልካች የስራ ለውጥ ትዕዛዝና የተጨማሪ ግንባታ ስራ ትዕዛዝ ለመፈጸም የሚያስፈልገው የጊዜ መጠን ላይ በመስማማት ስራው ከተከናወነ በኂላ የግንባታ ስራ ማጠናቀቂያ ጊዜው አልተራዘመም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ የግንባታ ስራ የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ ለመቀየር የሚደረግ ስምምነት በተለየ ፎርም እንዲሆን ህግ አያስገድድም፡፡ አመልካች ያቀረበው



www.chilot.me

የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት አረጋግጠው የወሰኗቸው ፍሬ ጉዳዮች የሚደግፍ እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆኑን የማያመላክት በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ እንዲሆንልኝ በማለት ሚያዝያ 8 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አቅርቧል አመልካች መስከረም 28 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩ አመልካችና ተጠሪ የግንባታ ስራው ስለሚጠናቀቅበት ጊዜ በመጀመሪያ ያደረጉት ስምምነት ተጠሪና የአመልካች አማካሪ መሀንዲስ በተለያየ ጊዜ ቃለ ጉባኤ በመያዝ ባደረጉት ስምምነት ተሻሽሏል በማለት አመልካች ያቀረቡት የተሻሻለ የከሣሽነት ክስ ውድቅ መደረጉ ተገቢ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1721፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1763 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1764 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ለመመርመር ጭብጥ ተይዞ ለሰበር ችሎት የቀረበ ነው፡፡ እኛም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ይህንን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
   5.1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ለሚከራከሩበት ጉዳይ ገዥነትና ተፈጻሚነት ያለው የህግ ክፍል የትኛው ነው? የሚለውን ነጥብ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ የግንባታ ስራውን የሚያጠናቅቅበት ጊዜ በህግ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ አልተሻሻለም በማለት የሚከራከረው ስለውሎች የተደነገገውን የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች በተለይም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1721፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1763 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1764 በመጥቀስ በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ከላይ የተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ ሆኖም የአመልካች ጠበቆች በስርና በሰበር ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ያቀረቡት ክርክርና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ህግ አውጭው የማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውልን በተመለከተ ገዥነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸዉ በማሰብ ከደነገጋቸው ልዩ የህግ ማዕቀፎችና በህግ ስልጣን የተሰጣቸው አስፈጻሚ አካላት ስለማይቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውል አውጥተው ተፈጻሚ ካደረጓቸው የአሰራር መመሪያዎች አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የማይንቀሣቀስ ንብረት ለመስራት የሚደረግ ውል ገዥነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው በማሰብ ህግ አውጭው ከደነገጋቸው የህግ ማዕቀፎች መካከል አንደኛው በፍታብሔር ህጉ አንቀጽ 3019 እስከ አንቀጽ 3040 የተደነገገው የሚገኘው ልዩ የህግ ክፍል ነው፡፡ "ስለማይንቀሣቀስ ንብረት ስራ ውል" በሚል ርዕስ ስር የተደነገጉት እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች የስራ "ተቋራጭነቱ ውል የተደረገው የህንጻን ስራ ለመስራት የተሰራውን ለማደስ ወይም አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማደራጀት የሆነ እንደሆነ ከዚህ በታች በተነገሩት ድንጋጌዎች የሚመራ ይሆናል" በማለት ህግ አውጭው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3019 ንኡስ አንቀጽ 1 በመደንገግ ለማይንቀሣቀስም ንብረት ግንባታ ስራ ውል ገዥነትና ተፈጻሚነት ያላቸዉ ልዩ የህግ ድንጋጌዎች መሆናቸዉን በግልጽ አውጇል፡፡

ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የስራ ውል አስመልክቶ የሚያቀርባቸው ክርክሮች ለጉዳዩ ገዥነትና ተፈጻሚነት ያላቸዉ ልዩ የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ሣይሆን ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ እንዲታይለትና እንዲወሰንለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡



www.chilot.me

የስራ ተቋራጭነት ውል ተፈጽሟል የሚባለው አሰሪውና የስራ ተቋራጩ ስለሚፈጽሙት ስራዎችና ስለ ዋጋው አከፋፈል የተስማሙ በሆነ ጊዜ እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 1 የሚደነግግ ሲሆን የስራው ተቋራጭ አሰሪው እያወቀ ስራዎቹን ለመስራት ጀምሮ እንደሆነ ወይም ከዋጋው ላይ አስቀድሞ ገንዘብ ተቀብሎ እንደሆነ ውል ለመኖሩ በቂ ማረጋገጫ ይሆናል በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ከላይ ከተገለጹት የህግ ድንጋጌዎች የምንረዳው የግንባታ ስራ ውል በልዩ ፎርም እንዲደረግ ስለማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውል የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያዙት ፣ መሆኑን ለመረዳት የሚቻል መሆኑን ነው፡፡

ይኸው የአመልካችና ተጠሪ ክርክርና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭበጥ የማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውል ልዩ ባህሪና ህግ አውጭው የማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውልን በተመለከተ ገዥነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸዉ በማሰብ የደነገጋቸውን ልዩ የህግ ድንጋጌዎች አግባብነት ያላቸዉ የህግ ማዕቀፎች መሠረት ያደረገ ከመሆኑ አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የማይንቀሣቀስ ንብረት ለመስራት የሚደረግ ውል አስመልክቶ ልዩ ተፈጻሚነትና ገዥነት ያላቸዉ ደንቦች ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3019 እስከ ፍታብሔር ህግ ቁጥር 3040 የተደነገጉት ድንጋጌዎች መሆናቸውን ህግ አውጭው "ስለማይንቀሣቀስ ንብረት የስራ ውል" በሚለው ክፍል " የስራ ተቋራጭነቱ ውል የተደረገው የህንጻ ስራን ለመስራት ፣ የተሰራውን ለማደስ ወይም አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማደራጀት የሆነ እንደሆነ ከዚህ በታች በተነገሩት ድንጋጌዎች የሚሰራ ይሆናል" በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3019 ንኡስ አንቀጽ 1 በግልጽ ደንግጓል፡፡ ስለማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውል አስረጅነት በልዩ ሁኔታ የተደነገገው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 1 የስራ ተቋራጭነት ውል አለ የሚባለው ሁለቱ ወገኖች /አሰሪውና የስራ ተቋራጩ /ስለሚፈጸሙት ስራዎችና ስለዋጋው የተስማሙ በሆነ ጊዜ እንደሆነ የሚደነግግ ሲሆን የስራው ተቋራጭ አሰሪው እያወቀ ስራዎቹን ለመስራት ጀምሮ እንደሆነ ወይም ከዋጋው ላይ አስቀድሞ ገንዘብ ተቀብሎ እንደሆነ ውል ለመኖሩ በቂ ማረጋገጫ እንደሚሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡

የሚሰራውን የግንባታ ስራ አይነትና መጠን እንደዚሁም ስራው ስለሚጠናቀቅበት ጊዜ መጋቢት 4 ቀን 1984 ዓ.ም በጽሁፍ ያደረጉት የስራ ውል ሐምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም ያሻሻሉት መሆኑን የስር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከዚህ በኋላ የአመልካች ወኪልና አማካሪ መሀንዲስ ከተጠሪ ጋር በመስማማትና ቃለ ጉባኤ በመያዝ የሰጣቸው የስራ ትዕዛዝ ለውጦችና ተጨማሪ የግንባታ ስራዎች ስለመኖራቸውና በአሰሪው ወኪል ለውጥ የተደረገውን ስራዎችና የስራ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው ተጨማሪ የግንባታ ስራዎች ለማከናወን የሚያስፈልገው ተጨማሪ ጊዜ የመጀመሪያው የስራ ውል በተደረገበት ፎርም መሠረት የተደረገ ባለመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1721ን በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ከላይ ሙሉ ይዘታቸው ከተገለጸው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ድንጋጌዎች አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የግንባታ ስራ ውል መጠን ፣ ክፍያና የግንባታ ስራ ውል የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ለማሻሻል አሰሪውና የስራ ተቋራጩ የተስማሙ መሆናቸውን ለማስረዳት የመጀመሪያው የስራ ውል በተደረገበት አይነት የተጻፈ ውል ማቅረብ ግዴታ እንዳልሆነ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ይዘት ፣ መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአሰሪው ተወካይ የሆነው አማካሪ መሀንዲስ በየዕለቱ የሚሰጣቸው የስራ ትዕዛዞች



www.chilot.me

የሚጽፋቸው ማስጠንቀቂያዎችና ከስራ ተቋራጩ ጋር የተስማማባቸው ሰነዶች የማይንቀሣቀስ ንብረት ግንባታ ስራ ውል ልዩና ውስብስብ ባህሪ አንጻር የስራ ተቋራጩን መብትና ወይም ግዴታ ለማስረዳት ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች እንደሆኑ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ስለግንባታ ስራ አፈጻጸም ባወጣው መመሪያ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች በወኪሉ አማካኝነት በተለያየ ጊዜ ከስራ ተቋራጭ ከሆነው ተጠሪ ጋር በማስማማትና ቃለ ጉባኤ በመያዝ የሰጣቸው የስራ ለውጥ ትዕዛዞችና ተጨማሪ የግንባታ ስራ ትዕዛዞችና የለወጣቸውን ስራዎችንና ተጨማሪ የግንባታ ስራውን ለማከናወን ተጠሪ የሚያስፈልገውን ጊዜ በሚመለከት ያደረጓቸው ስምምነቶች የመጀመሪያው የግንባታ ስራ ውል በተደረገበት ፎርም መሠረት የተከናወኑ ባለመሆኑ ህጋዊ ውጤት የላቸውም በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1721 በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

5.2. አመልካች የግንባታ ስራውን እንደ እሱ ሆኖ እንዲከታተሉለት የመደበው አማካሪ መሀንዲስ በተለያየ ጊዜ ከተጠሪ ጋር በተያዘ ቃለ ጉባኤ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ የሰጠና የተጨማሪ ግንባታ ስራ እንዲሰራ የተስማማ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በግንባታው ሂደት ለተደረገ የስራ ለውጦችና ተጨማሪ የግንባታ ስራዎች ተጨማሪ ክፍያ ሲፈጽም የቆየ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የሰጠው የስራ ለውጥና የተጨማሪ ስራ ትዕዛዝ ተጨማሪ ስራ የሚያስከትል በሆነ ጊዜ በስራው መጠን የስራ ተቋራጩ ተጨማሪ ክፍያ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3032 ንኡስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ አሰሪው የስራ ተቋራጩን ሀላፊነት የሚያከብድ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ ወይም ተጨማሪ የግንባታ ስራ በሚያዝበት ጊዜ የተለወጠውን የግንባታ ስራ ወይም ተጨማሪ የግንባታ ስራ ለመስራት ተጨማሪ ክፍያ /ገንዘብ/ ብቻ ሣይሆን ተጨማሪ ጊዜ የማያስፈልገው በመሆኑ አመልካች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1763 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥት 1764 በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር የማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ በአሰሪው ትዕዛዝ ስለማለውጥበት ወይም ተጨማሪ የግንባታ ስራ ትዕዛዝ በሚሰጥበት ወቅት የስራ ተቁራጩ የተቀያየረውንና በተጨማሪነት የተሰጠውን የግንባታ ስራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነ ጊዜና ገንዘብ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን በፍ.ሕ፤ቁ. 3032 የተደነገገውን በግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 4 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት የህንጻ ግንባታ ስራ ውል ሀምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም ያሻሻሉት መሆኑንና ከዚህ ጊዜ በኋላ አመልካች በወኪሉ አማካኝነት በሰጠው የስራ ትዕዛዝ ለውጥና የተጨማሪ ግንባታ ስራ ትዕዛዝ ምክንያት በተለያየ ጊዜ በቃለ ጉባኤ በመስማማት የግንባታው ስራ ማጠናቀቂያ ጊዜውን ያሻሻሉት በመሆኑ ተጠሪ በውሉ መሠረት የሚከፍለው ቅጣትም ሆነ የጉዳት ካሣ የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

5.3. አመልካች አማካሪ መሀንዲሱ የመጨረሻ ክፍያ የምስክር ወረቀት የማጽደቅ ስልጣን የሌለው መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አማካሪ መሀንዲሱ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ባዘጋጀው የክፍያ የምስክር ወረቀት የተመለከተውን ገንዘብ እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት አመልካች ወኪሉ በሆነው አማካሪ መሀንዲሱ ባዘጋጀው የመጨረሻ የክፍያ የምስክር ወረቀት የዘረዘረውን ክፍያ እንዲፈጽም የወሰነው ፣ የአመልካች

አማካሪ መሀንዲስ የመጨረሻ ክፍያ በተናጠል የማጽደቅ ስልጣን አለው ከሚለው መደምደሚያ በመድረሱ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የወሰነው አመልካች ክፍያውን አልፈጽምም የሚልበት ህጋዊ ምክንያት ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ተአማኒነት ያለው ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑንና ተጠሪ ክፍያ የጠየቀበትንና በአመልካች አማካሪ መሀንዲስ የክፍያ የምስክር ወረቀት የተዘረዘረውን ስራ በአግባቡ ያከናወነና ክፍያውም የሚገባው መሆኑን በማስረጃ ያስረዳ መሆኑን በግልጽ በማስፈር እንደሆነ የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልጽ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የግንባታ ስራውን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ለአመልካች ያስረከበ መሆኑንና ተጠሪ ለአመልካች ሰርቶ ካስረከበው ስራ ውስጥ ጉድለት የተገኘበት የእምነበረድ ስራ ብቻ መሆኑ አመልካች ባቀረበው የከሣሽ ከሣሽነት ክስ በተደረገው ክርክርና በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣኑን በመጠቀም ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ የእምነበረድ ስራውን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ባለመስራቱ አመልካች ጉድለቱን ለማስተካከል ሊያወጣ የሚችለውን ወጭ ተጠሪ ለመልካም አፈጻጸምና ለመያዣ ካስያዘው ገንዘብ ቀንሶ እንዲያስቀር የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
ስለሆነም ተጠሪ አማካሪ መሀንዲሱ ባዘጋጀው የመጨረሻ የክፍያ ሰርተፊኬት የገለጸውን የስራ መጠንና ዋጋ ያለው ስራ የሰራ መሆኑን በማስረጃ እንዳስረዳ በማረጋገጥ አመልካች ተጠሪ ለሰራው ስራ ክፍያ እንዲፈጽም የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር ባስቀምጥናቸው ምክንያቶች የአመልካች ክርክር ስለማይንቀሣቀስ ንብረት ግንባታ ስራ ተፈጻሚነት ያላቸውን ልዩ የህግ ድንጋጌዎችና የአሰራር መመሪያዎች መሠረት ያላደረገ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60720

ግንቦት 15 ቀን 2003

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሄሪያ መሐመድ ግርግቦ - ጠበቃ አምሣለ ፀሐዬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሽምሱ የሱፍ ጠበቃ በሻዳ ገመቹ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከመነሻው የስም መመሳሰልን መሠረት በማድረግ በሐሰተኛ ማስረጃ የተከናወነ የማይንቀሳቀስ ንብረት / መኖሪያ ቤት / ሽያጭ ውል ላይ የተደረገን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች የፍርድ ባለመብት በመሆን መብታቸውን ከአስከበሩ በሁዋላ የአሁኑ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ መታየት የጀመረ ነው፡፡

የተጠሪ የውሣኔ መቃወሚያ አቤቱታ ይዘትም፡- በወረዳ 25 ቀበሌ 04 ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 1413 የሆነውንና አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ ውሣኔ ባገኘው መኖሪያ ቤት ሐምሌ 25 ቀን 1998 ዓ/ም በውልና ማስረጃ በተደረገ የሽያጭ ውል የባለሃብትነት መብት ማቋቋማቸውንና ካርታው በስማቸው ተሰርቶላቸው ቤቱን ተረክበው ይዘው እንደሚገኙ በቤቱ ላይ አመልካች የፍርድ ባለመብት መሆናቸውንም ግንቦት 03 ቀን 2001 ዓ/ም በቤቱ ላይ ከተለጠፈው ማስታወቂያ ማወቃቸውን ገልፀው ቀድሞ በቤቱ ላይ ሚያዝያ 08 ቀን 1995 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እንዲነሳላቸውና ባለሃብትነታቸው እንዲረጋገጥላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ አቤቱታ በሰጡት መልስም ተጠሪ ውሣኔውን ለመቃወም የማይችሉ መሆኑን የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት መሆናቸው በፍርድ የተረጋገጠና ተጠሪም ከሕግ ውጪ አግኝቼበታለሁ በሚሉት ማስረጃ መሠረት ባለሃብት ሊሆኑ እንደማይችሉ ቤቱን ከመነሻውም ባለሃብት ያልሆኑት ወ/ሮ ሄሪያ መህመድ ኢብራሂም ለአቶ ሙዲ የሱፍ በመሸጥ አቶ ሙዲ የሱፍ ለተጠሪ መሸጣቸው ተግባሩን ሕጋዊ ሊያደርግ አይችልም በማለትና ቤቱ ለተጠሪ የተላለፈበትን መንገድ ሕገ ወጥ መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ፍሬ ነገሮችን በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ተጠሪ ቤቱን በውል እና ማስረጃ ፤ ከአቶ ሙዲ የሱፍ መግዛታቸውና በስማቸውም ካርታ ተሰርቶላቸው ቤቱን ይዘው የሚገኙ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ካርታውን የሰጠው አካል እስካልሰረዘው ድረስ ተጠሪን ባለሃብት ነው ብሎ ለመቁጠር የሚያስችል ነው የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ ቀድሞ አመልካች



www.chilot.me

የአከራካሪው ቤት ባለቤት ናቸው ሲል የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 360/2/ መሠረት ሰርዞታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ጸንቷል፡፡ አሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መስከረም 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የአመልካች ስለመሆኑና ለተጠሪ ሽያጭ ፈጸሙ የተባሉት ሰው ምንም አይነት መብት የሌላቸው መሆኑን፣ ተጠሪ የሽያጭ ውሉን የፈፀሙት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መሆኑ በተለያዩ ጊዜአት በተሰጡት የፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች በግልፅ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ስመ ሃብቱን በአስተዳደር አካሉ በተሰጠው ካርታ አስመዝግበዋል ተብሎ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት ናቸው ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አቶ ሙዲ የሱፍ የንብረቱ ባለቤት አይደሉም ተብሎ በተለያዩ መዛግብት ተወስኖ እያለ ለአሁኑ ተጠሪ በህጋዊ መንገድ እንደተሸጠ ተቆጥሮ የቤቱ ባለሃብት ተጠሪ ናቸው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአከራካሪው ቤት ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ታህሣሥ 20 ቀን 1987 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መሆኑን አመልካች ክስ የመሰረቱትም፡- 1ኛ/ በአቶ ሙዲ የሡፍ ፤ 2ኛ/ በመቶ አለቃ ሲሳይ መብራቱ ፤ 3ኛ / የሥጋ ሜዳ ተራራ የመኖሪያ ቤቶች የኅብረት ሥራ ማህበር ፣ 4ኛ/ በአቶ ከማል ሀምዛ እና 5ኛ/ በወ/ሮ ሄሪያ መሀመድ ኢብራሂም ላይ መሆኑን ፣ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሮ አቶ ሙዲ የሱፍ ቤቱን የያዙት ቤቱን ለመሸጥ ምንም መብት ከሌላቸው ሰው ስለሆነ ሽያጩ የተከናወነውም በሀሰተኛ ሰነድ በመጠቀም ስለሆነ ውሉ ሊፈፀም የሚቻል አይደለምና ፈራሽ ነው በማለት ቤቱን ለአሁኗ አመልካች እንዲመልሱ ሲል ሚያዝያ 08 ቀን 1995 ዓ/ም በዋለው ችሎት መወሰኑን ፣ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት የስር ተከሣሾችም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተናጠል አቅርበው አቶ ሙዲ የሱፍ የተባሉት ግለሰብ ያቀረቡት ይግባኝ በመ/ቁጥር 20831 ሐምሌ 02 ቀን 1995 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውድቅ የሆነ ሲሆን አቶ ከማል ሀምዛ እና ወ/ሮ ሄሪያ መሀመድ ኢብራሂም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ ላይ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ሚያዝያ 08 ቀን 1995 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ መጋቢት 05 ቀን 1999 ዓ/ም በመ/ቁጥር 21687 ቢሻርም በዚህ ውሣኔ ላይ አሁኗ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሮ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29978 ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተመልሶለት ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም በመ/ቁጥር 21687 ጉዳዩን እንደገና አይቶ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ መጋቢት 23

ቀን 2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት ማጽናቱን በዚህ ውሣኔ አቶ ከማል ሀምዛ እና ወ/ሮ ሄሪያ መሀመድ ኢብራም ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በመ/ቁጥር 45100 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት መወሰኑን ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱ ላይ ሕጋዊ መብት አቋቋሜአለሁ የሚሉት ሐምሌ 25 ቀን 1998 ዓ/ም ከአቶ ሙዲ የሱፍ ጋር የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በቅን ልቦና በውልና ማስረጃ የተደረገና ከውሉ በሁዋላ በስሜ ካርታ ተሰርቶ ቤቱን ይዤው የምገኝ ነኝ በሚል ምክንያት እንጂ ቤቱን ሻጭ የሠሩት የግል ሀብታቸው መሆኑን የሚያሳይ ሕጋዊ ማስረጃ አለ አመልካችም የቤቱ ባለሃብት አይደሉም በሚል ምክንያት አለመሆኑን ተንገዝበናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው አንድን ንብረት ለሌላ ሰው በሕጋዊ መንገድ ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ መብት ሲኖረው መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በሕግ ጥበቃ የማይደረግለት ወይም የሌለ መብት ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው የሕግ መርሕ ነው፡፡ የሌላ ሰው ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ ሕጋዊ የሆነ ስልጣን ሊኖር ይገባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ለተጠሪ አካራካሪውን ቤት የሸጡት አቶ ሙዲ የሱፍም ሆነ ቤቱን ከመጀመሪያውኑም ለአቶ ሙዲ የሱፍ ሸጡ የተባሉት አቶ ከማል ሀምዛ እና ወ/ሮ ሄሪያ መሀመድ ኢብራሂም የአመልካችን ሕጋዊ ስምምነት ወይም ወራሽነት አግኝተው ባይሆንም የቤቱ ባለሃብት መሆናቸውን የሚያሳዩ ሐሰተኛ ሰነዶችን ይዘው የነበሩ መሆኑ ፣ አቶ ሙዲ የሱፍ ቤቱን ከገዙ በሁዋላ የቤቱን ስመ- ሀብት ከተገቢው የአስተዳደር አካል ከአገኙ በኋላ ለአሁኑ ተጠሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው ቤቱን የሸጡላቸው የቤቱ ስመ ሃብትም በተጠሪ ስም የተመዘገበ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሠረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሠጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማንቀሳቀስውን ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊገመት እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው የሕግ ግምት ፍፁም የሆነ ወይም ደምዳሜ ላይ መድረስ የሚያስችል ማስረጃ አይደለም፡፡ ግምቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔዎች ስለመኖራቸው በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው በአስተዳደር አካል የተሰጠ ካርታ በመያዙ ብቻ በካርታው የተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሕጋዊ ባለሃብት እንደሆነ ሕጉ ግምት ቢወስድለትም ይህ ግምት ግን ካርታው የተሰጠበትን አግባብ ከደንቡ ከአሰራሩና ከስልጣኑ ውጪ እንዲሁም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሠረት ማስረጃው ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ የሕጉን ሕሊናዊ ግምት ማፍረስ እንደሚቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበሩት አቶ ሙዲ የሱፍ ቤቱን የያዙትና ለየአሁኑ ተጠሪ ያስተላለፋት ሕጋዊ ካልሆኑ ሻጮች በመግዛት መሆኑና ለጉዳዩ የቀረቡት ሰነዶች ሁሉ ሕጋዊ ዋጋ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦ አቶ ሙዲ የሱፍ የቤቱ ባለሃብት ሊሆኑ አይችሉም ተብሎ በተለያዩ የክርክር ደረጃዎች የተወሰነ ከሆነ አቶ ሙዲ የሱፍ ለአሁኑ ተጠሪ የሸጡት ሽያጭ ሕጋዊ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ ውሉን በውልና ማስረጃ ማድረጋቸው ከመነሻው ሕገወጥ የሆነን ተግባር ሕጋዊ ሊያደርግ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በቅን ልቦ የተደረገ ነው ተብሎም በሕግ ጥበቃ የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው



www.chilot.me

በውሉ ለገዥው መድህን ለመሆን ግዴታ ገብቶ ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 997 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ አቶ ሙዲ የሱፍ በቤቱ ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን ያወቁት ሐምሌ 02 ቀን 1995 ሲሆን ለተጠሪ ቤቱን በውልና ማስረጃ የሸጡት ግን ሐምሌ 25 ቀን 1998 ዓ/ም የቤቱ ባለመብት ያለመሆናቸውን እያወቁ ነው፡፡ አቶ ሙዲ ለአሁኑ ተጠሪ መድህን ለመሆን ግዴታ የገቡበት ሁኔታም የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች ለረዥም ጊዜ በክርክር ላይ በነበሩበት ሁኔታና በፍርድ መብታቸው ተረጋግጦ እያለ የክርክሩ ተሳታፊ የነበሩት ሰዎች በፍርድ መሸነፋቸውን አውቀው በአከናወኑት የሽያጭ ውል ሕጋዊ ገዥ ናቸው ሊባሉ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት የገዙት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ባለመሆኑ ሽያጩ የተከናወነው ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት በመሆኑና ካርታውም በስማቸው ተሰርቶ ተሰጥቷል በሚል ምክንያት ብቻ የሽያጭ ውሉ ሕጋዊ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1/ የተከበረላቸው እና በፍትሓ ብሔር ሕጉ ስለንብረት በሚደነግጉት ድንጋጌዎች ጥበቃ የሚደረግለት የባለሃብትነት መብታቸው ከሕግ አግባብ ውጪ ስለመደረጉ በተረጋገጠዉ የሽያጭ ውል ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት ሳይኖር የበታች ፍርድ ቤቶች የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለሃብት ተጠሪ ናቸው፡፡ በማለት የቀድሞውን ውሣኔ በመሻር የሠጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04917 ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 88537 ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአከራካሪዉ ቤት ተጠሪ ሕጋዊ መብት የላቸውም ፣ ቤቱ የአመልካች ሕጋዊ ንብረት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሠ/መ/ቁ 63042

ግንቦት 1 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነገረ ፈጅ አቶ ደስታ ሊበን - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሰለሞን ነጋሽ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አመልካች የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የሚጣራ የህግ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታ ክርክር መነሻ የሆኑት ጉዳዮች በመጀመሪያ የታዩት በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104138 ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በቀድሞው አጠራር ወረዳ 22 ቀበሌ 07 የቤት ቁጥር 117 የሆነውንና ለሆቴል አገልግሎት የሚውል የድርጅት ቤት በወር ብር 27,942.95 /ሃያ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከዘጠና አምስት ሣንቲም/ ለመክፈል ተስማምተው በፈረሙት የኪራይ ውል መሠረት የአስራ ሁለት ወር /የአንድ ዓመት / የቤት ኪራይ መጠባበቂያ የሁለት ወር ኪራይ ፣ በድምሩ የአስራ አራት ወር ኪራይ ብር 442,288.61 /አራት መቶ አርባ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከስልሣ አንድ ሣንቲም/ ለተከሣሽ /አመልካች/ ከፍያለሁ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ የነበረበት በመሆኑና የቀድሞው ተከራይ ሁከት ስለፈጠረብኝ ቤቱን ለተከራየሁበት ዓላማ ማዋል አልቻልኩም፡፡ ስለሆነም አከራዩ አመልካች የከፈልኩትን ገንዘብ እንዲመለስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል አመልካች/ ተከሣሽ/ በተከራይነት ቀርቦ የአከራይነት ግዴታውን የተወጣ መሆኑን ገልፆ የኪራይ ውሉ የሚፈርስበትና ከሣሽ/ ተጠሪ/ የከፈለውን የቤት ኪራይ የምንመልስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104138 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና ክርክር በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 65504 ሰምቷል፡፡



www.chilot.me

በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ በመሆን ተጠሪ ላይ ክስ መስርቶ በመዝገብ ቁጥር 136416 የአመልካቾችና የተጠሪን ክርክር በመስማት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 7 ቀን 2001 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች ተከራዩ /ተጠሪ/ ከሀምሌ 17 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ቤቱን ይዘው ኪራይ ያልከፈሉ በመሆኑ በውሉ መሠረት ኪራይ መቀጫና ሌሎች ክፍያዎች ብር 171,487.63/አንድ መቶ ሰባ አንድ ሺ አራት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከስልሣ ሶስት ሣንቲም/ ሊከፍል ይገባል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የኪራይ ውሉ እንዲፈርስ ክስ አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቤአለሁ፡፡ ተጨማሪ ኪራይ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ/ ተከሣሽ/ አመልካች/ከሣሽ/ በክሱ የጠየቀውን ብር 171,487.63 እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 82009 ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 65504 ያቀረበውን ይግባኝ ከይግባኝ መዝገብ ቁጥር 82009 ካቀረበው ይግባኝ ጋር በማጣመር መርምሮ አመልካች በቅድሚያ ክፍያነት ከተጠሪ የወሰደውን የቤት ኪራይ ብር 442,288.61/አራት መቶ አርባ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከስልሣ አንድ ሣንቲም/ ለተጠሪ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ የቤት ኪራይ ብር 171,487.63/አንድ መቶ ሰባ አንድ ሺ አራት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሥልሳ ሶስት ሣንቲም/ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104138 እና በመዝገብ ቁጥር 136416 የሰጣቸውን ውሣኔዎች ሙሉ በሙሉ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ታህሥ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በጨረታ ተወዳድረው የድርጅት ቤት ተከራይተዋል፡፡ በኪራይ ውሉ መሠረት ቤቱን አስረክበናቸዋል፡፡ አመልካች በኪራይ ውሉ መሠረት ግዴታውን ተወጥቷል፡፡ ተጠሪ በቤቱ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት አልቻልኩም በማለቱ ቤቱን ቀበሌ በይዞታው አድርጎ ለቆየበት ጊዜ በቅድሚያ ከፍሎት የነበረውን የኪራይ ገንዘብ እንድንመልስ  የከፍተኛው ፍርድ ቤትና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከራዩ ተጠሪ ቤቱን ለአከራዩ አመልካች መልሶ ከማስረከቡ በፊት ሊከፍለው የሚገባውን የኪራይ ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለበትም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል ይዘት ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጥር 3 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ያከራየኝ የድርጅቱ ቤት ሶስት የእግድ ትዕዛዞች ያለበት በመሆኑ የንግድ ፈቃድ ማውጣት እንደማልችል በሚመለከተው አካል ተነግሮኛል፡፡ አመልካች  የእግድ ትዕዛዙን እንዲያስነሳልኝ ሁለት ጊዜ ማስጠንቀቂያ

ሰጥቸዋለሁ፡፡ አመልካች እግዱን ያላስነሣ በመሆኑ የኪራይ ውሉ ፈርሶ በቅድሚያ የከፈልኩትን ብር 442,288.61 እንዲመልስልኝ የተሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኪራይ ውሉ ሣይታደስ አመልካች ቤቱን ይዞህ ቆይተሀል በማለት የጠየቀውን ብር 171,487.63 የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ያድርግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በፅሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ በኪራይ ውሉ መሠረት የከፈለውን የኪራይ ገንዘብ አመልካች እንዲመልስ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ያልከፈለውን የቤት ኪራይ ለአመልካች የመክፈል ሀላፊነት ያለበትም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚሉት ጭብጦች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪ በተከራየውና የተረከበውን ቤት ለሆቴል አገልግሎት እንዳላውል ተፈጥረውብኛል የሚላቸውን ሁከቶችና ሌሎች ችግሮች ተጠሪ በራሱ ስም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን በመፈፀም ሊያስወግዳቸው የሚችሉ ናቸው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በኪራይ በውሉ መሠረት የተረከበውን ቤት ለሆቴል አገልግሎት ድርጅት ለማዋል ያልቻለው በቤቱ ላይ ሶስት የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የነበረ በመሆኑ ንግድ ፈቃድ ማውጣት አልቻልኩም፡፡ የቀድሞው ተከራይ በየወቅቱ እያመጣ ሁከት ፈጥሮብኛል በማለት ነው፡፡

የማይንቀሣቀሥ ንብረት የኪራይ ውል ከተደረገና ንብረቱ ለተከራይ ከተላለፈ በኂላ በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎችና የሀብት ተግባራት በማስወገድ በኩል አከራዩ ብቻ ሣይሆን በተከራዩም ላይ በህግ የተጣለ ግዴታና ሀላፊነት እንዳለ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 ድንጋጌዎች ይዘት በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የተከራየው የማይንቀሣቀስ ንብረት የኔነው ወይም በዚሁ ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ክርክር በሶስተኛ ወገኖች ለፍርድ ቤት ክርክር ያቀረቡ በሆነ ጊዜ ተከራዩ ለአከራዩ የማሣወቅ ግዴታ እንዳለበትና አከራዩም በክርክሩም ጣልቃ ገብቶ በመከራከር ሀላፊነት ያለበት መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913 ድንጋጌዎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ የሚቻለው አከራዩ በዋቢነት ቀርቦ ክርክር የማድረግ ሀላፊነት ያለበት የተከራየው ንብረት ባለሀብት ነኝ የሚል ሰው በሚመጣ ጊዜ ወይም በተከራየው የማይንቀሣቀሥ ንብረት ላይ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠው መብት አለኝ የሚሉ ሶስተኛ ወገኖች ክርክር ያነሡ በሚሆንበት ጊዜ መሆኑን "የተከራየው የማይንቀሣቀሥ ንብረት የኔ ነው ወይም በዚሁ ንብረት ላይ መብት አለኝ ብሎ ሶስተኛ ወገን ክርክር ያነሣ እንደሆነ ተከራዩ ለአከራዩ ማሳወቅ አለበት" በሚል ይዘት ካለው የፍታብሔግ ህግ ቁጥር 2913 ንዑስ አንቀፅ 1 እና እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ተከራዩ ከክርክሩ ውጭ የሚሆን ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913 ንዑስ አንቀፅ 2 ከተደነገገው ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

በያዝነው ጉዳይ የቀድሞው የቤቱ ተከራይ ከሌሎች ሰዎች ጋር በነበረው ክርክር ምክንያት የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ የተሰጠው



www.chilot.me

በአመልካች ላይ  የቀድሞው ተከራይ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረቡ ምክንያት እንዳልሆነ ወይም ቤቱ የእኔ ንብረት ነው የሚል ክርክር በመቅረቡ ምክንያት እንዳልሆነ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ በፍርድ ቤት የተሰጠው የቤቱ ባለንብረት ነኝ ወይም በቤቱ ላይ ከውል ወይም ከህግ በመነጨ መብት አለኝ የሚሉ ሶስተኛ ወገኖች ክርክር በማቅረባቸው ሣይሆን ከቀድሞው ተከራይ ጋር ክርክር የነበራቸው ሰዎች የቀድሞውን ተከራይ የሆቴል ንግድ ድርጅት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲከበርላቸው ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪ በተከራየው ቤት ላይ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913/1/ መሠረት ከሶስተኛ ወገኖች የቀረበ ክርክር አለመኖሩ በሥር  ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ በቤቱ ላይ ከውል ወይም ከህግ ያመነጨ መብት የሌላቸው ሰዎች ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻ የተሰጠን የዕግድ ትዕዛዝ ማስነሳት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 መሠረት ቀላል የሆነ ሁብት የማስወገድ ተግባር ነው፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 ንዑስ አንቀፅ 1 በተከራየው የማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት መብት ወይም ሌላ መብት አለን በማይሉ በሶስተኛ ወገኖች አድራጎት ለሚነሳው ሁከት አከራዩ ዋስትና እንዲሰጥ የማይገደድ መሆኑን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ይህን የመሰለውን ሁከት ለማስወገድ ተከራዩ በራሱ ስም ለመከራከር ይቻላል በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ በፍርድ ቤት የተሰጠው አመልካች ባከራየው ቤት ላይ የቀድሞው ተከራይ በነበረው የንግድ ድርጅት ላይ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ቤቱን ከአመልካች የተከራየ መሆኑንና በትዕዛዝ የተከበረው የንግድ ድርጅቱ በተከራየው ቤት ላይ የሌለ መሆኑን  የዕግድ ትዕዛዙን በሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከት የዕግድ ትዕዛዙ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 158 መሠረት የመጠየቅና ተጠሪ በተከራየው ንብረት ላይ የተከሰቱ ቀላል ችግሮችን የማስወገድ ሀላፊነት የተከራዩ /የተጠሪ/ መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ መሆኑን ሣያገናዝብ የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ ቤቱን ከተከራየበትና ከተረከበበት ከሀምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ቤቱን በይዞታቸው ሥር አድርገው የቆዩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ በማለት የሚከራከር ቢሆንም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2936 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የኪራይ ውሉ ሲያልቅ በኪራይ የያዘውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ለአመልካች ያስረከበ መሆኑን ተጠሪ አላስረዳም፡፡ ተጠሪ ቤቱን ይዞ መቆየቱ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2968 ንዑስ አንቀፅ 1 ኪራዩን እንዳደሰ የሚያስቆጥረው ነው ስለሆነም አመልካች ከሀምሌ 18 ቀን 2000 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ያለውን ቤት ኪራይ ተጠሪ የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ስለሆነም የመጀመሪያው ጭብጥ ለመወሰን የሰጠውን የተሣሣተ የህግ ትርጉም መሠረት በማድረግ ተጠሪ ውዝፍ ቤት ኪራይ የመክፈል ሀላፊነት የለባቸውም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104138 እና በመዝገቡ ቁጥር 136416 የሰጣቸው ውሣኔዎች ፀንተዋል፡፡
3. ወጭና ኪሣራን ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 63352

ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ ቱሌ አብዶ በሌለበት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ ተጠሪ ለሥር የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ የሰበር አመልካች / በሥር 1ኛ ተከሣሽ / እና በሥር 2ኛ ተከሣሽ በነበረው ሁናን ሁንዴ የመንገድና የድልድይ ሥራ ድርጅት ላይ ያቀረቡት ክስ ፍሬ ቃሉ 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሽ በመካከላቸው ባደረጉት የመንገድ ሥራ ውል 2ኛ ተከሣሽ ዳከር በሚባል አካባቢ የሚገኘውንና በገማች ኮሚቴ ተገምቶ ግምት 166,115 የሆነውን የከሣሽ መጋዝን እንዲፈርስ በሰኔ ወር 2000 ዓ/ም ምልክት በማድረግ ግምቱ ሳይከፈል መጋዘኑን በታህሣሥ ወር 2001 ዓ/ም ያፈረሰ ከመሆኑም ሌላ ብር 20,000 የሚያወጣ አንድ ቤት እና ብር 15,000 የሚያወጡ ዛፎች ግምት ብር 15,000 ፣ የአንድ ክፍል ቤት ግምት 20,000 እና መጋዘኑ እንዲፈርስ ምልክት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ለ17 ወራት ገቢ የተቋረጠ ስለሆነ በቀን ብር 350 ሂሣብ 178,500 ሆኖ በድምር ብር 379,615 ተከሣሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር 1ኛ ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካችም በሰጠው መልስ በገማች ኮሚቴ ግምት መሠረት ንብረቱ እንዲነሣ መደረጉን በማመን ከመንገድ ክልል ውጪ ላሉት የከሣሽ ንብረቶች ግን ካሣ የመክፈል ግዴታ የለብኝም ፣ በገንዘብ ልክ ተመልክቶ የሚከፈል ካሣ ዘግይቶ በመክፈል ምክንያት ለደረሰ ጉዳት መክፈል ያለበት ህጋዊ ወለድ እንጂ የተቋረጠ ጥቅም አይደለም፣ መጋዘኑ እንዲፈርስ ምልክት ቢደረግም ከሣሽ በመጋዘኑ እንዳይጠቀሙ ስለመከልከላቸው አላስረዱም፣ የዕለት ገቢን በሚመለከት ከሣሽ የመንግስት ግብር የተከፈለበትን ደረሰኝ አያይዘው አልቀረቡም፣ ቤቱ ላይ ደረሰ ለተባለውም ጉዳት መጠየቅ የሚችሉት የጥገና ወጪውን እንጂ የአዲስ ቤት መሥሪያ ግምት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር 2ኛ ተከሣሽ በበኩሉ ባቀረበው መልስ ከሣሽ የካሣ ጥያቄአቸውን ህጉ በሚፈቅደው መሠረት 1ኛ ተከሣሽን ከሚጠይቁ በስተቀር 2ኛ ተከሣሽን ሊጠይቁ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡



www.chilot.me

የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም በሰጠው ፍርድ 1ኛ ተከሣሽ በገማች ኮሚቴ ተገምቶ የቀረበውን የመጋዘን ዋጋ ብር 166,115 እና የመጋዘኑ የዕለት ገቢን በሚመለከት የከሣሽ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ መጋዘኑ ከፈረሰበት ከታህሣሥ 2001 ጀምሮ የ17 ወራት ብር 178,500 ፣ እንዲሁም በተጨማሪ ክስ ከተጀመረበት እስከ ግንቦት 2002 ያለውን የ7 ወር ብር 73,500 ተጨምሮ በድምሩ ብር 418,115 1ኛ ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ 2ኛ ተከሣሽ ግን የንብረት ካሣን በሚመለከት ሀላፊነት ባይኖረውም በሌሎች የካሣ ዓይነቶች ሀላፊነት የለብኝም ለማለት የማይችል መሆኑን በውሣኔው አስፍሯል፡፡

ጉዳዩን የአሁኑ የሰበር አመልካች በይግባኝ ለሥር ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የመጋዘኑን የዕለት ገቢ በፍ/ህ/ቁ 2102 መሠረት በርትዕ ብር 75 በመወሰን የ24 ወራት ብር 54,000 ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪው እንዲከፍል አሻሽሎ በመወሰን በሌሎች ነጥቦች ላይ ግን የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም የመጋዘኑ ባለቤት ስለመሆናቸው ተጠሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ ወረቀት አላቀረቡም፡፡ የገማች ኮሚቴ ለመጋዘኑ ካቀረበው የግምት ውጤት ብር 166,155 በተጨማሪ በቀን በብር 75 ሂሣብ የ24 ወራት የተቋረጠ ገቢን ብር 54,000 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተወሰነው ህግና ማስረጃን መሠረት ያላደረገ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ለተጠሪው መጥሪያ ተልኮላቸው ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን አመልካች ለዚህ ችሎት በ28/8/2003 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ከመግለጹም በላይ ተጠሪው የሚኖሩበት ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በቁጥር አ/አ/ቀ/ሠ/10328/03 በቀን 26/8/2003 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ተጠሪው የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን በማረጋገጡ ክርክሩ በሌሉበት እንዲቀጥል ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በሥር ፍ/ቤት የተደረገው ክርክርና የአመልካች አቤቱታ ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ የተገለፀ ሲሆን እኛም ለመጋዘኑ ከቀረበው የግምት ገንዘብ በተጨማሪ ከመጋዘኑ የሚገኘው ገቢ ተቋርጧል በሚል የተቋረጠውን ገቢ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ከሥር ፍ/ቤት ጀምሮ ተጠሪው የመጋዘኑ ባለቤት ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ የላቸውም በማለት እንዲከፍል ከተወሰነበት የተቋረጠ ገቢ ጋር አያይዞ የሚከራከር ቢሆንም የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት በመንገድ ሥራ ምክንያት ንብረቶቻቸው ላይ ጉዳት ከደረሰባቸው ግለሰቦች መካከል አንዱ ተጠሪው ስለመሆናቸው የሶፊ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት አረጋግጧል በማለት በውሣኔው ካሰፈረው ጋር ሲገናዘብ ተጠሪው የንብረቱ ባለቤት አይደሉም በማለት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስ አመልካች የመጋዘኑን ግምት ዋጋ እንጂ ተጠሪው አጥተዋል የተባለውን የተቋረጠ ጥቅም መክፈል አይገባኝም በማለት ያቀረበውን የመከራከሪያ ሀሣብ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን ከወጣው አዋጅ ቁጥር 455/97 አንፃር መመርመር ተገቢነት የሚኖረው ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 2/1/ ለ " ካሣ " በተሰጠው ትርጉም መሠረት ካሣ ማለት የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ



www.chilot.me

በመሬቱ ላይ ለሠፈረው ንብረት በዓይነት ወይም በገንዘብ ወይም በሁለቱም የሚከፈል ክፍያ ሲሆን የመሬት ይዞታውንም የሚለቅ ባለይዞታም በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት ወይም ማሻሻል ካሣ እንደሚከፈለው በአዋጅ አንቀጽ 7/1/ ተደንግጓል፡፡ በይዞታው ላይ ለሚገኘው ንብረት የሚከፈለውም ካሣ ንብረቱን ባለበት ሁኔታ ለመተካት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው በመንገድ ሥራ ምክንያት የፈረሰባቸው አንድ መጋዘን ሲሆን ይኸው የመጋዘን ዋጋም በገማች ኮሚቴ ብር 166,115 ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ይህ የመጋዘኑ ግምትም በአዋጅ አንቀጽ 7/1/2/ በተደነገገው መሠረት የፈረሰውን መጋዘን ለመተካት በሚያስችል መልኩ የቀረበ ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪው ምናልባት ይኸው የመጋዘኑ ግምት መጋዘኑን ለመተካት የሚያስችል አይደለም የሚሉ ከሆነ በአዋጅ አንቀጽ 16 በተደነገገው መሠረት ይግባኝ ማቅረብ ከሚችሉ በስተቀር መጋዘኑ ተገምቶ የግምቱን ገንዘብ እንዲወስዱ ከተወሰነላቸው በኋላ መጋዘኑ እንዲፈርስ ምልክት ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የአጡትን ገቢ የሚጠይቁበት የህግ መሠረት የላቸውም፡፡ በሌላ አነጋገር የመጋዘኑ ግምት እንዲከፈል እስከጠየቁ ድረስ የግምቱን ገንዘብ ከሚወስዱ በስቀር ገቢ አጥቻለሁ በማለት የተቋረጠውን ገቢ ሊጠይቁ የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡

የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ ለውሣኔአቸው መሠረት ባደረጉት አዋጅ ቁጥር 455/97 ሆነ አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 135/99 የንብረቱ ካሣ ለባለንብረቱ ከሚከፈል ውጪ የተቋረጠ ገቢን ለባለንብረቱ እንዲከፈል በግልጽ ባልተደነገገበት ከተጠቀሱት ህጐች ዓላማ ውጪ ለተጠሪው የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል መፍቀዳቸው ወይም መወሰናቸው ተገቢነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የመሩት በአግባቡ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁጥሮችን ሳይከተሉ መሆኑን የክርክሩ መዝገብ ያመለክታል፡፡ ይኸውም ተጠሪው አመልካች እንዲከፍል የጠየቁት የካሣ መጠን ብር 379,615 ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤት ግን የመጀመሪያው ክስ ባልተሻሻለበት አመልካች ለተጠሪ ብር 418,115 እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይህም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182 /2/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ ለመስጠት አይችልም በሚል የተደነገገውን የሚቃረን ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ቢሆን ተጠሪው ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የ17 ወሩ የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈላቸው እንዲወሰን ጠይቀው እያሉና በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት መስቀለኛ ይግባኝ ባላቀረቡበት አመልካች ባስከፈተው የይግባኝ መዝገብ በሥር ፍ/ቤት ክርክር ያልተደረገውን የ7 ወራት የተቋረጠ ገቢን በመጨመር በድምሩ የ24 ወራት የተቋረጠ ገቢን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በሚል መወሰኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 329/1/ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተነሣውን ክርክርና ያልቀረበውን አዲስ ነገር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለመቀበል አይችልም ተብሎ በግልጽ የተደነገገውን ያልተከተለ ነው፡፡ ለማጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በመንገድ ሥራ ምክንያት እንዲፈርስ የተባለው የተጠሪ መጋዘን ተገምቶ ግምቱ ከቀረበ በኋላ ይኸው ገንዘብ ለተጠሪው እንዲከፍል መወሰን ሲገባቸው የመጋዘኑን የተቋረጠ ገቢ ጭምር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የሥር የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06653 በቀን 17/10/2002 በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01670 በቀን 05/4/2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪው የመጋዘኑን የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍል የተወሰነው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ስለሆነም የተቋረጠውን መጋዘን ገቢ አመልካች ለተጠሪ አይከፍልም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡ ተጠሪው በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው ያልተከራከሩ ስለሆነ የሚታዘዝላቸው ወጪና ኪሣራ የለም፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 62858

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ፓዝ ፋይንደር ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ - ጠበቃ ኒቆዲሞስ ጌታነ-ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ መንበር አድማሱ - ቀረቡ

2. የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ - ወኪል በላይ አንተ - ቀረቡ ፡፡

መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የስበር ጉዳይ የቀረበው አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በተከራይ እጅ እያለ በእዳ ምክንያት በተለላለፈ ጊዜ ገዥው በባለቤትነቱ ተከራይ ደግሞ በተከራይነቱ የሚኖራቸው መብት ምንድን ነው የሚለውን አስመለክቶ ግራቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር በማየት አስፈላጊውን ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመሰረተው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው የአመልካች የክስ ይዘትም ሐጂ ይማም ሙዙይን ከተባሉ ግለሰብ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04 ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 1212 የሆነ ቤት ሐምሌ 11 ቀን 2002 ዓ/ም በተጻፈና እስከ መስከረም 20 ቀን 2005 ፀንቶ በሚቆይ የኪራይ ውል ተከራይቶ በመጠቀም ላይ እያለ አከራዩ ግለሰብ ከአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የወሰዱን የብድር ገንዘብ ለመክፈል ባለመቻላቸው ባንኩ ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ መሸጡን ግልጸ የኪራይ ውሉ ከአከራዩ ጋር ባላበቃበት ሁኔታ ባንኩ የተከራይነት መብቱን ለአመልካች ሳይጠብቅ ለ2ኛ ተጠሪ ቤቱን በመሸጥ ተከራዩ አመልካች ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ የጻፈው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን የተጠቀመው መብት በመሆኑ ሁከት ሊባል አይችልም የሚል ሆኖ ክሱ ውድቅ እንዲሆን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ተጠሪም በሕጉ አግባብ ተጫርቶ የገዛው ንብረት በመሆኑ የሁከት ተግበር ሊባል እንደማይችል ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌደራሉ መጀመሪያ ደርጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የተጠሪዎች ተግባር ሁከት ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አደርጎታል በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኝ ለፌዴራሉ



www.chilot.me

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2931 እና 2933 በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 449 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታርም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1933 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ የሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በዚህ መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በፁሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባቀረበው የፁሐፍ መልስ የፍ/ብሕ/ቁጥር 2931 እና 2933 ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 97/90 የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው መሆኑን በመግልፅ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን 2ኛ ተጠሪም በሕጉ አግባብ የገዙት ቤት ስለሆነ ተግባሩ ሁከት ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንግዲህ ግራቀኙ ከሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ በጉዳዩ ላይ ያቀረቡት ክርክር እና ለሰበር ክርክሩ መነሻ የሆኑት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎች ይዘት ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይህንኑ ክርክራቸውን ከስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል ፡፡

እንደመረመርነውም ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ በሆነውና ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀረበው ክስ ላይ የአሁኑን አመልካች የጠይቁት ዳኝነት በኪራይ ውል በያዝኩት ቤት የኪራይ ውሉ ዘመን ከመራዘሙ በፊት ቤቱ በሐራጅ ለ2ኛ ተጠሪ ተሸጦ ርክክብ እንዲደረግ ማስጠንቀቂያ መውጣቱ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድ ይግባል የሚል ነው፡፡

አከራካሪ ሆኖ የተገኘውና የህግ ትርጉም የሚያሻው ነጥብ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ህንፃውን በጨረታ መሸጡና ቤቱን አመልካች ለቆ እንዲያስረክብ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ አመልካች በሻጭና በገዥው ላይ በመቃወሚያነት በማነሳት በፍ/ሕ/ቁ 2931 እና 2933 በተደነገገው መሰረት የኪራይ ውሉ ዘመን ሳያበቃ ቤቱን የማስረከብ ግዴታ የለብኝም ድርጊቱ ሁከት ነው ሊወገድ ይገባል በማለት ለመከራክር ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ነው፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራይ ለአሁን ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረከብ ማስጠንቀቅያ መስጠቱ ሁከት አይደለም የሚለውን ምክንያት ለውሳኔው መደምደሚያ መሰረት ያደረገው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2899 አና 2932/1/ እና አዋጅ ቁጥር 97/90 ስር የተመለከተው ዓላማ ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የተፈፃሚነት ወሰን አንድ ኪራይ ውሉ ይዞታን በተከራይ እጅ አፅንቶ ለማቆየት አከራዩ በእዳ ምክንያት ንብረቱ የሚሸጥበት ከሆነ ንብረቱን የሚገዛው ሶስተኛው ወገን ንብረቱን የመረከብ ሁኔታ የኪራዩ ውሉ ዘመን ከማብቃቱ በፊት ሊጠቀምበት የመቻሉን ሁኔታ እስከመገደብ የሚደርስ ነው? የሚለውን ለይቶ ማስቀመጡ ተገቢ መሆኑን ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የፍትሐብሔር ሕግ ደንጋጌዎች በተናጠልም ሆነ እረስ በእርሳቸው አስተሳስረን ስንመለከታቸው አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት የገዛ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1184 መሰረት በሽያጭ ውል አማካኝነት የባለቤትነት መብት በተላለፈለት ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1204 በህግ በተሰጠው የባለቤትነት መብት ተጠቅሞ ከመሸጡ በፊት በተሸጠው ንብረት ላይ በተከራይነት በይዞታቸው



www.chilot.me

አድርገው የሚገኙት ሰዎችን በማስለቀቅ የኪራይ ውሉን ማቋረጥ የማይችል በመሆኑ በፍ/ብሕ/ቁ 1204/2/ እንደተመለከተው ገደብ የጣሉበት ድንጋጌዎች መሆናቸውን የሚያሳዩ ሲሆን ይህ የሚሆነው ደግሞ ገዥው ንብረቱን ከአከራይ ገዝቶ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

አንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከአምስት ዓመት በላይ የተደረገ እና ይህም የኪራይ ውል ተመዝግቦ ከተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2899 እና 2931 ይህ ዓይነት የኪራይ ውል በገዥው ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችልና ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተከራዩ ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ ውሉ እንዲፈርስና የጉዳት ኪሳራን ለመጠየቅ የሚችል መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር ይህ ከአምት ዓመት በላይ የሆነው የኪራይ ውል ዘመን እስከሚያበቃ ድረስ ተከራይ አከራይ ባለበት እዳ ምክንያት የአከራዩን ንብረት በሕግ አግባብ በመሸጥ እዳን ለመሰብሰብ በሕጉ ስልጣን የተሰጣቸው አካል ጨረታ በማውጣት ንብረቱን ሲሸጡና በማስታወቂያ መሰረት ቤቱን ንብረቱን የገዛው ሰው ከቀድሞው አከራይ ሳይረከብና ማናቸውንም ጥቅም የመጠየቅ መብት የለውም ማለት እንዳልሆነ ሕጎቹ ያሳያሉ፡፡

በተመሳሳይ የኪራይ ውሉ ምንም እንኳ የተመዘገበ ባይሆንም የተረጋገጠ ቀን መኖሩ ከታወቀ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2933/1/ መሰረት ገዥው የሽያጭ ውሉን ካስመዘገበበት ቀን አንስቶ ተከራዩ እስከ አምስት ዓመት ድረስ መቃወሚያ ሊያደርገው ይችላል መባሉ ንብረቱን በእዳ ምክንያት በሕጉ አግባብ የሚሸጥ አካል እና በዚሁ መሰረት ንብረቱን የገዛው ገዥ በዚህ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በንብረቱ ላይ እንደ ባለመብት ንብረቱን ሳይረከብ ይቆያል ወይም ማናቸውም ጥቅም ሳያገኝ ይቆያል ማለት አይደለም፡፡

ይልቁንም የኪራይ ውል ባልተመዘገበ ጊዜ በግዥ ባለመብት የሆነው ሰው የኪራይ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጥረዋል ተብሎ በፍ/ብሕ/ቁ 2933/1/ መደንገጉ የኪራይ ውል የመመዝገብና ያለመመዝገብ ውጤት ገዥው አስቀድሞ ንብረቱን ከመግዛቱ በፊት የተደረገውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ እና ላለማቋረጥ ያለዉን መብት የሚያመለክት እንጂ ኪራዩን ከቀድሞው ተከራይ የግድ እንዲቀጥል ወይም ንብረቱን የመረከብ መብቶች እስካለመጠየቅ ሊያደርስ የሚችል መብት ሊያሳጡ የሚችሉ ድንጋጌዎች ናቸው ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም ፡፡

ስለሆነም እንደአሁኑ ባለው ጉዳይ ተከራይ በኪራይ የያዘውን ንብረት ለአዲሱ ባለንብረት በግዥ ላገኘው ባለሀብት ለማስረከብ ይገደዳል ወይስ አይገደድም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ንብረቱን ገዥው በመረከቡ የተነሳ ተግባሩ ሁከት ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም ፡፡ የሁከት ተግባር መብት የሌለው ሰው ሌላ ሕጋዊ መብት ባለው ሰው ይዞታ ላይ የኃይል ተግባር መፈፀም ወይም መስናከል ሆኖ ሲገኝ በሕግ አግባብ እንዲወገድ የሚደረግ ወይም የሚጠይቅ እንጂ በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል ከአከራዩ በእዳነት የሚፍለገውን እንቅስቃሴ ሁሉ የሚሸፈን አለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 97/90 ዓላማ እና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቅስ የፍ/ብ/ስ/ሕ/ቁጥር 449 ድንጋጌ መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ባለመሆኑ የምንቀበለው አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላላገኘው የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል ፡፡



www.chilot.me

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ፡፡ መዝገቡ ተዝግቷል ወደ ፡፡ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ረ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 62293

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡ -** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ መስፍን ጀምበሩ - ቀረበ

2. የሆሳእና ከተማ አስተዳደር - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የንብረት ግምት ይከፈለን ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ከቡታጅራ ሆሣዕና በሚያስራው መንገድ ምክንያት በሆሣዕና ከተማ የሚገኙ ንብረቶቻቸው እንዲነሱ የግምት ሥራ ተሰርቶላቸው በዚሁ መጀመሪያ ግምት የከተማው አስተዳደር ንብረቶቻቸውን ያስነሳቸው መሆኑን የንብረቶቻቸው ዓይነትና ግምት ምን ያህል እንደሆነ ዘርዝረው አመልካች ካሣ እንዲከፍለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሠረቱት የተናጥል ክስ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ ለመንገድ ሥራው የዲዛይን ለውጥ ማድረጉንና በተለወጠው ዲዛይን መሠረትም ንብረቶቹ መነሳት የማያስፈልጋቸው በመሆኑ ኃላፊነት እንደሌለበት የተነሱ ወይም እንዲፈርሱ የተደረጉ ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 455 አንቀጽ 3(1) እና 4(1) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን ሥርዓት ባልተከተለ መልኩ የተከናወነ በመሆኑ ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑን እንዲሁም አዋጁን ባልተከተለ መንገድ የራሱን ሥራ ለመስራት ንብረቶችን አስነሳ የተባለው የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ይታዘዝለት ዘንድ በመግለፅ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ክርክር በተለያዩ መዛግብት መርምሮ የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ ይግባልኝ የሚለውን የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎ አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለፅ ተጠሪዎች በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ወስኖላቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይኸው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መዛግብትን በአንድ ላይ በማጣመር መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቦ ይህ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ (የሆሳእና ከተማ አስተዳደር) ለክርክሩ የግድ ተካፋይ ሊሆን የሚገባው ወገን ሁኖ እያለ መታለፉ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር ይኸው ተጠሪ



www.chilot.me

ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ለስር ፍርድ ቤት መልሶለት የሥር ፍርድ ቤትም የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካችን ለጉዳዩ ኃላፊ በማድረግ የሆሳዕና ከተማ አስተዳደርን ግን ከኃላፊነቱ ነፃ አድርጎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ በድጋሚ የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሕዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት 5(አምስት) ገፅ የሠበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ የዳኝነት ሳይከፈልበት መታየቱ ያላግባብ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ያየው ከስልጣኑ ውጪ መሆኑንና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከተላከለት ውጪ ሶስተኛ ወገንን ጨምሮ ውሳኔ መስጠቱ የስነ ሥርዓት ግድፈት ያለበት መሆኑን በመጀመሪያ መንገዱ ሊሰራበት በታሰበው ስፋት መሠረት የተሠራው ግምት እጅግ የተጋነነ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው ለከተማ አስተዳደሩ አመልካች ከገለጸለት በኋላ አስተዳደሩም ይህንን አውቆ የዲዛይን ክለሳ እና በዚህም መሠረት የግምት ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀድሞው ዲዛይን መሠረት ተነስቷል የሚባል ንብረት ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ባልዋለበትና በህጉ አግባብ ላልተነሳ ንብረት ካሣ ለመክፈል ህጋዊ ግዴታ የሌለበት መሆኑን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሙሉ በሙሉ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው የጽሁፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሠበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ለተጠሪዎች ካሳ ይክፈል የተባለበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን እንደሚከተለው አይቶታል፡፡

ክርክሩ ሲጀመር በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በተናጠል ክሳቸውን አቅርበው ጉዳያቸው የታየ ሲሆን በይግባኝ ደረጃ የተጣመሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያየውም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ስልጣን በመወከል መሆኑንና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለበት ወገን ሁሉ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይገባ የነበረ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 322/95 እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ በመ/ቁጥር 54577 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመልሶ እንዲታይ ውሳኔ ሲሰጥ ይግባኙ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መታየቱ ላይ ያስቀመጠው ትችት ባለመኖሩና ክርክሩ ከወሰደው ጊዜ እንዲሁም ከሥነ ስርዓት አላማ ስንነሳ በይግባኝ አቀራረብ ሥርዓቱ ላይ የተፈጸመውን ስህተት አልፈነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በመጀመሪያ መንገዱ ሊሰራበት በታሰበው ስፋት መሰረት የተሰራው የንብረቶች ግምት ባልተለመደ ሁኔታ እጅግ የተጋነነ በመሆኑ እንደማይቀበለው ለከተማ አስተዳደሩ ገልጾና አሳውቆ የዲዛይን ክለሳና የግምት ሥራ ተጠናቅቆ ከአለቀ በኋላ ንብረቶቹ እንዲነሱ ወይም እንዲፈርሱ ለተደረገው ሁኔታ አመልካች ኃላፊነት



www.chilot.me

እንደሌለበትና ይህንን ድርጊት የከተማው አስተዳደር ለራሱ ሥራ ሲል ስለአከናወነው ኃላፊነት ሊወስድ ስለሚገባ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሊታዘዝ ይገባል በማለት የሥነ ሥርዓት ጥያቄ አንስቶ ይህ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 43424 የከተማው አስተዳደር ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ለጉዳዩ ኃላፊነት ያለበት ወገን እንዲለይ ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ሰምቶ አመልካች የዲዛይን ክለሳ ከማድረጉ በፊት የ1ኛ ተጠሪዎች ንብረቶች ተገምተው በአስቸኳይ እንዲፈርሱ መደረጉን፣ ይህንኑ ስራ ሲመሩ የነበሩት የአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኛም የ1ኛ ተጠሪዎች ንብረቶች እንዲፈርሱ ያደረጉ መሆኑን እንዲሁም የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የመንገዱ ዲዛይን ክለሳ ስለመኖሩ ያወቀው የ1ኛ ተጠሪዎች ንብረቶች እንዲፈርሱ ከተደረገ በኋላ ስለመሆኑና ከ1ኛ ተጠሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ንብረታቸው የፈረሰባቸው ሰዎች ካሳ በአመልካች መከፈሉ በአመልካች መከላከያ ምስክሮች ጭምር መረጋገጡን ምክንያት በማድረግ አመልካችን ለጉዳዩ ኃላፊ አድርጓል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆን/መሆኗ የተከበረለት/ላት መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 40(1) ስር በግልፅ ደንግጎ የምናገኘው ጉዳይ ነው፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(7) ድንጋጌም ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬቱ ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬቱ ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን እንደሚያካትት የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ስምንት ደግሞ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሁኖ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል በሚል ተቀምጧል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/97 ደግሞ ለህዝብ ጥቅም ትርጉም አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የህዝብ ጥቅም ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት አግባብ ያለው አካል በመሪ ፕላን ወይም በልማት እቅድ የሕዝብ ጥቅም ብሎ የሚወስነው ነው በሚል በአንቀፅ 2(5) ስር ይዞ እናገኛለን፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪዎች ይዞታቸው አመልካች ለሚያሰራው መንገድ የተወሰደባቸው መሆኑና ንብረቱ የፈረሰውም የመንገዱ ዲዛይን ክለሳ ከመደረጉ በፊት በአመልካች ባለሙያ ግፊት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ይህ ተቀባይነት በሌለው ሁኔታ የተረጋገጠ ስለሆነ ሕጋዊ አይደለም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በግልፅ የማስረጃ ጉዳይ መሆኑን የምንገነዘበው ሲሆን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የበታች ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3/ሀ) እና 25/1988 አንቀፅ 10 የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፀም ማረም በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ አሳማኝ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጉዳይ የሚመለከተው ሁኖ አላገኘውም፡፡ እንዲህ ከሆነ የ1ኛ ተጠሪዎች ይዞታ ቦታ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ሲወሰድና በቦታው ላይ የነበሩት ንብረቶች በአመልካች ባለሙያ ጭምር ግፊት ተደርጎ እንዲነሱና እንዲፈርሱ ከተደረገ በኋላ የዲዛይን ክለሳ ሲደረግ ንብረቶቹ የማይነሱ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ብቻ በመመስረት አመልካች የካሳ ገንዘቡን ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀፅ 3(1 እና 2) እንዲሁም ከአንቀፅ 4(1) ድንጋጌዎች ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር ተደምረው ሲታዩ የአመልካች



www.chilot.me

ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 03332 ግንቦት 05 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁጥር 51034

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ት ታሪክ ጌታቸው

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ ወ/ሮ አልጋነሽ ተጠምቀ

2ኛ ወ/ሮ ልዕልቲ በላይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው ክርክር መነሻ ሆኖ የተገኘው የሟች አቶ ጌታቸው በላይ ንብረት የሆነ በመቀሌ ከተማ የሚኝ 325 ካሬ ሜትር የቦታ ይዞታ ያለውን ቤት የሟች ልጅና ህጋዊ ወራሽ የሆነችው የአሁኗ አመልካች እያለች አቶ በላይ በየነ የተባሉት ሰው እና የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ አልጋሽ ተጠምቀ የሟቹ ወራሾች እኛ ነን ብለው ፍ/ቤት በመቅረብ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀው የወራሽነት ማስረጃ በመውሰድ የሟችን ቤት ስም ባለሃብትነት በሥማቸው ካዛወሩ በኃላ ልጃቸው ለሆነችው ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ልዕልቲ በላይ ብር 50,000 በመሸጥ አስተላልፈው በሥሟ እንዲመዘገብ አድርገው መገኘታቸው ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ የሟቹ የአቶ ጌታቸው በላይ ልጅና ህጋዊ ወራሽ መሆኗን 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች በማይመለከታቸውና ያለአግባብ የሟችን ቤትና ቦታ ተሻሽጠውና አዛውረው እንደሚገኙ በመዘርዝር እንዲያስረክቧት ጠይቃለች፡፡ አቶ ጌታቸው በላይ በ1986 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ስለመሆናቸውና ሟች ባደረጉት ኑዛዜ ስለልጅቱ አስተዳዳሪ ለወላጆቻቸው በሰጡት መሠረት የአሁኗ አመልካች የስድስት አመት ዕድሜ ሲሞላት 2ኛዋ ተከሣሽ ወደ ደሴ ከተማ መጥታ ልጅቷን ወደ መቀሌ ከተማ በመውሰድ ከእነርሱ ጋር ስትኖር ቆይታ ዕድሜዋ ለአካለመጠን ሲደርስ ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ፍ/ቤት ቀርባ የሟቹ ህጋዊ ወራሽ ስለመሆኗ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንደተሰጣት በክሱ ላይ ተገልጿል፡፡ አመልካች በክሷ ቤት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የጠየቀቻቸው ነገሮች ነበሩ፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች የነበሩት የይርጋ የመቃወሚያና ሌሎች የፍሬ ነገር ክርክሮች ያቀረቡ ሲሆን ቤቱን ገዝታለች የተባለችው 3ኛዋ ተከሣሽ የነበረችው የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ በበኩሏ 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ቤቱን በይዞታቸው ሥር ለ10 አመት አቆይተው በብር 50,000 ሸጠውልኝ ንብረቱ በሚመለከተው የሕግ ክፍል በፍትሐብሄር ሕግ



www.chilot.me

1723 መሠረት ተመዝግቦ በቅንነት የገዛሁትን መልሺ ተብዬ ልገደድ አይገባም በማለት ተከራክራለች፡፡ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን፣ የግራ ቀኙን ክርክሮች እና ማስረጃዎችን መርምሮ ክሱ በ10 አመት ይርጋ ይታገዳል በሚል ለተነሣው ክርክር ከሣሽዋ የአካለመጠን ዕድሜ በመድረስ የመክሰስ ችሎታ እንዳገኘች በ30/10/2000 ዓ.ም ክሱን ያቀረበች ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብሎ ውድቅ ካደረገው በኋላ የክሱን ዋና ፍሬ ነገር በተመለከተም ቤቱ የሟቹ የአቶ ጌታቸው በላይ ንብረት መሆኑ በቀረበው የጽሑፍ ማስረጃ ተረጋግጧል 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ከሣሽዋን በሞግዚትነት እያሳደጓት ባለበትና የመውረስ መብት ባልነበራት ወቅት ወራሾች ሣይሆኑ ተሯሩጠው የሟች ወራሽ ስለመሆናቸው በማስወሰን ቤቱን ለልጃቸው ለ3ኛዋ ተከሣሽ ሸጠው መገኘታቸው በሕግ የሚደገፍ አሻሻጥ አይደለም፣ የራሣቸው ያልሆነውን ንብረት መሸጥ በሕጉ አይፈቀድም፣ ሽያጩ በሕጉ ውጤት የለውም ፈራሽ ነው፤ ያገኙት ወራሽነትና ያደረጉት ሽያጭ ቅንነት የጉደለው የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት የተፈፀሙ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣ 3ኛዋ ተከሣሽም ንብረቱን የገዛችው ቅንነት ከሌላቸውና በቤቱ ላይ መብት ከሌላቸው ወራሾች ነው፣ ራሷም ብትሆን ቤቱን በቅንነት የገዛች ባለመሆኑ ሽያጩ ተቀባይነት የለውም በማለት በክሱ ላይ አዋሳኞቹ የተጠቀሰውን በውስጡ 8 ክፍል መኖሪያ፣ ሽንት ቤትና ማዕድ ቤት የያዘ የቦታ ስፋቱ 325 ካሬ ሜትር የሆነውን ቤት 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ለከሣሽዋ ለአሁኗ አመልካች ሊያስረክቧት ይገባል ብሎ ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በዚህ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረቡ ቢሆንም መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚተችበትና የሚጣራ ነገር የለውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት የሚያስቀርብ አይደለም ብሎ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

እንደገና የአሁኑ ተጠሪዎች በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት አይቶት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ቀርበው ክርክሩ ከተሰማ በኃላ ሰበር ሰሚው ችሎት በበኩሉ መርምሮ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ከባለቤቷ ጋር ሆና ሟቹ ልጃችን ወራሽ የለውም፣ ወራሾቹ እኛ ነን ብለው ቤቱን ወደ ሥማቸው በማዛወር ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ በብር 50,000 ሸጠው ስለተገኙ በህጋዊ መንገድ የገዙትን ቤት ሊያስረክቡ አይገባም፣ ቤቱን በመሸጥ ጥቅም ያገኘችው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ብር 50,000 ክሱ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ተከፍሎ እስኪያልቅድረስ 9% ወለድ ጨምራ ለአሁኗ አመልካች ትክፈል የሚል ውሣኔ በመስጠት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) መሠረት የቀረበ ሲሆን ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ ተብሎ በመወሰኑ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪዎች ተልኮ ቀርበው ክርክሩ እንዲሰማ ተደርጓል፡፡ በሁለቱም በኩል ቀርበው የተከራከሩት በየባለጉዳዮቹ የተወከሉት ጠበቆች ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት የአመልካች ጠበቃ ቤቱ ለ2ኛዋ ተጠሪ ተሸጧል የተባለበት ውል በተንኮል የተደረገ ስለሆነ ሊፀና አይገባም፣ ሻጮችም በቤቱ ላይ ህጋዊ መብት የላቸውም፣ በትክክል በሚታይበት ጊዜ ሁለተኛዋ ተጠሪ ቤቱን ሆን ብላ ነው የገዛችው፣ ገንዘቧን ማግኘት አለባት ከተባለም ማግኘት ያለባት ከሸጡላት ወላጆቿ ነው፡፡ ውሉ ፈርሶ ቤቱን



www.chilot.me

ለአመልካች መስጠት አለባቸው፣ ይህ እንኳን ቢታለፍ በክሱ ላይ የቤቱ ግምት ብር 120,000 ተብሎ ስለቀረበ እነርሱ የተሻሻጡበት ብር 50,000 ይከፈላት የተባለው ያለአግባብ ነው ብለው በመዘርዘር ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪዎች ጠበቃ በበኩላቸው 1ኛዋ ተጠሪ 10 አመት በሙሉ በቤቱ ሲገብሩበት ቆይተው ይዞታቸውን መሸጣቸው ህጋዊ ነው፣ ገዢዋም ብትሆን ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በሥማቸው ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት መግዛቷ ህገ ወጥ አያሰኝም፡፡ በቦታው ላይ 5 ክፍል ቤት ሠርታበታለች፣ ይዞታው ሁሉ ተለውጧል፣ ሽያጩ በአግባቡ ስለሆነ ሊፈርስ አይገባም፣ ብር 120,000 ነው የቤቱ ግምት ያሉት በክሱ እንዲከፈላቸው የጠየቁት ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑ ሊፀና ይገባል የሚሉትን ክርክሮች አቅርበዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሮቹ ይዘት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሲሆን ጉዳዩም ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ለክርክሩ መነሻ ሆኖ የተገኘው ቤት የአሁኗ አመልካች አባትና አውራሽ የሆኑት የሟቹ የአቶ ጌታቸው በላይ ንብረት መሆኑና 1ኛዋ ተጠሪ የአሁኗን አመልካችን አባቷ እንደሞቱ ገና የ6 አመት ህፃን ልጅ እያለች ወስዳት አብራቸው እየኖረች ባለበት ወቅት የሟች ልጅ መሆኗን እያወቀች 1ኛ ተከሣሽ ከነበረው ከአቶ በላይ በየነ ጋር በመሆን የሟች ወራሾች እኛነን ብለው ለፍ/ቤት በማመልከት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው አድርገው የሟቹን ቤት የባለሃብትነት ሥም በራሣቸው ሥም በማዛወር ልጃቸው ለሆነችው ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በመሸጥ በሥሟ እንዲዛወር ማድረጋቸው፣ በሥር ፍ/ቤት በተደረጉ ክርክሮችና በቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡

ከወላጆቿ ቤቱን ገዝታለች የምትባለው የአሁኗ 2ኛ ተጠሪም የአሁኗ አመልካች የሟች የአቶ ጌታቸው በላይ ልጅ ስለመሆኗና ቤቱም ቀደም ሲል የሟቹ ንብረት መሆኑን አላውቅም አትልም፡፡

የአሁኗ አመልካች አብራቸው እየኖረችና እንደ ሞግዚትም ሆነው እያሳደጓት እያሉ አካለመጠን ያልደረሰችውን ልጅ የአባቷን የውርስ ሀብት ጠብቀው በሥርዐት እንዲተላለፍላት ማድረግ ሲገባቸው ሆነ ብለው አካለመጠን ባልደረሰችው ልጅ ላይ ጉዳት ለማድረስና መብቷን ለማሳጣት፣ ለራሣቸው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት የፈፀሙት ድርጊት መሆኑን ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች መረዳት ይቻላል፡፡

በእንዲህ አይነት መንገድ አካለመጠን ላልደረሰችው ልጅ በሕጉ አግባብ በውርስ ሊተላለፍለት የሚገባውን ንብረት አሳዳጊዎቿ የነበሩት ሰዎች የሟቹ ወራሾች እኛ ነን ብለው የወራሽነት ማስረጃ በመውሰድ ቤቱን ለገዛ ልጃቸው ሸጥዋል ተብሎ መገኘቱ በሕጉ የሚኖረው ውጤት ምንድ ነው? ቤቱ ለህጋዊ ወራሿ እንዲለቀቅ የማይደረግበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም የሚለውን በተመለከተም የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2884(1) ላይ የተመለከተው ድንጋጌ የተሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል የሻጩ ሀብት ሣይሆን የቀረ እንደሆነ የመነቀልን የአላፊነት ዋስትናን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ያስረዳል፡፡ እነዚህ የመነቀልን የአላፊነት ዋስትና የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ደግሞ የአንድን ነገር ባለሃብትነት ማስተላለፍን ስለሚመለከቱት ውሎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መካከል ከፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2282 - 2285 የሚገኙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የተሸጠው ነገር ሌላ ሰው በነበረው መብት ምክንያት ይለቀቅልኝ በሚል ለሚቀርበው ጥያቄ ለገዢው መድን የሚሆነው ሻጩ ነው፡፡ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2284(2) የተሸጠው ነገር ለይለቀቅልኝ ባዩ በሚለቀቅበት ጊዜ በውላቸው ላይ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ ሻጩ በሽያጩ የተቀበለውን ዋጋ ለገዢው የመመለስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የሚደነግግ



www.chilot.me

ነው፡፡ ድንጋጌዎቹ ለማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2884 ድንጋጌ እና በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2884(2) እንዲሁም በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2285 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተያይዘው በአንድነት ሲታዩ የተሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል የሻጩ ሀብት ሣይሆን የሌላ ሰው ሀብት ሆኖ ከተገኘ ገዢው እንደሚነቀል ወይም እንዲለቅ የሚደረግ ስለመሆኑ የሚጠቅሱ ናቸው፡፡ ገዢው በሕጉ ያለው መፍትሄ ሻጩን መጠየቅ ነው፡፡

በሌላም በኩል አንድ ሰው አንድን ንብረት በሽያጭ ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ ትክክለኛ ህጋዊ ባለመብት ሲሆን ወይም በሕጉ አግባብ የንብረቱ ህጋዊ ባለመብት የሆነው ሰው የመሸጥና የመለወጥ ሥልጣን ሰጥቶት ሲገኝ ነው፡፡ የሌላውን ሰው ንብረት ንብረቴ ነው ብሎ መሸጥ ከሕጉ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ህገ ወጥ ነው፡፡ ሕገወጥ ውል ደግሞ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1716 መሠረት ፈራሽ ነው፡፡ ገዢው ከንብረቱ የሚነቀለው ወይም ለህጋዊ ባለመብቱ እንዲለቅ የሚደረገውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በቀረበው ጉዳይም የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ እና ክሱ ሲቀርብ 1ኛ ተከሣሽ የነበሩት አቶ በላይ በየነ የአሁኗ አመልካች የሟቹ የአቶ ጌታቸው በላይ ልጅ መሆኗን እየወቁና ወስደዋት በማሣደግ ከእነርሱ ጋር አብራቸው እየኖረች እያለ እኛ ነን የሟች ወራሾች ብለው ማስረጃ በመውሰድ በውርስ ለአመልካች ሊተላለፍ የሚገባውን ቤት በሥማቸው በማዛወር ከልጃቸው ከ2ኛዋ ተጠሪ ጋር አድርገናል የሚሉት የመሻሻጥ ውል ከዚህ የተለየ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ በወቅቱ አካለመጠን ካልደረሰችው የሟች ልጅ ንብረቱን ለማሸሽ ወላጆችና ልጅ ያደረጉት የሚችን ቤት መሻሻጥ ውል ህጋዊ ሊሆን አይችልም፡፡

የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁኗ አንዳኛ ተጠሪ እና አቶ በላይ በየነ ወራሾች ነን ብለው የቤቱን ሥመ ባለሃብትነት በሥማቸው በማዛወር ለልጃው ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ በብር 50,000 ከሸጡላት ቤቱን ለአሁኗ አመልካች ማስረከብ የለባትም፣ ቤቱን ሽጣ ጥቅም ያገኘችው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ስለሆነች ገንዘቡን ትመልስላት ያለውም ሥመ ባለሃብትነቱን በሥማቸው ማዘወራቸው ውሉን ህጋዊ ሊያደርገው ስለማይችል ተቀባይነት የለውም፡፡

2ኛዋ ተጠሪ ለቤቱ ዋጋ ብር 50,000 ለሻጮች ከፍላ ከሆነ በሕጉ መሠረት እንዲመልሱላት መጠየቅ ይኖርባታል፡፡

በሕጉ 2ኛዋ ተጠሪ ቤቱን ለህጋዊ ባለመብቷ ለመልቀቅ ትገደዳለች፡፡

ሲጠቃለል ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በህጋዊ መንገድ የገዛችው ስለሆነ ለአሁኗ አመልካች ልታስረክብ አይገባም፣ ቤቱ ተሸጧል የተባለበትን ዋጋ ብር 50,000 የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ትክፈል በሚል የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያለው በመሆኑ የሚሻርበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 31069 በ18/02/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(2) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 30843 በ05/09/2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 6429 በ26/08/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56011

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሳሙኤል ታደሰ አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** ወ/ት እጥፍ ወርቅ ኃይለማርያም አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የአፈፃፀም ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር የቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት አመልካች የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ንብረት የሆነ የኮንደሚኒየም ቤት ያለ በመሆኑ ቤቱ ተሽጦ በፍርድ የተረጋገጠለትን ገንዘብ ቤቱ በሀራጅ ተሽጦ እንዲከፈል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 በሠራተኛ ሠፈር ሣይት የህንፃ ቁጥር 01 የቤት ቁጥር 52-Bs-2506 የወለል ቁጥር 002 የቤቱ ስፋት 43.37 ካሬ ሜትር የሆነውን ኮንደሚኒየም ቤት በሐራጅ በመሸጥ ለፍርድ ቤት ባለመብት ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺ ብር/ በታህሣሥ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከ አለቀ ድረስ ከሚታሰብ ከአሥራ ሁለት በመቶ ወለድ ጋር እንዲከፈል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙ ፍሬ ነጥብ የሌለው መሆኑን በመግለፅ ሰርዞታል፡፡

አመልካች ግንቦት 9 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት በፍርድ የተወሰነብኝን ገንዘብ ለመክፈል የአንድ ወር ጊዜ እንዲሰጠኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ አለመቀበሉ የፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 186/2/ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኮንደሚኒየም ቤቱ አምስት ዓመት ሣይሞላው ለዕዳ መክፈያነት እንዲሸጥ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ የአዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 14/2/ እና አንቀፅ 21 እንደዚሁም የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 404/ሰ/ የተደነገገውን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ

በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ዕዳውን ያለመክፈል የተለያየ ሰበብ እየፈጠሩ አጉላልተውኛል፡፡ አዋጅ ቁጥር 19/97 የቤቱ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ዕዳው ተከፍሎ ሲያልቅ መሆኑን ከሚደነግግ በስተቀር ገንዘብ የተበደረና የኮንደሚኒየም ቤት ያለው ሰው ዕዳው ቤቱ ተሸጦ እንዳይከፈል አይከለክልም፡፡ ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተገቢ ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ታህሣሥ 22 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የፍርድ ባለዕዳ መሆናቸው በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ ባለዕዳ መሆኑ በፍርድ የተረጋገጠበት ሰው በፍርድ የተወሰነበትን ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ የማይከፍልበት በአፈፃፀም ወቅት ሊያነሣው የሚችለው መከራከሪያ ያለው ስለመሆኑ አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲያስረዳ ፍርድ ቤቱ እድል የሚሰጠው መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 378/1/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በፍርዱ መሠረት ፈፅሞ ከሆነ ፍርዱን የፈፀመ መሆኑን በፍርዱ መሠረት ያልፈፀመ ከሆነ ያልፈፀመበትን ምክንያት ሲጠየቅ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለመፈፀም ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን የአመልካችን ተጨማሪ ጊዜ ይሰጠኝ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የፍርድ አፈፃፀሙ በአመልካች ንብረት ላይ የሰጠው ትዕዛዝ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠኝ ይገባ ነበር በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ አመልካች ለፍርድ አፈፃፀምና ለአመልካቿ እዳ መክፈያ ይሆን ዘንድ የኮንደሚኒየም ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ የአዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 2 እና አንቀፅ 21 የሚጥሱና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ስንመረምረው ከላይ የተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ጠቅላላ ዋጋውን ከፍሎ ያጠናቀቀ የኮንደሚኒየም ቤት ባለሃብት የሆነው ሰው ክፍያ ያጠናቀቀበትን የኮንደሚኒየም ቤት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሸጦ ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዳይሆን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ሆነው አላገኘናቸውም፡፡ የአዋጅ ቁጥር 19/94 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ቃል በቃል ሲነበብ "ገዢው ጠቅላላ ዋጋውን ከፍሎ ቢያጠናቅቅም ቤቱን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ የሚቻለው ቤቱን ከገዛ በኋላ አምስት ዓመት ሲሞላው ብቻ ይሆናል" በማለት የሚደነግግ ሲሆን የአዋጁ አንቀፅ 21 ከአዋጁ ጋር የሚቃረን የተለመደ አሠራር ወይም ህግ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የለውም በማለት የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡

የአዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 14/2/ የኮንደሚኒየም ቤት ዋጋ ከፍሎ ያጠናቀቀ ባለሃብት ቤቱን የመሸጥ የመለወጥና ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብቱን በተሟላ ሁኔታ ተግባር ላይ የሚያውለው ከአምስት ዓመት በኋላ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ድንጋጌው የኮንደሚኒየም ቤት ባለሃብት የሆነው ሰው በራሱ ፈቃድና ፍላጎት ቤቱን በሽያጭ ወይም በስጦታ ስለሚያስተላልፍበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የቤቱን ዋጋ አጠቃሎ የከፈለ የኮንደሚኒየም ቤት ባለሃብት እንዲከፍል በፍርድ የተወሰነበት የሌላ ሰው ዕዳ ያለበት በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ዕዳው ተጠቃልሎ የተከፈለውን የኮንደሚኒየም ቤት በሀራጅ ተሸጦ ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ትዕዛዝ ከመስጠት

የሚከለክል ወይም ሥልጣናቸውን የሚገድብ የህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ አመልካች የጠቀሱት የአዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 21 ዋጋው ተጠናቅቆ የተከፈለውን የፍርድ ባለዕዳ የኮንደሚኒየም ቤት ፍርድ ቤቶች በሀራጅ ተሸጦ ለፍርድ ማስፈፀሚያ ከማድረግ የሚገደብ ይዘት ያለው ድንጋጌ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የፍርድ ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ በሀራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጡበት የኮንደሚኒየም ቤት በህግ ለሌላ ሰው እንዳይሸጥ ክልከላ የተደረገበት ነው በማለት የአዋጅ ቁጥር 19/77 አንቀፅ 14/2/ እና አንቀፅ 21 ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 404/ሰ/ ጋር በማጣመር ያቀረቡት ክርክር የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ግብ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍርድ ቤት በማፅናት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49428

ኀዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካቾች**፡- 1. ወ/ሮ ከበቡሽ ልሳነርቅ } የቀረበ የለም

2. ወ/ሮ መና ገብረ አጋይስት

**ተጠሪ**፡- 1. አቶ ፀዳሉ አዳነ የቀረበ የለም

2. የጐንደር ከተማ አገ/ጽ/ቤት- ከክርክር ውጪ ሆኗል፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የቤት ሽያጭ ውልን አፈፃፀም የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ ነው፡፡ የዳኝነት ጥያቄውም ጥር 9 ቀን 1989 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ከ1ኛ አመልካች የገዛውን ቤት ስመ ሐብት እንዲያዛውርለት እና ካርታ በስሙ እንዲሰራለት ማዘጋጃ ቤቱ ተጠይቆ ፈቃደኛ ስላልሆነ በፍርድ ሃይል ተገዶ ይፈጽምልኝ የሚል ነበር፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ ያከራከረው የከተማ ነክ ፍ/ቤት ማዘጋጃ ቤቱ አስተዳደራዊ ተግባሩን እንዲያከናውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የአመልካቾችን መቃወሚያ ባለመቀበል ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360/2/ መሰረት አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለከተማው ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አልተቀበለም፡፡

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቀርቦለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕግ ስሕተት የለውም በማለት አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ የጐንደር ከተማ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የዳኝነት



www.chilot.me

ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውንና ተጠሪ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተደረገ የሽያጭ ውል በማቅረብ ስም ይዛወርልኝ፤ ካርታ ይሰራልኝ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለው ወይንስ የለውም? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በይዘቱ ሲታይ የ1ኛ ተጠሪ ክስ በይርጋ ያልታገደ ስለመሆኑ፣የተጠየቀው ዳኝነትም በሕግ የተመሰረተ ውል መሰረት ያደረገ ስለመሆኑና የጐንደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና በግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር የተያዘውን ጭብጥ መሰረት አድርገን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የመጀመሪያው ጭብጥ የጐንደር ከተማ ፍ/ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣንን በተመለከተ ነው፡፡ በመሰረቱ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በሕግ የሚወሰን መሆኑ እሙን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው በግዥ ውል የተላለፈለትን መብት መሰረት በማድረግ የከተማው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥን የሚመለከት ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በአማራ ብ/ክ/መ/በወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ደንብ ቁጥር 12/2000 በተደነገገው መሰረት ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል በማለት ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች የወሰኑት ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን እንደተሰጣቸው በሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት በመሆኑ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሥልጣን መሰረት የለውም የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ ውልን በመያዝ ክስ የማቅረብ መብት አለውን? የሚለውን በተመለከተ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው 1ኛ ተጠሪ በግዥና ሽያጭ ውል ያገኘውን መብት መሰረት በማድረግ 2ኛ ተጠሪ ስም የማዛወር ግዴታ እና ካርታ የመስጠት ተግባር አልተወጡም በሚል መነሻ ክስ አቅርቧል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 33945 በሰጠው ውሳኔ እንደተመለከተው ገዥ በሽያጭ ውሉ መሰረት ስም ይዛወርልኝ ጥያቄን መሰረት በማድረግ ሻጭ ላይ የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም፡፡ ይልቁንም ይህ ተግባር የአስተዳደር አካል ተግባር ነው በሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን የከሰሰው የአስተዳዳር ተግባር አልተወጣልኝም በሚል ነው፡፡ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሰበር መዝገብ ውሳኔ መረዳት የሚቻለውም አስተዳደሩ በሕግ የተሰጠውን ተግባር ካልተወጣ ገዥ መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚገበው በአስተዳደር አካሉ ላይ ስለመሆኑ ነው፡፡



www.chilot.me

ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የ1ኛ ተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በሕግ አተገባበር ወይም አፈፃፀም ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህም ወሳኔው ባለበት ሁኔታ ሊፀና ይገባል ብለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በጉንደር ከተማ ነክ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00449 በ01/07/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፣የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00226 የሰጠው ትእዛዝ እና የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 01571 በ29/10/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሳኔ 2ኛ ተጠሪ የሚያቀርቡትን የሽያጭ ውል መነሻ ያደረገ የመብት ጥያቄ የሚገድብ አይደለም፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57045

ጥር 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች ፡-** ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ፅ/ቤት -

ምርመራና ክስ ኤክስፐርት አቶ ሰይፉ ይፍሩ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተስፋዬ አሰፋ - ጠበቃ አዜብ ገ/ወልድ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 406 በሆነው ቤት ውስጥ ከወላጅ እናታቸው ወ/ሮ አበበች ፍሰሃ ጋር ሲኖሩ እናታቸው በ28/05/1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ከሌሎች ተወላጆች ጋር ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የቤቱን ኪራይ በራሳቸው ስም እንዲዞር በማድረግ በቤቱ በመገልገል ላይ እያሉ አመልካች ያላግባብ ከቤቱ እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ የሰጣቸውና ይህም ተግባር ሁከት መሆኑን ገልፀው ሁከቱ እንዲወገድ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ለተጠሪ ሳይሆን ለወ/ሮ ቀለሟ ታየ በመሆኑ ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በአማራጭ ደግሞ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 406 የሆነውን ቤት ለቀው እንዲያስረክቡ ማስጠንቀቂያ የተሠጠው የሟች አበበች ፍሰሀ ልጅ ለሆኑት እና በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 967 የሆነ የቀበሌ ቤት በስማቸው ላለው ለወ/ሮ ቀለሟ ታዬ ሲሆን አንድ ግለሰብ ሁለት የመንግስት ቤት ሊይዝ ስለማይችል ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን ተገቢ ነው፣ ተጠሪ ወራሽነት ያገኙትም ያላግባብ ነው፣ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ አበበች ፍሰሀ ልጅ ሳይሆኑ የሟች እህት ልጅ ሁነው የሚኖሩትም በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 የቤት ቁጥር 779 በሆነው ቤት ውስጥ ከእናታቸው ከወ/ሮ ይመኙሻል ፍሰሀ እና ከአባታቸው ከአቶ አሰፋ አባተ ጋር ነው በማለት ክሱ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአመልካች በኩል የቀረቡትን የክርክር ነጥቦች ውድቅ አድርጎ በአመልካች የተሠጠው ማስጠንቀቂያ ይዘቱ ተጠሪ በቤቱ



www.chilot.me

ላይ እንዳይኖሩ የሚያደርግ በመሆኑ ተግባሩ ሁከት ነው በማለት ሁከቱ እንዲወገድ፣ የተለያዩ ወጪዎች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሰኔ 08 ቀን 2002 ዓ.ም የጻፉት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በአከራካሪው ቤት በወራሽነት የኪራይ መብት አግኝቼአለሁ የሚሉት በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ተገልፆ ቀበሌ የሚያስተዳድረውን ቤት እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ መፃፉ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ ሊወሰድ የማይገባው በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች ተግባር ሁከት ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሕጋዊ መሆኑን በመዘርዘር ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል ግንኙነቱ ተጠሪ የሚባለው በአመልካችና ተጠሪ እናቴ ናቸው የሚሏቸው ወ/ሮ አበበች ፍሰሃ ባደረጉት የቤት ኪራይ ውል መሆኑን፣ ተጠሪ ሚቿ ያላቸው የተከራይነት መብት በፍርድ ቤት ተረጋግጦ በተሰጣቸው የወራሽነት ማስረጃ ተላልፎልኛል በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም አመልካች ይኸው የወራሽነት ማስረጃ የተገኘው በተጭበረበረ መንገድ ነው በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የክርክሩ ይዘት የሚያሳየው ክርክሩ መሰረት ያደረገው የኪራይ ውሉን መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ሊጽፍ የቻለውም ቤቱ ያላግባብ ተይዟል በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊቀርብ የሚችለው ይዞታውን በእውን በሚያዘው ሰው አጠቃቀም ላይ ችግር ወይም መሰናክል ሲፈጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል፡፡ ባለይዞታው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ ይዞታውን በግልፅ ሁኔታ የያዘው መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በባለይዞታውና ሁከቱን ፈጠረ በተባለ ሰው መካከልም የተፈጠረው ግንኙነት ካለ ግንኙነቱ የሚገዛበት የሕግ አግባብ ተለይቶ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የአከራካሪው ቤት ባለቤት መሆኑ የሚያከራክር ሳይሆን ተጠሪ ወራሽ ነኝ ካሉ ከተጠሪ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ደግሞ የአከራይና የተከራይ ነው፡፡ ይህ ግንኙነት በመጀመሪያ የተፈጠረው በቀጥታ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሳይሆን በአመልካችና ተጠሪ አውራሼ ናቸው በሚሉት በሚች ወ/ሮ አበበች ፍሰሃ መካከል ነው፡፡ አመልካች ደብዳቤውን ሊፅፍ የቻለው ተጠሪ ቤቱን በሕጉ አግባብ የተከራዩት አይደለም በማለት መሆኑን ከክርክሩ ሂደት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ ሰፊ የሆነ የባለቤትነት መብት ካለው አመልካች ጋር ሊከራከሩ የሚችሉት በሕጉ አግባብ የተደረገ የኪራይ ውል መኖሩን በማሳየት በውሉ መሰረት መብታቸው እንዲጠበቅላቸው እንጂ የሁከት ይወገድልኝን ክስ በማቅረብ

ሊሆን አይችልም፡፡ ተጠሪ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ የወራሽነት ማስረጃ መያዛቸውም አመልካች ማስረጃውን በቅድሚያ እንደያሰርዝ የሚያስገድደው ካለመሆኑም በላይ ማስረጃው ዋጋ የለውም የሚለውን ተቃውሞ በማናቸውም የክርክር ደረጃ ከማቅረብ የሚከለክለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ የሚገዛው የኪራይ ግንኙነትን በሚገዙት ድንጋጌዎች ሆኖ እያለ አመልካች ማስጠንቀቂያ መፃፉን በመመልከት ብቻ ተግባሩ ሁከት ነው በማለት የደረሱበት ድምዳሜ በአመልካችና በተጠሪ መካከል አለ የተባለውን ግንኙነት ስለሁከት አጠቃላይ ይዘትና በዚህ ረገድ በፍርድ ቤት ስለሚጠየቀው መፍትሔ ከባለቤትነት መብት አድማስ ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ መጻፉ ሁከት ሊባል የሚችል አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት ሕጋዊ የኪራይ ውል አለ የሚሉ ከሆነ ይህንኑ መሰረት በማድረግ መብታቸውን ከሚያስከብሩ በስተቀር በአመልካች ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ራ/ታ



www.chilot.me

# ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53749

ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች ፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ - ነ/ፈጅ እመቤት ባዩ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አዱኛ አበሉ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያላግባብ የተከፈለ ቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባሁኑ አመልካች ላይ ሐምሌ 04 ቀን 1998 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከቱርክ አገር ሶስት ማሽነሪዎችን ሰኔ 09 ቀን 1995 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ማስገባታቸውን ለማሽነሪዎች የተሳሳተ ቁጥር 85489000 የሆነ የታሪፍ ኮድ እንዲሰጣቸው ተደርጎ የዋጋቸውን 40% ብር 40,514.02 እንዲከፍሉ መደረጉን ይህንኑ ገንዘብ እቃውን ለመረከብ ሲሉም መክፈላቸውንና እቃዎቹ በትክክለኛ የታሪፍ መጠን ተቀርጠው በአብላጫ የከፈሉት እንዲመለስላቸው አመልክተው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን መስከረም 04 ቀን 1996 ዓ.ም ለአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ በጻፈው ደብዳቤ በትክክለኛ የታሪፍ መደብ እንዲስተናገዱ በሚል ማሳወቁን በትክክለኛው ኮድ ሊከፍሉ ይችሉ የነበሩት የገንዘብ መጠንም የዋጋውን 5% ብር 12,510.42 መሆኑን ዘርዝረው በአብላጫ የተከፈለው ብር 28,003.06(ሃያ ስምንት ሺህ ሶስት ብር ከዜሮ ስድስት ሳንቲም) ከወለድ እንዲሁም ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካችም በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 55 መሰረት በአብላጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስን መመለስ የሚቻለው እቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባበት በስድስት ወር ውስጥ የታወቀ የሆነ እንደሆነ እንጂ እንደተጠሪ እቃው መስከረም 27 ቀን 1995 ዓ.ም አስገብቶ እቃውንም ህዳር 13 ቀን 1996 ዓ.ም አውጥቶ ከወሰዱ በኂላ አይደለም ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ በአብላጫ የተከፈለ ቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄ ያቀረቡት በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 55 ስር በተመለከተው የስድስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ አይደለም በማለት ክሱን በይርጋ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኂላ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የስር ፍርድ ቤት የጠቀሰው



www.chilot.me

ድንጋጌ ክፍያ ላይ ስህተት ሲፈጠር የሚፈፀም እንጂ ያላግባብ ለተከፈለ ክፍያ የሚሆን አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ መሰረት የሆነውን የገንዘብ መጠን ክሱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ (9%) ዘጠኝ በመቶ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ይርጋውን በተመለከተ አመልካች ያቀረበው ክርክር የታለፈው ከአዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለ አንቀጽ 55፣ 53 ድንጋጌዎች ውጪ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የትኛው ነው የሚለውን ነጥብ ለመለየት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ ተጠሪም በጠበቃቸው ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ አንድ ገፅ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ይርጋ መደበኛው ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ አመልካች አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አንቀጽ 53 እና 55 መሰረት አድርጎ ያቀረበው የይርጋ ክርክር የመታለፉ አግባብነት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ያላግባብ የከፈልኩት የቀረጥ ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ጥያቄው በስድስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበና በሕጉ አግባብ የተፈፀመ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የዋጋ ኢንቮይስ ውድቅ የሆነበት ቀረጥ ከፋይ ቅሬታ ካለው በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 53 መሰረት ለተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አቅርቦ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ የሚችል ሲሆን በዚሁ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ቅሬታ ካለው ብቻ ወደሚመለከተው ፍርድ ቤት መሄድ የሚችል መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አከራካሪ ስለሆኑ ጉዳዮች በሚለው በእቃዎች ዋጋ አተማመን፣ በታሪፍ አሰያየምና አመዳደብ እንዲሁም በታሪፍ ልክ ላይ ተቃውሞ የቀረበ እንደሆነ የተቃውሞ ነጥብ ከተመዘገበ በኋላ የጉምሩክ ሹም በሚወስነው መሰረት ቀረጡ እንደሚከፈል በተቃውሞ የተከፈለው ቀረጥ ጉዳዩ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ በባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ እንደሚሰጥበት ባለጉዳዩ በውሳኔው ካልተስማማ በውሳኔው አለመስማማቱን ገልፆ በሰላሳ ቀናት ውስጥ በፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ያለበት መሆኑን አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡ ይህ ስርዓት ሳይፈፀም በቀጥታ በፍ/ቤት ክስ የሚመሰረትበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከተጠቀሰው ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በሕጉ ላይ የተመለከተው የስነ ስርዓት



www.chilot.me

ጥያቄ ነው፡፡ ይኸው የስነ ስርዓት ጉዳይም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት ባግባቡ መፈፀም አለበት፡፡ ይህ ለአስተዳደራዊ ውሳኔም የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎም ይታሰባል፡፡

በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለከፋዩ ሊመለስ እንደሚገባ አዋጁ በአንቀፅ 55 ስር በግልፅ ደንግጓል፡፡ ይህንኑ ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 15 ድንጋጌ ደግሞ ቀረጡ ተመላሽ የሚደረገው ስህተቱ መኖሩን ባለሥልጣኑ እንዳወቀ ወይም ባለቤቱ ጥያቄ እንዳቀረበ ይሆናል በሚል ካስቀመጠ በኋላ ቀረጡ ተመላሽ የሚደረገው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አጠናቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጪ ሀገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወራት ውስጥ ስህተቱ የታወቀና ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ነው በማለት ፍጹም የሆነ የይርጋ ጊዜ ደንግጓል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ መኖሩን አረጋግጠው ክፍያው እንዲፈፀምላቸው የጠየቁት እቃው ወደ አገር ከገባ ከአንድ አመት አስራ አንድ ወራት በኋላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች መስሪያ ቤት ሹም በብልጫ የተከፈለ ቀረጥ እንዲመለስላቸው በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 53 መሰረት ጥያቄ አቅርበው ተገቢ ውሳኔ ተሰጥቶ ክሱን ፍርድ ቤት የመሰረቱ ሳይሆን ቀረጡ በስህተት መከፈሉን ተገንዝበው ስህተቱ ተስተካክሎ በብልጫ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስላቸው አቤቱታ አቅርበው ተገቢው እንዲፈፀም እናት መስሪያ ቤት ለቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የፃፈውን ደብዳቤ መሰረት አድርገው መፍትሔ ሳያገኙ ሲቀሩ በፍርድ ቤት ክስ መስርተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄያቸውን በአዋጁ መሰረት እቃውን ከውጪ ከአስገቡ በኋላ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ አላቀረቡም፡፡ ይህም የሚያሳየው የአመልካች ጥያቄ በሕጉ የተገደበ መሆኑን ሲሆን አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 55 መሰረት ያነሱት እና የተጠቀሙበት ተቃውሞ አለመኖሩን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ክስ የመሰረቱበትን የቀሪ ቀረጥ ክፍያ ጥያቄ በተጠሪዎች በኩል በአዋጁ አንቀጽ 53(1) መሰረት ተቃውሞ ቀርቦ ተገቢው ለውጥ ባልተደረገበት ሁኔታ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 55 መሰረት በስድስት ወር ጊዜ ያልቀረበ የቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ ባለመኖሩ በፍርድ ቤት ክስ መመስረታቸው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች መሻሩ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የአዋጁን ቁጥር 55 ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59693 መጋቢት 17 ቀን 2001 ተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 45757 ታህሳስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 73056 ሐምሌ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የተጠሪ የቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄ በስድስት ወር ይርጋ የታገደ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54203
ኅዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የኢት/ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ሙሉእመቤት ኃ/ሚካኤል - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የተጠሪን መኪና ያለአግባብ ይዟል ተብሎ መኪናውን እንዲመልስና የተቋረጠ ገቢ ብር 9944.44 እንዲከፍል የተሰጠው ውሣኔ እንዲታረም አመልካች ስላመለከተ ነው፡፡

የጉዳዩ አጀማመር ባጭሩ ሲታይ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 3-01017 አ.አ የሆነ መኪና አመልካች ያለአግባብ ይዞ በቁጥጥር ሥር አቆይቷል፡፡ መኪናውን እንዲለቅ እና መኪናው በመቆሙ የተቋረጠ ገቢ ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ ሲሉ ተጠሪ ያቀረቡትን ክስ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ መኪናው እንዲመለስ እና የተቋረጠ ገቢ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን መጠን አመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች በውሣኔው ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዟል፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በሕግ የተሰጠውን ተግባር ሲያከናውን ይዞ ያቆየውን መኪና አስረክብ መባሉ እና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍል መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 73 እና 78 አኳያ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በይዘቱም ተጠሪ በመንግሥት ፈቃድ ከውጪ ሀገር ያስገቡት መኪና ስለመሆኑ ገልጸው ይህ መኪና ለንግድ ሥራ እንዲውል የፌዴራል የመንገድና ትራንስፖርት ባለሥልጣን ፈቅዶላቸው እየሰሩበት ስለመሆኑና ይህም በአመልካች አውቅናና ስምምነት ለመሆኑ ዘርዝረው በመግለጽ መኪናው መያዙ ሕገ ወጥ ተግባር ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ክርክሩን አጠናክሮ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡



www.chilot.me

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተ ሲሆን እኛም በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች በሥር ፍ/ቤት አጥብቆ የተከራከረው ተጠሪ ከቀረጥ ነፃ ለግል አገልግሎት ከውጪ ሀገር ያስገቡትን መኪና ተገቢው ቀረጥ ሳይከፈልበት ለንግድ ሥራ አውለውት በመገኘታቸው ድርጊቱ በሕግ የተከለከለ በመሆኑ ይህንኑ ለማጣራት በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መኪናውን በቁጥጥር ሥር ያዋለ ስለመሆኑ እና ይህም በሕግ የተቀበለው ሃላፊነት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ ነው፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያና ሥልጣንና ኃላፊነትን የተመለከተው አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/1/ እንደሚያመለክተው ከቀረጥ ነፃ የገባ እቃ ለሌላ አገልግሎት ማዋል ሕገወጥ ተግባር አለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህንንም ተግባር እንዳይፈጸም ለመከላከል እንዲሁም ተፈጽሞ ሲገኝ መመርመር እና ሕጋዊ ውሣኔ የማሰጠት ኃላፊነት ለጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠ ስለመሆኑ የጉምሩክ አዋጅ ይዘት ያመለክታል፡፡

ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 368/95 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 78 ላይ እንደተደነገገው የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ የተገኙ እቃዎችን እና ማጓጓዣዎችን አግባብ ያለው የመጨረሻ ውሣኔ እስኪሰጥባቸው ድረስ መያዝና በቁጥጥር ማዋል ይቻላል በማለት ተደንግጓል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የተንቀሳቀሰ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪም መኪናውን ከቀረጥ ነፃ ለግል አገልግሎት ከውጪ ሀገር ያስገቡ ስለመሆኑ አምነው ነገር ግን መኪናው ለንግድ ሥራ እንዲውል የተደረገው በፌዴራል የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ፈቃድ እና በአመልካች እውቅናና ስምምነት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንግዲህ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር አንፃር መኪናው ለተጠሪ ሊመለስ ይገባል ወይንስ አይገባም? አመልካች መኪናውን በመያዙ የተቋረጠ ገቢ ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይንስ የለበትም የሚሉት ጭብጦች ውሣኔ ከማግኘታቸው በፊት ተጠሪ መኪናውን በምን ሕጋዊ አግባብ ለንግድ ሥራ አገልግሎት እንዲውል አደረጉት? ይኸው ከቀረጥ ነፃ የገባው መኪና ለንግድ ሥራ አገልግሎት ሲንቀሳቀስ በመልካች መያዙ ሕጋዊ አካሄድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው መሠረታዊ ጭብጥ ምላሽ የሚያሻው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

የሥር ፍ/ቤት እነዚህን ጭብጦች ከግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ አንፃር ከሕጉ በማገናዘብ ሳይመረምር አመልካች የተጠሪን መኪና ያለፍርድ በቁጥጥር ሥር ማድረጉና መወረሱ ተገቢ አይደለም ከሚል የተሣሣተ ድምዳሜ ደርሷል፡፡ በመሠረቱ አመልካች የተጠሪ መኪና ተወርሷል የሚል ክርክርም አላቀረቡም፡፡

ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ በተደነገገው አግባብ የግራ ቀኙን ክርክር መሠረት በማድረግ ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ በአግባቡ በማጣራት ውሣኔ መስጠት እየተገባው አመልካች መኪናውን እንዲመልስ እና የተቋረጠ ገቢ ለተጠሪ እንዲከፍል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በከፍተኛው ፍ/ቤትም ይኸው ውሣኔ መጽናቱ ተገቢውን የክርክር አመራር ሥርዓት ያልተከተለ እና ከሕጉ ጋር በአግባቡ ያልተገናዘበ ሆኖ ስላገኘው ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡



www.chilot.me

በመሆኑም በክርክር አመራር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 137829 ሰኔ 24 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83090 መጋቢት 2 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የተጠሪ መኪና ሊመለስ ይገባል? ወይንስ አይገባም? የተቋረጠ ገቢ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይንስ የለበትም? የሚለውን ጭብጥ ከመወሰኑ በፊት ተጠሪ ከቀረጥ ነፃ ያስገቡትን መኪና ለንግድ ሥራ አገልግሎት ያዋሉት በሕግ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም? አመልካች የተጠሪን ድርጊት ለመመርመር ሲል መኪናውን መያዙ ተገቢ ነው ወይንስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች ከግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ አንፃር መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፤ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 50375

ህዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፡- ሙሉእመቤት ውባየሁ ቀረበች

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ለተብርሃን አድሐኖም፡- ጠበቃ ተሰማ አበበ - ቀረበ

2. ሴፍ ትራንዚት ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>**ፍ ር ድ**</u>

ጉዳዩ በቀሪ ይፈለጋል የተባለውን ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው አመልካች 1ኛ ተጠሪ ከውጪ ሃገር ላስመጣቻቸው የአገለገሉ የፊያት መኪና ኢንጅኖች መክፈል የነበረባት ቀረጥና ታክስ ብር 526,654.25 ሆኖ ሳለ ብር 28,218.18 ብቻ ስለከፈለች ቀሪውን ትክፍል ዘንድ ይወሰንልኝ፡፡ 2ኛ ተጠሪም ወኪል በመሆኑ የጋራ ሃላፊነት አለበት ይባልልኝ በማለት ክሱን አቅርቦአል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ካሰማ በኋላ፣ 1ኛ ተጠሪ ላስመጣቻቸው ኢንጅኖች ልትከፍል የሚገባት ቀረጥና ታክስ ብር 28,218.18 ነው በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 4 ቀን 2002 ዓ.ም. በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ስለቀረጡ እና ታክሱ አከፋፈል በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም በግራቀኙ ወገኖች በዚህ ረገድ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በአመልካች ክስ እንደተገለጸው 1ኛ ተጠሪ የከፈለችው ብር 28,218.18 ብቻ ሲሆን፣ መክፈል የነበረባት ግን ከዚህ እጅግ ከፍያለ እንደሆነ በኋላ በተደረገው የኦዲተሮች ምርመራ እንደተረጋገጠ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ቀረጥና ታክሱ ኢንጅኖቹን ስትረከብ የከፈለችው ብቻ እንደሆነ እና ይህም በሕጉ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ተከራክራለች፡፡ 2ኛ ተጠሪም ቀረጥና ታክስ

ሊጠየቅ የሚገባው የዕቃው ባለቤት እንጂ ወኪል አይደለም የሚል የመከራከሪያ ነጥብ አንስቶአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የ1ኛ ተጠሪን ክርክር እንዳለ የተቀበለ ሲሆን፣ የሰጠው ምክንያትም አመልካች ለቀረጥና ታክሱ አተማመን መሠረት ያደረገው ሕግ ያገለገሉ የመኪና ሞተሮችን/ኢንጅኖችን/ አያጠቃልልም የሚል እንደሆነ ከውሳኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ሕግ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሥርዓት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.173/91 በአንቀድ 6(1) የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ/ክስ/ ውድቅ ያደረገው ለድንጋጌው ትርጉም በመስጠት እና ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ያገለገሉ ኢንጅኖች በድንጋጌው አይሸፈኑም በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ድንጋጌውን ወደ መተርጎም የገባው ኢንጅኖቹ በኤስ ጂ ኤስ ኩባንያ የቅድመ ጭነት ምርመራ ተደርጎላቸው ዋጋም ወጥቶላቸው የገቡ በመሆኑ መቀረጥ ያለባቸው ኩባንያው በሰጠው ዋጋ መሠረት ነው በማለት ተከሣሽ በመከራከርዋ እና አመልካች /የሥር ከሣሽ/ ደግሞ ኢንጅኖቹ አሮጌ /ያገለገሉ/ በመሆናቸው የቅድመ ጭነት ምርመራ እንዳይደረግባቸው ሕጉ ይከለክላል የሚል መከራከሪያ በማቅረቡ ነው፡፡ በእርግጥም አከራካሪው ነጥብ የሕግ ጭብጥ በመሆኑ በዚህ ረገድ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሚፈታ ነው የሚሆነው፡፡

ማንኛውም ወደ ኢትዮጵያ የሚላክ ዕቃ በማጓጓዣ ላይ ከመጫኑ በፊት የቅድመ ጭነት ምርመራ እንደሚደረግበት ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ በአንቀጽ 4(1) ተደንግጎአል፡፡ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሽፋን የእቃውን ዋጋ እና የምንዛሬውን ተመን ትክክለኛነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የአስተሻሸግ ሁኔታ እና የታሪፍ ምደባ የሚመለከት እንደሚሆንም በአንቀጽ 5 ተመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንቀጽ 4 መሠረት የሚደረገው የቅድመ ጭነት ምርመራ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው ዕቃዎች እንዳሉ ‹‹ልዩ ሁኔታዎች›› በሚል በተደነገገው በአንቀጽ 6 ተመልክተዋል፡፡ የቅድመ ጭነት ምርመራ አይደረግባቸውም የተባሉት ዕቃዎች በአንቀጽ 6(1) በዝርዝር የተመለከቱ ሲሆኑ፣ ያገለገለ ተሽከርካሪንም አጠቃለው የያዙ ናቸው፡፡ እንግዲህ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ወይም አነጋገር ከውጪ ሃገር ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው የአገለገለ ተሽከርካሪ ወይም መኪና በአንቀጽ 4 እንደተደነገገው አይነት የቅድመ ጭነት ምርመራ አይደረግበትም ማለት ነው፡፡ ተሽከርካሪው ወይም መኪና ሊሽከረከር ወይም አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው ሞተር ወይም ኢንጅን ሲኖረው እንደሆነም የሚዘነጋ አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከውጪ ሃገር ያስገባቻቸው ኢንጂኖች የፊያት መኪና ኢንጅኖች እንደሆኑ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በፊያት መኪኖች ተገጥመው ሥራ ላይ የሚውሉ ናቸው ማለት ነው፡፡ እውነታው ይህ ከሆነም ሕግ አውጪው በአሮጌ ወይም ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች (ፊያት መኪኖችን ጨምሮ) ላይ የቅድመ ጭነት ምርመራ አይደረግም እያለ ባገለገሉ ሞተሮቻቸው/ኢንጅኖች/ ላይ ግን የቅድመ ጭነት ምርመራ ይደረግባቸዋል የሚል ተቃራኒ ሃሳብ ይዞ ሕጉን ያወጣል ብሎ ማሰብ ምክንያታዊ አይሆንም፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ኢንጅኖቹ በአዋጁ አንቀጽ 6(1) አይሸፈኑም ለማለት የበቃው በዝርዝሩ ውስጥ ያገለገሉ የመኪና ሞተሮች በሚል አልተመለከተም በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ ሕግ አውጪው ሕጉን በሚተገብረው/በሚተረጉመው/ አካል በትርጉም ሊደረስበት የሚችለውን ነጥብ በሙሉ እየዘረዘረ ያወጣል ብሎ በጥቅሉ ማሰብ ተገቢም፤ ምክንያታዊም አይሆንም፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወይም መኪኖች በግልጽ እስከተመለከቱ ድረስ የመኪኖቹን/የተሽከርካሪዎቹን/ ዋነኛ አካል /አንቀሳቃሽ/ የሆነው ሞተር ተለይቶ ነው የሚታየው ወደሚለው መደምደሚያ መድረስ ትክክል አይሆንም፡፡ ሕጉም መተርጎም ያለበት



www.chilot.me

ምክንያትን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለድንጋጌው የሰጠው ትርጉም ከዚህ አንፃር ሲታይ በምክንያት ላይ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የሕግ አተረጓጎም ስልት ላይ በመመሥረት የተሰጠ ነው የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

በመቀጠል የተመለከትነው አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ከተባለ በምን አይነት አግባብ ሊታረም ይገባል የሚለው ነው፡፡ ከላይ በዝርዝር እንዳየነው የሥር ፍ/ቤቶች ክሱ ተቀባይነት የለውም እሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው እና ለዚህ ድምዳሜአቸው መሠረት ያደረጉት ለሕጉ የሰጡት ትርጉም በመሆኑ ወደ ፍሬ ነገሩ ክርክር ገብተው ስለቀረጥና ታክሱ መጠን በተመለከተ ውሳኔ አልሰጡም፡፡ ከዚህ የተነሳም ፍሬ ነገሩን በሚመለከት ከመጀመሪያው ክርክር ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 113733 ታህሣስ 8 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 76484 ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ኢንጅኖች በአዋጁ አንቀጽ 6(1) የሚሸፈኑ በመሆናቸው የቅድመ ጭነት ምርመራ አይደረግባቸውም ብለናል፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ ሊከፈል በሚገባው ታክስ እና ቀረጥ መጠን ከግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብለትን ክርክር ከሰማ በኂላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.343(1) መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡

4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዘቢ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 51090

ታህሣሥ 12 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች -** 1. ዘቴዊንስ ባር እና ሬስቶራንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠ/ውብሸት ክብሩ -ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፅጌ ወልዴ ገለቱ

**ተጠሪ -** የኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ነ/ፈ ገብረእግዚአብሔር ሁናቸው - ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን በመተላለፍ የተፈፀመ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡

ሥር ፍ/ቤት ክስ የቀረበው በተጠሪ በኩል ሲሆን የክሱ ምክንያት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እና 55 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 22/1/ እና 50/ለ-1/ የተመለከተውን በመተላለፍ በ30/07/2001 ዓ.ም ከቀኑ 10፡50 ሰዓት ላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቾች እና የ1ኛ አመልካች የነበሩት በሥር ፍ/ቤት ከ3-5 የነበሩት ተከሣሾች በተከሰሱበት ድርጊት ጥፋተኞች ናቸው በማለት 1ኛ አመልካች ብር ስልሳ ሺህ 2ኛ አመልካች ብር ሃያ ሺህ እና 1 ዓመት እስራት ከ3-5 ያሉት ተከሣሾች ብር አሥር ሺህ እና 1 ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ግራቀኙ ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሁለቱም ወገን የቀረበውን ይግባኝ ተቀብሎ ካከራከረ በኃላ መዝገቦቹን በማጣመር በመ/ቁ 82648 ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን የጥፋተኛነት ውሣኔ በማፅናት በቅጣት ረገድ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ቅሬታ መነሻ በማድረግ የእስራት ቅጣቱን በማሻሻል 2ኛ አመልካች እና ከ3-5 የነበሩት ተከሣሾች እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ ታህሣሥ 8 ቀን 2002 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሣኔ



www.chilot.me

በዝርዝር በመንቀፍ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ አመልካቾች በነፃ እንዲሰናበቱ እንዲወስን ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ አቤቱታ ተመርምሮ ሁለተኛ ተጠሪ ጥፋተኛ ተብለው የተሰጠው ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 285/94 56/1/ እና/3/ አንፃር አግባብነቱ በሰበር ሊመረመር ይገባል ተብሎ ተጠሪ ቀርቦ ክርክሩን እንዲያሰማ ተደርጓል፡፡ በዚሁ አግባብ ሚያዝያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራቀኙ ክርክር ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው 2ኛ አመልካች ጥፋተኛ ናቸው ተብለው እንዲቀጡ የተወሰነው የ1ኛ አመልካች ስራአኪያጅ ሆነው ሲሰሩ ድርጅቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን በመተላለፍ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት በመፈፀሙ የአዋጁን አንቀጽ 56/1/ እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና 55/ለ-1/ ተላልፈዋል ተብለው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የ1ኛ አመልካችን ሃላፊነትና ተጠያቂነት አረጋግጠው ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ እዚህ ፍ/ቤት ላይ አጥብቀው የተከራከሩት 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች /ድርጅቱ/ ሥራ አስኪያጅ ቢሆኑም ድርጊቱ ሲፈጸም በቦታው እንዳልነበሩና በድርጊቱ አፈፃፀም ላይ ስምምነትም ሆነ እውቀት አልነበራቸውም እንዲሁም ይህ ስህተት እንዳይፈጸም ሥራ አስኪያጁ /2ኛ አመልካች/ ተገቢውን ትጋትና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስደዋል በሚል በአዋጁ አንቀጽ 56/3/ መሠረት በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል የሚል ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው አንቀጽ 56/1/ አንቀጽ 22/1/ እና አንቀጽ 50/ለ-1/ ድንጋጌዎች ይዘት እንደሚያመለክተው አንድ የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው እሱ የሚመራው ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆኖ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ማከናወኑ ሲረጋገጥ ይኸው ጥፋት በሥራ አስኪያጁ እንደተፈፀመ ተቆጥሮ ተጠያቂ እንደሚሆን ነው፡፡

ስለሆነም የድርጅቱ ሃላፊነት ከተረጋገጠ የሥራ አስኪያጁ ሃላፊነት የሕግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ መንዘብ ይቻላል፡፡ ሥራ አስኪያጁ ከዚህ የሕግ ግምት ሃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው በአዋጅ አንቀጽ 56/3/ ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ጥፋቱ የተፈፀመው ሥራ አስኪያጁ ሳያውቁት ወይም ሳይስማሙበት እንደዚሁም ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመተውን ጥንቃቄና ተገቢውን ትጋትና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሲሰሩ ድርጅቱ ሽያጭ በሚያከናወንበት ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ወዲያውኑ ተጠቃሚው እንዲያገኝ በማድረግ ተገቢው አሰራር ተዘርግቷል በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በዚህ ረገድ በሥር ፍ/ቤት ክርክር እና ማስረጃ ቀርቦበት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ስለመኖሩ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አያመለክትም፡፡

በእርግጥ በወቅቱ 2ኛ አመልካች በቦታው አልነበሩም ቢባልም ከፍ ሲል እንደተመለከተነው በሕጉ ግምት የሚወሰድበት ጥፋት በመሆኑ 2ኛ አመልካች በቦታው ያልነበሩ መሆኑ በራሱ ከሃላፊነት ነፃ ሊያደርጋቸው የሚችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል 2ኛ አመልካች በፍሬ ነገር ደረጃ ሥር



www.chilot.me

ፍ/ቤት ተረጋግጧል ሲሉ የሚከራከሩበት ጉዳይ ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ መብራት ጠፍቶ ነበር የሚል ቢሆንም በማኑዋል የሚሰራ ደረሰኝ እንደነበራቸው ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም 2ኛ አመልካችን አስመልክቶ እዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ የአዋጁን አንቀጽ 56/3/ ይዘት በመዘርዘር በጠበቃቸው የተከራከሩ ቢሆንም በዚህ ረገድ በሥር ፍ/ቤት በዝርዝር ክርክር ተደርጐበት እና በማስረጃ ተረጋግጦ የቀረበ ፍሬ ነገር ባለመኖሩ ሥራ አስኪያጁ በሕጉ አግባብ እና መንፈስ መሠረት በተጠቃሹ ድንጋጌ መሠረት ነፃ ሊሆኑ የሚችሉበት ምክንያት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡

በመሠረቱ የዚህ ሰበር ችሎት ሃላፊነትና ተግባር በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠ ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ አተገባበር ወይም አተረጓጉም ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ማረም እንጂ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ክርክር የማጣራት ሥራ እንዳልሆነ ከኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/3-ሀ/ እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ላይ የቀረበው ክርክር የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እንጂ በሕግ ረገድ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚያሰኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህም የሥር ፍ//ቤት 2ኛ አመልካችን ጥፋተኛ አድርጐ የቅጣት ውሣኔ መወሰኑ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 82648 ህዳር 21 ቀን 2002 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል የሰጠው ፍርድ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 43996

ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የሰሜን ምስራቅ ጉምሩክ ሜሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ

**ተጠሪ**፡- በረከት አሰፋ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከሕግ ውጭ የተያዘው መኪናዬ ይለቀቅልኝ፣ በመኪናው ሰርቼ ላገኝ እችል የነበረው የቀን ገቢ ብር 700,00 ተሰልቶ ይከፈለኝ በማለት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ የመሠረተውን ክስ መነሻ አድርጎ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጠው መልስም ድርጊቱ ሕጉ በሰጠው ስልጣን መሠረት የተፈፀመና ኃላፊነት የሚያስከትል መሆኑንና ተቋረጠ የተባለው ገቢም ሕጋዊ ስለመሆኑ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ከመከራከሩም በተጨማሪ መኪናውን የያዙት የአመልካች መሥሪያ ቤት ሰራተኞች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ይታዘዙለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በሁዋላ አመልካች መኪናውን እንዲለቅ፣ እንዲሁም መኪናው በአመልካች ተይዞ በመቆየቱ ምክንያት ተጠሪ የቀን ገቢ የተቋረጠባቸው መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ብር 105, 000.00 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ ለተጠሪ አመልካች እንዲከፈል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማትም ይግባኙን ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የአመልካች አድርራት በአዋጅ ቁጥር 60/1989 መሠረት የተፈቀደ ሁኖ እያለና የተጠሪ የመኪና ገቢም በተገቢው መንገድ ግብር ሲከፈልበት የነበረ መሆኑ ሣይረጋገጥ የተቋረጠ ገቢ አመልካች ለተጠሪ ብር 105,000.00 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍል መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በጉምሩክ ተይዞ የቆየው መኪና የቤት መኪና መሆኑ ሣይካድ ተጠሪ ገቢ አጥቷል ተብሎ አመልካች ብር 105,000.00 ይክፈል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ



www.chilot.me

ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ በዚህ ፍርድ ቤት ጥሪ በተገቢው መንገድ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት የተደረገውን የግራ ቀኙን ክርክርና በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ከአመልካች የሰበር አቤቱታና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪን መኪና ይዞ በቁጥጥር ስር ሊያውል የቻለው መኪናዋ ኮንትሮባንድ እቃ የጫነውን መኪና ፊት ለፊት በመሆን አጅባ ትጓዝ ስለነበረ በኮንትሮባንድ ድርጊት ተሣትፎ አድርጋለች በሚል ጥርጣሬ ነው በማለት አመልካች የሚከራከር መሆኑና የተያዘችው የተጠሪ መኪና የቤት መኪና መሆኗ መረጋገጡን ነው፡፡

የአመልካች መ/ቤት ስልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 60/1989 በአንቀጽ 6 እና 58 ስር ተዘርዝሯል፡፡ እነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች የሚያሣዩት የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የጉምሩክ ባለሥልጣንና ሹም የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት በዝርዝር መቀመጣቸውን ነው፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 368/1995 ደግሞ ኮንትሮባንድ ማለት ሕጎችንና በሕግ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ወደ ጉምሩክ ክልል ዕቃዎችን በማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል በማስወጣት፣ በሕጋዊ መንገድ የመጡትን በሕገ ወጥ መንገድ መልሶ ማስገባት መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማዘዋወር ማስተላለፍ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ለማድረግ መሞከር እና እንደዚህ ላሉ ድርጊቶች መተባበርን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2/28/ተርጓሜ ሠጥቶበታል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው አመልካች ተግባሩን ሕጋዊ ነው ብሎ ሲከራከር በተለይ መሠረት ያደረጋቸው የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6/5/ እና 58/1/ለ/ ድንጋጌዎችን ነው፡፡ አንቀጽ 6/5/ ሙሉ ይዘቱ ሲታይ ባለሥልጣኑ "በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል፣ ይከላከላል፣ በዚሁ ሁኔታ የሚንቀሣቀሱ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ይይዛል፤ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል" በማለት ሲደነግግ አንቀጽ 58/1/ለ/ ደግሞ ወደ አገር እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንዳይወጡ የተከለከሉ፣ ገደብ የተደረገባቸው ወይም ቀረጥ እንዳይከፈልባቸው በማሰብ የተደበቁ ዕቃዎች በፍተሻ ሲገኙ ዕቃዎችን የመያዝ እንዲሁም እንደሁኔታው ማጓጓዣውን የማጓጓዣውን ኃላፊ ወይም የዕቃውን ባለቤት ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ሥር የማቆየት ስልጣንና ኃላፊነት የጉምሩክ ባለሥልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የጉምሩክ ባለሥልጣን በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሣቀሱ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ፣ በሕገ ወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ በሕገ ወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን ጭምር ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ስር የማቆየት ስልጣን በሕጉ የተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ እነዚህን ተግባራት የሚያከናውነው ግን ኮንትሮባንድ ተብሎ በሕግ የተሰጠው ትርጓሜ ተሟልቶ ሲገኝ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ማንኛውም የዕቃ እንቅስቃሴ ኮንትሮባንድ ስለመሆኑ አሣማኝ እና በቂ ምክንያት ሣይኖረው ባለሥልጣኑ መ/ቤት እንዲይዝና እንዲቆጣጠር ሕጉ ስልጣን ተሠጥቶታል ተብሎ አይታሰብም፡፡ እንዲሁም እቃው ኮንትሮባንድ ስለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረውም



www.chilot.me

ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ዕቃውን የመያዝ ስልጣን ያለው መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘት ያሣያል፡፡ የኮንትሮባንድ ድርጊት ደግሞ የኮንትሮባንድ እቃ ነው የተባለውን ጭኗል በተባለ መኪና ብቻ ይፈፀማል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ድርጊቱ ወንጀል እንደመሆኑ መጠን የአድራጊዎች ተሣትፎም የተለያየ ደረጃና መልክ ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል፡፡ በመሆኑም የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ሲወጣ ኮንትሮባንድ ስለመሆኑ የጠረጠረውን ዕቃ የጫነ መኪና ከመያዝ ባለፈ በቂና አሣማኝ ጥርጣሬ እስካለው ድረስ የኮንትሮባንድ ወንጀሉ ተሣታፊ ነው የሚለውን መኪና ሁሉ በመያዝ በቁጥጥር ሥር የማዋል ሥልጣን አለው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የኮንትሮባንድ እቃ ያልጫነ መኪናን አመልካች መያዙ ሕገወጥ ነው በማለት ሙሉ በሙሉ መደምደሙ ለአመልካች በሕግ ተለይቶ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ከኮንትሮባንድ ወንጀል አፈፃፀምና የተሣትፎ ሁኔታ ጋር ያልተገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም አመልካች መኪናውን መያዙ ሙሉ በሙሉ ሕገወጥ ተግባር ነው መባሉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በቂና አሣማኝ ጥርጣሬ ኑሮት እቃውን መያዝ ይችላል ማለት ተገቢና ምክንያታዊ ባልሆነ ጊዜ እቃውን ይዞ የመቆየት ስልጣን አለው ወደሚለው ድምዳሜ አያደርስም፡፡ በመሆኑም መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነቱንና ተግባሩን ሲወጣ በጥርጣሬ የያዘውን እቃ ተገቢና ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ አጣርቶ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ በጥርጣሬ የያዘውን ንብረት ምክንያታዊ ለሆነ ጊዜ ከያዘና ስልጣን ያለው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ የተያዘው ንብረት እንዲለቀቅ ውሣኔ ከሰጠ በሁዋላ ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ወዲያውኑ ከለቀቀ ተገቢና ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ንብረቱ በመቆሙ የታጣውን ገቢ እንዲከፍል የሚገደድበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የጊዜው ተገቢነትና ምክንያታዊነትም እንደ ጉዳዩ ባህርይና ከባቢያዊ ሁኔታዎች እየታየ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ነው፡፡ በጥርጣሬ የተያዘው እቃ ከምክንያታዊ ጊዜ በላይ መያዙ ከተረጋገጠ ግን አመልካች በሕግ አግባብ ኃላፊ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች የተጠሪ መኪና የተያዘው የኮንትሮባንድ እቃ ጭኗል በሚል ጥርጣሬ ሣይሆን የኮንትሮባንድ እቃ የጫነ መኪናን አጅቦ ሲሄድ ነበር ሲሆን ጉዳዩ ሲጣራ ቆይቶ መኪናው እንዲለቀቅ በፍርድ ቤት ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከሰጠ በሁዋላ መኪናው ወዲያውኑ ተለቋል፤ እንዲሁም ጉዳዩ እስከሚጣራና በፍርድ ቤት ውሣኔ ጉዳዩ እስከሚያልቅ ድረስ መኪናው በአመልካች ተይዞ የቆየው ለአምስት ወራት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የተጠሪን መኪና የያዘው የኮንትሮባንድ እቃ የጫነ መኪና አጅቦ ሲሄድ ነው በሚል ምክንያት ሲሆን ይህንኑ ምክንያት በማጣራት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደበትን ምክንያት በስር ፍርድ ቤት አላስረዳም፡፡ መኪናው ከተያዘበት ምክንያትና ከባቢያዊ ሁኔታዎች ስንነሣም ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ከሦስት ወራት ጊዜ በላይ ሊወሰድ ይችላል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ምክንያት የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን መኪና ከሶስት ወር ጊዜያት በላይ ያለበቂ ምክንያት ይዞ ለቆየባቸው ጊዜያት / ለሁለት ወር ጊዜያት/ ተግባሩ ሕገ ወጥ በመሆኑ ኃላፊ የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

አመልካች የተጠሪን መኪና ለሁለት ወራት ይዞ መቆየቱ ሕገወጥ ነው ከተባለ ቀጥሎ እልባት ማግኘት ያለበት ጉዳይ የካሣ መጠን ነው፡፡ ተጠሪ መኪናውን የቤት መኪና መሆኑን ጠቅሰው በኪራይ ብር 700.00 /ሰባት መቶ ብር/ በቀን ያገኙ እንደነበር ገልፀው የአምስት ወራት ገቢ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፣ አመልካች ደግሞ ገቢው ሕጋዊ መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪን ክርክር ሙሉ በሙሉ



www.chilot.me

ተቀብሏል፡፡ ይሁን እንጂ የቤት መኪና በኪራይ ገቢ ሊያስገኝ እንደሚችል የሚታመን ቢሆንም የኪራይ ገቢ ግን ሕጋዊነቱ መረጋገጥ አለበት፡፡ ሕጋዊነቱ የሚረጋገጠው ደግሞ ከሚመለከተው አካል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ፤ የንግድ ስራ ፈቃድ ሲቀርብ ወይም በዚህ ረገድ ተገቢ ማስረጃ ቀርቦ ሕጋዊነቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የተጠሪ የኪራይ ገቢ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድን መሠረት አድርጎ የተገኘ ስለመሆኑ ሕጋዊ ማስረጃ አልቀረበበትም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ ሣያረጋግጥ የተጠሪ መኪና በኪራይ መንገድ ገቢ ታስገኝ ነበር በማለት መደምደሙ ገቢ ተቋርጦብኛል የሚል ወገን በተገቢው መንገድ የማስረዳት ግዴታ አለበት በሚል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 የተቀመጠውን የሕግ መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ መኪናቸውን በቀን በብር 700.00 /ሰባት መቶ ብር/ አከራይተው ገቢ ያስገኙ ነበር የሚለው የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጠሪ መኪና በሕጋዊ ንግድ በመሰማራት ተገቢውን ግብር ተጠሪ የከፈሉባት ስለመሆኑ ስላልተረጋገጠ ገቢ ተቋርጧል ለማለት አይቻልም በማለት ያቀረበው ክርክርም ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም የተጠሪ መኪና የቤት መኪና መሆኗ እና በአመልካች ደግሞ ለሁለት ወራት ያህል ያለ በቂ ምክንያት በቁጥጥር ስር መዋሏ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ላይ ሙሉ በሙሉ የጥቅም ማጣት አልደረሰባቸውም ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለምና፡፡ ተጠሪ ለራሣቸውም ሆነ ለቤተሰባቸው የትራንስፖርት አገልግሎት መኪናውን እንደሚጠቀሙ የሚታመን ሲሆን መኪናው በአመልካች ቁጥጥር በመዋሉ ምክንያት ደግሞ ለወጪ እንደሚዳረጉ እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ያጡት ጥቅም የለም ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ ይሁን እንጂ መኪናውን ባለመገልገላቸው የደረሰባቸው እርግጠኛ ወጪ ይህ ነው ብሎ ለመደምደም መነሻ የሚሆን ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ሆኖም ስለ ጉዳቱ ምን ያህል ኪሣራ እንደሚከፍል በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዳኞቹ የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጎጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሣራውን ልክ በርትዕ ሊወስኑ እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ያጡት ጥቅም በርትዕ ሊወሰን የሚገባው ሁኖ በመገኘቱ ይህ ችሎት ተጠሪ ለሁለት ወራት ያህል ያጡት ጥቅም ለእያንዳንዱ ወር ከብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በላይ ሊሆን እንደማይችል ገምቷል፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ኃላፊነትን በተመለከተ የሰጡት ውሣኔ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 60/1989 መሠረት የተሰጠውን ስልጣን ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሲሆን የካሣ መጠኑም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ሁኔታዎችና ስለካሣ መጠን አወሳሰን የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሣሣይ ጉዳዮች ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር የማይጣጣም ሁኖ ስለአገኘነው ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአማራ ክልላዊ መንግሥት ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20751 ታህሣሥ 04 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 467/2001 ጥር 05 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የተጠሪን መኪናን የያዘው በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን ሲያከናውን ቢሆንም መኪናውን ይዞ የቆየው ተገቢና ምክንያታዊ ነው ሊባል ከሚቻለው ጊዜ በላይ በመሆኑ ከሶስት ወራት ጊዜያት በላይ መኪናውን ይዞ ለቆየባቸው ለሁለት ወራት የተቋረጠ ገቢ የማይከፈልበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡



www.chilot.me

3. አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው የሁለት ወር የቀን ገቢ በብር 200 /ሁለት መቶ ብር/ ሲታሰብ የሚመጣው ብር 12,000.00 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 59851

የካቲት 11 ቀን 2003 ዓ/ም.

ዳኞች-፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ዓለሙ ጋባ - ጠበቃ ወልደስላሴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐቃቤ ሕግ ሽመልስ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ተያይዞ የተነሳን የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- 1ኛ፡- አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው አንቀፅ 22(1) እና 50(ለ-1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ በሚገኝ ቁጥሩ 081 በተሰጠውና በንግድ ፈቃድ ቁጥር 02/1/3/01096/98 የሚሠራ የዓባይ ዙሪያ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው ቤት ጥር 14 ቀን 2002 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 አከባቢ የአንድ ለስላሳ እና ሻይ ግብይት በብር 5.25 ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሠኝ በሠራተኛቸው አማካይነት በመሸጣቸው ተከሰዋል የሚል ሲሆን ሁለተኛው ክስ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እንደተሻሻለው አንቀፅ በአንቀጽ 50(መ-1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በድርጅቱ ውስጥ በባልሥጣኑ እውቅና የተሰጠበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሥሪያ ከህዳር 25 ቀን 2002 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 24 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ገዝቶ የመጠቀም ግዴታ የተጣለበት ቢሆንም በሆቴሉ ውስጥ በባለስልጣኑ መሥሪያ ቤት እውቅና ያልተሰጠውንና "ናን ፊስካላይዝድ ማሽን" ሲጠቀሙ ተገኝተዋል የሚል ነው፡፡ አመልካችም እንደ አቃቤ ክስ ድርጊቱን ያለመፈጸማቸውን በመግለፅ ክሱን ክደው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ አሉኝ ያላቸውን የሰው ምስክሮችን አስቀርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ምስክሮችን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎችን ያላስተባበሉ መሆኑን በመግለፅ ቃላቸውን ውድቅ ከአደረገ በኋላ አመልካችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ በ1ኛ ክስ በሁለት አመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራትና በብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር)፣ በሁለተኛው ክስ ደግሞ በአንድ አመት እሥራት በድምሩ በሦስት አመትና በስድስት ወር እስራትና በብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር) እንዲቀጡ



www.chilot.me

ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተላለፈባቸው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ከተቀበለና ግራ ቀኙን ከአከራከሩ በሁዋላ በአመልካች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመቀበል የእስራት ቅጣት ውሳኔውን ግን ወደ ሁለት አመት እሥራት ዝቅ አድርጎ የገንዘብ መቀጮውን ደግሞ እንዳለ በመቀበል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፃፈ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡- የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የወሰኑት በሕጉ አግባብ አቃቤ ሕግ ባላስረዳበትና ተጨማሪ ማስረጃዎችም ቢሆኑ አመልካች ደረሠኙን እንዲታተም ለማድረግ እንዲሁም ማሽኑን ለማስገባት ተገቢውን ጥረት ሲያደርግ የነበረ መሆኑን ባረጋገጡት ሁኔታ ስለሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔው ሊሻር የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆኑ በመ/ቤቱ የተገለፀለት ደብዳቤ እጁ ከገባ ከታህሳስ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. ጊዜ ጀምሮ መ/ቤቱ በሰጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ደረሠኞችንና የሂሳብ መኪና ለማስገባት ተገቢውን እንቅስቃሴ ሲያደርጉ መቆየቱ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋገጦ እያለ ጥፋተኛ ተብለው መቀጣታቸው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ በመታዘዙ ተጠሪ ቀርቦ አመልካች ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል በሚል የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው ሙሉ በሙሉ ሊጸና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃም ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካች ጥፋተኞች ተብለው መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሲሆን ቅጣት ጋር ተያይዞ የቀረበው ክርክር በዚሁ ጭብጥ እልባት የሚያገኝ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609 እንደተሻሻለ አንቀፅ 22(1) እና 50(ለ-1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ማከናወናቸውን ተጠሪ በሕጉ አግባብ አስረድቷል ወይስ አላስረዳም?፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609 እንደተሻሻለ 50(መ-1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት እውቅና ውጪ የሽያጭ መኪና ይዘው ተገኝተዋል? ወይስ አልተገኙም? የሚሉትን ጥያቄዎችን በማንሳት በስር ፍርድ ቤት በአቃቤ ሕጉ ማስረጃዎችና በአመልካች ማስረጃዎች ጭምር ከተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች እና አግባብነት ካላው ሕግ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡ አመልካች የተከሰሱት 1ኛው ክስ፡- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 55 እና በአዋጅ ቁጥር 609 እንደተሻሻለ አንቀፅ 22(1) እና 50(ለ-1) በመተላለፍ ሆቴል ድርጅቱን በወኪልነታቸው በሚያስተዳድሩበት ጊዜ ሽያጭ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሠኝ አከናውነዋል በሚል ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት የተጠሪ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ይኸው ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሚያቀርቡት ክርክር ግብይቱ በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተከናውኗል የሚል ክርክር ሳይኖራቸው አጥብቀው



www.chilot.me

የሚከራከሩት በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ደረሠኞችንና የሂሳብ መኪና ለማስገባት ተገቢውን እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት አመልካች በውክልና የሚያስተዳድሩትን የሆቴል ድርጅት በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመዘገበው ከጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑና የምስክር ወረቀት መስጠቱን፣ ግብይቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሠኝ የተከናወነው ደግሞ ጥር 14 ቀን 2002 ዓ/ም መሆኑ በአቃቤ ሕጉ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ግብር ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት ተመዘገበ የሚባለው ደግሞ ከተመዘገበበት ቀን ወይም ምዝገባው ከሚጸናበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 22(1) ድንጋጌ ሲታይም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት የተመዘገበ ማንኛውም ሰው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ለሚያድርገው ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለተጠቃሚው ወዲያውኑ መስጠት እንደአለበት አስገዳጅነት ባለው ኃይለቃል ደንግጎ እናገኛለን፡፡ ሕጉ በተገቢው ጊዜ ደረሠኝ ሳያሳትም ግብይት ያከናወነ ግብር ከፋይ ጥረት እያደረገ ቢቆይና ግብይቱን ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ከአከናወነ ተጠያቂነት የሌለበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ድግንጋጌ የለውም፡፡ አመልካች ተገቢውን ጥረት ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን ተረጋግጧል የሚሉት በመከላከያ ምስክሮችና በሠነድ ማስረጃዎቻቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ደረሠኙን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ያላሳተሙበትን ሕጋዊ ምክንያት ያላስረዱ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ከውሳኔው ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት በተሰጠው ሥልጣን የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሱበትን ድምዳሜ የሚያጣራበት ወይም ማስረጃውን የሚመዝንበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ደረሠኙን እንዲዘጋጅ ሳያደርጉ ወይም ያላዘጋጁት ከራሳቸው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ ስለመሆኑ ባላስረዱበት ሁኔታ በ1ኛ ክስ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሕጋዊ የሽያጭ መኪና ሳይጠቀሙ ከሕግ ውጪ በሆነ ሁኔታ (ከባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት እውቅና ውጪ) ናን ፊሲካላይዝድ የሚባል የሽያጭ መኪና ይዘው መገኘታቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ተጠሪ አመልካች ከሕዳር 25 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ታህሳስ 24 ቀን 2002 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ እውቅና የተሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ ያለመጠቀማቸውን አስረድቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5፣ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 64፣ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 117 መሠረት ደግሞ ለጉዳዩ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ያለው አካል ተለይቶ የተቀመጠ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ ደንብ ቁጥር 139/1999 ወጥቷል፡፡ በዚህ ደንብ ደግሞ ለጉዳዩ አፈፃጸም መመሪያ ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት መመሪያ ለማውጣት የሚችልበት አግባብ ያለ ስለመሆኑ አንቀጽ 22 የሚያስቀምጥ ሲሆን ደንቡን ተከትሎ ደግሞ መመሪያ ቁጥር 46/1999 ተብሎ የሚጠቀስ መመሪያ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህም መሠረትም ተጠሪ መሥሪያ ቤት ግብር ከፋይ የሆነውና አመልካች በውክልና የሚያስተዳድሩት የሆቴል ድርጅት ሕጋዊውን የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ገዝቶ እንዲጠቀም በሚገባ ያሳወቃቸው ስለመሆኑ ተረጋገጧል፡፡ አመልካች የተገለፀላቸው ጊዜ አልፎ ሕጋዊውን የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ሳይጠቀሙ ሕጋዊ ያልሆነውን ሲጠቀሙ መገኘታቸው ከተረጋገጠ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 በአዋጅ ቁጥር 609 እንደተሻሻለው በአንቀጽ 50(መ) መሠረት ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፡፡ አመልካች



www.chilot.me

ተገቢውን ጥረት ሲያደርጉ ነበር፣ መሳሪያውን ገዝተው እንዲጠቀሙ የተሠጣቸውና የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ የተባለበት የጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም. መቀራረብ ሲታይ የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም የሐሳብ ክፍሉ አልተሞላም ለማለት የሚያስችልበት ምክንያት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሁለተኛው ክስም ጥፋተኛ ተብለው መቀጣታቸው የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

በአመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195((2(ለ-2)) መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48628

ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ በርሄ ሐጐስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የስር ከሣሽ /ያሁን የሰበር አመልካች/ በስር ተከሣሽ /በሰበር ተጠሪ/ ያቀረበው ክስ ተከሣሹ ንብረትነቱ የራሱ በሆነው ኮድ3-29644 አይሱዙ የጭነት መኪና 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ ከጨርጨር ወደ መቀሌ ከተማ በ26/4/2001 ዓ.ም ምሽት 3፡30 ሲጓዝ እጅ ከፍንጅ በመያዙ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/1/ ተላልፎ በመገኘቱ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሣሹም ፍ/ቤት ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉ ሲጠየቅ ወንጀሉን አለመፈጸሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የስር የትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከቀረቡት የግራ ቀኙ ማስረጃዎች አንጻር ከመረመረ በኋላ ከሣሹ ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን የወንጀል አንቀጽ 64/1/ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 113/2/ መሠረት ለውጦ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ስር ጥፋተኛ ነው በማለት ተከሣሹ በ3 ዓመት ቀላል እስራትና በ5000 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ፣ የተያዘው 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ለመንግስት ገቢ እንዲሆንና መኪናው ለተከሣሽ እንዲመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የይግባኝ ባዩን /የስር ከሣሽን/ ይግባኝ በመሠረዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/1/ ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘው የአሁኑ አመልካችም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 365/95 አንቀጽ 64/4/ ተጠሪው በራሱ መኪና በህግ የተከለከለውን 56 ቦንዳ ጭኖ በመገኘቱ ክስ ተመስርቶበትና በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ተጠቅሶ ክስ ከቀረበበት የህግ አንቀጽ መንፈስ ወጪ መኪናው ለተጠሪ ይመለስ ተብሎ የተወሰነው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የተፈጸመው የህግ ስህተት ታርሞ መኪናው ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡



www.chilot.me

ለሰበር ቅሬታው ተጠሪው በሰጠው መልስ አመልካች በ24/6/2001 ዓ.ም ለስር ትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ወንጀሉ ብቻ የሚመለከት እንጂ አሁን ቅሬታ የቀረበበት መኪና ይወረስልኝ በሚል አይደለም፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም በተጠሪ አሽከርካሪነት 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ የተያዘው መኪና ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ ከግራ ቀኙ ማስረጃዎች አንጻር ሲመረመር ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የለውም በሚል በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ስር ጥፋተኛ ነው ብሏል፡፡ በዚህ አንቀጽ ጥፋተኛ የተደረገ ሰው ደግሞ የተያዘበት ዕቃ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፍል ከሚገባው ጠቅላላ የቀረጥና የታክስ ሂሣብ በማያንስ የገንዘብ መቀጮና ከሶስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን የስር ፍ/ቤት እንዳረጋገጠው ያሁኑ የሰበር ተጠሪ ንብረትነቱ የራሱ በሆነው አይሱዙ የጭነት መኪና የተጠቀሰውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ እጅ ከፍንጅ ተይዟል፡፡ በዚህ የወንጀል ድርጊትም በአዋጁ የማጓጓዝ ሀላፊነት የሚያስከትለውን ግዴታ በመጣሱ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያለው እንደ ስር ፍ/ቤቶች አተረጓጉም አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ሣይሆን የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 64/4/ ነው፡፡ የተጠሪው ድርጊት በአንቀጽ 64/4/ የሚሸፈን ከሆነ ደግሞ የሚወረሰው በኮንትሮባንድ የተያዘ ዕቃ ብቻ ሣይሆን የዕቃው ማጓጓዣ /መኪና/ ጭምር ነው፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካችን ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን የህግ ቁጥር ያለአግባብ በመለወጥ ጥፋተኛ ነው በማለት የቅጣት ውሣኔ ያስተላለፋበት የህግ ቁጥር የማጓጓዣ ሀላፊነት ግዴታ ጥሶ ለተገኘው ለመጓጓዣው ባለቤት ተፈጻሚነት የሌለው በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የስር የትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 10/12117 በቀን 24/10/2001 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት በመ/ቁ 33108 በቀን 06/12/2001 ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽለዋል፡፡
2. የሰበር ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ ስር ጥፋተኛ ነው ብለን ወስነናል፡፡ ቅጣትን በሚመለከት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በ3 ዓመት ቀላል እስራትና በ5000 /አምስት ሺ.ህ/ መቀጮ ተጠሪው እንዲቀጣ የወሰነው በአግባቡ በመሆኑ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ተጠሪው ጥፋተኛ የተደረገበት አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ የኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነው ማጓጓዣ ጭምር እንዲወረስ የሚደነግግ በመሆኑ በተጠሪ አሽከርካሪነት የተያዘው የተጠሪ ኮድ 3-29644 አይሱዙ የጭነት መኪና ተወርሶ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወስነናል፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ.ከ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 57100

ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጅማ ቅ/ጽ/ቤት ነገረ ፈጅ - ምህረቱ ቁምላቸው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ አዳለ ሰይድ

2. ፍሮሚሲስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ካቀረበው የቀደምትነት ባለመብት ክርክር ጋር የተያያዘው ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግስት በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ድርሻው እንዲሰጠው በመክሰስ ካስወሰነ በኂላ በአፈጻጸም መዝገብ የ2ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነው ክሊንክ ተሸጦ የአፈጻጸም ድርሻ እንዲሰጠው በታዘዘው መሠረት ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ገዢ ባለመቅረቡ የፍርድ ባለመብት /1ኛ ተጠሪ/ ንብረቱን ለመረከብ ጥያቄ አቅርቦ እያለ የአሁን አመልካች ጣልቃ ይግባ፡፡ የአሁን አመልካች በ09-2-2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ 508,564.67 ብር የግብር እዳ ከአፈጻጸም ተከሣሽ /ከአሁን 2ኛ ተጠሪ/ ላይ ስላለን በግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት የቅድሚያ መብት ስላለን የቅድሚያ መብታችን እንዲከበር የሚል ነበር፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ አመልካች /የአሁን አመልካች/ ከላይ እንደተመለከተው ያመልክቱ እንጅ በአዋጅ ቁ. 286/2002 አንቀጽ 78/1/ መሠረት የባለዕዳውን መያዝ የሚችለው ንብረት አፈጻጸም ላይ ከሌለ እና በዋስትና ያልተያዘ ከሆነ በመሆኑና ከላይ የተጠቀሰው ንብረት ደግሞ በአፈጻጸም ላይ ስላለ የጉምሩክ ጽ/ቤት የቀደምትነት መብት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ብሎ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት አጽንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን በቀን 08/10/2002 ዓ.ም በ2 ገጽ በተጻፈ ማመልከቻ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት አመልካች ለግብር ዕዳ ሲጠየቅ ዋስትና ከተሰጣቸው አበዳሪዎች /ባንኮች/ ተከትሎ የቅድሚያ መብት



www.chilot.me

ያለው ስለመሆኑ እየታወቀ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለውና በሶስተኛ ወገን የሚገኙቱን ንብረቶች ለማስለቀቅ የተደነገገውን የአዋጁን አንቀጽ 78/1/ በመጥቀስ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ 1ኛ ተጠሪ በቀን 20-4-2003 ዓ.ም በ3 ገጽ እና 2ኛ ተጠሪ ተወካይ በቀን 20-4-2003 ዓ.ም በ2 ገጽ በመጻፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰጡት መልስ ፍሬ ሃሣብ በአጭሩ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ጥያቄ የዘገዬና ንብረቱንም በጊዜያዊነት እንዲያስተዳድር ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ የቀረበ ከመሆኑም በላይ የቀድምትነት መብት አይገባውም የሚል ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች አቅርቦት የነበረው የቀደምትነት መብት ውድቅ ተደርጐ የተወሰነው ውሣኔ አግባብ ባለመሆኑ ተሽሮ የአመልካች የቀደምትነት መብት እንዲከበር በማለት መልሷል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

በግራ ቀኝ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል አመልካች በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት በሌላው ሰው ገንዘብ ጠያቂነት በተያዘ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት አለው ወይስ የለውም የሚል ጭብጥ በመሆኑ ከዚሁ አኳያ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሁለተኛ ተጠሪ /ፎሮምሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር/ በገንዘብ ጠያቂነት ወይም ድርሻውን ለማስከራል እንደሆን አላከራከረም፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ /ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላይ/ ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ በሚመለከተው ንብረት ላይ ቀድሞ በዋስትና ያልተሰጠው ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡

ይሄንን መሠረታዊ ሃሣብ ይዘን የአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

"ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ተከፋይ ከሚሆንበት አንስቶ ተከፍሎ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሃብት ላይ ባለስልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች ዕዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡" የሚል ነው፡፡

ከዚህ አንቀጽ በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው ከአመልካች ሊቀድም የሚችለው በዋስትና ቀድሞ የተያዘ ከሆነ ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በተመለከተው አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 78/1/ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነቱን ስንመረምር የግብር ከፋይ ንብረት የሆነ በሌላ ሶስተኛ ወገን ሲገኝና በግብር አስገቢው ባለስልጣን እንዲያስረክበው ሲጠየቅ የማስረከብ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑና የማያስረክብበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለው በአፈጻጸም ላይ ስለመሆኑ በመግለጽ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ይሄ አንቀጽ ከተያዘው ጉዳይ ጋር በቀጥታ አግባብነት ያለው ባይሆንም አንቀፁ ሊደነግግ ያሰበው ንብረቱን ለመረከብ ሲፈልግ መከተል ያለበትን ስነ ሥርዓት ከመደንገግ አኳያ በመሆኑ የቀደምትነት መብትን ቀሪ የሚያደርግ አይደለም፡፡



www.chilot.me

በአጠቃላይ በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት አመልካች ያቀረበው የቀድምትነት መብት በዚሁ አንቀጽ መሠረት ታይቶ መወሰን ሲገባው ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን የአዋጁን ሌላ አንቀጽ በመጥቀስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉና የይግባኝ ሰሚውም ፍርድ ቤት ይሄንን ሣያስተካክል ውሣኔውን ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

***<u>ው ሣ ኔ</u>***

1. በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግስት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 10/86 በቀን 18-2-2002 ዓ.ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 89407 በቀን 05-9-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የጠየቀው የግብር ዕዳ በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት ከአንደኛ ተጠሪ የቀደምትነት መብት አለው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64819

ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐቃቤ ህግ ገብረሚካኤል ወልዴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አንተነህ ካሣዬ - አልቀረቡም

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን አመልካች በአሁኑ ተጠሪና በሌላ የእቃው ባለቤት በተባለ ግለሰብ ላይ በቀረበው ክስ የወንጀል ህግ ቁ 32/1/ሀ/ እና የገቢዎችና ጉምሩክ አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ - ሥርዓት ያልተፈፀመባቸውን የተለያዩ አልባሣት ባጠቃላይ ለመንግስት ሊከፍል የነበረው ቀረጥ እና ታክስ 26,576 ብር ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-04051 ደሕ የሆነ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለቤትና ሹፌር  በመሆኑ የተከሠሠ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በተከሠሠበት የህግ አንቀጽ ጥፋተኛ አድርጎታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የደቡብ ክልል የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በተከሠሠበት አንቀጽ ጥፋተኛ ካደረገው በኋላ የአሁኑ ተጠሪ በ7/ ሰባት/ ዐመት ፅኑ እሥራት እና በ5000/አምስት ሺህ / ብር እንዲቀጣ በመወሰን ከላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ ለባለቤቱ እንዲመለስ ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ያስቀርባል በማለት ሲመለከተው ከቆየ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 195/2/ ለ/ 2/ መሠረት አፅንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ  ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 21/5/2003 ዓ.ም በ2 ገፅ በመፃፍ ያቀረበው የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ፡- ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት አዋጅ ቁ 622/01 አንቀጽ 91/2/ ስንመለከት የእሥራትና የገንዘብ መቀጫው ሊጣል የሚችለው ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃና መሣሪያ እና የወንጀሉ ፍሬ መወረሱ እንደተጠበቀ መሆኑን የሚደነግግ  በመሆኑ ፣ ተጠሪ ደግሞ የመኪናው ባለቤትና በወቅቱ ሹፌር መሆኑን ራሱም ከማመኑ  በተጨማሪ በማስረጃም የተረጋገጠ ሆኖ ሣለ ዕቃውን ሲያጓጉዝ የነበረው የተጠሪ መኪና እንዲወርስ መታዘዝ ሲገባው መታለፉ ያለአግባብ በመሆኑ፣ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 104/1/ የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተሠጠ ተጨማሪ



www.chilot.me

ትዕዛዝ መስጠት ሣያስፈልግ ዕቃው ወይም ማጓጓዣው እንዲወረስ ይደረጋል በማለት የደነገገ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ የሠጡ ቢሆንም ተሸከርካሪው እንዲወርስ ባለማዘዛቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ፣ ተጠሪ በቀጥታ በወንጀሉ ተሣታፊ በመሆኑ መኪናውን ከመወረስ የሚያስቀር አግባብ ሣይኖር የሥር ፍ/ቤቶች መኪናው ለባለቤቱ ይመለስ በማለት የሠጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ግንቦት 08 ቀን 2003 ዓም በ4 ገፅ ፅፎ ያቀረበው የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች የጠቀሳቸው የህግ አንቀጾች የተገለፀው ተሸከርካሪ እንዲወርስ የሚደነግግ አይደለም ፣ በተጠቀሰው አዋጅ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ዕቃና መሣሪያ የሚለው በእንግሊዝኛው /goods & equipment / ተብሎ የተተረጎመ በመሆኑ መኪናን አይጨምርም፣ የተላለፍኩት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ባለመኖሩ መኪናው ሊወረስ አይገባም ፣ የቀረበው ክስ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 91/2/ በመሆኑ እና በአዋጅ አንቀጽ 104/1/ መሠረት መኪናው እንዲወርስ የቀረበብኝ ክስ ሣይኖር የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ስለሌለው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም፡- በወንጀል ክሱ የተመለከተውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ስታጓጉዝ የተገኘችው የተጠሪ መኪና ልትወርስ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግንተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት እንደሚከተለው ተመርምሮአል፡፡ ተጠሪ ስያሽከረክረው የነበረው መኪና ኮድ ቁ 3-04051 ደሕ የሆነ የህዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ የራሱ የግል ንብረት የሆነ መሆኑ፣ ሁለተኛ ተከሣሽ በነበረና በመኪናው የተሣፈረ ሰው የተጫነ የኮንትሮባንድ ዕቃ ለመንግስት ሊከፈል የሚገባ ታክስ እና ቀረጥ ከ21,791.66 ብር ያልተከፈለበት ሲያጓጉዝ በፖሊሶች መያዝ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጠው ከመሆኑም አልፎ የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ቅጣት በተጠሪ ላይ የተጣለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚሁ ፍርድ ቤት የተሠጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና ቅጣት ስለመለወጡ በተጠሪ በኩል የተመለከተ ነጥብ የለም፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁ 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የህግ ስህተት ማረም በመሆኑ ማስረጃን የመቀበል እና የመመዘን ሥልጣን የበታች ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በመሆኑ በዚህ ረገድ /በፍሬ ነገር / በበታች ፍርድ ቤት የተደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይሄ ከሆነ ደግሞ በተጠሪ ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት ውሣኔ በተሽከርካሪው መወረስ አለመወረስ ጋር ተያይዞ የሚያስከትለው ውጤት ምን እንደሆነና የበታች ፍርድ ቤቶች መኪናው ለባለቤቱ /ለተጠሪ/ ይመለስ ማለታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የኮንትሮባንድ ወንጀል በአዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃ ፣መሣሪያ እንደዚሁም የወንጀሉ ፍሬ የሚወረስ መሆኑ እና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2/1/ ሥር ዕቃ ለሚለው ቃል ተንቀሣቃሽ ንብረት /መኪና/ በመጨመር ከመደንገጉም በላይ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 104/1/ መሠረት ደግሞ የተሽከርካሪ ባለቤትና ሹፌር ሆኖ

ተጠሪ ሲያሽከረክር በተፈፀመ የኮንትሮባንድ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ ተጨማሪ ትዕዛዝ መስጠት ሣያስፈልግ ወይም ተጠሪ እንደሚከራከረው በአመልካች ላይ ሌላ ክስ ማቅረብ ሣያስፈልግ መኪናው እንዲወረስ መታዘዝ እንዳለበት ይደነግጋል። ይሄ ከሆነ ጉዳዩን በመጀመሪያ የወንጀል ክሱን የተመለከተው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሲሠጥ ወንጀሉ የተፈፀመበትን የተጠሪ ተሽከርካሪ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማዘዝ ሲገባው ለባለቤቱ ይመለስ ማለቱ የአዋጁን ግልፅ ድንጋጌ ፣ ዓላማና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል። በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል።

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የደቡብ ብሔ/ብ/ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 39555 በቀን 24/3/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 12612 የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 195/2/ መ/ መሠረት ተሻሽሎአል።
2. በተጠሪ ስመንብረት ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-04051 ደሕ የሆነች ህዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ የኮንትሮባንድ ወንጀል የተፈፀመበት ተሽከርካሪ በመሆኗ በመንግስት እንድትወርስ በማለት ታዟል።
3. ተጠሪ የተሠጠውን ውሣኔ እንዲያውቀው በአርባ ምንጭ ማረሚያ ቤት በኩል ይተላለፍላቸው ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58266

ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አልማዝ ደሴ - ከጠበቃቸው በላቸው ታደሰ ጋር - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የጉምሩክ ዐ/ሕግ ታደለ ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በዚህ በተያዘው ጉዳይ በሁለት ተከሣሾች ላይ ክስ አቅርቦባቸው የነበረ ሲሆን 1ኛ ተከሣሽ ያሁኗ አመልካች ናት፡፡ የክሱ ፍሬ ቃልም ተከሣሾች የወ/ሕ/ቁ/32/1/ሀ/ እና የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/1/ሀ/ለ/ በመተላለፍ 1ኛ ተከሣሽ በዲክላራሲዮን ሴሪ ቁጥር 31701 ተመዝግቦ ከቀረጥ ነፃ ያስገባችውን የሴለዳ ቁጥሩ ኮድ 2.76388 አ.አ ሱዚኪ መኪና ለ2ኛ ተከሣሽ አሳልፋ በመስጠት እንዲሁም አቶ ጥላሁን አበበ የተባለው ግለሰብ ከወጋገን ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ ለተበዳረው ገንዘብ መኪናውን በዋስትና በማስያዝ በህግ ከተፈቀደው ውጪ ለሌላ ሰው አገልግሎት እንዲውል አድርጋለች፤ 2ኛ ተከሣሽ መኪናውን እያሽከረከረ የካቲት 06 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 6፡00 ብሔራዊ ትያትር አካባቢ በመገኘቱ ሁለቱም ተከሣሶች ከቀረጥ ነፃ የገባውን መኪና አለአግባብ ሲገለገሉ ተገኝቷል የሚል ነው፡፡

1ኛ ተከሣሽ ወንጀሉን አለመፈፀሟንና ጥፋተኛ አለመሆኗን ክዳ በመከራከሯ የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የከሳሽንና የ1ኛ ተከሳሽን ማስረጃ ከመረመረ በኂላ ተከሳሿ ከቀረጥ ነፃ የገባውን መኪና መብቱ ከተሰጠበት ፈቃድ ውጪ ለሌላ ሰው አገልግሎት እንዲውል ማድረጓ በበቂ ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ተጠቅሶ ክስ በቀረበባት አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/1/ሀ/ ሥር ጥፋተኛ ናት ሲል በመወሰን በመኪናው ላይ የሚፈለገውን ቀረጥ ብር 100,489.37 /አንድ መቶ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ከሰላሣ ሰባት ሳንቲም/ መቀጮ እንድትቀጣ በሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-76388 አ.አ የሆነው መኪናም ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ እንዲሁም በ6 ወር እሥራት እንድትቀጣና የእሥራቱ ቅጣት ቢፈፀሙ በምታስተዳድራቸው ልጆች ላይ ከሚደርሰው ጉዳት አኳያ የእሥራቱ ቅጣት ተገድቦ ለተከሣሽ የፈተና ጊዜ ቢሰጥ ፍ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል በማለት ስለመልካም ጠባይ ብር 5000 /አምስት ሺህ/ ዋስትና ስታቀርብ ቅጣቱ ሳይፈፀም ታግዶ እንዲቆይ ወስኗል፡፡

ተከሣሽዋም በሥር የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ብታቀርብም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/195/2/ለ/2/ መሠረት የሥር የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታም በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ሲሆን በዋናነት የዘረዘራቸው የቅሬታ ነጥቦች አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/1/ከቀረጥ የገባ ዕቃ ለሌላ ሰው ያስተላለፈ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት እንዲውል ያደረገ ሰው የሚጠየቅበት ሕግ ሲሆን "ማስተላለፍ" የሚለው ቃል በአዋጁ ትርጉም አልተሰጠውም ፡፡ በመሆኑም በፍ/ሕ/ቁ 1186/1/ ንብረት የገዛ ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን እጁ ባደረገ ጊዜ የተላለፈ ይሆናል በሚል ስለሚደነግግ እንደሁም ስለመያዣ በፍ/ሕ/ቁ/ 2834/1/ በመያዣ ውል ውስጥ በዕቃው ላይ ባለመብት የሚሆነውን ለይተው ካልተዋዋሉ በቀር አስያዡ በመያዣነት ለሰጠው ዕቃ ባለቤት ሆኖ ይቆያል የሚል በመሆኑ አመልካች መኪናውን በተባሉት መንገዶች ይዞታውንም ሆነ ባለቤትነት መብት ያላስተላለፍኩ ስለሆነ በወንጀል ሕግ መከሰስ አይገባኝም ነበር፣

- መኪናው ከባንክ ለተሰጠው ብድር ለብር 90,000 በዋስትና የተያዘ ቢሆንም ለመኪናው ያልተከፈለ ገንዘብ ደግሞ ብር 100,489.73 በመሆኑ በልዩነትም ብዙ የሚተርፍ ገንዘብ በመኖሩ አመልካች የጉምሩክ ቀረጥ ለማስቀረት አስቤ ያደረግኩት ነገር ባለመሆኑ ድርጊቱ በወንጀል ሕግ ቁጥር 23 መሠረት የወንጀልን ድርጊት ከሚያቋቁሙት ግዙፍ ተግባራት የሐሳብ ክፍሉን አላሟላም

በመሆኑም ወንጀል በሌለበት ቅጣት አይኖርም፡፡

- መኪናውን ስያሽከረክር የነበረው የእህቴ ልጅ / 2ኛ ተከሣሽ የሆነው/ ሲሆን በጊዜው አይኔን አሞኝ ስለነበር እንዲይዝልኝ ያደረግኩ በመሆኑ ይኸው ድርጊት "ማስተላለፍን" አያሟላም
- ከቀረጥ ነፃ የገባው መኪና አለአግባብ ተገለገለ ቢባል እንኳን የጉምሩክ መ/ቤት መመሪያ ቁጥር 46/2002 አንቀጽ 7 መሠረት የቀረጥና የታክስ 25% መቀጫ በማስከፈል መኪናው ለአመልካች መመለስ ሲገባው እንዲወረስ ማድረጉ ሕግን የሚቃረን ነው የሚሉ ናቸው

ለሰበር ቅሬታ ተጠሪው በሰጠው መልስ የቀረጥ ነፃ መብት ያለተጠያቂነትና ያለገደብ የተሰጠ አይደለም፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 60/89 እና 368/95 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73 ከቀረጥ ነፃ የገባን መኪና መብቱ ከተሰጠበት አላማ ውጪ አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ የተከለከለና የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስከትል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ከአዋጅ ቁጥር 60/89 እና አዋጅ ቁጥር 368/95 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/2/ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ መኪናውን እንዲያሽከረክር ላልተፈቀደለት ሰው አሳልፋ ሰጥታለች፡፡ ይኸው የሥር 2ኛ ተከሣሽም መኪናውን ሲያሽከረክር መገኘቱን በሥር ፍ/ቤት ባቀረብነው ማስረጃ አረጋግጠናል፡፡ ከዚህ ሌላ አመልካች ከቀረጥ ነፃ የገባውን መኪና ለባንክ መያዣነት በመስጠት የብድር አገልግሎት አግኝታለች፡፡ አመልካች ይደግፈኛል በማለት የጠቀሰችው የጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 46/2002 ሥራ ላይ የዋለው ከግንቦት 13 ቀን 2002 ጀመሮ ሲሆን አመልካች ጥፋተኛ ነው ተብላ ውሣኔ ከተሰጠ ከአንድ ዓመት በኋላ የወጣ በመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶ መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቋል፡፡



www.chilot.me

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም የሥር ፍ/ቤቶች የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካችን ጥፋተኛ በማድረግ የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፈባት በአዋጅ ቁጥር 60/89 እና 368/ 95 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73/1/ሀ/ ሲሆን አንቀጹም ማንኛውም ሰው ከቀረጥ ነፃ፣ በቅናሽ ቀረጥ ወይም በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ የገባን ዕቃ አዋጁን በሚቃረን መልኩና የቀረጥ ነፃ መብት ከተሰጠበት ምክንያት ውጪ መጠቀም እንደማይችል ይናገራል፡፡ በተጠቀሰው ሕግ አንቀጽ 73/1/ሀ/ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ዕቃዎችን፣ የገዛ ፣የተቀበለ፣ ያስተላለፈ ፣ የተገለገለ፣ አሳልፎ በሌሎች ሰዎች ግልጋሎት እንዲውል ያደረገ ሰው ደግሞ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 በፊደል “ለ” በተዘረዘሩት ቅጣቶች የሚቀጣ ይሆናል፡፡

አመልካችም ከቀረጥ ነፃ ያስገባችውን መኪና በአዋጁ መሠረት መጠቀም ሲገባት ለሥር 2ኛ ተከሣሽ አሳልፋ መስጠቷንና ይኸው ተከሣሽም ሲያሽከረክር መገኘቱን እንዲሁም በዋስትና አስይዛ ከባንክ ብድር ማግኘቷን በሥር ፍ/ቤት የፍሬ ነገር ክርክር በሚደረግበት ጊዜ መረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ያመለክታል፡፡

በመሆኑም በሥር ፍ/ቤት አመልካች አዋጁን በሚቃረንና የቀረጥ ነፃ መብት ከተሰጠበት ምክንያት ውጪ መሥራቱን በማረጋገጥ በአዋጅ ቁጥር 60/89 እና 368/95 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73/1/ ሥር ጥፋተኛ ናት ሲል በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤት አመልካች ለመኪናው ሊከፈል በሚገባ የቀረጥ ሂሳብ መጠን በገንዘብ መቀጮና በ6 ወር እሥራት እንድትቀጣና መኪናውም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የወሰነው መሠረታዊ የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን የተከተለና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/181633 በቀን 12/10/2001 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና በተጠቀሰው መዝገብ በቀን 15/10/2001 ዓ/ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/195/2/ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/82371 በቀን 18/8/2002 የሰጠው ፍርድ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/195/2/ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60400

12/11/2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሞያሌ ቅርንጫፍ ተወካይ አቶ ዳሉ አብዶ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ኤፍታታ እና ቢ ኤም ኤም ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ከሣሽ የነበረ ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም ከሣሽ ባለኝ የውጪ ንግድ ፈቃድ መሠረት 400 ኩንታል ቦሎቄ ግምቱ ብር 300,000 የሚሆነውን ወደ ኬኒያ ለማሻገር እንዲያስችለኝ ተከሣሽ መ/ቤት ተገቢውን የጉምሩክ ሥርዓት እንዲፈጽምልኝ በ13/04/2002 ዓ/ም ከቀኑ በግምት ከ7፡00 - 8፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ መኪናው እንደጫነ ወደ ተከሣሽ መ/ቤት ሳቀርብ ተከሣሽም በ15/4/2002 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ያልተሟሉ ነገሮች ማለትም የባንክ ፈቃድ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ የመሳሰሉትን አሟልቼ እንድቀርብ በማስታወቁ ከሣሽም ከተጠየቁት ነገሮች ውስጥ የባንክ ፈቃድ ብቻ አለመያዜን በመግለፅ መኪናው እንደጫነ በማቆም ወደ አዲስ አበባ የተመለስኩ ሲሆን ተከሣሽም በመሃሉ ኮንትሮባንድ ነው በሚል ከመኪናው በማራገፍ ስለከለከለኝ በፍ/ህ/ቁ 2028 እና 2031 መሠረት የጉዳቱን ዋጋ (9%) እና የጠበቃ አበል 10% እንዲከፍል ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሣሽም ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ ቦሎቄውን ወደ ተከሣሽ መ/ቤት ያቀረበውም የጉምሩክ ሥርዓት ለማስፈፀም ሲሆን ምርቱን ወደ ውጪ ለመላክ ፈቃድ ያለው ከመሆኑም ሌላ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ በጊዜው የነበረው ቢሆንም እነዚህን ነገሮች ብቻ መያዝ በቂ ባለመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 12 እና 13 ሥር የተገለፁ ነገሮች ሁሉ ተሟልተው መቅረብ ያለባቸው ሆኖ እያለ ከሣሽ በህጉ መሠረት ሳያሟላ ቦሎቄው በጉምሩክ ጠረፍ ውስጥ ገብቶ ስለተገኘ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2/42/ እና 9/1/ ሥር የተጠቀሰው መሠረት ኮንትሮባንድ ነው በሚል ተከሣሽ መያዙ በአግባቡ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ያከራከረው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም በሰጠው ውሣኔ ተከሣሽ የያዘው ንብረት /ቦሎቄ / የተከለከለ ካለመሆኑም ሌላ ከሣሽ ህጋዊ በሆነ ሁኔታ የላኪነት



www.chilot.me

ፈቃድ ኖሮት የንግድ ሥራውን የሚያከናውን ሆኖ እያለ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለመፈፀም ያልተሟሉ ነገሮች ካሉ እንዲሟሉ ከማድረግ በቀር ቦሎቄውን ኮንትሮባንድ ነው ብሎ ተከሣሽ መያዙ ያለአግባብ ነው በማለት የተያዘው 400 ኩንታል ቦሎቄ ለከሣሽ እንዲመለስ ብሏል፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካችም በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርብም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋቱ አመልካች በሥር ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካች በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡- ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2/17/ ፣ 12/4/ እና 13/1/ መሠረት አስፈላጊ ከሆኑ ሠነዶች አንድም ሳያመጣ የጉምሩክ ጠረፍ አቋርጦ ወጥቶ እያለ የተያዘውን ቦሎቄ ኮንትሮባንድ አይደለም መባሉ ህግን መሠረት ያደረገ አይደለም ፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን ዕቃ ከጉምሩክ ጠረፍ ማቋረጥ ይችላል መባሉ ተገቢነት የለውም፣

የአመልካች ጽ/ቤት የጉምሩክ ጠረፍን በማቋረጥ ከጉምሩክ ክልል ውጪ ከኬኒያ ድንበር 100 ሜትር በማይደርስ ርቀት የሚገኝ ሲሆን የጉምሩክ ሥነ ሥርዐት በአንድ ዕቃ ላይ መፈፀሙንና አለመፈፀመን የሚረጋገጥበት ቦታ እንጂ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚፈፀምበት ባለመሆኑ አመልካች መ/ቤት ተጠሪው ያልተሟሉ ሠነዶችን እስኪሚያመጣ ድረስ መጠበቅ ነበረበት መባሉ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው ለሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ በማንኛውም መስፈርት በህጋዊ መንገድ ወደ ውጪ ሊላክ የነበረው ቦሎቄ ኮንትሮባዱ ነው ሊባል የሚችልበት ሁኔታ ስለሌለ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን እኛም ተጠሪው ወደ ውጪ ሲልክ በአመልካች የተያዘው ቦሎቄ ኮንትሮባንድ ባለመሆኑ አመልካች ይመልስ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ? ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ተጠሪው ወደ ውጪ ሊልክ የነበረውን ቦሎቄ ኮንትሮባንድ ነው በማለት በዋናነት የሚከራከረው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 2/17/ ፣ 12/4/ እና 13/1/ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ተጠሪው አሟልቶ ባለመገኘቱ ነው፡፡ እነዚህን አመልካች አልተሟሉም የሚላቸውን ሁኔታዎች ከመመርመራችን በፊት በተጠቀሰው አዋጅ ስለኮንትሮባንድ ወንጀል የተደነገገውን የአንቀጽ 91/1/ ይዘት መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ በተጠቀሰው አንቀጽ መሠረት ማንኛውም ሰው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 ወይም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች ህጐች ወይም በእነዚሁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የተከለከሉ፣ ገደብ የተደረገባቸው ወይም የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸውን ዕቃዎች ወደ ጉምሩክ ክልል ካስገባ ወይም ከጉምሩክ ክልል ካስወጣ ወይም በህጋዊ መንገድ የወጡ ዕቃዎችን በህገወጥ መንገድ መልሶ ካስገባ ወንጀሉ የተፈፀመባቸው ዕቃዎችና መሳሪያዎች እና የወንጀሉ ፍሬ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጮና ከሰባት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል ይላል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ መንፈስ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ዕቃ ኮንትሮባንድ ነው ለማለት ዕቃው ወደ ጉምሩክ ክልል እንዳይገባ ወይም እንዳይወጣ በህግ የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ሲሆን ይገባል፡፡ እንዲሁም ከድንጋጌው መገንዘብ እንደሚቻለው የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ዕቃው ኮንትሮባንድ እንዲባል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የኮንትሮባንድ ወንጀልን የሚያቋቁም ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ድንጋጌው በህጋዊ መንገድ እንኳን የወጡ ዕቃዎችን በህገወጥ መንገድ ወደ ጉምሩክ ክልል ማስገባት እንደኮንትሮባንድ ወንጀል እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡

ይህንኑ የአንቀጽ 91/1/ መንፈስ ይዘን የአመልካችን ክርክር ስንመለከት አመልካች የተጠሪን ቦሎቄ የያዘው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ባለመፈፀሙ ሲሆን የያዘውም በጽ/ቤቱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ወደ ጉምሩክ ጽ/ቤት በመምጣቱ ኮንትሮባንድ ነው ተብሎ እንደሚወሰድ አንቀጽ 91/1/ አይገልጽም፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ዕቃው ኮንትሮባንድ ነው ሊባል የሚችለው ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ ጉምሩክ ክልል ሲገባ ወይም ከጉምሩክ ክልል ሲወጣ ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 2/7/ መሠረትም የጉምሩክ ክልል ማለት የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ነው፡፡ በመሆኑም ዕቃው ኮንትሮባንድ ነው ለማለት አመልካች ተጠሪው በህገ ወጥ መንገድ ቦሎቄውን ከኢትዮጵያ ግዛት /ከጉምሩክ ክልል/ ሲያስወጣ መያዙን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን በአግባቡ ባላስረዳበትና እንዲሁም በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁኑ አመልካች ተጠሪው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለማስፈፀም ወደ አመልካች ጽ/ቤት ቦሎቄን ጭኖ እንደመጣ ፣ በጊዜው ተጠሪው የሳኒነት ንግድ ፈቃድ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር / TIN/ ይዞ እንደነበር በማመን ሲከራከር ከቆየ በኋላ በሰበር ደረጃ የክርክሩን ጭብጥ በመቀየር ተጠሪው ከጉምሩክ ጠረፍ አቋርጦ ሲወጣ ተይዟል በማለት መከራከሩ እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ጠቅሶ የተከራከረባቸው የአዋጅ ድንጋጌዎች ማለትም 2/17/ ፣ 12/4/ እና 13/1/ የተጠሪው ቦሎቄ ኮንትሮባንድ ነው ብሎ ላቀረበው ክርክር የሚረዱ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የአዋጅ አንቀጽ 2/17/ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ትርጉም የሚደነግግ ሲሆን አንቀጽ 12/4/ እና 13/1/ ደግሞ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በሚፈፀምበት ወቅት መሟላት የሚገባቸውን ሁኔታዎች ወይም ፎርማሊቲዎች የሚደነግጉ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ወይም ፎርማሊቲዎች ተጠሪው አሟልቶ ካልተገኘ ደግሞ የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት በውሣኔው እንዳሰፈረው እንዲያሟላ ከሚደረግ ውጪ ቦሎቄውን ኮንትሮባንድ ነው ብሎ መውረስ ህግን የተከተለ አሠራር አይደለም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ቦሎቄውን ኮንትሮባንድ ነው በማለት የያዘው ያለአግባብ ነው በማለት ለተጠሪው እንዲመልስ በሰጡት ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05017 በቀን 14/12/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሥር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 105644 በቀን 02/13/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች የወረሰውን 400 ኩንታል ቀይ ቦሎቄ ወይም በጨረታ የሸጠውን የቦሎቄ ዋጋ ለተጠሪ እንዲመልስ መወሰኑ አግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡



www.chilot.me

4. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ለሥር ፍ/ቤት ተሳልፎ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 65656

ሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - ባህር ዳር ቅርንጫፍ አቶ ዮሱፍ አብሬ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሪት ትዕግስት ጥላሁን - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ብሔራዊ ክልል የሰሜን ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ተጣርቶ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ወደ ሱዳን ለመላክ የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ አሟልታ ባቄላውን ወደ ሱዳን ሳጓጉዝ ተከሣሹ ተጨማሪ ሰላሣ ኩንታል ባቄላ አግኝቻለሁ በሚል ሰበብ የያዘብኝ ስለሆነ ባቄላውን ዋጋ ሱዳን በምሸጥበት ዋጋ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች አራት መቶ ኩንታል ባቄላ የጉምሩክ ሥርዓት የተፈጸመበት ቢሆንም ይህንን ሽፋን በማድረግ ሰላሣ ኩንታል ባቄላ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ሣያሟሉ ወደ ሱዳን ለማሻገር ሲሞክሩ ተይዘዋል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ንብረቱን መያዝና መወረስ እንደምንችል በህግ የተደነገገ በመሆኑ የከሳሽ ክስ የህግ መሠረት የለውም፡፡ የባቄላውን ዋጋ መክፈል አለባችሁ የሚባል ከሆነም ባቄላው በሀራጅ የተሸጠ በመሆኑ በሀራጅ በሸጥንበት ዋጋ እንጅ ከሣሽ በጠየቁት መሆን የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ወደ ሱዳን በመጓጓዝ ላይ ከነበረው ጭነት ውስጥ ሰላሣ ኩንታል ባቄላ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ሣይፈጸምበት ያገኘ ቢሆንም የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተፈጸበትን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ መያዝና መውረስ አልነበረበትም በማለት አመልካች ብር 362,346.23 የባቄላው ዋጋና የሌሎች ወጭዎች ብር 21,236.23 አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያወጡትን ያተለያዩ ወጭዎች በማለት የወሰነውን ብር 21,236.23 ተገቢ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ብር 362,346.23 ለተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡



www.chilot.me

አመልካች የካቲት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ 400 ኩንታል ባቄላ ሱዳን ወስደው ለመሸጥ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ካሟሉ በኋላ 430 ኩንታል ወደሱዳን ሲወስዱ መገኘታቸው በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተሟላበትንና የጉምሩክ ፎርማሊቲ ያልተሟላበትን ባቄላ መያዝና መውረሳችን በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 በተደነገገው መሠረት የፈጸምነው ህጋዊ ተግባር ሆኖ እያለ አላግባብ በልጽጓል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የባቄላውን ዋጋ እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

አመልካች የመኪናውን ዋጋ ይመልስ ቢባል እንኳን ባቄላው በሀራጅ የተሸጠበትን ብር 141,556.95 መሆን ሲገባው በዶላር ሂሣብ በማስላት እንድንከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የጠበቃ አበልና ወጭና ኪሣራም አላግባብ ተወስኖብናል በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ወደ ውጭ እንዲልክ 168 ኩንታል ባቄላ ቀሪ አለኝ ይህ ከሆነ አመልካች የሰላሣ ኩንታል ታክስና ቀረጥ በማስከፈል ከተፈቀደልኝ 168 ኩንታል መቀነስ ሲገባው መውረሱ ህጋዊ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በስር ያላቀረበውን አዲስ ክርክር በሰበር ደረጃ ያቀረበ ስለሆነ ክርክሩ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 329/1/ መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ ዝርዝር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የቀረበው ክርክርና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች አላግባብ በልጽጓል በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2163 መሠረት በማድረግ አመልካች የአራት መቶ ኩንታል ባቄላ ዋጋ በዶላር ምንዛሬ ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ወደ ሱዳን ለመላክ የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ አሟልተው ባቄላውን ወደ ሱዳን በሚያጓጉዙበት ጊዜ በጉምሩክ የመጨረሻ ጣቢያ ላይ ሲፈተሽ አራት መቶ ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ተጭኖ መገኘቱን በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ያልተሟላበት ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ተጠሪ የጫነች መሆኗ ስላልተረጋጠና ለዚህ ተጠያቂው ሹፌር ስለሆነ አመልካች ተጠሪ የጉምሩክ ቀረጥ የከፈለችበትንና አራት መቶ ኩንታል ባቄላ መወረሱ የህግ መሠረት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የህግ ትርጉም አዋጅ ቁጥር 60/89 መሠረታዊ ዓላማና አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ይዘት ያገናዘበ መሆኑን መርምረናል፡፡

ተጠሪ ወደ ሱዳን ለመላክ ከጫኑት ዕቃ ውስጥ አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ተገቢው የጉምሩክ ሥርዓት ፎርማሊቲ የተሟላበት ሲሆን ከዚህ ጋር ተቀላቅሎ የተጫነው ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ተገቢው የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ ሣይሟላ የተጫነ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ተጠሪ የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ አሟልተው ከጫኑት አራት መቶ ኩንታል ጋር በመቀላቀል ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ለማስወጣት ሲሞክሩ በመጨረሻው የጉምሩክ ጣቢያ በተደረገ ፍተሻ የተያዘ መሆኑን ነው፡፡ ከተጠሪ የጉምሩክ ሥርዓት አሟልተው ከጫኑት አራት ኩንታል ባቄላ ጋር ተቀላቅሎ የተያዘው ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ሊወጣ ሲል የተያዘ ዕቃ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 28 ኮንትሮባንድ ማለት ህጐችንና በህግ መሠረት

የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ወደ አገር ውስጥ ለመግባት የመጀመሪያውን ከአገር ለመውጣት የመጨረሻውን የጉምሩክ ጣቢያ በማለፋ ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ማስወጣት እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ መሞከር ወይም መርዳት ወይም እነዚህን የንግድ መጠን ያላቸውን ዕቃዎች መያዝ መሸጥ ማስተላለፍና በእነዚህ ዓይነት ድርጊቶች መተባበርን ጨምሮ መሆኑ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ተጠሪ ወደ ሱዳን አገር ለመላክ የጫኑት ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ተሟልቶ የተጫነ ዕቃና በኮንትሮባንድ ከአገር ለማውጣት የተጫነ ዕቃ አቀላቅሎ የያዘ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች በኮንትሮባንድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር የመከላከልና በዚህ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችንና መጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 5 ተሰጥቶታል፡፡ አመልካች የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ በማሟላት ተጠሪ የጫኑት አራት መቶ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ለማስወጣት ከተጫነው ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ጋር ተቀላቅሎ ሲያገኘው በህጋዊ መንገድ ከአገር እንዲወጣ የተፈቀደውን ዕቃና በኮንትሮባንድ ሊወጣ የነበረውን ዕቃ መውረሱ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ህጋዊ ስልጣን ሥር የሚወድቅ ተግባር ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ መታየት ይገባዋል፡፡ ለዚህም ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት አዋጅ ቁጥር 60/89 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 ማንኛውም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወደ አገር የሚያስገባውን ወይም ከአገር የሚያስወጣውን ዕቃ በሚመለከት ቀረጥ እንዲቀንስ እንዳይከፈል ወይም እንዲመለስ የተከለከለ ገደብ ወይም ቁጥር የተደረገበት ዕቃ እንዲገባ እንዲወጣ ወይም እንዲተላለፍ በማሰብ ለባለስልጣን በጽሁፍ በቃል በአካል እንቅስቃሴ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም በሚያቀርበው ወይም በሚያደርገው የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ ዋጋቸው ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ የሆኑ ሰነዶች ያቀረበ ሰነዶችን የደለዘ የፋቀ አስመስሎ የሰራ ወይም ማናቸውም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት ዕቃና ለማጭበርበሩ በሽፋንነትና ከለላነት ያገለገሉት ዕቃዎች ውርስ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፈል ከሚባው ቀረጥና ታክስ በማያንስ የገንዘብ መቀጮና ከአስራ አምስት እስከ ሀያ አምስት በሚደርስ እስራት ሁለቱንም በማጣመር ይቀጣል በሚል መንገድ የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 67 በማሻሻል ደንግጓል፡፡

የጉምሩክ ቀረጥ ሣይከፍል ዕቃ ወደ ውጭ ለማሳለፍ በማሰብ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ያልተሟላበትን የኮንትሮባንድ ዕቃ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከተሟላበት ዕቃ ጋር ቀላቅሎ ጭኖ መገኘት ከላይ በተገለጸው የህግ ድንጋጌ መሠረት የማጭበርበር ድርጊት እንደተፈጸመ ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም የሚለው በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 ማናቸውንም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ የሚለው የአማረኛው ቅጅ እና በእንግሊዝኛው ቋንቋ "do any mischievous act" በሚል መንገድ ከተገለጸው አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በህጋዊ መንገድ ወደ ውጭ እንዲላክ ከተዘጋጀ ዕቃ ጋር በህጉና በመመሪያው መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ያልተከፈለበት የኮንትሮባንድ ዕቃ ቀላቅሎ በመጫን የጉምሩክ የመጨረሻ ኬላ ለማለፍ መሞከር የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 አማረኛው ቅጅ ማናቸውም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ በሚል መንገድ በገለጸውና የእንግሊዝኛው ቅጅ "do any mischievous act" በሚል መንገድ ከገለጻቸው የማጭበርበር ድርጊቶች ውስጥ የሚካተት ህገ ወጥ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በህጋዊ መንገድ

ወደ ሱዳን ለመላክ የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ ያሟሉበትን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ በሽፋንነትና በከለላነት በመጠቀም ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ውጭ እንዲወጣ የማድረግ ተግባር የተፈጸመ መሆኑን ያረጋገጠው አመልካች በኮንትሮባንድ ከአገር ውጭ ሊወጣ የነበረውን ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ብቻ ሣይሆን ይህንን ባቄላ በኮንትሮባንድ ለማስወጣት በሽፋንነትና ከለላነት ያገለገለውን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ መውረሱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 ገዥነት ባለው ሁኔታ በደነገገው መሠረት የኮንትሮባንድ ወንጀል ለመፈጸም በሽፋንነትና በከለላነት ያገለገለውን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ የወረሰ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2163 ድንጋጌዎች በመጥቀስ አመልካች በህግ በተደነገገው መሠረት የወረሰውን ዕቃ ዋጋ በወቅቱ በነበረው የዶላር ምንዛሬ ታስቦ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 60/89 እና አዋጅ ቁጥር 368/95 መሠረታዊ አላማና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ያሟሉት አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ተቀላቅሎ የተጫነውን ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ለማስወጣት በሽፋንነትና ከለላነት ያገለገለ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አንድ ላኪ ዕቃ ወደ ውጭ ለመላኩ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ካሟላ በኂላ ዕቃውን ከመነሻው እስከ መድረሻው በመጓጓዝ ሂደት ሊከበሩ የሚገባቸው ሥርዓቶች በአዋጅ ቁጥር 60/89 ከአንቀጽ 16 እስከ አንቀጽ 18 ተደንግጓል፡፡ የዕቃው ላኪ እነዚህ ህጋዊ ሥርዓቶችና ደንቦችን ባከበረ ሁኔታ ከመነሻው እስከ መድረሻው ዕቃው የተጓጓዘ መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት እንዳለበትና ይህንን ግዴታውን በአግባቡ ሣይወጣ ቀርቶ ቀረጥ ያልተከፈላቸውና የተደበቁ ዕቃዎች ተቀላቅለው ከተጫኑ የዕቃው ባለቤት በሀላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 58 ንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው ተጠሪ ህጋዊ ቀረጥ የከፈለበት አራት መቶ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ዕቃ ለማስተላለፍ በሽፋንነትና በከለላነት በማያገለግልበት ሁኔታ በጥንቃቄ ከመነሻው እስከ መድረሻው እየተጓጓዘ መሆኑን የመከታተል ህጋዊ ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው ተጠሪ ይህንን ሀላፊነታቸዉ ሣይወጡ ቀርተው ዕቃው የኮንትሮባንድ ዕቃ ለማሳለፍ በሽፋንነትና በከለላነትና ያገለገለ መሆኑን አመልካች ካረጋገጠ አመልካች በኮንትሮባንድ ከአገር ሊወጣ የነበረውን ዕቃ ብቻ ሣይሆን በኮንትሮባንድ ዕቃ ለማሳለፍ በከለላነትና ሽፋንነት ያገለገለውን ዕቃ ለመያዝና ለመውረስ እንደሚቻል በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 የተደነገገ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በኮንትሮባንድ ከአገር ሊወጣ የነበረውን ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በተጠሪ የተጫነ መሆኑ ስላልተረጋገጠ አመልካች ህጋዊ ቀረጥ የተከፈለበትን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ለመውረስ የሚችልበት ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ለማስወጣት በሽፋንነትና ከለላነት ያገለገለውን የተጠሪን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ የወረሰው በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 5 እና በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሆኖ እያለ አላግባብ በተጠሪ ንብረት በልጽጓል በማለት የአራት መቶ ኩንታል ባቄላ ዋጋ በወቅቱ በነበረው የዶላር ምንዛሬ ሂሣብ እንዲከፍል የሰሜን ጉንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል የሰሜን ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 65 በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 መሠረት የወረሰውን የአራት መቶ ኩንታል ባቄላ ዋጋ ለተጠሪ የመመለስና የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57243

መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የሚሴ ገቢዎችና ጉምሩክ - ዓ/ህግ ግርማ መርሃ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ደረጀ ከፍያለው ሲማ - ከጠበቃ በላቸው ታደሰ ጋር - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ከተከሰሰበት የኮንትሮባንድ ወንጀል በነፃ የተሰናበተ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104/3/ሀ መሠረት ተሽከርካሪው እንዲወረስ በስር ፍ/ቤቶች አለመወሰናቸው የሕግ ስህተት ነው በሚል እንዲታረም ጠይቋል፡፡

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ የቀረበው በአመልካች በኩል ነው፡፡ የክሱ መነሻም ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-15475 ኦሮ. ቅጥቅጥ አይሱዙ የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ከሐረር ወደ አ/አ ሲጓዝ አዋሽ ጉምሩክ ፍተሻ ላይ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን የኮንትሮባንድ እቃ ጭኖ በመገኘቱ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/1/ መሠረት ሾፌሩ፣ ረዳቱ እና 3ኛ ተከሳሽ /ባለንብረቱ/ በኮንትሮባንድ ወንጀል ተከሰዋል፡፡ የአፋር ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የስር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጥፋተኛ ናቸው ብሎ የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ 3ኛ ተከሳሽ /ባለንብረቱ/ የአሁኑ ተጠሪን ጥፋተኛ የሚያሰኝ ድርጊት አልፈፀመም በማለት ከክሱ በነፃ አሰናብቷል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረቱ ይኸው ሆኖ ተጠሪው ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ቢባልም የኮንትሮባንድ እቃ የጫነው /ያጓጓዘው/ መኪና እንዲወርስ ሊወሰን ይገባ ነበር የሚል ነው፡፡ የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ ስለንብረቱ መወረስ ወይም አለመወረስ ትዕዛዝ አለመሰጠቱ ተገቢነት ከተጠቀሰው ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ተጠሪ እንዲቀርብ አዝዟል፡፡

ተጠሪው ነሐሴ 17 ቀን 2002ዓ.ም ባቀረበው የጽሑፍ መልስ በጉምሩክ ሕግ ገደብ የተደረገበት ወይም ቀረጥ ያልተከፈለበት እቃ የተጫነው በሹፌሩ እና በረዳቱ እንጂ በተጠሪ አለመሆኑን እንዲሁም የእቃ መደበቂያ /ሻግ/ ተሰራ የተባለው ለክሪክ፣ ለሸራና ለጎማ በተሰራ መያዣ መሆኑና ድርጊቱ የተፈፀመው ከተጠሪ እውቀትና ፍላጎት ውጪ መሆኑ ተረጋግጦ በነፃ መሰናበቱን



www.chilot.me

ጠቅሶ መኪናውም ሊወረስ እንደማይገባ ተረጋግጦ እንዲመለስለት በስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ መሰጠቱ በአግባቡ ነው በማለት በስር ፍ/ቤት ውሳኔ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

የአመልካች ዓ/ህግ በሰጠው የመልስ መልስ መኪናው እንዲመለስ የተሰጠው ትዕዛዝ አለአግባብ ነው ሲል አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደመርመርነውም የተጠሪ ከቀረበበት የኮንትሮባንድ ወንጀል ክስ በነፃ የተሰናበተ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ዓ/ህግ አጥብቆ የተከራከረው ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው የሕዝብ ማመላለሻ መኪና የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን እቃ ጭኖ መገኘቱ ተረጋግጦ ሹፌሩና ረዳቱ ጥፋተኞች ተብለው የተቀጡ ስለሆነ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104/3/ መሠረት መኪናው /ማጓጓዣው/ እንዲወረስ ዓ/ህግ ያቀረበውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በማየት መወረስ ነበረበት የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ሲል የያዘው ጭብጥ ስለማጓጓዣው መወረስ ወይም አለመወረስ የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሳይሰጥበት የማለፉን አግባብነት ለማጣራት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ በሰጠው መልስ መኪናው ለተጠሪ እንዲመለስ ፍ/ቤቱ ከውሳኔው አስቀድሞ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ ዓ/ህግ በመልስ መልሱ ላይ ይህንን ሳይክድ መኪናው እንዲመለስ የተሰጠው ትዕዛዝ የአዋጁን አንቀጽ 104/3/ ይቃረናል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው መኪናው እንዲመለስ በስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለመሰጠቱ ግራ ቀኙ የተማመኑበት መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህም የሰበር ችሎቱ ውሳኔ የሚሻ ጉዳይ መኪናው ለተጠሪ እንዲመለስ መታዘዙ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ከክርክሩ መረዳት የተቻለው ተጠሪ የመኪናው ባለንብረት ቢሆንም ከወንጀል ድርጊቱ በነፃ የተሰናበተ መሆኑን ነው፡፡ ተከሳሽ በነፃ የተሰናበተ እንደሆነ ንብረቱ ሊወረስ የሚቻልበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 104/3/ሀ/ ስር በተለየ ሁኔታ (exceptional situation) ተመልክቷል፡፡ ይኸውም ስለድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ የሚያስረዳ አጥጋቢ ማስረጃ መቅረቡንና ፍ/ቤቱ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው (Where the court is satisfied) ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር ስንመለከት ሹፌሩና ረዳቱ ጥፋተኛ ሆነው የተቀጡት በመኪናው ለክሪክ እና ሽራ፣ ጎማ መፍቻና ሌሎች መሰል እቃዎች ማስቀመጫ ተብሎ ከሹፌሩ ወንበር ጋር ተያይዞ በተሰራ ክፍል ውስጥ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት እቃ ደብቀው በማጓጓዛቸው ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡

በስር ፍ/ቤት የቀረበው እና የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ተጠሪ መኪናው ላይ ያሰራው የእቃ ማስቀመጫ ክፍል ከፍ ሲል ለተጠቀሰው አገልግሎት እንጂ ለሕገ ወጥ ዓላማ ነው ሊያስብል የሚያስችል አይደለም ተብሎ በወንጀሉ አፈፃፀም ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሐሳብ ነበረው ሊያሰኝ የሚችልበት ሁኔታ እንደሌለ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ የተነሳ በሕጉ አነጋገር የተጠሪ ንብረት የሆነው መኪና እንዲወረስ ለማድረግ ፍ/ቤቱን ሊያሳምን የሚችል ማስረጃ በአመልካች በኩል ያልቀረበ ስለመሆኑ መረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ አንፃር የተጠሪ መኪና ሊወረስ አይገባም ሲል የስር ፍ/ቤት



www.chilot.me

የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ባለበት ሁኔታ ሊፀና ይገባል ብለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በአፋር ብ/ክ/መ/ ገብረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01206 በ17/05/2002ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 89430 በ24/09/2002ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ሰኔ 17 ቀን 2002ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሶ/በ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 65330

ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡-ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር

**ተጠሪ**፡-1. አቶ ተክሌ ጋርደው

2. አቶ ሐይማኖት አባተ

3. አቶ ታረቀኝ ወልዴ

4. አቶ ተሾመ አረጋይ

5. አቶ አብነት ደምሰው

6. አቶ አቡኪያ ቤኛ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር00944/2002 ሚያዚያ 15 ቀን 2002 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ውሳኔ ባግባቡ ነው ሲል በፍ/ይ/መ/ቁጥር 55990 ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው ምክንያነት የሆነው ጉዳይም አገልግሎትና የእድሜ መስፈርቱን የማያሟሉ ሰራተኞች ከስራ ሲሰናበቱ የመልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ እንዲያገኙ ሲደረግ በክፍያው ላይ የስራ ግብር ሊቀነስ ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ላይ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስራ ግብር ሊቀነስ አይገባም በማለት ውሳኔ በመስጠታቸው ነው፡፡በዚህ መሰረት በቀረበው አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለው ይህንኑ ነጥብ ለማጣራት ሲሆን አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ተመርምሯል፡፡ ለዚህም ስለገቢ ግብር የሚደነግገውን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 መመልከቱ

ተገቢ ነው። በአዋጁ አንቀጽ 10(1) ስር በግልፅ እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ የገቢ ግብር ይከፍላል በማለት ተቀምጧል። ከግብር ክፍያ ነጻ የሆኑትን አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 13 ላይ በዝርዝር ሲገልጽ አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ጉዳይ አይነት በግልፅ ከስራ ግብር ነፃ ስለመሆኑ አይጠቅስም። ይህ አንቀፅ ከግብር ክፍያ ነፃ የሆኑትን ከዘረዘራቸው ውስጥ ማናቸውንም አይነት የጡረታ ጥቅም፣ወይም በተቀባዩ ሰው ላይ በደረሰ የአካል ጉዳት ካሳ ወይም በሌላ ሰው ላይ በደረሰ የሞት አደጋ የሚሰጥ የካሳ ክፍያ የሚሉት ይገኙበታል።የካሣ ክፍያ ሲባልም በሕጉ ላይ በግልፅ እንደተመለከተው በደረሰ የአካል ጉዳት ወይም በደረሰ የሞት አደጋ የሚሰጥ የካሳ ክፍያ የሚመለከት እንጂ ማናቸውንም የካሳ ክፍያ ሁሉ ከግብር ነጻ መሆኑን የሚጠቅስ አይደለም።በመሰረቱ የስራ ግብር የሚከፈለው ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 10(1) በግልፅ ያሰፈረው ሲሆን አዋጁ ገቢን አስመልክቶ በሰጠው የትርጉም ክፍል ላይ ገቢ ማለት ማናቸውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማናቸውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት በማናቸውም መልክ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው በስሙ የተያዘለትን ወይም የተቀበለውን ጥቅም ሁሉ እንደሚጨምር እንዲሁም ግብር የሚከፈልበት ገቢ ማለት ደግሞ በአዋጁና በአዋጁ መሰረት በሚወጡት ደንቦች መሰረት ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው የገቢ መጠን መሆኑ አዋጁ በአንቀጽ 2(10) እና 1(11) አስፍሯል። በመሆኑም ለተጠሪዎች ይከፈል የተባለው የመቋቋሚያ ክፍያ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት አላገኘንም።በዚህም መሰረት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል።

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 9711

ሰኔ 14 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ሸበል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ብናልፈው ነጋ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐቃቤ ህግ ተወዳጅ ሲማ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀርቦ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አመልካች ያቀረባቸውን ሶስት መሠረታዊ ክርክሮች ውድቅ በማድረግ ወስኗል አመልካች የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተጠሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ በግምት መወሰኑን ፣ ተጠሪ አመልካች ቅጣት እንዲከፍል መወሰኑና የተጨማሪ እሴት ታክስ ከመዝገቡ በፊት የሽያጭ ታክስ የተከፈለበትን አለመቀነሡን በመቃወም ያቀረብኩትን የህግ ክርክር አልፎብኛል በማለት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ በመዝገብ ቁጥር 43485 ከመረመረ በኋላ ተጠሪ አመልካች እንዲከፍል በግምት የወሰነውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 12/1/ የሚጥስ ነው በማለት ሽሮታል፡፡ ተጠሪ አመልካች የተለያዩ ቅጣቶች እንዲከፈል የሰጠው ውሣኔ የህግን ድንጋጌ የተከተለ አይደለም በማለት በግልፅ ሽሮታል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በሽያጭ ታክስ መልክ ገቢ የሆነው ገንዘብ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ሊቀነስልኝ ይገባል በማለት ያቀረበውን ክርክር በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሶ ልኮለታል፡፡

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ውሣኔ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43985 ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ጉዳዩን አጣርቶ መስከረም 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን በማስቀረብ ተገቢውን ማጣራትና ምርመራ ካደረገ በኋላ አመልካች ታህሣሥ 23

ቀን 1995 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆንም የተጨማሪ እሴት ታክስ ያስታወቀው ነሐሴ 13 ቀን 1995 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህን ጊዜ በቅፅ 202 ያስታወቀው የሰኔ ወር 1995 እንቅስቃሴን እንጅ በህጉ መሠረት ሊመለስለት የሚገባውን የሽያጭ ታክስ በመዘርዘር የሽያጭ ታክሱ እንዲመለስለት ጥያቄ አላቀረበም፡፡ ስለሆነም አመልካች በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና ደንብ ቁጥር 79/95 መሠረት ማስታወቅና ጥያቄ ማቅረብ በሚገባበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ያሳወቀ በመሆኑ በሽያጭ ታክስ የከፈልኩት ይቀነስልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመዝገብ ቁጥር 72906 ከሰማ በኂላ የጉባኤውን ውሣኔ ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካች መቶ ፐርሰንት ግብር አልከፈለም በማለት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 ድንጋጌ ጠቅሶ ሰርዞታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥራ ላይ ከመዋሉ ከስድስት ወር በፊት ተገዝተው በነበሩ ዕቃዎች የከፈለውና በህጉ አግባብ ሊቀናነስለት የሚገባውን የሽያጭ ታክስ ተጠሪ ሲያቀናንስለት ከቆየ በኂላ እንቢተኛ ሆኗል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሽያጭ ታክስ የተከፈለውን እንዲቀናነስልን የምንከራከር ሆኖ እያለ መቶ ፐርሰንት ግብር ሣይከፍል የቀረበ ይግባኝ በመሆኑ ይግባኙ አይታይም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ስለሆነም በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንዲከፍላቸው የሚፈልገው ገንዘብ የግብር ገንዘብ በሌለበት ሁኔታ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥራ ላይ ከመዋሉ ከስድስት ወር በፊት የከፈልኩት የሽያጭ ታክስ እንዲቀናነስልኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ መቶ ፐርሰንት ግብር ከፍለህ አልቀረብክም ብሎ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ አደረገብኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ አይደለም አመልካች ብር 9,652,121.44 ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል ተጠሪ የሰጠውን የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው አፅንቶታል፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንን የግብር ገንዘብ መቶ ፐርሰንት ሣይከፍል ይግባኙ እንደማይታይለት በመግለፅ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 285/94 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ጥያቄው የይቀናነስልኝ ጥያቄ በመሆኑ መቶ ፐርሰንት የሚከፈል ግብር የለም፡፡ ይኸም ቢታለፍ አመልካች ግብሩን ከፍሎ እንዲቀርብ ሊደረግ ይገባው ነበር ታህሣሥ 20 ቀን 2003 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በማለት ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ ከስድስት ወራት በፊት በአመልካች እጅ በነበሩት ዕቃዎች ላይ ተከፍሎ የነበረው የሽያጭ ታክስ ሊቀናነስልኝ ይገባል በማለት የሚከራከረው ተጠሪ ወስኖ ካሣወቀው የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብርና በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ከፀደቀው የግብር ውሣኔ መሆኑን በሥርና በዚህ ፍርድ ቤት በግራ



www.chilot.me

ቀኙ ከተደረገው ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በተጨማሪ እሴት ታክስ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በተሰጠ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ሥርዓት በግብር ይግባኝ አዋጅ ቁጥር 286/94 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 285/94 በአንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4 በግልፅ ይደነግጋል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሣኔ የህግ ስህተት አለበት የሚል ቅሬታ ያለው ግብር ከፋይ ይግባኙን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት የሚያቀርበው በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የተወሰነበትን የግብር ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ሲከፈል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 4 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች በግብር ይግባኝ ጉባኤ እንዲከፍል የተወሰነበትንና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ሙሉ በሙሉ የከፈለ መሆኑ ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚው ችሎት ለማቅረብ በህግ የተደነገገ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ የአመልካች ጥያቄ የሽያጭ ታክስ ከተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲቀናነስልኝ የቀረበ ነው በሚል ምክንያት በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የተወሰነበትን የተጨማሪ እሴት ግብር ሙሉ በሙሉ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማያያዝ የቀረበውን ይግባኝ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4 እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገውን ቅድመ ሁኔታ ሣይሟላ የቀረበ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት መሠረዙ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና ምንም አይነት የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው፡፡

አመልካች ለይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኙን ከማቅረቡ በፊት በህግ የተጣለበትን ቅድመ ሁኔታ ያሟላ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች በህጉ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ሣያሟላ የይግባኝ መዝገብ አስከፍቶ ያገኘው ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ቅድመ ሁኔታውን አሟልቶ እንዲመጣ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ቅድመ ሁኔታውን አሟልቶ የሚመጣ መሆኑን ለመጠባበቅ ቀጠሮ ሰጥቶ እንዲጠባበቅ የሚያስገድድው የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ይግባኝ ባይ ይግባኙን ለማቅረብ ሚሟላት የሚገባውን ቅድመ ሁኔታ ሣያሟላ ይግባኝ እንዳቀረበ ከተረዳ የህጉ የተደነገገውን ግዴታ ሣያሟላ ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ይግባኝ በመሰረዝ መዝገቡን መዝጋት እንደሚችል ከአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4 እና ከአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌዎች የጣምራ ንባብ መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚው አቅርቦ ለማሰማት በህግ የተደነገገውን ቅድመ ሁኔታ ያሟላ መሆኑን የማስረዳተና የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት አመልካች በህጉ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታና ግዴታ ሣይፈፅም ያቀረበውን ይግባኝ  ይግባኝ ሰሚው ተቀብሎ አለመሰማቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ በሰበር ችሎት የተጠቀሱት የደንብ ቁጥር 79/95 አንቀፅ 5 ፣ አንቀፅ 8 እና አንቀፅ 9 አመልካች ከፍያዋለሁ የሚለው የሽያጭ ግብር ከተጨማሪ እሴት ታክስ ግብሩ ሊቀናነስለት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን መሠረታዊ ጭብጥ በመወሰን ሒደት ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የሚገቡ የህግ ድንጋጌዎች ናቸው በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የተወሰነበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ በሙሉ ሣይከፈል ያቀረበው ይግባኝ በህግ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ የሚያሟላ አይደለም ብሎ ይግባኙን መሰረዙ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ሆነው አላገኘናቸውም፡፡



www.chilot.me

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀጽ 4 እና አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌዎችን ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

# ከውል ውጭ ኃላፊነት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54021

ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ዱላ ያሲን - ከጠበቃ መላኩ ገ/ሥላሴ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አበበች እሸቴ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች አንደኛ ተከሳሽ አቶ አማረ ዘውዴ ሁለተኛ ተከሳሽ አዋሽ ኢንሹራንስ አክስዮን ማህበር ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ንብረቴ የሆነችውና የሰሌዳ ቁጥር 3-47351 የሆነ አይሱዙ የህዝብ ማመላለሻ መኪና ሀምሌ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ከሱልልታ ወደ አዲስ አበባ ተሳፋሪዎች ጭኖ ሲጓዝ በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛው ተከሳሽ በሆነው አቶ አማረ ዘውዴ የአንደኛ ተከሳሽ ማለትም የአመልካች ንብረት የሆነውን ኮድ 3-27054 በደረሰበት ግጭት በተሣፋሪዎችና በአሽከርካሪው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን መኪናው በወቅቱ ብር 132,000(አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ብር) ግምት ያለው መኪና ወድሟል፡፡ መኪናውን አስጠግኖ ሥራ እንዲጀምር ለማድረግ 28,000 (ሀያ ስምንት ሺህ ብር) ወጥቷል፡፡ ስለሆነም ለመኪና የወጣው 160,000 እንደዚሁም ከሀምሌ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 8 ቀን 2001 ያለው የተቋረጠ ገቢ በቀን 250(ሁለት መቶ ሀምሣ ብር) በድምሩ 190,000 እና ወደፊት በክርክሩ ሒደት የሚደርስ ጉዳት እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ በክርክሩ ጣልቃ የገባው አዋሽ ኢንሹራንስ የመኪናዋ ግምት ብር 132,000 ነው በማለት ያቀረቡት ግምት ተገቢነት የለውም፡፡ ስለዚህ የአገልግሎት ዘመኑ ተቀንሶ በመንገድ ትራንስፖርት ይገመት ከዚህ በተረፈ በወቅቱ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) እንዲቀበሉ ጠይቀናቸው እንቢ ያሉ በመሆኑ ከዚያ በኂላ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም በጣልቃገቡ የተነሱትን የመከራከሪያ ነጥቦች አንስተው ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ጣልቃገብ ግምቱን በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ በማድረግ መኪናውን አገልግሎት ላይ ለማዋል ብር 25,000 ወጭ ተደርጓል፡፡ መኪናው በደረሰበት አደጋ ውሣኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ

የተቋረጠ ገቢ ብር 81,420 የቀረ በመሆኑ መክፈል አለበት፡፡ መኪናው ለተጠበቀበት ብር 7080 ተከሳሾች ይክፈሉ በአጠቃላይ 245,500 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) አመልካችና ጣልቃ ገብ እንዲከፍሉ ከዚህ ውስጥ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) ጣልቃ ገቡ አዋሽ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ቀሪውን አንደኛ ተከሳሽ (አመልካች) ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ መኪናው የ1985 ዓ.ም ሞዴል በመሆኑ ግምቱ 132,000 እንደማያወጣ ያቀረብኩትን ክርክር የሥር ፍርድ ቤት አላግባብ አልፎብኛል፡፡ መኪናዋን አስነስቼ ያቆምኳት ስሉልታ ፖሊስ ጣቢያ አንስቶ ወስዶ ለጥበቃ ገንዘብ አውጥቻለሁ በማለት ተጠሪ ላቀረቡት ክስ እኔ ሀላፊ መባሌ ተገቢነት የለውም፡፡ መኪናው ሙሉ በሙሉ ወድሟል ተብሎ ሙሉ ግምቱን ክፈሉ ብሎ የሥር ፍርድ ቤት ከወሰነ በኋላ ለመስታወት ለወንበር ለጋራዥ ኪራይ ያወጡትን ገንዘብ ክፈሉ ብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ መኪናው በወር ሰላሣ ቀን አይሠራም ስለዚህ ኪሣራው ወሩን ሙሉ እንደሚሠራ ተደርጎ መታሰቡ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ክስ የቀረበበት ብር 190,000 ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ዳኝነት ከጠየቁት በላይ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው መኪናውን ከገዛሁት በኋላ ወንበር መስታወት ስላልነበረው ይህንን በማስተካከል ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) አውጥቻለሁ፡፡ አሁን ንብረቱን በፊት ባለው ዋጋ ለመተካት የሚቻል አይደለም መኪናው ላይ ጉዳት በመድረሱ ገቢ መቋረጡ የሚካድ አይደለም፡፡ ስለዚህ ለተቋረጠ ጥቅም አመልካች ካሣ እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመኪናው ሙሉ ዋጋ ገምተው ከጠየቁ በኋላ ለእያንዳንዱ የመኪና አካል ካሣ መጠየቃቸው በአግባቡ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመኪናውን ቅሪት እንድንወስድ ፍርድ ቤቱ ያልወሰነልን ወይም የቅሪት አካል ዋጋ እንዲቀነስልን ማድረግ ሲገባው ይህንን አለማድረጉ ተገቢ ባለመሆኑ ሰበር ችሎቱ እንዲወስንልን በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ መካከል የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የወሰኑት የካሣ መጠን ስለካሣ አወሳሰን የተደነገጉትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በጭብጥነት የያዝነውን መሠረታዊ ጉዳይ ለመፍታት የሥር ፍርድ ቤት መኪናዋ ለአገልግሎት ለመብቃት ተጠሪ አወጣሁ ያሉትን ወጭ አመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ተጠሪ ለመኪናዋ ማስጠበቂያ አወጣሁ ያሉትን ወጭ አመልካች ለተጠሪ እንዲተኩ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? መኪናዋ ላይ ጉዳት በመድረሡ ተጠሪ ያቀረባቸውን ገቢና የደረሰባቸው ጉዳትና አመልካች ሊከፍሉት የሚገባውን የካሣ መጠን ለማስላት የተከተለው ስልት ህጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የበታች ፍርድ ቤቶች ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-47351 ተሳፋሪዎች ጭኖ ሲጓዝ በአመልካች መኪና የግጭት አደጋ ስለደረሰበት ሊጠገን

በማይችል ሁኔታ የወደመ መሆኑን በውሣኔያቸው ገልፀዋል፡፡ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጥ የነበረው የተጠሪ ንብረት የሆነው መኪና አደጋው ሲደርስበት ሙሉ ዋጋውና ግምቱ 132,000 (አንድ መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር) እንደሆነ ተጠሪ በክሳቸው የገለፁ ሲሆን አመልካች ግምቱ የተጋነነ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ሆኖም የሥር ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የመኪናውን ጠቅላላ ዋጋ ብር 132,000 (አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ብር) በመገመት ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የተጋነነ አይደለም በማለት አመልካችና ጣልቃገብ ተከራካሪው መኪናው አደጋ ሲደርስበት የነበረውን ግምት ብር 132,000(አንድ መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ለመኪና ወንበር የመስታወትና የቴክኒክ ዋጋ ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) አመልካች ከመኪናው ግምት በተጨማሪ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 ለደረሰ ጉዳት የሚከፈለው ካሣ በተበዳዩ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን እንዳለበት የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) መኪናዋን ከገዛኂት በኋላ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንድትሰጥ ለማድረግ ለወንበርና ለመስታወት ያወጣሁት ነው በማለት በይግባኝና በሰበር ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም መኪናው አደጋ የደረሰበት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ባለበት ወቅት ነው፡፡ መኪናው አደጋ በደረሰበት ጊዜ የሚያወጣው ወቅታዊ ግምት ብር 132,000(አንድ መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር) ነው በማለት ተጠሪ ያቀረቡትን ግምት አመልካች ተቃውመው ፍርድ ቤቱ የተለያዩ ማስረጃዎችን ከመረመሩ በኋላ መኪናዋ የግጭት አደጋ በደረሰበት ጊዜ ወቅታዊ ግምት ዋጋው ብር 132,000(አንድ መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር) ስለሆነ አመልካች ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ መኪናው ከመገጨቱ በፊት ተጠሪ ለእያንዳንዱ የመኪና አካል በተናጠል ከፍየዋለሁ የሚሉትን ገንዘብ በመደመር አመልካች ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ በተጠሪ መኪና ከደረሰው ጉዳት በላይ አመልካችን ካሣ እንዲከፍሉ የሚያስገድድና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ መኪና ያስጠበቁበት ብር 7080 (ሰባት ሺህ ሰማንያ ብር) ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡትን ውሣኔ በተመለከተ ተጠሪ ለመኪና መጠበቂያ ከፍያለሁ ያሉትን ገንዘብ ወጭ ያደረጉት አደጋ ከመድረሱ በፊት መኪናቸውን ለማስጠበቅ ያወጡትን ገንዘብ በመደመር የጠየቁት መሆኑን ወይም ገንዘቡን የከፈሉት የመኪናውን ቅሪት ለማስጠበቅ መሆኑን ሣያጣሩ ውሣኔ የሰጡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ መኪናቸው ከመገጨቱ በፊት የመኪናቸውን ደህንነት ለማስጠበቅ የከፈሉትን ገንዘብ አመልካች እንዲተኩላቸው የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የመኪናዋ ቅሪት አካል ሱልልታ ፖሊስ ጣቢያ ያስቀመጡት መሆኑን በመግለፅ ያቀረቡትን ክርክርና የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በግልፅ በመካድ መልስ አልሰጡበትም፡፡ ጉዳቱ የደረሰ መሆኑንና በጉዳቱ የደረሰ ኪሣራ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ካሣ እንዲከፈለው የሚጠይቀው ሰው እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2141 ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ ለመኪናው ማስጠበቂያ አወጣሁ ያሉት ወጭ መቼና በምን ሁኔታ እንዳወጡትና በተለይም ወጭውን ያወጡት በአደጋው ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ (Burdon of Presentation of Evidence) ባልተወጡበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ ለመኪና መጠበቂያ አውጥቻለሁ ያሉትን ብር 7080(ሰባት ሺህ ሰማኒያ ብር) እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2141 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 ድንጋጌን መሠረት ያላደረገና ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. የተጠሪ መኪና በግጭቱ ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ምክንያት አመልካች በቀን ብር 230(ሁለት መቶ ሰላሣ ብር) ስሌት አደጋው ከደረሰበት ሀምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እስከሰጠበት ሀምሌ 3 ቀን 2001 ዓ.ም ተጠሪ የቀረባቸው ገቢ ብር 81,420 (ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ሀያ ብር) እንዲከፍሉ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መኪናው በዓመት ውስጥ ለጥገናና ለሰርቪስ የሚቆምበትን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሰጠ ውሣኔ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሥር ፍርድ ቤት በጣልቃገብነት ተከራካሪ የነበረው አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ጉዳቱ እንደደረሰ ተጠሪ በመድን ፖሊሲው መሠረት ብር 100,000 (መቶ ሺህ ብር) እንዲቀበሉ ጠይቋቸው የነበረ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ይህንን የሚያስተባብል ክርክርና ማስረጃ ከሥርም ሆነ ከዚያ በኋላ በተደረገው ክርክር ያላቀረቡ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ተጠሪ ይህንን ገንዘብ በቅንነት በመቀበል ቀረብኝ የሚሉትን ገንዘብ ከአመልካች መጠየቅ የሚችሉበት እድል በኢንሹራንስ ድርጅቱ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተበዳይ ላይ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈለው ካሣ ለቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ አኳኋን ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ከአመልካች ጋር ያለውን የመድን ውልና በውሉ ላይ ያለውን ጣሪያ መሠረት በማድረግ እንዲቀበሉት የጠየቃቸውን ብር 100,000(አንድ መቶ ሺህ ብር) በቅንነት ቢቀበሉ ገቢ በመቋረጡ ምክንያት የደረሰባቸውን ኪሣራ ሊያስቀሩት ወይም ሊቀንሱት የሚችሉበት አቅም ይፈጥርላቸው ነበር፡፡ ተጠሪ ይህንን ባለማድረጋቸውና ወደ ክርክር መግባት የማይፈልገውን አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) በጣልቃ ገብ ተከራካሪነት እንዲጠራ የሚያስገድድና ስድስት ወር የፈጀ ክርክር ከአመልካች ጋር ለማድረግ ተገደዋል፡፡ ሌላ ሰው ኃላፊ በሆነበት ድርጊት ወይም አደጋ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱን ለማስቀረት ወይም የጉዳቱን መጠን ቀላል ለማድረግ ግዴታና ሀላፊነት እንዳለበት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 2 ተበዳዩ በማስተዋል ቢሠራ ኖሮ የደረሰበትን ጉዳት ሊያግደው ወይም ሊያቀለው የሚችል ሲሆን በደረሰበት ጉዳት መጠን በሙሉ ካሣ ለመጠየቅ አይችልም በማለት በግልፅ ደንግጎታል፡፡ ተጠሪ በግጭቱ ጉዳት የደረሰበት መኪና ጠቅላላ ዋጋ ብር 132,000 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ከዚህ ውስጥ አዋሽ ኢንሹራንስ ለመክፈል ሙሉ ዝግጁነቱን ያሣየበትን ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ተቀብለው ቢሆን ኖሮ ከዚህ ገንዘብ ሌላ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ በመሥራት ወይም በዚህ ገንዘብ አነስተኛ መጠን ያለው ሌላ መኪና በመግዛት ወይም ተጨማሪ ገንዘብ ተበድረው አደጋ የደረሰበትን መኪና ምትክ በመግዛት በአደጋው ምክንያት የተቋረጠባቸውን የገቢ መጠን ለመቀነስ እየቻሉ ገንዘቡን ለመቀበል እንቢተኛ በመሆናቸው ምክንያት ኪሣራውን ለማስቀረት ወይም ሊያቀሉት እንዳልቻሉ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ከላይ የጠቀስነውን የህግ ድንጋጌ ግምት ውስጥ ሣያስገቡ ተጠሪ በአደጋው ምክንያት የተቋረጠባቸውን ገቢ አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ እስከሰጠበት ጊዜ ድረስ ያለውን በሙሉ አስበው የሰጡት ውሣኔ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) አደጋው እንደደረሰ እንዲቀበሉ የጠየቃቸውን ብር 100,000 (መቶ ሺህ ብር) ቢቀበሉ ኖሮ መኪናው በአደጋ በመውደሙ ምክንያት ሊያገኙት የነበረው ገቢ ከሶስት ወር በላይ ተቋርጦ የሚቀጥልበት ሁኔታ እንደማይኖር የነገሮችን ተራ ሁኔታዎችና ተጠሪ ተገቢውን ጥረት ያላደረጉና የቅንልቦና ጉድለት ያለባቸው መሆኑን በማገናዘብ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097(2) ወስነናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ ለቀረባቸው ጥቅም መክፈል የሚገባው የካሣ መጠን በቀን ብር 230(ሁለት መቶ ሠላሳ ብር) ሒሳብ የዘጠና ቀን ቀሪ ገቢ በድምሩ



www.chilot.me

ብር 20,700(*ሀያ ሺ.ህ ሰባት መቶ ብር*) ብቻ *መሆን ይገባዋል* በማለት በፍታብሔር *ሥነ ሥርዓት* ሕግ ቁጥር 348(1) አሻሽለን ወስነናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና በተራ ቁጥር 2 በተገለፁት ነጥቦች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ *መሠረታዊ* የሆነ የካሣ አወሳሰን *መርሆችን መሠረት ያላደረጉና* ተገቢነት የሌላቸው በቁጥር 3 የተመለከተው ነጥብ ደግሞ ተጠሪ በመኪናው *መውደም* ምክንያት የተቋረጠባቸውን የገቢ መጠን ለመቀነስ ወይም ለማቅለል የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት በቅን ልቦናና በአስተዋይነት ያደረጉት እንቅስቃሴ የሌለ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ያልሰጡና ውሣኔያቸው በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና ሊሻሻል የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የካሣውን መጠን በተመለከተ የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪ መኪና አደጋ በደረሰበት ወቅት የነበረውን ግምት ብር 132,000(*አንድ መቶ ሠላሳ ሁለት ሺ.ህ ብር*) ይክፈል ከዚ.ህ ውስጥ በሥር ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የሆነው አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ብር 100,000(*አንድ መቶ ሺ.ህ ብር*) ይክፈል በማለት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ ለመኪናው ወንበር መስታወትና የማስጠገኛ ያወጡትን ብር 25,000(*ሀያ አምስት ሺ.ህ ብር*) እንደዚሁም ተጠሪ መኪናውን ለማስጠበቅ ያወጡትን ብር 7080(*ሰባት ሺ.ህ ሰማኒያ ብር*) እንዲከፍሉ በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከላይ የተገለፀውን ብር 32,080 (*ሰላሣ ሁለት ሺ.ህ ሰማኒያ ብር*) ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ወስነናል፡፡
4. የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ መኪናቸው ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ምክንያት ተጠሪ ለተቋረጠባቸው ገቢ ብር 81,420(*ሰማኒያ አንድ ሺ.ህ አራት መቶ ሀያ ብር*) አመልካች እንዲከፍል በማለት የሰጡትን ውሣኔ አሻሽለን አመልካች በቀን ብር 230(*ሁለት መቶ ሠላሳ ብር*) ታስቦ የዘጠና ቀናት የተቋረጠ ገቢ ብር 20,700(*ሀያ ሺ.ህ ሰባት መቶ ብር*) ብቻ የመክፈል ሀላፊነት አለበት ብለናል፡፡
5. በአጠቃላይ በዚህ ውሣኔ መሠረት አመልካች ለተጠሪ የሚከፍሉት በሁለተኛ ተራ ቁጥር እንዲከፍሉ የተወሰነባቸውን ብር 32000 እና በተራ ቁጥር 4 የተወሰነባቸው 20,700 በድምሩ ብር 52,700(*ሀምሳ ሁለት ሺ.ህ ሰባት መቶ ብር*) ብቻ ነው ብለናል፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52595

ታህሳስ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ነገረ ፈጅ መና ህብስቱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ ሻሎም ተስፋዬ
2 ርግዓእት ገብረእየሱስ
3. ብርቱካን ገብረእየሱስ
4. ራዓዋ ገብረእየሱስ

} አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የክርክሩ መሠታዊ ጉዳይ አመልካች እንደስላሴ ከተማ ቀበሌ 02 ህንፃ ሠርቶ እንዲያስረክበው በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳች ለነበሩት አቶ አዲሱ አብርሀ በህንፃ ሥራ ውል ሠጥቷል፡፡ በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አዲስ አብርሀ የአንደኛ ተጠሪን ባለቤትና ስማቸው ከሁለተኛው ተራ ቁጥር እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር የተገለፀውን ተጠሪዎች ወላጅ አባት አቶ ገብረእየሱስ አባይን ቀጥሮ ሥራ በመሥራት ላይ እያሉ አቶ ገብረእየሱስ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በግንባታ ላይ ካለው ህንፃ ላይ ወድቀው በደረሰባቸው ጉዳት ወደ ሆስፒታል ከተወሰዱ በኋላ ነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች አመልካች በግንባታ ላይ የሚገኘው ጅምር ህንፃ ባለቤት በመሆናቸው አቶ አዲሱ አብርሀ የሟች የአቶ ገብረእየሱስ አባይ ቀጣሪ በመሆናቸው በሟች መሞት ምክንያት ለደረሰብን ጉዳት ብር 154,200 /አንድ መቶ ሀምሣ አራት ሺ ሁለት መቶ ብር/ እንዲከፍሉን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ሟች ህንፃውን ለመሥራት የተዋዋለው ሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ በመሆናቸውና ከህንፃው ወድቀው ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ በኋላፊነት የሚጠየቀው የሟች አሠሪ እንጅ እኔ አይደለሁም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ አመልካችና የሟች አሠሪ በአንድነትና በነጠላ



www.chilot.me

ለጉዳቱ ሀላፊ ናቸው በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አዲሱ አብርሀና አመልካች በአንድነትና በነጠላ ለተጠሪዎች /ከሳሾች/ ብር 36,000 /ሰላሣ ስድስት ሺ ብር/ የዳኝነትና ሌሎች ወጭዎችን በቁርጥ ፍርድ ቤቱ ወስኖ ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የህንፃው ባለቤት ከውል ውጭ በሀላፊነት ሊጠይቅ የሚቻለው ህንፃው ለሚያደርሰው ጉዳት ብቻ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2077 ተደንግጓል፡፡ ህንፃው በአሠራር ጉድለት ፈርሶ ወይም የህንፃው ክፍል የሆነ ነገር ወድቆ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ከላይ በተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ መሠረት ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ይኖርብናል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሟች የኮንትራክተሩ ሠራተኛ ናቸው፡፡ ሟች ሥራ እየሠሩ እያለ ከህንፃው ላይ ወድቀው ለደረሰባቸው ጉዳት ህንፃውን ለተቋራጭ ሠጥቶ እየሠራ ያለው አመልካች በኃላፊነት የሚጠይቅበት የህግ አግባብ ሣይኖር ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት አለባችሁ ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሟች የሞተው ከህንፃው ላይ ወድቆ ነው፡፡ ሟች የወደቀው ህንፃው የተሠራበት ቶንዲኖ ብረት በመታጠፉ ምክንያት ነው፡፡ አመልካች በውሣኔው መሠረት ድርሻውን ከፍሏል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በሟች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሟች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ለሞት የተዳረጉት የአመልካችን ህንፃ የሥራ ተቋራጭ ሆኖ የሚሠራው የሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ ሆነው ህንፃውን እየሰሩ እያሉ ከህንፃው ላይ ወድቀው ነው፡፡ የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ሟች ህንፃውን ከሚሰራው ኮንትራክተር ጋር በነበራቸው ውል መሠረት ህንፃውን ሲሰሩ ወድቀው ለደረሰባቸው የሞት አደጋ አመልካች ኃላፊ የሚሆነው በየትኛው የሕግ ድንጋጌ መሠረት እንደሆነ አልጠቀሱም በአመልካችና በሟች መካከል የውል ግንኙነት የሌለ በመሆኑ አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ የሚሆነው ከውል ውጭ በሚመጣ ኃላፊነት የሕግ ድንጋጌዎች አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚደነግጉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

አመልካች እየተሠራ ያለው ጅምር ህንፃ ባለቤት መሆኑ አልተካደም፡፡ የአንድ ህንፃ ወይም ቤት ባለቤት ከውል ውጭ ኃላፊ የሚሆንበት መሠረታዊ መርህ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ይዘት "የአንድ ህንፃ ባለሀብት ወይም ለይዞታ ሕንፃው ሊደርስ ይችላል ተብሎ ያልታሰበ ድንገተኛ ነገር ቢደርስም ይኸ ህንፃ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ ነው" የሚል ነው፡፡ ሟች በመገንባት ያለው ህንፃ በመፍረሱ ወይም የህንፃው አንድ ክፍል በመደርመሱ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው የሞት አደጋ ያጋጠማቸው ሰው አይደሉም፡፡ ሟችን የሞት አደጋ ያጋጠማቸው ህንፃውን የሚሠራው ኮንትራክተር ሠራተኛ ሆነው ህንፃውን በመሥራት ላይ እያሉ ከህንፃው ላይ



www.chilot.me

በመውደቃቸው ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ አይደለም፡፡

ሟች አመልካች የሚያሠራውን ህንፃ በውል የመሥራት ግዴታ ካለበት የሥራ ተቋራጭ ጋር ባላቸው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በሥራ ላይ እያሉ ወድቀው የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡ ይኸም በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ስለሚሰጡ ክፍያዎች በሚለው በምዕራፍ ሶስት ሥር የሚሸፈንና የሚተዳደር እንጅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሚወድቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በሟች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሀላፊ ስለሆነ ለተጠሪዎች ካሣ መክፈል አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልል የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ካሣ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57904

ታህሣስ 15 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች:-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነገረ ፈጅ አቶ አያሌው አለማየሁ - ቀረቡ

**ተጠሪ:-** አቶ ወልዱ ገብረሥላሴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ የጉዳት ካሣ ጥያቄ ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሦስተኛው ተከሣሽ የነበሩት አቶ ሣህለ ሀብተማርያም በተቋራጭነት የሚሠሩትን በስር የሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩትን የአቶ ታከለ ገብሬ ባለሁለት ፎቅ ህንፃ በመሥራት ላይ እያሉ በሚሠሩበት ቦታ የሚያልፈው ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር አደጋ አድርሶባቸዋል፡፡ በአደጋው ምክንያት ሁለት እጆቻቸው መቆረጡና ሁለት ጭናቸው ላይ ጉዳት መድረሱ በየካቲት 12 ሆስፒታል የሀኪሞች ቦርድ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በአደጋ በደረሰባቸው ጉዳት 100% /አንድ መቶ ፐርሰንት/ የመሥራት ችሎታቸውን እንዳጡ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

አመልካች በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ካሣ እንዲከፍሏቸው አመልካችን በአንደኛ ተከሳሽነት የቤቱን ባለሀብት አቶ ታከለ ገብሬን በሁለተኛ ተከሣሽነት አሠሪያቸውን አቶ ሣህለ ሀብተማርያምን በሦስተኛ ተከሳሽነት ከሰዋል፡፡ አመልካችና ሌሎቹ ተከሣሾች በኃላፊነት አንጠየቅም የሚሉባቸውን ምክንያቶች በማንሣት ተከራክረዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በደረሰው አደጋ በኃላፊነት መጠየቅ ያለበት አንደኛ ተከሣሽ/አመልካች/ ነው በማለት ተጠሪ ለዘጠኝ ዓመት /ወደፊት/ የሚያገኘው ገቢ በቀን 50 ብር /ሀምሣ ብር/ እና በዓመት ውስጥ 200 /ሁለት መቶ/ የሥራ ቀናት የሚያገኘውን የተቋረጠበትን ገቢ ብር 50 × 200 ቀናት × 9 ዓመት አስልቶ 90,000 /ዘጠና ሺህ ብር/ የሞራል ካሣ ብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ በድሩ 91,000 /ዘጠና አንድ ሺህ ብር/ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በዓመት ሁለት መቶ ቀን ብቻ ይሠራል በሚል ሒሳብ ካሣው መሠላቱ ተገቢ አይደለም በማለት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ይግባኝ አጣምሮ በማየት ለአደጋው አመልካች ብቻ ኃላፊ መባሉ ተገቢ አይደለም። በስር ፍርድ ቤት ሦስተኛ ተከሣሽ በይግባኝ ሦስተኛ መልስ ሰጭ የነበሩት የአመልካች አሠሪ አቶ ሣህለ ሀብተማርያም ለደረሰው ጉዳት ከአመልካች ጋር ኃላፊነት አለበት። የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በዓመት ተጠሪ 200 ቀናት ብቻ ነው የሚሠሩት ማለቱ ተገቢ አይደለም። ተጠሪ በዓመት ውስጥ 300 ቀን መሥራት ይችላል። በማለት የ300 ቀናት በቀን 50 /ሀምሣ ብር/ ሒሣብ የዘጠኝ ዓመት ብር 112,500 /አንድ መቶ አሥራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ እና የሞራል ካሣ ብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 113,500 /አንድ መቶ አሥራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር/ አመልካችና በከፍተኛው ፍ/ቤት ሦስተኛ መልስ ሰጭ የነበሩት አቶ ሣህለ ሀብተማርያም እንዲከፍሉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል።

አመልካች የኤሌክትሪክ መስመሩ ጉዳት እያደረሰ የማሠራው ህንፃ ቁመት እየጨመረ ሄዶ ወደ ኤሌክትሪክ መስመሩ በመጠጋቱና ተጠሪ ይዘውት በነበረው ፌሮ ብረት የኤሌክትሪክ መሥመሩን በመንካታቸው ነው። ተጠሪ መስመሩ ካልተነሣ ሥራውን ማቆም ይገባቸው ነበር። ስለዚህ ለደረሰው ጉዳት የህንፃው ባለቤትና የተጠሪ አሠሪ እንጂ እኛ ኃላፊ መባላችን መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል። ተጠሪ በበኩላቸው በማናቸውም መንገድ ወይም ህዝብ በብዛት በሚገኝበት ሥፍራ የሚዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር የአደጋ መከላከያ ሊኖራቸው እንደሚገባ በኤሌክትሪክ ደንብ ቁጥር 49/91 አንቀጽ 35 እና አንቀጽ 41 ተደንግጓል። አመልካች ይህን ኃላፊቱን በአግባቡ አልተወጣም ስለዚህ በወቅቱ ለደረሰው ጉዳት የመካስ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል። መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ተጠሪ ይህንን ሥራ በሚሠሩበት ወቅት በአካባቢው በሚያልፈው የኤሌክትሪክ መስመር በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ሁለት እጆቻቸው የተቆረጡ መሆኑ ተረጋግጧል። አመልካች በሰበር ደረጃ አደጋው የደረሰው ተጠሪ ከፍተኛ መስመር ይተላለፍበት የነበረውን የኤሌክትሪክ መስመር በፌሮ ብረት ስለነካ ነው። ጥፋቱ የተጠሪ በመሆኑ ኃላፊ ልንሆን አይገባም በማለት በሰበር አቤቱታው ገልጿል። ሆኖም ይህ አመልካች በሰበር ያቀረበው ክርክር ለስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ የፍሬ ጉዳይ መከራከሪያና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329/1/ የሚቃረን በመሆኑ ሥርዓቱን ጠብቆ የቀረበ መከራከሪያ ሆኖ አላገኘነውም። ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በወቅቱ አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና በከፍተኛ ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በስር ፍ/ቤት ማስረጃ የማቅረብና ክርክሩን የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ ሳይወጣ በሰበር ያቀረበው ክርክር ለሰበር ችሎት በህገመንግሥቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ያላስገባና ህጋዊ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል።

አንድ ሰው የሚፈነዱ ወይም መርዝ የሚሆኑ ቅመማት ሥራ ላይ በማዋል ወይም በማከማቸት ወይም ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት ወይም መሬትን የተፈጥሮ መልክ በመለወጥ ወይም በተለይ አደገኛ የሆነ የኢንዱስትሪ ሥራ በማካሄድ ይህ ሥራው በሌላው ሰው ላይ አደጋ ያደረሰ እንደሆነ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069/1/ የሚደነግግ ሲሆን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ተግባራትን በመፈፀም በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰው መንግሥትም ቢሆን ወይም ሥራውን እንዲሠራ በባለሥልጣን የተፈቀደለት መሥሪያ ቤት ቢሆንም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ደንብ ተፈፃሚ የሚሆን መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች ከላይ በተገለፁት የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ለደረሰው ጉዳት የኤሌክትሪክ መስመሩ ባለሀብት በመሆኑ ብቻ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች በጉዳቱ ካደረሰው ጉዳት በኃላፊት የማይጠይቀው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2086 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገው መሠረት ጉዳቱ የደረሰው በሙሉ ወይም በከፊል በተበዳዩ ጥፋት መሆኑን በማስረጃ በማስረዳትና በማረጋገጥ ነው፡፡ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ አለመሆኑን ለማስረዳትም በመጀመሪያ የኤሌክትሪክ መሥመሩን የሚንስትሮች ምክር ቤት ስለ ኤሌክትሪክ ሥራዎች ባወጣው ደንብ ቁጥር 49/1991 አንቀጽ 35 ስለ ኤሌክትሪክ መስመሮችና መሣሪያዎች ደህንነት የደነገገውን በሚያሟላ ሁኔታ ተዘርግቶ የነበረ መሆኑንና በዚሁ ደንብ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በስር ሁለተኛ ተከሣሽ በነበረው ግቢ ከምድር በላይ ዘርግቶት የነበረው መስመር የአደጋ መከላከያ ፕላስቲክ ተሸፍኖ የነበረ መሆኑንና ተጠሪ ጥፋት የሆነ አደጋ የሚያስከትል ተግባር በመፈፀሙ ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234/1/ እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 223 መሠረት ከመከላከያ መልስ ጋር ዘርዝሮ በማቅረብና የሠነድ ማስረጃዎቹን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 339/1/ በሚደነግገው መሠረት በማቅረብ የማስረዳት ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከላይ በተገለፀው መሠረት አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤትና ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔና ለጉዳቱ የወሰነው የካሣ መጠን መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ይህ ፍርድ ቤት ሐምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58920

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አለምነው አበበ አካሌ - ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ህብረት ኢንሹራንስ አ/ማ - ቃልኪዳን ንጉሴ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በመኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት መነሻ በማድረግ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ በወቅቱ ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ አመልካችን የከሰሰው የመድን ዋስትና በገባለት የደንበኛው መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት ነው፡፡ አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የሥረ ነገር ክርክር አቅርቦአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኂላ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎአል በዚህ መሠረትም አመልካች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል የወጣውን ወጪ ብር 5,500 ከእነ ሕጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ክርክሩ ሊነሣ የቻለው አመልካች በተጠሪ የመድን ዋስትና የተገባለትን መኪና በመግጨት ጉዳት አድርሶአል በመባሉ ነው፡፡ ገጭቶ ጉዳት ያደረሰው መኪና የአመልካች ንብረት ከመሆኑም በላይ ሲሽከረከር የነበረውም በራሱ ማለትም በአመልካቹ እንደሆነ አላከራከረም፡፡ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች የይርጋ መቃወሚያ ያነሣው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2143/1/ የተቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ክሱን የሰማው

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃሚያው ሣይቀበል የቀረው ለይርጋው መቃወሚያ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በንዑስ ቁ./1/የተመለከተው ሣይሆን፣ በንኡስ ቁ. /2/ ያለው ነው በማለት ነው፡፡ ጊዜው ከዚህ ድንጋጌ አንፃር እየታየ ሲሰላም የክስ ማቅረቢያ ጊዜው አልፎአል ሊባል አይችልም እሚል መደምደሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ደርሶአል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው አቤቱታ የይርጋ መቃወሚያውን በሚመለከት ያነሣው ዋነኛ የመከራከሪያ ነጥብ በወንጀል ተከስሼ አልተቀጣሁም፡፡ ስለዚህም በንኡስ ቁ. /2/ የተመለከተው ድንጋጌ ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት ሊደርስ የቻለው በአመልካች ጥፋት አይደለም የሚል በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ይልቁንም ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ጥፋት ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሶአል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ነው ከተባለ ደግሞ ድርጊቱ በወንጀልም የሚያስከስስ /የሚያስቀጣ/ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ድርጊቱ /ጉዳቱ/ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት በወንጀል ሕጉ በተደነገገው መሠረት እንደሚሆን ከላይ በተመለከተው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2143/2/ ተደንግጎአል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ደግሞ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑ ከሚታይ በቀር የድርጊቱ ፈፃሚ ተከሶ መቀጣት እግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም በወንጀል አልተከሰስኩም ወይም አልተቀጣሁም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት ያለው አይደለም በመጨረሻም የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረጋቸው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 158634 ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 94803 ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡን ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ53598

ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ይልማ ደጀኔ - ጠበቃ አቶ ስሜነህ ተክሉ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መዲና ዲታም - ጠበቃ አቶ ዘካሪያስ ምንተስኖት - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክራዋል፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው ተከሣሹ /አመልካች/ የሻንሲ ቁጥር 8991 የሆነ ተሣቢ መኪና በውል ገዝተን ነበር፡፡ ተከሣሽ የገዛውን የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነ ተሣቢ መኪና ዴክላራሲዮን ትክክለኛነት አረጋግጣለሁ በማለት የሌሎች ተሣቢ መኪኖች ማለትም የሻንሲ ቁጥሩ 8951 እና የሻንሲ ቁጥሩ 8793 ተሣቢ መኪና ዴክላራሲዮን ከከሣሽ ወስዷል፡፡ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል ቀሪ ሆኖ ተከሣሽ በቅድሚያ ክፍያነት የከፈለውን ብር 50,000 /ሀምሣ ሺ ብር/ ከከሣሽ ተቀብሎ ወስዷል፡፡ ተከሣሽ የሶስቱን ተሣቢ መኪኖች ዲክላራሲዮን እንዲመልስ ቢጠየቅ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ተከሣሽ የተሣቢ መኪኖቹን ዴክላራሲዮን ባለመመለሱ ከሣሽ በተሣቢ መኪኖቹ ሰርተው የሚያገኙት ገቢና ጥቅም ቀርቶባቸዋል፡፡ መኪኖቹ ከቆሙበት ከሐምሌ 22 ቀን 1999 ዓ.ም ክስ እስከ ቀረበበት ጥር 6 ቀን 2000 ዓ.ም የአንድ ተሣቢ የወር ገቢ ብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ የሶስቱ ተሣቢ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺ ብር/ ሂሣብ የአራት ወር ከሃያሰባት ቀን ብር 147,000 /አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺ ብር/ እና መኪኖቹን ለማስጠበቅ የወጣ ብር 22,500 /ሃያ ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 169 500 /አንድ መቶ ስልሣ ዘጠኝ ሺ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ የአሁን አመልካች በተከሣሽነት ቀርበው የሻንሲ ቁጥር 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል ቀሪ አልሆነም፡፡ ተከሣሽ ከከሣሽ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺ ብር/ የወሰድኩት የመኪናው ቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ተመልሶልኝ ሣይሆን ከከሣሽ ጋር ባለኝ የግል ግንኙነት የሰጡኝ ነው፡፡ እኔ የተቀበልኩት የተሣቢ መኪና ዲክላራሲዮን የለም፡፡ ለክስ ሀላፊነት የለብኝም፡፡ አንድ ተሣቢ መኪና በወር ብር



www.chilot.me

10,000 /አስር ሺ. ብር/ ገቢ አያስገኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል አልፈረሰም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ተከሣሽ የሻንሲ ቁጥሩ 8951 እና 8993 የሆኑትን ተሣቢዎችና የገዛውን ተሣቢዎች ዴክራላሲዮን ይዞ ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከሣሽ በመኪናዎቹ ሊያገኙ ይችሉት የነበረው ጥቅም ቀርቶባቸዋል፡፡ ጉምሩክና የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን በሰጠው መረጃ መሠረት የሁለቱ ተሣቢ መኪናዎች የቀረ ገቢ ብር 99,290.80 /ዘጠና ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ብር ከሰማኒያ ሣንቲም/ ለተሣቢ መኪኖቹ ማስጠበቂያ የወጣ ብር 12,800 /አስራ ሁለት ሺ ስምንት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 112090.80 /አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺ ዘጠና ብር ከሰማኒያ ሣንቲም/ ከነ ወለዱ ተከሣሽ ለከሣሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን ተሣቢ መኪና አመልካች ለመግዛት ያደረገው ውል ፈራሽ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ በይግባኝ ይታይልኝ፡፡ የሁለቱ ተሣቢ መኪኖች የቀረ ገቢ የአንደኛው በወር ብር 10,000 /አስር ሺ ብር/ የሁለቱ ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረብኩትን ማስረጃ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገብኝ አሳግባብ ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሶስት ተሣቢ መኪና ዴክላራሲዮን ወስደሀል በዚህም ጉዳት አድርሰሀል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በሚል መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ ላይ አመልካች የሰጡትን መልስና ክርክር ከተቀበለና አመልካች ባቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ ላይ ግራቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኂላ የአመልካችን መስቀለኛ ይግባኝ የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውድቅ አድርጐታል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪን ይግባኝ ክርክር በመቀበል የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ሽያጭ ውል እንዳይፈጸም ችግር የፈጠረው የአሁን አመልካች መሆኑን ከዘረዘረ በኂላ ተጠሪና አመልካች የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን ተሣቢ በተመለከተ ያደረጉት የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሉ ፈራሽ አይደለም በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሻንሲ ቁጥራቸው 8951 እና 8793 ከሆኑ ሁለት ተሣቢዎች የቀረ ገቢ የአንዱ በወር ብር 10,000 የሁለቱ ተሣቢ ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ ሂሣብ መያዝ ይገባዋል በማለት አመልካች ከሐምሌ 22 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ በይግባኝ ውሣኔ እስከተሰጠበት ታህሣስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም ታስቦ ብር 480,000 /አራት መቶ ሰማኒያ ሺ ብር/ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የካሣ ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ዴክላራሲዮን ወስዷል ተብሎ ጥፋተኛ መባሉና ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ የተሣቢ መኪና ሽያጭ ውሉ አፈጻጸም ጋር ለማቀላጠፍ አመልካች የሰራውን ስራ የሚያሣይና ሰነድ መስጠት የተጠሪ ግዴታ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል ተጠሪ በበኩላቸው ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሣቢዎቹ የወር ገቢን በተመለከተ ከግል የትራንስፖርት ድርጅት የተሰጠውን መረጃ መሠረት በማድረግ መወሰኑና የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን መረጃ ተቀባይነት የለውም በማለት መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውንና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት በመጀመሪያ አመልካች የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን ተሣቢ መኪና ከተጠሪ ለመግዛት የተዋዋልኩት ውል እንዲፈርስ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት የለውም በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን መኪና ተጠሪ ለአመልካች ለመሸጥ የተዋዋሉት ውል ፈራሽ አልሆነም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በግልጽ ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡

ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪና አመልካች የሻንሲ ቁጥሩን 8991 የሆነ ተሣቢ መኪናን በተመለከተ ያደረጉት የሽያጭ ውል አመልካች አፈጻጸሙን አስቸጋሪና ከባድ ያደረገው በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል ሊጸናና ህጋዊ ውጤት ሊኖረው ይገባል ወይስ ፈራሽ ሊሆን ይገባል የሚለውን ጭብጥ ማዕከል በማድረግ አመልካችና ተጠሪን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡ ይኸውም በመሆኑ አመልካች የተሣቢ መኪናውን ሽያጭ ውል በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ የሚገባቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ይህንን የይግባኝ ስርዓት ሣይጨርሱ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ብሎ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በሰበር እንዲታይላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ጉዳዩን አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የመስጠት ስልጣን ባለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ ያልታየና የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3 /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተደነገገውን መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ በሰበር ችሎት ቀርቦ ለመታየት የሚችል ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው በውል ያልገቧቸውንና የመኪናዎቹን ዴክላራሲዮን ይዞ ለመቆየት የሚያስችላቸው ከውል ወይም ከህግ የመነጨ መብት ሣይኖራቸው ንብረታቸው የተጠሪ የሆኑ ሁለት ተሣቢዎች ዴክላራሲዮን ይዞ ቆይቷል፡፡ አመልካች የሻንሲ ቁጥራቸው 8793 እና 8951 የሆኑ ተሣቢ መኪኖች አላግባብ በመያዙና ለተጠሪ ለመመልስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጥፋት በሆነ ድርጊት ተጠሪ ሁለቱን መኪኖች አስፈላጊ ፎርማሊቲ በማሟላት ወደ ስራ አሰማርተው ሊያገኙ የነበረው ጥቅም እንዲቀር ምክንያት ሆኗል ተብለው ነው፡፡ አመልካች ዴክላሲዮኖቹን አላግባብ በመያዝ ጥፋት ስለመፈጸማቸውና በዚህ ምክንያት ተጠሪ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው



www.chilot.me

ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ለጉዳቱ አላግባብ ሀላፊ ተብያለሁ በማለት ያቀረቡትን የሰበር ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ለተጠሪ መክፈል የሚገባውን የካሣ መጠን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የካሣ ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በማሻሻል ውሣኔ የሰጠውን የካሣ ውሣኔ በተመለከተ ይግባኝ ስለሚቀርብበትና ተቀባይነት ስለሚያገኝበት ሁኔታ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ መሆኑ ወይም አለመሆኑ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ሁለት መኪናዎች ወደ ስራ ቢሰማሩ ያስገኙ የነበሩትን የገቢ መጠን ከመወሰኑ በፊት ተሣቢ መኪናዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በስራ ተስማርተውና ገቢ አስገኝተው የማያውቁ በመሆኑ የካሣውን መጠን ተሣቢዎቹ ሰርተው ወይም ተከራይተው ያስገኙትን ገቢ ለመወሰን የማይቻል መሆኑ የካሣው መጠን አወሣሰን ላይ ችግር የፈጠረ መሆኑን በውሣኔው ገልጿል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተሣቢ መኪናዎቹ ሰርተው ወይም ተከራይተው የሚያስገኙት ገቢ በማይታወቅበት ሁኔታ የሻንሲ ቁጥራቸው 8951 እና 8793 የሆኑት ተሣቢ መኪኖች የተመረቱበትን ዘመንና የመሸከም አቅማቸው ተመሣሣይ የሆኑ ተሣቢ መኪኖች አማካኝ አመታዊ ገቢ ምን ያህል እንደሆነ የኢትዮጵያ ጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ መረጃ ማግኘቱ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት መረጃው እንዲላክለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ጉምሩክና ገቢዎች ባለስልጣን በስር ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከተመረተ /ከተፈበረከ/ አስራ አምስት ዓመት ያልሞላው ተሣቢ አማካኝ አመታዊ ገቢ በ 36,888 /ሰላሣ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር/ እንደሆነና ከተመረተ /ከተፈበረከ/ ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሆነው ተሣቢ መኪና ገቢ 31,355 /ሰላሣ አንድ ሺ ሶስት መቶ ሀምሣ አምስት/ መሆኑን በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ተሣቢ መኪኖች ከተመረቱ አስራ ስምንት ዓመት በላይ የሆናቸው ለመሆኑ የጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን የሰጠውን ማረጋገጫ መሠረት በማድረግ አመልካች ለተጠሪ መክፈል ያለበትን የካሣ መጠን ወስኗል፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሀላፊ የሆነው ከውል ውጭ ጥፋት በሆነ ድርጊት የሁለቱን መኪናዎች ዴክላራሲዮን አላግባብ ይዞ አልመልስም በማለቱ ምክንያት ነው፡፡ ከውል ወጭ ሀላፊ የሆነ ሰው ለተጉጂው የሚከፍለው የካሣ መጠን በመርህ ደረጃ ይግባኝ የማይቀርብበት እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 ስለኪሣራ ጥቅም አከፋፈል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች የተወሰነ ፍርድ ላይ ለበላይ ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ማለት አይቻልም በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የካሣ ውሣኔ በሰጠው ፍርድ ቤት ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚፈቀደው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ልዩና የተጠበቁ ሁኔታዎች ሲኖሩ ነው፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 የተደነገጉት ልዩና የተጠበቁ ሁኔታዎች ሶስት ሲሆኑ እነርሱም፡-

/ሀ/ ዳኞች ሊገምቱት የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ አላግባብ በመያዝ ውሣኔ ሰጥተው እንደሆነ ወይም ሊገምቱት የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ ትተው ያላግባብ የሆነውን አገማመት መንገድ ይዘው የተገኙ እንደሆነ

/ለ/ በዳኞች የተወሰነው የኪሣራ ገንዘብ ልክ በግልጽ ከአእምሮ ግምት ውጭ የሆነና የተወሰነውም በማዳላት ወይም በዝንባሌ መሆኑ እርግጥ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ



www.chilot.me

/ሐ/ በዳኞች የተወሰነው የጉዳት ካሣ በሒሣብ መሣሣት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን አጣርቶ የላከለትን ዓመታዊ አማካኝ ገቢ መሠረት በማድረግና ተሣቢዎቹ ወደ ስራ ተሰማርተው የማያውቁና ለካሣ ውሣኔ መነሻ የሚሆን እርግጥኛ ገቢ የሌላቸው መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የወሰነው የኪሣራ /የካሣ ውሣኔ/ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 ከተደነገገው በተለየ ሁኔታ በይግባኝ ሊታይ የሚችልበት ልዩ ምክንያትና ሁኔታ ያለ መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ድንጋጌዎች አንጻር የሰጠው ምክንያትና ትንታኔ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የወሰነው የካሣ ውሣኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ከተደነገጉትና ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት የሚያስችሉ ልዩ ሁኔታዎች የትኛውን ድንጋጌ የስር ፍርድ ቤት እንደተላለፈ ሣይገጽና ሣያረጋግጥ የካሣውን መጠን በይግባኝ አይቶ ማሻሻሉ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 መሠረታዊ መርህ የሚጥስና ህግ አውጭው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 በመደንገግ ሊያሣካ የሚፈልገውን መሠረታዊ ግብና ዓላማ የማያሣካ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ሁለት ተሣቢዎች ወደ ስራ ተሰማርተው ገቢ አስገኝተው የማያውቁ ከተመረቱ ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሆናቸው በተጠሪ ተሣቢ መኪኖች የመሸከም አቅምና እድሜ የሚገኙ ተሣቢዎች በአመት የሚያስገኙት የተጣራ ገቢ ብር 31,355 /ሰላሣ አንድ ሺ ሶስት መቶ አምሣ አምስት ብር መሆኑን የኢትዮጵያ ጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን አጣርቶ የሰጠውን ማስረጃ መነሻ በማድረግ በመሆኑ በጉዳዩ ሊገመቱ የሚገባቸውን የነገሩን አካባቢ ሁኔታዎች በአግባቡ በመያዝና ትክክለኛውን መንገድ በመከተል የካሣ መጠኑን ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ያሣያል፡፡

በሌላ በኩል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጣራ ሁለት ተሣቢ መኪኖች የተመረቱበትን ዘመን የመኪኖቹን ጭነት የመሸከም አቅምና መኪኖቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ሰርተው የማያውቁ በመሆኑ መኪኖቹ ሊያስገኙት የሚችሉትን እርግጠኛ ገቢ ለመወሰን ችግር እንዲፈጠር ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ የኢትዮጵያ ጉምሩክና ገቢዎች ባለስልጣን የላከውን መረጃ ያለ በቂ ምክንያት ውድቅ በማድረግ የግል የትራንስፖርት ድርጅት የጻፈውን አስተያየት ብቻ መነሻ በማድረግ አንድ ተሣቢ በወር ብር 10,000 /አስር ሺ ብር/ የተጣራ ገቢ ያስገኛል፤ ሁለቱ ተሣቢዎች በወር ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ የተጣራ ገቢ ያስገኛሉ በማለት የስር ፍርድ ቤት የወሰነውን የካሣ መጠን በመሻሻል አመልካች ለተጠሪ ብር 480,000/ አራት መቶ ሰማኒያ  ሺህ ብር/ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች የተደነገጉት ልዩና የተጠበቁ ጉድለቶች የሚታዩበትና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ከጅምሩ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የካሣ መጠን በይግባኝ ለማየትና ለማሻሻል የሚያስችሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 የተደነገጉ ጉድለቶች ያሉበት መሆኑን ሣያረጋግጥ ጉዳዩን በይግባኝ በማየትና የኢትዮጵያ ጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን አጣርቶ የላከውን መረጃ ወደ ጐን በመተው የግል የትራንስፖርት ድርጅት የተጻፈውን አስተያየት መሠረት በማድረግ የካሣውን መጠን መወሰን ነበረበት በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔን በማሻሻል የሰጠው የካሣ ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አመልካት ተጠሪ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና በተመለከተ ያደረጉት የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 መሠረት በይግባኝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሣይታይና ሣይወሰን በሰበር ቀርቦ መታየት የሚችል ባለመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡
2. የሻንሲ ቁጥራቸው 8951 እና 8793 የሆኑ ተሣቢ መኪኖች በአመልካች ጥፋት ምክንያት ባለመስራታቸው አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባዋል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ጉዳዩን አይቶና አሻሽሎ የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 የሚጥስ ሆኖ በመገኘቱ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 112090.80 /አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺ ዘጠና ስምንት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንተናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 44427

መጋቢት 09 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** አቶ ለገሠ ጥቀሄር - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር - ነ/ፈጅ ጌታሁን ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካች የተጠሪ ባንክ አ/ማህበር ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በማለፍ በፈፀመው ተግባር ምክንያት በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ያለበት ኃላፊነት ምንድን ነው? የሚለውን ግራቀኙ ባሉበት አከራክሮ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች የተጠሪ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ እያገለገሉ በነበሩበት ጊዜ ከተሰጣቸው ሥልጣን በላይ በማለፍ ስርዎት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ለተባለ ድርጅት ብር 2,899,984.25 (ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ከ25/100) የሆነ የብድር ገንዘብ ያለምንም ዋስትና ብድር እንዲፈቀድለት በወሰኑት መሠረት ይኸው የብድር ገንዘብ ለተበዳሪው መለቀቁንና ተበዳሪውም በገባው ግዴታ መሠረት በብድር የወሰደውን ገንዘብ ሊመልስ አለመቻሉ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን፤ ይህም ከሥልጣኑ በላይ በማለፉ ብድር እንዲለቀቅ የሚያደርግ ውሣኔ የመስጠት ተግባር ባንኩ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ መልሶ ለመሰብሰብ ያላስቻለውና በዚህም ሳቢያ ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑም አላከራከረም፡፡ ይህንኑ በብድር የተሰጠውን ገንዘብ በሙሉም ሆነ በከፊል ተጠሪ ሰብስቧል የሚል ክርክርም አልቀረበም፡፡

አመልካች የተጠሪ ባንክ የሥራ ኃላፊ መሆኑ፤ የሥራ ኃላፊነቱን ሲያከናውን በተሰጠው ሥልጣን ክልል ውስጥ መሆን እንደሚገባው ከባንኩ የበላይ ውሳኔ ሰጭ አካል የገንዘብ ጣሪያ ተበጅቶ ኃላፊነት መረከቡን፤ ይህንኑ የሥልጣን ወሰን በመተላለፍ ተግባር ፈፅሞ በቀጣሪው ባንክ ላይ የገንዘብ ጉዳት አድርሶ መገኘቱ የተረጋገጡ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ሆነው እስከተገኙ ድረስ



www.chilot.me

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2524 እንደተመለከተው አመልካቹ በፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ተግባር ምክንያት በአሠሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አስረጂ ነው፡፡

በተጠሪ ላይ ለደረሰው የገንዘብ ጉዳትም ይህ የአመልካቹ ተግባር ቀጥተኛ መንስኤ መሆኑን ከሚያመለክት በቀር ለብድሩ አለመመለስ ምክንያት የሆነ ሌላ ጉዳይ ስለመኖሩ ሳይገለፅ፤ ሳይረጋገጥ በብድር የተሰጠው ገንዘብ ሳይመለስ መቅረቱ በዚህ በአመልካች ተግባር ምክንያት ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይደለም፤ በምክንያቱና በውጤቱ መካከል ቅርብ የሆነና በቂ ግንኙነት አለ ማለት አይቻልም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ትንታኔ ከላይ በፍሬ ነገር ረገድ ላይ የተረጋገጠውንና በጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በውል ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህም ምክንያት በተጠሪው ላይ ለደረሰው የገንዘብ ጉዳት አመልካች ኃላፊ መሆኑን ጠቅሶ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በተጠሪው ላይ የደረሰው የጉዳት ልክ ምን ያህል ነው የሚለውንም ነጥብ በተከታይ እንዳየነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2524(2) አስቦ ወይም በቸልተኝነት ወይም ባለመጠንቀቅ በአሠሪው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሠራተኛው ኃላፊ መሆኑ ከታወቀ በአሰሪው ላይ የደረሰውን ጉዳት አስልቶ እንዲከስ ለማድረግ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ መሠረት ልናደርግ ይገባል ይህ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ተገቢ ያልሆነው የአመልካች ተግባር የተፈፀመውና ጉዳቱ የደረሰው አመልካችና ተጠሪ ካደረጉት የቅጥር ውል የመነጨ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1676(1) እንደተመለከተው የግራ ቀኙን ውል በሚገባው ልዩ የውል ደንብ ውስጥ ደረሰ የሚባለውን የጉዳት ዓይነትና መጠን የሚያመለክት ዝርዝር ህግ ካልተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1790(2) እና 2090 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት የጉዳት ልክ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ከዚህም አንፃር ይህንን ጉዳይ ስንመለከተው አመልካች ከሥልጣኑ በላይ በፈፀመው ተግባር ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት የገንዘብ ሲሆን መጠኑም የብድር ገንዘቡ በአግባቡ ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ ባንኩ ማስመለስ ይቻል የነበረው ነገር ግን ሳይመለስ የቀረው እንጂ ከዚህ ያነሰ ወይም የበዛ ሆኖ አይታይም በዚህ ሁሉ ምክንያት የግራ ቀኙን ጉዳይ በይግባኝ ተመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የኃላፊነቱን እና የጉዳት መጠኑን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም በኢትዮጵያ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት አንድ የመጨረሻ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታረም የሚችለው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ መሆኑን በማየት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 37856 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር ክርክር ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ ስላላገኘነው ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
   በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጭና ኪሣራ ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ራ/ታ

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59698

መጋቢት 6 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገብረ ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሚኪያስ ከበደ ከጠበቃ ገ/ክርስቶስ ኪዳነ ማርያም ጋር - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ ምስራቅ ንጉሴ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ አልማዝ ገብረብርሀን } ጠበቃ ተስፋዬ ደጉ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር የቀረበ በመሆኑ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች አመልካች ከአቶ ከበደ ታዬ ጋር በመሆን እያንዳንዳችን አምስት አምስት ሰው በኮንደሚኒየም ቤት እንዲያገኙ እድል የተሰጣቸው መሆኑን በመግለፅ አንደኛ ተጠሪ /አንደኛ ከሣሽ/ ከዘጠኝ ዘመዶቼ ሰብስቤ የሰጠሁትን ብር 185,000/አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ብር/ ሁለተኛ ተጠሪ /ሁለተኛ ከሣሽ/ ከዘመድ ሰብስበው የሰጡትን ብር 210,000/ሁለት መቶ አስር ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 395,000 /ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር / ወስደዋል፡፡ ስለሆነም በማታለልና በማጭበርበር የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካችና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት አቶ ከበደ ታዬ ተጠሪዎች / ከሣሾች/ ክስ ያቀረቡባቸው በይሆናል እና በግምት ነው ማስረጃ የላቸውም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን ምስክሮችና በአመልካችና በአቶ ከበደ ታዬ ላይ የተጀመረውን የፖሊስ የወንጀል ምርመራ መዝገብ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካች ብር 395,000 /ሶስት መቶ ዘጠኛ አምስት ሺህ ብር / የወሰደ መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በመግልፅ አመልካች ለተጠሪዎች ብር 395,000/ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር/ እንዲመልስና አቶ ከበደ ታዬ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 130,000 አቶ ከበደ ታዬ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካችን በተመለከተ የተሰጠው ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡



www.chilot.me

አመልካች ነሐሴ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች ገንዘብ ለእኔ የሰጡ መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ ሳላቀረቡም ፍርድ ቤቱ ለፖሊስ የተሰጠን ቃል አላግባብ በማስረጃነት በመጠቀምና በፖሊስ ተፅዕኖ የደረሰብኝ መሆኑን ለማስረዳት እየጠየቅሁ እያለሁ አላግባብ ብር 395,000 ለተጠሪዎች እንድመልስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ኮንደሚኒየም ቤት አሰጣችኋለሁ በማለት የማታለል ክስ ያቀረብንበትን ገንዘብ የወሰደ መሆኑን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ አመልካችም ለፖሊስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/1/ በሰጠው የተከሣሽነት ቃል ብቻ ሣይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 ለፍርድ ቤት በሰጠው የእምነት ቃል አረጋግጧል፡፡ ይኸ ማስረጃ በፍታብሔር ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በሥር ያላነሳውን አዲስ ክርክር በማቅረብ ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

አመልካች ታህሣሥ 20 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ የጠቀሱትን ገንዘብ ለተጠሪዎች እንዲመለስ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለዉ ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ የሆኑት አቶ ከበደ ታዬ፣ ቤቱ ለልማትና ኢንቨስትመንት የፈረሰበት ሰው ዘጠኝ ዘጠኝ ሰው ኮንደሚኒየም ቤት እንዲያገኝ ማድረግ እንደሚችል በመንግስት ውሣኔ የሰጠበት በመሆኑ ገንዘብ አሰባስባችሁ አምጡ በማለት ከአንደኛ ተጠሪ ብር 185,000 ከሁለተኛ ተጠሪ ብር 210,000 የራሳቸውን ድርሻና ከዘመድ ያሰባሰቡትን ከወሰዱ በኋላ ሌሎችን ሰዎች በመቁጠር የተወሰነውን ገንዘብ የመለሱ መሆኑንና ብር 395,000 የሚፈለግባቸው መሆኑን የሚያስረዱ የሰው ምስክሮች አቅርበዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች ገንዘቡን ለእኔ የሰጡ መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ ሳላቀረቡም የበታች ፍርድ ቤቶች በህግ በኩል ተቀባይነት የሌለውን የሰው ምስክር በመስማት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ ለደከመው ሰው የመመለስና የመካስ ግዴታ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 በመሠረታዊ መርህነት ተደንግጓል፡፡ አመልካች የኮንደሚኒየም ቤት ታገኛላችሁ ለኮንደሚኒየም ቤት የሚከፈል ነው በማለት ከተጠሪዎች ገንዘብ በመውሰድ ያልመለሰና ያለበቂ ምክንያት በገንዘቡ የተጠቀመ መሆኑን ተጠሪዎች በምስክር አስረድተዋል፡፡ ከሣሽ ተከሣሹ በንብረቱ ወይም በገንዘቡ አላግባብ የበለፀገና የተጠቀመ መሆኑን የሰነድ ማስረጃ ብቻ በማቅረብ ማስረዳት ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ግልፅ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ የአንድ ማስረጃ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ የሚወሰነው በህግ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪዎችን በማታለል ከተጠሪዎች ገንዘብ የወሰደ መሆኑን በምስክርና በሌላ ማስረጃ እንዲያስረዱ የበታች ፍርድ ቤቶች መፍቀዳቸው ተገቢ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተቀብሎ የወሰደ መሆኑን በማታለል ወንጀል በተደረገበት ምርመራ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት ለፖሊስና ለፍርድ ቤት በማመን ቃላቸውን የሰጡ መሆኑን በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በማስረጃነት ከቀረበው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ተረጋግጧል፡፡ በማለት በሥርና በሰበር ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ለፖሊስ የሰጡት የተከሣሽነት ቃል በፖሊስ በደረሰብኝ ተፅዕኖ የተሰጠ ነው በማለት በሰበር አቤቱታቸው ከመግለፃቸው በስተቀር ከተጠሪዎች ገንዘብ ተቀብለው የወሰዱ መሆኑን በማመን ለፖሊስና ለፍርድ ቤት ቃል አልሰጠሁም በማለት በግልፅ ክደው አልተከራከሩም፡፡ አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 27 እና አንቀፅ 35 የተሰጠው የዕምነት ቃል የተጠሪዎችን ክስ ለማስረዳት የማይችልና ተገቢነት የሌለው ማስረጃ ነው በማለት ለሰበር በሰጠው የመልስ መልስ ያቀረበው ክርክር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 235/2/ መሠረት በመሸሽ መልክ የተሰጠና እንደታመነ ሊቆጠር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ገንዘቡን ከተጠሪዎች ተቀብሎ የወሰደ መሆኑ በፖሊስና በፍርድ ቤት ከሰጠው የዕምነት ቃል እንዳረጋገጠ በሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተገልፆል፡፡ አንድ ሰው ባለዕዳ መሆኑን ያመነ እንደሆነ ዕዳው የታመነለት ሰው ባለዕዳው ዕዳውን ያመነበትን ምክንያት የማስረዳት/የማረጋገጥ / ግዴታ የሌለበት መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2019 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ተቃራኒ ማስረጃ ከሌለ በስተቀር ባለዕዳው ዕዳ እንዳለበት በማመን የሰጠው የዕምነት ቃል በአእምሮ ግምት በሚገባ/ በአግባቡ / የተሰጠ ቃል ነው ተብሎ የሚቆጠር መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2019 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡

አመልካች ለፖሊስ የተከሣሽነት ቃሌን ስሰጥ ከተጠሪዎች ገንዘብ ተቀብዬ ወስጃለሁ በማለት ቃሌን የሰጠሁት ፖሊስ ባደረሰብኝ ተፅዕኖ ምክንያት ነው በማለት በሰበር አቤቱታው የገለፀ ቢሆንም ይህንን ክርክሩን የሚያስረዳ ማስረጃ ለሥር ፍርድ ቤት አላቀረበም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የተጠሪዎች ዕዳ እንዳለበት በማመን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 የሰጠው የእምነት ቃልን ለማስተባበል የሚችል ተቃራኒ ማስረጃ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2019 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት አላቀረበም፡፡ ስለሆነም አመልካች በሰበር ደረጃ ያነሣው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሣና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329/1/ን የሚጥስ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የፖሊስን የምርመራ መዝገብ በማስቀረብ በምርመራ መዝገቡ የሰጠሁት የተከሣሽ ቃል በማስረጃነት መጠቀሙ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ቅሬታ አቅርቧል፡፡ ሆኖም በፍታብሔር ጉዳይ ፖሊስ ያጣራውን የምርመራ መዝገብ አስቀርቦ እንዳያይ የሚከለክል የማስረጃ ህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በህግ ተቀባይነት የሌለውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ የበታች ፍርድ ቤቶች ወስነውብኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በማስረጃ ህግ መሠረት ተቀባይነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመቀበልና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 ፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2164 /1/ እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2019 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የሰበር ችሎት ታህሣሥ 13 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64590

ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች** ፡- ሜሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ - ጠበቃቸው አቶ ኃይልዬ ሳህለ

**ተጠሪ** ፡- ወ/ት ሠናይት ዓለማየሁ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በሰበር ተጠሪ ከሳሽነት ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ፍሬ ቃሉ በተከሳሽ ድርጅት /በሰበር አመልካች/ ምርመራ ተደርጎልኝ "ኖርፕላንት" የተባለ የወሊድ መከላከያ መደኃኒት በክንድ እንዲቀበር ከተደረገ በኃላ መድኃኒቱ ህመም ስላስከተለብኝ ተከሳሽ በራሱ የህክምና ባለሙያዎች መድኃኒቱ እንዲወጣ ሲያደርግ በባለሙያዎቹ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ባለመደረጉ የተነሣ መድኃኒቱ የተቀበረበት እጄን ለማያቋርጥ ህመምና ስቃይ የዳረገኝ ከመሆኑ ሌላ በጡትና በጀርባዬ ላይ ባስከተለው የመሸማቀቅ ህመም የተነሣ የጀርባ ህመም፣ የፊት ማበጥ እና የልብ ህመም አስከትሎብኛል፡፡ ህመሙም በመወሳሰቡ የደም ዝውውር ስርዓት ላይ ችግር በማስከተል የደም ቱቦ በመዘጋቱ እጄ እየመነመነ በመምጣት ሥራዬን መሥራት እንዳልችል በማድረጉ ህክምናውን በውጪ ሀገር እንድከታተል ሌሎች የህክምና ተቋማት ያረጋገጡልኝ ስለሆነ ተከሳሽ ላደረሰብኝ ጉዳት ሀላፊ ነው ተብሎ እንዲወሰንበትና ታይላንድ ሀገር ሄጄ ለመታከም፡-

- ለህክምና ወጪ ብቻ ብር 192,881
- ለደም ሥርዓት ማስተካከያ ቀዶ ጥገና ብር 114,699
- ለደም ምርመራ ኤክስሬይ /x-ray/ እና ላቦራቶሪ ምርመራ ብር 22,100
- ኤም.አር ምርመራ ብር 13,377
- ታይላንድ ደርሶ መልስ የአውሮኘላን ትኬት ብር 14,000
- የ10 ቀን የሆቴል ወጪ ብር 6,500
- ለ10 ቀን የሆስፒታል አልጋ ወጪ ብር 159,949
- ለህክምና ተጨማሪ ወጪ መጠባበቂያ ብር 100,000
- ታይላንድ ባንኮክ የታክሲ፣ የፖስፖርት እና ሌላ ወጪ ብር 13,400
- ለአስታማሚ ትራንስፖርት ሆቴል፣ የጉዞ ሠነድ ወጪ ብር 34,780

- በጉዳቱ ምክንያት ሥራ በማቆሜ ያጣሁትን ብር 632 ክስ እስከቀረበበት ሐምሌ 2001 ታስቦ ብር 22,752
- የሞራል ካሣ ብር 1,000

  በድምሩ 694,918 ብር /ስድስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት/ ተከሳሽ እንዲከፍለኝ እንዲወሰንበት የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽም በሰጠው መልስ አንድ ሀኪም ብሎም ሆስፒታል በሙሉ ሀላፊነት የሚጠየቀው የሞያ ደንብ ተጥሶ ሲገኝ ሲሆን ይኸው ደንብ ተጥሶ በመሰራቱ ምክንያት በከሳሽ ላይ ጉዳት ስለመድረሱ አላስረዳችም፣ ከሳሽ በውጪ ሀገር ለመታከም የሚያስችላትን ሰርትፍኬት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በማስረጃነት አላቀረበችም በውጪ ሀገር ህክምና ያስፈልጋታል ቢባል እንኳን የዚህ ዓይነት ህክምና በቅርብ በኬኒያ ወይም ህንድ ሀገር የሚሰጥ በመሆኑ ታይላንድ ሀገር ለመታከም የጠየቀችው ያለአግባብ ነው፡፡ ከሣሽ ለህክምና የጠየቀችው ብር 192,881 በማስረጃ ያልተረጋገጠ ከመሆኑ ሌላ ለምርመራ በማለት ልዩ ልዩ ወጪዎችን መጠየቋ ተገቢነት የለውም፣ በሆስፒታል ለ10 ቀናት እንደምትቆይ በመጥቀስ የጠየቀችው ገንዘብም ቢሆን ከ2 ቀን በላይ በሆስፒታሉ ስለማትቆይ በጣም የተጋነነ ነው ለአስታማሚ በሚል የጠየቀችውን ገንዘብ ተከሣሽ መክፈል አይገባውም ፣ የደረሰባት ጉዳት የግል ሥራዋን የሚከለክላት ስለመሆኑም ማስረጃ አላቀረበችም፣ የሞራል ካሣም ቢሆን ተከሳሽ ለከሳሽ መክፈል የለብኝም ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የመረመረው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም የከሳሽ የህክምና ወጪዎች በትክክል ለማወቅ የሚያስቸግር ናቸው በማለት በርትዕ ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 300,000 ሊከፍል ይገባል ብሏል፡፡

በዚህ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የሥር ተከሣሽ ይግባኝ በፍትሀብሄር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሲዘጋ በከሳሽ የይግባኝ መዝገብ ላይ ክርክር ተካሂዶ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል መልስ ሰጪ /ተከሳሽ/ ለይግባኝ ባይ በሥር ፍ/ቤት ቀደም ሲል የተወሰነላትን ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ የተቀበለች ስለሆነ ይኸው የተቀበለችው ገንዘብ የሚታሰብ ሆኖ ብር 694,918 /ስድስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት/ እንዲከፍላት በሚል ወስኗል፡፡

በዚህ በጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የዘረዘራቸው ነጥቦችም፡- በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት /ሊከፈላት የሚገባው የካሣ መጠን/ ሊታወቅ የሚችል ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የካሣ መጠኑን በርትዕ መወሰን አይገባቸውም፣ በርትዕት የሚወሰን የካሣ መጠን አነስተኛ መሆን ይገባዋል፣ ለተጨማሪ የካሣ ክፍያ የብር ተመን መውረድን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት እንደምክንያት መውሰዱ ተገቢነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ለሰበር አቤቱታ ተጠሪዋ በሰጠች መልስ አመልካች ለደረሰብኝ ጉዳት በሥር ፍ/ቤቶች ሀላፊነት እንዳለበት ተወስኖ እስከ ሰበር ድረስ በመ/ቁ. 58041 ቅሬታውን አቅርቦ ጉዳዩን የመረመረው የፌ/ሰበር ሰሚ ችሎትም በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመም በሚል አቤቱታውን ውድቅ ያደረገበት ስለሆነ የካሣን መጠን በሚመለከት ያቀረበውን ክርክር የሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ባለመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክራለች፡፡

አመልካችም ለተጠሪዋ መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን በማጠናከር አቅርቧል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ ከላይ በተገለፀው አኳኋን የቀረበ ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው የካሳ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር የአመልካች የህክምና ድርጅት ለተጠሪ ህክምና ባደረገላት ወቅት በተፈጠረው ችግር የተጠሪዋ ጤና ላይ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ ይህም የደረሰባት ጉዳት በሀገር ውስጥ በህክምና ለማዳን የሚቻል ባለመሆኑ ታይላንድ ሀገር ሄዳ እንድትታከም ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ለዚህ ቅሬታ ዋና መነሻ የሆነው ለህክምናና ለተለያዩ ወጪዎች ጠቅላይ ፍ/ቤቱ አመልካች ለተጠሪዋ የህክምናና ልዩ ልዩ ወጪዎች በርትዕ ከፍ አድርጐ መወሰኑ ነው፡፡

በእርግጥ በመርህ ደረጃ በጉዳቱ ምክንያት ተበዳዩ የሚካሰው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሣራ በመክፈል መሆኑን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090 የሚደነግግ ሲሆን ለጉዳቱ ሀላፊ የተደረገው ሰውም ሀላፊነቱ ያመጣውን ጉዳት በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ተመዛዝኖ መክፈል ይኖርበታል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን የጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለደረሰው ጉዳት ካሣ ለማስከፈል እንደ አማራጭ የወሰደው ርትዕን ነው፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ከተጠቀሱት ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ ተጠሪዋ ያቀረበቻቸው ለህክምናው ወጪ ያስፈልጋሉ የተባሉት ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት የህክምናው ወጪ ከፍተኛ ነው፣ ለተጠሪዋም አስታማሚ የሚያስፈልጋት ሲሆን ወጪውም ምን ያህል እንደሆነ ከወዲሁ ለማወቅ የሚያስቸግር ነው፣ በመላው ዓለም እየታየ ያለውም የዋጋ ንረት ለተጠሪዋ ህክምና ወጪ የራሱ የሆነ ሚና ይኖረዋል፣ የብር ምንዛሪ መውረዱ ተጠሪዋ ለህክምና ያስፈልገኛል በማለት በጠየቀችው የገንዘብ መጠን ላይ መዋዥቅን ያስከትላል የሚሉ ናቸው፡፡

በፍትሃብሄር ህጉ አንቀጽ 2102 ዳኞች ስለደረሰው ጉዳት ኪሣራን በርትዕ እንዲወስኑ መብት የተሰጠውም በግልጽና በትክክል የኪሣራውን መጠን ለመወሰን አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ አንፃር የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ በርትዕ ከዚሁ አንፃር የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ በርትዕ ለማስከፈል የጠቀሳቸው ምክንያቶች የቀረቡትን ማስረጃዎች እና በአሁኑ ጊዜ በዓለም እየታየ ያለውን የዋጋ ንረት ያገናዘቡ በመሆናቸው ይህ ችሎትም የሚቀበለው ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሣት ያለበት አመልካች ዳኞች የጉዳት ካሣን በርትዕ ሊወሰኑ የሚችሉት ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው በማለት የተከራከረው በአግባቡ ቢሆንም ርትዕን መሠረት አድርገው ዳኞች ካሣ ሊወሰኑ የሚችሉት የካሣ መጠን ለመቀነሥ እንጂ ከፍ ለማድረግ አይደለም ሲል የተከራከረው ግን ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ፍ/ቤቱ በርትዕ ሲወስንም ሊገመቱ የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያለአግባብ ስለመያዙ ወይም ሊገመቱ የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ በመተው ያለአግባብ የሆነውን የአገማመት መንገድ ስለመያዙ አመላካች ነገር የለም፡፡ የተወሰነውም የካሣ ልክ በግልጽ ከአእምሮ ግምት ውጪ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም ከዚህ በላይ በተገለጹት የህግ ምክንያቶች የተነሣ በጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 58732 በቀን 15/04/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተገኘበት በመሆኑ ፀንቷል፡፡
2. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ማለትም በሰበር ደረጃ የተደረገውን ክርክር በሚመለከት አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ቅ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 67973

ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች :-** አቶ በቀለ ወልቻም - ጠበቃ አቶ አለሙ ገ/ህይወት

**ተጠሪ :-** አቶ ጥበቡ ጦና - ጠበቃ አቶ ታደሰ ሲሳይ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-03593 /ደ.ህ/ በሆነ የህዝብ ማመላለሻ መኪና በመሳፈር ነሐሴ 6 ቀን 2001 ዓ.ም እየተጓዘ እያለ የአመልካችን መኪና ያሽከረክር የነበረው አቶ ወንድወሰን ሽታ ከተፈቀደለት የፍጥነት ወሰን በማለፍ በማሽከርከሩ መኪናው ተገልብጦ የቀኝ እግሬ ተቆርጧል፡፡ የተከሣሽ /አመልካች/ ሹፌር የነበረው አቶ ወንድወሰን በሀዋሣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በሶስት ወር እስራት እንዲቀጣ ተወስኖበታል፡፡ የደረሰበኝ ጉዳት 60% /ስልሳ ፐርሰንት/ የመሥራት አቅሜ እንደቀነሰ በጥቁር አንበሳ የሀኪሞች ቦርድ ተረጋግጧል፡፡ አደጋው ከመድረሱ በፊት ብር 658 /ስድስት መቶ ሃምሣ ስምንት ብር/ በየወሩ ተቀጥሬ ስሰራበት ከነበረው ሚዛን ተፈሪ ሆስፒታል ይከፈለኝ ነበር፡፡ በአደጋው ምክንያት ለህክምና ያወጣሁትን ወጭና ሌሎች ወጭዎች ተከሣሽ መተካት ያለበት ሲሆን የተቋረጠ ጥቅምና ገቢዬን የመክፈል ሀላፊነት ያለበት ስለሆነ ብር 348,247.22 /ሶስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሰባት ብር ከሀያ ሁለት ሣንቲም/ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ የሰላሣ አምስት ዓመት ደመወዝ ያለምንም ቅንስናሽ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ አይደለም፡፡ የደመወዝ ጭማሪ አገኝ ነበር በማለትና የጡረታ ገንዘብ በማለት ያቀረበው ጥያቄም የህግ መሠረት የለውም፡፡ እስከ 80 ዓመት እኖራለሁ ብሎ አስልቶ የጠየቀው የካሣ ገንዘብ ተገቢ አይደለም፡፡ የህክምና ማስረጃ የአካል ጉዳት እንደደረሰበት እንጅ 60% የከሣሽ የመስራት አቅም እንደቀነሰ አያረጋግጥም፡፡ የስር ፍርድ ቤት በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተከሣሹ



www.chilot.me

ሀላፊ ነው ወይስ አይደለም? ተከሣሽ ጉዳቱን የመካስ ሀላፊነት አለ ቢባል ሊከፈል የሚገባው ካሣ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጭብጦች መስርቷል፡፡ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተከሣሽ /አመልካች/ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት የለብኝም የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ ተከሣሽ ለጉዳቱ ሀላፊ የሚሆነው በንግድ ህግ ቁጥር 599 በተደነገገው መሠረት መሆን አለበት በማለት ወስኗል፡፡ የካሣውን መጠን በተመለከተ ከሣሽ አደጋው ሲደርስ እድሜው ሰላሣ ዓመቱ ነው፡፡ ወደፊት ጡረታ እስኪወጣ ሰላሣ ዓመት ይቀረዋል፡፡ የከሣሽ ደመወዝ በወር ብር 658 ሲሆን የገቢ ግብር ብር 51.20 ሲቀነስለት የተጠሪ ገቢ 606.80 ነው፡፡ የዚህ ስልሣ ፐርሰንት ገቢ እንደቀረበት ተደርጐ የካሣው መጠን መሰላት ይገባዋል በማለት ተከሣሽ /አመልካች/ ብር 131,068.80 /አንድ መቶ ሰላሣ አንድ ሺ ስልሣ ስምንት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም/ የተቋረጠ ጥቅም ስለሆነ ሊከፍል ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለህክምናና ሌሎች ወጭዎች የወጣ ብር 7604.34 /ሰባት ሺ ስድስት መቶ አራት ብር ከሰላሣ አራት ሣንቲም/ እና የህሊና ጉዳት ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ ተከሣሽ /አመልካች/ ለከሣሽ /ተጠሪ/ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የስር ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት መኪናው በድንገት በመገልበጡ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች አጓዥ በመሆኑ ለተጠሪ ልከፍለው የሚገባው የካሣ መጠን የንግድ ህግ ቁጥር 597ን መሠረት በማድረግ ሊወሰን ሲገባው የንግድ ህግ ቁጥር 599 መሠረት ተደርጐ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የሰላሣ ዓመት ገቢ እንደተቋረጠበት ተደርጐ ካሣው መሰላቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት እግሩ ላይ በመሆኑ ሌላ ስራ ሰርቶ ገቢ ማግኘቱን የሚከለክለው አይደለም፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ሰኔ 3 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የካሣ መጠን አጓዡ በተጓዡ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት እስከ ምን ድረስ ካሣ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት የሚደነግግ መሠረታዊ መርህ ሲሆን የንግድ ህግ ቁጥር 599 በመርህ ከተደነገገው በላይ አጓዡ ለተጓዡ ካሣ እንዲከፍል የሚገድቡትን ልዩ ሁኔታን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው የአመልካች ሰራተኛ ከተፈቀደለት በላይ በፍጥነት በማሽከርከሩ አደጋው የደረሰ መሆኑ ተረጋግጦ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በወንጀል የተቀጣ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት በማድረግ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ የካሣውም መጠን ቢሆን በማስረጃ በማጣራት የተሰጠ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለውን የካሣ መጠን የንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት በማድረግ ማስላታቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ

ለመወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎችን ይዘትና ትርጉም እንደዚሁም ድንጋጌዎቹ ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የንግድ ህግ ቁጥር አንቀጽ 587 በሚደነግገው መሠረት የአጓዥና የመንገደኛ ግንኙነት መኖሩን አመልካችና ተጠሪ በስር ፍርድ ቤትና በሰበር ባቀረቡት ክርክር የሚተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰው ለመጓጓዝ የተደረገ ውል መኖሩን አመልካችና ተጠሪ የሚስማሙበት ነጥብ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ዋጋ ከፍለው ሲጓጓዙበት የነበረውን የትራንስፖርት መኪና ባለሀብት ሲሆኑ ተጠሪው መንገደኛ ናቸው፡፡ አጓዡ መንገደኛውን በመልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ስለ ምቾቱና ስለ ጉዞው በውሉ የተወሰነውን ጊዜ አክብሬ እንደተወሰነው እመድረሻ ስፍራ የማድረስ ግዴታ እንዳለበት የንግድ ህግ አንቀጽ 588 ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የአጓዡን የትራንስፖርት መኪና በሀላፊነት ተረክቦ የመኪናውን ደህንነትና ብቃት አረጋግጦ በትራፊክ ደንብና ሥርዓት አክብሮ የማሽከርከር ሀላፊነት ያለበት አሽከርካሪ /ሹፌር/ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች የመንገደኛውን መልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ምቾት በመጠበቅ መንገደኛውን ከመነሻው እስከ መድረሻው የማድረስ ሀላፊነታቸውን ካልተወጡ አጓዡ በንግድ ህግ ቁጥር 588 የተጣለበትን ህጋዊ ግዴታ እንዳልተወጣ የሚቆጠር መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አጓዡ ይህንን ህጋዊ ሀላፊነቱን በአግባቡ ካልተወጣ መንገደኛው በጉዞው ላይ ስለሚደርስበት መዘግየትና በጉዞው ጊዜ ወይም በሚሣፈርበት ወይም በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል ማጉደል ወይም የህይወት ማለፍ አጓዡ ሀላፊ እንደሚሆን የንግድ ህግ አንቀጽ 595 በግልጽ ይደነግጋል፡፡

   የንግድ ህግ አንቀጽ 595 አጓዡ መንገደኛው በጉዞ ጊዜ በሚሣፈርበትና በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል መጉደል ወይም ህይወት ማለፍ አጓዡ በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን በመሠረታዊ መርህነት የሚደነግግ ሲሆን ፣ አጓዡ ከሀላፊነት ነጻ የሚሆንባቸዉን ልዩ ሁኔታዎች የሀላፊነቱን መጠንና አጓዡ በህግ ከተደነገገው መጠን በላይ በሀላፊነት ሊጠይቅ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች በንግድ ህጉ ተካተዋል፡፡

2. የመጀመሪያ በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ከተደነገገው ሀላፊነት አጓዡ ነጻ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግገው የንግድ ህጉ አንቀጽ 596 ነው፡፡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 አጓዡ በመንገደኛው ላይ የአካል መጉዳት ወይም የሞት አደጋ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ሀይል መሆኑን ፣ ወይም ጉዳቱ የደረሰው በሶስተኛ ሰው ጥፋት መሆኑን ወይም በመንገደኛው ጥፋት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ አጓዡ ከሀላፊነት ነጻ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ አጓዡ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻሉ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት አጓዡ በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑንና የሀላፊነቱ መጠን ለአንድ መንገደኛ ከብር 40,000 /አርባ ሺ ብር/ እንደማይበልጥ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 በግልጽ ይደነግጋል፡፡

   ሆኖም በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የሀላፊነት መጠን አጓዡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 የተደነገጉትና ከሀላፊነት ነጻ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታና መንገደኛው በንግድ ህግ አንቀጽ 599 በሚደነግገው መሠረት አጓዡ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ባልቻለበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአመልካች ንብረት የሆነውን የትራንስፖርት መኪና ያሽከረክር የነበረው የአመልካች ሰራተኛ የመኪናው ሹፌር ከተፈቀደለት



www.chilot.me

ፍጥነት በላይ በማሽከርከሩ መኪናው የተገለበጠና ተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑ የአመልካችን መኪና ያሽከረክር የነበረው ሹፌር በሀዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 21372 በወንጀል ተከስሶ የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በፍርድ ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ በሶስት ወር እስራት የተቀጣ መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ በንግድ ህግ ቁጥር 588 በሚደነግገው መሠረት የመንገደኛውን መልካም ይዞታ ደህንነትና ምቾች በመጠበቅ መንገደኛውን የማጓጓዝ ሀላፊነቱን አጓዡ የሚወጣው አጓዡ ራሱ የመኪናው አሽከርካሪ ከሆነ አጓዡ፣ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች አማካኝነት ሲሆን አጓዡ የመኪናው አሽከርካሪ ካልሆነ መኪናውን በሀላፊነት ይዞ በሚያሽከረክረው ሹፌር ፣ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች በኩል መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በተመሣሣይ ሁኔታ በንግድ ህግ ቁጥር 599 በተደነገገው መሠረት አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑን እያወቀ አጓዡ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን መንገደኛው የሚያስረዳው አጓዡ የመኪናው አሽከርካሪ ከሆነ እሱ ራሱ መኪናውን ሲያሽከረክር ወይም ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች በፈጸሙት ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡ አጓዡ መንገደኛው የተሣፈረበትን መኪና የማያሽከረክር በሆነ ጊዜ መኪናውን አጓዡ በሀላፊነት ተረክቦ ሲያሽከረክር የነበረው ሰው ፣ ረዳቱ ወይም ሌላ የአጓዡ ሰራተኛ አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡

በንግድ ህግ አንቀጽ 599 "አጓዡ የተፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት" የሚለው ሀረግ አጓዡ በግሉ የፈጸመውን ተግባር ወይም ጉድለት የሚመለከት ሣይሆን የአጓዡ ሰራተኞች አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጠር እንደሚችል እያወቁ የፈጸሙትን ተግባር ወይም ጉድለት የሚያካትት ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ ይዘት ህግ አውጭው ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሀላፊነት "አንድ ሰራተኛ ስራውን በሚሰራበት ጊዜ ሀላፊነትን የሚያስከትል ጥፋት የሰራ እንደሆነ በፍታብሔር በሀላፊነት የሚጠየቀው አሰሪው ነው" በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2130 የደነገገውን መሠረታዊ መርህ በሚያካትት ሁኔታ መተርጐምና የህጉ ድንጋጌ ተግባራዊ እንዲሆን ካልተተረጐመ የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ህግ አውጭው የሰጠውን ግብ የሚያሣካ አይሆንም፡፡

ከዚህ አንጻር ስንመለከተው አደጋው የደረሰው የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ከተፈቀደለት ፍጥነት በላይ ማሽከርከሩ አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑ በቂ የሙያ ዕውቀትና ክህሎት እያለው ከተፈቀደለት ፍጥነት በላይ በማሽከርከሩ መሆኑን ተጠሪ ስላስረዳ የበታች ፍርድ ቤቶች የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ለጉዳዩ ተፈጻሚ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በተጠሪ አካል ላይ ጉድለት ያደረሰው አደጋ የተከሰተው የአመልካች ሰራተኛ የሆነውና መኪናውን ያሽከረክረው የነበረው ሹፌር የትራፊክ ደንብና ስርዓት በመጣስ መኪናውን ከተፈቀደለት ፍጥነት በላይ በማሽከርከር በፈጸመው ተግባር መኪናው የተገለበጠ መሆኑን ተጠሪ በበቂ ማስረጃ እንዳስረዳ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት በንግድ

ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የሀላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢና የህግ ስህተት ያሌለበት በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

3. አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የሀላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት እንዳለበት የንግድ ህግ አንቀጽ 599ን መሠረት በማድረግ የበታች ፍርድ ቤቶች መወሰናቸው ተገቢ ነው የሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡ ከዚህ በኂላ የሚነሣው የህግ ጥያቄ አመልካች ለተጠሪ በንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት ሊከፍለው የሚገባው ምን ያህል ነው የካሣው መጠንስ እንዴት ነው የሚሰላው የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 ጉዳት የደረሰበት መንገደኛ ገቢ በጉዳቱ ምክንያት የደረሰበትንና ወደፊት የሚደርስበት ኪሣራ ከብር 40,000 በላይ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳን አጓዡ ለአንድ መንገደኛ የሚከፍለውን የካሣ መጠን በብር 40,000 መለወጥ እንደሌለበት የሚደነግግና የሀላፊነቱን መጠን የሚወሰን ድንጋጌ ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ከላይ ለተገለጸውና የሀላፊነቱን መጠን ከሚወሰነው አንቀጽ 597 በልዩ ሁኔታ የተደነገገ ድንጋጌና መንገደኛው ከአጓዡ ከብር 40,000 በላይ ካሣ ለመጠየቅና ለማግኘት የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡

በግንድ ህግ ቁጥር 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት አጓዡ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 የተደነገጉት የካሣ አከፋፈል መርሆች አግባብነት ያላቸው ናቸዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባውን የካሣ መጠን የወሰነው ከላይ የጠቀስናቸውን መሠረታዊ የካሣ አከፋፈል ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ በአደጋው ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ለመታከም ያወጣውን ወጭና ሌሎች አስፈላጊ ወጭዎች በማስረጃ  በማረጋገጥ ለተጠሪ እንዲከፈል የንግድ ህግ አንቀጽ 599ን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 ጋር አጣምሮ በመተርጐም የወሰነ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት አመልካች አደጋው ሲደርስበት ያገኝ ከነበረው የወር ደመወዝ ለገቢ ግብር የሚከፍለውን በመቀነስ ፣ ተጠሪ ከሚያገኘው የወር ደመወዝ ስልሣ ፐርሰንቱን ብቻ አመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የጡረታ መገለያ እድሜው እስኪደርስ ያገኝ የነበረው የተጣራ ገቢ ስልሣ ፐርሰንቱን ብቻ አመልካች እንዲከፍል የንግድ ህግ አንቀጽ 599ን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 ጋር አጣምሮ በመተርጐም የካሣውን መጠን የወሰነ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የስር ፍርድ ቤት የንግድ ህግ አንቀጽ 599 አግባብነት ካላቸው የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ማጽናታቸው ተገቢና የህግ ስህተት ያሌለበት በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው የአካል መጉደል ካሣ የሚከፍለው በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ድንጋጌዎች መሠረት ሣይሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት ነው በማለት የካሣውን መጠን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 መሠረታዊ መርሆች በመጠቀም መወሰናቸው ተገቢና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 24643

ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች ፡-** ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም - ጠበቃ ኪሩቤል ኃ/ማርያም - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ ፡-** አቶ አለማየሁ አህመድ - ቀረቡ፡፡

**ፍ ር ድ፣**

ለሠበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ፣ የስር 3ኛ ተከሣሽ የነበሩት የሠ/ቁ 3-03657 የሆነ መኪና ሲያሽከረክሩ ምናሴ ከበደ የተባለውን ልጃቸውን ገጭተው በመግደላቸው በወንጀል ተከሠው ተፈርዶባቸዋል፡፡ መኪናውን የሥር 2ኛ ተከሣሽ ገዝተው የባለቤትነት ስሙ በስማቸው ባይተላለፍም በይዞታቸው ሥር ነበር፣ የአሁኑ ተጠሪም የመኪናው የባለቤትነት ስም በስማቸው በመሆኑ የመኪናው ባለቤት ናቸው፡፡ በመሆኑም ሶስቱም ተከሣሾች ለደረሠው አደጋ ኃላፊነት ስላለባቸው የጉዳት ካሣ ይክፈሉኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሠምቶ የአሁኑ ተጠሪ መኪናውን ለሥር 2ኛ ተከሣሽ ሸጠው ኃላፊነቱ ለ2ኛ ተከሣሽ የተላለፈ በመሆኑ ሊጠየቁ አይገባም በማለት የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ብቻ ለደረሠው ጉዳት ሃላፊ በመሆናቸው የጉዳት ካሣውን ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካችም ተጠሪ ሃላፊ ሊሆኑ አይገባም በማለት በተሠጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ቅሬታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ የሠበር ችሎትም ጉዳት ያደረሠው መኪና የባለቤትነት ስም በተጠሪው ስም በመሆኑ ተጠሪው በሃላፊነት ሊጠየቁ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ መልስ ማግኘት ያለበት ጭብጥ የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለሃብትነት ወደ ሌላ ሰው ተላለፈ የሚባለው መቼ ነው? መኪኖች እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከውል ውጭ ባሉ ግንኙነቶች ለሚያደርሱት ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቀው ማነው? የሚለው ይሆናል፡፡ ለተያዘው ጭብጥ መልስ ለመስጠት የተንቀሳቃሽ ንብረት ባለሃብትነት የሚተላለፍበትን

መንገድ የሚመለከቱትን የህጉ ድንጋጌዎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ በተለይ በዚህ ጉዳይ ክርክር የተነሣበት ሃብት መኪና በመሆኑ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ልዩ ከሆኑ አንዳንድ የሚንቀሣቀሱ ንብረቶችን በሚመለከት የተደነገጉትን የህግ ድንጋጌዎች መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1186 "ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሣቃሽ ንብረቶች ባለሀብትነት ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን እጁ ባደረገ ጊዜ የተላለፈለት ይሆናል" በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ የህግ ድንጋጌ መሠረትም የአንድ የሚንቀሣቀስ ንብረት ባለሃብት ለመሆን ሌላ ተጨማሪ ሁኔታ ማሟላት ሣያስፈልግ ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኋን ንብረቱን አግኝቶ በእጅ በማድረግ ብቻ ባለሀብት ሊሆን የሚቻል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም ይህ ድንጋጌ  ልዩ የሆኑ አንዳንድ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ባለሀብትነት ለማስተላለፍ በተለይ የተመለከቱትን የሕግ ድንጋጌዎች የማያጠቃልል መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1186(2) ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት የምዝገባና የባለሀብትነት ማስተላለፊያ ስርዐትን በመከተል ብቻ ባለሀብትነት ከሚተላለፍባቸው ግዙፍነት ካላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች መካከል መኪና እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ዋንኞቹ ስለመሆናቸው በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን ለመቆጣጠርና ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 256/1960 ተከትሎ የወጣውን እና የተለያዩ ክፍሎቹ በየጊዜው የተሻሻሉትንና እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት ያለውን የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 360/1961ን መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

በቅድሚያ የፍጥነት ወሰኑ በሰዓት ከ20 ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ልዩ ተሽከርካሪ መሣሪያዎች በስተቀር ማናቸውንም ባለሞተር ተሽከርካሪ የማስመዝገብ ግዴታ በአስገዳጅነት በሕጉ የተጣለ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 256/1960 አንቀጽ 6 "ን" እንደአግባብነቱ ካሻሻለው እና የሚኒስቴሩን መ/ቤት በአዲስ ካቋቋመው አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 21 መረዳት ይቻላል፡፡

ባለሞተር ተሽከርካሪን ከማስመዝገብ ግዴታ ጋር ተያይዞ ማንም ሰው በደንብ ቁጥር 360/1961 አንቀጽ 6 መሠረት የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር አያስፈልጋቸውም ተብለው ከተመለከቱት ተሽከርካሪዎች ውጭ ያሉ ተሽከርካሪዎችን ለአገልግሎት ከተላለፉበት ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰጠው ለአዋጅ አስፈጻሚ መ/ቤት ማመልከቻውን  ማቅረብ የሚገባው መሆኑን በደንቡ ቁጥር 7 ላይ ተመልክቷል፡፡ በማንኛውም መንገድ ተሽከርካሪው ለአገልግሎት የተላለፈለት ሰው በስሙ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰጠው ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋርም የንብረቱን ባለሀብትነት ያገኘበትን አግባብ የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማቅረብ የሚገባው መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት የተሽከርካሪው ባለሀብትነት የተገኘው ከቀድሞው ባለቤት ላይ ከሆነ የቀድሞውን ባለቤት የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር፣ ወይም ማመልከቻው የሚመለከተው ከዚህ በፊት በውጭ አገር የተመዘገበን ተሽከርካሪ እንደሆነ በተባለው አገር የተሰጠ የባለንብረት መታወቂያ ሰነድ ወይም የተሽከርካሪውን ባለንብረትነት ለማወቅ ለሚኒስቴሩ መ/ቤት አስፈላጊ ናቸው የሚባሉትን ማናቸውንም ሰነዶችና መረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ የሚገባ መሆኑን በደንቡ ቁጥር 7 (1) እና (3) ላይ ተደንግጓል፡፡ ይህ የደንቡ ክፍል በአዲስ የተገዙትን፣ በውጭ አገር አገልግሎት ሰጥተው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን  እና በአገር ውስጥ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ከአንዱ ወደ ሌላው በተለያየ ምክንያት ሲተላለፉ ተሽከርካሪው ለአገልግሎት



www.chilot.me

የተላለፈለት ሰው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰጠው ከማመልከቻው ጋር በማያያዝ ሊያቀርብ የሚገባቸው ሰነዶች የትኞቹ እንደሆኑ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአገር ውስጥ የሠራ ተሽከርካሪ ለአገልግሎት ከአንዱ ወደ ሌላው ሲተላለፍ የተላለፈለት ሰው የአስተላለፈውን የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲረከብና ሁለቱ ወገኖች በደብተሩ ውስጥ የሚገኘውን የባለንብረትነት መታወቂያ ገጽ በሚገባ ሞልተው እና ፈርመው ማቅረብ የሚገባቸው መሆኑን በደንቡ ቁጥር 8 እና 11(1) ላይ ተመልክቷል፡፡ በመጨረሻም የሚኒስቴሩ መ/ቤት ማመልከቻው እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ካረጋገጠ ማመልከቻ አቅራቢው የተሽከርካሪው ባለቤት ነው እንዲባል አንድ የባለንብረት መታወቂያ ደብተር የሚሰጠው መሆኑን በቁጥር 9 ላይ ተመልክቷል፡፡

ከፍ ብለው ከተመለከቱት የደንቡ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ነገር ቢኖር፣ የፍጥነት ወሰናቸው በደንቡ ላይ የተመለከቱት ተሽከርካሪዎች ከአንዱ ወደ ሌላ በሽያጭ፣በስጦታ ወይም በሌሎች መንገዶች ተላልፈው ሲገኙ እንደ አብዛኛዎቹ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ዋጋ ሰጥቶ ንብረቱን በእጅ በማድረግ ብቻ የባለሀብትነት መብት የማይተላለፍ መሆኑን፤ ይልቁንም ልዩ የሆኑትን እነዚህን ግዙፍነት ያላቸውን ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ባለሀብት ሆኖ ለመገኘት ሻጭ እና ገዥ ወይም ስጦታ አድራጊና ስጦታ ተቀባይ ከሚያደርጉዋቸው የተሳኩ የውል ስምምነቶች ባሻገር ከፍ ብለው በደንቡ በተመለከተው እንኳን የተሽከርካሪውን ባለሀብትነት ከአስተላላፊው ወደ ተላለፈለት ሰው የሚዘዋወርበት ስርዓት በሚኒስቴሩ መ/ቤት መጠናቀቅ የግድ መሆኑን ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ባለንብረትነቱ የታወቀለት ሰው ተሽከርካሪው ከጥቅም ውጭ ሆኖ በወላለቀና ጨርሶ በወደመ ጊዜ እንኳን ይህንኑ ሁኔታ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ መ/ቤት አሳውቆ በስሙ የተመዘገበው የባለቤትነት ደብተር እንዲሰረዝና ከመዝገብ እንዲፋቅ ካላስደረገ በቀር ባለሃብቱ ስሙ በመታወቂያ ደብተሩ ላይ የተመዘገበው ሰው ሆኖ እንደሚቀጥል ከደንቡ ቁጥር 42 እስከ 45 እና በቁጥር 11(2) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመመርመር መረዳት ይቻላል፡፡

ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በሰው ልጆች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ውስጥ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ የመሆኑን ያህል እነዚህ ማሽኖችና ተሳቢዎች በጐዳናዎች ላይ በሚሽከረከሩበት ጊዜ በሰውና በንብረት ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት የጉዳት መጠን የዛኑ ያህል ከፍተኛ በመሆኑ እነዚህ ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ወደ አገር ውስጥ ሲገቡም ሆነ በቴክኒክ ረገድ ብቃት ኖራቸው በጐዳናዎች ላይ ሲሽከረከሩ፤ እንዲሁም በተለያዩ ሁኔታዎች ንብረቶቹ ከአንዱ ወደ ሌላው ሲተላለፉም ሆነ ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ጨርሶ ሲወድሙ ልዩ የምዝገባና የቁጥጥር ሥርዐት እንዲደረግባቸው ማድረጉ ማህበራዊ ደህንነትን ከመጠበቅ አኳያ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ አገሮች ባለሞተር ተሽከርካሪዎች እና ተሳቢዎቻቸውን ከሞላ ጐደል ተመሣሣይነት ባላቸው ልዩ ደንቦች እንዲመሩ የሚያደርጉ መሆኑን የተለያዩ አገሮችን ልምድ በመዳሰስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የመኪና እና ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለሀብትነት የሚገኘው ከፍ ብለን በገለጽነው ሥርዐት ብቻ መሆኑ ከታወቀ በመቀጠል ሊነሳ የሚገባው ጭብጥ የባለሀብትነት ዝውውር ሥርዐቱ ደንቡ በሚጠይቀው አኳኋን ሳይከናወን አንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ከሻጭ ወደ ገዥ ወይም ከስጦታ አድራጊ ወደ ስጦታ ተቀባይ ይዞታው ተላልፎ በነበረበት ጊዜ መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት አድርሶ ቢገኝ ኃላፊው ንብረቱ በስሙ የሚገኘው ሰው ነው? ወይስ ንብረቱን በእጁ አድርጎ ሲገለገልበት የነበረው ሰው? የሚለው ይሆናል፡፡ እነዚህን



www.chilot.me

ጭብጦች ለመመለስ እንድንችል መዝገቡን አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር መመርመሩ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የአሁኑ አመልካች ክሳቸውን ሲመሰርቱ የስር 3ተኛ ተከሳሽ የነበረው ሾፌር የሠ/ቁ. 3-03657 የሆነውን መኪና እያሽከረከሩ ጉዳት በማድረሳቸው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንዲባሉ፤ የስር 2ተኛ ተከሳሽ ጉዳት ያደረሰውን መኪና ገዝተው በይዞታቸው ሥር እያለ ጉዳት በማድረሱ 2ኛ ተከሳሽም ኃላፊ እንዲባሉ፣ የመኪናው የባለቤትነት ስም ደግሞ በስር 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ ተጠሪ ስም በመሆኑ ተጠሪው የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንዲሆኑ ጠይቀዋል፡፡ ከመዝገቡም የስር 3ተኛ ተከሳሽ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን፣ ጉዳት ያደረሰውን መኪና የሥር 2ተኛ ተከሳሽ ገዝተው የተረከቡ መሆኑን ነገር ግን የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ በአሁኑ ተጠሪ ስም መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በዚህ መሠረት ለጭብጦቹ ምላሽ ለማግኘት በቅድሚያ በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የሚገኙትን ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መፈተሹ አግባብነት ይኖረዋል፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) መሠረት የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው ንብረቱ ተሰርቆ በነበረበት ጊዜ ለደረሰው አደጋ ከተጠያቂነት ነጻ ከሚሆን በስተቀር መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለመንዳት ባልተፈቀደለት ሰው እንኳን ተነድቶ ጉዳት አድርሶ ቢገኝ የመኪናው ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት ከውል ውጭ በሚደርሱ ኃላፊነቶች ውስጥ በፍትሐብሔር ሕጉ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ከሚባሉት ምድቦች ውስጥ የሚመደብ በመሆኑ መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ላደረሰው ጉዳት ባለቤቱ ኃላፊ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ስሙ በባለቤትነት ያልተመዘገበ መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበትና ሲጠቀምበት የነበረው ሰው መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው በእጁ በነበረበት ጊዜ ለደረሰው ጉዳት ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል ማለት አለመሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2082(1) መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መነሻነት በአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ሰው የመኪናውን ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪውን ባለቤት ወይም በንብረቱ ተገልጋይ የነበረውን ማንኛውም ሰው በአንድነትም ሆነ በተናጥል ከሶ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ ለመጠየቅ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) እና 2082 (1) መሠረት መብት ያለውን ያህል የመኪናው ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ተብሎ የሚታወቀው ሰው የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ ብቻ ተበዳይን ተገዶ ከካሰ በኋላ መኪናውን በእጁ አድርጉ ሲገለገል የነበረውን ማንኛውም ሰው የከፈለውን ገንዘብ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 2083 (1) ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ነገር ደንቡ የሚጠይቀውን የመኪና ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪ የባለቤትነትን የማስተላለፍ ሥርዐት ባልተከናወነበት ጊዜ ሁሉ በመኪናው ወይም በባለሞተር ተሽከርካሪው ለሚደርስ አደጋ ስሙ በባለቤትነት የሚታወቀው ሰው የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ ብቻ የሚጠየቅ መሆኑን እና ንብረቱን በማናቸውም መንገድ በእጁ አድርጉ ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበት የነበረ ሰው ለደረሰው ጉዳት ምንግዜም የመጨረሻው ኃላፊነት የማይቀርለት መሆኑን



www.chilot.me

ነው ፡፡ ከዚህ ሌላ ስለባለቤቱ ወይም ስለሌላ ሰው ሆኖ በአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ይሰራ የነበረ ታዛዥ መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ጉዳት አድርሶ የተገኘው በራሱ ጥፋት ምክንያት ካልሆነ በቀር እንደ ባለቤቱ ወይም እንደ ንብረቱ ተገልጋይ ሰው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደማይሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2082(2) ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን የሥር 3ተኛ ተከሳሽ የነበረው ሾፌር በወንጀል ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በፍትሐብሄር ሕግ ቁ. 2082(2) መሠረት ለጉዳቱ ኃላፊ ነው መባሉ ተገቢ ነው፡፡

ባጠቃላይ የአሁኑ ተጠሪ ጉዳት ያደረሰውን ተሽከርካሪ በሽያጭ ለስር 2ተኛ ተከሳሽ ለነበሩት ሰው በማስተላለፋቸው ብቻ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2324(1) በተመለከተው አኳኋን የጉዳት ኃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ ወደ ገዢው ብቻ ተላልፏል ለማለት አይቻልም፡፡ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ልዩ የምዝገባና የባለሃብትነት ስም ዝውውር የሚሻ ንብረት በመሆኑ እንደአብዛኛዎቹ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ዋጋ ሰጥቶ ንብረቱን በእጅ በማድረግ ብቻ ባለሃብትነት የሚተላለፍ አይደለም፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2267(2) በተደነገገው መሠረት አንዳንድ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን የሚመለከቱ ልዩ ሕጎች ውስጥ የሚገኙ ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ ስለሽያጭ በተጻፉ ደንቦች አይነኩም በማለት የተደነገገውም የህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

በመሆኑም የተሽከርካሪው የባለሃብትነት ስም ዝውውር ደንቡ በሚጠይቀው አግባብ ባልተጠናቀቀበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች የአሁኑ ተጠሪ ተሽከርካሪውን ለሥር 2ተኛ ተከሳሽ በሽያጭ አስተላልፏል በሚል ብቻ ተጠሪ ኃላፊ ሊሆኑ አይገባም ብለው መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የመኪናው ባለኃብትነት በስሙ የሚታወቀው በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በንብረቱ አማካኝነት ለደረሰው የሞት አደጋ ንብረቱን ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበት ከነበረው ከሥር 2ተኛ ተከሳሽ እና ስለ 2ተኛ ተከሳሽ ሆኖ በመኪናው ይሰራበት ከነበረው እና በጥፋቱ ኃላፊ ከተባለው ከሥር 3ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነት ኃላፊ ናቸው ብለናል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በልጃቸው ሞት ምክንያት እንዲከፈላቸው የተወሰነውን ብር 71,887.50 /ሰባ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ከስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በተጨማሪ የአሁኑ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡ ተጠሪ የከፈሉትን የጉዳት ካሣ ከሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በ5/8/97 በመ/ቁ 03696 በሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የካቲት 8 ቀን 1998 በቁጥር 40410 በሰጠው ትዕዛዝ ላይ የአሁኑ ተጠሪ ከተጠያቂነት ነጻ ናቸው በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል ብቻ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55228

ጥር 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** አቶ አብራር ሳቢር - ጠበቃ ቸርነት ወርዶፋ - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** 1. ወ/ሮ አለምፀሐይ ወሰኔ - በሌሉበት የሚታይ ነው

2. ጥበቡ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ አበበ ምትኩ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የሰሌዳ ቁጥር 2-37663 ሀይሉክስ ቶዮታ መኪና፣ ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች የሆነች ባለቤታቸውን (አቶ አብርሃም አክሊልን) በአቶ ዘነበ ብርሃኑ ጥቅምት 25 ቀን 1996 ዓ.ም በመነዳት ላይ እያለች ሸረራ በተባለ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ውስጥ ስትደርስ መንገዱን በመልቀቅ ሮጣ ከእንጨት ላይ በመጋጨት በአቶ አብርሃም ላይ ጉዳት በማድረሷ አቶ አብርሃም በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ታህሳስ 03 ቀን 1996 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን፣ በሕይወት እያሉም የፍራፍሬ ንግድ ስራ ሰርተው ገቢ ያስገኙ እንደነበር፣ ሟች እድሜአቸው 32 ዓመት እንደነበር፣ በሚያገኙት ገቢም ተጠሪን ያስተዳድሯቸው እንደነበርና የገቢ መጠኑንም ጭምር በመግለጽ በጉዳቱ ምክንያት ብር 134,400.00(አንድ መቶ ሰላሳ አራት ሺህ አራት መቶ ብር) ገቢ የተቋረጠባቸው መሆኑን፣ ለህክምናና ለቀብር ወጪ ማውጣታቸውን የሕሊና ጉዳትም የደረሰባቸው መሆኑን ጠቅሰው በጠቅላላው ብር 138,400(አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ብር) በክሱ ምክንያት ካወጡት ወጪና ኪሳራዎች ጋር አመልካች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመኪናዋ ባለንብረት ቢሆኑም መኪናዋን ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በኰንትራት ሰጥተው በነበሩበት ወቅት ጉዳቱ መድረሱን ገልጸው ኃላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከሩ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪም ወደ ክሱ እንዲገባ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክሱ እንዲገባ ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪም ቀርቦ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የአሁኑን አመልካች በመኪናው ባለንብረትነቱ ለጉዳቱ ኃላፊ ሲያደርግ 2ኛ ተጠሪን ግን ከክሱ ነጻ አድርጎታል፡፡ የጉዳት መጠኑን በተመለከተም



www.chilot.me

በርትዕ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ) ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ለጉዳቱ ኃላፊ፣ 2ኛ ተጠሪን ደግሞ ነፃ በማድረግ የሠጠውን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የጉዳት መጠኑን ብቻ ብር 25,000.00(ሃያ አምስት ሺህ ብር) እንዲሆን በማሻሻል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ተብለው መወሰኑም ሆነ ለ1ኛ ተጠሪ ካሳ ይከፈል ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095፣ 2082፣ 2089 እና 2102 ድንጋጌዎች ውጪ ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ኃላፊነትን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ ሕጋዊነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 2ኛ ተጠሪ ቀርቦ በጠበቃው አማካኝነት ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሱን የሰጠ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ግን በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2082(2) እና 2089 ድንጋጌዎች አንፃር ለይቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት አብርሃም አክሊል ንብረትነቱ የአመልካች በሆነች ሃይሉክስ ቶዮታ መኪና ተሳፍረው ሲሄዱ በደረሰው አደጋ ምክንያት ከዚህ አለም በሞት የተለዩ መሆኑን፣ መኪናው ጉዳቱን ባደረሰበት እለት በ2ኛ ተጠሪ እጅ የነበረ መሆኑ፣ መኪናው ወደ ሁለተኛ ተጠሪ እጅ ሊገባ የቻለውም በኪራይ ስለመሆኑ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች 2ኛ ተጠሪን ለጉዳቱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ሊወስኑ የቻሉት 2ኛ ተጠሪ ሲገለገልበት አልነበረም በሚል ምክንያት ሳይሆን መኪናው ጉዳቱን ባደረሰበት ጊዜ ይሽከረከር የነበረው በአመልካች በተቀጠረ ሹፌር በመሆኑና መኪናውን የመቆጣጠር ኃላፊነት የሹፌሩ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) መሠረት የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው ንብረቱ ተሰርቆ በነበረበት ጊዜ ለደረሰው አደጋ ከተጠያቂነት ነፃ ከሚሆን በስተቀር መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለመንዳት ባልተፈቀደለት ሰው እንኳን ተነድቶ ጉዳት አድርሶ ቢገኝ የመኪናው ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት ከውል ውጭ በሚደርሱ ኃላፊነቶች ውስጥ በፍትሐብሔር ሕጉ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ከሚባሉት ምድቦች ውስጥ የሚመደብ በመሆኑ መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ላደረሰው ጉዳት ባለቤቱ ኃላፊ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ስሙ በባለቤትነት ያልተመዘገበ መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለግል ጥቅሙ



www.chilot.me

ሲገለገልበትና ሲጠቀምበት የነበረው ሰው መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው በእጁ በነበረበት ጊዜ ለደረሰው ጉዳት ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል ማለት አለመሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2082(1) መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መነሻነት በአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ሰው የመኪናውን ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪውን ባለቤት ወይም በንብረቱ ተገልጋይ የነበረውን ማንኛውም ሰው በአንድነትም ሆነ በተናጠል ክሶ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ ለመጠየቅ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) እና 2082(1) መሠረት መብት ያለውን ያህል የመኪናው ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ተብሎ የሚታወቀው ሰው የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ ብቻ ተበዳይን ተገዶ ከካሰ በኋላ መኪናውን በእጁ አድርጐ ሲገለገል የነበረውን ማንኛውም ሰው የከፈለውን ገንዘብ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2083(1) ተመልክቷል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች የተከሰሱት የመኪናው ባለንብረት በመሆናቸው ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ወደ ክሱ እንዲገቡ የተደረገውም መኪናውን ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ ሲገለገልበት ነበር በሚል ምክንያት ሁኖ ይኸው ስለመሆኑም በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ 2ኛ ተጠሪ መኪናውን ሲገለገልበት የነበረ መሆኑ ከታወቀ የመኪናውን አሽከርካሪ ባለንብረቱ መቅጠሩ መታወቁ መኪናውን ሲገለገልበት የነበረን ሰው ከኃላፊነት ነጻ ሊያደርገው የሚችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2082 ድንጋጌ በመስፈርትነት ያላስቀመጠው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳቱን ያደረሰውን መኪና ሲገለገልበት የነበረው 2ኛ ተጠሪ መሆኑ ከተረጋገጠ የመጨረሻ ኃላፊነቱን (ultimate liability) ሊወስድ የሚገባው ይኸው ተጠሪ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለክሱ ኃላፊ፣ 2ኛ ተጠሪን ከክሱ ነጻ በማድረግ ውሳኔ መስጠታቸው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2081፣ 2082(1) እና 2083 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሟች በፍራፍሬ ንግድ ስራ ላይ የነበሩ መሆኑና ሲያገኙ የነበሩት የገቢ መጠን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካችም ሆነ ጣልቃ ገብ የነበረው 2ኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ማስረጃ የሚያፈርስ የመከላከያ ማስረጃ አለማቅረባቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳቱ ምክንያት በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረባቸውን ጥቅም በተጠሪ ማስረጃ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ ተጠሪዋ የሚገባቸውን የካሳ መጠን በርትዕ በመለየት ወስነዋል፡፡

ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን፣ መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣ 2091፣ 2092፣ 2095 እና 2102 ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሁኖ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች በሚሰጡት የካሣ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ለ1ኛ ተጠሪ ይከፈል የተባለው ካሳ መጠን ብር 25,000.00(ሃያ አምስት ሺህ ብር) የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ አመልካችን ኃላፊ በማድረግ ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሲሆን በካሳ መጠኑ ግን ሊነቀፍ የሚችል ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ ተጠሪ ጉዳቱን ያደረሰውን መኪና ሲገለገልበት የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2082(1) መሰረት ለጉዳቱ ኃላፊ ነው ብለናል፡፡
3. ለ1ኛ ተጠሪ ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ) የጉዳት ካሳ ሊከፍላቸው የሚገባው አመልካች ሳይሆኑ 2ኛ ተጠሪ (ጥበብ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር) ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54518

የካቲት 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልድ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ከበደ ዓለሙ - ቀረበ

**ተጠሪዎች** ፡- 1. ፀሐዬ ዘሙይ

2. ሱልጣን ካሕሣይ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ እንዲወሰን የተያዘው ጭብጥ የቤት ኪራይ ውልን መነሻ ባደረገው ክስ የተጠየቀው የገንዘብ ክፍያ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2024/መ/ የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የሰጠው ውሣኔ በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚል ነው፡፡ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ሲሆን፣ ተጠሪዎችን የከሰሰው በሕግ አግባብ እና በኤጀንሲው የኪራይ መመሪያ መሠረት የኪራይ ውል ሣይኖራቸው በቤቱ የተገለገሉ በመሆናቸው ያለአግባብ በበለፀጉበት መጠን ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መልስ በእነሱ እና በአመልካች መካከል የኪራይ ውል ወይም ግንኙነት እንደሌለ በመግለጽ የመክሰስ መብት የለውም እንደዚሁም ገንዘቡ የተጠየቀው በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ስላልሆነ ክሱ ሊስተናገድ አይገባም በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የክሱን ሥረ ነገር በሚመለከትም ቤቱን የያዝነው ከቀድሞው ተከራይ የንግድ መደብሩን በመግዛት ነው፡፡ ቤቱ በአሁኑ ጊዜ ፈርሶአል የሚሉትን የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሣት ክሱ ውድቅ ይደረግላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ክርክሩን የመረመረ ሲሆን፣ በመቀጠልም የክፍያ ጥያቄው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የሥር ፍ/ቤቶች



www.chilot.me

የተጠየቀው ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የህሊና ግምት የወሰዱት ሕጉን በአግባቡ በመተርጎም ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የአመልካች እና የተጠሪዎች ግንኙነት በኪራይ ውል ላይ የተመሰረተ ላለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካች ተጠሪዎችን የከሰሰው የውል ግዴታ አልተወጡም ወይም በገቡት የኪራይ ውል መሠረት ኪራይ አልከፈሉም በማለት እንዳልሆነም ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ክስ የመሠረተው ተጠሪዎች ቤቴን ያለአግባብ ይዘው ከህግ ውጪ በልጽገዋል በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የጠየቀውን ገንዘብ ያሰላው ቤቱን በማከራየት አገኝ ነበር ባለው መጠን ነው፡፡ ተጠሪዎችም በቤቱ አልተገለገልንም የሚል ክርክር አላነሱም፡፡ ይልቁንም ከአመልካች ጋር የውል ግንኙነት የለንም በማለት ገንዘቡን መክፈል የለባቸውም እንዲባልላቸው የተከራከሩት በመሆኑም እነዚህን ፍሬ ነገሮች ደምረን ጉዳዩን ስንመለከተው ክርክሩ ከኪራይ ክፍያ ጋር የሚያያዝበት ምክንያት የለም፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት አለው በማለት የጠቀሱት የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2024 የሚገኘው " ስለውሎች በጠቅላላው " በሚል በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 12፣ በምዕራፍ 7 በክፍል 3 ሥር ሲሆን፣ ክስ የቀረበበት ገንዘብ በሁለት ዓመት እንደተከፈለ የሚያስቆጥር የህሊና ግምት የሚወሰድባቸውን አግባቦችም በዝርዝር ያመለክታል፡፡ የህሊና ግምት ከሚወሰድባቸው የክፍያ ጥያቄዎች አንዱ የቤት ኪራይ እንደሆነም በንኡስ ቁጥር /መ/ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ የኪራይ ገንዘብ እንደሆነ ከላይ በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2024 ለክርክሩ አወሳሰን የሚጠቀስ ወይም አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል በውል ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የለም፡፡ ይህም ሆኖ ግን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚያስችል ምክንያት አለው፡፡ ቤቱን ያለዋጋ ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡ ይህን የመሠለ ግንኙነት የሚገዛው ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነት እና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በሚል በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 በምዕራፍ 2 ሥር ባሉት ድንጋጌዎች ነው፡፡ የሌላ ሰው ሐብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አለአግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠን ለባለሐብቱ ኪሣራ መክፍል እንዳለበት ከፍ ሲል በተጠቀሰው በምዕራፍ 2 ሥር በሚገኘው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2162 ተመልክቶአል፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ተጠሪዎች የአመልካች ንብረት በሆነው ቤት አልተገለገልንም የሚል ክርክር የላቸውም፡፡ አመልካች አስልቶ ባቀረበው የገንዘብ መጠንም ተቃውሞ አላነሱም የገንዘብ መጠኑ የተሰላው የንግድ ሥራ የሚካሄድባቸው ቤቶች ለሌላ ሰው በንግድ ሽያጭ ውል ሲተላለፉ ኪራይ ለመተመን በኤጀንሲው በወጣው መመሪያ መሠረት ነው፡፡ ይህም ማለት ቤቱ በተጠሪዎች በመያዙ ምክንያት አመልካች የወሉን ገቢ ነው የጠየቀው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በቤቱ መገልገላቸው እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች ቤቱን ባለው መመሪያ መሠረት አከራይቶ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ገንዘብ ያክል የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታዎች ሣያገናዝቡ ሕጉን ተከትለው ጉዳዩን ሣይመረምሩ በመወሰናቸው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 130183 ሐምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 84627 ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 138,122.19 /አንድ መቶ ሠላሣ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከአሥራ ዘጠኝ ሣንቲም/ ለአመልካች በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 38117

ሐምሌ 9 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ብርሃኑ ፈይሳ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ናይል ኢንሹራንስ /አ.ማ/

2. አቶ ሰለሞን አህመድ በሌሉበት ታይቷል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ በመዝገብ ቁጥር 15427 ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 5984 መጋቢት 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በማመልከታቸው ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ንበረትነቱ የአንደኛው ተጠሪ የሆነ ሱዙኪ ቪታራ መኪና በሁለተኛው ተጠሪ በማሽከርከር ላይ እያለ የካቲት 6 ቀን 1996 ዓ.ም ከቀኑ በግምት ስድስት ሰዓት ሲሆን በአንጉለላናጠራ ወረዳ መኪ. ከተማ ከትምህርት ቤት ፊት ለፊት መንገዱን በመሳት የአስራአንድ ዓመት ታዳጊ ወጣት የሆነውን ልጄን ዮሐንስ ብርሃኑን በመግጨት የሞት አደጋ አድርሶበታል፡፡ በልጄ መሞት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰብኝ ሲሆን ልጄ አስራ ስምንት ዓመት ከሞላው በኋላ ለእኔ ሊያደርግልኝ የነበረ ድጋፍ እንክብካቤና የገንዘብ እርዳታ ቀርቶብኛል፡፡ ስለዚህ ታዳጊ ወጣት ብርሃኑ ፈይሳ ቢኖር ኖሮ እድሜው አካለ መጠን ሲደርስ ሊያደርግልኝ የሚችለው ድጋፍ እንክብካቤና የገንዘብ ድጋፍ የቀረብኝ በመሆኑ አንደኛ ተከሳሽ /ተጠሪ/ የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ሁለተኛው ተጠሪ /ተከሳሽ/ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ዩሐንስ ብርሃኑን ለሞት የዳረገ በመሆኑ ብር 76,800 /ሰባ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ብር/ ካሣ እንዲከፍሉኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው በተናጠል የመከላከያ መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በህፃኑ መሞት ምክንያት አመልካች በክሱ የገለፁትን ያህል ወደፊት የሚገኝ ጥቅም የቀረባቸው መሆኑን በማረጋገጥ አላቀረቡም፡፡ ሟች ህፃን ብርሃኑ ፈይሳ ራሱን በመርዳት ለአባቱ



www.chilot.me

እገዛ ማድረግ የሚችል ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለም፡፡ ስለዚህ ከሳሽ /አመልካች/ ለደረሰባቸው የህሊና ጉዳት የሞራል ካሣ ከሚጠይቁ በስተቀር የቀረባቸው ጥቅም ስለመኖሩ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ጥያቄአቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ህፃን ብርሃኑ ፈይሳ ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ አላፊነት አለባቸው በማለት ኃላፊነቱን በሚመለከት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የካሣውን መጠን በተመለከተ ከሳሽ /አመልካች/ በልጃቸው መሞት ምክንያት የቀረባቸው ጥቅም ያለ መሆኑንና ለወደፊቱም የሚቀርባቸው ጥቅም ስለመኖሩ ያላረጋገጡ ስለሆነ ጥያቄአቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ በአደጋው ምክንያት ልጃቸው በመሞቱ ለደረሰባቸው የህሊና ጉዳት ካሣ ብር 800 /ስምንት መቶ ብር/ አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም አሻሽሎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ልጄ ብርሃኑ ፈይሳ በደረሰበት የመኪና አደጋ በመሞቱ ልጄን ለማሳደግና ለማስተማር ያወጣሁት ወጭ ፍሬ አልባ ከመሆኑ በተጨማሪ ከትምህርት ቤት መልስ ያደርግልኝ የነበረው እገዛና ይሰጠኝ የነበረው ግልጋሎት ተቋርጦብኛል፡፡ እኔ ሚች ታዳጊ ወጣት ብርሃኑ ፈይሳ ከትምህርት ቤት መልስ ከብቶችን በመንከባከብና በሌሎች የእርሻ ሥራዎች የሚያደርግልኝን እገዛ ከሌላ ሰው ለማግኘት በቀን አስር ብር /10 ብር/ እከፍላለሁ፡፡ ልጄ በህይወት ቢኖር ኖሮ በእውቀቱና በጉልበቱ ሠርቶ ሊያገኝ የሚችለው ገቢ እየጨመረ እንደሚሄድና ሌላ የሌለኝ በመሆኑ በእሱ መሞት ምክንያት ከፍተኛ ችግርና ኪሣራ እንደሚገጥመኝ የታወቀ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 559/2000 ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የሚገባው የመድን ዋስትና መነሻው ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን መነሻ በማድረግ አለመወሰናቸውና በህፃን ብርሃኑ ፈይሳ መሞት ምክንያት የደረሰብህና ለወደፊትም የሚደርስብህ ጉዳት የለም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ሁለተኛ ተጠሪ መጥሪያው በፍርድ ቤት ቅጥር ጊቢ ተለጥፎ ያልቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ ተጠሪዎች በሌሉበት እንደሚታይ ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ህፃን ብርሃኑ ፈይሳ በመሞቱ የደረሰባቸው እርግጠኛ ጉዳት ያለ መሆኑንና ህፃን ብርሃኑ ፈይሳ ለሌላ ሰው የሚከፍሉትን በቀን የአስር ብር ወጭ ይሸፍንላቸው እንደነበር ወደፊትም ያለጧሪ መቅረታቸው ራሱን የቻለ ጉዳት እንደሆነ በቃል ክርክር አስረድተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች በጽሁፍና በቃል ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች እድሜው አስራ አንድ የሆነው ልጃቸው የሞት አደጋ ስለደረሰበት የደረሰባቸው እርግጠኛ ጉዳትና የቀረባቸው ጥቅም አለ ወይስ የለም? አመልካች በህፃኑ መሞት ምክንያት ወደፊት ሊያገኙ ይችሉ የነበሩት ጥቅም ቀርቶባቸዋል ወይስ አልቀረባቸውም? የሚሉት ነጥቦች የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ አርሶ አደር መሆናቸውን ከመዝገቡ ውስጥ ያሉት ፍሬ ጉዳዮች ያሳያሉ፡፡ በእርሻ ሥራ ውስጥ ሚች የሚያደርግላቸው እገዛና የሚሰጣቸው ግልጋሎት እንደነበር ተጠሪዎች በግልጽ ክደው



www.chilot.me

አልተከራከሩም፡፡ ይኸም ተጠሪዎች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234/1/ ሠ መሠረት በአመልካች በኩል የተነሱትን ነጥቦች እንዳመኑ የሚያስቆጥር ነው፡፡ ሟች ለአመልካች ከትምህርት ቤት ሲመለስና በእረፍት ቀናት የተለያዩ አገልግሎቶች እገዛ ያደርግላቸው የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ በሟች መሞት ምክንያት የደረሰበት ጉዳት የለም ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የአስራ አንድ አመት ልጃቸው በደረሰበት የመኪና አደጋ በመሞቱ ልጃቸው ወደፊት የሚሰጣቸው የጉልበትና ሌሎች እገዛዎች የተቋረጠ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች የአስራ አንድ ዓመት ልጃቸው በደረሰበት የመኪና አደጋ በመሞቱና ከልጃቸው ያገኙት የነበሩት የእርሻ ሥራ ድጋፍና እገዛ ተቋርጦባቸዋል፡፡ አመልካች ይህንን እገዛ ወደፊት ሊያገኙ የሚችሉ የነበረ ቢሆንም ወደፊት ከልጃቸው ሊያገኙት የሚችሉት እገዛና ድጋፍ ተቋርጦባቸዋል፡፡

ስለዚህ አመልካች የካሣ ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2090 እና በፍታብሐር ሕግ ቁጥር 2091 የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የካሣው መጠንም መወሰን ያለበት አመልካች ልጃቸው ቢኖር ሊያገኙት የሚችሉትን ጥቅም መሠረት በማድረግ ሳይሆን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2095 ንዑስ አንቀጽ 2ን መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች የደረሰባቸውንና ወደፊት ሊደርስባቸው የሚችለውን እርግጠኛ የጉዳት መጠን ለማረጋገጥ ባይቻልም እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ዳኞች ፍትህንና ርትዕን መሠረት በመድረግ እንደሚወስኑ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2092/1/ የሚደነግግ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በዚህ ድንጋጌ መሠረት የአመልካችን ጥያቄ ተቀብለው ውሣኔ አለመስጠታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የሞራል ካሣ ብር 800 /ስምንት መቶ ብር/ ብቻ ይከፈላቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

የካሣውን መጠን በተመለከተ ርትዕና ፍትህን መሠረት በማድረግ እንዲወስኑ ጉዳዩ ለሥር ፍርድ ቤት ቢመለስ የሚያስከተለውን ወጭና በአመልካች ላይ የሚደርሰውን መጉላላት ታሳቢ በማድረግ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2092/2/ መሠረት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠዎች የሥር ፍርድ ቤት የወሰነውን የሞራል ካሣ 800 እና በዚህ ፍርድ ቤት የተወሰነውን ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ/ በድምሩ 12,800 /አስራ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ይክፈሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/መ



www.chilot.me

# አፈፃፀም



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48042

ጥቅምት 3 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ዓልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ጉና ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ - ጠበቃ ጥላዬ ተገኝ ቀረበ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. ቡሬ ባጉና የማዕድን ውሃ ፋብሪካ

2. ሞሃ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ አ/ማ - ጠበቃ ተፈራ ደንበል - ቀረበ፡፡

3. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ታምራት አባተ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአፈፃፀም ሂደት የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የአፈፃፀም መዝገቡ የተከፈተው የአሁኑ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ለማስፈፀም ነው፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ክርክሩ ውስጥ የገቡት የአፈጻጸም ሂደቱ የእኛን መብት ነክቶአል በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው አመልካች በፍርድ ባለመብትነቱ በ1ኛ ተጠሪ ፋብሪካ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ አሰጥቶ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፋብሪካው የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በ1ኛ ተጠሪ ላይ ላሰጠው ውሳኔ ማስፈጸሚያነትይውል ዘንድ በፋብሪካው ላይ የሐራጅ ማስታወቂያ አስቀድሞ አውጥቶ እንደነበር እና በዚህ ጨረታም 3ኛ ተጠሪ ተወዳድሮ በማሸነፍ ፋብሪካውን እንደገዛ፣ በመቀጠልም 3ኛ ተጠሪ ፋብሪካውን ለ2ኛ ተጠሪ እንደሸጠው፣ 2ኛ ተጠሪም ዋጋውን ከመክፈሉም በላይ፣ ፋብሪካውን በስሙ አስመዝግቦ ባለቤት እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም እነዚህን ሁኔታዎች በተጨባጭ ካረጋገጠ በኋላ፣ አመልካች የ1ኛ ተጠሪ ፋብሪካ ነው በማለት አሰጥቶት የነበረውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲቋረጥ ወስኖአል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2001 ዓ.ም. በጻፈው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ/ትዕዛዝ/ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ አቤቱታ አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ክርክሩን

ሰምተናል፡፡ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የቀረቡት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሲሆኑ፣ 1ኛ ተጠሪ በጥሪው መሠረት ባለመቅረቡ ክርክሩ የተሰማው በሌለበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ለወደፊቱ የሚሰጥ ፍርድን ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ለዋስትና ሲባል የተከበረ ንብረት በሌላ እዳ ምክንያት በተሸጠ ጊዜ ቀደም ሲል ንብረቱን ያስከበረው ወገን የሚኖረው መብት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ አግባብነት ካለው ሕግ አኳያ ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራቀኝ ወገኖች በዚህ ረገድ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ /ትዕዛዝ/ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ፋብሪካው የተሸጠው ፍ/ቤት በሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረት ነው፡፡ በወቅቱ የፍርድ ባለመብት የነበረው ግብር አስገቢ የሆነው የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ወይም መሥሪያ ቤት ነው፡፡ አመልካች ንብረቱን አስከብሬ /በፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ አሰጥቼ/ ነበር የሚለው ፋብሪካው ከመሸጡ በፊት ነው፡፡ ሆኖም ከፋብሪካው ይፈለግ የነበረው የግብር ዕዳ በመሆኑ እና የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ከማናቸውም ሌሎች ባለዕዳዎች የቀድምትነት መብት እንዳለው በገቢ ግብር አዋጅ ቁ. 286/1994 አንቀጽ 80/1/ በመደንገጉ ፋብሪካው የግብር ዕዳውን ለመክፈል ሲባል መሸጡ ተገቢ ነው፡፡ አመልካችም በዚህ ጊዜ የነበረው መብት ከሺያጩ ገንዘብ ላይ ተራፊ ካለ መብቱን አስረድቶ መውሰድ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ፋብሪካውን የመከተል ወይም ከገዛው ወገን ላይ ወስዶ ማሸጥ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ፋብሪካውን የገዛው ከ3ኛ ተጠሪ ላይ ነው፡፡ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በግብር ዕዳው ምክንያት በወጣው ጨረታ ተወዳድሮ በማሸነፍ ፋብሪካውን ገዝቶአል፡፡ በዚህም የፋብሪካው ባለቤት ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ መልክ ያገኘውን የባለቤትነት መብት መሠረት በማድረግም ነው ፋብሪካውን ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠው፡፡ በመሆኑም አመልካች በ3ኛ ተጠሪ ላይ ያልነበረውን መብት በ2ኛ ተጠሪ ላይ ሊኖረው አይችልም፡፡ ሲጠቃለል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር በዚህ ረገድ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.51946 ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ.45060 ግንቦት 21 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ-ሥ ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53943

ኀዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1. ወ/ሮ አስካለ ደሣለኝ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ብዙነሽ ደሣለኝ - ቀረቡ

3. አቶ ደረጃ ደሣለኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. ወ/ሮ የትምወርቅ ታደሰ - በሌሉበት ይታያል

2. አቶ በድሩ የሱፍ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች የፍርድ ባለእዳዎች (የአፈፃፀም ተከሳሾች) አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት (የአፈፃፀም) ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የወረዳው ፍርድ ቤት ባወጣው የሀራጅ ማስታወቂያ መሰረት በጨረታ በመካፈል በብር 32,000 (ሰላሣ ሁለት ሺ ብር) አሸናፊ በመሆን ቤት ገዝቷል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት ከቤቱ ሽያጭ ዋጋ የአንደኛ ተጠሪ ድርሻ 16,100(አስራ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ብር) መሆኑንና አንደኛ ተጠሪ ድርሻዋን እንዲከፍላት አድርጓል፡፡ ቀሪው ብር 16,100(አስራ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ብር) የአመልካቾች ድርሻ መሆኑንና አመልካቾች ድርሻቸውን ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በሞዴል 85 ተይዞ እንዲቆይና በጠየቁ ጊዜ እንዲሰጣቸው ትእዛዝ ሰጥቶ የአፈፃፀም መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚህ የአፈፃፀም ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከሐራጅ ሽያጩ በፊት ቤቱ ብር 40,000 መገመቱን አንደኛ ተጠሪ በእርቅ ብር 20,000 ለመውሰድ ተስማምታ እያለ በእርቅ ስምምነቱ መሰረት እንዲፈጸመላት የአፈፃፀም ክስ ስታቀርብ ቤቱ በብር 28,047.50(ሃያ ስምንት ሺ



www.chilot.me

አርባ ሰባት ብር ከሃምሣ ሣንቲም) ግምት መነሻ ለጨረታ እንዲቀርብና በብር 32,200 እንዲሸጥ ማድረጉ ስህተት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ ሽሮታል፡፡

በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት የቤቱ የጋራ ባለሐብት የሆነችው አንደኛ ተጠሪና ቤቱን በሐራጅ ተጫርቶ የገዛውና የቤቱን ሙሉ ዋጋ ለወረዳው ፍርድ ቤት ገቢ ያደረገው ሁለተኛው ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፍርድ ባለእዳዎች የአፈፃፀም ክሱና መጥሪያው ደርሷቸው በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ቤቱ በሃራጅ እንዲሸጥ የወሰነ መሆኑን በመግለጽ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ የወረዳው ፍርድ ቤት ትእዛዝ የሰጠው በእርቅ ውሣኔው መሰረት የማይፈጽሙበትን ምክንያት በቀነ ቀጠሮው ቀርበው ባለማስረዳታቸውና በሌሉበት የተሰጠውን ትእዛዝ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 ሣያስነሱ አዲስ ክርክር በይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ማቅረባቸው የሕግ ድጋፍ የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡ አመልካቾች መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አንደኛ ተጠሪና ሟች አባታችን የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት እንድናካፍላት አንደኛ ተጠሪ ክስ አቅርባ ቤቱ በብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ ተገምቶ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ልንከፍላት በሽማግሌ ታርቀን እርቁ በፍርድ ቤት ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ያቀረበችው የአፈፃፀም ክስና መጥሪያ ሣይደርሰን በብር 28,047.50 ለሐራጅ ቀርቦ በብር 32,200 መሸጡ ተገቢነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ሐራጅ በሚከናወንበት ወቅት ቤቱን ለማስቀረት ጠይቀን በወረዳው ፍርድ ቤት ተከልክለናል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሐራጅ ሽያጩ የፍትሐብሔር የሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎችን ያልተከተለ መሆኑን በማረጋገጥ የወረዳውን ፍርድ ቤት ትእዛዝ በመሻር የሰጠውን ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ መጥሪያው በፍርድ ቤት ግቢ ተለጥፎ ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካቾች ለወረዳው ፍርድ ቤት በፍርድ ቤት በፀደቀው የእርቅ ስምምነት መሰረት የማይፈጽሙበትን ምክንያት እንዲያስረዱ በተሰጠው ቀነ ቀጠሮ ቀርበው ባለማስረዳታቸውና በሂደቱም ሐራጁን ለማስቆም ወይም ለማሳገድ ያደረጉት እንቅስቃሴ ሣይኖር በሕጉ መሰረት ተጫርቼ ከገዛሁና ሙሉ ዋጋውን ከከፈልኩ በኋላ በሥር ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን ክርክር በማንሣት ሐራጁ እንዲሰረዝ የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ ድጋፍና መሰረት የለውም ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 ለአፈፃፀም ክርክር ተፈፃሚነት እንዳለው በመቁጠር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር የቀረበ መሆኑን በመገንዘብና የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ የሚሻርበት ህጋዊ ምክንያት አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡



www.chilot.me

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾችና አንደኛ ተጠሪ በመጀመሪያ በፍርድ ቤት የተከራከሩበት በኋላም የእርቅ ስምምነት አድርገውና በፍርድ ቤት አጸድቀው የጨረሱት መሰረታዊ ጉዳይ የአመልካቾች ወላጅ አባትና የአንደኛ ተጠሪ የጋራ ሐብት የሆነውና በሃራጅ የተሸጠው ቤት ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካቾች በገቡትና በፍርድ ቤት በፀደቀው የእርቅ ስምምነት መሰረት ብር 20,000(ሃያ ሺህ ብር) እንዲከፍሏት የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስና መጥሪያ አልደረሰንም በማለት አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የገለፁ ቢሆንም የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው ደርሷቸው በቀነ ቀጠሮው በፍርድ ቤት በፀደቀው የእርቅ ስምምነት መሰረት የማይፈጽሙበትን ምክንያት ባለማስረዳታቸው የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካቾች አባትና አንደኛ ተጠሪ የጋራ ሐብት የሆነው ቤት በሐራጅ እንዲሸጥ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች የፍርድ ቤቱ መጥሪያና አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ የደረሳቸው መሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተረጋገጠና በውሣኔውም በግልጽ ያሰፈረው በመሆኑ አመልካቾች የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው አልደረሰንም በማለት ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢና ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 መሰረት ማስነሳት ነበረባቸው የሚል ትችት በውሣኔው ውስጥ አስፍሯል፡፡ የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው ደርሶት የፍርድ ባለእዳው ሣይቀርብ በሚቀርበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ሥርአት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 70/ሀ/ ድንጋጌን መሰረት የሚያደርግ አይደለም፡፡ ስለሆነም የፍርድ ባለእዳው ባለመቅረቡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 መሰረት ለማስነሣት የሚቻልበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለፍታብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 በአፈፃፀም ክርክር የፍርድ ባለእዳው በሌለበት የተሰጠውን ትእዛዝ ለማስነሣት እንደሚያገለግል በመቁጠር የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 78ን አላግባብ የጠቀሰና የተረጐመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአፈፃፀም ክርክር ስለሚመራበት ሥርአት የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ስንመለከት የአፈፃፀም ክስ ማመልከቻውና የፍርድ ቤቱ መጥሪያ የደረሰው የአፈፃፀም ተከሳሽ ወይም የፍርድ ባለእዳ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ቀነ ቀጠሮ በመቅረብ ፍርዱን ፈጽሞ ከሆነ ፍርዱን መፈፀሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ወይም ፍርዱን የማይፈጽምበት ምክንያት ካለው ይህንኑ ምክንያቱን ለፍርድ ቤቱ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ የፍርድ ባለእዳው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ ከላይ በተገለፀው መንገድ ካላስረዳ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም አስፈላጊ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 386/2/ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስና መጥሪያ ከደረሳቸው በኋላ አመልካቾች ፍርድ ቤቱ በያዘው ቀነ ቀጠሮ ያልቀረቡ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካቾች አባትና የአንደኛ ተጠሪ የጋራ ሐብት የሆነው ቤት በሐራጅ ተሰጦ አንደኛ ተጠሪ ድሻዋን እንድትወስድ የሰጠው ትእዛዝ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 386/2/ ንመሰረት ያደረገና ጉድለት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ለፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 የተሣሣተ ትርጉም የሰጡ ቢሆንም ስህተቱ በውጤት ደረጃ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የደረሱበትን መደምደሚያ ውሣኔ ሊያስለውጥ የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት አይደለም፡፡



www.chilot.me

አመልካቾች የቤቱ በሐራጅ መሸጥ የቤት ግምትና ሌሎች ነጥቦችን በማንሣት የወረዳው ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት በመቅረብ አልተከራከሩም፡፡ አመልካቾች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የእርቅ ስምምነት መሰረት የማይፈጽሙበትን ምክንያት በቀነ ቀጠሮው ቀርበው አላስረዱም የወረዳው ፍርድ ቤት ቤቱ በባለሙያ ተገምቶ ለጨረታ እንዲቀርብ ማድረጉ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 423ና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካቾች የጨረታው ሒደት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 445 የተደነገጉ ተግባራት የተፈፀሙ መሆኑን ያላስረዱ በመሆኑ የእርቅ ስምምነት ያደረግንበት የቤት ዋጋ ቤቱ በሐራጅ ለሁለተኛ ተጠሪ ከተሸጠበት የበለጠ ነበር የሚል ምክንያት በማቅረብ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ በማጽናት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማጽደቁ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 40945

ጥር 13 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ኮሎኔል ግርማ ኃይለሥላሴ - ወኪል ስርጉት በላይ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ አስማማው መንግሥቱ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሁለት የፍርድ ባለመብቶች መካከል አንዱ የፍርድ ባለእዳን ንብረት ቀድሞ ተረክቧል ሊባል የሚችልበትን የሥነ ሥርዓት አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በአስከፈቱት የአፈፃፀም መዝገብ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻና ይዘትም የሚከተለው ነው፡፡ አመልካች አቶ ፍስሐ ወረታ የተባሉት ግለሰብ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አ.አ ቅርንጫፍ ለከባድ የጭነት መኪና መግዣ ብር 291,100.00/ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር/ ሲበደሩ ዋስ በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ በድሮው አጠራር ወረዳ 16 ቀበሌ 12 / ባሁኑ አጠራር የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14/ ክልል ውስጥ የሚገኝ ቪላ ቤታቸውን በመያዣ ሰጥተው የነበረ ሲሆን ዋናው ተበዳሪ የብድር ገንዘቡን መክፈል ባለመቻላቸው ባንኩ ከአሁኑ አመልካች የያዘውን መያዣ በመሸጥ አመልካች የዋናውን ተበዳሪ እዳ ዋናውን ገንዘብ ከእነ ወለዱ ጨምረው ብር 316,300.00 /ሶስት መቶ አስራ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ብር/ ለባንኩ ከፍለዋል፣ ባንኩም ይህንኑ አረጋግጦ ለአመልካች ደረሰኝ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች በአቶ ፍስሐ ወረታ ላይ በዋስትናቸው የከፈሉትን ገንዘብ እንዲተኩላቸው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ለባንኩ የከፈሉትን ገንዘብ ዋናው ተበዳሪ እንዲተካላቸው ፍርድ አግኝተዋል፡፡ ይህንኑ ፍርድ መሠረት በማድረግ የአፈፃፀም መዝገብ ከፍተው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መመልከት ጀምሮ የፍርድ ባለእዳ የሆኑትን ግለሰብ /አቶ ፍስሐ ወረታ/ እንደፍርዱ እንዲፈጽሙ፣ ወይም የማይፈጽሙበትን ምክንያት ካለ ይህንኑ እንዲያስረዱ ተደርጎ ባለእዳው ለአመልካች ገንዘቡን ሊተኩላቸው ወይም ንብረት ካለ እንዲጠቀሙ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የአሁኑ አመልካች የአቶ ፍስሐ ወረታን ንብረት አፈላልገው አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት እንዲገልፁ ተደርጎ አመልካች የፍርድ ባለእዳ ባለቤት በሆኑት ወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ስም የተገዛ ቤት ነው የሚሉትን ለፍርድ ቤቱ ገልፀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም አመልካች የጠቆሙት ቤት በወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ስም የሚታወቅ መሆኑን የሚመለከተው አካል አጣርቶ ለፍርድ ቤቱ ውጤቱን እንዲልክ ፍርድ ቤቱ



www.chilot.me

ትእዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩ ይመለከተዋል የተባለው የየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19 አስተዳደር ጽ/ቤት ቤቱ በእርሱ በኩል የማይታወቅና ማህደር የሌለው በመሆኑ እንደፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ለመፈፀም የማይችል መሆኑን ገልጿል፡፡ የአሁኑ አመልካች ቤቱ የፍርድ ባለእዳው ባለቤት ለመሆኑ ማስረጃ አለኝ በማለትም ግንቦት 11 ቀን 1994 ዓ.ም ተደርጓል ያሉትን የሽያጭ ውል አቅርበዋል፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መመርመሮ አለ የተባለው የሽያጭ ውል በሕጉ አግባብ የተደረገ አይደለም፣ የባለእዳው ባለቤት በሻጮች ስም ተተክተው የተመዘገቡና ባለሀብት ስለመሆናቸው አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አለ በተባለው ቤት አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም ሲል የአመልካችን አፈፃፀም የፍርድ ባለእዳ ንብረትን አፈላልገው ባቀረቡ ጊዜ የማንቀሣቀስ መብታቸውን በመጠበቅ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው አመልካችና አቶ ፍስሐ ወረታ ከተከራከሩ በሁዋላ ቤቱ የጨረቃ ቤት በመሆኑ ብቻ በሐራጅ ከማሸጥ የሚከለክል ሕግ የለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ትእዛዝ ሽሮ አፈፃፀሙ አመልካች አለ ባሉት የአቶ ፍስሐ ወረታ ባለቤት ቤት ላይ እንዲቀጥል በመ/ቁጥር 55873 ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በሁዋላ የአሁኑ ተጠሪ አፈፃፀሙ ይቀጥልበት የተባለው የወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ቤት ከተጠሪ በነበረባቸውና በፍርድ ቤት በተረጋገጠው እዳ ምክንያት የተረከቡትና የርክክቡ ስምምነትም በፍርድ ቤት የተመዘገበበት ነው በማለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ እንዲሰርዝላቸው የተቃውሞ አቤቱታቸውን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበው ከአሁኑ አመልካች ጋር እንዲከራከሩ ከተደረገ በሁዋላ ተጠሪ ከአመልካች ቀድመው አከራካሪውን ቤት በእዳ ምክንያት ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል የተረከቡት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የቀድሞውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360/2/ መሠረት በመሠረዝ ታህሣሥ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ ሰጥቶታል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚሁ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈፃፀሙ በቤቱ ሊቀጥል አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

በበኩላችን አመልካች ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈው ማመልከቻ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መሠረት በማድረግ ለተጠሪ ጥሪ አድርገን ክርክሩን በፅሑፍ ሰምተናል፣ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የተባሉትን የበታች ፍርድ ቤቶችን ዋና መዛግብትም በማስቀረብ የክርክሩን አጠቃላይ ሂደት ተመልክተናል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች የፍርድ ባለእዳ ባለቤት ስለመግዛታቸው በማረጋገጥ አፈፃፀሙ በቤቱ እንዲቀጥል ያቀረቡት አቤቱታ የአሁኑ ተጠሪ በቤቱ ላይ ቅድሚያ መብት አላቸው ተብሎ ውድቅ የተደረገው ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 7405 በሆነው መጋቢት 09 ቀን 1994 ዓ.ም ክስ የመሠረቱ ሲሆን ሐምሌ 12 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሊፈፀም የሚችል ፍርድ በአቶ ፍስሐ ወረታ ላይ ያስፈረዱ መሆኑን፣ ይኸው ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ ማመልከቻ አቅርበው የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 23051 ማስከፈታቸውን፣ አፈፃፀሙን፣ የያዘው ፍርድ ቤትም ለፍርድ ባለእዳ እንደፍርዱ እንዲፈጽሙ፣ የማይፈጽሙበት ምክንያት ካለም ቀርበው እንዲያስረዱ ትእዛዝ ሰጥቶ የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ፍስሐ ወረታ ፍ/ቤት ቀርበው እንደፍርዱ ለመፈፀም የማይችሉ መሆኑን ከመግለጽ ውጭ እንደፍርዱ ላለመፈፀምያቀረቡት ምክንያት የሌለ

መሆኑን ፍ/ቤቱ ገልጾ አፈፃፀሙ ከቀጠለ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች የፍርድ ባለእዳ ንብረትን በማፈላለግ አሁን አከራካሪ የሆነው ንብረት እንዲከበርላቸው አቤቱታ አቅርበው አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤትም የፍርድ ባለመብት የሆኑት የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር የሌለው የፍርድ ባለእዳ ባለቤት በሆኑት የወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ስም የሚገኝ ቤት ተከብሮ እንዲቆይ በማለት ጥቅምት 08 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቶ እንደትእዛዙ እንዲፈጽም ለክፍሉ ቀበሌ ትእዛዙን ሲልክ የክፍሉ ቀበሌ ቤቱ የለም በማለት ጥቅምት 16 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ ገልጿል፡፡ ፍርድ ቤቱን የፍርድ ባለመብት የሆኑት የአሁኑ አመልካች ማስረጃ ካላቸው እንዲያቀርቡ እና የፍርድ ባለእዳውም አስተያየት እንዲሰጡበት ከአደረገ በሁዋላ የፍርድ ባለመብት በቤቱ ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ያቀረቡት አቤቱታ ቤቱ የጨረቃ ቤት ነው ስለተባለ ተቀባይነት የለውም በማለት ሚያዚያ 17 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ባለመብት ሁኚበታለሁ የሚሉበት መንገድ የመነጨው በሁለት መዛግብት ሲሆን አንዱ፡- በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 43327 መስከረም 20 ቀን 1997 ዓ.ም በወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ላይ በመሠረቱት ክስ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ሚያዚያ 09 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሣሽ የነበሩት ወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ለአሁኑ ተጠሪ ብር 23,752.55 /ሐያ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሣ ሁለት ብር ከአምሣ አምስት ሣንቲም/ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ አስወስነው ይኸው ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ሰኔ 09 ቀን 1998 ዓ.ም የተፃፈ የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው የአፈፃፀሙ ጉዳይ በፌዴራሉ የመ/ደ/ፍ/ቤት መ/ቁጥር 71496 በሆነው ተከፍቶ አሁን እያከራከረ ባለው ቤትም ተጠሪ የእግድ ትእዛዝ ታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በፍርድ ቤት አሰጥተው ጉዳዩ እየታየ ባለበት ሂደት ግራ ቀኙ ወገኖች ጉዳዩን ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም አቅርበው ፍርድ ቤቱ በእርቅ ስምምነቱ መሠረት አፈፃፀሙ ማለቁን ተገንዝቤአለሁ በማለት የአፈፃፀሙን መዝገብ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ዘግቶታል፡፡ ሌላው ተጠሪ በወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ላይ ፍርድ ያገኙ ስለመሆኑ ያሣያል የተባለው ጉዳይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 85943 የታየው ሲሆን ተጠሪ ክስ የመሠረቱት መጋቢት 24 ቀን 1999 ዓ.ም ሁኖ ጉዳዩ ሲታይ ቆይቶ ግራ ቀኙ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ጉዳዩን በስምምነት ጨርሰናል በማለት ስምምነቱ በፍርድ ቤቱ እንዲፀድቅላቸው አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም በስምምነቱ መሠረት ወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ለአሁኑ ተጠሪ ብር 52,769.73 /ሃምሣ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ስልሣ ጠዘኝ ብር ከሰባ ሶስት ሣንቲም/ በመክፈል መዝገቡ እንዲዘጋላቸው ግራ ቀኙ መስማማታቸውን ገልፀው አቤቱታ አቅርበዋል፣ ስምምነቱም ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ተረጋግጧል የሚል ምክንያት በመያዝ ስምምነቱን በማጽደቅ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ጋር አድርጌአለሁ የሚሉት የእርቅ ስምምነት ቤቱን ለሁሉም እዳዎች ስለመረከቤ ያረጋግጣል የሚሉት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ከላይ ከተጠቀሱት መዛግብት በፍሬ ነገር ደረጃ በተረጋገጡት ነጥቦች መሠረት ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

በመሠረቱ ፍርድ እንደፍርዱ መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 378 እና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሣያል፡፡ በአንድ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ አፈፃፀሙን የቀጠሉ ተራ የፍርድ ባለመብቶች ካሉም ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 403 ድንጋጌ መሠረት ምላሽ ሊያገኝ እንደሚችል ሕጉ ያሣያል፡፡



www.chilot.me

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 85943 ተሰጠ የሚሉት ትእዛዝ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ጋር ያደረጉትን ስምምነት ለሕግ እና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን በማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ አጽድቆታል የሚሉት ሲሆን ፍርድ ቤቱ የመዘገበው ትእዛዝ የሚያሣየው ወ/ሮ አበበች ለአሁኑ ተጠሪ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ የከፈሉ መሆኑን እንጂ ለሚፈለግባቸው ገንዘብ አሁን እያከራከረ ያለውን ቤት ለማስረከብ ተስማምተው፣ ስምምነቱም ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም ተብሎ የተመዘገበ አለመሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በመ/ቁጥር 71496 ባስከፈቱት የአፈፃፀም መዝገብ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ትእዛዝም ቢሆን እርቁን የመዘገበ ሣይሆን አፈፃፀሙ በእርቅ መሠረት መፈፀሙ ተረጋግጧል በማለት የፍርድ አፈፃፀም መመሪያ የያዘውን አፈፃፀም ሂደት እንዲያቆም የተደረገበት ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው አሁን እያከራከረ ያለውና ባለሀብትነቱ የወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ስለመሆኑ የተረጋገጠውን ቤት ቅድሚያ ያስከበሩት የአሁኑ አመልካች መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በመ/ቁጥር 85943 ላይ በስር ፍርድ ቤት ባሰጡት ትእዛዝ ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል የሚፈልጉት ገንዘብ የተከፈላቸው መሆኑን መዘገቡ በግልጽ ያሣያል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በመ/ቁጥር 71496 የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ለመውሰድ ያደረጉት ጥረት ስለመኖሩ በማረጋገጥ ይህንኑ ያፀደቀ ሣይሆን አፈፃፀም መቋጨቱን ያረጋገጠበት ነው፡፡ በመ/ቁጥር 71496 የተከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ ሲሆን የሚያወሣውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የሚገኘውንና ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም በተጠሪና በወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል መካከል ተደረገ የተባለውን የእርቅ ስምምነት ሲሆን በመ/ቁጥር 85943 ለፍርድ ቤቱ ቀረበ የሚባለው ደግሞ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ስምምነት ሁኖ ወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ለተጠሪ እዳቸውን የከፈሉ መሆኑን የተረጋገጠበት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በእዳ ምክንያት ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ሙሉ በሙሉ ተረክቤአለሁ የሚሉት መክፈሉ በተረጋገጠበት ገንዘብ ጭምር በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ በሌላ አገላለጽ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ከአመልካች ቀድመው ወስደዋል ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ መክንያት የለም፡፡ ሌላው ተጠሪ በዚህ የሰበር ደረጃ የሚያቀርቡት ክርክር አከራካሪውን ቤት ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል በመረከብ ባሁኑ ጊዜ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሸጬአለሁ የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የክርክር ነጥብ በተጠሪ ሊነሣ የሚችልበት እና ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በአጠቃላይ አከራካሪው ቤት ላይ ተጠሪ ከአመልካች አስቀድመው በእዳ ምክንያት ወስደዋል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ በእያንዳንዱ መዝገብ ላይ ሲደረግ የነበረውን አጠቃላይ የክርክር ሂደት ከጊዜ ቅደም ተከተሉና በተለያዩ ጊዜአት ሲሰጡ የነበሩትን ትእዛዝ ይዘት በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ስለፍርድ አፈፃፀም የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 55873 ታህሣሥ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35155 ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23035 ሚያዚያ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ በዚህም መሠረት አፈፃፀሙን እንዲቀጥል የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታዝዟል፡፡ ይፃፍ፡፡



www.chilot.me

3. ተጠሪ ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል የሚፈልጉትን ገንዘብ ከመጠየቅ ይህ ፍርድ አያስቀርም ብለናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 62804

ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1- አቶ ብርሀን ገ/እግዚአብሔር

2- ወ/ሮ አልጋነሽ ገ/እግዚአብሔር

3- ወ/ሮ ዝማም ገ/እግዚአብሔር

4- ወ/ሮ ሙሉ ገ/እግዚአብሔር

5- ወ/ሮ አልማዝ ገ/እግዚአብሔር

6- ወ/ሪት ገነት ገ/እግዚአብሔር

7- የአቶ አበበ ገ/እግዚአብሔር ወራሾች /ወ/ሪት ትከሻዬ አበበ ና አቶ ዮሐንስ አበበ

} 1ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር ለተጠቀሱት ጠበቃ አቶ ደስታ በርሄ ቀረቡ

8- ወ/ሪት ሊንዳ ገ/እግዚአብሔር - ቀረቡ

9- ወ/ሮ ምፅላል ገ/እግዚአብሔር

10- ወ/ሮ ፅጌወይኒ ገ/እግዚአብሔር

11- አቶ ሀይሉ ገ/እግዚአብሔር

12- አቶ ግዛቸው ገ/እግዚአብሔር

} ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ቀረቡ

የተጠቀሱት ወኪል አንደኛ ተጠሪ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ለታይ ገ/ጊዮርጊስ ጠበቃ አቶ ደረጀ ወረቁ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡



www.chilot.me

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በቦሌ ክፍለ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 17 ቀበሌ 24 የቤት ቁጥር 166 ሥር የመኖሪያ ቤትና መጋዘን ያሉ ሲሆን መኖሪያ ቤቱ የአመልካቾች አውራሽና የተጠሪ የጋራ ሃብት መሆኑ በፍርድ የተወሰነ ሲሆን መጋዘኑ የአመልካቾች አውራሽ የግል ንብረት መሆኑ ተወስኗል፡፡

አመልካቾችና ተጠሪ የሚከራከሩት በግቢው ውስጥ የሚገኘው ባዶ ቦታ የመኖሪያ ቤቱ ነው ወይስ የመጋዘኑ ነው በሚለው ነጥብ ላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው የሥር ፍርድ ቤት የቦሌ ክፍለ ከተማ ቦታው በባለሙያ እንዲታይ ካደረገ በኋላ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ቦታ የሚጠቃለለው ወደ መኖሪያ ቤቱ መሆኑን ወይም ወደ መጋዘኑ መሆኑን ወይም መኖሪያ ቤቱና መጋዘኑ የየራሳቸው ይዞታ ካላቸው የይዞታቸውን ስፋት ምን ያህል መሆኑን ለይቶ የእስኬች ማብራሪያ እንዲልክ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ቦታ ለመጋዘን ይሁን ለመኖሪያ ቤቱ ለማሳወቅ የሚቸገር እንደሆነና ቀደም ሲል በነበረው ካርታ ይዞታው ተለይቶ ያልተቀመጠ መሆኑንና ለአመልካቾች አውራሽ 1973 ዓ.ም ቦታው የተሰጣቸው የመኖሪያ ቤት በመሥራት እንዲገለገሉበት መሆኑን በመግለፅ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረበለትን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ባዶ ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ እንዲጠቃለልና አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሠኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማብራሪያ መጠየቅ አልነበረበትም መጋዘኑ ኤል ሼፕ በመሆኑ ቦታውን ለአመልካቾች ማስረከብ ነበረበት፡፡ መጋዘኑ የተሠራው 1973 ዓ.ም ሲሆን የመኖሪያ ቤቱ የተሠራው 1978 ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ በመ.ቁ 723592 ባቀረቡት ክስ ቦታው የመጋዘኑ አካል መሆኑን በማመን ገልፀው እያለ በፍርዱ መሠረት ባዶ ቦታውን በእጅ ማስረከብ ሲገባው ከመኖሪያ ቤቱ ጋር እንዲጠቃለል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ህዳር 24 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በባለሙያ በኩል እንዲጣራ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ የህግ ስህተት የለበትም በመዝገብ ቁጥር 723592 የአጥር ግንባታ የተገነባበትን ግምት ከሚጠይቅ ውጭ ስለቦታ የቀረበ ክርክርና የተሰጠ ውሣኔ የለም፡፡ የአመልካቶች አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀመ መሆኑን የማያሣይ ከመሆኑም በላይ ዕውነታውን የሚያንፀባርቅ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች መጋቢት 17 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



www.chilot.me

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት የመኖሪያ ቤቱና መጋዘኑ ከተሠራበትና በአንድ ካርታ በተጠቃለለው ይዞታ ቦታ ላይ የሚገኘው ባዶ ቦታ የመኖሪያ ቤቱ ነው ወይስ የመጋዘኑ ነው በሚለው ነጥብ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ባዶ ቦታ በመጋዘኑ ሊጠቃለል እንደሚገባ ውሣኔ እንደተሰጠበት በማንሣት የሚከራከሩ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 30811 ውሣኔ የሰጠው መጋዘኑ የአመልካች አውራሽ የግል ንብረት መሆኑን እንጅ በግቢው የሚገኘው ባዶ ቦታ ከመጋዘኑ ጋር ሊጠቃለልና ለአመልካቾች ሊሰጥ የሚገባው መሆኑን አልወሰነም፡፡ በሌላ በኩል በመዝገብ ቁጥር 723592 ተጠሪ ከጋብቻ በኋላ አጥር በማጠር ወለል ሊሾ በማድረግ ያወጡትን ገንዘብ ጠይቀው ውሣኔ የተሰጠበት ሲሆን የባዶ ቦታ ክርክር አቅርበው የተወሰነ ውሣኔ የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ቦዶ ቦታ ከዚህ በፊት በፍርድ ያልተወሰነ በመሆኑ ፍርዱን በማስፈፀሙ ሂደት ቦታው መጠቃለል ያለበት ከመኖሪያ ቤቱ ጋር ነው ወይስ ከመጋዘኑ ጋር የሚለው ጥያቄ ሲነሳ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቦታውን በማየት ካርታውን በመመርመር መግለጫ እንዲሰጥበት አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ቦታው የመጋዘኑ ነው ወይም የመኖሪያ ቤቱ ነው ብሎ ለመለየት ያልተቻለና በካርታውም ላይ ያልተመለከተ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል የአመልካቾች አውራሽ በ1973 ዓ.ም ቦታውን የተመሩት ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት መሆኑን የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ያረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ ከመኖሪያ ቤቱ ጋር እንዲጠቃለል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የሚገምተውን ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያለው መሆኑን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 392 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ድንጋጌ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአመልካቾች አውራሽ ቦታውን የመኖሪያ ቤት ለመሥራት የተመሩት መሆኑን ከክፍሉ አስተዳደር የቀረበለትን ማረጋገጫ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ እንዲጠቃለል የሰጠውን ትዕዛዝ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማፅናቱ ስለፍርድ አፈፃፀም በተለይም የፍታብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ 392 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ የተሰጠና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

*የሰበር/መ/ቁ. 63754*

*ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም*

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ ዓለም ባህታ - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ ኑኑሽ ሽህምሎ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አመልካች ተሰጠ የተባለውን የፍርድ አፈጻጸም አደናቅፎአል በማለት የፌ/የመ/ደረጃ/ፍ/ቤት በአምስት ወር እስራት እንዲቀጣ መወሰኑና ይሄው ውሣኔ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ ቅሬታ ነው፡፡

አመልካች በተፈረደበት የፍርድ አፈጻጸም ማሰናከል ቅጣት ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ያለውን ታህሣስ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ቅሬታ ያመለከተ ሲሆን መሠረታዊ ፍሬ ሃሣቡ አመልካች አፈጻጸም በማሰናከል ከዚህ በፊት በ5 ወራት የእስራት ቅጣት የተቀጣ ሲሆን ይሄ ውሣኔ ይግባኝ ቀርቦበት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 73402 የተሻረ ሆኖ እያለ አዲስ ፍሬ ነገር ሣይኖር እንደገና በዚህ ጉዳይ ፍርድ አሰናክሏል በማለት ቅጣት መጣሉ ያለአግባብ ነው አመልካችም የፈጸሙት የማሰናከል ተግባር ባለመኖሩ እና አመልካቹ ላይ የተጣለውም ቅጣት የከበደ በመሆኑ የተሰጠው ቅጣት እንዲሻርልን በማለት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ በተጠሪ ጠበቃ በኩል በመጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡- ቀድሞ የተቀጣበት የፍርድ አፈጻጸም ማሰናከል ጉዳይ ከአሁን ጋር የማይገናኝ በመሆኑና በውሣኔ ያለቀ ጉዳይ የማይባል በመሆኑ ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የፍርድ ማሰናከል ተግባር ተፈጽሟል እና የተጣለበት ቅጣትም የከበደ ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም በዚህ ጉዳይ ላይ መፍትሄ ማግኘት ያለበት፡-



www.chilot.me

1. አመልካች የተቀጣበት የፍርድ አፈጻጸም የማሰናከል ኃላፊነት በፊት ከተቀጣበት ምክንያት የተለየ ተግባር በመፈጸም ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ጋር በማገናዘብ መታየት ያለበት በመሆኑ
2. የተፈጠረ የፍርድ ማሰናከል ተግባር አለ ወይስ የለም? እንዲሁም፡-
3. የተጣለው የእስራት ቅጣት አግባብነትን በመመልከት መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

በዚሁ መሠረት ወደ መጀመሪያው ጭብጥ ስንመለስ አሁን ለዚህ ክርክር መነሻ ከሆነው ቅጣት በፊት አመልካች በፍርድ ማሰናከል ተግባር ኃላፊ ተብለው በአምስት ወር እስራት የተቀጡ የነበርና ጉዳዩ በይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር 73402 የተሻረ መሆኑን ግራቀኙ አልተካካዱም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ቀድሞ ከተጣለው ቅጣት በኋላ አዲስ የማሰናከል ተግባር ስላልተፈጠረ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት አዲስ ኃላፊነት ሊጣል አይገባም በማለት የአመልካች ጠበቃ ሲከራከሩ በተጠሪ በኩል ደግሞ በቀድሞው የፍርድ ማሰናከል ተግባር ኃላፊ የተደረጉበት ምክንያት ከአሁኑ ጋር የተለየ በመሆኑ ጉዳዩ በውሣኔ የተቋጨ ነው ለማለት የማይችል ባለመሆኑና በሁለቱም ጊዜ ሊያዝ የሚገባው ጭብጥ የተለያየ በመሆኑ ውሣኔ ያገኘና የተቋጨ ጉዳይ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም የሚል ነው፡፡

አሁን እየቀረበ ካለው ክርክር አኳያ ጉዳዩን ስንመረምረው የቀድሞው የፍርድ ማሰናከል ኃላፊነት በአመልካች ላይ የተወሰነው ለፍርድ አፈጻጸም እንዲውል የታገደው የሰሌዳ ቁ. 3-27755 የሆነ መኪና አመልካች በቃለ መሀላ ስር ሆነው መኪናውን ገዝተው እንዳላቸው ከገለጸ በኋላ መኪናውን በወ/ሮ ደብሪቱ ውክልና ነው የገዛሁት በማለታቸው እንደሆነ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ያስረዳል፡፡ በአሁኑ ጉዳይ ግን በሌላ ችሎት ተጠይቀው ከላይ የተጠቀሰውን መኪና ከአቶ ተስፋዬ ሞላ የገዙት መሆኑን እንደገና የገለጸ ሲሆን በዚህ መሠረት እንዲፈጽሙ ሲጠየቁ ግዢውን አፍርሼያለሁ ያፈረስኩትም ስመንብረቱን ወደ ራሴ ስም ማዛወር ስላልቻልኩ ነው ከሻጭ ወኪል 100.000 /አንድ መቶ ሺህ/ ብር ተቀብዬ መኪናውን መልሼለታለሁ የተቀበልኩትንም ገንዘብ ተጠቅሜበታለሁ በማለት በማቅረቡ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ከዚህ መረዳት የሚቻለው አሁን ለቀረበው ጉዳይ አመልካች ገዝቶ የነበረውን መኪና የተሰጠው እግድ ሳይነሣ መኪናውን ለሻጭ በመመለስ የገዛበትን ገንዘብ መልሶ የተቀበለ ሲሆን ገንዘቡንም ተጠቅሜበታለሁ ማለቱ ከቀድሞ ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት ጭብጥ የሚያዝበት ባለመሆኑ ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል አይችልም ብለናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ በመኪናው ላይ የተላለፈው እግድ ሣይነሣ አመልካች መኪናውን ገዝቶ እያለ ስመ ንብረቱ ወደ እሱ ያለመዞሩን አጋጣሚ በመጠቀም መኪናውን ለሻጭ በመመለስ የገዛበትን ገንዘብ መቀበሉን ገልጿል፡፡ መልሶ በተቀበለው ገንዘብ ላይ አፈጻጸሙ እንዳይቀጥል /እንዳይከፍል/ ደግሞ ተጠቅሞበታል ወይም ገንዘቡ የለም ማለቱ የፍርድ ባለዕዳው ለአፈጻጸሙ የታገደውን መኪና ከማሸሹም በላይ ቢያንስ የተቀበለውን ገንዘብ እንኳ ለዕዳው አለማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 389/1/ /ሀ/ /ለ/ መሠረት ያለበቂ ምክንያት ፍርዱን ላለመፈጸም ከመንቀሣቀሱ በላይ ፍርዱ ያልተፈጸመው አመልካች ፍቃደኛ ባለመሆኑ ብቻ የተለያዩ መሰናክሎችን በመፍጠሩ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፍርዱን አፈጻጸም አላሰናከልኩም በማለት ያነሱት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡



www.chilot.me

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ 389 /1/ /ለ/ መሠረት እስከ 6 /ስድስት/ ወር ሊደርስ በሚችል እስራት ሊቀጣ እንደሚችል ስለሚደነግግ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት የጉዳዩን አጠቃላይ ሂደት በማመዛዘን በ 5 ወራት እስራት የቀጣው መሆኑ ሲታይ የከበደ ቅጣት ነው የሚያሰኝ ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች የፍርድ አፈጻጸም አደናቆፎአል በማለት የሰጡት የእስራት ቅጣት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ/ቁ. 89236 በቀን 26-01-2003 ዓ.ም እና የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 115299 በቀን 13-5-02 ዓ.ም በዋሉት ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች የፍርድ አፈጻጸም አደናቅፈዋል በማለት የተላለፈባቸው የ5 ወራት የእስራት ቅጣት በአግባቡ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ለሚመለከተው ይጻፍ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራቀኙ ላይ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡን ዘግተናል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 66988

ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ ቀደመ ተሾመ - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ** ፡- አቶ ኢብራሂም ሐመዱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምርን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 159867 በቀን 30/3/2002 የሰጠውን ፍርድ በአፋር ብ/ክ/መ/ የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና እንዲያስፈፅም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽምላቸው የአሁኑ የሰበር አመልካች የአፈፃፀም ክስ ሲያቀርቡ ከፍተኛው ፍ/ቤት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ ሂሳብ ሳይጣራ የተሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ለማስፈፀም ይቸገራል በማለት ባለመቀበል ፍርድ በመስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በማፅናቱ ነው፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካችም በሥር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱትም የቅሬታ ነጥብ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 152121 የተሰጠው ፍርድ የአፈፃፀም ተከሳሾችን መብትና ጥቅም የሚጐዳ ከሆነ በይግባኝ ወይም በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ በተቀመጠው መሠረት መቃወሚያዎችን በማቅረብ ስህተቱ እንዲታረም ከሚያደርጉ በስተቀር እንዲፈፀም የቀረበውን ፍርድ ሂሳብ ሳይጣራ የተሰጠ ፍርድ ነው በሚል በመተቸት ለማስፈፀም የሚያስቸግር ነው መባሉ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው የአሁኑ ተጠሪ /የሥር 2ኛ የአፈፃፀም ተከሳሽ/ በሰጡት መልስ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍርድ እና ትዕዛዝ ላይ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም የሥር ፍ/ቤቶች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ ባልተጣራና ባልተመረመረ ሂሳብ የተሰጠ በመሆኑ በውክልና አፈፃፀሙን ለመቀጠል የሚያስቸግር ነው ያሉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዞን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 371/1/ መሠረት ፍርድ የሚያስፈጽመው ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት ወይም ፍርዱን እንዲያስፈፅም የታዘዘ ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን እንዲያስፈፅም ለሌላ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሰጠ ጊዜም እንዲያስፈፅም የታዘዘው ፍርድ ቤት ስለ ፍርዱ ትክክለኛነት ወይም በግልባጮች ላይ ስለሰፈረው ነገር ሌላ መግለጫና ማብራሪያ ሳይጠይቅ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ማስፈፀም እንዳለበት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 373/2/ ይደነግጋል፡፡ ፍርድ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍ/ቤትም ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት ማረጋገጫ እንዲልክለት የሚጠይቀው የፍርዱ ወይም የትዕዛዙ ወይም የግልባጩ ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ካለው ብቻ ነው፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ፍርዱን እንዲያስፈፅም የታዘዘው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚህ በላይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 373/2/ ከተደነገገው ውጪ ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በአግባቡ ሂሳብ ሳይጣራና ሳይመረመር የተሰጠ ነው በማለት በመተቸት ማብራሪያ መጠየቁና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይኸንኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሥር የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈ/መ/ቁ 1917 በቀን 02/11/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2155 በቀን 21/6/2003 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የሥር የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠውን ፍርድ እንዲያስፈፅም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት እንዲያስፈፅም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ ክርክሩን መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64354

ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**:- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ - አልቀረቡም

**ተጠሪ**:- ወ/ሮ ኡልባሬ ሰማን - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የአፈጻጸም ክርክር ነው፡፡ የክርክሩ አመጣጥ አመልካች ከአቶ ሁሴን መሐመድ ጋር የነበረውን የብድር ውል አቶ ሁሴን መሐመድ በብድር ውሉ መሠረት ያልፈጸሙ መሆኑን ገልጾ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የብድር ውሉን በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቀርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል አቶ ሁሴን መሐመድ ብር 601154.55 /ስድስት መቶ አንድ ሺ አንድ መቶ ሀምሣ አራት ብር ከሀምሣ አምስት ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍሉ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህንን ፍርድ ለማስፈጸም የአፈጻጸም ክስ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ አቅርቧል፡፡ የአመልካች የአፈጻጸም ክስ የቀረበለት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሆነውና በአቶ ሁሴን መሐመድ ሚስት በወ/ሮ ከድጃ አወል ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቁጥሩ 425 የሆነ ቤት ተሽጦ ለፍርድ ማስፈጸሚያ እንዲሆን በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 59328 መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረቱ የሚገኝበት የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሻሸመኔ ከተማ በዲዳ ቦቄ ቀበሌ የሚገኘውንና ቁጥሩ 425 የሆነውን ቤት በመሸጥ ፍርዱን እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠረት በማድረግ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሻሸመኔ ከተማ በዲዳ ቦቄ ቀበሌ የሚገኘውና በወ/ሮ ከድጃ አወል ስም

ተመዝግቦ ያለውን ቁጥሩ 425 የሆነው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ሰጥቶ የሀራጅ ማስታወቂያ ወጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁን ተጠሪ የሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበትን ቤት ከወ/ሮ ከድጃ አወል ሀምሌ 6 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ ውል ገዝተው በእጃቸው አድርገው እየተጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽና የቤቱን የሀራጅ ሽያጭ በመቃወም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 መሠረት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ቤቱን የገዙት በመሆኑ ለፍርድ ማስፈጸሚያ ሊሸጥ አይገባውም በማለት ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቀረበ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በመሻር ቤቱ ተሸጦ ለፍርድ ማስፈጸሚያ ሊውል ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጠ፡፡

ተጠሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቀረቡ፡፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ሰምቶ ብይን የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍርዱን እንዲያስፈጽም በሰጠው የውክልና ስልጣን ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሰጠው ብይን የሚቆጠር በመሆኑ ይግባኝ መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሌለውን የይግባኝ ስልጣን በመጠቀም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ጥር 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 374 /1/ን በመተርጐም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 372 /ሐ/ ድንጋጌን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፍርዱን በውክልና የሚያስፈጽም ፍርድ ቤት የሚሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚኖረውን ውጤትና በትዕዛዝ ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ያገናዘበ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራክሮ ውሣኔ ሊሰጥበት የማይችለውን የተጠሪን ጣልቃገብነት ጥያቄ በመቀበል የሰጠው ውሣኔ ከስልጣኑ ወሰን ያለፈ ነው፡፡ ስለሆነም የውክልና ስልጣኑን በማለፍ የሰጠውን ትዕዛዝ በይግባኝ አይቶ የማረም ስልጣን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው በማለት ሚያዝያ 17 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ በአፈጻጸሙ ሂደት ያቀረቡትን የጣልቃ ገብነት ጥያቄ በመቀበል የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡



www.chilot.me

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ፍርድ ለማስፈጸም የዳኝነት ስልጣን ስላለው ፍርድ ቤትና ፍርድ የማስፈጸም መሠረታዊ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ፍርዱን ሌላ ፍርድ ቤት እንዲያስፈጽም ስለሚችልበት ሁኔታ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን በሰባተኛው መጽሀፍ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተሰጡትን ፍርዶች ስለማስፈጸም የሚደነግጉ የሥነ ሥርዓት ህጐች ተደንግገዋል፡፡ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ሰባተኛ መጽሐፍ ማለትም ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 371 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥዓርት ህግ ቁጥር 455 የተደነገጉትን የሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ግዛት የተሰጠን ፍርድ የማስፈጸም ስልጣን ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ወይም ፍርዱን እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት መሆኑን በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ፍርድ የሚያስፈጽመው ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ወይም እንደፍርዱ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት ነው በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 371 ንኡስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ፍርዱን ያልሰጠው ፍርድ ቤት በሌላ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑና ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ያልሰጠው ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን ተከታትሎ እንዲያስፈጽምለት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 372 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ያልሰጠው ሌላ ፍርድ ቤት ውሣኔውን ተከታትሎ እንዲያስፈጽምለት ትዕዛዝ በሚያስተላልፍበት ጊዜ አብሮ ሊገልጻቸውና ሊልካቸው የሚገቡ ጉዳዮች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 373 የተደነገገ ሲሆን

"ፍርዱን አስፈጻሚው ፍርድ ቤት ስለፍርዱ አፈጻጸም የሚሰጠው ትዕዛዝና በትዕዛዙም ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ያለው ስልጣን ዋናውን ፍርድ ከወሰነው ፍርድ ቤት ስልጣን ጋር እኩል ሆኖ ይቆጠራል በማለት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 374 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች ፍርድን በሰጠው ፍርድ ቤት ውሣኔውን ተከታትሎ እንዲያስፈጽምለት ለሌላ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመስጠት ስለሚችልበት ሁኔታ ትዕዛዙን የሚሰጠው ፍርድ ቤት ሊያሟላቸው ስለሚገቡ ሥነ ሥርዓቶችና ፍርድ እንዲያስፈጽም በሌላ ፍርድ ቤት የታዘዘው ፍርድ ቤት በአፈጻጸም ሂደት ስላለው ስልጣን የሚደነግጉ ተያያዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም አመልካች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 372 ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 374/1/ ጋር ተያያዥነት የሌለውና ራሱን የቻለ ድንጋጌ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. አመልካች ውሣኔውን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም የታዘዘ ፍርድ ቤት ሊወስናቸው የሚችላቸው ጉዳዮች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 የተደነገጉት ብቻ ናቸው፡፡ በአፈጻጸም ክርክር የሚቀርብ የጣልቃገብነት ጥያቄ ተቀብሎ የማከራከርና የመወሰን ስልጣን ፍርዱን በውክልና የሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ያለው ስለመሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 ያልተደነገገ በመሆኑ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የሰጠው ብይን ከተሰጠው የውክልና ስልጣን ውጭ ነው በማለት ሰፊ ክርክር አቅርቧል፡፡

ሆኖም ይህ የተጠሪ ክርክር የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ባህሪና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ የአመልካች ክርክር ፍርድ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ሰባተኛ መጽሐፍ በምዕራፍ አንድ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማለትም ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 371 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 455 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ፍርዱን የማስፈጸም ስልጣን እንዳለው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 371 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ ግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 በመሠረታዊ ባህሪው ፍርድ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች ምንምን እንደሆኑ የሚያመላክት ድንጋጌ /indicative provision of law/ እንጂ ፍርድን እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት የሚያቸውን ጉዳዮች በሙሉ የሚዘረዝር ድንጋጌ /conclusive provision of law/ አለመሆኑ ነው፡፡ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 ድንጋጌዎችን አመላካች የህግ ድንጋጌ መሆኑን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 ንኡስ አንቀጽ 1 በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር የመቃወም አቤቱታ ሲቀርብ ወይም በዚሁ ንብረት ላይ ቀዳሚ መብት አለኝ የሚል ተቃዋሚ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያ ያቀረቡት ወይም እንዲያዝ በታዘዘው ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለን የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ክርክር ተካፋይ ባይሆኑም በያዝነው ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው በመቁጠር የሚያቀርቡትን መቃወሚያ አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር አለበት በማለት አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ህግ አውጭው የደነገገውን ድንጋጌና ከዚህ በላይ ባለው ንኡስ ቁጥር የተነገረው መቃወሚያ ወይም አቤቱታ የሚቀርበው በጽሁፍ ሆኖ ፍርድን ለሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ነው በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪን በአፈጻጸሙ ጣልቃ በመግባት ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በመመርምር ውሣኔ የሰጠው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2ን መሠረት በማድረግ በመሆኑ አመልካች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 በመጥቀስ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

3. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሻሸመኔ ከተማ በዲዳ ቦቄ ቀበሌ የሚገኘውንና በወ/ሮ ከድጃ አወል ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቁጥሩ 425 የሆነውን ቤት በሀራጅ በመሸጥ ፍርዱን እንዲያስፈጽም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 372 ንኡስ አንቀጽ /1/ሐ/ እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 373 የተደነገገውን ስርዓት በማሟላት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ፍርዱን የሚያስፈጽመው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤቱ የፍርድ ባለዕዳው ባለቤት የወ/ሮ ከድጃ አወል ሣይሆን የእኔ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡትን የጣልቃገብነት ክርክር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 371 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሠረት መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይኽ ውሣኔ የኦሮሚይ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሰጠው ትዕዛዝ ጋር እኩል በመሆኑ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የሚቀርበውን ይግባኝ የማየት ስልጣን ያለው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሣይሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ



www.chilot.me

ሥርዓት ህግ ቁጥር 374 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍርድ እንዲያስፈጽም ያዘዘው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነው በማለት ወስነናል፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59301

ግንቦት 04 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- መምህርት አታቱ ከበደ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- ስቴፕስ አት.ኢዱኬሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር - በሌለበት የሚታይ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በስቴፕስ ትምህርት ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከስቴፕስ ት/ቤት ጋር በመምርነት ስራ ከመስከረም 1998 ዓ/ም ጀምሮ የስራ ውል ግንኙነት በመመስረት እስከ ጥቅምት 23 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ በወር ብር 1,050.00 እየተከፈላቸው ሲሰሩ ቆይተው ከህግ ውጪ በተከሳሽ እንደተሰናበቱ ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲክፍሉቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የማያሳይ ነው፡፡ የስር ተከሳሽ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካች ተቀጠርኩበት በሚሉበት ጊዜ ስቴፕስ ት/ቤት በሌላ ሰው ስም የነበረ መሆኑን ገልጾ በጠየቁበት ዘመን በስቴፕስ ት/ቤት እንዳልሰሩ ክሱም ሊቀርብ የሚገባው ስቴፕስ አት ኢዱኬሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር በመሆኑ እንዲሻሻል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የገለጸ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ስቴፕስ አት ኢዱኬሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር የፈረሰና የተዘጋ መሆኑን ተረጋግጦ በድርሻቸው መልስ እንደሚሰጡ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የነበረው ትምህርት ቤት ጋብቻው ፈርሶ ሲከፋፈል አመልካች ወደ ሴትየዋ ሄደው መስራቱን መቀጠላቸው መረጋገጡንና ከዚህ በሁዋላም ሴትየዋ አመልካችን አላሰናበትኩም የሚል ክርክር የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ለአመልካች የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ዘርዝሮ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ስቴፕስ አት ኢዱኬሽናል የተባለ ትምህርት ቤት የንግድ ፈቃዱ መሰረዙ መረጋገጡን በመግለፅ አመልካች ክሱን ከትምህርት ቤቱ ስራ አስኪያጅና ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ተነጥለው ሊከሰሱ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትን ትምህርት ቤትና ስራውን ሲያሰራ የነበረን ትምህርት ቤት ከጋብቻው መፍረስ በሁዋላ የንግድ ፈቃዱ



www.chilot.me

ተሰርዟል ከተባለው የስቴኘስ አት ኢዱኬሽናል ትምህርት ቤት ጋር አንድ አድርጎ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ የክስ አቀራረቡንና በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ሁኔታ ባግባቡ ሳያገናዝብ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ድርጅት መደበኛ ስራውን እያከናወነ አይደለም የሚለውን ብቻ በመያዝ ሊከሰስ አይችልም በሚል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ድርጅት መጥሪያው ተልኮለት ሊቀበል አለመቻሉ ተረጋግጦ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገርና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገዝነብ የተቻለው አመልካች ክስ የመሰረቱት ስቴኘስ ት/ቤት በሚል ሲሆን ይህ ትምህርት ቤት ሊከሰስ እንደማይገባ ፣ አመልካች ስራውን የጀመሩት ስቴኘስ አት ኢጁኬሽናሉ ኃ.የተ.የግል ማህበር ጋር ሆኖ ይህ ትምህርት ቤት በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክርክር ምክንያት የተከፋፈለ በመሆኑ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው በዚህ ትምርት ቤት መሆኑን የስቴኘስ ት/ቤት ባለቤት ተብለው የተከሰሱት ግለሰብ ጠቅሰው መከራከራቸውን፣ የስር ፍርድ ቤት የባልና ሚስት ንብረት የተከፋፈለ ቢሆንም የአሁኗ አመልካች የመምህርነት ስራውን የሴትዬዋ /ማዳም ፐሽ ፓላታ/ ንብረት በሆነው ስቴኘስ ት/ቤት መቀጠላቸው መረጋገጡን፣ ይህ ትምርት ቤትም አመልካችን አላሰናበትኩም የሚል ክርክር የሌለው መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋገጦ ለአመልካች የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው የወሰነ መሆኑን ፣ ይህ ውሳኔ በየትኛውም እርከን በሚገኝ ፍርድ ቤት አለመለወጡንና ለስር ፍርድ ቤት የአፈጻጸም አቤቱታ ቀርቦለትም በመ/ቁጥር 16902 በሆነው የአፈጻጸም መዝገብ ተከፍቶ የፍርድ ባለእዳ የሆነው ስቴኘስ ት/ቤት ፍርዱን እንዲፈጽም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ዋናው ፍርድ እንዲፈጸም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኝ ቀርቦለት አመልካችንና ስቴኘስ አት.ኢዱኬሽናል ኃ.የተ.የግል ትምህርት ቤት የተባለውን በይግባኝ ባይነት አከራክሮ ይኸው ድርጅት የንግድ ፈቃዱ መሰረዙ ተረጋግጧል፣ ስራውን ባቆመ ድርጅት ስራ አስኪያጅ የነበረ በመሆኑ ብቻ ተጠያቂ መሆን የለባቸውም በሚል ምክንያት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ እንግዲህ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ባይ የተጠቀሰው ድርጅት እና የስር ፍርድ ቤት በዋናው ክርክር ኃላፊ አድርጎ አፈጻጸሙን የቀጠለበት ድርጅት የተለያዩ መሆናቸውን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ ሊፈጸም የሚገባው እንደፍርዱ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዩቹ ቁጥሮች የተመለከቱትና አፈጻጸምን የሚገዙ ድንጋጌዎች ያሳዩናል፡፡ ስለሆነም አንድ የፍርድ አፈጻጸም የሚመራው እንደፍርዱ ነው፡፡ አንድ ፍርድ እንደፍርዱ የማይፈፀመው ፍርዱ በይግባኝ ሥርዓት የተለወጠ የሆነ እንደሆነ ወይም ፍርዱን ለመፈፀም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 386 መሰረት ሕጋዊ ምክንያቶች ያሉ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ነው፡፡ ፍርዱ ተለውጧል ሊባል የሚችለውና ለአፈጻጸም መሰረት ሊሆን የማይችለው ደግሞ ዋናው ክርክር ላይ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው በማለት ሳይሆን ዋናው ክርክር ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ/ሰበር ስርዓት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በማስለውጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሻረው የንግድ ስራውን ባቆመ ድርጅት ስራ አስኪያጁ ብቻውን ሊጠየቅ አይችልም በሚል ምክንያት ሲሆን ይህ ምክንያት ይዘቱ ሲታይ ከዋናው ፍርድ ይዘት ውጪ የሆነ፣

በዋናው ክርክር ጊዜ ቀርቦ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያጣና በሥርዓቱ መሰረት በበላይ ፍርድ ቤት ያልተለወጠ በመሆኑ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በዋናው ክርክር የተሠጠውን ፍርድ በአፈፃፀም መዝገብ የሚሽርና አፈጻጸም ከሚመራበት ስርዓት ውጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ስለአፈጻጸም የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 93697 ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16902 የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡ በመሆኑም ይኸው ፍርድ ቤት በዚሁ አፈጻፀም መዝገብ በጀመረው መሰረት አፈጻጸሙን በመቀጠል እንደዋናው ፍርድ እንዲያስፈጽም ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

*ቅ/መ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52110

ታህሣሥ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች -*** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካቾች -*** 1. ወ/ሮ ይሕደጋ ሳሙኤል - አልቀረቡም

2. ወ/ሮ አልጋነሽ ሳሙኤል ״

3. ወ/ት ዘነበሽ ሳሙኤል - ቀረቡ

***ተጠሪዎች -*** 1. ወ/ሮ አሰፋ ሳሙኤል

2. ወ/ሮ አስኳል ሳሙኤል

3. ወ/ሮ በላይነሽ ሳሙኤል

4. አቶ ሞገስ ሳሙኤል

5. አቶ ሙሉ ሳሙኤል

6. ወ/ሮ ንግስቲ ሳሙኤል

7. ወ/ሮ ምልእተ ሳሙኤል

8. ወ/ት ዓይንምሽት ሳሙኤል

9. ወ/ሮ ሃና ሳሙኤል

10. አቶ ሰለሞን ሳሙኤል

11. ወ/ሮ ርግበ ሳሙኤል

12. ወ/ሮ ደሞዝ ሳሙኤል

(ተጠሪዎች 1–12) አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአመልካቾች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የውርስ ንብረት ክፍያ አፈፃፀም ክርክር በፍርድ አፈፃፀም መዝገብ ላይ ሰኔ 29 ቀን 2000 ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቶ የአፈፃፀም መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ መሠረት አቤቱታ በማቅረባቸው ይህንኑ የሥር ፍ/ቤቶች ተቀብለው ትዕዛዝ መስጠታቸውን በመቃወም አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በአፈፃፀም በተያዘ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78 መሠረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ መደረጉ በአግባቡ መሆን /አለመሆኑን ድንጋጌው ተፈፃሚነት አለው ቢባል እንኳን በጉዳዩ ላይ ትዕዛዝ ከተሰጠ ከአንድ ዓመት በኃላ የቀረበ አቤቱታ ተቀባይነት ማግኘቱ በሥነ ሥርዓት ሕግ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ አኳያ የታየ መሆን /አለመሆኑን እንዲሁም ተጠሪዎች ቀደም ሲል ቀርበው የሚፈለገውን ገንዘብ ከፍለው ንብረቱን ለማስቀረት ዳኝነት ጠይቀው ውሣኔ ያረፈበት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የተጠሪዎች የመከራከር መብት አልተጠበቀም ማለት ይቻላልን? የሚሉት ነጥቦች ሊመረመሩ የሚገባቸው ሆኖ ስለተገኙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የተጠሪዎች ጠበቃ ሚያዚያ 4 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በይዘቱም ተጠሪዎች የተለያየ ቦታ ይኖሩ እንደነበር ጠቅሰው በሥር ፍ/ቤት ቀድሞ የተሰጠው ትዕዛዝ እንደማያውቁትና የቤቱ ስመሀብት በአመልካቾች እንዲመዘገብ የተደረገው በ22/06/2001 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ መሆኑን እና እነሱም ይህንን ያወቁት በ15/10/2001 ዓ.ም እንደሆነና ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያቀረቡትም በ26/10/2001 ዓ.ም ስለመሆኑ ዘርዝረው አቤቱታ ያቀረቡት ጉዳዩን ባወቁ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ እንደሆነ ተከራክረዋል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ ተፈጻሚነት በተመለከተ ጉዳዩ በአፈፃፀም ላይ ያለ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አመሳስሎ በመተርጐም መቀበሉ አግባብ ነው በሚል እንዲሁም ቀደም ሲል በአፈፃፀም ሂደት ተጠሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበው ክርክር እንዳላቀረቡ ጠቅሰው የሥር ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡

አመልካቾች ክርክራቸውን አጠናክረው የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እልባት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳዩ ተጠሪዎች ቀደም ሲል በአፈፃፀም ክርክር እንዲቀርቡ ተደርጓል ወይንስ አልተደረገም? ቀርበው እንዲከራከሩ አልተደረገም ከተባለ በአፈፃፀም ጉዳይ ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78 ተፈፃሚነት አለው ወይንስ የለውም? ተፈፃሚነት አለው ከተባለ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ተፈጻሚነትን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት ከአንድ አመት በኂላ መቀበሉ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም የሚሉትን በየተራ እንመለከታለን፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቾች አጥብቀው የተከራከሩት ተጠሪዎች ቀደም ሲል በአፈፃፀም ክርክር ላይ ቀርበው የውርስ ንብረት በዓይነት ለማስቀረት እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ተቀባይነት አጥተዋል፡፡ በሂደቱም ተከራካሪ የነበሩ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት መዝገብ ተረጋግጧል የሚል ነው፡፡



www.chilot.me

እኛም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ከዚህ ፍሬ ነገር አንፃር መርምረናል፡፡ የአክሱም ከተማ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05063 ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው ፍርድ ላይ እንዳረጋገጠው ከተጠሪዎች ውስጥ 1ኛ - 4ኛ፣ 6ኛ፣ 8ኛ - 10ኛ እና 12ኛ ተጠሪ በአፈፃፀም ክርክር ላይ በተለያዩ ቀናት ችሎት ቀርበው የበኩላቸውን ክርክር ያቀረቡ ስለሆነ ነው የተቀሩት ተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጐላቸው እንዳልቀረቡ ፍርድ ቤቱ የአፈፃፀም መዝገብ አስቀርቦ መርምሮ እንዳረጋገጠ በውሣኔው አሰፍሯል፡፡ በዚህም መነሻ መሠረት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ መሠረት የአፈፃፀም መዝገቡ በ19/10/2000 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ተዘግቶ ካደረ በኃላ ተጠሪዎች በ26/10/2001 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ሲል ውሣኔ የሰጠው፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪዎች ቀደም ሲል ቀርበው የተከራከሩ መሆኑን ፍሬ ነገር በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን አንዳችም ምክንያት ሳይሰጥ ሽሮታል፡፡

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪዎች ቀደም ሲል የበኩላቸውን ክርክር አቅርበው ተቀባይነት አጥቶ ያደረ ሆኖ ሳለ እንደአዲስ አቤቱታ ማቅረባቸው አግባብ እንዳልሆነ ነው፡፡ በመሠረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ ክርክሮች በተወሰነ ደረጃ እና ጊዜ እንዲቋጭ ማስቻል እንጂ ጉዳዮች ያለገደብ በሙግት ላይ ተንጠልጥለው እንዲቆዩ ማድረግ አይደለም፡፡ በዚህም የተከራካሪ ወገኖችን እንዲሁም የፍርድ ቤቱን ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ያለአግባብ ብክነት ማስቀረት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም ቀደም ሲል ስለውርስ ንብረት ክፍያ አፈፃፀም በ19/10/2000 ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ካበቃ በኃላ ተጠሪዎች ከአንድ አመት በኃላ በ26/10/2001 ዓ.ም እንደ አዲስ ተከራካሪ ወገን አቤቱታ ማቅረባቸው እና በሥር ፍ/ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ከሥነ ሥርዓት ሕጉ ዓላማና መንፈስ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል አይደለም፡፡

ስለሆነም ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አብዛኛው ወገን በጉዳዩ ላይ የበኩላቸውን ክርክር ያቀረቡ ሆነው ሳለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡ የተቀሩት ሶስት ተጠሪዎችም ቢሆኑ ክርክሩ የውርስ ንብረት ክፍያን የሚመለከት እንደመሆኑና የሁሉም ተጠሪዎች መብት በአንድ መስመር የተወሰነ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ ከአብዛኞቹ የተለየ ክርክርና መብት አላቸው የሚባልበት ሁኔታ አልተጠቀሰም፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር በአክሱም ወረዳ ፍ/ቤት ደረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ መሠረት ሊስተናገዱ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡

ስለዚህም ጉዳዩ በመጀመሪያው ጭብጥ ብቻ እልባት ያገኘ በመሆኑ ወደተከታዮቹ ነጥቦች መግባትና መመርመር አስፈላጊ አይደለም፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182/3/ የመጀመሪያ ዐረፍተነገር ይዘት ይህንኑ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔ ከሥነ ሥርዓት አኳያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መ የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15276 በ9/2/2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 35416 በ14/03/2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአክሱም ከተማ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05063 በ13/12/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ላይ የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ግራቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58009

ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡ - ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡** - 1. አቶ ስለሺ ወርቅነህ - ጠበቃ ግሩም አየለ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ብርቅነሽ መኮነን

3. ወ/ሮ ራሄል መኮነን } አቶ የውሴፍ አእምሮ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡** - 1. አቶ ሁሪሳ ደመሳ - ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ለማ

2. ወ/ሮ ሰውነት ፈቃዱ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልካቾች ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ እንዲሰረዝላቸው አመልካቾች ያቀረቡት ጥያቄ በየደረጃው ያሉ የክልል ፍርድ ቤቶች ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ይዘት አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ ገንዘብ አበድሮ ያልተከፈለው መሆኑን በመግለጽ ክስ አቅርቦ ሁለተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ የተበደሩትን ገንዘብ እንዲከፍሉ በፍርድ ተወስኖባቸዋል፡፡ ከዚህ በኂላ አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳ ሆነው አንደኛ ተጠሪ በአስከፈቱት የአፈፃፀም መዝገብ ተከራክረው ንብረትነቱ የሁለተኛ ተጠሪ ነው የተባለ ቤት በሀራጅ የሚሸጥ መሆኑ በበከልቻ ጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ቤቱ ተሽጦ ለሁለተኛዋ ተጠሪ እዳ መክፈያነት እንዲውል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ቤቱ ከተሸጠና የአፈፃፀም መዝገቡ ከተዘጋ በኂላ ለሁለተኛ ተጠሪ እዳ መክፈያነት የተሸጠው ቤት የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት ሣይሆን የአንደኛ ተጠሪ፣ የሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የጋራ ንብረት ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ጋር በመሆን ህዳር 26 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአንደኛ አመልካች የሸጡትና አንደኛ አመልካችም በውሉ መሠረት ብር 82,640.29

(ሰማንያ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) ቤቱን ከባንክ መያዣነት ለማስለቀቅ የከፈሉ መሆኑን የቤቱን ስመ ሀብት ወደ ወራሾቹ ለማዛወር ብር 31,884.42 (ሰላሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከአርባ ሁለት ሳንቲም) የከፈለ መሆኑን ብር 16,799 ለወራሾቹ የከፈለ መሆኑን በመግለጽ ንብረቱ ላይ የተደረገው የሀራጅ ሽያጭ እንዲሰረዝላቸው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልክተዋል፡፡

አንደኛ ተጠሪ ቤቱ በሀራጅ የሚሸጥ መሆኑ ማስታወቂያው በቤቱ ላይ ያልተለጠፈ መሆኑን በማመን የሀራጅ ማስታወቂያው በጋዜጣ የወጣ በመሆኑ የሽያጩን ሥርአት ለማሰረዝ የሚያበቃ ምክንያት አይደለም፡፡ ቤቱ የፍርድ ባለዕዳዋ የሁለተኛ ተጠሪ ንብረት እንደሆነ በክፍሉ አስተዳደር ተረጋግጧል፡፡ ሽያጩ እንዲሰረዝ ጥያቄው የቀረበው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1) በተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ በአምስት ወሩ ነው፡፡ አመልካቾች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 መሠረት ጣልቃ መግባት የሚችሉት ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ነው፡፡ አንደኛ አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 መሠረት ቤቱን የገዛ መሆኑን ያቀረበው ማስረጃ ስለሌለ የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ ለማመልከት የሚያስችል መብት የለውም በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ (የፍርድ ባለዕዳዋ) በበኩሏ ከአንደኛው ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ገንዘብ ተበድሬ መክፈል ስላልቻልኩኝ ቤቱ ተሸጦ ተከፍሏል፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከእዳ ቀሪ ከሆነው ገንዘብ ድርሻቸውን እንዲሰጣቸው ከሚጠይቁ በስተቀር ሽያጩ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ አይችሉም፡፡ ቤቱ ከተሸጠና ገንዘቡ ከተከፈለ በኋላ ሁለት ወር አልፎታል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን አቤቱታና የተጠሪዎችን መልስ ከመረመረ በኋላ

1. የጨረታው ማስታወቂያ በተሸጠው ቤት ላይ ተለጥፏል ወይስ አልተለጠፈም?
2. የጨረታ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣ የሀራጅ ማስታወቂያው በሚሸጠው ቤት ላይ መለጠፍ ነበረበት በማለት አቤቱታ አቅራቢዎች (አመልካቾች) የሚያቀርቡት ክርክር ትክክል ነው ወይስ አይደለም?
3. አቤቱታ አቅራቢዎች የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ ጥያቄ ያቀረቡት ህጉ በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው ወይስ አይደለም?
4. የአንደኛው አቤቱታ አቅራቢ (አመልካች) ቤቱን ለመግዛት ያደረገው ውል በህግ ፊት ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም?
5. በፍርድ አፈፃፀም ሂደት መብታችንና ጥቅማችንን ያሳያል የሚሉ ሰዎች የጣልቃ ገብነቱን ጥያቄ መቼ ማቅረብ አለባቸው? የሚሉትን ጭብጦች መስርቷል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤቱ የሀራጅ ማስታወቂያ በቤቱ ላይ ያልተለጠፈ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ሆኖም የሀራጅ ማስታወቂያው በጋዜጣ የወጣ በመሆኑ የሀራጅ ማስታወቂያው በሚሸጠው ቤት ላይ አለመለጠፉ የሀራጅ ሽያጩን ለመሰረዝ የሚያበቃ ምክንያት አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካቾች ሽያጩ እንዲሰረዝላቸው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1) የተደነገገው የሁለት ወር የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ ስለሆነ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አራተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አንደኛው አመልካች የሁለተኛ ተጠሪ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ አመልካች የጋራ ሀብት የሆነውን ቤት በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 1723 መሠረት የገዛ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በቤቱ ላይ የተደረገውን ሽያጭ እንዲሰረዝለት ለመጠየቅ የሚያስችለው መብት የለውም በማለት ብይን የሰጠ ሲሆን አምስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ በአፈፃፀም ሂደት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418



www.chilot.me

መሠረት ጣልቃ መግባት የሚቻለው ፍርዱ ከመፈፀሙና ንብረቱ ከመሸጡ በፊት በመሆኑ የአመልካቾች ጥያቄ ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌው መሠረት አልቀረበም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የፍርድ ባለዕዳ (ሁለተኛ ተጠሪ) ባመነችው መሠረት ድርሻቸውን ከሚጠይቁ በስተቀር ሽያጩ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጐታል፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 6 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች ከሁለተኛዋ ተጠሪና በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑት ሄኖክ መኮንን እና ራሄል መኮንን የጋራ ንብረት የሆነ ቤት በቡራዩ ከተማ ነበራቸው፡፡ ይህንን የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት ህዳር 26 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ውል አንደኛው አመልካች የገዛው ሲሆን ውሉ በምዕራብ ሸዋ ዞን ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ የፍርድ ባለመብት ነው የተባለው አንደኛው ተጠሪ በሽያጭ ውሉ ላይ በምስክርነት የፈረመ ሲሆን ለሽያጭ ውሉ መልካም አፈፃፀም ለሻጮች ሀላፊ እሆናለሁ በማለት የዋስትና ግዴታ ገብቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 15876 በመጀመሪያ ለእኔ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ብዙ ገንዘብ ገዥ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡ ሲሆን ከዚህ በኋላ ክሳቸውን በማሻሻል ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ክስ አቅርበው ነበር፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሁለተኛ ተጠሪን ክስ በመቃወም በክርክሩ ጣልቃ ከገቡ በኋላ መዝገቡ የዳኝነት ሳይከፈል የተከፈተ በመሆኑ ሁለተኛ ተጠሪ የዳኝነት ከፍለው እንዲቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቶ የዳኝነት ስላልከፈሉ የዳኝነት ሲከፈል መዝገቡ እንደሚንቀሳቀስ ገልፆ ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም መዝገቡን ዘግቶ አሰናብቶናል፡፡

ከዚህ በኋላ ሁለተኛ ተጠሪ ክርክራቸው የማያዋጣቸው መሆኑን በመለየት በቤቱ ሽያጭ ላይ በምስክርነት የፈረሙትና ለአፈፃፀሙ ዋስ ከሆኑት አንደኛ ተጠሪ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ለሁለተኛ ተጠሪ እንዳበሩ የሚገልጽ ሁለት የብድር ውል በማዘጋጀት በፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርበው አስፈርደውና የአፈፃፀም ክስ አቅርበው የሀራጅ ማስታወቂያው ቤቱ ላይ ሳይለጠፍ ሀራጅ እንዲከናወን በማድረግ የአንደኛ ተጠሪ የአክስት ልጅ ቤቱን በሀራጅ እንዲገዛው አድርገዋል፡፡ እኛ ቤቱ በሀራጅ የተሸጠ መሆኑን ያወቅነው ከአምስት ወር በኋላ የአንደኛ ተጠሪ የአክስት ልጅ ቤቱን በፍርድ ቤት በወጣ ሀራጅ ስለገዛሁት ልቀቁ ብሎ ሲጠይቀን ነው፡፡ በአንደኛ ተጠሪና በሁለተኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የብድር ውል ሀሰተኛ የብድር ውል መሆኑን ፖሊስ በወንጀል እንዲያጣራልን ጠይቀን የብድር ውሉ በሀሰት የተዘጋጀ የብድር ውል መሆኑን በፖሊስ ምርመራ የተረጋገጠ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1)፣ ድንጋጌ ይዘትና ተጠቃሽና ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418ን አላግባብ በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ለአመልካች የሰበር አቤቱታ አንደኛ ተጠሪ ህዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ አመልካቾች ለሥር ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን አዲስ መከራከሪያ በሰበር ያቀረቡ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 329 መሠረት ውድቅ ይደረግልኝ፡፡ አመልካቾች አቤቱታቸውን ያቀረቡት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 ን በመጥቀስ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ ድንጋጌ በአፈፃፀም ጣልቃ መግባት የሚችለው ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ነው በማለት የሰጠው ትርጉም ስህተት የለውም፡፡ የሀራጅ ማስታወቂያው ቤቱ ላይ አለመለጠፉ የሀራጅ ሽያጩን ለማሰረዝ የሚያስችል ምክንያት አይደለም፡፡ አመልካቾች ጥያቄያቸውን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1) በተደነገገው የጊዜ ገደብ አላቀረቡም፡፡ ስለሆነም የሀራጅ ሽያጩ የህጉን ሥርአት ተከትሎ የተፈፀመ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ህዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርበዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የጨረታ ማስታወቂያው ቤቱ ላይ አለመለጠፉ የሀራጅ ማስታወቂያው በጋዜጣ የወጣ በመሆኑ የሀራጅ ሽያጩን ለመሰረዝ የሚያበቃ አይደለም፡፡ አመልካቾች ጥያቄያቸውን በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ አላቀረቡም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች አቤቱታቸውን ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን ውልና ማስረጃ የተደረገውን ውል ሁለተኛ ተጠሪ የሚያውቁት አይደለም፡፡ የብድር ውሉ በሀሰት የተደረገ ነው ይበሉ እንጂ በፍርድ ቤት ውሣኔ የተረጋገጠ ነው፡፡ ቤቱን የገዛው የክርስትና ልጅ ነው ለሚሉት የክርስትና ልጅ መሆኑን ማስረጃ አላቀረቡም የክርስትና ልጅ እንዳይገዛ ህጉ አይከለክልም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 እና ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች ሲተረጉሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሰሩ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት ታህሣሥ 15 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት አመልካቾች የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በአግባቡና ለጉዳዩ ተጠቃሽና ተፈፃሚ መሆን የሚገባቸውን የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ በአፈፃፀም የተሸጠው በቡራዩ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቤት የማን ንብረት ነው? የሚለውን መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም እንዲሸጥ ያደረገው ቤት የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት አለመሆኑን ሁለተኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሠበር ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር ያመኑት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ በአፈፃፀም በሀራጅ የተሸጠው ቤት የሁለተኛ አመልካች፣ የሶስተኛ አመልካች፣ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆኑት ሄኖክ መኮንንና ራሄል መኮንን እና የሁለተኛ ተጠሪ የጋራ ሀብት የነበረ ነው፡፡ በቤቱ ላይ ሁለተኛ ተጠሪ ድርሻ የነበራቸው ቢሆንም ይህንን ድርሻቸውን ቤቱ በአንደኛ አመልካች እንዲሸጥ በሰጡት ፈቃድና ስምምነት መሠረት ሸጠዋል የሚለው ነጥብ በሥር ፍርድ ቤት የቀረበና ውሉ የህጉን ፎርም አላሟላም በማለት የታለፈ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ውሉ በምዕራብ ሸዋ ዞን ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑን በመግለጽ



www.chilot.me

ላቀረበው ክርክር ምዕራብ ሸዋ ዞን የተደረገውንና የተመዘገበውን ውል አላውቀውም በማለት ሁለተኛ ተጠሪ በመሸሽ መልክ መልስ የሰጡ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ ከሌሎች የቤቱ የጋራ ባለሀብቶች ጋር በመሆን ቤቱን ለአንደኛ አመልካች አልሸጥኩም በማለት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) መሠረት አልተከራከሩም፡፡ ከዚህ የምንረዳው ቤቱ የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት እንዳልሆነና ሁለተኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸውን መብት ከሌሎች የጋራ ባለሀብቶች ጋር በመሆን ለአንደኛ አመልካች ለፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የሆነውን የብድር ገንዘብ ከአንደኛ ተጠሪ ከመበደራቸው በፊት የሸጡ መሆኑን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት እንዳመኑ የሚቆጠር ነው፡፡ በአፈፃፀም የተሸጠው ቤት የፍርድ ባለዕዳዋ ካልሆነና የፍርድ ባለዕዳዋ በቤቱ ላይ የነበራቸው የጋራ ንብረት ባለቤትነት መብት ከሌሎች ባለሀብቶች ጋር በመሆን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1266 በሚደነግገው መሠረት ለአንደኛ አመልካች የሸጠች መሆኑን ክዳ ባልተከራከረችበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1) የተደነገገው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው አቤቱታ ያቀረባችሁት በማለት የሰጡት ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አንደኛ አመልካች ንብረቱ የጋራ ባለሀብት ከሆኑ ሰዎች ቤቱን የገዛው መሆኑን ሁለተኛ ተጠሪ በግልጽ ክደው አልተከራከሩም፡፡ በአፈፃፀም የተሸጠው ቤት የጋራ ባለሀብት የሆኑት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አንደኛ አመልካች ቤቱ ላይ በባንክ የሚፈለገውን እዳ በመክፈልና የማዘጋጃ ቤትን ዕዳ በመክፈል ቤቱን ነፃ ያደረገ መሆኑንና ከሁለተኛ ተጠሪና ከሌሎች የጋራ ባለሀብቶች በሙሉ ፈቃድና ስምምነት ገብቶ ቤቱን ይዞ የሚገኝ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ገደብ በአፈፃፀሙ ሂደት ተከራካሪ የነበሩት የፍርድ ባለዕዳው ወይም የፍርድ ባለመብቱ ወይም በሀራጅ ጨረታው ተሳትፎ ቤቱን የገዛው ሰውና ለአፈፃፀሙ ሙሉ እውቀት የነበራቸው ሌሎች በጉዳዩ ይገባናል የሚሉ ሰዎች የሀራጅ ጨረታውን ለማስፈረስ በቂ ምክንያት ካላቸው ሽያጩ እንዲሰረዝላቸው በሁለት ወር ውስጥ ማመልከት ያለባቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ በአፈፃፀም በሀራጅ በተሸጠው ቤት ላይ መብት ያለውን ሶስተኛ ወገን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ገደብ ውስጥ አላመለከትክም ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ለማድረግ በመጀመሪያ ቤቱ በፍርድ ምክንያት እግድ የተሰጠበት መሆኑና ሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበት መሆኑን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በቤቱ ላይ የተለጠፈ መሆኑን ማረጋገጥ የግድ የሚያስፈልግ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሁለተኛ ተጠሪ የግል ሀብት ያልሆነው ቤት የሀራጅ ማስታወቂያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት በቤቱ ላይ አልተለጠፈም፡፡ ይኼም በመሆኑ ቤቱን ከሁለተኛ ተጠሪና ከሌሎች የቤቱ የጋራ ባለሀብቶች ገዝቶ የያዘው አንደኛ አመልካችና ቤቱን ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር በመሆን ለአንደኛ አመልካች የሸጡት የቤቱ የጋራ ባለሀብት የሆኑት ሁለተኛ እና ሶስተኛ አመልካቾች ቤቱ በሁለተኛ ተጠሪ እዳ ምክንያት እግድ የተሰጠበትና የሀራጅ ጨረታ የወጣበት መሆኑን ለማወቅ የሚያስችላቸው ሁኔታ አልነበረም፡፡



www.chilot.me

ሕግ አውጪው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 423 የተደነገገውን ሁኔታ አሟልቶ በጋዜጣ እንዲወጣ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገገው በተጨማሪ የሀራጅ ማስታወቂያው በሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ቤት ላይ እንዲለጠፍ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገበት የራሱ የሆነ መሠረታዊ ምክንያት አለው። ይኸው የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበት ወይም የሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበት የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ መብት ያላቸው ሰዎች ንብረቱ የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበት ወይም ለሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበት መሆኑን በመገዘብ በአፈፃፀሙ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 መሠረት ጣልቃ ገብተው መብታቸውን እንዲያስከብሩ ለማድረግ ንብረቱ የጋራ ባለሀብቶች በሆነ ጊዜ የንብረቱ የጋራ ባለሀብቶች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 443 የተጠበቀላቸውን መብት እንዲያስከብሩ ንብረቱ በሀራጅ የሚሸጥ መሆኑን እንዲያውቁት ለማድረግና በመጨረሻም የሀራጁን ሂደት በመከታተል በሂደቱ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 445 የተደነገጉት ሕገ ወጥና የማጭበርበር ተግባራት ከተፈፀሙ የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ለማመልከት እንዲችሉ ነው። ህግ አውጭው ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች የማሳካት ሀሳብና ፍላጎት ባይኖረው ኖሮ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያውና በማይንቀሳቀስ ንብረት በፍርድ በተወሰነ እዳ ምክንያት የእግድ ትእዛዝ ሲሰጥ በማይንቀሳቀሰው ቤት ላይ እንዲለጠፍ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 አይደነግግም ነበር። ስለሆነም የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው በሚሸጠው ቤት ላይ አለመለጠፍን እንደ ቀላል የሥነ ሥርአት ግድፈት በመቁጠር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጓሜ ከላይ በዝርዝር የተገለፀውንና ህግ አውጭው ሊያሳካቸው የሚፈልጋቸውን ግቦች ያላገናዘበ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

3. በአፈፃፀም በተያዘው ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ሰው ፍርድ ከመፈፀሙ በፊት አለኝ የሚለውን ክርክር ማቅረብ እንደሚገባው የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚደነግገው የሀራጅ ሽያጩ ከመፈፀሙ በፊት ፍርድ ቤቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚሰጠውን እግድ ትእዛዝና የሀራጅ ማስታወቂያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚለጠፍ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከላይ የተገለፀውን ሥርአት የሚሟላ መሆኑንና የሀራጅ ሽያጩ እየተካሄደ መሆኑን የማያውቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸውን ሰዎች የሚመለከትና በእነርሱ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው።

የሀራጅ ማስታወቂያው በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሣይለጠፍ የያዙት የማይንቀሳቀስ ንብረት በአፈፃፀም ምክንያት የእግድ ትእዛዝ በሌላ ወይም የሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበት መሆኑን ሳያውቅ በሌላ ሰው እዳ ምክንያት የያዙት ንብረት በሀራጅ የተሸጠባቸው ሰዎች በምን መንገድና መቼ የሀራጅ ሽያጭ እንዲሰረዝላቸው ለማመልከትና በንብረት ላይ አለን የሚሉትን የንብረት ባለቤትና ሌሎች ተዛማጅ መብቶች ለማስከበር ይችላሉ? የሚለው ነጥብ የያዝነውን ጉዳይ ለመወሰን መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው። የማይንቀሳቀስ ንብረት በሀራጅ ከተሸጠ በኋላ በንብረቱ ላይ መብት ያለው ሰው ንብረቱን ለገዢው እንዲያስረክብ ሲጠየቅ ንብረቱን መልቀቅ አይገባኝም በማለት አቤቱታውን ሊያቀርብ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 1 የሚደነግግ ሲሆን እንደዚህ በሚሆን ጊዜ ፍርድ



www.chilot.me

ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ በመያዝ መስማት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ሂደት አመልካች ንብረቱን የያዘው በራሱ መብትና ከሌላ ሰው በተላለፈለት መብት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ንብረቱ እንዲመለስለት ለመወሰን እንደሚቻል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝላቸው የጠየቁት አንደኛ አመልካች ከሁለተኛ ተጠሪ /የፍርድ ባለዕዳ/ እና ከሌሎቹ ባለሀብቶች ገዝቶ የያዘውን ቤት በሀራጅ ከፍርድ ቤት ትእዛዝ ስለገዛሁት ልቀቅልኝ በማለት ገዥው ሀራጁ ከተከናወነ በኋላ ከአምስት ወር በኋላ ሲጠይቀው መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 453 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ማስተናገድና ውሣኔ መስጠት ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 ን በመጥቀስ የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ይህንን ውሣኔ ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. በሁለተኛ ተጠሪ ዕዳ ምክንያት በፍርድ አፈፃፀም በሀራጅ የተሸጠው ንብረት ሁለተኛ ተጠሪ ከሌሎቹ የቤቱ የጋራ ባለሀብቶች ጋር በመሆን ለአንደኛ አመልካች የሸጡት የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የፍርድ ባለመብት በመሆን በቤቱ ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ያደረገው አንደኛ ተጠሪ ሁለተኛ ተጠሪና ሌሎቹ የጋራ ባለሀብቶች ይህንን ቤት ለአንደኛ አመልካች የሸጡ መሆኑን ሙሉ እውቀት እንዳለውና በምስክርነት በሽያጭ ውሉ ላይ እንደፈረሙ በመግለጽ አመልካቾች በአቤቱታቸው የገለጹ ሲሆን አንደኛ ተጠሪ ይህንን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) መሠረት በግልጽ በመካድ ያልተከራከረ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት እንዳመነ የሚቆጠር ነው፡፡ የፍርድ ባለመብት ነኝ የሚለው አንደኛ ተጠሪ በእዳ ምክንያት የሚሸጠው ቤት የፍርድ ባለዕዳዋ ሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት እንዳልሆነና ቤቱ የጋራ ሀብት መሆኑን እያወቀና የጋራ ባለሀብቶቹም ቤቱን ለአንደኛ አመልካች የሸጡ መሆኑን እያወቀ ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳዋ የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት እንደሆነ አድርጐ ባቀረበው የአፈፃፀም ማመልከቻ መነሻ አመልካቾች ቤቱ ለሀራጅ መቅረቡን ለማወቅ በማይችሉበት ሁኔታ የሀራጅ ሽያጩ መከናወኑ የአመልካቾችን መብት በጠቅላላውና ቤቱን ከሁለተኛ ተጠሪና ከሌሎቹ የጋራ ባለሀብቶች ስምምነት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1266ን መሠረት በማድረግ ገብቶ የተለያዩ የቤቱን እዳዎች ከፍሎ ቤቱን በይዞታው ሥር አድርጐ የሚገኘውን የአንደኛውን አመልካች መብት የሚጎዳ የማጭበርበር ተግባር የተፈፀመበት የሀራጅ ሽያጭ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ሀራጁን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ቀሪ በማድረግ ቤቱን አንደኛ አመልካች እንደያዘ እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት ሲገባቸው ሀራጅ ሽያጩ መሠረት ቤቱን እንዲያስረክብ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያከናወነው የሀራጅ ሽያጭ ማጭበርበር የተፈፀመበትና የህጉን ሥርአት ያልተከተለና የፍርድ ባለዕዳ ያልሆኑትን የአንደኛ አመልካችንና የሌሎች አመልካቾችን መብት የሚጎዳ በመሆኑ የሀራጅ ሽያጩ ሊሠረዝ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

ሃ/ዓ                                                                                  የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48997

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የቦሌ ክ/ከ/ገቢዎች መምሪያ ነ/ፈጅ ታደሰ አንዳርጌ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች**፡- 1. አቶ መዓዛ ሽፈራው - ጠበቃ ወርቅነሽ መንግሥቱ - ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ስብለ ከፈለኝ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ አቤቱታ የቀረበው በተጠሪዎች መካከል የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የቀዳሚነት መብት ይፈጽምልኝ ሲል አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ባለመቀበላቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስለጠየቀ ነው፡፡

አመልካች ለሰበር ችሎቱ ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በኮንስትራክሽን ሙያ የተሰማሩ ነጋዴ ስለመሆናቸው፣ አመልካችም በአዋጅ ቁጥር 286/94 እና 285/94 መሠረት የንግድ ትርፍ ገቢ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ከ1997 እስከ 2000 ዓ.ም. ያለባቸው የመንግሥት እዳ ብር 405,070.88 እንዲከፍሉ ማስታወቂያ ደርሷቸው ባለመክፈላቸው በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለማስፈጸም እንደሚችል፣ 1ኛ ተጠሪ በተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰቡት ገንዘብ ብር 40,140.63 ጭምር መታገዱን በመግለጽ ይህንኑ ለማስፈጸም ያቀረበውን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ የሥር ፍ/ቤት አለመቀበሉ ስሕተት ነው ተብሎ እንዲታረም በሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዟል፡፡

1ኛ/ ተጠሪ በ24/06/2002 ዓ.ም. ባቀረበው የጽሁፍ መልስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በነበረው ክርክር ንብረቶቹ በመታገዳቸው የመንግሥት እዳ /ግብር/ ለመክፈል አለመቻሉን ገልፆ በዚህም ምክንያት የሥራ ፈቃዱም እንዳልታደሰ በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲታረም ጠይቋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሏ በ18/5/2002 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርባለች፡፡ ይዘቱም የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 መሠረት ተቀባይነት እንደሌለው ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለገው

የግብር ገንዘብ መጠን በ1999 እና 2000 ዓ.ም. የተከፋፈለ በመሆኑ ተጠሪዋ ደግሞ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራት ግንኙነት በ1999 ዓ.ም. የተቋረጠ በመሆኑ የጋራ እዳ ሊባል እንደማይገባ በዚህም ምክንያት የጋራ ሀብት ሊያዝ እና ሊፈፀምበት እንደማይገባ በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲፀና ጠይቃለች፡፡

አመልካች ክርክሩን በማጠናቀር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው በ1ኛ ተጠሪ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የንብረት ክፍፍልን በተወሰነው መሠረት አፈፃፀሙ በ2ኛ ተጠሪ አመልካችነት መዝገብ ተከፍቶ በሂደት ላይ ባለበት ሁኔታ ግራ ቀኙ ንብረቱን ከመከፋፈላቸው በፊት ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለግ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ በቀዳሚነት ለማስፈጸም አመልካች አቤቱታ ያቀረበ ስለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች ለአቤቱታው መሠረት ያደረገው መሠረታዊ ሕግ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና አዋጅ ቁጥር 286/94ን ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 32/1/ እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80/1/ ላይ እንደተደነገገው ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ወይም ግብሩ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ ወይም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ሀብት ላይ ባለሥልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች እዳዎች የቀደምትነት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ በዚህ ረገድ የሕጉ አገላለጽ ግልጽ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች መካከል ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ መወሰኑን ተከትሎ የፍርድ ባለመብት የሆነችው 2ኛ ተጠሪ ባስከፈተችው የአፈፃፀም መዝገብ በ2ኛ ተጠሪ ስም አለ የተባለን ሀብት ያስከበረች ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በፍርድ ባለእዳ ጥያቄ የታገደና የተከበሩት የ2ኛ ተጠሪ ሀብቶች አንድም በዓይነት አልያም ተሸጠው ለፍርድ ባለመብት የሚከፈል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ንብረቱ ለፍርድ ባለመብት ከመከፈሉ በፊት አመልካች በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መብቱን ለማስከበር እና ለማስፈጸም አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረቡ ሲታይ ከሕግ የመነጨ መሠረት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች በአፈፃፀም በተያዘ ንብረት ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 ጠቅሶ አቤቱታ ማቅረቡም ቢሆን በሥነ ሥርዓት ሕጉ እንደተደነገገው የቀዳሚነት መብቱን መሠረት /መነሻ/ ምክንያት ማስረዳት የሚጠበቅበት እንጂ በዋናው ውሣኔ እንዲከራከር አያስገድደውም፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው የሕጉን ዓላማና ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛዋ ተጠሪ የጋራ አፈፃፀም አይመለከተኝም የሚል ክርክር በዚህ ሰበር ችሎት በአማራጭ አቅርባለች፡፡ በመሠረቱ ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለገው የተከሣሽ እና የግብር እዳ የግል ወይንስ የጋራ? የሚከፈለውስ ከግል ሀብት ወይንስ ከጋራ ሀብት የሚሉት እና ተያያዥ ጭብጦች በሥር ፍ/ቤት ተመርምሮ ውሣኔ ያልተሰጠባቸው ስለሆነ በዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመርበት የሕግ አግባብ የለም፡፡



www.chilot.me

ስለሆነም በዚህ ረገድ ጉዳዩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው የሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ክርክር እና ማስረጃ መሆን እንዳለበት ታምኗል፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን የቀዳሚነት መብት ይከበርልኝ ጥያቄ የሥር ፍ/ቤት ሳይቀበል መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በማረም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 140988 በ05/08/2001 ዓ.ም. የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ በመ/ቁ. 81055 ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በማጽናት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካችን አቤቱታ ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መዝገቡን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም ችሎት መልሰናል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

# ልዩ ልዩ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56934

መስከረም 26 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ አሰገደች የእናቶች እና የሕጻናት ሆስፒታል - ጠበቃ ብስራት መኮንን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር - ነ/ፈጅ እድገት ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአስፈጻሚ አካል ውሳኔ ይሰረዝልን ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ አመልካቾች በሕጉ አግባብ የመከራከር መብት ሳይጠብቅላቸውና ጥፋታቸውም በአግባቡ ሳይረጋገጥ የሙያ ሥነ ምግባር ጉድለት ፈፅመዋል ተብሎ ድምዳሜ መደረሱም ሆነ የተጣለው ቅጣት ሕጉን ያልጠበቀ ከመሆኑም በላይ የውሳኔው ሀሳብ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤት ያቀረበው አካል ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ከሕግ ውጪ የተሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ውሳኔው በሕጉ አግባብ የተሰጠ በመሆኑ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በሁዋላ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ሕጉን መሰረት አድርጎ የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት የአመልካቾችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ሕጉን ተከትሎ የተሰጠ አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሳኔን ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሠጠው ውሳኔ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ሰኔ 04 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሰባት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የአመልካቾች የመከላከል መብት በሕግ አግባብ ሳይጠበቅና ውሳኔው ሥልጣን በሌለው አካል የተሰጠ ሆኖ እያለ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ አይሰረዝም ተብሎ



www.chilot.me

የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሕክምና ሥነ ምግባር ጉድለት ተፈፅሟል? ወይስ አልተፈፀመም? የሚለውን ጉዳይ የጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚመረምርበት ጊዜ ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ ስድስት የተዘረዘሩት አመልካቾች ስለጉዳዩ ሙሉ የመከራከርና የመሰማት መብታቸው ታልፎ በመታየቱ የተነሳ በየጉዳዩ ውጤት ላይ ለውጥ ያስከትላል ወይስ አያስከትልም? እንዲሁም በዚህ ጉዳይ በፍትሐብሔሩ የካሣ ጥያቄ ቀርቦ አመልካቾች በፍርድ ኃላፊነት የለባቸውም በሚል በነጻ የተሰናበቱ ከመሆኑ አኳያ ጉዳዩን ለማየት ይቻል ዘንድ በሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ተጠሪ ቀርቦ ሐምሌ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ አመልካች ፈቃድ ተሰጥቶት የሚሰራ የጤና ተቋም ሁኖ ሌሎች አመልካቾች ደግሞ 1ኛ አመልካች ተቋም ውስጥ የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች መሆናቸውን በ1ኛ አመልካች ውስጥ ህክምና ሲሰጣቸው የነበሩት ወ/ሮ የኔነሽ ደምሰው ለሕልፈት መዳረጋቸውን ለህልፈት የተዳረጉትም ከህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ጉድለት ጋር የተያያዘ ነው የሚል አቤቱታ ለተጠሪ ሲቀርብለት የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጉዳዩን ሲያጣራ ቆይቶ የካቲት 8 እና 11 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጋቸው ስብሰባዎች በ1ኛ አመልካች ላይ የስድስት ወር የፈቃድ እገዳ በዶ/ር አሰገደች ላቀው ላይ የአንድ ዓመት የስራ ፈቃድ እገዳ፣ በዶ/ር ጌታቸው ተፈራ እና በሲስተር አበባ ኪዳኔ ላይ የስድስት ወር የስራ ፈቃድ እገዳ፣ በሲ/ር ወጋየሁ አለሙና በአቶ አረፋይኔ ገ/እግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤና ቅጣት ውሳኔ አስተላልፎ ተጠሪ መስሪያ ቤት የኮሚቴውን ውሳኔ ተቀብሎ ማጽደቁን ነው፡፡

አመልካቾች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉበት አንዱ ምክንያት ለ1ኛ አመልካች በተላከው መጥሪያና ክስ ሌሎች አመልካቾች ቀርበው ለኮሚቴው መልስ ሰጥተው አልተከራከሩም፣ አልተሰሙም በማለት እና ይህ አካሄድ የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎችን መማክርት ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 16 ስር የተመለከተውን ያላሟላ ነው የሚል ነው፡፡ ይኸው የተጠቀሰው ደንብ ድንጋጌ የሙያ ሥነ ምግባር ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባርን ያስቀመጠ ሲሆን በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ ስር የጤና ሙያ የሚጠይቀው ሥነ ምግባር ባለመከበሩ በባለሙያ ላይ የሚቀርብ ክስን ተቀብሎ ምርመራ እንደሚያካሂድና እንደሚያጣራ የደነገገ ሲሆን የአንቀጹ ንኡስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ በንዑስ ቁጥር አንድ መሰረት የሚቀርበውን ክስ ለማየት በቂ ማስረጃ መኖሩን ካረጋገጠ መልሱን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይዞ እንዲቀርብ በመግለጽ ክሱን ክስ ለቀረበበት ባለሙያ ይልካል በሚል አስቀምጧል፡፡ እንግዲህ ንዑስ ኮሚቴው ሊከተለው የሚገባውን ሥርዓት ሕጉ ከላይ በተመለከተው መልኩ ያስቀመጠው ሲሆን ይህ ስነ ስርአት የባለሙያውን የመሰማት መብት የሚያስጠብቅ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ምላሽ የሚይስፈልገው ነገር ይህ ሥነ ሥርአት በሕጉ መንፈስ መሰረት አልተጠበቀም ለማለት ይቻላልን? የሚለው ነው፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ የሚከራከሩት በሕጉ መሰረት ለአመልካቾች ክሱና ማስረጃው ደርሷቸው መልስ ሳይሰጡና መልሳቸው ሳይመረመር ውሳኔ ተሰጥቷል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ 1ኛ አመልካች ክሱ ደርሶት በጹሑፍ መልስ የሰጠበት፣ ሌሎች



www.chilot.me

አመልካቾች ደግሞ በጽሑፍ መልስ ባያቀርቡም ቀጠሮ ተሰጥቷቸው ጉዳዩን በያዘው ንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርበው ቃላቸውን የሰጡ ስለመሆኑ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ አስቀርቦ ይህንኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም 1ኛ አመልካች ክስና ማስረጃ አልደረሰኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር እውነትነት የሌለው በመሆኑ የሥነ ሥርዓት ግድፈት አለበት ለማለት የማይቻል ሲሆን ሌሎች አመልካቾችን በተመለከተ ደግሞ ምንም እንኳ አመልካቾች በፁሑፍ ክስና ማስረጃ ደርሷቸው ወደ ክርክሩ ሂደት ባይገቡም በንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርበው ግን ተገቢውን ቃላቸውን የሰጡ በመሆኑ እነኚህ አመልካቾች አልተደመጡም ወይም የመሰማት መብታቸው ተነፍጓል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ጉዳዩን ሲመለከት የነበረው አካል ሲያካሂዳቸው የነበራቸው ስብሰባዎች በርካታ ጊዜ የተደረጉ፣ በተገቢ ባለሙያዎች አስተያየት የተሰጠበት የነበረ መሆኑን የአስተዳደር ውሳኔ አካሄድና ይዘት ከማሳየቱም በላይ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ውሳኔ የሚያስተላልፉበት ጥብቅ የሆነ የክርክር ሥርዓትን ጠብቀው ነው ለማለት የማያስደፍር መሆኑን በኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎችን መማክርት ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 16 ስር የተመለከቱት አጠቃላይ የስነ ስርአት ደንቦች አስገዳጅ የሆነ ሥርዓት አለመሆናቸው የድንጋጌዎቹ ይዘታቸውና አቀራረፃቸው የሚያስገነዝብ መሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ በአመልካቾች የመሰማት ወይም የመደመጥ መብት ላይ መሰረታዊ የመብት መጣበብ ወይም ግድፈት ያስከተለ ሁኔታ ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ክሱን የመከላከል መብት አልተከበረም በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው ከዚሁ ነጥብ ጋር ተያይዞ በአመልካቾች የቀረበው ቅሬታና በዚህ ችሎትም እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ አመልካቾች በፍትሐብሔር የካሣ ጥያቄ ቀርቦ አመልካቾች በፍርድ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ በነፃ መሰናበታቸው የመከላከል መብታቸው ቢከበር ኑሮ ሊያስከትል ይችል የነበረው ውጤት ነው፡፡ በእርግጥ አመልካቾች በፍትሐብሔር የካሣ ጥያቄ በመደበኛው ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦባቸው የመከላከያ ማስረጃ አሰምተው ክሱ ውድቅ ሁኖ በነፃ የተሰናበቱ መሆኑን በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 51700 ግንቦት 03 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ የሚያሳይ ሲሆን ይህ ውሳኔ ለማስረጃነት በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ሲሆን በዚህ ሰበር ችሎትም በመከራከሪያነት የቀረበው የመከላከል መብት ቢጠበቅ ሊከተል ይችል የነበረውን ውጤት ያሳያል በሚል እምነት በመሆኑ እና ይህ ችሎት ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው አመልካቾች የመሰማት መብታቸው ተነፍጓል ለማለት አይቻልም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰ በመሆኑ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር የካሣ ጥያቄ ላይ የሠጠው ውሳኔ በአመልካቾች ላይ ተጠሪ ለወሰደው እምርጃ አመልካቾች የመሰማት መብት ቢከበርላቸው ኑሮ የተለየ ውጤት ሊያስከትል ይችል ነበር ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ሊሆን የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት በሕጉ በተዘረጋለት ሥርዓት መሰረት የሰጠው ውሳኔ እንጂ ከሕጉ ውጪ የተሰጠ ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥረ 47731 ግንቦት 23 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡



www.chilot.me

2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

በዚህ ችሎት ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 32282

መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

በላቸው አንሺሶ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች ፡-** ሚ/ር ካርሎ ካስቴሊ

**ተጠሪ ፡-** የወ/ሮ ዘውዴ ደሚኒኮ ውርስ አጣሪ አቶ ታምራት ኪዳነ ማርያም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43181 ጥቅምት 7 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና ከውሣኔው በፊት ባቀረብኩት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ላይ የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 28021 ግንቦት 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሀምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የወ/ሮ ዘውዴ ዶሜኒኮ የውርስ አጣሪ ሆነው ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜኒኮ በአሜሪካን አገር በእንግሊዘኛ ቋንቋ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ፌብሪዋሪ 6 ቀን 2005 ዓ.ም በአደረጉት ግልፅ ኑዛዜ የተሾሙ መሆኑን በመግለፅ የአሁን አመልካች ከሟች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሚኒኮ ጋር መስከረም 29 ቀን 1990 ዓ.ም በተደረገ የኪራይ ውል በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 23 ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 1822 በወር ብር 6500 (ስድስት ሺ አምስት መቶ ብር) ለመክፈል ተስማምተዋል ስለዚህ የኪራይ ገንዘቡን እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቡ በማለት አቶ ታምራት ኪዳነማርያም ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አመልካች አቶ ታምራት ኪዳነማርያም በውርስ አጣሪነት ተሹሜበታለሁ የሚሉት ኑዛዜ በውጭ አገር የተደረገ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም ስለዚህ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ሥልጣን ስለሌለው ክስ ሊያቀርብብኝ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ብይን ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ በማከራከር አመልካች ተጠሪ ክስ ያቀረበበትን ቤት ለውርስ አጣሪው እንዲያስረክብ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ



www.chilot.me

ስህተት የለም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በውጭ ቋንቋ ተፅፈው ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ሰነዶች በኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤቶች ተረጋግጠው ካልገቡ በስተቀር ውጤት እንደማይኖራቸው የሰነዶች ምዝገባ አዋጅ 334/95 አንቀፅ 2 አንቀፅ 26 እና አንቀፅ 27(1)ን አጣምሮ በማንበብ ለመገንዘብ እየተቻለ በኢትዮጵያ ቆንጺላ ባልተረጋገጠና ሚች ወ/ሮ ዘውዴ አሜሪካን አገር አድርገውታል ተብሎ በቀረበ ኑዛዜ የውርስ አጣሪ ሆኖ ተሹሟል በሚል ምክንያት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ሥልጣን ሣይኖረው ያቀረበውን ክስ ተቀብሎ ማስተናገዱና ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሥለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሚች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሚኒኮ በውጭ የኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤቶች አለመረጋገጡ ሰነዱን ህጋዊ ውጤት እንዳይኖረው የሚያደርግ ምክንያት አይደለም፡፡ ህጋዊ ውጤት እንዲኖራቸው የግዴታ መመዝገብና መረጋገጥ የሚገባቸው ሰነዶች ዝርዝር በአዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 5 ተደንግጓል፡፡ የኑዛዜ ሰነድ ህጋዊ ውጤት ለማግኘት መመዝገብና መረጋገጥ ያለበት ሰነድ ስለመሆኑ በአንቀፅ 5 አልተደነገገም፡፡ ስለሆነም አመልካች ሚች ዘውዴ ዶሜንኮ በአሜሪካን አገር ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ ሰነድ የመመዝገብና የማረጋገጥ ሥልጣን ባላቸው የኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤት ያልተረጋገጠ ስለሆነ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ በፅሑፍ ካደረጉት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን የሚችን ወራሾች በመወከል በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበውና የውርስ አጣሪ ሆኜ ተሹሜአለሁ የሚለው ሰው የውርስ አጣሪ ሆኖ የተሾመበት የወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ በውጭ አገር አድርገውታል የተባለው ግልፅ ኑዛዜ ሰነድ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው ሚች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜኒኮ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ፌብሪዋሪ 6 ቀን 2005 ዓ.ም በአሜሪካን አገር ሆነው በእንግሊዘኛ ቋንቋ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 881 መሠረት ባደረጉት ግልፅ ኑዛዜ ክስ የቀረበበትን ቤት በኤርትራ ግዛት አሥመራ ከተማ ውስጥ የእየሱስ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደቂ ገብሩ ለሚገኝና አብርሀበሀታ አይነስውራን ትምህርት ቤት ሙሉ የባለቤትነት መብቱ እንዲዛወር የተናዘዙ መሆኑንና ይህንንና ሌሎች የኑዛዜ ቃሎችን እንዲያስፈፅም አቶ ታምራት ኪዳነማርያም በውርስ አጣሪነት የሾሙ መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ ነው፡፡ ተጠሪ የሚከራከሩት ይህ ኑዛዜ በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 ሰነድ በሚለው ትርጉም ሥር የሚወድቅ ቢሆንም ሰነዱ በውጭ አገር የኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤቶች አለመመዝገቡና አለመረጋገጡ ህጋዊ ውጤት አያሳጣውም፡፡ ምክንያቱም “ኑዛዜ” ካልተረጋገጠና ካልተመዘገበ ህጋዊ ውጤት ከማይኖራቸው ሰነዶች አንደኛው አለመሆኑን ከአዋጁ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መረዳት የሚቻል በመሆኑ የሚል ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን አተረጓጎም በመከተል ሚች በውጭ አገር አድርገውታል የተባለው የኑዛዜ ሰነድ ህጋዊ ውጤት አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

በእኛ በኩል ተጠሪ ያቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ ኢትዮጵያ ውስጥ ያደረጉት የኑዛዜ ሰነድ ቢሆን ከላይ የተሰጠው የህግ ትርጉም ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ ያቀረበው ሚች ኢትዮጵያ ውስጥ ያደረጉትን የኑዛዜ ሰነድ ሣይሆን በአሜሪካን አገር ፈፅመውታል የተባለውን



www.chilot.me

የኑዛዜ ሰነድ በሌላ አነጋገር የውጭ አገር ሰነድ (Foreign document) ነው፡፡ አንድ ሰነድ የውጭ አገር ሰነድ (Foreign document) የሚባለው በውጭ አገር ተፅፎ ተዘጋጅቶ ከውጭ አገር የተላከና ወደ አገር ውስጥ የገባ ሲሆን ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤቶች ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ የውጭ አገር ሰነድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ቢቀርብ ህጋዊ ውጤት ይኖረዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 334/1995 በውጭ አገር የተደረጉ ሰነዶች በአዋጁ መሠረት ካልተመዘገቡና ካልተረጋገጡ ህጋዊ ተቀባይነትና ውጤት አይኖራቸውም በማለት ያስቀመጠው ራሱን የቻለ ግልፅ ድንጋጌ የለም፡፡ አዋጁ ስለ "ውጭ ሰነዶች" መረጋገጥና ህጋዊ ውጤት ስለሚያገኙበት ሁኔታ ከላይ በተገለፀው መንገድ በግልፅ ያልደነገገ ቢሆንም በውጭ አገር ተደርጓል ተብሎ የቀረበ ኑዛዜ በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ወይም ቆንጺላ ጽ/ቤቶች ባይረጋገጥም በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ፊት ሲቀርብ ህጋዊ ውጤት ይኖረዋል ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከውጭ አገር የሚገቡ የመንግስትም ሆነ የግል ሰነዶች ትክክለኛነታቸው በኢትዮጵያ ኤምባሲ ጽ/ቤቶችና በውጭ በሚገኙ የኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤቶች እየተረጋገጡና እየተመዘገቡ መግባት ያለባቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 "በውጭ አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንጺላ ጽ/ቤቶች ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ሰነዶችን ያረጋግጣሉ" በሚል መንገድ የደነገገና ይኸም ድንጋጌ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ መሆኑን በድንጋጌው የእንግሊዘኛ ቅጅ "Ethiopian Embassies and Consular offices shall authenticate documents entering in to Ethiopia" በማለት ከውጭ አገር የሚገቡ ሰነዶች ትክክለኛነት በኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት ትክክለኛነታቸው መረጋገጥ ያለበት መሆኑ አስፈላጊና የግድ መፈፀም የሚገባው ተግባር መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የውርስ አጣሪ ሆኜ ተሹሜበታለሁ የሚለው በውጭ አገር ሟች አድርገውታል የተባለው የኑዛዜ ሰነድ የአዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት አሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ትክክለኛነቱ ተረጋግጦና ተመዝግቦ የመጣ ሰነድ አይደለም፡፡ ሰነዱ በህጉ በአስገዳጅነት የተቀመጠውን መስፈርት ማለትም በውጭ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት ትክክለኛ ሰነድ መሆኑ ተረጋግጦና ተመዝግቦ ያልቀረበ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው ስለማይገባ ተጠሪ የውርስ አጣሪ ሆኜ ተሹሜበታለሁ በማለት ያቀረበው ሰነድ አመልካችን በፍርድ ቤት ከስሶ ለመከራከር የሚያስችለው ሰነድ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ክስ ለማቅረብ ሥልጣን አግኝቼበታለሁ በማለት ያቀረበው ኑዛዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገ ሣይሆን በውጭ አገር ተደረገ ተብሎ የቀረበና ኑዛዜው የሟች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ ትክክለኛ የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበና ይኸም በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ሣያገናዝቡ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በመቀበል አከራካሪውን ውሣኔ መስጠታቸው ከላይ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ ይዘት መንፈስ ዓላማና የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43181 ጥቅምት 7 ቀን 1999 የሰጠው ውሣኔና ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይን ሙሉ ለሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ግንቦት 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
3. ሟች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ በአሜሪካን አገር አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ ትክክለኛነት አሜሪካን በሚገኘው በኢትዮጵያ ኤምባሲ ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የሌለውና ተጠሪን ክስ ለማቅረብ የሚያስችል አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 44226

ታህሳስ 15 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- 1. ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ
2. አቶ እየሱስወርቅ ዛፉ
3. አቶ ወርቅሸት በቀለ ደምሴ
} ጠበቃ እስራኤል ተክሌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ በአመልካች የወጣውን መመሪያ ሕጋዊነት አስመልክቶ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች የሕብረት ባንክ ባለ አክሲዮኖች መሆናቸውን፣ በ1952ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ የአክሲዮን ማህበር አስተዳደር ለማህበረተኞች እንጂ ለሌላ ሊሰጥ እንደማይችል በአንቀጽ 347/1/ ላይ የተገለፀ፣ ከባለ አክሲዮኖች መካከል በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ማለትም በባለ አክሲዮኖች እንደሚመረጡ በአስተዳደሪነት መመረጥ የሚችለው ለሶስት አመት እንደሆነ ሆኖም ግን የኩባንያው መመስረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ እስካልከለከለው ድረስ በድጋሚ ለምርጫ መቅረብ እንደሚችል በአንቀጽ 350 ስር መደንገጉን፣ የህብረት ባንክ መመስረቻ ጽሑፍም በድጋሚ መመረጥን እንደሚፈቅድ፣ የባንኩ መተዳደሪያ ደንብም በድጋሚ መመረጥን የሚከለክል ድንጋጌ የሌለው መሆኑን፣ 1952ዓ.ም የወጣው የንግድ ሕግ የአንድ ኩባንያ ዳይሬክተር በሌላ ኩባንያ ውስጥ በዳይሬክተርነት እንዲያገለግል የሚከለክል ድንጋጌ የሌለው መሆኑን፣ አዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 ስለባንክ ጉዳዮች መውጣታቸውንና ለአመልካች መመሪያ የማውጣት ስልጣን የሰጡት ቢሆንም በንግድ ሕጉ ስለ ዳይሬክተሮች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ለውጥ ያላደረጉ ወይም ገደብ ያላደረጉ ወይም ሌላ ወገን ገደብ እንዲያስቀምጥ ስልጣን ያልሰጡ መሆኑን፣ አመልካች ባንክ የስልጣኑ ምንጭ ሁለት አዋጆች ሆነው እያለ የባንክ ስራ ፍቃድና ቁጥጥር የተሻሻለ የአዲስ ባንክ የስራ ፍቃድና የዳይሬክተሮችና የዋና ስራ አስፈፃሚ ሹመት ማጽደቂያ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ/39/2006 የሚል በእግሊዝኛ የተፃፈ መመሪያ አውጥቶ በመመሪያው ላይ በአንቀጽ 5.1.4 እና 5.1.5 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ገደብ



www.chilot.me

የሚጥሱና ከንግድ ሕጉ፣ ከሕብረት ባንክ የመመስረቻ ጽሑፍ ጋር ፍፁም የሚጋጩ መሆናቸውን ዘርዝረው አመልካች ያወጣው መመሪያ እንዲታገድና በስራ ላይ እንዳይውል እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፣ አመልካች ሕገ ወጥ መመሪያ አላወጣም፣ መመሪያው የባለ አክሲዮኖችን የመመረጥና የመምረጥ መብት አላስቀረም የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 83/86 እና 84/86 መመሪያ የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ቢሆንም መመሪያ የሚወጣባቸው ጉዳዮች በአዋጆቹ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቻ በመሆኑ እና በሌሎች ህጎች በተለይም ከመመሪያው በላይ በሆኑ አዋጆች የተሰጡትን መብቶችና የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የማይቃረን መሆን የሚገባው ስለሆነ የተሻሻለው አዲስ የባንክ ሥራ ፈቃድና የዳሬክተሮች፣ የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሹመት ማጽደቂያ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ /39/2006 ላይ በአንቀጽ 5.1.4 እና 5.1.5 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሕጋዊ አይደሉም የሚል ምክንያት በመስጠት እነዚህ ድንጋጌዎች ተሽረዋል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 04 ቀን 2001ዓ.ም በፃፉት አምስት ገጽ አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑንና አከራካሪው መመሪያም የሕግ አወጣጥ ስርዓቱን መስረት አድርጎ የወጣና ከንግድ ሕጉም በላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮም ለሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጥቅምት 17 ቀን 2002ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ አመልካች ባወጣው የተሻሻለ አዲስ የባንክ ስራ ፈቃድና የዳይሬክተሮች፣ የዋና ስራ አስፈፃሚ ሹመት ማጽደቂያ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ /39/2006/ ስር የተመለከቱት አንቀጽ 5.1.4 እና 5.1.5 ድንጋጌዎች ሕጋዊ አይደሉም ተብሎ መሻሩ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

በመሠረቱ ሕግ የማውጣት ስልጣን በስልጣን ክፍፍል መርህ መሠረት የሕግ አውጪው አካል ስለመሆኑ እሙን ነው፡፡ በሕግ አውጪው የመንግስት አካል የሚወጡ ሕጎች ቀዳማዊ /Primary legislations/ ተብለው የሚታወቁ ሲሆን ሌሎቹ እንደአስፈላጊነታቸው አግባብ ባለው አካል የሚወጡ የበታች ሕጎች /Subsidiary legislations/ ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ሕግ አውጪው የመንግስት አካል በተለያዩ ቴክኒካዊ፣ ሙያዊና ማህበራዊ ምክንያቶች ቀዳሚውን ሕግ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ዝርዝር ሕጎች ያስፈልጋሉ ብሎ ባመነ ጊዜ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው አካል የበታች ሕጎችን እንዲያወጣ ስልጣን መስጠት የተለመደና ተቀባይነት ያለው አሰራር ነው፡፡ ይህ አሰራር በሕግም በምክንያትም የተደገፈ እና የዳበረ ልምድ ስለመሆኑ የታወቀ ነው፡፡ አሁን በተግባር ሥራ



www.chilot.me

ላይ ያለው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 14/88 አንቀጽ 2/1/ እንደሚያመለክተው ሕግ የሚላቸው አዋጅ ደንብና መመሪያዎችን ነው፡፡

ክርክሩ በተነሳበት ወቅት ተፈፀሚነት የነበረው አዋጅ ቁጥር 83/1986 ሲሆን ይህ አዋጅ ለገንዘብና ለባንክ አዋጅ የተደነገገ ሲሆን በዚህ ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከዚህ አዋጅ በፊት የተቋቋመ ሲሆን ባለበት እንዲቀጥል የደነገገ እና ስለ ባንኩ ዓላማዎች፣ ስልጣን እንዲሁም ተግባር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 84/1986 ደግሞ ለባንክ ስራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ነበር፡፡ በዚህ አዋጅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ፣ የኢንሹራንስና የአነስተኛ ገንዘብ ተቋማትን በተመለከተ ለመስራት የሚፈለጉ ሰዎችን ፈቃድ እንዲሰጥ፣ ከፈቃዱ በኂላ ቁጥጥር እንደሚያደርግ፣ ለፈቃዱ አሰጣጥ በቅድሚያ ሊሟሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ ያሳያል፡፡ አዋጅ ቁጥር 83/1986 አንቀጽ 61 ድንጋጌ ሲታይም ባንኩ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትና ይህንን አዋጅ በሚገባ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት እንደሚችል ሕግ አውጪው ስልጣን ሰጥቶታል፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 6 ስር የባንኩ ዓላማዎች የተረጋጋ የገንዘብ ሁኔታ መፍጠር፣ የአገሪቱ ገንዘብ አስተማኝ እንዲሆን ማድረግ፣ አስተማማኝ የፋይናንስ አቅም እንዲኖር ማድረግ እንዲሁም ለኢኮኖሚ እድገት አመቺ የሆኑ የክሬዲትና የምንዛሬ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ መጣር መሆናቸውን ደንግጓል፡፡ እነዚህን ዓላማዎችን ለማስፈፀምም ብሔራዊ ባንክ ስልጣንና ተግባሩ በአዋጁ አንቀጽ 7 ስር ተመልክቷል፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 60/2/ ስር ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም በሚል ደንግጓል፡፡ አዋጅ ቁጥር 84/1986 አንቀጽ 36 ደግሞ መመሪያ የማውጣት ስልጣንን ለአመልካች ሰጥቶታል፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 35 ስር ከአዋጁ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም በማለትም ተደንግጓል፡፡

እንግዲህ አመልካች በሕግ ኃላፊነትና ተግባሩ ተለይቶ የተሰጠው ሲሆን ይህንኑ ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣትና ሕጉን ለማስፈፀም መመሪያ የማውጣት ስልጣን በሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 የተሰጠው መሆኑን ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የባንኮችን ሥራ የመቆጣጠር ተግባርና ኃላፊነት ደግሞ እንደማንኛውም ቁጥጥር የማድረጊያ ስርዓት ሊፈፀም የሚችለው የፋይናንስ ተቋሞችንና የባንኮችን ተግባርና ኃላፊነት አስቀድሞ በሕግ በመወሰን፣ ይህንኑ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ስራ ላይ የሚያውሉበትን ደንብ እንዲኖራቸው በማድረግ እና በአመራራቸውም ላይ በተለያየ ሕጋዊ መንገዶች ቁጥጥር በማድረግ ስለመሆኑ ይታመናል፡፡ የባንኮችን ስራ የመቆጣጠር ስራ ለጉዳዩ የተለየ እውቀትና ልምድ ያለውን ተቋም /አካል/ ባለሙያ የሚያስፈልግ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት በሰፊው የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው መሆኑም ይታወቃል፡፡ በ1952ዓ.ም በወጣው የንግድ ሕግ የአንድ ኩባንያ ዳይሬክተር በሌላ ኩባንያ ውስጥ በዳይሬክተርነት እንዲያገለግል የሚከለክል ድንጋጌ የሌለው መሆኑና አጠቃላይ ስለ ዳይሬክተሮች የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነታቸው የነበረው ከባንክና ከፋይናንስ ተቋማት ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የንግድ ማህበራትም ላይ ጭምር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሕግ አውጪው ባንክና የፋይናንስ ተቋማትን በተወሰነ ደረጃ በተለየ የሕግ ማዕቀፍ እንዲገዙ አድርጓል፡፡ በ1952ዓ.ም የወጣው የንግድ ህግ በሕጎች አወጣጥ ደረጃ አዋጅ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986ዓ.ም ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው ሕጎች ናቸው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 በሚሸፈኑ ጉዳዮች የንግድ ሕጉ የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑ ከሕጉቹ አወጣጥ ቅደም ተከተልና ደረጃ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 ከንግድ ሕጉ እኩል



www.chilot.me

ደረጃ ያላቸው በመሆኑና በኂላም የወጡ በመሆኑ በገንዘብና በባንክ እንዲሁም ስለ ባንክ ስራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር ቀዳሚ ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን ከሕጎች አተረጓጎም ደንብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አዋጆቹ ከንግድ ሕጉ ቀድመው የሚፈፀሙ ናቸው ከተባለ አመልካች ያወጣው መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ /39/2006 እነዚህ አዋጆቹን መሠረት አድርጎ የወጣ በመሆኑ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ከንግድ ሕጉ በላይ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ የስር ፍ/ቤት ሕጎቹ የወጡበትን ስርዓት፣ ሕጉቹ የሚፈፀሙትን ጉዳይ እና በአፈፃፀም ደረጃ ያላቸውን እርከን በአግባቡ ሳይለይ አመልካች ባወጣው መመሪያ ውስጥ የተካተቱት አንቀጽ 5.1.4 እና 5.1.5 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ሊኖራቸው አይገባም በማለት እንዲሻሩ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 93620 ጥር 02 ቀን 2000ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64552 ታህሳስ 09 ቀን 2001 የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 መመሪያውን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ የተሻሻለው አዲስ የባንክ ስራ ፈቃድና የዳይሬክተሮች፣ የዋና ስራ አስፈፃሚ ሹመት ማጽደቂያ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ /39/2006 አንቀጽ 5.1.4 እና አንቀጽ 5.1.5 ከ1952ቱ የንግድ ሕግ ጋር የሚጋጭ ነው ተብሎ ሊሻር የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሶ/በ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53221

ታህሳስ 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ተስፋዬ ምንዳገኝ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ንጋቱ ወ/ሰንበት - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ፀሐይ በቀለ ባል ነኝ በማለት የሰጠው ውሳኔ የባልና ሚስት ግንኙነት (ጋብቻ) ሳይኖር የተሰጠ በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች መቃወሚያውን ያቀረበው ተጠሪ የሟች ባል መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ ለሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በመቃወሚያ ሥረ ነገር ላይ ገብቶ ሳያከራክር ተጠሪን መልስ እንዲሰጥ ሳያደርግ አመልካች መቃወሚያውን ለማቅረብ የሚያስችል መብት የለውም በማለት ሳያስተናግደው ቀርቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ትዕዛዙን በመቃወም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች በተሰጡት ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል በማለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርብም፤ የሰበር ችሎቱ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው አመልካች ተጠሪ በሰጠው የባልነት ውሳኔ ላይ መቃወሚያ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች መቃወሚያ ሲያቀርብ የቻለው ተጠሪ ሐሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ በተሰጠው የባልነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በመጠቀም የጡረታ አበል እንዲከፈለው በማስወሰኑ እና ይህን ውሳኔ መሠረት በማድረግም አበሉን መውሰድ በመጀመሩ ነው፡፡ በእርግጥም ተጠሪ የሟች ባል ነው ተብሎ የጡረታ አበል እንዲከፈለው ከተወሰነ አመልካች በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም ይገደዳል፡፡ ከዚህ ግዴታ ነፃ ሊሆን የሚችለው ተጠሪ የሟች ባል ነው የተባለበትን ውሳኔ ከመሠረቱ ማሻር ሲችል ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መቃወሚያ ያቀረበውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች መቃወሚያውን ሳያስተናግዱ የቀሩት ተጠሪ የሟች ባል ነው በመባሉ መብቱ (የአመልካች) ተነክቶአል ሊባል አይችልም የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

በሕግ መሠረት የጡረታ አበል የሚከፈላቸው ሰዎች አበሉን የሚያገኙ ከአመልካች ኤጀንሲ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አመልካች አበሉን መክፈል ያለበት ሕጉን መሠረት በማድረግ ብቻ እንደሆነም አያከራክርም፡፡ ይህ ሁኔታ ከሌላ አቅጣጫ ሲታይ ደግሞ አመልካች በሕግ የተመሠረተ መብት ለሌለው ሰው አበሉን አልከፍልም የማለት መብት አለው ማለት ነው፡፡ አመልካች በዚህ በያዝነው ጉዳይ እያለ ያለውም ይኸው ነው፡፡ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሳኔ (ክፈል የሚል) በመኖሩ ግን በራሱ ሥልጣን መክፈል ማቆም ያስቸግረዋል፡፡ በመሆኑም ለአበሉ ክፍያ መሠረት ሆኖአል ያለውን ውሳኔ ለመቃወም ቀርቦአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.358 እንደተደነገገው ቀደም ሲል ለተሰጠው ውሳኔ መሠረት በሆነው ክርክር ተካፋይ ያልነበረ ሰው ውሳኔው እንዲሻርለት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ (ውሳኔ) መብቱን የሚነካበት እንደሆነ ነው፡፡ ፍርዱ መብቱን የሚነካበት ከሆነ ደግሞ በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ የመሆን በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተረጋገጠለት መብት አለው ማለት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ሕጋዊ መሠረት የሌለውን የጡረታ አበል የመክፈል ግዴታ የለበትም ወይም ደግሞ አልከፍልም የማለት መብት አለው የሚል መነሻ ተይዞ ነው መቃወሚያው የቀረበው፡፡ በእርግጥም አመልካች መብቱን ማስከበር የሚችለው በክርክሩ ውስጥ በመግባት የበኩሉን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች መቃወሚያውን ባለማስተናገዳቸው ክርክሩን ለማቅረብ አልቻለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የተከተሉት አካሄድ ሕጉንና የሥነ ሥርዓት ደንቦቹን የተከተለ አይደለም፡፡ የሰጡት ውሳኔም በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ የካ-1624/98 መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁ 10067 ህዳር 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የይግባኝ ሰሚው ሰበር ችሎት በመ.ቁ 12586 የካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበለትን መቃወሚያ በመቀበል እና ተጠሪ በመቃወሚያው ሥረ ነገር ላይ የሚሰጠውን



www.chilot.me

መልስ በመስማት ግራቀኝ ወገኖቹን በማከራከር ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.341(1) መሠረት ወሰነናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

ራ/ታ

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

የሰ/መ/ቁ. 59261

ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡ - ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡** - የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ወኪል ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡** - አቶ ታዬ በዛብህ ፊኖ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው በቀጥታ ለፍ/ቤት በቀረበ ክስ መነሻ ፍትህ ሚኒስቴር ለአሁኑ ተጠሪ የጥብቅና ፈቃድ በመስጠት እንዲመዘግባቸው በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10(3) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄ ለፍትህ ሚኒስቴር አቅርበው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ በሚመለከት በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 21 መሠረት በጥብቅና ገምጋሚ ኮሚቴ ተመርምሮ የተሰጠው የውሣኔ ሃሳብ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 26 መሠረት ለሚኒስትሩ ቀርቦ የጥብቅና ፈቃድ እንዳይሰጣቸው ተብሎ በመወሰኑ በአዋጅ አንቀጽ 29(1) በሚደነግገው መሠረት የጥብቅና ፈቃድ ጠያቂው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ክርክሩ ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ መርምሮ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ “2” መሠረት በሕጉ ጉዳይ ላይ ውሣኔ በመስጠት መታየት ይገባዋል ባለው ፍሬ ነገር ላይ ሚኒስትሩ አይቶ በ30 ቀን ውስጥ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብሎ የመለሰው ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ሚኒስትሩ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆን ለ40 ቀናት ውሣኔ ሳይሰጥበት በማቆየት የጥብቅና ፈቃድ እንዳላገኝ ስላደረገ ክልከላው ተወግዶ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጠኝ ይታዘዝ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 314(1) መሠረት በቀጥታ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ በዚህ የክልከላ ይወገድ ክስ ተከሳሽ የሆነው የፍትህ ሚኒስቴር ወኪል ቀርበው ጉዳዩን ገምጋሚ ኮሚቴ ተመልክቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት አስተላልፈናል የሚል መልስ እንደሰጡ ተመዝግቦ ፍ/ቤቱ መርምሮ ፍትህ ሚኒስቴር ጉዳዩን ለማየት ፈቃደኛ መሆኑን ከመግለጽ በቀር ክልከላው የማይወገድበት ምክንያት ስለመኖሩ ስላላስረዳ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 314(2) መሠረት ክልከላው ተወግዶ ለከሣሹ የጥብቅና ፈቃድ በመስጠት ይመዝግባቸው በሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡



www.chilot.me

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤትም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ምክንያት የቀረበ ሲሆን ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ ተብሎ ስለታዘዘ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪው ታህሣሥ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፣ የአመልካቹ አቤቱታ ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም የሚሉባቸውን ምክንያቶች ገልፀው አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተጠሪው በኩል የተሰጠውን መልስ በማስመልከት የመልስ መልስ እሰጣለሁ ካለ ይቅረብ የተባለ ቢሆንም ከመዝገቡ እንደሚታየው ያቀረበው የመልስ መልስ የለም፡፡

ሰበር ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠኝ ጥያቄ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ በሚመለከት በተለይ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 20፣21 እና 26 መሠረት ታይቶ ሚኒስትሩ የጥብቅና ፈቃድ እንዳይሰጥ ብሎ በሰጠው ውሣኔ ላይ ፈቃድ ጠያቂው በተጠቀሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29(1) መሠረት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክሩ ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ መርምሮ የሕግ ጉዳይ ነው ባለው ነጥብ ላይ ውሣኔ በመስጠት በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "2" መሠረት በቀሪው ፍሬ ነገር ላይ ሚኒስትሩ አጣርቶ በ30 ቀን ውስጥ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብሎ መልሶት ሚኒስትሩ ውሣኔ ሳይሰጥበት ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ እያለ ተጠሪው ሚኒስትሩ በተባለው 30 ቀን ውስጥ ውሣኔውን ባለመስጠቱ ምክንያት የአሁኑ አመልካች ያደረገብኝ የጥብቅና ክልከላ ይወገድ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.314(1) መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት በሕጉ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም? የአሁኑ ተጠሪ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት ፍትህ ሚኒስቴር በ30 ቀን ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ሳይሰጥ ቢቀርና ቢያዘገየው ምን ማድረግ አለባቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ሲታዩ፡ -

በፌዴራል ፍ/ቤቶች ለመስራት የሚቀርብ የጥብቅና ፈቃድ መስጠትና ምዝገባ ጥያቄን በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 19 መሠረት አይቶ የመወሰን ስልጣን የተሰጠው ለፍትሕ ሚኒስቴር ነው፡፡

በመጀመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 20 እና 21 መሠረት የአመልካቹን የጥብቅና ፈቃድ ጥያቄ አይቶ ማስረጃዎቹን በመመርመር ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዳይሰጠው ለሚኒስትሩ የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርበው የጥብቅና ገምጋሚ ኮሚቴ ነው፡፡ በአንቀጽ 26 ላይ እንደተመለከተው የጥብቅናው ፈቃድ ይሰጥ ወይንስ አይሰጥ የሚለውን የመጨረሻውን ውሣኔ የሚሰጠው ሚኒስትሩ ነው፡፡ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የሚኖረው ከዚህ የሚኒስትሩ ውሣኔ በኋላ በአዋጅ አንቀጽ 29 መሠረት በይግባኝ ደረጃ ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ይግባኝ የሚያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ሚኒስትሩ የጥብቅና ፈቃድ እንዳይሰጥ በማለት በሰጠው ውሣኔ መነሻ በቀጥታ ለፍ/ቤት የሚቀርብ ክስ አይኖርም፡፡ በሕጉ ይግባኝ እንዲባልበት ብቻ የተፈቀደ ነው፡፡

በአሁኑም ጉዳይ ተጠሪው አዋጁን በተከተለ መንገድ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠኝ ጥያቄ ለፍትሕ ሚኒስቴር አቅርበው ታይቶ ሚኒስትሩ የጥብቅና ፈቃድ እንዳይሰጥ የሚል ውሣኔ በመስጠቱ በሕጉ በተፈቀደው የይግባኝ ሥርዓት በመጠቀም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክሩ ተሰምቶ ፍ/ቤቱ መርምሮ በሕጉ ጉዳይ የራሱን ውሣኔ ሰጥቶበት በቀሪ ፍሬ ነገር ላይ ራሱ ፍትህ ሚኒስቴር አይቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት የመለሰው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ወደ ፍትህ ሚኒስቴር የመለሰው በ30 ቀን ውስጥ አይቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት ነው፡፡ ሆኖም ፍትሕ ሚኒስቴር ከፍተኛው ፍ/ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ ታይቶ እንዲወሰን በመፈለግ ውሣኔው በ30 ቀን ውስጥ አይቶ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት ባዘዘው መሠረት ሳይፈጽም ቆይቷል፡፡ ጉዳዩም ገና በእንጥልጥል ላይ ስለሚገኝ ውጤቱ ምን እንደሚሆን አይታወቅም፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ሁኔታ ምን ማድረግ ይችላሉ? በሕጉ ክስ ማቅረብ ይችላሉ ወይ? የሚለውን በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለፀው በቀጥታ ክስ ለፍ/ቤት ቀርቦ የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡ የጥብቅና ክልከላ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 29(1) መሠረት ሥልጣኑ ለሚመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ቀርቦ ታይቶ የሚወሰን እንጂ ክልከላ ይወገድ በሚል በቀጥታ ለፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብበት ባለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.314 ድንጋጌ በእንዲህ አይነቱ ጉዳይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ ተጠሪ የአሁኑ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንደገና ጉዳዩን አይቶ ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት ባለመፈለግ የሚያዘገየው ከሆነ በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀምላቸው ማመልከት ያለባቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በውሣኔው መሠረት እንዲፈጸም ሊያስገድደው የሚችለውም ይኼው ውሣኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ መንገድ በመጠየቅ በጥብቅና ፈቃድ ጥያቄው ላይ ውሣኔ እንዲሰጥ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች የጥብቅና ፈቃድ ክልከላ አድርጉብኛል በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.314(1) መሠረት ክልከላው ይወገድ በሚል በቀጥታ ለፍ/ቤት የክስ አቤቱታ ያቀረቡት በሕጉ አግባብ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የጥብቅና ፈቃድ ጉዳይን በተመለከተ በተለይ በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/1992 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት ታይቶ የሚወሰንና ለፍ/ቤትም የሚቀርበው በይግባኝ ደረጃ ብቻ መሆኑ እየታወቀ የጥብቅና ፈቃድ ክልከላ ተደርጓል በሚል ምክንያት በቀጥታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.314 መሠረት የቀረበውን ክስ በመቀበል የአሁኑ አመልካች ለተጠሪው የጥብቅና ፈቃድ በመስጠት እንዲመዘግባቸው በሚል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.166328 በ25/8/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 94250 በ27/09/2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59979

የካቲት 9 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን - ሠላማዊት ሀይሉ - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ከበደ ወዳጆ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በወሮጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ለሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ አመልካች (ተከሳሽ) በጅማ ገነት ወረዳ ውስጥ የገጠር መንገድ ሲጠግን አላግባብ በእርሻ መሬት ይዞታዬ በመግባት የተለያዩ ቋሚ አትክልቶች የሰብል ምርትና ሣር ቤት አውድሞብኛል፡፡ ተከሳሽ በቆፈረው ጉድጓድ በሬ ገብቶ ስለሞተብኝ የበሬውንም ዋጋ እንዲከፍለኝ በማለት በአጠቃላይ የጉዳቱን መጠን ብር 71950 ብር በመገመት ካሳ እንዲከፈለው ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የይርጋ ጊዜው አልፏል፡፡ ሥራ ያሠራሁት በክልሉ አዋጅ ቁጥር 11/88 በተሰጠኝ ሥልጣንና ሀላፊነት መሠረት ነው፡፡ ከሳሽ አሉ የሚሏቸው ንብረቶች በቦታው ላይ አልነበረም፡፡ የበሬ ዋጋ ልንከፍል አንገደድም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች (ተከሳሽ) በተጠሪ ይዞታ ሥር የነበሩ ግምታቸው ብር 7,850 (ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሀምሳ ብር) ያላቸው የተለያዩ ተክሎች አውድሟል፡፡ የከሳሽ(ተጠሪ) በሬ ተከሳሽ ከቆፈረው ጉድጓድ ገብቶ የሞተ ስለሆነ ብር 2,500 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) በጠቅላላው ብር 10,350 (አስር ሺ ሶስት መቶ ሀምሳ ብር) አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይዞታው የተጠሪ ይዞታ መሆኑ በተጠሪ ይዞታ ላይ ያለው ተክል ላይ አመልካች አላግባብ ጉዳት እንዳደረሰ የተረጋገጠ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች ለተጠሪ ብር 7,750 (ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) እንዲከፍል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው፡፡ አመልካች



www.chilot.me

የበሬ ዋጋ ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ጳጉሜ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2143ን በመጥቀስ ያቀረብነውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው አላግባብ ነው፡፡ በመሬቱ ላይ አትክልትና ንብረት እንደሌለ ተረጋግጦ እያለና በአዋጅ በተሰጠኝ ሥልጣን መሠረት መንገድ የጠገንኩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ካሣ እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የጠቀሳቸው የይርጋ ድንጋጌዎች ማለትም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149(1) እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2143 በእኔና በአመልካች መካከል ባለው ክርክር ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡ አመልካች በህጋዊ ይዞታዬ ላይ በነበሩት ቋሚ አትክልቶች ላይ ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ለህዝብ ግልጋሎት የሚሰጥ የመንገድ ጥገና ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የተጠሪን ይዞታና በተጠሪ ይዞታ ላይ ያሉ የተለያዩ ተክሎች ላይ ጉዳት ስላደረሰ ካሣ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ከውል ውጭ የሚደርስ ሀላፊነትን የሚመለከት ክስ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ አመልካች ይዞታውን ለህዝብ ጥቅምና ግልጋሎት የሚውል መንገድ ለመጠገን ከወሰደ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 8 መሠረት በይዞታው ላይ ለነበረው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ በመሬቱ ላይ የነበሩትን ተክሎች ዋጋ ይክፈለኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 8 መሠረት ለተወሰደ ንብረት ካሣ እንዲከፈላቸው ተጠሪ የመጠየቅ መብት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2143 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ የማይገደብ መሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42629 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢና መሠታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ በይዞታ መሬቴ ላይ ነበሩ ከሚላቸው የተለያዩ አይነት ቋሚ ዛፎችና አትክልቶች ጠቅላላ ግምት ከብር 60,000(ስልሣ ሺህ ብር) በላይ እንደነበርና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በተጠሪ ይዞታ ላይ የነበሩትና በአመልካች ጉዳት የደረሰባቸው ተክሎችና ዛፎች ግምት 7,750 (ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ይህንን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል ወስነዋል፡፡ አመልካች በቦታው ላይ ምንም አይነት ንብረት የለም በማለት በሰበር አቤቱታው የሚከራከር ቢሆንም ይህ የአመልካች ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች የካሣውን መጠን በተመለከተ ያቀረበው አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የቀረበና ሕጋዊ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡



www.chilot.me

በአጠቃላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58008

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካቾቾች**፡- 1. ኤርሰዴ ንግድ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ አብዱርማን መሀመድ - ቀረቡ

2. አቶ ፀደቀ ማርቆስ - ጠበቃ አቶ ዳንኤል ወ/ጊዮርጊስ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የፌዴራል ዐ/ሕግ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የአሁን ተጠሪ ለሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረባቸው ሁለት የወንጀል ክሶችን ሲሆን 1ኛ ክስ በሥር 1ኛ ተከሳሽ /በአሁን 1ኛ አመልካች/ ላይ የቀረበ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ቃልም ተከሳሹ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና የቡና ጥራት ቁጥጥር እና ግብይት አዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 14/3/ እና 15/3/ በመተላለፍ የቡና ላኪነት ፈቃድ አውጥቶ በቡና ግብይት ሥራ ላይ ተሠማርቶ ሲንቀሳቀስ በአንድ የምርት ዘመን ከጨረታ ማዕከላትና ከኢት/የምርት ገበያ የገዛውን ቡና የሚቀጥለው የምርት ዘመን ከመድረሱ በፊት በሚመለከተው ገበያ አቅርቦ መሸጥ ሲገባው መጋቢት 23 እና 30/2001 የቡና ክምችቶ ቆጠራ በተደረገበት ወቅት በድርጅቱ መጋዘኖች ከተገኘው 203,577 ኪሎ ግራም ውስጥ ለኤክፖርት የተዘጋጀ 101,580 ኪ.ግ የከረመ ቡና ለገበያ ሳያቀርብና ለሚመለከተው አካል ሳያሳውቅ ቡና አከማችቱ በመገኘቱ ተከሷል የሚል ሲሆን፣ 2ኛ ክስ በሥር 2ኛ ተከሳሽ /በአሁኑ 2ኛ አመልካች/ ላይ የቀረበ ነው፡፡ 2ኛ የሥር ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 14/3/ እና 15/3/ ሥር በ1ኛ ክስ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በመፈፀሙ ተከሷል የሚል ነው፡፡

የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከቀረቡት ማስረጃዎች አንፃር በመመርመር በሰጠው ፍርድ 1ኛ ተከሳሽን ክስ በቀረበበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና በአዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 15/3/ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት በብር 40,000 እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 15/3/ ሥር ጥፋተኛ ሆኖ በ1 ዓመት ቀላል እሥራት እና በብር 30,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡



www.chilot.me

በዚሁ በፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ የሥር ተከሳሾች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሥር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች ካከራከረ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤትን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካቾች በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

የተጠሪ ክስ አቀራረብ ከአዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 15/3/ አባባል ጋር ተጣጥሞ ባለመቅረቡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130/1/ መሠረትም የአመልካቾችን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ያቀረብነውን ተቃውሞ የሥር ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ያለአግባብ ነው፤

- የወንጀሉ አፈፃፀም ከጥርጣሬ በፀዳ መልኩ ሳይረጋገጥ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ መሠጠቱ ተገቢነት የለውም፤
- ከረመ የተባለው ቡና የምርት ዘመኑ ሳያልፍ ጥር 10 ቀን 2001 ዓ/ም ተሸጦ የውል መፈፀሚያው ቀን የክፍያ ማረጋገጫ የቀረበበት ቀን ተደርጐ መወሰዱ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ለሰበር አቤቱታ ተጠሪው በሰጠው መልስ አመልካቾች ክሱ ተጠቅሶ የቀረበብንን የአዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 15/3/ ዝርዝር ሁኔታን አያሟላም በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130/1/ እና 119 መቃወሚያ በማቅረብ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ጠይቀን ታልፎብናል ያሉትን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤት ምላሽ እንድንሰጥበት በጊዜው ጠይቆን አመልካቾች ቡናን ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ ፈቃድ አውጥተው የሚንቀሣቀሱ እንደመሆናቸው መጠን ቡናን ለማገበያየት ፈቃድ ካለው አካል የገዙትን ያልተዘጋጀ ቡና ለኤክስፖርት በሚመጥን መልኩ አዘጋጅተው ወደ ውጪ ሀገር ከሚልኩ በስተቀር ቡናውን ለሌላ አላማ ሊያውሉት እንደማይችሉና የተከማቸውም ቡና ለግብይት የሚውል መሆኑን አስረድተናል፡፡ አመልካቾች የሽያጩ ጊዜ ከማለፉ በፊት ሽያጩ ተከናውኗል ያሉትም ቢሆን ገዥ ነው የተባለው ኩባንያ የግዥ ማረጋገጫ የላከው የካቲት 26 ቀን 2001 መሆኑን አመልካቾች ያልካዱት ሲሆን ይህም የሚያሳየው ሽያጩ የተጠናቀቀው የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ/ም መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ቁጥር 602/2000ን ተከትሎ የወጣው መመሪያ ላይ ላልታጠበ ቡና የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የተከናወነ ሽያጭ ነው፡፡ በማለት የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግና የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

አመልካቾች በሰጡት የመልስ መልስ ክርክራቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡ የግራቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን የቀረበ ሲሆን እኛም በሥር ፍ/ቤቶች የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪ በመጋቢት 23 ቀን 2001 እና መጋቢት 30/2001 ዓ/ም በአመልካቾች መጋዘን ባደረገው ቆጠራ 42,646 ኪሎ ግራም የከረመ ያልታጠበ ቡና ተከማችቶ የተገኘ ሲሆን ተጠሪዎች ግን ተከማችቶ ተገኝቷል የተባለው ቡና በጀርመን ሀገር የሚገኘው ሀምቡርግ የተባለው ኩባንያ ጥር 10 ቀን 2001 ዓ/ም በቃል በተደረገ ስምምነት መግዛቱንና የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ/ም የስምምነት ደብዳቤ መላኩና ቡናውም ሳይጫን የዘገየው ገዥው ተግባሩን ባለመወጣቱ ምክንያት ነው በሚል

ተከራክሯዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ቡናው በመጋዘናቸው ተከማችቶ የቆየ ስላለመሆኑ ክደው አልተከራከሩም፡፡

ይህ የከረመው ቡና ያልታጠበ እስከሆነ ድረስ ኢዲስ አመት ከገባ ከየካቲት 01 ቀን እስከ ሚቀጥለው ጥር 30 ድረስ ወደ ገበያ ወጥቶ መሸጥ የነበረበት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት የፍሬ ነገርን ክርክር በሚያጣራበት ጊዜ የተጠሪ ምስክሮች ቀርበው ሙያዊ ምስክርነት የሰጡ ሲሆን ቡናው በተለያዩ ችግሮች ለገበያ ካልቀረበ ደግሞ ለሚመለከተው አካል የማስታወቅ ግዴታ አመልካቾች ያለባቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 602/2000 እና ይኸንኑ አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 159/2001 እንዲሁም የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ያወጣው መመሪያ ይደነግጋሉ፡፡

በመሆኑም ቡናው ስለመክረሙ በሕጉ በተጣለባቸው ግዴታ መሠረት አግባብ ላለው የመንግስት አካል አመልካቾች እስካላሳወቁ ድረስ የተጠቀሰባቸውን የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ጥሰው ተገኝተዋል በማለት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው በአግባቡ ስለሆነ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 160177 በቀን 07/8/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 91949 በቀን 21/10/2002 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለባቸው በመሆኑ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ /ለ-2/ ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ቅ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60025

ግንቦት 2 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ሐጎስ መልድ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነገረፈጅ ተስፋዬ ከርጋ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች**፡-1. አቶ ወልዱ በየነ ቀረቡ፡፡

2. አቶ ታምሩ አያለው - ቀረቡ፡፡

3. አቶ አየለ ዋቀዮ
4. አቶ ተስፋዬ በዳዳ
} በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ተወካይነት ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የደሞዝ ጨማሪን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በበታች ፍ/ቤት ከሣሾችና አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱ የቀረበው በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግሥት የምሥረቅ ኦሮሚያ አሰሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን ቀርቦ የነበረው ክስ በጡረታ እድሜያችን የጡረታ አበል ያገኙ የነበረና ተከሣሽ በኮንትራት ሲቀጥረን በጡረታ በምናገኘው ክፍያ ላይ 291 ብር ጨምሮ ይከፍለን የነበረና የጡረታ ደብተራችንም የተመለሰ መሆኑ ይሁን እንጂ የጡረታ እና ዋስትና ባለሥልጣን ከሐምሌ 1999 ዓ.ም ጀምሮ ጭማሪ ቢያደርግም የአሁን ተከሣሽ በደሞዛችን ላይ እንዲጨምርልን ስንጠይቅ መልስ ሣይሠጠን ቆይቶ ከጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ ግንቦት 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ብቻ ከፍሎናል፡፡ ስለዚህ ከሐምሌ 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ18 ወር ውዝፍ እንዲከፍል የሚል ነበር፡፡



www.chilot.me

ተከሣሽ በበኩሉ በሠጠው ከሣሾች በጡረታ ላይ የነበሩ ቢሆንም በግልፅ ውል በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 4 መሠረት ተቀጥረው እንደማንኛውም ሠራተኛ የሚመለከታቸውን ደሞዝና ጥቅማጥቅም እያገኙ ነው፣ ማህበርዊ ዋስትና በኑሮ ውድነት ምክንያት ደሞዝ ሲጨምር እኛም መጨመር እንዳለብን የተደረገ ስምምነት የለም፡፡ እንዲሁም ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆናል በማለት ተከራክሯል፡፡

ቦርዱ ከላይ እንደተመለከተው ከክርክር በኋላ የቀረበው ክስ የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁን ተጠሪዎች ቅር በመሠኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብለው ፍ/ቤቱ ከክርክር በኋላ የአሁን አመልካች ከሐምሌ 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ መንግሥት በጨመረው መሠረት ለአሁን ተጠሪዎች ሊከፍላቸው ይገባል በማለት የቦርዱን ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ ከዚሁ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሲሆን በ03/13/2003 2 ገጽ በተፃፈ አቤቱታ መንግሥት የሰጠውን ጭማሪ አስቀምጦ በውላችን ውስጥ የካተተ ነገር ባለመኖሩ ልንከፍል አየገባም፡፡ በተጨማሪም ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት አመልክቷል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በ29/03/2003 ዓ.ም 2 ገጽ ላይ ጽፈው ባቀረቡት መልስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑ እንድፀና የሚል ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች የመልስ መልስ እንድያቀርብ በተቀጠረበት ባለመቅረቡ መዝገቡ ለምርመራ አድሯል፡፡

በግራ ቀኙ የተደረገው የክርክር ሂደቶች ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረበውን ቅሬታ ከተያዘው ጭብጥና ከሚመለከታቸው ሕጎች ጋር መርምሮአል፡፡ እንደመረመርነውም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል የክፍያውን አግባብነት በግራ ቀኙ መካከል ከተመሠረተው የሥራ ውል አኳያ ለመመርመር ነው፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን ከዚህ አኳያ መርምሮታል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የአሁን ተጠሪዎች በጡረታ ላይ የነበሩ ሰዎች ሆነው የቅጥር ውል ከአሁን አመልካች ጋር የፈፀሙ ስለመናቸው አላከራከረም፡፡ ይሄ የሥራ ውል ግንኙነት በመፈጠሩ ምክንያት የጡረታ ደብተራቸውን ለሚመለከተው የመንግሥት አካል የመለሱ መሆናቸውን ተጠሪዎች ራሣቸው አመልክተዋል፡፡ በግራ ቀኙ የሥራ ውል ውስጥ አመልካች ለአሁን ክስ ምክንያት የሆነውን ክፍያ ለመክፈል የገባው ግዴታ ያለመኖሩን አመልካች የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎችም በውላቸው ውስጥ የተቀመጠ ግዴታ ስለመኖሩ ያነሱት ነገር ካለመኖሩም በላይ እንደዚህ ዓይነት ግዴታ በመካከላቸው ያለመኖሩን የበታች ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡



www.chilot.me

በሌላ በኩል አንድ ጡረታ የወጣ ሰው ተመልሶ ብቀጠር እንደማንኛውም ተቀጣሪ ሠራተኛ ማግኘት ያለበትን ክፍያ ከመጠየቅ ባለፈ ለጡረተኞች የክፍያ ጭማሪ በማደረጉ ብቻ አመልካች የተደረገውን ጭማሪ እንድከፍል የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች መንግሥት ለጡረተኞች ያደረገውን የደመወዝ ጭማሪ ለተጠሪዎች እንዲከፍል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/93661 በ29/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምሥራቅ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በቁጥር 664/01/2002 በ26/6/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች ጡረታኝነታቸውን በመተው የሥራ ቅጥር ውል ከአመልካች ጋር ከፈፀሙ በኂላ መንግሥት ለጡረተኞች በኑሮ ውድነት ምክንያት ደሞዝ ጨምሯል በሚል አመልካች ጭማሪውን እንዲከፍል ለመጠየቅ የሚያስችል ከውል ወይም ከህግ የሚመነጭ መብት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ላይ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልስናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ



www.chilot.me

*የሰ/መ/ቁ. 60353*

*ግንቦት 04 ቀን 2003 ዓ.ም*

**ዳኞች**:- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** :- አቶ ባልቻ ወ/ፃድቅ - ቀረቡ

**ተጠሪ** :- አቶ ግርማ ቀለታ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ቃረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ያቀረበ ነው አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት የጥበቅና ግልጋሎት አሰጣጥን በሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የነበረኝን የፍታብሔር ክርክር ለመከታተልና ጉዳዩን እስከሰበር ችሎት ድረስ እኔን በመወከል ሊከራከሩልኝ ከተጠሪ ጋር ውል ተዋውለናል፡፡ ከሳሽ በውል ከተስማማነው ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ውስጥ ብር 1,000 /አንድ ሺ ብር/ ለተከሳሽ ከፍያለሁ፡፡ ተከሳሽ ተገቢውን የጥብቅና አገልግሎት ያልሰጡኝ በመሆኑ የከፈልኩትን ገንዘብ ከነኪሣራው እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ የማህበራዊ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የተዋዋለው በአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለመከራከር እንጂ በይግባኝና በሰበር ለመከራከር አይደለም በማለት የማህበራዊ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለከተማው ሰበር ችሎት አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ጋር ያደረግሁት የጥብቅና አገልግሎት ውል ተጠሪ እኔ ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር ባለኝ የፍታብሔር ክርክር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር ሊቆሙልኝ መሆኑ በውሉ ተገልፆ እያለ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ ያየው የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት ውሉ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር የተደረገነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ በአዲስ አበባ



www.chilot.me

የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የጥብቅና ግልጋሎት ለመስጠት የተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረቡ የማይጠቅማቸው መሆኑን መክሬአቸዋለሁ፡፡ አመልካች ከሙያ አንፃር የማያዋጣውንና የማላምንበትን ጉዳይ ይግባኝ ካላቀረብክ በማለት ያቀረቡት ክስ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገው የጥብቅና አገልግሎት ውል ስምምነት "እኔ ውል ሰጭ ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስላለኝ የቦታ ክርክር ጉዳይ ውል ተቀባይ ባላቸው የጥብቅና ሙያ ጉዳዬን እስከ መጨረሻ ድረስ ሊከራከርልኝ ለዚህ አገልግሎታቸው ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ልከፍላቸው የተሰማማን ሲሆን" በሚል መንገድ በተራ ቁጥር 1 የአመልካችን ግዴታ የሚገልፅ ሲሆን በተራ ቁጥር 2 "እኔም ውል ተቀባይ በተራ ቁጥር 1 ላይ በተገለፀው መሠረት የውል ሰጭው ጉዳይ እስከመጨረሻ ድረስ ልከራከርላቸው ተስማምተን በቅደሚያ ብር /አንድ ሺ ብር/ ተቀብያለሁ" በሚል መንገድ የተጠሪን ግዴታ የሚገልጽ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በተደረገው ውል ውስጥ " እስከመጨረሻ ድረስ ሊከራከሩልኝ" የሚለውና "እስከ መጨረሻ ድረስ ልከራከርላቸው" የሚለው ቃል ተጠሪ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር የውል ግዴታ እንደገቡ በማድረግ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1732 እና የጥብቅና አገልግሎት በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀፅ 8/2/ የተደነገገውን ያላገናዘበና የአተረጓጉም ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ "እስከ መጨረሻ ድረስ" ልከራከርላቸው በማለት ተጠሪ የገቡት ውል ይዘት አመልካች ከሙያ አንፃር የሚያዋጣ ከሆነ ይግባኝ አቅርቦ የመከራከርና በሰበር አቤቱታ አቅርቦ መከራከረን የሚጨምር በመሆኑ በዚህ በኩል የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው በሰበር ችሎት የሰጡት ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም ተጠሪ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር ነው በጥብቅና አገልግሎት ውሉ የተስማማሁት በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ አልተቀበልነውም፡፡

የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን ውል ሲተረጉሙ ስህተት የሰሩ ሲሆን ተጠሪ ያቀረበው ሁለተኛ መከራከሪያ ስንመለከተው ፍርድ ቤቶቹ የደረሱበትን መደምደሚያ የሚያስለውጥ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ከሙያ አንፃር አመልካች ከህግ አንፃር ማድረግ የሚገባቸውን የማስረዳትና ግልፅ የማድረግና የማማከር ግዴታና አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ክስና ክርክር ያለማቅረብ ግዴታ እንዳለበት በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 28 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በአመልካችና በወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ መካከል በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የነበረው ክርክር የቦታ ይዞታ ክርክር ሲሆን በጉዳዩ አመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበው ነበር፡፡ በክርክሩ ሂደት ክርክር የተነሳበት ቦታ የማናቸው ይዞታ እንደሆነ አጣርቶ እንዲገልፅ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳዳር ተጠይቆ ተከሳሽ ወ/ሮ እታገኘሁ የአመልካችን ቦታ አልፎ እንዳልያዘ እና በተቃራኒው አመልካች የወ/ሮ እታገኘሁን ህጋዊ ይዞታ አልፎ የያዘ መሆኑን በማረጋገጡ የአመልካች ክስ ውድቅ መሆኑን የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00076 ሀምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይ



www.chilot.me

ይግባኝ ባይ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ከሙያ አንፃር እንደማያዋጣ የምክር አገልግሎት ከሰጠ ለአመልካች የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡ አመልካች የተጠሪን ምክር ወደጎን በመተው ይግባኝ አቅርቦ ይግባኙ የተሠረዘበት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ተገቢ የሆነ የሙያ ግልጋሎትና ምክር ለአመልካች የሰጠ በመሆኑ በውጤት ደረጃ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ምክንያቱ ተለውጦ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ቅ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 60508

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች** ፡- 1. ወ/ሮ ሮዛ አባተ

2. አቶ ጌትነት አባተ

3. አቶ በላይ አባተ

4. አቶ ዮሐንስ አባተ ጠበቃ አቶ አበበ አሣመረ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡ - የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነገረፈጅ ሚካኤል ጌታቸዉ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/06/07 የሚገኝና ቁጥሩ 832 የሆነና በርካታ ክፍሎችን የያዘ ህንጻ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶና ተረክቦት እስከ ህዳር 1992 ዓ.ም እያከራየ ሲጠቀምበት የኖረ መሆኑን ከገለጸ በኋላ ህንጻውን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሰጠው ውሣኔ መሠረት ህዳር 24 ቀን 1992 ዓ.ም አስረክቤያቸው ነበር፡፡ ሆኖም ቤቱን ተከሣሾች እንዲከራዩ ውሣኔ የተሰጠው በሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑን በማረጋገጥ ተከሣሾች ለከሣሽ ቤቱን እንዲያስረክቡ ሀምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ወስኗል፡፡ ከሣሽ ከህዳር 1992 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን በማከራየት ያገኘው የነበረው ጥቅም ተቋርጦበታል፡፡ ተከሣሾች የተቋረጠውን ጥቅም /ኪራይ/ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ በማሰብ እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት በአመልካቾችና በሌሎች አራት ሰዎች ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች በተከሣሽነት ቀርበው ከሣሽ አላግባብ በልጽጋችኋል በማለት ያቀረበው ክስ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ከሣሽ ከሀምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም በኋላ ያለውን ኪራይ ከሚጠይቅ በስተቀር በውሣኔ ባለመብት ሆነን ቤቱን ከያዝንበት ከህዳር 1992 ዓ.ም ጀምሮ ኪራይ እንድንከፍል ያቀረበው ጥያቄ የህግ



www.chilot.me

መሠረት የለውም፡፡ተከሣሾች ቤቱን ከተረከብን በኋላ ብር 1,630,000 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሣ ሺ ብር/ በማውጣት ቤቱን ያሣደስን በመሆኑ ሊቻቻልልን ይገባል የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተከሣሾች ከሣሽ ቤቱን ካስረከበበት ህዳር 12 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን እስከተረከበበት ድረስ ባሉት 117 ወራት /አንድ መቶ አስራ ሰባት ወራት/ ቤቱን አከራይቶ ሲያገኝ የነበረውን ገንዘብና የተጨማሪ እሴት ታክስ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተደምሮበት ለከሣሽ የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች መስከረም 14 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ዳኝነት ከጠየቀበት ገንዘብ በላይ እንድንከፍል ወስኖብናል፡፡ አመልካቾች ቤቱን ለማሣደስ ከብር 1,630,000 እንዳወጣን በመግለጽ ያቀረብነውን የመቻቻል ጥያቄ በመቃወም ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይኸም ተጠሪ የአመልካቾችን ክርክር እንዳመነ የሚያስቆጥረው መሆኑ በፍታብሔር ሥነ-ሥነዓት ህጉ ተደንግጐ እያለ በተጠሪ በታመነው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ሣይሰጥበት ማለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የከፊል አገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አገልግሎት አይደለም፡፡

ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፈል የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም ተጠሪ ቤቱን በፊት ከሚያከራይበት በተሻለ ዋጋ ያከራየው ቤቱን እኛ ከተረከብን በኋላ ስላሳደስነው ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በእኛ በኩል የቀረቡ መከራከሪያዎችን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ታህሣስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካቾች ቤቱን በኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ውሣኔ ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ቤቱን ለተጠሪ እንዲመልሱ እስከተወሰነበት ሀምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠሪ ቤቱን በማካራየት ሊያገኝ ይችል የነበረውን ገቢ እንዲከፍሉ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በህጋዊ ውሣኔና ፍርድ ንብረት የተረከበ ሰው ባለመብት የሆነበት ውሣኔ ሲሰረዝ ወይም ሲሻር በኢትዮጵያ ህግ ያለበት ሃላፊነትና ግዴታ ምንድነው? የሚለውን ነጥብ መመለስ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 ይዘት ትርጉምና የተፈጻሚነት ወሰን አስመልክቶ ሰፊ የህግ ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ለመወሰን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349 ድንጋጌዎች አግባብነት ያላቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349/1/ ጉዳዩን በመጀመሪያ አይቶ የወሰነው ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተለወጠ ወይም የተሻረ ሲሆን በተለወጠው ወይም በተሻረው ፍርድ መሠረት የተወሰደ ንብረት የሚመለስበትና የተከራካሪ ወገኖች መብት እንዲስተካከል ፍርድ ቤቱ ተስማሚ

መስሎ የታየውን ትዕዛዝ መስጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349 ንኡስ አንቀጽ 2 በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን ለማስፈጸም ፍርድ ቤቱ የተወሰደ ገንዘብ እንዲመለስ ወለድ እንዲከፈል ፣ ኪሣራ እንዲወሰን ፣ ካሣና ያላግባብ የተወሰደ ጥቅም እንዲከፈል ወይም በፍርዱ መሻሻል ወይም መለወጥ ምክንያት የተካራካሪ ወገኖች መብትን ለማስተካከል ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችል መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 349 በመጀመሪያ ጉዳዩን ባየው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሚለወጥበት ወይም በሚሻርበት ጊዜ ተፈጻሚ እንደሚሆን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 349 የመጀመሪያ ውሣኔ ወይም ፍርድ በይግባኝ ሲሻርና ሲለወጥ ብቻ ሣይሆን የመጀመሪያውን ውሣኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን በህግ የተሰጠው አካል የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 6 እና ሌሎች የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደገና አይቶ ቀደም ብሎ የሰጠውን ውሣኔ በሚያሻሽልበት ወይም በሚሽርበት ጊዜ ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ እንደሆነ የድንጋጌውን ርዕስ አቀራራጽና መሠረታዊ ግብና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ቤቱን ለአመልካቾች እንዲያስረክብ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ወስኖ የነበረው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 6 መሠረት እንደገና በማየት ከዚህ በፊት የሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሰርዞታል፡፡

የኤጀንሲውን ውሣኔ የማስፈጸም ስልጣን የፍ/ቤት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 193/92 ተደንግጓል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ የማስረከብ ብቻ ሣይሆን ተጠሪ ቤቱን እያከራየ ያገኝ የነበረውን ጥቅም እንዲተኩ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ወሣኔ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2ን መሰረት ያደረገ በመሆኑ አመልካቾች ቤቱን በህጋዊ ውሣኔ ከተረከብን በኋላ ተጠሪ ያቀረቡትን የቤት ኪራይ እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ነው በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካቾች ቤቱን እስከሚያስረክቡበት ጊዜ ድረስ ያለው ሂሣብ ታስቦ እንዲከፈለው በግልጽ የዳኝነት ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ከጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ በላይ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

2. አመልካቾች ቤቱን ከተረከብን በኋላ ቤቱን ለማደስ ያወጣነው ገንዘብ ሊቻቻልልን ይገባል በማለት ለስር ፍርድ በተጠሪ ለቀረበባቸዉ ክስ መልስ ሲሰጡ እንደተከራከሩ ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን የመቻቻል ጥያቄ በጭብጥነት በመያዝ ውሣኔ እንዳልሰጠበት ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የመቻቻል ጥያቄ ተጠሪን የከሣሽ ተከሣሽ አመልካቾችን የተከሣሽ ከሣሽ የማድረግ ውጤት ያለው እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 236 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ በዚህ መንገድ የሚቀርቡ ክርክሮች በዳኝነት ታይተው ውሣኔ የሚሰጥባቸው በመጀመሪያ የዳኝነት ተከፍሎባቸው ሲቀርቡ እንደሆነ ከፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 215 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካቾች ቤቱን ከተረከቡት በኋላ ብር 1,630,000 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሣ ሺ ብር/ በማውጣት እንዳሣደሱ በመግለጽ



www.chilot.me

የመቻቻል ጥያቄ ያቀረቡት ከላይ የጠቀስነው የሥነ-ሥርዓት ህግ በሚደነግገው መሠረት የዳኝነት ገንዘብ ከፍለውና ሥርዓቱን አሟልተው ስለ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካቾች የዳኝነት ገንዘብ ሣይከፍሉና ሥርዓቱን ሣያሟሉ ያቀረቡትን የመቻቻል ጥያቄ በጭብጥነት ሣይዙና ውሣኔ ሣይሰጡበት ማለፋቸው የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 67280

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች** ፡- የኢ.ፌ.ዲ. ፍትሕ ሚኒስቴር - ዐ/ህግ አልጋነህ ተሾመ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- 1. አቶ ተስፋዬ በርሄ - ቀረቡ

2. አቶ በለጠ ታፈሰ - ቀረቡ

3. ወ/ሪት ሕይወት ሲሳይ - ቀረቡ

4. አቶ ተሾመ አንጀሎ - የቀረበ የለም

5. አቶ መኳንንት ደግነት - ቀረቡ

በሰ/መ/ቁጥር 67275፣ 67276፣ 67277 እና 67281 የቀረቡት ጉዳዮች በዚህ መዝገብ በተያዘው ጭብጥ ተጠቃለው እንዲታዩ የተደረገ በመሆኑ መዛግብቱን አንድ ላይ አጣምረን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ለሚሠሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 11/2/ ሥር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ለጥብቅና ሙያ ፈቃድ የሚሰጥበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ይህ አቤቱታ የቀረበው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ለተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ያለፈተና የጥብቅና ፈቃድ እንደማይሰጣቸው ባሳወቀው ውሣኔ ቅር በመሰኘት በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 29(1) መሠረት ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በተለያዩ መዛግብት አከራክሮ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሠጠውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪዎች ያለፈተና የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሟልና ሊታረም ይገባዋል በማለት ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና ዲግሪ ከመያዛቸው



www.chilot.me

በፊት የሥራ ልምድ ያላቸው ቢሆንም ከዲግሪ በኋላ የአምስት ዓመት የሥራ ልምድ የሌላቸው በመሆኑ በፌደራል ማናቸውም ፍርድ ቤት ለመከራከር የሚያስችል የጥብቅና ፈቃድ የመግቢያ ፈተና ለመቀበል አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀፅ 11(2) የግድ የሚላቸው ሆኖ እያለ ከዲግሪ በፊት ያለው የሥራ ልምድ ሊቆጠር ይገባል ተብሎ ትርጉም መስጠቱ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሠበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሠበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሠበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 21 ቀን 1996 ዓ.ም ከሮያል ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ፣ ሚያዝያ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ከሮያል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ ባችለር ዲግሪ የተመረቁ ሁነው በሥራ ልምድ ረገድ ደግሞ ከግንቦት 01 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 1995 ዓ.ም፣ ከታህሳስ 01 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ነገረ ፈጅ፣ ከሐምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 03 ቀን 2002 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ዐቃቤ ሕግ ሁነው ያገለገሉ መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪ (አቶ በለጠ ታፈሰ) በበኩላቸው ሐምሌ 07 ቀን 1982 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሕግ ዲፕሎማ፣ የካቲት 04 ቀን 2000 ዓ.ም ደግሞ ከሮያል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ ባችለር ዲግሪ የተመረቁ ሁነው በሥራ ልምድ ረገድም ከሰኔ 14 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 21 ቀን 1987 ዓ.ም በኢትዮጵያ የችርቻሮ ንግድ ድርጅት ኮርፖሬሽን ውስጥ በነገረ ፈጅነት፣ ከጥር 15 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 14 ቀን 1988 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ የቤት እና የቢሮ ዕቃዎች ድርጅት ውስጥ በነገረ ፈጅነት፣ ከታህሳስ 10 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 6 ቀን 1989 ዓ.ም ድረስ በእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን ውስጥ በነገረ ፈጅነት፣ ከሐምሌ 10 ቀን 1989 ዓ.ም እስከ መስከረም 27 ቀን 1984 ዓ.ም ድረስ በነገረ ፈጅነት፣ ከመስከረም 28 ቀን 1984 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1996 ዓ.ም የሕግ አማካሪ ቢሮ ተጠባባቂ ሓላፊ፣ ከነሐሴ 06 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሕግ አገልግሎት ተጠባባቂ ኃላፊ፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 08 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ የሕግ አገልግሎት ኃላፊ በመሆን በውሃ ሥራዎችና ኮንስትራክሽን ድርጅት ውስጥ የሠሩ መሆኑን፣ 3ኛ ተጠሪ (ሕይወት ሲሳይ) ደግሞ ሐምሌ 11 ቀን 1994 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሕግ ዲፕሎማ፣ እ.ኤ. አቆጣጠር ጁላይ 22 ቀን 2010 ደግሞ ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ በሕግ ባችለር ዲግሪ የተመረቁ ሲሆን በሥራ ልምድ ደግሞ ከነሐሴ 16 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ዐቃቤ ህግ ሁነው ያገለገሉ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን፣ 4ኛ ተጠሪ (አቶ ተሾመ አንጀሎ) ደግሞ በትምህርት ዝግጅት እ.ኤ.አ. ኖቬንበር 11 ቀን 2004 ዓ.ም ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሕግ ዲፕሎማ፣ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 01 ቀን 2009 ደግሞ ከአልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ ባችለር ዲግሪ ያላቸው ሁነው በሥራ ልምድ ረገድም ከየካቲት 01 ቀን 1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 01 ቀን 1999 ዓ.ም በአማራ ክልል ውስጥ ዐቃቤ ሕግነት፣ ከሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 03 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በኢ.ፌ.ድ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር አቃቤ ሕግ ሁነው የሠሩ መሆኑ መረጋገጡን፣ 5ኛ ተጠሪ (አቶ መኳንንት ደግነት) በበኩላቸው ነሐሴ 16 ቀን 1993 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ፣ ጳጉሜ 01 ቀን 2001 ዓ.ም ደግሞ ከሮያል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ ባችለር ዲግሪ የተመረቁ መሆኑንና



www.chilot.me

በሥራ ልምድ ረገድም ከታህሳስ 01 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ደግሞ የዐቃቤ ሕግ ረዳት፣ ከጥር 01 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ በዐቃቤ ሕግ ደረጃ አምስት፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በዐቃቤ ሕግ ደረጃ አራት፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ጥር 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በዐቃቤ ሕግ ደረጃ ሦስት የሠሩ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪዎች ያለፈተና የጥብቅና ፈቃድ ሊሰጠን ይገባል በማለት የሚከራከሩት የሥራ ልምዳቸው መያዝ ያለበት ከዲግሪ በሁዋላ ሳይሆን በፊት ያለውም ጭምር ነው በሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ የሚከራከረው የሥራ ልምድ ሊያዝ የሚገባው ከዲግሪ ምረቃ በሁዋላ ያለውን ጊዜ ነው በሚል ተገንዝበናል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የአመልካች ጥያቄ ያለፈተና ለማናቸውም የፌደራል ፍርድ ቤቶች የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 11 (2) በተመለከተው ሁኔታ ሆኖ ይህ ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 8 እና 9 ለተመለከቱት ድንጋጌዎች ልዩ ድንጋጌ ነው በሚል ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 199/92 የፌደራል የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 8 (1) በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚቻልባቸው ሁኔታዎች በግልፅ የተዘረዘሩ ሲሆኑ እነዚህም በሕግ ዲፕሎማ ያለው፣ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ሕጐችን ማወቅ እንዲሁም አግባብነት ባለው ሙያ ቢያንስ 5 ዓመታት ልምድ ያለው ወይም በሕግ ዲግሪ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጐችን የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ የሁለት ዓመት ልምድ ያለው፣ ለፍትህ ሥራ አካሄድ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ ለደረጃው የሚሰጥን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ያለፈ፣ ምግባረ ብልሹነትን በሚያመላክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፣ የሙያ ኃላፊነት መድህን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚሉ ሲሆኑ ለፈቃዱ መሰጠት ፈተና መቀመጥንና ማለፍን የግድ የሚል መሆኑ የአዋጁን አንቀፅ 8 ከአዋጁ አንቀፅ 11(1) ጋር አጣምረን በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የፌደራል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት ደግሞ  በአዋጁ አንቀፅ 9 ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟሏት ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የፌደራል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ የሚሠጠው በሕግ ዕውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በሕግ ዲግሪ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጐችን የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ አምስት ዓመት ልምድ ያለው፣ ለፍትህ ሥራ አካሄድ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ ለደረጃው የሚሠጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ያለፈ፣ ምግባረ ብልሹነቱን በሚያመላክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣና፣ የሙያ ኃላፊነት መድህን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ላቀረበ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 8 እና 9 ድንጋጌዎች የጥብቅና ፈቃድ ደረጃውን የሚለዩ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሁኖ ፈቃዱ የሚሠጠው ለደረጃው የሚሠጠውን ፈተና ላለፈ ኢትዮጵያዊ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በሌላ በኩል አዋጁ ያለፈተና የጥብቅና ፈቃድ የሚሠጥባቸውን ሁኔታዎች ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህም በአዋጁ አንቀፅ 10 ሥር የተመለከተው የፌደራል ልዩ የጥብቅና ፈቃድ አንዱ ሲሆን ሌላው በአዋጁ አንቀፅ 11 (2) ሥር የተመለከቱ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ኢትዮጵያዊያን የሚመለከተው ነው፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 11 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ በአዋጁ አንቀፅ 8 እና 9 ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶችን የሚያሟላ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ የጥብቅና ፈቃድ የሚሠጠው የፈተና መመዝገቢያ ክፍያ ፈፅሞ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ሲወስድና ፈተናውን ሲያልፍ መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ የዚህ ንዑስ አንቀፅ ድንጋጌ ከተጠቀሰው አንቀፅ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ጋር ተጣምሮ ሲነበብም ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ጠያቂዎች በኢትዮጵያ ከፍተኛ



www.chilot.me

የትምህርት ተቋማት ውስጥ ቢያንስ በረዳት ፕሮፌሰርነት ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከዚያ በላይ በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት ወይም በታወቁ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በሕግ አማካሪነትና በነገረ ፈጅነት ቢያንስ አምስት ዓመት ያገለገለ ማንኛውም ሰው ሥራውን በለቀቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ ካቀረበ የጥብቅና መግቢያ ፈተና እንዲወስድ አይገደድም በሚል በኃይለ ቃል የተቀመጠ ሲሆን ይህ ድንጋጌ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ክርክር ያስነሣው የሥራ ልምዱ ሊቆጠር የሚገባበትን ጊዜ አስመልክቶ ነው፡፡ አመልካች የሥራ ልምዱ ሊቆጠር የሚገባው ከዲግሪ ምርቃት በኋላ ነው በሚል የሚከራከር ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው የሚከራከሩት በዲግሪ ከመመረቃቸው በፊት የነበራቸው የሥራ ልምድ ሊያዝ እንደሚገባ ሕጉም ያሣያል፣ የአመልካች የቆየ አሠራርም ያስረዳል ይህ ሠበር ሰሚ ችሎትም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል በሚል ነው፡፡ እኛም የአከራካሪውን ድንጋጌ አቀራረፅ ይዘትና መንፈሱን አይተናል፡፡ በዚህም መሠረት የድንጋጌው የአማርኛው ቅጂ ፡-

" በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሕግ ቢያንስ በረዳት ፕሬፌሰርነት ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ <u>**ኖሮት**</u> በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከዚያ በላይ በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት ወይም በታወቁ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና በልማት ድርጅቶች በሕግ አማካሪነት እና በነገረ ፈጅነት ቢያንስ ለአምስት ዓመት ያገለገለ ማንኛውም ሰው ሥራውን በለቀቀ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ ካቀረበ የጥብቅና መግቢያ ፈተና እንዲወስድ አይገደድም፡፡ " በሚል የተቀመጠ ሲሆን የድንጋጌው የእግንሊዝኛ ቅጂ ደግሞ፡-

"Any person who has taught law in Ethiopian higher educational institutions at least as an assistant professor or has served, <u>**holding degree in law**</u>, at least for five years as a judge or public prosecutor in federal first instance court or above, or as a legal consultant and attorney in known government organs and public enterprises **may not be** required to take an examination, where he applies for a license within a period of one year from the termination of his employment." በሚል የተቀመጠ ነው፡፡

ከላይ የተመለከቱትን መስፈርቶችን የሚያሟሉ ፈቃድ ጠያቂዎች ከፈተና ነጻ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት ሲታይም የሥራ ፀባይ በሙያው የዳበረ ልምድ የሚያስጨብጣቸውና ስለ ፍርድ ቤቶችም አሠራር በቂ እውቀት ለማግኘት በበቂ ሁኔታ የሚያስችላቸው መሆኑን በመታመኑ ስለመሆኑ የአዋጁ ሐተታ ዘ ምክንያት ያሣያል፡፡ ከላይ ከተመለከቱት የድንጋጌው አማርኛ እና እንግሊዝኛ ቅጂዎች ውስጥ እንደ ቅደም ተከተላቸው ….**ኖሮት** …. እና **Holding a degree in law** ….. የሚሉት ቃላትና ሐረግ ሲታዩ የሥራ ልምድ ዲግሪ ኖሮት እና ከዚህ ጊዜ በኋላ መቆጠር እንዳለበት ለትርጉም በማይጋብዝና ትርጉሙን በማያሻማ ሁኔታ ከትምህርት ዝግጅቱ በሁዋላ ያለው ጊዜ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ድንጋጌው በአቀራረፁ፣ በይዘቱና በመንፈሱ ሲታይ ግልፅ በመሆኑ ድንጋጌው ግልፅ እስከሆነ ድረስ ትርጉም የማያስፈልገው መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጐም ደንቦች የሚያሣዩን ጉዳይ ሲሆን ግልፅነት የለውም፣ ትርጉም ያስፈልገዋል ቢባል እንኳን ድንጋጌው በአዋጁ በአንቀፅ 8 እና 9 ጋር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች እና የጥብቅና ሙያ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንፃር የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶችን ከፍ በማድረግ በዚህ አገልግሎት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሙያዎች የብቃት ደረጃ ከሚሠጡት አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ለማድረግ ከሚለው የአዋጁ ዓላማ ጋር ተዛምዶ መተርጎም ያለበት ነው፡፡ የተጠቀሰው አዋጁ በአንቀፅ 8 እና 9



www.chilot.me

ሥር የሚሠጠው የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈቃድ የትምህርት ዝግጅቱንና የሥራ ልምዱ መስፈርቶች ራሣቸውን ችለው የተቀመጡ መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑ መቆጠር ያለበት በዲፕሎማ ወይም በዲግሪ ከተመረቁበት ጊዜ ጀምሮ አለመሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች አቀራረፅና ይዘት መሠረት የትምህርት ዝግጅቱና የሥራ ልምዱ ራሣቸውን ችለው የቆሙ መስፈርቶች ሁነው እኩል ዋጋ ያላቸው ሲሆን እነዚህን መስፈርቶችን የሚያሟላ ፈቃድ ጠያቂ ለደረጃው የሚዘጋጀውን ፈተና ማለፉ ከተረጋገጠ የጥብቅና ሙያ ፈቃድ እንደሚሰጠው ከአንቀፅ 11 (1) ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀፅ 8 እና 9 የተቀመጡት ድንጋጌዎች የሥራ ልምድ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ ኖሮት በሚል ያስቀመጡ ሣይሆን የሥራ ልምዱ ከትምህርት ዝግጅት ጋር በፊትም ቢሆን እንኳን ከትምህርት ዝግጅቱ እኩል ዋጋ የሚሠጠው መሆኑን ለያይተው የሚገልፁ በመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 11 (2) ሥር ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር አንድ ናቸው ሊባል የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ሕግ አውጪው የትምህርት ዝግጅቱንና የሥራ ልምዱን ለያይቶ እኩል ዋጋ በአንዱ አንቀፅ ከሰጠ በሁዋላ በተከታዩ ድንጋጌ ተመሣሣይ መንፈስ ያለው አንቀፅ ያስቀምጣል ማለት ትርጉም አልባ ከመሆኑም በላይ የሕጎችን ዐውደ ንባብ (contextual interpretation) **ትርጓሜ** ያልተከተለ፤ አዋጁ ውጤት እንዲኖረውና በአዎንታዊ መንገድ ታይቶ ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል የአተረጓጎም መንገድ ሆኖ አይገኝም፡፡ አንድ ድንጋጌ ግልፅነት የሚጎድለው መሆኑ ከታመነበት የድንጋጌው ትክክለኛ ትርጉሙ የሕጉን አጠቃላይ ድንጋጌዎችን በማየት ሊተረጎም እንደሚገባ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀፅ 11 (2) ሥር የተመለከተው ድንጋጌ በአዋጁ አንቀፅ 8 እና 9 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እና ከሌሎች የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ለተያዘው ጉዳይ ልዩ ድንጋጌ ሲሆን ጉዳዩ መገዛት ያለበትም በዚሁ ልዩ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ የሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአዋጁን አንቀፅ 11(2) ድንጋጌ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በግልፅልነቱ በመቀበል ወይም ልዩ ድንጋጌ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ውጤት ባለው መልኩ በመተርጎም ተግባራዊ ማድረግ ሲገባው በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ የሚተገበረውን የሥራ ልምድ አያያዝ አሠራር በመመርኮዝ የሥራ ልምዱ ከዲግሪ ምርቃት በሁዋላ ሊሆን አይገባም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሰው ከአዋጁ አላማ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ በዋቢነት የጠቀሰውና በሠ/መ/ቁጥር 37375 ይህ ሠበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉምም በመዝገቡ የሰበር አመልካች የነበሩት ግለሰብ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ለመውሰድ እንዲፈቀድላቸው ቢያመለክቱም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአመልካች ጥያቄና ማስረጃ በማገናዘብ በሰጠው ውሣኔ አመልካች ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በሕግ ዲፕሎማ ከተመረቁ በኂላ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሠጣጥ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀፅ 8/1/ መሠረት በሙያው 5 ዓመት ያላገለገሉ ናቸው በማለት የአመልካች ጥያቄን ሳይቀበለው በመቅረቱ በድንጋጌው የተመለከተው የሥራ ልምድና የትምህርት ዝግጅት እኩል ዋጋ ያላቸው የተለያዩ መስፈርቶች ከሚሆኑ በስተቀር ሁለቱም አንድ ጊዜ እንዲሟሉ ሕጉ የግድ አይልም፣ የሠበር አመልካቹ ለፈተና እንዲቀመጡ ሊፈቀድላቸው ይገባል ተብሎ የተሰጠ ትርጉም ነው እንጂ በአዋጁ አንቀፅ 11(2) ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶች ተመልክቶ ትርጉም የሰጠበት መዝገብ አይደለም፡፡ በመሆኑም አንድ የሠበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉም በማናቸውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድደው ተመሣሣይ ለሆኑ ጉዳዮች ነው፡፡ የተያዘው ጉዳይ ይህ ሠበር ሰሚ ችሎት



www.chilot.me

በሰ/መ/ቁጥር 37375 ን ከሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር ተመሣሣይነት የሌለው በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የሰ/መ/ቁጥር 37375 ለውሣኔው በዋቢነት መጠቀሱ አግባብነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪዎች ለጠየቁት የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ በሕጉ የተመለከቱትን መስፈርቶች አላሟሉም በማለት አመልካች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች መስፈርቱን እንዳሟሉ በማድረግ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ውሣኔ በመሻሩ በሕጉ አተረጓጎምና አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 98707፣ 99105፣ 99561፣ 99563 ታህሳስ 14 ቀን 2003 ዓ.ም፣ በመ/ቁጥር 99156 ታህሳስ 19 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥተው በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀኑት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ያሳወቀው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ግልባጩ ከሠ/መ/ቁ 67275፣ 67276፣ 67277 እና 67281 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/ም.ፋ



www.chilot.me

*የሰ/መ/ቁ. 55238*

*መጋቢት 9 ቀን 2003ዓ.ም*

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድማ

**አመልካቾች**፡- 1. የየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር - ነገረ ፈጅ ፍፁም ካሣዬ ቀረቡ

2. ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ አልቀረቡም

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ሕድአት ፍስሀፅዬን ከጠበቃ አቶ ሚሊዬን አበራ ጋር ቀረቡ

አንደኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 55238 ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የተደረገውን ክርክርና ሁለተኛ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 55153 ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ የተደረገውን ክርክር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 11/5/ መሠረት በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካቾች በተናጠል ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 29861 የአሁን ተጠሪ አመልካች የአሁን አመልካቾች ተጠሪዎች ሆነው ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ ጉዳዩን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደገና አይቶ እንዲወሰን ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራቀኛችንን ክርክር በመስማት ህዳር 24 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ መጋቢት 28 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ የአሁን ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግንቦት 22 ቀን 1994 ዓ.ም ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ሁለተኛ አመልካች አዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 314 የሚገኘውን ቤቱን ከታህሣሥ 23 ቀን 1991ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ ብር 3,000/ሦስት ሺ ብር/ ኪራይ ለመክፈል ተስማምተው ተከራይተውታል፡፡ በውላችን መሠረት ያልከፈሉኝ ብር 117,000 /አንድ መቶ አሥራ ሰባት ሺ ብር/ የቤት ኪራይ ያለባቸው ስለሆነ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ፡፡

አንደኛው አመልካች ህግና መመሪያ ሣይከተል ቁጥሩ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ቤት ለሁለተኛ አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ሸጧል፡፡ አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ



www.chilot.me

ከነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉና ቤቱንም ለቅቀው እንዲያስረክቡኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ቤቱን ለሁለተኛ አመልከች የሸጠው ቤቱ የኤርትራዊያን ንብረት መሆኑ በወቅቱ በተቋቋመው አጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ ስለቀረበለት መሆኑን ገልጾ የተጠሪ ክስ ተገቢ አይደለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ አመልካችም መንግስት ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሠረት በህጋዊ መንገድ የገዛሁ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የሚፈርስበትም ሆነ ቤቱን የምለቅበት ምክንያት የለም፡፡ የቤት ኪራይ ለተጠሪ ወኪል ከፍያለሁ የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ለሁለተኛ አመልካች የተጠሪን ንብረት የሸጠው ከህግ ውጭ ነው፡፡ ስለዚህ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ ያስረክቡ፡፡ የቤት ኪራይ ከነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን በአንድነትና በነጠላ አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት በመዝገብ ቁጥር 07632 ታህሣሥ 28 ቀን 97 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፣፣ አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 36844 ሀምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት በመዝገብ ቁጥር 26905 የካቲት 2 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ስርዞታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 79183 አለ የሚሉትን የሚስትነትና የልጆቻቸውን የወራሽነት ማስረጃ በማስቀረብና ተገቢውን በመፈፀም እንደዚሁም ተገቢነት አላቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች ሁሉ በማስቀረብ በግራ ቀኙ የመከራከሪያ ነጥቦች ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት በሰበር መዝገብ ቁጥር 29861 ጥር 14 ቀን 2001 ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጥር 14 ቀን 2001ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ጉዳዩን በማንቀሣቀሥ አጣርቶ እንዲወሰንላቸው የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረት መዝገቡን በማንቀሣቀሥ ሊቀርቡ ይገባቸዋል የሚላቸውን ማስረጃዎች በማስቀረብ 24-3-2002 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ ለመክሰስ የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም; አመልካቾች ክስ የቀረበበትን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ወይስ አይገባም; ተጠሪ ክስ ያቀረቡበትን የኪራይ ገንዘብ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም; አመልካቾች ተጠሪ የጠየቁትን የቤት ኪራይ የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው ወይስ የላባቸውም; የሚሉትን ጭብጦች መሥርቷል፡፡

ክርክር የተነሳበት ቤት በብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ስም የተመዘገበ ነው፡፡ ተጠሪ የሟች ብርጋዴር ጄኔራል ገብርአብ ወልዳይ ሚስት መሆናቸው በሥር ፍይል መዝገብ ቁጥር 79/83 ተረጋግጦ በፍርድ ተወስኗል፡፡ የቤቱ ስመ ሀብት በብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ስም የተመዘገበ ቢሆንም ተጠሪ ቤቱን በጋብቻ ያፈሩት የጋራ ሀብታቸው በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሥልጣን ባለው የመንግስት አካል የተሰጣቸው በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 470/94 አንቀፅ 5/4/ መሠረት ክስ ማቅረብ ይችላሉ በማለት ወስኗል፡፡ ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አንደኛ



www.chilot.me

አመልካች ቤቱን ለሁለተኛ አመልካች የሸጥኩት የክልል 14 መስተዳድር ጽ/ቤት መጋቢት 15 ቀን 1992ዓ.ም በቁጥር አመ/አአ 73/6/53 በፃፈው ደብዳቤና ባወጣው መመሪያ መሠረት ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም መመሪያው በወቅቱ በመንግስት ውሣኔ ከአገር እንዲወጡ የተደረጉት ኤርትራዊያን ንብረት በጨረታ የሚሸጥበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ ብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ግንቦት 23 ቀን 1983 ዓ.ም መሆኑና በኢትዮጵያ ውስጥ የተቀበሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ብ/ር ጄኔራሉ የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ወታደራዊ ባለሥልጣን የነበሩና ተጠሪ አሁንም ከኢትዮጵያ መንግስት ጡረታ በሚች ስም እየተቀበሉ መሆናቸው ተገልጿል፡፡ የቤቱ ባለንብረት ኢትዮጵያዊ ሆነው እያለ በተሣሣተ መረጃ አንደኛ አመልካች ቤቱ የኤርትራዊና በመንግስት ውሣኔ ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ሰው ንብረት እንደሆነ በመቁጠር ለሁለተኛው አመልካች የፈፀመው ሽያጭ ፈራሽ ነው፡፡

ስለዚህ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ የማስረከብ ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል፡፡ ሦስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17068 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት ሁለተኛ አመልካች ከመጋቢት 20 ቀን 1992 በፊት የነበረውን የቤት ኪራይ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2024 መሠረት እንደተከፈለ የሚገመት በመሆኑ ሁለተኛ አመልካች ከመጋቢት 20 ቀን 1992 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 26 ቀን 1993 ዓ.ም ያሉትን አሥራ ስምንት ወራት ኪራይ ብቻ በብር 3,000 ተሰርቶ ብር 54,000 ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አራተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከነሐሴ 28 ቀን 1993ዓ.ም ጀምሮ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን የያዙት በሽያጭ ውል በመሆኑ ለተጠሪ ኪራይ የመክፈል ሀላፊነት የለባቸውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን የሚጣራ ፍሬ ነጥብ የለውም በማለት በመዝገብ ቁጥር 89888 መጋቢት 28 ቀን 2002 በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 ሠርዟል፡፡ ሁለተኛ አመልካች በበኩላቸው ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙ የሚጣራ ነጥብ የለውም በማለት በመዝገብ ቁጥር 88806 መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አንደኛው አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 89888 የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ቤቱን ለሁለተኛ አመልካች የሸጥነው መንግስት የኤርትራዊያን ንብረት እንዲሸጥ ባወጣው መመሪያ መሠረት ነው፡፡ ተጠሪ ሽያጩ ሲከናወን ኢትዩጵያዊ የነበሩ መሆኑን አላስረዱም፡፡ ተጠሪ ኢትዩጵያዊ ባለመሆናቸው በባንክ የተቀመጠውን ገንዘብ ከሚጠይቁ በስተቀር የቤት ሽያጩ ውሉ እንዲፈርስ መጠይቅ አይችሉም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በወቅቱ ያልወጣውን አዋጅ ቁጥር 270/94 በመጥቀስ መወሰኑ የህግ ስህተት አለበት በማለት ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የተከራከረ ሲሆን ሁለተኛ አመልካች በበኩላቸው የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 88806 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የሚች ብ/ር ጄኔራል ገብረአብ ሚስት ቢሆኑም ኤርትራዊ ዜግነት ያልያዙ እንደነበሩ ባላሥረዱበት ሁኔታ መንግስት ባወጣው መመሪያ መሠረት የገዛሁትን ቤት እንዳስረክብ መወሰኑ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የቤቱ ስመ ሀብት በገዥዋ በሁለተኛ አመልካች ስም የተዛወረና ውሉ የተፈፀመ በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ ኢትዩጵያዊ ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡

ቤቱን ከገዛሁ በኃላ ከብር 500,000 በላይ ወጭ በማድረግ የግንባታ ሥራ አከናውኛለሁ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሰበር ችሎቱን ትዕዛዝ በመከተል አጣርቶ አልወሰነም፡፡ የውጭ ዜጋ ንብረቱን ለኢትዩጵያዊ እንዲያስተላለፍ ማስገደድ እንደሚችሉ በፍ/ታብሔር ህግ ቁጥር 390 እና በፍ/ታብሔር ህግ ቁጥር 391 የተደነገገ በመሆኑ አንደኛ አመልካች ቤቱን ለእኔ ለመሸጥ ሥልጣን አለው ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በመሻር የተፈፀመውን የህግ ስህተት እንዲያርሙልኝ በማለት ከዚህ መዝገብ ጋር በተጣመረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 55153 ሚያዚያ 8 ቀን 2002ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ አመልካቾች በተናጥል ባቀረቡት መልስ ቤቱ የሚች ብ/ር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ቤት ነው፡፡ ሚች የኢትዮጵያ የጦር መኮንንና ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ መንግስት የጡረታ አበል እየከፈለኝ መሆኑን በቂ ማስረጃ አቅርቤለሁ፡፡ እኔም የሚች ሚስት መሆኔን በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች የኤርትራዊ ንብረት ነው ከሚሉት ውጭ ቤቱ በመንግስት ውሣኔ ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ ንብረት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ስለሆነም አንደኛ አመልካች ለሁለተኛ አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ምክንያትና ሥልጣን ሣይኖረው ሚች ብ/ር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ በመንግስት ውሣኔ ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ ናቸው በሚል ምክንያት ቤቱን መሸጡ የተረጋገጠ ስለሆነ ሽያጩ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ስኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በተናጠል የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ያደረጉት ክርክር ያለፈበት ሂደትና ጉዳዩ የተመለሰለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔና ግራቀኙ በተጣመሩት መዝገቦች በሰበር ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አንደኛ አመልካች በቀድሞው ወረዳ 16 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 314 ለሁለተኛ አመልካች ለመሸጥ ያደረገው ውል ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም; የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ቁጥር 314 አንደኛ አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ለመሸጥ ህጋዊ መሠረት ያደረገው የክልል 14 መስተዳድር ጽ/ቤት መጋቢት 15 ቀን 19992ዓ.ም በቁጥር አመ/አስ 73/6/53 ያፃፈውን ደብዳቤና በመንግስት ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ኤርትራዊያን ንብረት ስለሚሸጥበት ሁኔታ የወጣውን መመሪያ ነው፡፡ መመሪያው አስተዳደሩ በመንግስት ውሣኔ ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ኤርትራዊያን ንብረት እንዲሸጥ ሥልጣን የሚሰጥ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ተጠሪ የሚከራከሩበትን ቤት ለሁለተኛ አመልካች የሸጠው ቤቱ በስማቸው የተመዘገበው አቶ ገብረአብ ወልዳዊ ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ ናቸው በማለት እንደሆነ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች በማስረጃነት ያቀረበው ሰነድ ጭምር ተረጋግጣል፡፡

አንደኛ አመልካች ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ ናቸው በማለት ቃለ ጉባኤ ይዞ ንብረታቸው እንዲሸጥ የወሰነባቸው ብርጋዴል ጄኔራል ገብረአብ ወልዳዊ ኤትርራዊ ዜግነት የሌላቸው ኢትዮጵያዊ የጦር መኮንን እንደነበሩና ግንባት 23 ቀን 1983 ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህም አንደኛ አመልካች በህግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ ከሁለተኛ አመልካች ጋር የቤት ሽያጭ ውል ያደረገ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡



www.chilot.me

በሌላ በኩል ተጠሪ የሚች ብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ሚስት መሆናቸውንና የኢትዮጵያ መንግስት የጡረታ አበል እስካሁን ድረስ የሚከፍላቸው መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በመንግስት ውሣኔ ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ መሆናቸውን አመልካቾች ለበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ በትውልድ ኢትዩጵያዊ የሆኑ የሌላ አገር ዜግነት ያላቸው መሆኑን የሚያስረዳ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የመታወቂያ ካርድ የተሰጣቸው መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ" የሚል መታወቂያ የሚሰጠው አንድ ሰው በአዋጅ ቁጥር 270/1994 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2ን ለሚያሟላ የውጭ አገር ዜጋ መሆኑ በደንብ ቁጥር 101/96 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደንግጓል፡፡ የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራን ዜግነት መርጦ የያዘ ሰው "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ" የሚለውን ትርጉም የማይሸፍን ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 270/94 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጋ" መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የመታወቂያ ካርድ ከኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋገጡ በመሆኑ የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራ ዜግነት መርጠው ይዘው ያልነበረ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነው፡፡ ስለሆነም አንደኛ አመልካች በህግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ ንበረትነቱ የኢትዮጵያዊው ብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑት የተጠሪን ንብረት ለሁለተኛ አመልካች ለመሸጥ ነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ህገ መንግስቱ ለግል ንብረት ባለቤትነት በአንቀጽ 40/1/ የሰጠውን ጥበቃና ዋስትና መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ቤቱን ከመግዛታቸው በፊት ያሉትን አስራስምንት ወራት የቤት ኪራይ ሁለተኛ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጠው ውሣኔም በሁለተኛ አመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አንደኛ አመልካች በዚህ መዝገብ የሽጠውና ክርክር ያቀረበበት ኢትዮጵያዊ ዜግነት የነበራቸውን ብርጋዴል ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይንና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑትን የተጠሪን የጋራ ሀብት መሆኑ ስለተረጋገጠ ይህ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17986 አከራክሮ ውሣኔ ከሰጠበት ጉዳይ ጋር ተመሣሣይነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በሰበር መዝገብ ቁጥር 17986 የተደረገው ክርክርም ሆነ የሰበር ችሎቱ የሰጠው ውሣኔ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ይህንን መዝገብ በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 1993ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ በመሆኑ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠውን ውሣኔ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛ አመልካች ቤቱን ከገዛሁ በኃላ ከብር 500,000/አምስት መቶ ሽ ብር/ በላይ ወጭ በማድረግ የግንባታ ሥራ አከናውኛለሁ በማለት በሰበር አቤቱታቸው ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ሁለተኛ አመልካች ቤቱን ከተረከቡ በኃላ ያደረጉት ግንባታ ስለመኖሩ በሥር ፍርድ ቤት አንስተው ያልተከራከሩ መሆኑን የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 07632 በማስቀረብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ሁለተኛ አመልካች በሥር ያልተከራከሩበትን አዲስ ፍሬ ጉዳይ በሰበር ደረጃ ማንሳታቸው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡



www.chilot.me

በአጠቃላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በመንግስት ውሣኔ ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ኤርትራዊያን ንብረትን ለመሸጥ ያወጣውን መመሪያ ይዘትና የተፈፃሚነት ወሰን ያገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07632 ህዳር 24 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 88806 እና በመዝገብ ቁጥር 89888 መጋቢት 28 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 67146

ሐምሌ 01 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- - ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- ሻምበል ተሾመ ደምሴ - ጠበቃው ያለለት ተሾመ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- የፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ሕግ ገበያው ስማቸው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ መ/ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ የሰጠው የዲስፕሊን ውሣኔ ሲሆን ውሣኔውም ለተጠሪ መ/ቤት የበላይ ሀላፊ ቀርቦ ይፈፀም በመባሉ ምክንያት ለከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ በአሁኑ አመልካች ይግባኝ ጠያቂነት ቀርቦ ከፍተኛው ፍ/ቤትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት ይግባኝ ባዩን በማሠናበቱ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ለዲስፕሊን ኮሚቴ ውሣኔ መነሻ የሆነውን አቤቱታ ለተጠሪ መ/ቤት ያቀረቡት ወ/ሮ ዮላንዳ ካፑሲ ሲሆኑ የአቤቱታውም ፍሬ ቃል ከአቶ ሩፋኤል ዴልጋውዲ ከተባለው ጋር ባልና ሚስት ሆነን ከቆየን በኋላ በመካከላችን በተፈጠረው አለመግባባት በፍ/ቤት ጉዳያችን እየታየ ባለበት ወቅት ባለቤቴ የጋራ ሃብታችንን በሙሉ በእጁ በማድረጉ የንብረት ክፍፍሉ እስከሚደረግ ድረስ ለወደፊት ከንብረቱ ከሚደርሰኝ የሚታሰብ በየወሩ ብር 10,000 እንዲከፍለኝ ተወስኖልኝ ሲከፍለኝ ከቆየ በኋላ ተጠሪው /የአሁኑ አመልካች / የባለቤቴ ጠበቃ በመሆናቸው ለፍ/ቤቱ የካቲት 02 ቀን 1999 ዓ/ም በሰጡት የመልስ መልስ እኔ “ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ግሩፕ” የሚባል የግል ድርጅት ሳይኖረኝ እንዳለኝ በማስመሠል ሐሰተኛ የቢዝነስ ካርድ በማዘጋጀት አቅርበው በፈፀሙት ህገወጥ ድርጊት ከፍተኛ እንግልትና ጉዳት ያደረሱብኝ ስለሆነ በዲስፕሊን ኮሚቴ ይጠየቅልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተጠሪውም /የአሁኑ አመልካች/ በሰጡት መልስ የአቤቱታ አቅራቢዋ ባለቤት የቢዝነስ ካርዱን ስለሰጣቸው ለፍ/ቤቱ እንዳቀረቡ ገልፀዋል፡፡

የሥር የዲስፕሊን ኮሚቴውም የአሁኑ አመልካች የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች ሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 29/2/ እና አንቀጽ 56/4/6/ ላይ የተደነገጉትን የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች ጥሰዋል በማለት በብር 10,000 /አሥር ሺህ / እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም



www.chilot.me

በተጠሪ መ/ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሣኔና በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያሉ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- የተጠሪ የዲስፕሊን ኮሚቴ ለውሣኔው መሠረት ያደረጋቸው ድንጋጌዎች ላይ ያሉት ነጥቦች ስለመኖራቸው አልተረጋገጠም ፣
- የዲስፕሊን ኮሚቴው ማስረጃዬን ሳይሠማና ሳይመረምር ውሣኔ መስጠቱ ያለአግባብ ነው፣
- በደንበኛዬ ትክክለኛ መሆኑ ተገልጾ የተሰጠኝ ሰነድ ሀሰተኛ መሆን አለመሆኑን የማጣራት ግዴታ የሌለብኝ ሆኖ ሣለ ጥፋተኛ መባሌ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ለአመልካች የሰበር አቤቱታ ተጠሪው በሰጠው መልስ ለሥር የዲስፕሊን ኮሚቴ አቤቱታው እንዲታይ የጠየቀት ግለሰብ የንግድ ድርጅት ያላቸው ስለመሆኑ ምንም አይነት ህጋዊ ሠነድ ከአመልካች ደንበኛ ሳይቀርብላቸውና በቢዝነስ ካርዱ የተመለከቱት ዝርዝር ሁኔታዎችን በአግባቡ ሳያረጋግጡ አመልካች ካርዱን ለፍ/ቤቱ በማቅረብ ለግለሰቧ የሚከፈለው ቀለብ እንዲቋረጥ ማድረጋቸው ከቅን ልቦና ውጪ የፈፀሙት መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሣለ አመልካች የሠነዱን ሀሰተኛነት አላውቅም ያሉት ከተጣለባቸው ሙያዊ ግዴታ አንፃር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች በሰበር ቅሬታቸው ማስረጃቸው ያልተሰሙ መሆናቸውን ቢገልጹም የተጠሪ የዲስኘሊን ኮሚቴ 7 የአመልካች ማስረጃዎችን አቅርቦ የሰማ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት የዲስኘሊን ኮሚቴውም ሆነ የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በውሣኔያቸው የፈፀሙት የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም አመልካች በተከሰሱበት የዲስኘሊን ክስ ጥፋተኛ ናቸው ተብለው በገንዘብ የተቀጡት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የተጠሪ መ/ቤት የዲስኘሊን ኮሚቴ ውሣኔ እንደሚያመለክተው አመልካች ጠበቃ ሆነው ሲከራከሩ የነበሩት የወ/ሮ ዩላንዳ ካፑሲ ባለቤት ወክሎአቸው ሲሆን አመልካች የተባለውን የቢዝነስ ካርድ ያገኙት ከደንበኛቸው መሆኑን እና ለፍ/ቤቱ ግለሰቧ የንግድ ድርጅት እንዳላቸው ካርዱን በማቅረብ ጭምር የገለጹት ይኸው ደንበኛቸው በሰጡት መረጃ መሠረት ነው ብሏዋል፡፡ ይበሉ እንጂ ደንበኛው ያቀረባቸውን ማስረጃዎች ባለሙያው /ጠበቃው/ እንዳለ ተቀብሎ ለፍ/ቤት ማቅረብ አለበት? ወይስ የለበትም የሚለውን ነጥብ መመለስ ተገቢነት ያለው ይሆናል፡፡ ለዚህም በመጀመሪያ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 92/1/ን መመልከት የሚገባ ሲሆን የተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ስለማናቸውም ጉዳይ የሚቀርብ አቤቱታ በሌላ ሁኔታ እንዲቀርብ የሚያዝ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በአቤቱታው ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ነገር አቤት ባዩ ወይም ነገሩን የሚያውቅ ሌላ ሰው በአቤቱታው ግርጌ ይህ የቀረበው አቤቱታ እውነት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ይላል፡፡ ከዚህ ከህጉ መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ያቀረበው አቤቱታ እውነት ስለመሆኑ የማረጋገጥ የህግ ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ ቢሆን ደንበኛቸውን በመወከል ግለሰቧ የንግድ ድርጅት ያላቸው ስለመሆኑ አመልካች ካርዱን ጭምር ይዘው ለፍ/ቤት የቀረቡ ሲሆን ይህ አለ የተባለው የንግድ ድርጅት ስለመኖሩ ደግሞ አስቀድሞ በእርግጠኝነት ሊያውቁ ይገባ ነበር፡፡

ይህ ሆኖ ሣለ አመልካች በእርግጠኛነት የሚያውቁትን ጉዳይ ብቻ ክርክሩን ለያዘው ፍርድ ቤት ማቅረብ ሲገባቸው የቢዝነስ ካርዱን ሐሰተኛ መሆንና አለመሆን የማጣራት ግዴታ የለብኝም ያሉት ከተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ህግ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ አይደለም፡፡



www.chilot.me

በሌላ በኩል የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 3 በመርህ ደረጃ ማንኛውም ጠበቃ በተለይም ለደንበኛው፣ ለሌሎች የህግ ሙያተኞችና ተከራካሪ ወገኖች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለሙያው እና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ያለበትን የሙያ ሃላፊነት በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት መውጣት እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን በደንቡ አንቀጽ 29/2/ ደግሞ ማስረጃን ማሳሳት ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሠል አድራጐት እንዲፈጽሙ መምከር ወይም መርዳት የተከለከለ ተግባር እንደሆነ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በደንቡ አንቀጽ 56/4/ ሆን ብሎ ፍርድ ቤትን የሚያሳስት ወይም የተጋነነ ጽሁፎችንና ንግግር ማድረግ ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 56/6/ እንደተደነገገው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ አግባብነት እንዳለው አስመስሎ ማቅረብ የማይፈቀዱ ድርጊቶች እንደሆኑ ተጠቅሰዋል፡፡

ይህ ሆኖ ሣለ አመልካች ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 92/1/ ውጪ እና ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ በሚቃረን መልኩ የደንበኛቸው ባለቤት የነበሩት ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ግሩኘ የሚባል የንግድ ድርጅት ሳይኖራቸው አላቸው በማለት በሐሰት የተዘጋጀ የቢዝነስ ካርድ ለሥር ፍ/ቤት በማቅረብ ፍ/ቤቱን በማሳሳት ከቅን ልቦና ውጪ ለግለሰቧ እንዲከፈላቸው ተወስኖ የነበረውን ቀለብ እንዲቋረጥ ማድረጋቸው በተጠሪ የዲስኘሊን ኮሚቴ በማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ አመልካችንም ባቀረቡአቸው የመከላከያ ማስረጃዎች ማስተባበል ባለመቻላቸው ጥፋተኛ ተደርገው የቅጣት ውሣኔ የተላለፈባቸው እንዲሁም የተጠሪው የዲሲኘሊን ኮሚቴ ውሣኔ በይግባኝ ቀርቦ መጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የተጠሪ መ/ቤት የዲስኘሊን ኮሚቴ በ14/05/2002 ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 90784 በቀን 26/04/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች የመቀጮ ገንዘብ ብር 10,000 /አሥር ሺህ / ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ የተወሠነው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55794

ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች ፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** እነ አቶ ግርማይ ካሕሳይ - ጠበቃ ዜና ደባሱ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሥዩም ታደሰ ሐጎስ - ወኪል ሂሩት ታደሠ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ እጣው ከመድረሱ በፊት አባልነትን ያቋረጠ የእቁብ አባል ለእቁብ የከፈለው ገንዘብ ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ ኃላፊነት ያለበትን ወገን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች እና ቀድሞ የእቁቡ ሰብሳቢ ነበሩ በተባሉ በአንድ ግለሰብ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ተጠሪ አመልካቾች በኃላፊነት በሚሰሩትና በየሳምንቱ በሚጣል እቁብ ውስጥ ማህበርተኛ ሁነው በመመዝገብ 63,300.00(ስልሳ ሦስት ሺህ ሶስት መቶ ብር) መክፈላቸውን፣ ይሁን እንጂ እቁቡ ሳይጠናቀቅ መክፈል ማቆማቸውን፣ ለአመልካቾች የከፈሉት ገንዘብ እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርበውም ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር) ከፍሏቸው ቀሪውን ብር 33,300.00(ሰላሳ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ብር) እቁቡ ሲጠናቀቅ እንደሚከፍሏቸው አመልካቾች የፈረሙላቸው መሆኑን፣ ሆኖም ለመክፈል አመልካቾች ከፈረሙላቸው በኋላ ቀሪውን ገንዘብ እንዲከፍሏቸው ተጠሪ ጥያቄ ቢያቀርቡላቸውም አመልካቾች ያልፈፀሙላቸው መሆኑን ገልፀው ለእቁቡ ከፍለው ያልተመለሰላቸውን ብር 33,000.00 (ሰላሳ ሶስት ሺህ ብር) በአንድነትና በነጠላ ከእነ ሕጋዊ ወለዱ እንዲሁም ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት ግለሰብም ክሱ በቀረበበት ወቅት ከእቁቡ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና ጉዳዩ የሚመለከተው የአሁኑን አመልካቾችን መሆኑን ገልፀው በራሳቸው ላይ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን የተከራከሩ ሲሆን የአሁኑ አመልካቾችም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችንና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በመከራከሪያነት ያቀረቡት ነጥብም ተጠሪ አመልካቾችን ለመክሰስ ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ መብት የሌላቸው መሆኑን፣ በእቁቡ መተዳደሪያ ደንብም አመልካቾች ያለባቸው ኃላፊነትም የተጠሪን ክስ አይነት አለመሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ የተከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአመልካቾችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ በማድረግ በዋናው ጉዳይ ላይ



www.chilot.me

የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የስር 1ኛ ተከሳሽን ከክሱ ነጻ ሲያወጣ፣ የአሁኑ አመልካቾችን ግን ገንዘቡን ለመክፈል መፈረማቸው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ከተለየዩ ወጪና ኪሣራ ጋር በአንድነት እና በነጠላ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር.337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለተጠሪ የእቁቡን ገንዘብ ለመክፈል ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሳይኖርባቸው በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በእቁቡ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 7.4 ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካቾች በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የጎደለውን የእቁብ አባል ክስ መስርተው እየተከራከረ መሆኑ ከታወቀ ከዚህ በማለፍ የመክሰስ ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ በደንቡ ተሸፍኗል? ወይስ አልተሸፈነም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ያለውን አሰራርና ልምድ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት የፅሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ተጠሪ አባል ሁነው ገንዘብ መክፈላቸው በተረጋገጠው የእቁብ ማህበር ውስጥ በኃላፊነት ቦታ የሚሰሩ መሆኑ፣ ተጠሪ ለእቁቡ ከከፈሉት ገንዘብ ውስጥ ብር 30,000.00 ተመልሶላቸው ቀሪ ብር 33,000.00 ያልተከፈላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ ቀሪ ገንዘብ ደግሞ አመልካቾች ለተጠሪ ለመክፈል በፊርማ ያረጋገጡላቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ነጥቦች መሆናቸውን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾች ግዴታ ምንጩ የክፍያ ሰነዱ ላይ የተቀመጠው ፊርማቸው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን ክርክር ያላስተባበሉ መሆኑንም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልፅ ያሳያል፡፡ አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘቡን እንከፍላለን በማለት ግዴታ መግባታቸው ከተረጋገጠ የማይጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሲሆን ከኃላፊነት ነጻ ያደርገናል በማለት የሚጠቅሱት የእቁቡ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 7.4 ሙሉ ይዘቱ ሲታይም ሙሉ በሙሉ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያለባቸው የእቁቡ ፀሐፊና ዋናው ተቆጣጣሪ መሆናቸውን የሚጠቅስ ሁኖ አግኝተናል፡፡ 1ኛው አመልካች የእቁቡ ፀሐፊ፣ ሁለተኛው አመልካች ደግሞ የእቁቡ ተቆጣጣሪ የመሆናቸው ጉዳይ ደግሞ በሚገባ የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ አመልካቾች ራሳቸው በፊርማቸው አረጋግጠው በሰጡት የሰነድ ማስረጃ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ከመረጋገጡም በላይ ከላይ እንደተጠቀሰው የእቁቡ መተዳደሪያ ደንብም ቢሆን ይዘቱ ሲታይ ከተጠያቂነትና ኃላፊነት ነፃ የማያደርጋቸው ሲሆን አመልካቾች ግዴታውን ባልተወጣው የእቁቡ አባል ላይ ክስ መመስረታቸው በውጤት ደረጃ ተጠሪ አመልካቾችን እንዳይጠይቁ የሚያደርግ አይደለም፡፡ ግዴታውን ባልተወጣው ግለሰብ ላይ አመልካቾች ክስ መመስረታቸውን በስር ፍርድ ቤት ገልፀው ይኸው ተረጋግጦ ጥያቄአቸው ውድቅ መደረጉ ወይም ግዴታውን አልተወጣም የተባለው ግለሰብ ተጠሪ በመሰረቱት ክስ ውስጥ የክርክሩ ተካፋይ ያለመሆኑ ጉዳዩ በአንድ ላይ ቢታይ የክርክሩን አመራር ተገቢ ያደርገው ነበር ከሚባል በስተቀር ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በሚኖራቸው መብት፣



www.chilot.me

አመልካቾች ደግሞ ለተጠሪ በሚወጡት ግዴታ ለሚመለከተው ሰው የተወጡትን ግዴታ እንዲተካላቸው ለመጠየቅ ከሚኖራቸው መብት አንፃር ሲታይ የመብት መጣበብን ሊያስከትል ይችላል ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የሌለው በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54567

የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች ፡-** ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት - ዓ/ህግ መቅጫ ለገሠ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አ.ማ - ነ/ፈጅ ኃይለእየሱስ ደምሴ - ቀረቡ፡፡

2. ሮማን ገብሩ - የቀረበ የለም፡፡

3. ማሩ አላምረው - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍትሐብሔር ክርክር ሂደት በፍርድ ቤት የታገደ ንብረት እግዱ ተግባራዊ በሆነበት ጊዜ ተሸጦ ሲገኝ እግዱን ያሰጠውና የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን ስላለው መፍትሔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአመልካች ጠያቂነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የተደረጉ ናቸው፡፡ የስር ከሳሽ የክስ ይዘትም አቶ ብርሃኑ ታርቆ የተባሉ ግለሰብ በከሳሽ ድርጅት በቋሚ ሰራተኛነት ተቀጥረው ከ1988 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ በገንዘብ ያዥነት ሲሰሩ በነበረበት ጊዜ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመዘንጋትና አጋጣሚውን በመጠቀም ብር 28,794.70 /ሃያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና አራት ብር ከሰባ ሳንቲም/ በማጉደላቸውና ለግል ጥቅም በማዋላቸው ይህንን ገንዘብ እንዲከፍሉ ለምዕራብ ጎጃም መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ በመመስረት የመ/ቁጥር 2312 ተከፍቶ ተከሳሽ አቶ ብርሃኑ ታርቆ ተጠርተውና በጉዳዩ ላይ ተከራክረው የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው ፍርድ ቤት መጋቢት 08 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቶ ብርሃኑ ታርቆን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ዋናውን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለዱና ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል ውሣኔ መስጠቱን፣ ለዚህ ፍርድ ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ የአቶ ብርሃኑ ታርቆን ቤት የፍርድ ባለመብት የሆነው ድርጅት በዋናው ክርክር ጊዜ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ አሰጥቶ ለባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የእግድ ትዕዛዙን ያደረሰ ቢሆንም እግዱ ተጥሶ ቤቱን የፍርድ ባለዕዳው ሸጦ መገኘቱን ገልጾ ማዘጋጃ ቤቱ የፍርዱን ገንዘብ እንዲተካለት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም በቤቱ ላይ እግድ መሰጠቱን ሳይክድ ሁኔታው የተከሰተው በሰራተኞች ጥፋት መሆኑን ገልጾ መስሪያ ቤቱ ኃላፊነት እንደሌለበት፣ ሰራተኞቹም ወደ

ክርክሩ እንዲገቡለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም በአሁኑ አመልካች ጥያቄ መነሻነት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ተደርጐ ባቀረቡት መከራከሪያ ለጉዳዩ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በሁዋላ የአሁኑን አመልካች ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለ1ኛ ተጠሪ የፍርዱን ገንዘብ ያህል እንዲከፍል በማለት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ግን በነፃ በማሰናበት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙንና የሰበር አቤቱታውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ጥፋቱ ሰራተኛ የሆኑት የ2ኛ እና የ3ኛ ተጠሪዎች ሁኖ እያለ መስሪያ ቤት የሆነው አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ መባሉ ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ኃላፊነት አለበት ቢባል ደግሞ የኃላፊነት መጠኑ ሊሆን ይገባ የነበረው ቤቱ የተሸጠበት የገንዘብ መጠን እንጂ 1ኛ ተጠሪ በፍርድ ከአቶ ብርሃኑ ታርቀ እንዲከፈለው የተወሰነውን መጠን ያህል ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ ተብሎ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ ይክፈል ተብሎ የመወሰኑ ሁኔታ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ ተጠሪ ከአቶ ብርሃኑ ታርቀ የሚፈልገው የገንዘብ መጠን በፍርድ የተረጋገጠ ሲሆን በዋናው ክርክር ጊዜ ደግሞ የአቶ ብርሃኑ ታርቀ ንብረት የሆነውን ቤት በፍርድ ቤት በማስከበር የእግዱን ትዕዛዝ ለአሁኑ አመልካች አድርሶ ባለበት ሁኔታ የቤቱ ባለቤትና የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት ግለሰብ ቤቱን ለሌላ ሰው ራሳቸው ሸጠው በመገኘታቸው 1ኛ ተጠሪ ፍርዱን ሊያስፈጽም የሚችለውን የአቶ ብርሃኑ ታርቀን ንብረት ሊያገኝ ያልቻለ መሆኑን፣ እንዲሁም የቤቱ ሽያጭን በተመለከተ ተገቢ ነው የሚለውን ክርክር 1ኛ ተጠሪ አቅርቦም እስከ መጨረሻው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን፣ የአሁኑ አመልካች ሃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከረውም እግዱ ለመስሪያ ቤቱ መድረሱን በመካድ ሳይሆን ተግባሩ የተፈፀመው ሰራተኛ በሆኑት የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥፋት ነው በማለት መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው የእግድ ትዕዛዙ ደርሶት እያለ ይህንኑ ጥሶ ቤቱ እንዲሸጥ አድርጐአል፣ የሰራተኞች ጥፋት ስለመኖሩም አላስረዳም በሚል ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ አጥብቆ የሚከራከረው ጥፋቱ በሰራተኞች የተፈፀመ እንጂ በመስሪያ ቤቱ የተፈፀመ ነው ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የአመልካች ሰራተኛ በሆኑት የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የተፈፀመ ጥፋት ስለመኖሩ አመልካች ያላስረዳ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ይህ ድምዳሜ የማስረጃውን ታዓማኒነት መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ደግሞ ይህ ችሎት ሊመረምር የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የእግድ ጥሰት ተግባር የተፈፀመው በሰራተኞች ጥፋት መሆኑን አመልካች ካላስረዳ ደግሞ ራሱ ሃላፊነት የማይወስድበት ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም



www.chilot.me

የፍርድ ቤት እግድ ትዕዛዝ አለማክበር በሕግ ላይ በትክክል ተገልጾ የተደነገገውን ልዩ ደንብና ሥርዓት መጣስ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2028፣2035 እና 2126 መሠረት ኃላፊነትን የሚያስከትል ተግባር ነውና፡፡ በመሆኑም አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃን ከሕጉ ጋር ያገናዘበ እንጂ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች የሚከራከርበት ነጥብ የካሳ መጠኑን በተመለከተ ሲሆን በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ኃላፊነት መጠኑ ሊሆን የሚገባው ቤቱ በእርግጠኝነት የተሸጠበት ዋጋ እንጂ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከአቶ ብርሃኑ ታርቆ ላይ የሚፈልገው የፍርድ ገንዘብ መጠን አይደለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቤቱ በጨረታ ሳይሆን ከዚህ ውጪ የተሸጠ በመሆኑ በትክክል በምን ያህል ዋጋ እንደተሸጠ ተረጋግጧል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ቤቱ የተሸጠው በገበያ ዋጋ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች የኃላፊነት መጠኑን የሚቃወምበት ሕጋዊ ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የሌለ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 44804

ጥቅምት 04 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሰናይት ተመስገን - ጠበቃ አልታዬ ወ/አማኑኤል - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እጥፍወርቅ በቀለ - ጠበቃ አስናቀ ከፋለ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኗ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ክሱ ታህሣሥ 09 ቀን 1993 ዓ.ም የተፃፈ ሁኖ አመልካች የሟች አባታቸው የአቶ ተመስገን በቀለ ወራሽ መሆናቸውን በመግለጽ ሟችና ተጠሪ (በስር ተከሳሽ) በውርስ የተላለፈላቸውን በወረዳ 23፣ቀበሌ 13፣የቤት ቁጥር 1597/ለ/ እና /ሀ/ እንዳላቸውና ይህም መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ የቦታ መለያ ውል ድርሻ ድርሻቸውን ተከፋፍለው ከቆዩ በኋላም ሟች ከሞቱ ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ የሟችንም ድርሻ ጠቅልለው በመያዙ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ብር 30100.00(ሰላሳ ሺህ አንድ መቶ ብር) የኪራይ ገቢ እንዳገኙና የሟች የተለያዩ ቁሳቁሶችንም እንደያዙ በመዘርዘር ተጠሪ ክስ የቀረበበትን የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍሉ እና ቁጥሩ 159/ለ/ የሆነውን እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንዳ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ለማስረጃነትም የሰነድና የሰው ምስክሮችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ክሱ ያለ ማስረጃ የቀረበ ነው፡የውርስ ክፍፍል አላደረግንም፣እንዲያ ቢሆን ኑሮ ሌሎች ወንድሞቻችን በተካፈሉ ነበር፣ መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም የተደረገው የአጥር መለያ ጊዜአዊ ስምምነት ነው፣ ከሳሽን ባለቤትና ባለቦታ የሚያደርግ ካርታ ወይም ደብተር አላቀረቡም፣ክስ የቀረበበትን ቤት ተረክቤ የማስተዳድረው ሆኖ ሳለ ኪራይ ልጠየቅ አይገባም፣የቤት ቁሣቁስ አልተረከብኩም፣ቤቱን ግን ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ተረክቤ አስተዳድራለሁ፣ የቤት ቁጥር 1597/ለ/ እና /ሀ/ ሟች 600 ካ. ሜትር የቦታ ስፋት ጋር እናቴ ሐምሌ 3 ቀን 1957 የሰጡኝና ቤቱም በራሴ ገንዘብ የተሰራ በመሆኑ የግል ቤቴ ነው፣ካርታና ደብተር ለመቀበልም በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ በማለት ዘርዝረው የአመልካች ክስ ያለምንም ሕጋዊ ማስረጃ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡ ለማስረጃነትም የሰነድና የሰው ምስክሮችን ዘረዝረው አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን ከመመረመረ በሁዋላ ከ600 ካ.ሜትር ውጪ ያረፈውና መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም በአጥር የተለየው አከራካሪው ቤት ቁጥር



www.chilot.me

1597/ለ/ ወይም 1597/2/ በሚል የሚታወቀው ቤት የሟች አቶ ተመስገን በቀለ በመሆኑ ቤቱን የሟች ወራሽ ለሆኑት የአሁኗ አመልካች ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል፣ የኪራይ ገንዘብና የቤት ቁሳቁስን በተመለከተ የቀረበው ክስ ግን በማስረጃ የተደገፈ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ በተወሰነው የውሳኔ ክፍል፣ የአሁኗ አመልካች ደግሞ የቤት ኪራይ ገንዘብንና የቤት ቁሳቁስን በተመለከተ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት የየራሳቸውን ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ እና ተገቢው መጣራት ተደርጐ የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎች ከቀረቡ በሁዋላ የይግባኝ መዛግብቱ ተጣምረው ጉዳዩ ከተመረመረ በሁዋላ አመልካች ያቀረቡት ይግባኝ ውድቅ ሲደረግ የተጠሪ ተቀባይነት አግኝቶ አከራካሪው ቤት የተጠሪ እንጂ የአመልካች አውራሽ አይደለመ ተብሎ ተወስኗል፡፡ አመልካች ቤቱ የተጠሪ ነው ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አንድ ገጽ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አከራካሪው ቤት የአውራሻቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ይግባኙን የሰማው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው እና በይግባኝ ጊዜ ከሥነ ሥርአቱ ውጪ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጐ እንዲሁም የተጨማሪ ማስረጃዎችን ይዘት ባግባቡ ባላገናዘበ መልኩ ማስረጃውን መዝኖ የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ውሳኔው ተሽሮ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ ተጠሪ አቶ ተመስገን በቀለ ከሞቱ በሁዋላ ያዙት የተባለውና ከይዞታቸው 600 ካ.ሜትር ውጪ ያለ እንዲሁም መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት የተለየው በቀድሞው ወረዳ 23፣ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 1597/ለ/ ወይም 1597/2/ የሆነውን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ክርክሮችንና ማስረጃዎችን ይዘት ባገናዘበ መልኩ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ታህሣሥ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ዳኝነት የጠየቁበት ቤት የአውራሻቸው የሟች አቶ ተመስገን በቀለ መሆኑን ገልጸው ሲሆን ተጠሪ ቤቱን ሟች በሕይወት እያሉ ሲኖሩበት የነበረና ከሕልፈተ ሞታቸው በሁዋላ ተረክበው ማስተዳደር የጀመሩት መሆኑን እንዲሁም መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት መኖርን ሳይክዱ ቤቱን የሰሩት ሟች ሳይሆኑ ተጠሪ በግል ገንዘባቸው የሰሩት የግል ንብረታቸው መሆኑንና ምንጩም ሐምሌ 03 ቀነ 1957 ዓ.ም የተሰጣቸው የስጦታ ወሉ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን፣የግራ ቀኙ ምስክሮች በስር ፍርድ ቤት ቀርበው መሰማታቸውን ነው፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደጋቸው ምክንያቶች የተጠሪ ቤት በ600 ካ.ሜትር ቦታ ላይ ማረፉ በቀረበው ካርታ ተረጋግጧል፣በቀበሌው የቤት ቁጥር 1597/ለ/ በሚል የሚታወቅ ቤት ከካርታው ክልል ውጪ ያለና ተጠሪ እና የአመልካች አባት



www.chilot.me

መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም የይዞታ ስምምነት ያደረጉበት የአመልካች አውራሽ ቤትና ይዞታ በመሆኑ የተጠሪ ይዞታ አይደለም፣ በ1992 ዓ.ም በቤት ቁጥር 1597/2/ የተሰጠው የግብር ሂሳብ ማስታወቂያ የአመልካች አባት ካፈሩት በኂላ ለተጠሪ መመዝገቡን የሚያስገነዝብ ነው፣ ማስታወቂያው ለአመልካች አባት ይዞታው በ1980 ዓ.ም መሰጠቱንና የተጠሪ ይዞታ ከሆነው ከ600 ካ.ሜትር ውጪ መሆኑን ያሳያል የሚሉ መሆናቸውንም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የቤት ቁጥር 1597/ለ/ ወይም 1597/2/ የሆነውን ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክቡ ሲል የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሻረው በ28/2/92 ዓ.ም በተወሰደ የቦታ ልኬት የቦታ ስፋት ልዩነት መገኘቱ ለአመልካች አውራሽ ለቤት ቁጥር 1597/ለ/ የይዞታ ማረጋገጫ ሊሆን እንደማይችል፣ የግብር ማስተወቂያው ለአመልካች አባት በወርስ የተላለፈላቸው ሃብት ስለመኖሩና ለዚሁ የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ተደርጐ ሉወሰድ የማይችል መሆኑን፣ መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም ተደረገ የተባው ስምምነትም የድንበር መለያ ስምምነት እንጂ የውርስ ሃብት ድርሻ ክፍፍል የተደረገበት አለመሆኑን፣ ቤቱን የአመልካች አባት በውርስ ወይም በስጦታ አግኝተውት ባለሃብት ስለመሆናቸው የቀረበ የማስረጃ የለም፣ የአመልካች አባት በ30/05/1982 ዓ.ም ለሚኖሩበት ሰርቪስ ቤት ቁጥር እንዲሰጥ ጠይቀው በኮሚቴ 1597/ለ/ የሚል ቁጥር መስጠቱና ውሃና መብራት መግባቱም የይዞታ ማስረጃ ሊሆን እንደማይችል፣ የንፋስ ስልክ ላፍቶ አስተደደር ጽ/ቤት ኀዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ ለአመልካች አባት በጠየቁት መሰረት ከመፈቀዱ ውጪ የቦታ ይዞታ በተጠሪና በባለቤታቸው አቶ ከበደ ወ/ጊዮርጊስ ስም ብቻ መሆኑና በ1967 ዓ.ም የቤት ቁጠር ሲሰጥም የተሰጠው ቁጥር 1597 ሆኖ በተጠሪና በባለቤታቸው ስም መሆኑን ማረጋገጡን፣የክፍሉ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ታህሣሥ 06 ቀን 1998 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ የይዞታው አመጣጥ ተጠሪ ከእናታቸው በስጦታ ያገኙት መሆኑና በማህደር ውስጥ የቤት ቁጠር 1597 የሚል ከመሆኑ ውጪ በ/ሀ/ እና በ/ለ/ የተለየ ቤት ቁጥር የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩን እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ይዞታው በካርታ ቁጠር 05/203/11862/00 በተጠሪ፣ በግዛቸው በከበደና በትዝታ አበበ መመዝገቡን ማረጋገጡን፣ተጠሪ ከ1968-1992 ዓ.ም ድረስ በቤት ቁጥር 1597/2/ ግብር ስለመክፈላቸው ማስረጃ ማቅረባቸውን፣ የካቲት 17 ቀን 1998 ዓ.ም የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ለፍርድ ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ በተጠቀሰው ካርታ ውስጥ የቤት ቁጥር 1597/ለ/ የሚል ቤት አለመኖርንና በግቢው ውሥጥ የቤት ቁጠር 1579/2/ ራሱን የቻለ ቤት እንደሚገኝ ሪፖርት የቀረበለት መሆኑን ማረጋገጡን፣የአመልካች ምስክሮች የአመልካች አባት ቤት ሲሰራ አየን ባሉበት ግቢ ውስጥ ሌሎች ቤቶች መኖራቸውን፣የተሰራው ቤት፣የቤት ቁጥር እና ቦታው የማን እንደሆነ እንደማያውቁ የመሰከሩ ናቸው፣በተጠሪ፣በግዛቸው ከበደና ትዝታ አበበ ስም የተመዘገበ የቤት ቁጥር 1597 ካርታ ይዞታ 666 ካ.ሜትር መሆኑ ተረጋግጧል የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ነው፡፡

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያጣሩት ነጥብና ማስረጃውን በመመዘን የደረሱበት ድምዳሜ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት ጉዳዩን እንዲመረምር ጉዳዩ ለችሎቱ ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ በዚህ ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር ሲያደርጉ የተጠሪ ጠበቃ የተያዘው ጭብጥ የማስረጃ ጉዳይ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው አይደለም በማለት ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ በእርግጥ ይህ ሰበር ችሎት ሊመለከተውና ማረም የሚገባው ጉዳይ የማስረጃን ጉዳይ ሳይሆን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ



www.chilot.me

10 ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሰበር ችሎት እንዲመለከተው የተያዘው ጭብጥ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ይዘት ባግባቡ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር እንጂ የማስረጃውን ክብደት ወይም ታአማኒነት ለመመርመር ተብሎ አይደለም፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም በጉዳዩ ላይ የቀረቡት የሰው ምስክሮች አከራካሪው ቤት በሟች አባቱ የተሰራ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሁነው እያለ እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘትም ይህንኑ የሚደግፍ ሁኖ እያለ በአግባቡ ሳይታይ ታልፏል በሚል ነው፡፡ በመሆኑም ሊነሣ እና ሊታይ የሚገባው ጭብጥ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የቀረቡት ማስረጃዎችን ይዘት መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚል ሲሆን ለክርክሩ የቀረቡት ማስረጃዎች ይዘት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነጥብ ከሕጉ ጋር በአግባቡ ተዛምዶ አልታየም የሚለው ቅሬታ የሕግ ነጥብ እንጂ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት ባለመሆኑ የተጠሪ ጠበቃ ጉዳዩ የማስረጃ ምዝና ስለሆነ በሰበር ችሎቱ የሚታይ አይደለም በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ቀጥለን ተጠሪ ከ600 ካ.ሜትር ውጪ ያለውንና በመጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት በአጥር የተለየውን ቁጥሩ 1597/ለ/ ወይም 1597/2/ በሚል የሚታወቀውን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ተመልክተናል፡፡ አከራካሪው ቤት በአመልካች አባት የተሰራ ስለመሆኑ የአመልካች ምስክሮች ማረጋገጣቸውን የበታች ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ክስ መልስ ሲሰጡ ቤቱ በገንዘባቸው የተሰራ መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን ምስክሮቻቸው ቤቱ በተጠሪ የግል ገንዘብ የተሰራ መሆኑን አስረድተዋል ወደሚለው ድምዳሜ የስር ፍርድ ቤቶች አልደረሱም፡፡ በመሆኑም ቤቱ በአመልካች አባት የተሰራ መሆኑ በሰው ምስክሮች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የአመልካች አባት የቦታውና የቤቱ ባለሃብት ስለመሆናቸው የሚያሳይ ማስረጃ የለም ተብሎ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ድምዳሜ የተያዘው የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት በመመርመር ነው፡፡ አከራካሪው ቤት ተጠሪ ከእናታቸው በስጦታ ባገኙት ቦታ የተሰራ መሆኑ የተካደ አይደለም፡፡ ሆኖም ዋናው ነገር በቦታው ላይ ያለውን ቤት የሰራው ሰው ተጠሪ ወይስ? የአመልካች አባት? የሚለው ነው፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ ደግሞ አመልካች ባቀረቧቸው የሰው ምስክሮች በሚገባ መረጋገጡን ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ነው፡፡ በሕጉ አግባብ የሚታወቀው ቦታ ቀድሞ የነበረው ስፋት እንደነበር፣ ስፋቱ በሁዋላ እየተቀነሰ ግብር ሲገበርበት የነበረ መሆኑም በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ተገቢው ማብራሪያ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ እነዚህ አካላት የቦታውን አመጣጥ፣ በቦታው ላይ በማህደር የሚታወቀው ቤት ቁጥር ስንት እንደሆነ፣ ካርታው በማን ስም እንደተመዘገበ እና ስፋቱ ስንት እንደሆነ መግለጫ መስጠታቸውን መሰረት በማድረግ አከራካሪው ቤት የአመልካች አውራሽ ስለመሆኑ ማስረጃ የለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ቤቱን ማን ሰራው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ፣ለጉዳዩ አወሳሰን ቁልፍ የሆነውን ፍሬ ነገርን በተመለከተ የቀረቡትን ማስረጃዎችን ይዘት ባግባቡ ሳይመረመር ነው፡፡ ተጠሪ ቦታውን በስጦታ አገኘሁ ከማለት ውጪ ቤቱን በግል ገንዘባቸው የሰሩት መሆኑን አላስረዱም፡፡ መሬት የኢትዮጵያ ህዝቦችና የመንግስት ብቻ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/3/ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ሕገ መንግስቱ በተጠቀሰው አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ስር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት መሆኑ/መሆኗ በሕግ የተከበረለት መሆኑ የተደነገገ ሲሆን የግል ንብረት በጉልበት፣ በፈጠራ ችሎታ ወይም በካፒታል የሚፈራ ስለመሆኑና ጥበቃም የሚደረግለት መሆኑን ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው መሬት የመንግስት እና የሕዝብ ብቻ መሆኑን



www.chilot.me

በጉልበት፣ በፈጠራ ችሎታ ወይም በካፒታል የተፈራ ንብረት በሕግ ጥበቃ የተደረገ መሆኑ እንዲሁም በሕጉ አግባብ የተገኘ የመሬት ባለይዞታነት የሕግ ጥበቃ የሚደረግለት መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1204 እና 1026 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎችም የባለቤትነት መብት የሕግ ጥበቃ ያለው መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በሕጉ አግባብ የተፈራ ንብረት ደግሞ ለሟች ወራሾች በውርስ ሊተላለፍ የሚችል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826/2/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

ተጠሪ ቦታውን በስጦታ ከእናታቸው ያገኙት ነው ቢባልም ባዶ ቦታውን የአመልካች አውራሽ ይዘው ቤት ሲሰሩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1178 እና 1179 መሠረት ተቃውሞ ያሰሙ ስለመሆኑ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ በሕጉ አግባብ በተሰጣቸው ካርታ ውስጥ አከራካሪው ቤት ተሰርቷል ቢባል እንኳ ቤቱ በአመልካች አውራሽ ጉልበትና ገንዘብ ስለመሰራቱ እንዲሁም ተጠሪ በወቅቱ ተቃውሞ የነበራቸው አለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የቦታው ካርታ አንድ ነው፣ ግብርም በዚሁ ካርታ መሠረት ስለመገበሩ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ብቻ ቤቱ የተጠሪ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪ ከአመልካች አባት ጋር መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት ሲታይም የድንበር መለየት ጉዳይን የሚመለከት ቢሆንም በቦታው ላይ ሁለት ቤቶች እንደነበሩ፣ የአመልካች አባት ይዘውት የነበረው ቤት ተጠሪ ከያዙት ከ600 ካ.ሜትር ውጪ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሲሆን ስምምነቱ የውርስ ክፍፍል ስለመሆኑ የማያሳይ ቢሆንም አከራካሪው ቤት በአመልካች አባት አልተሰራም ለማለት ግን የሚያስችል አይደለም፡፡ ተጠሪ ቤቱን ከአመልካች አባት ሞት በኋላ መረከባቸውን በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክርክር ገልፀዋል፤ ሆኖም ቤቱ የግላቸው ንብረት ስለመሆኑ ግን አላረጋገጡም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤት በአመልካች አባት የተሰራ መሆኑ ስለመረጋገጡ ተቀብሎ እያለ የውርስ ድርሻ ክፍፍል የተደረገበት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ቤቱ የአመልካች አባት የግል ንብረት አይደለም ማለቱ በሚመለከታቸው አካላት የተሰጠው የሰነድ መግለጫ ማስረጃም የቦታውን አመጣጥና በቦታው ላይ ያሉ ቤቶች በሕጉ አግባብ የተሰጠውን መለያ ቁጥር ከሚገልጽ በስተቀር ቤቱ በማን ተሰራ የሚለውን ጥያቄ በግልጽ ምላሽ ባልሰጠበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ መሻሩ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ይዘት ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግስት እና የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46403 ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42971 የካቲቲ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት በከፊል ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01180 መጋቢት 29 ቀን 1998 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ ከአቶ ተመስገን በቀለ ሞት በሁዋላ የያዙትንና ከተጠሪ ይዞታ /600 ካ.ሜትር/ ውጭ ያለውንና መጋቢት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት ድንበሩ የተለየውን በቀድሞ ወረዳ 23 ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 1597/ለ/ ወይም 1597/2/ የሆነውን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58822

መጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐቃቤ ሕግ ታደሰ ተስፋዬ - ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** አይንሽምስ ሁሴን አብደላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር በወንጀል ክስ ምክንያት በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየውና በኋላ ከወንጀሉ ክስ በነፃ ለተሰናበቱት ለአሁኑ ተጠሪ ይመለስ የተባለው የአፈር ወርቅ ይዞት በቆየው አካል በአሁኑ አመልካች ተሽጦ ከተገኘ ለወርቁ ባለቤት ሊከፈል የሚገባው ተሸጧል የተባለበት ዋጋ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ 2512 ግራም የአፈር ወርቅ በህገወጥ መንገድ ደብቆ ሊያሣልፍ ሲል ተይዟል ተብሎ በቀረበበት የወንጀል ክስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክርና ማስረጃዎቹን መርምሮ ወንጀሉን መፈፀሙ ተረጋግጧል ብሎ ጥፋተኛ በማድረግ በኤግዚቢትነት የተያዘው የአፈር ወርቅም እንዲወረስ ወስኖ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር ከክሱ በነፃ እንዲሰናበት ፣ በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየው የአፈር ወርቅም ለአሁኑ ተጠሪ እንዲመለስለት ወስኗል፡፡

ይህ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ይግባኝ ተብሎበት የተለወጠ ባለመሆኑ ኤግዚቢቱ ይመለስልኝ የሚለውን ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው ሲሆን የአሁኑ አመልካች ቀርቦ ሲጠየቅ የአፈር ወርቁን በወቅቱ በነበረው ዋጋ እክፍላለሁ የሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች የአፈር ወርቁን ዋጋ እከፍላለሁ ያለውን ቢቀበሉትም የሚከፈለው በወቅቱ በነበረው ዋጋ ነው በሚለው ላይ ሣይስማሙ ቀርተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአሁኑ አመልካች ገንዘቡን የምከፍለው በወቅቱ በነበረው ዋጋ ነው ያለው ተገቢ አይደለም በማለት ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ዋጋው ታስቦ ለአሁኑ ተጠሪ መክፈል ይገባዋል የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡



www.chilot.me

በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራቀኙ እንዲቀርቡ አድርጐ በጉዳዩ ላይ ካከራከረ በኋላ መርምሮ በሰጠው ፍርድ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ አመልካች የአፈር ወርቁን ዋጋ መክፈል ያለበት በወቅቱ በነበረው ዋጋ መሠረት ሣይሆን በኋላ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በነበረው የገበያ ዋጋ መሠረት ነው በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የቀረበ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ተብሎ በመታዘዙ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በጽሑፍ በሰጠው መልስ የአሁኑ አመልካች በወቅቱ የአፈር ወርቁ የተሸጠበትን ዋጋ እከፍላለሁ በማለት የጠየቀው ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም፣ ወርቁን በአይነት መመለስ ካልቻለ በጊዜው በወጣው የብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ዋጋ መሠረት መክፈል ይኖርበታል በማለት ተከራክሯል፡፡ በተጠሪ በኩል በጽሑፍ የተሰጠው መልስ ለአመልካች የተሰጠ ቢሆንም ከመዝገቡ እንደሚታየው በጽሑፍ ያቀረበው የመልስ መልስ የለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ የሰበር ችሎቱም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ መክፈል የሚገባው የኤግዚቢቱ የአፈር ወርቅ ዋጋ በወቅቱ ሽጫለው የሚልበትን ዋጋ ነው ወይንስ በኋላ ፍ/ቤት ወርቁን መመለስ አለበት የሚል ትዕዛዝ በሰጠበት ጊዜ የነበረውን ዋጋ ነው? የሚለውን ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተ፡-

የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ተጽፎ ባቀረበው የሰበር ማመልከቻው ላይ በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየውን የአፈር ወርቅ ሊሸጠው የቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑን ተጠሪ በወንጀሉ ጥፋተኛ በማድረግ መጋቢት 22 ቀን 1997 ዓ.ም ወርቁ እንዲወረስ በማለት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መሆኑንና ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወርቁ እንዳይሸጥ የሚል ትዕዛዝ ያስተላለፈው ወርቁ በውርስ ውሣኔው መሠረት እንዲሸጥ ከተደረገ በኋላ ሰኔ 15 ቀን 1997 ዓ.ም እንደሆነ የገለጹ ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን ገልጿል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ይህንን በሚመለከት በጽሐፍ ባመጣው መልስ ላይ የአሁኑ አመልካች ወርቁን የሸጠው መቼ ነው? ከፍ/ቤቱ ዕግድ በኋላ ወይንስ በፊት? የሸጠውስ በምን ያህል ነው? የሚለውን በሚስጥር ይዞ ስለማቆየቱና ክርክሩም በማስረጃ የተደገፈ እንዳልሆነ ገልጿል ከማለት በቀር አመልካች ወርቁን የሸጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዳይሸጥ የሚል የዕግድ ትዕዛዝ ከሰጠና ከደረሰው በኋላ ነው በሚል በግልጽ ያቀረበው ክርክር የለም በግልጽ ያልተካደ ፍሬ ነገር ደግሞ በሕጉ እንደታመነ የሚቆጠር ነው፡፡

አመልካች በኤግዚቢትነት ይዞ የቆየውን የአፈር ወርቅ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወርቁ እንዳይሸጥ በማለት የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪን በወንጀሉ ጥፋተኛ በማድረግ ወርቁ ይወረስ ብሎ በሰጠው የውርስ ወሣኔ መሠረት የሸጠው መሆኑ የታመነ ሆኖ ከተገኘ አመልካች ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደደው በወቅቱ ወርቁን የሸጠበትን ዋጋ ነው፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ተጠሪን ከወንጀል ክሱ በነፃ በማሰናበት ወርቁ ይመለስለት ብሎ ባዘዘበት ጊዜ በነበረው የገበያ ዋጋ መከፈል አለበት በሚል የቀረበው ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1ኛ) የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ/43191 የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና

2ኛ) የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ. 90395 ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሻሽሎ የአሁኑ አመልካች በኤግዚቪትነት ተይዞ የቆየውን 2512 ግራም አፈር ወርቅ በወቅቱ የሸጠበትን ዋጋ ለአሁኑ ተጠሪ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

3ኛ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

4ኛ) በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52530

ኀዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ አቶ ሰናይ ልዑልሰገድ(ሁለት ሰዎች) - ጠበቃ መኮንን ሰሙ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ ትእግስት ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር አመልካች የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሲሆኑ የአቤቱታቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ልዑል ሰገድ መዘምር ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውንና የሟቹን ንብረት የአሁኑ ተጠሪዎች ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው ተጠሪዎች ተጠርተው ቀርበው የውርስ አጣሪ እንዲሾምና ውርሱ ተጣርቶ ሲቀርብ አስፈላጊው ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካቾችን አቤቱታ መርምሮ ውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው በማለት መዝገቡን በትእዛዝ ዘግቶታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የውርስ ማጣራት ጉዳይ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን ነው ተብሎ መወሰኑ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 35657 ከሰጠው የሕግ ትርጉም አኳያ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው ሚያዝያ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸው ላይም የሰበር ችሎቱ በመ/ቁጥር 35657 የሰጠው ትርጉም በመ/ቁጥር 36205 የተለወጠና መለወጡም ባግባቡ መሆኑን ገልጸው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡



www.chilot.me

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ይህ ችሎት አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 እና ስለውርስ አጣሪ በ1952 ዓ.ም በወጣው በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎችን በመመርመር ውርስ አጣሪን የመሾም ሥልጣን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ መሆኑን በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኘውን ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁ. 35657 ጥቅምት 13 ቀን 2001 ዓ.ም፣በሰ/መ/ቁ. 42015 ኅዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም፣በሰ/መ/ቁ. 51329 ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ የሕግ ትርጉም አለመለወጡንም ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 51329 ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በግልጽ አረጋግጧል፣ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ እንደሚችል የደነገገ ቢሆንም በዚሁ አግባብ ቀድሞ የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁ. 36205 አልተለወጠም፡፡ በተያዘው ጉዳይም የስር ፍርድ ቤቶች ይህ ሰበር ችሎት ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በሕጉ አግባብ ባልተለወጠበት ሁኔታ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ሳይቀበሉ መቅረታቸው ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ማንኛውም ፍርድ ቤት አንድ ጉዳይ ሲቀርብለት ጉዳዩን የማየት ሕጋዊ ስልጣን ያለው መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ስልጣኑ የሆነውን ጉዳይ ደግሞ ከሕጉ አግባብ ውጪ በሆነ ምክንያት አልተመለከትም ሊል አይችልም፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/ለ/ሸ/ እና አዋጅ ቁጥር 408/96 መሰረት የወራሽነት የምስክር ወረቀት ከመስጠት በስተቀር ውርስ እንዲጣራ አጣሪውን የመሾም የስረ ነገር ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ ተገልፆ በዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ መሰረት ባልተለወጠበት ሁኔታ የከተማው ፍርድ ቤት ውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን አለው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. በ21/11/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83998 ታህሳስ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. የውርስ አጣሪ የመሾም የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው ብለናል፡፡
3. የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ የሚቀርበውና ውርስ አጣሪውንም መሾም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር ስለሚወድቅ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ እንዲመለከት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

## የልዩነት ሐሳብ

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ የማልስማማ በመሆኑ የምለይበትን ሐሳብ እንደሚከተለው አሰፍራለሁ፡፡

በእኔ እምነት የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን አላቸው፡፡ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀጽ 1/ሸ/ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን በመመርመር ውሣኔ የመስጠት ስልጣን እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ወራሽ የሆነው ሰው የሟች የኑዛዜ ወይም የሕግ ወራሽ መሆኑንና ከውርስ የሚደርሰውን ድርሻ የሚይዝ እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 996 ተመልክቷል፡፡ ይህንን ለማወቅ የግዴታ የውርስ አጣሪ መሾምና በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብትና ግዴታዎቹን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ሕግ አውጭ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡ ሥልጣን ሲሰጥ ለወራሽነት የምስክር ወረቀት ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ሁሉ የመፈፀም ሥልጣን እንዲሰጣቸው ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው ነው ስለሆነም በዚህና ከዚህ በፊት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35654 በገለጽኳቸው ምክንያቶች አብላጫው ድምጽ ከሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53328

ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ዓብዱል መሐመድ - ጠበቃ አሰፋ መኮንን - ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ዘበናይ ኃይሌ - ቀረበች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው ተጠሪ ናት፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው ከሟች እህቴ በኑዛዜ የወረስኩትን ቤት ከሕግ ውጪ ይዞ ስለሚገኝ ለቆ ያስረክበኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የሥረ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ መቃወሚያዎቹ ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያስችል መብት የላትም እንዲሁም ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚሉ ሲሆን፣ ሥረ ነገርን በተመለከተም ቤቱ ከወ/ሮ ንጋቷ /ሟች/ በብር 250000 በውል ገዝቼዋለሁ፡፡ ከዋጋው ውስጥ ብር 240000 በመክፈል ቤቱን ተረክቤአለሁ፡፡ ከሣሽም ጉዳዩን /ውሉን/ ለማስፈጸም ብር 40000 ከኔ ወስዳለች የሚሉትን ነጥቦች ማንሳቱን ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቦ ተጠሪ በውሉ መሠረት የማስፈጸም ግዴታ ያለበት በመሆኑ የቤቱን የባለቤትነት መብት እና ካርታ በስሜ እንድታስተላልፍ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ስለመጠየቁ ከመዝገቡ አረጋግጠናል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሁለቱንም ወገኖች ክርክር መርምሮአል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችን ክርክር ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 22 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ አቤቱታ አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ለሕጉ የተሰጠው ትርጓሜን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ



www.chilot.me

መሠረትም አመልካች እና ተጠሪ በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ በሚመለከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት መቃወሚያ ያቀረበው ከሟች ጋር በተደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ገንዘቡን ከፍዬ ቤቱን ተረክቤያለሁ የሚልበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው በ1988 ዓ.ም. ሆኖ ተጠሪ ክስ የመሠረተችው ደግሞ በ2001 ዓ.ም. ነው፡፡ ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው የሽያጭ ውሉን ሳታስፈርስ እንደሆነም መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1168 በተደነገገው መሠረት ለ15 ዓመት ግብር በተከታታይ ከፍሎ ቤቱን ስለመያዙ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነም ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቤቱን ይዞ የሚገኘው አመልካች ላቀረበው የይርጋ መቃወሚያ አወሳሰን ተገቢነት አለው በማለት የጠቀሰው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1168 “ስለግል ሃብት” በተመለከተ በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕግ በአንቀጽ 7 ሥር ነው የሚገኘው፡፡ የዚህ አንቀጽ አንደኛው ክፍል የሆነው ምዕራፍ 1 ሀብት ስለሚገኝበት ሁኔታ፣ ሀብትን ስለማስተላለፍ እንዲሁም ሀብት ስለሚቀርበት እና ስለ ሀብትነት ማስረጃ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቶ የያዘ ሲሆን፣ ከፍ ሲል የተጠቀሰው ቁ. 1168 በተለይ የሚገኝበት የምዕራፉ ክፍል 1 ደግሞ ሀብት ስለሚገኝበት ሁኔታ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዞአል፡፡ በዚህ መሠረትም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው በንብረቱ ላይ የባሃብትነት መብት የሚያገኝበት ሁኔታ በቁጥር 1168 ተደንግጎአል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው መርህ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በይዞታው ሥር ያደረገው ሰው የዚህኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ አሥራ አምስት /15/ ዓመት በስሙ ከከፈለ የንብረቱ ባለቤት እንደሚሆን ነው የሚያመለክተው፡፡ በመሆኑም የማይንቀሳቀሰውን ንብረት የያዘው ሰው ንብረቱን እንዲለቅ ሲከሰስ ድንጋጌውን በመጥቀስ ሊከራከር የሚችለው በድንጋጌው የተመለከቱትን ሁኔታዎች አሟልቶ በመያዙ የንብረቱ ባለሃብት መሆኑን ለማረጋገጥ እንጂ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ለማለት አይደለም፡፡ የይርጋ መርህ ክስን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት በመሆኑ ንብረትን በመያዝ ወይም ባለይዞታ በመሆን የባለሃብትነት መብት ከሚገኝበት መርህ ወይም አግባብ የተለየ ነው፡፡ ስለዚህም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ ለይርጋው መቃወሚያ አወሳሰን መሠረት ማድረጉ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመቀጠል የተመለከትነው አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የሚደረግበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካች ቤቱን የያዘው ከሟች ወ/ሮ ንጋቷ ሃይሌ (ተጠሪ አውራሼ ናት የምትላት) ጋር በ1988 ዓ.ም ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግንዛቤ እንደተወሰደበት ከውሳኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሌላ በኩል ግን የሺያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 በተደነገገው መሰረት በውል አዋዋይ ፊት ያልተመዘገበ በመሆኑ ለአመልካች የሚሰጠው መብት የለም፤በሻጭም ሆነ በወራሽ (ተጠሪ) ላይም የሚያስከትለው ግዴታ የለም፤ በአጠቃላይ ውሉ ሕጋዊ ውጤት የለውም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ፍ/ቤቱ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጕአል፡፡ በእርግጥ ፍ/ቤቱ የይርጋውን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው ከላይ በተገለጸው ምክንያት በመሆኑ ውሉ በሕጉ የተቀመጡትን የፎርም ሁኔታዎች (መስፈርቶች) አያሟላም ከሚለው ትችቱ ጋር አላያያዘውም፡፡ ይሁንና ትችቱ የሽያጭ



www.chilot.me

ውል መደረጉን ስለሚያመላክት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ በመወሰን ረገድ ጠቃሚ ፍሬ ነገር ነው፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ በክስዋ ያቀረበችው የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ቤቱን ያስረክበኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ተጠሪ ቤቱን ልትረከብ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው የሥረ ነገር ጭብጥ ከመታየቱ በፊት ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባው የይርጋ መቃወሚያ አቅርቦአል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የአመልካችን የይረጋ መቃወሚያ ውድቅ ታስደርግ ዘንድ በቅድሚያ ይጠበቅባታል፡፡ አመልካች ቤቱን የያዘው በውል እንደመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው ወይም ተሰርዞአል ሳይባል እንዲለቅ የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡ በእርግጥ አመልካች በመከራከሪያነት ያቀረበው ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 በተደነገገው መሰረት አልተደረገም ተብሎአል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል በጽሑፍ እና ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ወይም በፍ/ቤት ካልተደረገ ውጤት እንደማይኖረው የተጠቀሰው ድንጋጌ ያመልክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በሕጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርአት አለመከተል የሚያስከትለው ውጤት ምን እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808/2/ ተደንግጉአል፡፡ በዚህም መሰረት ይህን የመሰለ ውል የሚፈርሰው ከተዋዋዮቹ አንዱ ወይም ማናቸውም ጥቅም ያለው ሰው ሲጠይቅ እንደሆነ ሕጉ ያመለክታል፡፡ ይህም የሚያስገነዝበን የአፃፃፍ ሥርአትን ያላሟላ ነው የተባለው ውል በሕጉ በተመለከቱት ሰዎች እንዲፈረስ ጥያቄ እስካልቀረበበት ድረስ ከጅምሩ ፈራሽ ነው ሊባል እንደማይችል ነው፡፡ ውሉ እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄም በጊዜ የተገደበ ነው፡፡ የአፃፃፍ ሥርአቱን ያልተከተለ ውል እንዲፈረስ ጥያቄው መቅረብ ያለበት በአሥር /10/ ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808/2/ እና 1845 ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መንፈስ እና ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው መስከረም 12 ቀን 88 ሆኖ ተጠሪ ክስ የመሰረተችው ደግሞ ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም እንደሆነ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት ክሱ የቀረበው ውሉ ከተደረገ ከ13/ አሥራ ሦስት/ ዓመት በኋላ ነው ማለት ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጉ ባለማየቱ ከተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ችሎአል፡፡ ከፍ ሲል እንደገለጽነው ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያላቸው ድንጋጌዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808/2/ እና 1845 በመሆናቸው አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ ውድቅ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጉም ረገድ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39406 ጥቅምት 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 87347 ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 42824

ኅዳር 08 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ብርሃኔ ተሰማ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ታምራት አያኔ - ጠበቃ ወረደ ወ/አማኑኤል - ቀረቡ

2. የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

በሌሉበት የሚታይ ነው፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1225 ስር የተመለከተውን ንውጽውጽታን /Nuisance/ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች የስር ከሣሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ ክሱም የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ ሆኖ ይዘቱም ባጭሩ በመኖሪያነት በተሰጣቸው ቦታ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የገነቡት ቤት ያላቸው ሆኖ ይኸው ተጠሪ በመኖሪያ ቤታቸው ላይ የብየዳ ሥራ በመስራታቸው ጎረቤት በሆኑት አመልካች ላይ የድምጽ ብክለት ሁከት መፍጠራቸውን፣ 2ኛ ተጠሪም የብረታ ብረት ብየዳ ሥራ በኢንዱስትሪ ዞን መስጠት ሲገባው ያላግባብ ፈቃዱን መስጠቱን ገልፀው የተፈጠረው የድምጽ ሁከት ሊወገድላቸው፣ የሥራ ፈቃድም እንዲሠረዝ እንዲደረግ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪም ጉዳዩን በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ሊታገድ እንደሚገባውና የብይዳ ማሽኑ ዝቅተኛ ድምጽ ያለው መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪም የሥራ ፈቃዱን የሰጠው በሕግ አግባብ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የታገደ ነው፣ 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ደግሞ የሰጠውን ፈቃድ የሚሰርዘው ራሱ እንጂ ፍርድ ቤት አይደለም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው



www.chilot.me

አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሁከቱ በክፍሉ ደንብ አስከባሪ ትእዛዝ መሠረት ቆሞ ቆይቶ እንደገና ሲፈጠር ክስ ያቀረበ ሆኖ እያለ በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ይታገዳል ተብሎ መወሰኑ የሕግ ግድፈት ያለበት ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ ተገቢው ውሣኔ እንዲሰጥበት ይደረግ ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም አመልካች የተፈጠረው ሁከት ለተወሰነ ጊዜ ከተወገደ በኂላ እንደገና ሁከቱ በመጀመሩ ምክንያት የቀረበው ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው 1ኛው ተጠሪ ሲቀርቡ 2ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የአመልካች የሰበር ቅሬታ ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሣ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊነሳ አይገባም፣ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ መወሰኑም ባግባቡ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊመመርመር ይገባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሮታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ጉረቤት ሆነው በሚኖሩበት አካባቢ 1ኛ ተጠሪ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ወስደው የብረታ ብረት ብየዳ ሥራ እንደሚሰሩና በስራው ወቅት ጥቅም ላይ የሚውለው ማሽን በሚያሰማው ድምጽ አመልካች ሁከት ተፈጥሮብኛል የሚሉ መሆኑን ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ የብየዳ ሥራውን ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ የሚሰሩት መሆኑን በመግለጽ የሚከራከሩ መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1225 ስር በባለቤትነት መብት ያለመጠን መገልገልን የሚደነግገው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 ስር ከተመለከተው በይዞታ ላይ ሁከት ስለመፍጠር እጅጉን የተለየ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1225 ስር የተመለከተው ጉዳይ በሰፊ የባለቤትነት መብት ላይ በህጉ ከተመለከቱት ገደቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ ባለቤቱ ድርጊቱን የሚፈጽመው ወይም ሥራውን የሚፈጽመው በራሱ ንብረት ወይም ቤት ውስጥ ቢሆንም የድርጊቱ ወይም የሥራው ውጫዊ መገለጫዎች ሌላውን ጉረቤት ወይም ባለቤት፣በሌላ ሕጋዊ አግባብ ተጠቃሚ የሆነውን ሰው እንዳይረብሽ፣ እንዳያውክ ወይም በማናቸውም መልኩ ከተገቢው በላይ የሆነ ችግርን እንዳያስከትል በማድረግ መብቱን በልክ ባለቤቱ ይጠቀም ዘንድ ህጉ ያበጀው፣ የባለቤትነት መብትን አጠቃቀም አድማስን የሚወሰን ሥርአት ስለመሆኑ ከአንቀጽ 1226 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ጋር አዛምደን በምናነብበት ጊዜ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 ስር የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የክርክሩ ባህርይ የሚያሳየው የአመልካች ጥያቄ በይዞታቸው ላይ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድላቸው ሳይሆን የማሽኑ ድምጽ የፈጠረባቸው ረብሻ እንዲወገድላቸው ነው፡፡ የማሽኑ ድምጽ ሥራው እስከተሰራ ድረስ የሚቀጥል መሆኑም ግልጽ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የብየዳው ሥራ ከተጀመረ በኂላ የጊዜ ማለፍ ሁኔታ መኖር በድምጽ ሁከት ተፈጥሮብኛል በማለት ክስ ለማቅረብ የሚገድብ አይደለም፡፡ ዋናው ቁልፉ ነገር ድምፁ ከመጠን በማለፉ ረብሻ መፍጠሩን ማረጋገጥ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1225 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማውም ባለሐብቱ በመብቱ በሚገለገልበት ጊዜ የጉረቤቱ ርስት ጥቅም የሚቀንስበትን ወይም



www.chilot.me

የሚጐዳበትን ማናቸውንም ከመጠን ያለፈ ነገር ከመስራት መከላከል ነው፡፡ አንዴ የተፈጠረ የድምጽ ብክለት እንዲቀጥል የሚደረገበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ተከራካሪ ወገኖች የጠቀሱትን ድንጋጌ ብቻ በመያዝ ለፍሬ ጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ በመያዝ ውሳኔ መስጠት የዳኝነት አካሄድ የሚፈቅደው አይደለም፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመለየት ዳኝነት መስጠት የፍርድ ቤት የእለት ተእለት የስራ ድርሻ እንጂ የተከራካሪ ወገኖች አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ የጉዳዩ ይዘት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1225 እና 1226 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን የሚመለከት ሆኖ እያለ በይዞታ ላይ ሁከት ሲፈጠር የይርጋ ጊዜን የሚመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡

2ኛ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው ተጠሪ ስለንግድ ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ በወጣው አዋጅ መሰረት መሟላት ያለባቸው ነገሮች ሲሟሉ ፈቃድ የመስጠት በኋላም ጉድለት ካገኘ የማገድና የመሰረዝ ሥልጣን አለው እንጂ የከተማውን የቦታና መሬት አጠቃቀም የመወሰን ሥልጣን የለውም በሚል ምክንያት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የስር ፍርድ ቤት ይርጋን አስመልክቶ የሰጠውን ውሳኔ ስህተት ነው የሚሉበትን ምክንያት ከመዘርዘር ውጪ 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ቅሬታቸውን አልዘረዘሩም፡፡ በሌላ በኩል ይህ ችሎት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/89 ሲመለከተው የንግድ ፈቃዱን የተሰጠው ሰው በሌላ ሰው ላይ በስራ በሚፈጥረው ረብሻ የንግድ ፈቃድ የሰጠው አካል ሊሰርዘው የሚገባ ስለመሆኑ የማይደነግግ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 10 ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ቁጥር 12960 ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69348 ኀዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. የአመልካች ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበት ምክንያት ስለሌለ 1ኛ ተጠሪ በሚሰሩት የብየዳ ሥራ የሚሰማው ድምጽ ከመጠን በማለፍ ወደ አመልካች መኖሪያ ዘልቆ ሁከት የሚፈጥር መሆን ያለመሆን፣ለመከላከል ያደረጉት ነገር መኖር ያለመኖሩን፣ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1225 ድንጋጌ አኳያ በመመልከት ጉዳዩ ላይ ተገቢው ውሳኔ እዲሰጥበት ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. 2ኛውን ተጠሪ በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57044

ጥር 25 ቀን 2003 ዓ/ም

**ዳኞች** ፡- ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- 1. የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07/14 አስተዳደር ፅ/ቤት ነ/ፈጅ ሠይፉ ግርማ ቀረቡ

2. በልደታ ክ/ከተማ የመሬት ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና ይዞታ አስተዳደር ፅ/ቤት ነ/ፈጅ ሠይፉ ግርማ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ታሪኩ ዑርጌሣ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በወረዳ 03 ቀበሌ 47 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ቁጥሩ 04613 የሆነ ቤት ተጠሪ በጨረታ አሸንፈው የገዙት መሆኑን፣ ቤቱ በእርጅና ምክንያት ሊፈርስ በመድረሱ በጊዜአዊነት በላሜራ እንዲያድሱ መስከረም 15 ቀን 2002 ዓ/ም የእድሳት ፈቃድ ተፈቅዶላቸው ቤቱን ሰርተው ሲጨርሱ የተሠጠው የጊዜአዊ ግንባታ ፈቃድ ከመመሪያ ውጪ ነው በማለት ግንባታውን እንዲያፈርሱ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸው ተግባሩ ሁከት በመሆኑ እንዲወገድ ዳኝነት ሊሰጥ ይገባል በማለት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የእድሳት ፈቃድ የተሰጠበት መንገድ ከሕግ ውጪ ነው በመሆኑም ግንባታው እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ ተፅፏል፣ ይህ ደግሞ ሕጋዊ ተግባር እንጂ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክራዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የግንባታ ፈቃዱ የተሰጠው ከመመሪያው ውጪና በስህተት መሆኑ ስለተረጋገጠ እና የአመልካቾች እርምጃ ሕጋዊ እንጂ ሁከት ሊባል አይችልም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የግንባታ ፈቃዱ ለተጠሪ መሰጠቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ በቅን ልቦና የገነቡት ግንባታ የሚፈርስበት ምክንያት የለም፤ የአመልካቾች ተግባር ሁከት ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር



www.chilot.me

ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም የግንባታ ፈቃዱ የተሰጠው ከመመሪያ ውጪ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአመልካቾች ተግባር ሁከት ነው ተብሎ መወሰኑ የአመልካቾችን ኃላፊነት እና ተግባር ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለተጠሪ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሕጋዊ መንገድ ባለንብረት ሁነውና ከመንግስት አካል ጊዜአዊ ፈቃድ ወስደው የገነቡት ግንባታ እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ መጻፍ ሁከት ነው ተብሎ መወሰኑ ምንም የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የተሠጣቸው ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከዓላማው ውጪ በስህተት የተሰጠ መሆኑ በሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነጥብ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት የተፃፈውን ማስጠንቀቂያ ሁከት ነው ወደሚለው ድምዳሜ ሊደርስ የቻለው ተጠሪ በተሰጣቸው ጊዜያዊ የግንባታ ፈቃድ መሰረት በቅን ልቦና ግንባታ ከአከናወኑ ለስህተቱ ኃላፊነት መውሰድ ያለበት ፈቃዱን የሰጠው አካል ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሠረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታውን ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈጸምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ንብረቱ እንዲመለስለት ሕጉ ከሚጠብቃቸው መንገዶች አንዱ አማራጭ የይዞታ ክስ ማቅረብ (Possessory Action) ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1149(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ መቅረብ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረው ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም አይነት መብት በሌለው ሰው ላይ ስለመሆኑም የድንጋጌው መንፈስ ያስረዳል፡፡ የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅራቢ በማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ንብረቱ በይዞታው ስር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጢር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው፡፡ የሁከት ተግባር የሚኖረው ባለይዞታ የሆነ ሰው በይዞታው ስር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ሲሆንበት ወይም ረብሻ ሲፈርጥበት ነው፡፡ እንግዲህ የሁከት መፍጠር ድርጊት ትርጓሜና ይዘቱ ከላይ የተመለከተው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እስከ 1149 ድረስ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርበው ሰው ንብረቱ በእርሱ ግልፅ ቁጥጥር ስር መሆኑንና በዚህ ንብረት እንዳይገለገልበት ተከሳሹ ረብሻ የፈጠረበት ወይም መሰናክል የሆነው ስለመሆኑ ከተከሳሽ በተሻለ ማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም፤ አንድ ባለይዞታ ይዞታውን ከሕጋዊ አካል ከወሰደ በኋላ ይዞታው የተሰጠበት አግባብ ከሕግ ውጪ መሆኑ ከተረጋገጠ ይኸው ስህተት እንዲስተካከልና ሕጋዊ



www.chilot.me

እንዲሆን ለማድረግ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ በተሳሳተ መንገድ በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅን ልቦና አድሮበት ለኪሳራ የተዳረገ ሰው ደግሞ በሕጉ አግባብ ተገቢውን ኪሳራ ለመጠየቅ ይችል ይሆናል ከሚባል በስተቀር ቀድሞ በስህተት የተሰጠ ፈቃድ ወይም ሌላ ውሳኔ ጸንቶ ሊኖር ይገባል ብሎ ሊጠይቅ የሚችልበትና ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሊቀበል የሚገባበት አግባብ አይኖርም፡፡ አንድ የአስተዳደር አካል የሰጠው ውሳኔ ወይም የወሰደው እርምጃ ሕገ ወጥ መሆኑን ከአረጋገጠ ይኸው ውሳኔ እንዲስተካከል የማድረግ ኃላፊነትና ተግባር አለውና፡፡ በመሆኑም ለተጠሪ የተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ከመመሪያው ዓላማ ውጪ መሆኑ በመረጋገጡ ይህንኑ ሕጋዊ ያልሆነ መመሪያ መሰረት በማድረግ የተሰራ ግንባታ እንዲፈርስ ለተጠሪ የተፃፈው ማስጠንቀቂያ አስተዳደራዊ ኃላፊነትንና ተግባርን ለመወጣት የተደረገ ነው ከሚባል በስተቀር የሁከት ተግባር ሊሆን የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የአመልካቾች ተግባር ሁከት ነው በማለት የከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩና የከተማው ሰበር ሰሚው ችሎትም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ማጽናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12735 መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 13339 ሚያዝያ 28 ቀን 2002 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18533 የካቲት 02 ቀን 2002 ዓ/ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካቾች በተጠሪ ላይ የፈጠሩት ሁከት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54121

ህዳር 01 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች** ፡- ሲ.ኤ.ኤስ - ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ሳልዝጊተር ጂ.ኤም.ቢ.ኤች ጠበቃ ፍቃዱ ሞላ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ካሳሁን ተወልደብርሃን ጠበቃ ፈቃዱ አስፋው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክር የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ የስር ከሳሽ ክስ ይዘት ሲታይም ከአመልካች ድርጅት ጋር የመሰረቱት የቅጥር ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካቹ የስራ መሪ መሆናቸውንና የግራ ቀኙ ስምምነት ጉዳዩ በጀርመን ሕግ እንደሚዳኝ የሚገልጽ መሆኑን በመጥቀስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ዳኝነት ስልጣን የሌለው መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የስራ መሪ ስለመሆናቸው አልተረጋገጠም ብሎ ከደመደመ በኋላ በቅጥር ስምምነቱ ላይ ጉዳዩ በጀርመን ሕግ እንደሚታይ መስማማታቸውን ገልጾና የግለሰብ የአለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2/ሀ/ መሠረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው ሲል ክሱን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ አመልካችም ተጠሪ የስራ መሪ አይደሉም ተብሎ የተሰጠው ብይን ላይ መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ተጠሪ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መሆኑን፣ ተጠሪ የስራ መሪ ስለመሆናቸው ግን አለመረጋገጡን ገልጾ የስር ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341 መሠረት ተመልሶለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡



www.chilot.me

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 14 ቀን 2002ዓ.ም በፃፉት የሰበር ማመልከቻ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ ስለሆነ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልክቶ ብይን ይስጥበት ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ይኸው ትዕዛዝ በይግባኝ መሻሩ ያላግባብ መሆኑን ማስረጃ ሳይሰማ ተጠሪ የስራ መሪ አይደሉም ተብሎ መወሰኑም ተገቢነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸውም ተመርምሮ ክሱን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማየት አለበት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው መስከረም 21 ቀን 2003ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ጥቅምት 15 ቀን 2003ዓ.ም የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚገዛው ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ነው ብሎ ጉዳዩን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን እንዲመለከተው መመለሱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክር ሒደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ መስከረም 20 ቀን 2001ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት መሠረት በመካከላቸው የሚነሳው አለመግባባት በጀርመን ሕግ የሚታይ መሆኑን መስማማታቸውን፣ በመካከላቸው የነበረው ግንኙነትም የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መሆኑን፣ ተጠሪ ኢትዮጵያዊ ሆነው የሚኖሩትና ስራውን ለመስራት ግዴታ የገቡት በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን፣ አመልካች የውጪ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበውና ስራውን የሚሰራው በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2/ሀ/ ስር የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ (Private International Law) የሚመለከቱ ጉዳዩች በሚኖሩ ጊዜ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ አዋጁ ይህን ድንጋጌ ሲያስቀምጥ የራሱ የሆነ ምክንያት አለው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህም መሠረት ሕግ አውጪው ይህንን ድንጋጌ ያስቀመጠው አንድም ወደ ፊት በስራ ላይ የሚውለውን የአገሪቱን የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ በሕግ አውጪው አካል ፀድቆ በስራ ላይ ሲውል በዚህ ረገድ የሚነሱ የህግ ክርክሮች የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን አይቶ እንዲወስን ወይም አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለዳኝነት በቀረበ አንድ ጉዳይ ላይ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የኢትዮጵያ ሕግ ከአመልካቹ አገር ሕግ ወይም ከሌላ አገር ሕግ ጋር ይጋጫል ወይም ይቃረናል በማለት በኢትዮጵያ ሕግ እንዳይዳኝ ወይም በራሱ ወይም በሌላ አገር ሕግ ጉዳይ እንዲታይና እንዲወሰንለት ሲያመለክት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባህርይው ከአንድ በላይ የሆኑ የሕግ ስርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ሕግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚለው ክርክር ሲነሳ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን አይቶ እንዲወሰን ከመደረጉ ውጪ በማናቸውም ሁኔታ ተከራካሪዎች የአገሪቱን ሕግ በሚፃረር መልኩ ስምምነት አድርገው ሲገኙ ሁሉ ተከራካሪ ወገን ክርክር ስላነሳ ብቻ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ከዚህ አንፃር ግራ ቀኙ አደረጉ



www.chilot.me

የተባሉትን ስምምነት ስንመለከት የኢትዮጵያ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሕግ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የሚያደርግ መሆኑ ሲታይ ስምምነቱ ተቀባይነት አለው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማ እና መንግስት አዋጁ ላይ ካለው ጠቅላላ ፍላጎት አንፃር የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የመንግስትም ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ሕግ ሲሆን ይህን አዋጅ የሚመለከቱ ስምምነቶች ሕጋዊ እና የሕዝብን ጥቅም የማይፃረሩ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የሚኒስተሮች ምክር ቤት በደንብ ካልወሰነ በስተቀር አዋጅ ቁጥር 377/96 የውጪ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ከአዋጁ ድንጋጌ 3/3/ለ/ ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የወጣ ደንብ የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግ ጥያቄን ስምምነቱን መሠረት አድርጎ ያስነሳል ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈፃሚነት እንዳለው በመግለጽ ጉዳዩን ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መመለሱ ምንም የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ የስራ መሪ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ነጥብ በሰበር ችሎት እንዲታይ በጭብጥነት ያልተያዘ በመሆኑና ከአመልካች የመልስ መልስ ክርክር ላይም ያልተነሳ በመሆኑ መመልከቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1/ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 82430 የካቲት 8 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው ብለናል፡፡

3/ ለክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሶ/በ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 66945

ሰኔ 2 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- የእንግሊዝ ህጻናት አድን ድርጅት - ጠበቃ ጥላዬ ተገኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ገአስ ኡስማን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የተጀመረ ነው፡፡ ጉዳዩ አሰሪ የሆነው የአሁን አመልካች ሰራተኛ በሆኑት በአሁን ተጠሪ ላይ የወሰደውን የስንብት እርምጃ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የተወሰደብኝ እርምጃ ህገ ወጥ በመሆኑ የተቋረጠብኝ ክፍያ ተሰጥቶኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ ሲሉ በአመልካች ላይ ክስ መስርተዋል፡፡ አመልካች ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጐ በውሣኔው ላይ ቢገለጽም ተወካዮቹ ቀርበው በጽሁፍ መልስ የሰጡ ስለመሆኑ ግን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡ የአመልካች የመከላከያ መልስ ክርክርም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስንብቱን ተገቢነት ይገልጻል የሚለውን መልስ አቅርቦ የተከራከረ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡ ክሱ የቀረበለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዞን አራት ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ መታየቱ ፍርድ ቤቱ ክሱን አዛውሮ ከማየት ስልጣኑ አንጻር ተገቢ ነው የሚለውን ምክንያት በመስጠት በስልጣን ረገድ የተነሣውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከአለፈው በሁዋላ ዋናውን ጉዳይ በተመለከተም መርምሮ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች ድርጅት ተጠሪን አሰናበተ ከተባለበት ከጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም እስከ ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲሁም ከጥር 27 ቀን 2002 እስከ የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ ከቆላ አበሉ ጋር የደመወዝ ጭማሪ እንዲሁም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በመክፈል ወደ ቀድሞው የስራ መደብ እንዲመልሰው በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ የመመልከት ስልጣን የሌለው መሆኑን ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱም ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመልከቱም ሆነ ጉዳዩን የመራበት ስርዓት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው

ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የጽሁፍ መልስ የሰጡ ሲሆን በመልሣቸው ላይም የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ይህም ችሎት በቅድሚያ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው አቢይ የህግ ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዋነኛነት ሊፈታ የሚገባው የነገሩ ጭብጥ፡-

የአሰሪና ሰራተኛን ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት አድርጐ የሚነሣውን የግል የስራ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ በማየት የመዳኘት ስልጣን የማነው? የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው? ወይስ የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት? የሚለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ የማግኘቱ ጉዳይ ስለ ስራ ክርክር ስለ ቦርድና ስለ ፍርድ ቤት ስልጣን የሚገልጹትን የአዋጅ ቁ. 377/96 ድንጋጌዎችን ተመስርቶ ጭብጡን መመርመርን ይጠይቃል፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 ከአዋጅ ቁ. 25/1988 በኋላ የወጣ ሲሆን በአንቀጽ 136/3/ ስለ ስራ ክርክር ምንነት ትርጓሜ የሚሰጥ ድንጋጌ ከመያዙም በላይ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 147 ስለቦርድ ስልጣን የሚደነግገው ሲሆን የፍ/ቤት ስልጣንን ደግሞ የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 138/2/ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 138/1/ የተዘረዘሩትንና መሰል የግል የስራ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን ለፍ/ቤት መስጠቱን ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ አዋጁ የስራ ክርክርን የክልልና የፌዴራል ጉዳይ ነው የሚል መለኪያ በመስጠት የስነ-ነገር የዳኝነት ስልጣን መከፋፈሉን በግልጽ አያሣይም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 322/95 "ም" ሆነ በህገ መንግስቱ መሠረት የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስራ ክርክርን አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በውክልና ሊመለከት ይችላል የሚባልበት አግባብም የለም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 138/1/ ድንጋጌ መሠረት ለፍ/ቤት የሰጡትን የስራ ክርክሮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 139/1/ /ሀ/ ደግሞ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በስራ ክርክር ችሎት የተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የይግባኝ ስልጣን እንዳለው ያሣያል፡ በመሆኑም የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138 መሠረት በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚታዩት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ስልጣን ያለው መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 139/1/ሀ/ በግልጽ ያሣያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የስራ ውል ከህግ ውጭ የተቋረጠ ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ቀድሞው ስራ እንዲመለስ ፣ ጭማሪ ደመወዝ እንዲከፈለኝ ፣ የቆላ አበል እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች እንዲከፈሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን በይዘቱ በአዋጅ አንቀጽ 138/1/ለ/ መሠረት የሚታይ የግል የስራ ክርክር ሁኖ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ለክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት በአንቀጽ 139/1ሀ/ መሠረት አቅርቦ የሚያሣይበት ጉዳይ ነው፡፡ የአፋር ክልል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሊመለከት የቻለው ጉዳዩን ለማየት ስልጣኑ በህጉ በግልጽ ተሰጥቶኛል በሚል ምክንያት ሣይሆን የክስ መዛወር ጥያቄ ሲቀርብ ለማስተናገድ የምችለው እኔ ነኝ በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችለናል፡፡ ይሁን እንጂ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ /Change of Venue/ የሚስተናገድበትን አግባብ ህጉ የዘረጋው ስርዓት ያለ ሲሆን የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለብይኑ ዋቢ ያደረገው በ1958ቱ የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 31 ስር የተመለከተው አንዱ ሲሆን ከዚህ ህግ በሁዋላ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች የወጡት የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆችም ተመሣሣይ ይዘት ያለውን ድንጋጌ ስራ ላይ አውለው ይገኛሉ፡፡ አንድ ክስ ወደ ሌላ ስፍራ ሊዛወር



www.chilot.me

የሚችልበትን አግባብ ከሚደነግጉት የስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ጥያቄው ከተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ መሆኑና ህጋዊ ምክንያቶች ተብለው በህጉ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ መሟላት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን የአፋር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ወደራሱ ያዞረው በተከራካሪ ወገኖች የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ቀርቦለትና በህጉ ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎችም ተሟልተው ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሣይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ወደ ራሱ አዙሮ የተመለከተው ህጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ አይደለም ፣ በውጤቱም በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ እንዲመለከተው በህጉ ያልተሰጠውን ስልጣን በመውሰድ ጉዳዩን በማየት በህጉ ጥበቃ ያገኘነው የተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብት ያጣበበ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዞን አራት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00126 የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ሊታይ የሚገባው በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሊታይ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት/አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሣቸውን ይቻሉ ብልናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 65688

ሐምሌ 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** :- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ- - አቶ እሸቱ በቀለ /ነገረ ፈጅ/ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** :- አቶ ንጉሴ በያን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለባንክ ብድር መያዣ የሠጠበት የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣው ከመያዙ በፊት በሽያጭ ለሶስተኛ ወገን ተላልፎና ስመ ሀብቱም ከመያዣው በኋላ ለገዥው ዙሮ ሲገኝ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻና ይዘትም የሚከተለው ነው፡፡ አመልካች ለአቶ አያሌው መንገሻ የሠጠውን ብድር ተበዳሪው ባለመመሰሉ ምክንያት እና ተበዳሪው በውሉ መሰረት የወሰደውን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ክስ አቅርቦባቸው ውሳኔ እንዳገኘ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጸምለት ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርቦ በቅድሚያ በዋስትና የተያዘ ቤት በአገምሳ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 026 እና 96 የሆነ ተገምቶ በጨረታ በሐራጅ እንዲሸጥ አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም ቤቶቹ በሐራጅ እንዲሸጡ ትእዛዝ ሰጥቶ ከተሸጡ በሁዋላ የአሁኑ ተጠሪ ይህ ቤት አመልካች በዋስትና ከመያዙ በፊት በውል ስምምነት ገዝቼ የንብረት ባለቤትነት ስም ወደ ስሜ ተዛውሮ የሚገኝ መሆኑን ገልፀው የሐራጅ ሽያጩ ውድቅ እንዲሆንላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ቤቱ በሽያጭ ስምምነት ለተጠሪ መዛወሩና ስም በተዛወረበት ወቅትም የአሁኑ አመልካች ያቀረበው ወይም ያነሳው ተቃውሞ የለም በሚል ምክንያት የሐራጅ ሽያጩን ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ አከራካሪው ቤት በ10/10/1988 ዓ/ም በዋስትና መያዙ ተረጋግጧል፣ ስመ ሀብቱ ለተጠሪ የዞረውም በ1992 ዓ/ም ውስጥ ነው የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3059(1) ድንጋጌ የቅድሚያ መብት አለው በማለት ሽያጩ ሊቀጥል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ተጠሪ ቤቱን በ01/10/1988 ዓ/ም ገዝተው ሲገዙ ከነበረበት ከአስር ቆርቆሮ ወደ አንድ መቶ ቆርቆሮ በማሳደግ ግንባታ ያከናወኑ መሆኑ መረጋገጡን፣ ስመ ሃብቱ ሲዞርም በቤቱ ላይ እዳና እገዳ የሌለው መሆኑን

የሚመለከተው ቀበሌ አስተዳደር መገለጹን እንዲሁም ተጠሪ ቤቱን የገዙት ከባለእዳው ጋር ተመሳጥረው ለማሸሽ ነው አለመባሉን በምክንያትነት ይዞ ቤቱ ከተሸጠ በኋላ በመያዣነት ተይዞ ብድር በባለእዳው መወሰዱን ከክርክሩ ሂደት መገንዘቡን ጠቅሶ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ቤቱን በ01/10/1988 ዓ/ም ገዛሁ ቢሉም ስመ ሀብቱ የዞረው በ1992 ዓ/ም ሁኖ አመልካች ቤቱን በመያዣ የያዘው በ10/10/1988 ዓ/ም መሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች የቅድሚያ መብት የለውም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተምርምሮም ክርክር የተነሳበት ቤት ተጠሪ አመልካች በመያዣ ከመያዙ በፊት ነው የተገዛው ተብሎ ለተጠሪ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ቤቱን ገዛሁ የሚሉት ጊዜ በ01/10/1988 ዓ/ም ሁኖ ስመ ሀብቱ የዞረው በ1992 ዓ/ም መሆኑን፣ ስመ ሀብቱ ሲዞርም በቤቱ ላይ እዳና እገዳ የሌለው መሆኑን የክፍሉ ቀበሌ ማረጋገጡና ተጠሪ አስር ቆርቆሮ ቤት ገዝተው ባሁኑ ጊዜ አንድ መቶ ቆርቆሮ በማድረግ ይዘው የሚጠቀሙበት መሆኑን፣ ተጠሪ ቤቱን ይዘው ግንባታ ሲያከናውኑም አመልካች ያነሳው ተቃውሞ የሌለ ሁኖ ሽያጩን ያከናወኑትም ከባለእዳው ጋር ተመሳጥረው ስለመሆኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክርክር ያላቀረበበትና ይህንኑ የሚያሳይ ሁኔታም አለመኖሩን፣ ቤቱ እንዲታገድ በ10/10/1988 ዓ/ም ቀበሌው ሰጠ የተባለው የአመልካች የሰነድ ማስረጃም ቀበሌው በሁዋላ ስመ ሀብቱ ወደ ተጠሪ ሲዞር በቤቱ ላይ እዳና እገዳ የሌለ መሆኑን በ25/2/1992 ዓ/ም ከገለፀበት ማስረጃ አንፃር ሲታይ ተጠሪ ቤቱን እዳና እገዳ እያለ ገዝተዋል ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገርን ሲያጣራና ማስረጃን ሲመዘን ያረጋገጣቸውና ለውሳኔው መሰረት ያደረጋቸው ምክንያቶች መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በግልፅ መረዳት የሚቻለው በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ ውል በአከራካሪው ቤት ላይ አለመደረጉን ፍርድ ቤቱ ፍሬ ጉዳዩን በማጣራትና ማስረጃውን በመመዘን የደመደመው ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ አመልካች በቤቱ ላይ የመያዣ ውሉን በሕጉ አግባብ ስለማቋቋሙ ሊታመን በሚችል ማስረጃ አለማስረዳቱን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያስገነዝብ ሁኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች ቤቱን በመያዣነት የያዘው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3051(2) ድንጋጌ መሰረት በቅን ልቦና ነው ለማለት የሚያስችል ፍሬ ነገርም በክርክሩ ሂደት አለመረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ አመልካች በመያዣ ከመያዙ በፊት ነው የተገዛው ተብሎ ሐራጁ በቤቱ ሊቀጥል አይገባም ተብሎ የተወሰነው ፍሬ ነገሩና ማስረጃው ተመዝኖ በመሆኑና ይህ ፍሬ ነገርና ማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 51557 ሕዳር 24 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53551

መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የቀበሌ 10 ባለአደራ ቦርድ - ወኪል ታደሰ ሃብቴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዳንኤል አድርሴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና አመልካች የሚያስተዳድረውን የሥጋ መሸጫ ቤት ሐምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የኪራይ ውል በወር ብር 500.00(አምስት መቶ) ተከራይተው እየከፈሉ በመስራት ላይ እንዳሉ አመልካች በወቅቱ በአቢይ ጾም ምክንያት የሥጋ ቤቱ ለሁለት ወር ስለሚዘጋ ኪራይ እንዲቀንስላቸው ተጠሪ ማመልከታቸውን፣አመልካችም ይህንኑ ተቀብሎ በወር ብር 105(አንድ መቶ አምስት ብር) ቅናሽ ተደርጐላቸው እየከፈሉ ባለበት ሁኔታ ባለአደራ ኮሚቴ በአዲስ ኮሚቴ ተተክቶ ለአዲሱ ኮሚቴም ሁኔታውን ተጠሪ ገልፀው በመነጋገር ላይ እንዳሉ የተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ያልሰሩትን የኪራይ ክፍያ ከእነወጪው ብር 2010.00(ሁለት ሺህ አስር ብር) መጋቢት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የከፈሉ ቢሆንም አመልካች የኪራይ ውሉን መጋቢት 22 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በማቋረጥ ስጋ ቤቱን እንዲያስረክቡ መጠየቁን ገልጸው ድርጊቱ ሁከት ስለሆነ ሁከቱ ይወገድልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ በኪራይ ውሉም ግዴታቸውንም በወቅቱ ባለመወጣታቸው የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉን ገልፆ ሁከት ሊባል ስለማይገባ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር አመልካች ድርጊቱን የፈጸመው የኪራይ ውልን መስረት በማድረግ በመሆኑ አድራጐቱ ሁከት ነው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ አመልካች ለመክሰስም ሆነ ለመከሰስ ሕጋዊ ሰውነት የሌለው አካል ነው የሚል ምክንያት በመያዝ የበታች



www.chilot.me

ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ወኪል መጋቢት 01 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ቦርዱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ በ1988 ዓ.ም የወጣው መመሪያ የሚያሳይ ሁኖ እያለ ሕጋዊ ሰውነት የለውም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ተጠሪ ቀርበው ሚያዚያ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በጠበቃቸው አማካኝነት በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ አመልካች ሕጋዊ ሰውነት የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑና መመሪያ የሚባለውም በአመልካቹ በራሱ የወጣ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የሰበር ቅሬታው ሕጋዊ መሰረት የሌለው ስለሆነ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡፡ አመልካች በበኩሉ ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የሕግ ሰውነት የለውም ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ ባግባቡ ነውን? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም ዓላማው በ1988 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት ተዘርዝሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 361/95 በአንቀጽ 14 ስር በተመለከተው መሰረት የከተማው ምክር ቤት አዋጅ የማውጣት ስልጣን ያለው ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 10/3/ሐ/ ስር የቀበሌ ሥልጣን አካላት ስር የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ አንዱ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ የከተማው ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 14/1/ረ/ እና 66/2/ መሰረት በተሰጠው ስልጣን ክሱ ሲመሰረት ስራ ላይ የነበረውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1995 አውጥቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 ስር በቦርድ ወይም በምክር ቤት (ካውንስል) ስለሚመሩ ማዘጋጃ ቤታዊ ያልሆኑ አስፈፃሚ አካላት የሚደራጁበት ሁኔታ ተመልክቷል፡፡ ይህ አዋጅ የሻረው አዋጁን የሚቃረን ማናቸውንም አዋጅ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ ስለመሆኑ በአንቀጽ 54 ስር በግልጽ አመላክቷል፡፡ ይህም ቀድሞ በመመሪያ የተቋቋመ የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ሕልውናው እንዲያከትም የተደረገ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘትና የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ካለው አጠቃላይ ዓላማ እንዲሁም ከሚመራበት አሰራር ስንነሳ የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑን ፍርድ ቤት በራሱ ጊዜ ግንዛቤ የሚወስድበት ጉዳይ(ጉዳዩ የሕግ ጉዳይ በመሆኑ) ሆኖ አግኝተናል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ውድቅ ያደረገው አመልካች ክስ ለማቅረብ ወይም ለመክሰስ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 397 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑን ፍርድ ቤቱ የራሱን ግንዛቤ(judicial notice) የሚወስድበት ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ መርሆዎች የሚያስገነዝቡት ነጥብ እንጂ ተከራካሪ ወገን ለፍርድ ቤት ሕጉን ለማስረጃነት እንዲያቀርብ የሚገደድበት ሁኔታ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች የሕግ



www.chilot.me

ሰውነት የሌለው በመሆኑ ሊከሰስ ወይም ሊከስ የሚችል አይደለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሱትን ሕጐች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም የተጠሪን የክስ አቀራረብ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ነጥብ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ያስተላለፉት ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ በእርግጥ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ ጭብጥ መስርቶ የሰጠው ውሳኔ የለም፡፡ ነገር ግን የከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ እና ይህም የሕግ ጥያቄ ከፍትሓብሔር ሥነ ሥርአት ህጉ አላማም አንፃር በዚህ ችሎት ቢታይ ተገቢ ሁኖ በመገኘቱ ጉዳዩን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መመለሱ አስፈላጊ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ተጠሪ ክሱን የመሰረቱት አመልካች ሁከት ፈጠረብኝ፣ሊወገድልኝ ይገባል በሚል ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጠው መልስ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት የኪራይ ውልን መሰረት ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ስላልተወጡ ተገቢውን መፈጸሙን ገልጾ ተግባሩ ሁከት ሊባል የሚገባው አይደለም በሚል ተራክሮ የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ የአመልካችን ክርክር በመቀበል የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከተው አመልካችና ተጠሪ ግንኙነታቸው ውል እስከሆነ ድረስ የአመልካች ጥያቄም በውሉ መሰረት እንዲፈጸም የሚል በመሆኑ ተጠሪ የአመልካችን እርምጃ ሁከት ነው በማለት ክስ የሚመሰርቱበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140፣1148 እና 1149 ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ መብታቸውን ሊያስከብሩ፣ የሚችሉት ውላቸውን መሰረት በማድረግ እንጂ በሁከት ይወገድልኝ ክስ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ተግባር ሁከት አይደለም በሚል ምክንያት የተጠሪን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ምንም የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 08792 ታህሣሥ 02 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለመክሰስም ሆነ ለመከሰስ ሕጋዊ ሰውነት አለው ብለናል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02754 ሐምሌ 01 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመ/ቁጥር 07713 ሕዳር 09 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

ይህ ችሎት ሚያዝያ 06 ቀን 2002 ዓ.ም ሰጥቶት የነበረው እግድ ተነስቷል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ቤ/ኃ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60392

ታህሣሥ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፣** አቶ ጌትነት የኔው - ቀረቡ

**ተጠሪ፣** አቶ ኢዩብ ቢንያም ወ/ቢኒያም ዮሐንስ - ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ሁከት ይወገድልኝ ሲል አመልካች ያቀረበውን ክስ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ እንደክሱ አቀራረብ ከወሰነ በኃላ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሲል መሻሩን በመቃወም አመልካች በዚህ ሰበር እንዲታረም ስላመለከተ ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በድሬደዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱም የድሬደዋ ከተማ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ስለጉዳዩ አጣርቶ መግለጫ እንዲያቀርብ ካደረገ በኃላ በዚሁ መነሻ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ክልል ገብቶ ሁከት ፈጥሯል ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የድሬደዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ሥር ተከሣሽ /ተጠሪ/ በአከራካሪው ይዞታ ላይ የግንብ አጥር የሰራው በ1987 ዓ.ም መሆኑን አመልካች ደግሞ ክስ ያቀረበው ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን በማመልከት የአመልካች ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/2/ መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም ባሻገር በፍሬ ነገር ረገድም በይዞታ ላይ ክርክር ሲነሳ ይዞታውን በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት ባለይዞታ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1144/2/ ይደነግጋል በማለት ይዞታው የተጠሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በአመልካች በኩል የቀረበው የይዞታ ማረጋገጫ ውድቅ ተደርጐ ተጠሪ አከራካሪውን ቦታ ቀደም ሲል ይዞት ነበረ በሚል ይዞታው ለተጠሪ እንዲፀና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ህዳር 29 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል በይዘቱም አከራካሪው ይዞታ 52 ካ.ሜ የተባለው የአመልካች ይዞታ ሳይሆን ተጠሪ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በእጁ አድርጐ የሚያዝበት ስለመሆኑ በመጥቀስ አመልካች በይዞታው ሥር በሌላ ቦታ ሁከት ተፈጥሮብኛል በማለት ያቀረበው ክስ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡



www.chilot.me

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

አመልካች ክስ ባቀረበበት ይዞታ ላይ ባለመብት ስለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር 02473 መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ስለመሆኑ ይኸው ማስረጃ ሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ አመልካች በዚሁ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው ይዞታ ስፋት 180 ካ.ሜ ሆኖ ከዚህ ውስጥ 52 ካ.ሜ በተጠሪ የተያዘ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡

ተጠሪ ይህንን ይዞታ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ይዠዋለሁ ይበል እንጂ የቀበሌው አስተዳደር የተጠሪ ይዞታ እና የተሰራው ግንባታ ሕገወጥ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1140 እና 1144/2/ ተጠቅሶ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ሲታይ ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ይዞ በእጁ በማድረጉ ለሕገወጥ ተግባር ሕጋዊ ሽፋን እንደመስጠት ያህል መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

የፍ/ብ/ሕጉ ዓላማ በሕግ አግባብ ባለይዞታ ለሆነው ወገን ጥበቃ ለማድረግ እንጂ ሕገወጥነትን ለማበረታታት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1146/1/ እንደሚያስገነዝበን በስውር ወይም በሚያሻማ አኳኃን የተደረገው ይዞታ ማንኛውንም መብት አይሰጥም፡፡

ስለዚህም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን ለመሻር መሠረት ያደረገው የሕግ ድንጋጌ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በዚህ አከራካሪ ይዞታ ባለመብት ስለመሆኑ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም ሆኖ ክስ የመሠረተው ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑ ሲታይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/2/ መሠረት የሁለት ዓመት ጊዜ አልፎበታል የሚባልበት ሁኔታ የለም፡፡

በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ የተሻለ መብት ያለው መሆኑን ከአስተዳደር አካል የተሰጠውን የምስክር ወረቀት መሠረት አድርጐ ያቀረበው ክስ መታየት የሚገባው ይህንኑ ማስረጃ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ይዞታውን በእጁ ካደረገበት ጊዜ ሊሆን አይገባም፡፡

ባጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በአግባቡ ሳያገናዝብ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 00514/2002 ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የድሬዳዋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01098 ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገው ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ



www.chilot.me

## የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ከቅጽ 8 - 10 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

**ቅጽ - 8**

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | [illegible] |
|---|---|---|---|---|---|
| **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | | 1 |
| 1 | ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) | 33945 | አቶ ሣልህ ሁሴን እና ደግፌ ደርቤ | ጥቅምት 20/2001 | 2 |
| 2 | ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ብቻ ስለመሆኑ | 36848 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና መኰንን ግርማይ (ሦስት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 5 |
| 3 | በክርክር ሂደት ተቃዋሚ ወገን መጠራት ያለበት ምስክር ከመሰማቱ በፊት ስለመሆኑ | 35946 | እነ አቶ ማማሽ ወ/ስላሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 27/2001 | 7 |
| 4 | መጥሪያ ለምስክር እንዲደርስ በሚል ፍ/ቤቶች ሊልኩ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103 | 36479 | ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ ወልዱ | ጥቅምት 25/2001 | 9 |
| 5 | በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነበት ተከራካሪ ፍ/ቤት ህጉን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 | 36412 | ተስፋሁን ዋኘው እና በጃክ አግሮ ኮሜርሻል ኢንተርኘራይዝ | ጥቅምት 13/2001 | 12 |
| 6 | የቃል ክርክር ለመስማት እና የጽሁፍ መልስ ለመቀበል በሚል ፍ/ቤቶች በአንድ ቀጠሮ ሁለት ተግባራትን ለማከናወን የሚሰጡት ትዕዛዝ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ስለመሆኑ | 36380 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታረቀኝ ገ/ፃዲቅ | ጥቅምት 18/2001 | 16 |
| 7 | የበላይ ፍ/ቤቶች ውሣኔን ወደጐን በመተው በሥር ፍ/ቤቶች የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | 37725 | እነ በቀለ ድሪብሣ (ሁለት ሰዎች) እና የምክር በሪሁን | ጥቅምት 6/2001 | 18 |
| 8 | በግልፅ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ/እንዲነጥር/ ሣይደረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 37105 | ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እና ሰለሞን አበበ ኮከብ | ጥቅምት 25/2001 | 21 |
| 9 | ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል /ትተዋል/ ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢያዊ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሳቸው ስምምነት | 37678 | ድራጋዶስ ጄ ኤንድ ፒ.ጆይንት ቬንቸር እና ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር | ህዳር 18/2001 | 23 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ባደረጉ ጊዜ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 350(1) እና (2) | | | | |
| 10 | በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1), 182(2) | 37762 | ገወኔ ኢንተርፕራይዝ ኃ/ተ/የግ/ማህበር እና አቶ የሱፍ ይማም | ታህሣሥ 9/2001 | 26 |
| 11 | ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የሚጠየቁ ክፍያዎች ሳይነጣጠሉ በአንድ ላይ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4), 5 | 38601 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና ወ/ሮ ከድጃ ሳቢር | ታህሣሥ 14/2001 | 30 |
| 12 | • ክርክር ከሚካሄድበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅም እንዳለ የተረጋገጠ እንደሆነ በክርክር ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br>• በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ጥያቄ (ተቃውሞ) አለማቅረብ ሚስት/ባል የሆነን ወገን የጋራ ነው በሚለው ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያግድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 | 37742 | ወ/ሮ አልማዝ ጉንፌ ኦሪቲ<br>እና<br>ወ/ሮ ፀሐይ ሊበን | ታህሣሥ 7/2001 | 32 |
| 13 | በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ሥር የሚገኙ ሁለት ራሳቸውን የቻሉና የህግ ሰውነት ያላቸው ተቋሞች የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቁ አካላት በመሆናቸው ብቻ እንደ አንድ መቆጠር የሌለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358<br>አዋጅ ቁጥር 1/1995,18/1997,2/1995,4/2000 | 37502 | የአዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዩች ቢሮ እና እነ ወ/ሮ የኃላሸት ገመዳ ቤኛ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 2/2001 | 34 |
| 14 | ፍ/ቤቶች ለክርክር ፍትሐዊነት ተገቢ ነው ብለው ሲያምኑ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ አስቀርበው መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 145,345,327/3/ | 29861 | ወ/ሮ ህጽአት ፍስሐጽዬን እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 14/2001 | 37 |
| 15 | የክርክር ዋነኛ ጭብጥ በሆነ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሣኔ ፍ/ቤት በድጋሚ "ስህተት ለማረም" በሚል ምክንያት ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 | 37303 | ኤ.ሲ..ዲ አይ/ቮካ-ኢትዮጵያ እና እነ ሃይደር አሊ (ስምንት ሰዎች) | ጥር 26/2001 | 41 |
| 16 | ዳኝነት የሚጠየቅበት መብትና ጥቅም በግልጽ ተለይቶ ያልተመለከተበት አቤቱታ የክስ ምክንያት እንደሌለው የሚቆጠር በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33, 231 | 38419 | የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 አስ/ጽ/ቤት እና አቶ ያሲን ጀማል | የካቲት 5/2001 | 43 |
| 17 | ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ክርክር መሠረት በማድረግ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይመሰርቱ የሚሰጡት ውሣኔ ህጋዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ | 37391 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ ስዩም ማሞ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 3/2001 | 46 |
| 18 | በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች በሚሰጠው ውሣኔ ጥቅማቸው /መብታቸው/ ሊነካ የሚችል የሆነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.40 | 39540 | ናስ ፉድስ የድ/ዳ/ጨ/ጨ/ፋብሪካ ተከራይ እና<br>እነ ስንዱ ደጀኔ (ዘጠና ሦስት ሰዎች) | የካቲት 26/2001 | 48 |
| 19 | አንድ ጉዳይ ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው | | ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ | መጋቢት | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 | 36780 | እና አቶ ገ/ኪዳን እንግዳ | 3/2001 | 51 |
| 20 | ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሣ ክርክርን የክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት የሚገኘው ወይም ውል የተደረገው በአንደኛው ክልል እንኳን ቢሆን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2) | 36460 | መሐመድ ሰዓዳይ ረጃ እና እነ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፈረጀ (ሰባት ሰዎች) | መጋቢት 24/2001 | 59 |
| 21 | በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀን ዳኝነት አስመልክቶ ግልጽ ፍርድ አለመስጠት ስህተት ስለመሆኑ | 39144 | አቶ ልዑልሰገድ ቦኔ እና ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 24/2001 | 62 |
| 22 | የቀረበበትን ክስ ያመነ ተከሣሽ ባመነው መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚከለክል በቂ የህግ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ | 38597 | እነ ጋሻው መንግስቴ ካሣ (ሁለት ሰዎች) እና ናይል ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 6/2001 | 65 |
| 23 | በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ተከራካሪዎች እና አንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረው እንዲታዩ ያለማድረግ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 11(5) | 40024 | ሽራተን አዲስ እና እነ አቶ እያሱ መገርሣ | ሚያዝያ 29/2001 | 67 |
| 24 | የሥር ፍ/ቤቶች የፈፀሙትን ሥህተት ለማረም በሚል በሥር ፍ/ቤት ተከራካሪ ከነበሩ ወገኖች መካከል አንዱ ወገን ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሌላኛው ወገን ሳይጠራና ሳያከራክር ውሣኔ መስጠት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) | 34504 | አቶ አበባው የሺድንበር እና አቶ ካሣ በቀለ | ሚያዝያ 6/2001 | 71 |
| 25 | በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 329(1), 182(2) | 37761 | ገብረመስቀል ንጉሴ እና አዲስ ልብስ ስፌት አ.ማ | ሚያዝያ 20/20001 | 73 |
| 26 | ክስ በሚሰማበት የቀጠሮ ዕለት የይግባኝ ባይ አለመቅረብ ጋር በተያያዘ መዝገብ ሊዘጋ የሚችለው መልስ ሰጪው ይግባኙን ሙሉ በሙሉ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ | 38181 | የኢትዮጵያ መንግዶች ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድይፍራው (ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 4/2001 | 76 |
| 27 | ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገን ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሚጠቅም ያልሆነ እንደሆነና የሰው ምስክር በተጨማሪነት የቀጠረ እንደሆነ ፍትሐዊ የሆነ ውሣኔን ለመስጠት የምስክሮችን ቃል መስማት ያለበት ስለመሆኑ | 42706 | ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ እና አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር | ግንቦት 25/2001 | 78 |
| 28 | በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መለወጥ ወይም መሻሻል ተከትሎ ማናቸውም ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚሰጥ ትዕዛዝ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ እንጂ የግድ የሚሰጥ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349(1) | 37741 | አቶ መኮንን ዘውዴ እና እነ<br>አቶ ተሾመ ሽፈራው (ሦስት ሰዎች) | ሰኔ 4/2001 | 80 |
| 29 | ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ ለማስተናገድ ስልጣን | 38452 | የአ.አ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ | ሰኔ | 82 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(2) | | እና<br>አቶ አለም ገብሩ | 11/2001 | |
| 30 | አንድን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሣት ስልጣን የለኝም ያለ ፍ/ቤት ጉዳዩ በበላይ ፍ/ቤት ታይቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ እንዲያከራክር ጉዳዩ የተመለሰለት እንደሆነ ሌላ ተጨማሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለማየት አልችልም ማለት የማይገባው ስለመሆኑ | 39014 | አለሙ መግራ<br>እና<br>እምነቱ እንዳሻው ህንፃ ተቋራጭ | ሰኔ<br>23/2001 | 84 |
| 31 | የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት ተከራካሪ ወገን የሚያቀርበው የማስፈቀጃ ማመልከቻ በበቂ ምክንያት የተደገፈ መሆን/አለመሆኑን ፍ/ቤቶች በጥሞና መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326(1) | 38145 | ወ/ሮ አያልነሽ ዘገየ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ደምሴ | ሰኔ<br>30/2001 | 86 |
| 32 | አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች (የሙያ) ማስረጃው በፍ/ቤቱ በኩል በጭብጥነት ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት ያለው እና በህግ ተቀባይነት ያለው እስከሆነ ድረስ ቀርቦ መሰማት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111, 249 እና 257 | 38683 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ሣህሉ ወ/ማርያም | ሰኔ<br>25/2001 | 88 |
| 33 | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ሳይመረምሩ እና ለውሣኔያቸው በቂ ምክንያት ሣይሰጡ መሻር የማይችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1) | 38844 | የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን<br>እና<br>ጋድ ቢዝነስ<br>ኃ/የተ/የግ/ማህ | ሰኔ<br>25/2001 | 90 |
| 34 | ተከራካሪ ወገኖች በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብላቸው የሚጠይቁት ማስረጃ የተያዘውን ጉዳይ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ዕልባት ለመስጠት የሚያስችል እስከ ሆነ ድረስ ጥያቄውን ፍ/ቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ስለመሆኑ | 36979 | ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ሚስተር ሽሬሣሪ ብራማሻሪ ጉፓል | ሐምሌ<br>23/2001 | 94 |
| 35 | ሦስተኛ ወገኖች በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር እንዲገቡ የሚያስፈልግበት ሁኔታ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 | 41544 | ሰላም የህዝብ ማመላለሻ (አ.ማ) እና<br>ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ | ሐምሌ<br>8/2001 | 96 |
| | **አሰሪና ሰራተኛ** | | | | 98 |
| 36 | የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀፅ 2/ሰ/ | 35197 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ<br>እና ኤፍሬም ንዋየማሪያም | ጥቅምት<br>13/2001 | 99 |
| 37 | ለፕሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች የተቀጠሩበት የፕሮጀክት ሥራ ሲጠናቀቅ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥ ስለመሆኑ | 35621 | ሰንሻይን ኮንስትራክሽን እና እነ አቶ ፍቃዱ ገቢሣ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት<br>11/2001 | 102 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10/1//ሠ//ሀ/ | | | | |
| 38 | በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 ባልተሸፈነ ጉዳይ ላይ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል የተደረገ የህብረት ስምምነት መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ | 36692 | አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እና ተስፋዬ መኰንን | ጥቅምት 25/2001 | 104 |
| 39 | ሠራተኞች ለሚፈፅሙት ጥፋት በህብረት ስምምነት የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡ በሆነ ጊዜ አሰሪው በሠራተኛው የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት መወሰን የሚችል ስለመሆኑ | 37027 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት አሰለፈች ደስታ | ጥቅምት 11/2001 | 106 |
| 40 | አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በህግ ከተደነገገው ማዕቀፍ ሳይወጣ/ሳይጥስ/ የሥራ ሰዓቱን ማሻሻል ስለመቻሉ<br>አዋጅ 377/96 አንቀፅ 61/1/ | 36518 | ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ እና እነ ሳሙኤል ተፈራ (አራት ሰዎች) | ጥቅምት 4/2001 | 108 |
| 41 | የአሰሪ ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደል ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1/ተ/ | 35484 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና አቶ ደረጀ ማሞ | ህዳር 25/2001 | 110 |
| 42 | አሰሪ ሠራተኛውን በሣምንት ዕረፍቱ ሥራ እንዲሰራ ለማድረግ የሚችል ስለመሆኑ | 37815 | አለማየሁ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ እና አቶ አብዮት በፈቃዱ | ህዳር 2/2001 | 112 |
| 43 | በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ “የሥራ ቀናት” የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(3) | 36377 | የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና ተሾመ ኩማ | ህዳር 2/2001 | 114 |
| 44 | የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም/ እና የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ | 37048 | የሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሣህሉ ምትኩ | ህዳር 2/2001 | 116 |
| 45 | በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ መውጣት በራሱ አንድን ሠራተኛ ወደ ቀድሞ ሥራ ለመመለስ መብት የሚሰጥ ስላለመሆኑ | 37256 | አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አስተዳደር እና ወ/ሮ የውብዳር ጥላሁን | ህዳር 4/2001 | 119 |
| 46 | ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሥራ ገበታ ላይ ያለበቂ ምክንያት አለመገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ | 37402 | የንኮማድ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ቡሽራ በቀለ | ህዳር 11/2001 | 122 |
| 47 | ከሥራ ጋር በተገናኘ በሚፈፀም ድርጊት መነሻነት በሠራተኛው ላይ በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ | 37573 | የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ መሐመድ አደን | ህዳር 16/2001 | 125 |
| 48 | የሥራ ውል በስምምነት ተቋረጠ ለማለት የሚቻለው ስምምነቱ በፅሁፍ የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ | 37575 | ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ እና ብርሃኑ ልደት ወልዴ | ህዳር 2/2001 | 127 |
| 49 | በአሰሪ በተደረገ የሥራ ዝውውር ቅሬታ አድሮብኛል በሚል ምክንያት ከሥራ መቅረት የህግ ድጋፍ የሌለው ስለመሆኑ | 37778 | አዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪ አከፋፋይ አ.ማ እና አቶ ካሣሁን ከበደ | ህዳር 4/2001 | 129 |
| 50 | በአሰሪና በሠራተኛ መካከል የሥራ ውል ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻልበት አግባብ | 03171 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፓሬሽን እና ወ/ት ትርሲት ደገፋ | ህዳር 16/2001 | 132 |
| 51 | አዲስ መዋቅርን ተግባራዊ ያደረገ | 36210 | አቃቂ መለዋወጫ | ህዳር | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተቋም/ድርጅት/ ሠራተኞቹን “ራሱ ባወጣው መስፈርት” መሰረት ሊመድብ ስለመቻሉ | | ዕቃዎችና መሣሪያዎች አ.ማ እና አቶ ኃይለ ሳልቫቶር | 2/2001 | 136 |
| 52 | • አንድ ሠራተኛ በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበት የሚችልበት አግባብ<br>• በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ “የአሰሪ ንብረት” በሚል የተገለፀው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1//ሽ/ | 34669 | አድማስ ኮሌጅ እና ሠለሞን ሙሉአለም | ታህሣሥ 2/2001 | 138 |
| 53 | የተረከበው የአሠሪ ንብረት የጠፋበት ሰራተኛ ንብረቱን ለግል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ያዋለው ያለመሆኑን ካላስረዳ በቀር የንብረቱ መጥፋት ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)(ቀ) 14(2)(ለ)(2) | 39118 | ደሣለኝና ቤተሰቡ ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ በፈቃዱ በላይ | ታህሣሥ 23/2001 | 141 |
| 54 | በህብረት ስምምነት ወይም በሌላ አካኋን የተወሰነ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ምክንያት ካለ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ያልተመለከተ ቢሆንም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 3787/96 አንቀፅ 27/1/ | 36591 | ማታዶር አዲስ ጎማ አ.ማ እና ደረጀ ኡመታ | ታህሳስ 14/2001 | 144 |
| 55 | የሥራ መሪ በሆነ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት መስራት ግለሰቡን የሥራ መሪ ከመሆን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 3/2/ /ሐ/ | 36894 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሙላት ታረቀኝ | ታህሳስ 30/2001 | 146 |
| 56 | ለተወሰነ ጊዜ በተደረገ የሥራ ውል ግንኙነት ለሠራተኛው የሚከፈል የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ የሚፈፀም ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 35/2/ | 37201 | ማታዶር አደስ ጎማ አክሲዮን ማህበር እና እነ አቶ ኤልያስ በቀለ (አስራ አራት ሰዎች) | ታህሣሥ 30/2001 | 148 |
| 57 | የጥበቃ ሥራን የሚሠራ ሠራተኛን በተመለከተ የሥራ ውሉ ያለአግባብ ተቋርጧል በሚል ሲወሰን በአሠሪውና ሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚገባው ከፍተኛ መተማመን የሚሻክር በመሆኑ ሰራተኛው ወደ ሥራ እንዲመለስ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43 | 37454 | ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል እና ከበደ ሰይፉ | ታህሣሥ 16/2001 | 151 |
| 58 | ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ የሥራ ክርክሮችን የሚወስነው አካል ሠራተኛው አግባብነት ያላቸውን ክፍያዎች ተከፍሎት ከሥራ እንዲሰናበት ሊወሰን የሚችለው በመጀመሪያው ፍርድ መሠረት ያልተፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/ | 38255 | አበባ ትራንስፖ'ርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አለምሰገድ ኃይሉ | ታህሣሥ 23/2001 | 154 |
| 59 | የሥራ ውሉን በፍቃዱ የቋረጠ ሠራተኛ የህብረት ስምምነት የሚፈቅድለት ከሆነ | 37551 | አቶ ድካምየለህ ጥበቡ እና አርሾ የህክምና | ታህሣስ 9/2001 | 157 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፕሮቪደንት ፈንድና የሥራ ስንብት የማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ | | ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር | | |
| 60 | የስራ ውል የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው ተብሎ በተወሰነ ጊዜ የስራ ውሉ የተቋረጠበት ወገን/ሠራተኛ/ ሊወሰኑለት የሚገቡ ክፍያዎች | 34476 | ኩመላ በጅሣ እና ብሔራዊ አስጐብኚና ጉዞ ወኪል | ታህሳስ 2/2001 | 160 |
| 61 | አንድ የሥራ ዘርፍ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም በዚሁ ዘርፍ ሠራተኞችን ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ቀጥሮ ሊያሰራ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሐ) | 40305 | የኢትዮጵያ ፐልኘና ወረቀት አ.ማ<br>እና<br>እነ አቶ ታመነ ጫላ | ታህሣሥ 21/2001 | 163 |
| 62 | አንድ ሠራተኛ ይሰራው የነበረ የሥራ መደብ መሰረዝ ወይም አለመኖር ለሥራ ውሉ መቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1) (መ) | 40804 | ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና እነ ተክሉ ኡርጌ ኢደኤ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 26/2001 | 165 |
| 63 | አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ሲሄድና ከሥራ ወጥቶ ወደቤቱ ሲመለስ አሰሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሰበት መሆኑ ከተረጋገጠ ሦስተኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖር አሰሪው የጉዳት ካሣ ላለመክፈል እንደመከላከያ ሊሆነው ስላለመቻሉ እና የጉዳት ካሣው በጉዳት የተነሣ ህይወቱን ላጣው ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፈልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 95/2/, 96/1/, 98/2/, 97/1/, 107/1//ሐ/, 110/ 112 | 36194 | ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቴ<br>እና<br>ፍሬድሪክ ኤቨርት ሲቲፍቱንግ | ጥር 28/2001 | 167 |
| 64 | በድርጅት ውስጥ በተደረገ የመዋቅር ማሻሻያ የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ የሥራ መደብ የተሰረዘበትን ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1)(መ) | 38811 | ርሆቦት ሆሊ ሴቪየር ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ አማረ አድማሱ | የካቲት 17/2001 | 173 |
| 65 | በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ በሌላ 3ኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የስራ ውል ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28 | 38435 | ኤስ.ኦ.ኤስ የህፃናት መንደር እና እነ አቶ ከበደ ኩምሣ (ስድስት ሰዎች ) | የካቲት 17/2001 | 175 |
| 66 | ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል የሚቋረጠው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስለመሆኑ | 38023 | የመንግስት ቤቶች ኤጅንሲ እና ብርሃኑ ደስዬ | የካቲት 17/2001 | 178 |
| 67 | በአሰሪያቸው ላይ ክስ አቅርበው ያስፈረዱ ሠራተኞች የአሰሪውን ንብረት በዋስትና ከያዙ ባለገንዘቦች ይልቅ የቅድሚያ ክፍያ መብት ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 167<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀጽ 2857(1)<br>አዋጅ ቁ. 186/94 አንቀጽ 80<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ- መንግስት አንቀፅ 13(2) | 40921 | አቢሲንያ ባንክ (አ.ማ)<br>እና<br>አብዱ አህመድ (ሁለት መቶ ስልሣ ስድስት ሰዎች) | የካቲት 26/2001 | 180 |
| 68 | የአንድ ሠራተኛን ድርጊት ከባድ ቸልተኝነት ነው ለማለት የሥራውን ባህሪ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ | 41115 | ሜድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ሞገስ ሽፈራው | የካቲት 26/2001 | 183 |
| 69 | አሠሪ የአንድን ሠራተኛ ደሞዝ እና ሌሎች | | ሙገር ሲሚንቶ | መጋቢት | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጥቅማጥቅም ሣይነካ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ አዛውሮ ሊያሠራ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7) | 40938 | ኢንተርኘራይዝ<br>እና<br>አቶ ኃይሉ መንግስቱ | 24/2001 | 186 |
| 70 | አንድ ሠራተኛ የአሠሪው ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደሉ የተረጋገጠ እንደሆነ አሠሪው ሠራተኛውን በፍ/ብሔር ክሶ ገንዘቡን የማስመለሱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ) | 42292 | የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ከበደ አቡነቴ | መጋቢት 24/2001 | 188 |
| 71 | በአሠሪው ወደሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሠራ የተደረገ ሠራተኛ ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወም የተዛወረበት የሥራ ገበታ ላይ ለ5 ተከታታይ ቀናት የቀረ እንደሆነ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27 (1)(ለ) | 41623 | አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ሣሙኤል ኪዳኔ | መጋቢት 8/2001 | 191 |
| 72 | • ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛን ከሥራ የማገድ ተግባር ሠራተኛን እንደማሰናበት የማይቆጠር ስለመሆኑ<br>• አሠሪው ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛው ለታገደበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፍል የሚደረግበት አግባብ<br>• ከሥራ ያለአግባብ ታገድኩኝ በሚል የቀረበን ክስ በማስተናገድ ላይ ያለ ፍ/ቤት በክርክሩ ሂደት ሠራተኛው ከሥራ የተሰናበተ መሆኑን ካወቀ የተያዘው ጭብጥ እንዲሻሻል እና ጭብጡ እንዲስተካከል በማድረግ ጉዳዩን ማየት ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(4) | 41411 | ሙሉሙል ዳቦ መጋገሪያ ድርጅት<br>እና<br>አቶ በለጠ ተገኝ | ግንቦት 11/2001 | 193 |
| 73 | • አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ከጉዳቱ በኋላ የቀድሞ ስራውን መስራት መቀጠሉ ብቻ አሰሪውን የጉዳት ካሣ ከመክፈል ነፃ የማያወጣው ስለመሆኑ<br>• በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተገናኘ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ውስጥ የተመለከተውና "የመስራት ችሎታ" የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ እና የጉዳት ካሣ መጠንና ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 109, (1) እና (3) , 107, 99(1), 102(3)<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 33 | 43370 | የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ጌታቸው ገድሌ | ግንቦት 12/2001 | 196 |
| 74 | • የድርጅት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሠራተኛ ቅነሣ የሚደረግበት አግባብ<br>• ቅነሣ የሚደረግበትና ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ | 42752 | እነ ወ/ት ማሚ አሠፋ (ሰላሳ ስድስት ሰዎች)<br>እና<br>ብሔራዊ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል(NTO) | ግንቦት 12/2001 | 199 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ), 29(3) | | | | |
| 75 | በሠራተኛ እጅ የሚገኙ የአሠሪ ንብረቶች መመለስ ወይም አለመመለስ ጉዳይ ሠራተኛው የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚያነሣቸውን ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለማስተናገድ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 36, 38 | 39464 | ሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ አብዱልቃድር አብዱረዛቅ | ግንቦት 25/2001 | 202 |
| 76 | ቀድሞ ይሰራበት የነበረን የሥራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ሠራተኞችን በማሰናበት ፋንታ በክፍያ አነስተኛ ወደሆነ ሌላ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ያደረገ አሠሪ ለሠራተኞቹ በቀድሞው ደመወዝ መሠረት እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 41786 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ አቶ አሰፋ አቤቦ (ሦስት ሰዎች) | ግንቦት 26/2001 | 204 |
| 77 | በጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ እንዲጠብቅ የተሰጠው የአሰሪ ንብረት የጠፋ እንደሆነ ሰራተኛው ለንብረቱ መጥፋት አስተዋጽኦ ያለማድረጉን ማረጋገጥ ካልተቻለ በስተቀር በሃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ | 39650 | የየረር በር ምስራቅ ፀሐይ ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክ እና እነ ቄስ ሰፊነው ደሣለኝ | ግንቦት 27/2001 | 207 |
| 78 | በተጭበረበረ ማስረጃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የማጭበርበር ድርጊቱ የታወቀ/የተደረሰበት/ ከሆነ ማጭበርበሩ የተከሰተው ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ተቆጥሮ ሊያስናብተው የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1) (ሐ) | 39543 | የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ በረከት ተ/ማርያም | ግንቦት 4/2001 | 209 |
| 79 | ለፕሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቅነሣ በሚካሄድበት ወቅት አሰሪው በአዋጅ ቁ.377/96 ላይ የተመለከተውን የሠራተኞች ቅነሣ ሥነ-ሥርዓት መከተል የማይጠበቅበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30(1) | 39042 | ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ጀማል መሐመድ | ግንቦት 26/2001 | 211 |
| 80 | የሥራ መደብ ዝውውርን በመቃወም ቅሬታን በማሰማት ላይ መሆን በስራ ቦታ ላይ ላለመገኘት እንደ በቂ ህጋዊ ምክንያት የሚወሰድ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) | 38189 | ሮፖክ ኢንተርናሽናል ኃላ/የተ/የግል ማህበር<br>እና ይደርሳል አእምሮ | ግንቦት 27/2001 | 213 |
| 81 | አሠሪ የሥራ መሪ የሆነን ሠራተኛውን ያሰናበተው ያለበቂ ምክንያት ቢሆንም እንኳን ተገቢ የሆነ ካሣ ለመክፈል ከሚገደድ በስተቀር ሠራተኛውን ወደ ሥራ እንዲመልስ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ | 37982 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ታደሰ ዘነበ | ሰኔ 16/2001 | 216 |
| 82 | ለሥራ ማስኬጃነት የተቀበሉትን የአሰሪ ገንዘብ አጉድሎ መገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ) | 41720 | የእንጨት መሠንጠቂያና መገጣጠሚያ ድርጅት<br>እና<br>ረዲ እንዳለ | ሰኔ 9/2001 | 219 |
| 83 | የሥራ ውል የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ | 39861 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ሣምሶን በለጥካቸው | ሰኔ 18/2001 | 221 |
| 84 | በቃል ከሥራ ተሰናበትኩ በሚል ክስ | 43610 | ናይኮ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር | ሐምሌ | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚያቀርብ ሠራተኛ አሰሪው ከሥራ ያሰናበተው ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ | | እና አቶ ሰለሞን ተሰማ | 21/2001 | 224 |
| 85 | አሠሪ የሆነ ወገን የሥራ ቅልጥፍናን፣ ውጤታማነትን፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድን ሠራተኛ የተቀጠረበትን ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በጠበቀ ሁኔታ አዛውሮ ለማሰራት የሚችል ስለመ ሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2 (1), 4 | 44033 | መንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት<br>እና አቶ ይበልጣል አጥናፉ | ሐምሌ 22/2001 | 226 |
| 86 | በህግ ወይም በሕብረት ሥምምነት የተመለከተው የጡረታ እድሜ ሣይደርስ በመንግሥት መመሪያ በጡረታ እንዲገለሉ የተደረጉ ሠራተኞችን በተመለከተ አሰሪ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ | 42906 | የኢትዮ-ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ<br>እና እነ ትዕግስት ማሞ (ሰማንያ አንድ ሰዎች) | ሐምሌ 21/2001 | 228 |
| 87 | የኮንስትራክሽን ሥራ የሚሰራ ድርጅት የሥራው መጠን በቀነሰ ጊዜ ሠራተኞችን ለማሰናበት የማስጠንቀቂያና ሌሎች የቅነሳ ሥነ-ሥርዓቶችን ሳይከተል ቅነሳ ለማካሄድ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30 | 42075 | አፍሪካዊት የህንፃ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ አቶ እንድሪስ ዓሊ | ሐምሌ 16/2001 | 231 |
| 88 | የሥራ ውል □ንደተቋረጠ የጡረታ አበል ለማግኘት መብት ያለው ሠራተኛ የሥራ ስንብት የማይከፈለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2) (ሰ) | 39808 | ናዝሬት ሣሙና ፋብሪካ<br>እና<br>ዘውዴ ኃ/ማርያም | ሐምሌ 21/2001 | 233 |
| 89 | የሥራ መሪ ከሠራተኛ ሊለይ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3, አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2 | 42901 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና ወ/ሮ ንግስት ለጥይበሉ | ሐምሌ 21/2001 | 235 |
| 90 | በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በሚካሄድ የሥራ ክርክር የሚያዘው ጭብጥ አሰሪው ገንዘብ ይከፈለኝ በሚል በሠራተኛው ላይ ክስ ባቀረበ ጊዜ ከሚያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ | 39471 | ኤርሚያስ ሙሉጌታ እና በከልቻ ትራንስፓርት አ/ማ | ሐምሌ 29/2001 | 237 |
| 91 | በሃይማኖት ተቋም ውስጥ መንፈሳዊ(ሃይማኖታዊ) አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ የሚሸፈን ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 18419 | ሐመረወርቅ ቅ/ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ዲያቆን ምህረት ብርሃን(ስድስት ሰዎች) | ግንቦት 4/1998 | 239 |
| | **ቤተሰብ** | | | | 242 |
| 92 | የውርስ ሀብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክስ የግዴታ ውርስ ከተጣራ በኋላ መቅረብ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) | 34703 | እንዳሻው ፍቃዱ እና እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ(ሰባት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 243 |
| 93 | ኑዛዜ ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም በሚል የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ | 36604 | ወ/ሮ ፅጌ መንግስቱ እና እነ አቶ ወንድይራድ | ጥቅምት | 245 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ኑዛዜው በተነበበ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973 | | መንግስቱ(ሁለት ሰዎች) | 25/2001 | |
| 94 | ከጋብቻ በፊት የግል የነበረን ንብረት መነሻ በማድረግ በጋብቻ ጊዜ በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 58(2), 57, 62(2) | 37275 | ሻ/ባሻ ገዛኸኝ ድልነሣው እና<br>ወ/ሮ ተዋበች ደመቀ | ጥቅምት 18/2001 | 247 |
| 95 | ግልፅ ኑዛዜ ህጋዊ እንዲሆን መሟላት ያለበት ፎርማሊቲ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 | 36777 | አቶ ወንድም አገኝ ዘውዱ እና እነ አቶ ታፈሰ ወንድአፈራሽ (ሶስት ሰዎች) | ጥቅምት 25/2001 | 251 |
| 96 | ህፃናትን ማዕከል ያደረጉ ክርክሮች የልጆችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ | 35710 | ወ/ሮ እፀገነት እሸቱ እና ወ/ሮ ሰላሚዊት ንጉሴ | ታህሣስ 16/2001 | 253 |
| 97 | የስጦታ ውል የተፈፀመው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ከሆነ ይኼው ግለሰብ እንደ ምስክር ተደርጐ ባይፃፍም ምስክር ተደርጐ ሊቆጠር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443,881,882 | 37562 | አቶ ሣሙኤል ፈረንጅ እና አቶ ግርማ ታፈሰ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 258 |
| 98 | ጋብቻ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው በህግ አግባብ ተፈፅሟል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 28(3) | 41896 | ወ/ሮ ታደለች ዋለልኝ እና እነ ወ/ሮ አዲስዓለም ፀጋ (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 26/2001 | 261 |
| 99 | የሟች እዳን ለመክፈያ በአፈፃፀም ሊያዝ የሚገባው በውርስ የተገኘውን ሀብት እንጂ የወራሾች የግል ሃብት ስላለመሆኑ | 38691 | አቶ ለገሰ ቢራቱ እና አቶ ደረጀ ጅማ ገርግሶ | የካቲት 24/2001 | 263 |
| 100 | የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት በሌለኛው ተጋቢ የተሸጠ እንደሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ውስጥ እንዲሁም በማናቸውም ሁኔታ ደግሞ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየት ስለመቻሉ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 69(2) | 38126 | ዲያቆን ኃይለጊዮርጊስ ወንድምሲያምረኝ እና እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 22/2001 | 266 |
| 101 | በኑዛዜ የተገኘ ንብረት በ10 (አሥር) ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተጠየቀ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ | 38152 | የወ/ሮ ገነት ዳምጤ ወራሾች እና እነ አቶ ይልማ አስፋው | ሚያዝያ 29/2001 | 268 |
| 102 | የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ ከመረመረ በኂላ የጉዳዩን ጭብጥ በመያዝ ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰው እንደሆነ አስቀድሞ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ፍርድ እንደሌለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ | 37313 | እነ አቶ መሐሪ ተ/ማሪያም (ሁለት ሰዎች) እና የወ/ሮ ገነት መኮንን ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 18/2001 | 271 |
| 103 | ወራሽ የሆኑ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ተገቢነት ያላቸው ማስረጃዎች በሙሉ አሰባስቦ በመስማት ያልተከናወነ የውርስ ማጣራት ሪ□ርት በህግ አግባብ የተከናወነ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241, 270 እና 345 | 42525 | እነ አቶ አብዱልዋሲቅ አርጋው እና<br>ወ/ሮ አልዋያ አባበሊስ | ግንቦት 27/2001 | 274 |
| 104 | የተናዛዡ ህጋዊ ንብረት ባልሆነ ነገር ላይ | | ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ | ሰኔ | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተደረገ ኑዛዜ በፍ/ቤት ቢፀድቅም እንኳን የኑዛዜ ሰነዱ ዋጋ የማይኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 865 | 32817 | እና እነ ወ/ሮ ቴቱ ዘውዴ(ሦስት ሰዎች) | 11/2001 | 277 |
| 105 | የገበያ ዋጋን መሠረት ያላደረገና የግንባታ ዋጋ ግምት ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚደረግ የውርስ ሀብት ክፍፍል ፍትሐዊ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ | 40510 | ቴዎድሮስ መንበሩ እና ገ/ህይወት ታደሰ | ሰኔ 23/2001 | 281 |
| 106 | ጋብቻ በሁለት የተለያዩ ሥርዓቶች የተፈፀመ ቢሆንም አንድ ጊዜ በህግ አግባብ የተደረገ ፍቺ በቂና ሙሉ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 75(ሐ) | 40781 | ፍቅረስላሴ ካህሣይ እና ወ/ሮ ሮማን ታደሠ | ሐምሌ 30/2001 | 283 |
| 107 | በውርስ ሃብት ክፍፍል ላይ ተወላጅ የሆነ ሰው ከሩብ በላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ክፍፍሉ እንዲቀር ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ. 11/22,913,1060,1037-1051,942 | 18394 | ወ/ሮ ዝናሽ በቀለ ማንደፍሮ እና ወ/ሮ ሐረገወይን በቀለ | መጋቢት 21/1999 | 286 |
| | **ውል** | | | | 290 |
| 108 | የደረሰው ወይም ይደርሣል ተብሎ የሚጠበቀው ኪሣራ በጉዳት ኪሣራ ሊካስ የሚችል በሆነ ጊዜ ውሉን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 | 35472 | አቶ መሐመድ ካሣሁን እና አቶ ሰለሐዲን ኑር | ጥቅምት 6/2001 | 291 |
| 109 | የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723"ን" መስፈርት ለላሟላም በሚል ውል እንዲፈርስ የተደረገ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1815 | 34803 | መ/ር መኳንንት ወረደ እና እነ መስከረም ዳኛው (አራት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 294 |
| 110 | ከአንቨርነት ውል ጋር በተያያዘ ለሚኖር የጉዳት ሃላፊነት ካሣ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 595, 596, 597<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 2090, 2091, 2092, 2141, 2102 | 32854 | ወ/ሪት ማርታ አድማሱ እና እነ አቶ በረከት ሰብስቤ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 20/2001 | 307 |
| 111 | የተከራዩትን ቤት ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ለውል ማፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ | 36520 | የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ይብራህ ግርማይ | ጥቅምት 27/2001 | 310 |
| 112 | መሐይምነትን ወይም ዓይነስውርነትን መሠረት በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ አቤቱታ በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719,1845 | 29363 | ወ/ሮ ወርቅነሽ አምዴ እና አቶ ጥላሁን አርምዴ | ህዳር 18/2001 | 313 |
| 113 | የማይንቀሣቀስ ንብረት የሽያጭ ውል ተደረገ የሚባለው በውል ውስጥ ያሉ ወገኖች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሽያጭ ውሉን ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ እንጂ የአስተዳደር ጉዳዩች ተጣርቶ የመስሪያ ቤቱ ማህተም ካረፈበት ቀን አንስቶ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723(1), 2015(ሀ) | 36740 | አቶ አብዱልዋሐብ ኢብራሂም እና እነ ወ/ት መሰለች ከፍያለች (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 23/2001 | 316 |
| 114 | በማኅበር በመደራጀት የተሠራ ቤትን ለሶስተኛ ወገን ከማስተላለፍ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚነሣ | 36294 | ወ/ሮ ሠናይት ገነሜ ገንታ | ህዳር | 319 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክርክርን አስመልክቶ የፍ/ብ/ሀ/ቁ 1723 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሀ/ቁ.1723 | | እና<br>እነ በቀለ ገመዳ ዳኖ<br>(ሁለት ሰዎች) | 9/2001 | |
| 115 | በአሰሪ ወይም በ3ኛ ወገን ወጪ ትምህርትን ተከታትሎ ለማገልገል በሚል የተገባን ውል (ስምምነት) የጣሰ ሰው ግዴታውን በአማራጭ ሊወጣ የሚችል ስለመሆኑ | 33473 | ወ/ሮ ሃርሴማ ሰለሞን እና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ | ህዳር 16/2001 | 322 |
| 116 | የዕቃ አስተላላፊነት ሃላፊነትና ተግባር ዕቃን የማጓጓዝና የማስረከብ ሥራን የሚያካትት ስለመሆኑ | 32571 | አቶ ሚፍታህ ከድር እና የባህር ትራንዚት አገልግሎት | ታህሣሥ 9/2001 | 326 |
| 117 | ክርክር የሚካሄድበት ጉዳይን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ የሌለ እንደሆነ ስለ ውሎች በጠቅላላ በሚለው ክፍል የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 1677፣1845 | 34940 | ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ<br>እና<br>አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዩ | ታህሣስ 28/2001 | 329 |
| 118 | • ፍ/ቤት የቀረበለትን የውል ይሰረዝልኝ፣ ጥያቄ ወደጐን በመተው የውል የፎርማሊቲን የተመለከተ ጭብጥ በማንሣትና ምክንያቱን በመለወጥ ውሣኔ መስጠት የማይገባው ስለመሆኑ<br>• በፍ/ብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ጭብጥ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ | 32299 | እነ አቶ ሰለሞን ከተማ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ሴንትራል ሼኑ /የተ/የግል ማህበር (አራት ሰዎች) | ጥር 7/2001 | 331 |
| 119 | በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161<br>የንግድ ሕግ ቁ. 124 | 34586 | አቶ አያሌው ድልነሳው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረግ<br>(አራት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 336 |
| 120 | በውል ግንኙነት ውስጥ የራስን ግዴታ ሳይወጡ ሌላው ወገን ግዴታውን አልተወጣም በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1757 | 39568 | አቶ ሸንቁጤ ተ/ማርያም እና አቶ ገብሬ ጉንጤ | መጋቢት 24/2001 | 339 |
| 121 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጐት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ያላሳወቀ እንደሆነ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት የመጠየቅ መብቱ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731(1), 1732, 1789 እና 1845 | 38935 | እነ አቶ ወልደፃዲቅ ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ስንታየሁ አያሌው | መጋቢት 3/2001 | 343 |
| 122 | በፍ/ብሔር ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846 | 36756 | አቶ ፀጋዬ ምትኩ እና እነ ወ/ሮ አበበች ምትኩ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 17/2001 | 348 |
| 123 | ለብድር በዋስትና መልክ የተሰጠን ንብረት ለተበዳሪው መመለስ ብድሩ እንደተከፈለ የሚያስቆጥር ስለመሆኑ | 41571 | ማህደር አእምሮ እና ላእከ ገ/መድህን | ሰኔ 2/2001 | 351 |
| 124 | በህግ ፊት በማይፀና ውል አማካኝነት የተሣሠሩ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ይመለሱ | 39336 | ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ | ሐምሌ | 354 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በሚል ውሣኔ መስጠት የሚቻለው መመላለሱ አንደኛውን ወገን በእጅጉ የሚጐዳ ወይም ለሌላኛው ያልተገባ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል አለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ | | እና እነ አዱኛ እጅጉ (ሁለት ሰዎች) | 7/2001 | |
| 125 | በፍ/ቤት በንብረት ላይ የሚሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ተቋቁሟል ለማለት የሚያበቃ ስለመሆኑ | 39170 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ክንዴ አፍራሶ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 357 |
| 126 | የባለዕዳውን ዕዳ ለባለገንዘብ የከፈለ ወገን በባለገንዘቡ መብቶች ላይ በመዳረግ (subrogation) ባለገንዘቡ የነበረውን መያዣን መሰረት ያደረገ የቀዳሚነት መብት ሊሰራበት የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1968 - 1974 | 39778 | ሕብረት ባንክ አ/ማ እና አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ | ሐምሌ 30/2001 | 361 |
| 127 | ፈራሽ የሆነን የስጦታ ውል ተከትለው የተሰሩ ስራዎችን ቀሪ ማድረግና ተዋዋዬችን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የሚቻለው በቅን ልቦና የተዋዋለ 3ኛ ወገን መብትን የማይጐዳ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815,1816,1817 | 41116 | ፍሌንስቶን ኢንጀነሪግ እና እነ ወ/ት ሐና ተስፋዬ (ስድስት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 368 |
| 128 | የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት እንደተሰጠ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2863 - 2874 | 39256 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ሞሣ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 371 |
| 129 | በብድር የተሰጠን ገንዘብ እጥፍ ለመቀበል በሚል የሚደረግ የብድር ስምምነት የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ | 43372 | አቶ ደረሱ አለሙ እና አቶ ሙሊሣ ወርቁ | ሐምሌ 22/2001 | 379 |
| 130 | ስልጣን ያለው የአስተደደር አካል የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነቱን አውቆለት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከሰጠው ሰው ጋር የተደረገ የንብረቱ የመያዣ ውል የተሰጠው የምስክር ወረቀት የተሰረዘ ቢሆን እንኳን መያዣ ተቀባዩ በቅንልቦና አለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የፀና ሆኖ የሚቀጥል ስለመሆኑ | 41388 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ከፍያለው ሞልቶት (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 381 |
| 131 | የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዥ ውል እንዲፈፀምለት ሻጭን የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384(ሀ), የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2892(3) | 39725 | እነ ወ/ሮ አለምሸት ካሣሁን (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ሽመልስ እንዳለ | ሐምሌ 23/2001 | 384 |
| 132 | የማይንቀሣቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረግ የስጦታ ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም በህግ የፀና ውል ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443, 881, 1723(1) | 39803 | አቶ አለኸኝ ገ/ህይወት እና እነ እማሆይ አጢነሽ በቀለ (ሦስት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 387 |
| | **አፈፃፀም** | | | | 390 |
| 133 | በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ተካሄዶ ሽያጭ | 31963 | አቶ አብዱልሐኪም | ጥቅምት | 39 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈፀመ እንደሆነ ሽያጩ ሊፈርስ የሚችለው በአሻሻጥ ሥርዓቱ የተነሣ መብት ወይም ጥቅም ያለው ሰው ላይ ቀጥተኛ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 445 | | ሁሴን እና እነ አቶ ቀነኒ ሁንዴ (ሁለት ሰዎች) | 20/2001 | 1 |
| 134 | የፍርድ ባለመብት ባለመቅረቡ የተዘጋ የአፈፃፀም መዝገብ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ10(አሥር) ዓመት ይርጋ ካልታገድ በቀር ሊንቀሳቀስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384 | 35018 | በዛብህ አበበ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥቅምት 18/2001 | 394 |
| 135 | • የፍርድ አፈፃፀም ክርክር የሚጀመረው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በፍርዱ መሰረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/<br>• የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ወይም የአፈፃፀም የውክልና ስልጣን ለተሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371,372 | 21359 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ ተገኝ ማንደፍሮ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 28/2001 | 396 |
| 136 | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥሮች 358 እና 418 ተፈፃሚ የሚሆኑበት አግባብ | 32143 | መሐመድ አስማኤል ተርቢ እና መሐመድ አህመድ ኑር | ጥቅምት 18/2001 | 400 |
| 137 | የአንድ ንብረት ወቅታዊ ዋጋ ማለት ንብረቱ ለጨረታ ሽያጭ ቀርቦ የሚያወጣው ዋጋ ስለመሆኑ | 37503 | አቶ ወልደዮሐንስ ኀብተየስ እና ወ/ሮ ያምሮት ሸዋረጋ | መጋቢት 24/2001 | 402 |
| 138 | የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ሊሸጥ የሚችልበት ሥነ- ሥርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 426,428(2) | 39175 | ወ/ሮ በለጡ ጋሼ እና እነ አንዱአለም ቴድሮስ (ሦስት ሰዎች) | መጋቢት 24/2001 | 404 |
| 139 | በቀጥታ ክስ ወቅት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት በአይነት ካልተገኘ እና የንብረቱ ዋጋ በልጦ ከተገኘ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው ንብረቱን በአይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ዋጋ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 392 | 39485 | የህፃን ሠላማዊት ቴድሮስ ሞግዚት እና መምህር ሚካኤል ግደይ | መጋቢት 17/2001 | 407 |
| 140 | በህግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የሞራል ወይም የህሊና አስተሳሰብን መሠረት በማድረግ ብቻ ዋጋ አልባ ሊደረግ የማይችል ስለመሆኑ | 38041 | ታደሠ ገ/መስቀል እና እነ ሙሉጌታ ዘካርያስ (ሰባት ሰዎች) | መጋቢት 22/2001 | 410 |



www.chilot.me

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | □ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ወንጀል** | | | | 1 |
| 1 | በወንጀል ጉዳይ የክስ ሂደት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ | 35697 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ከበደ ወርቅነህ | ጥቅምት 20/2001 | 2 |
| 2 | • በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ የተሻሻሉና የተለወጡ ሁኔታዎች ከነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ጋር በቀጥታ ተጣምረው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• በወ/ሕ/ አንቀጽ 543(3) የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት የሚከለከል ስለመሆኑ<br>የወ/ሕግ አንቀፅ 543 የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63 | 35695 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና አቶ ተመስገን አዲስ | ህዳር 11/2001 | 5 |
| 3 | በተወሰነበት ፍርድ ላይ ይግባኝ እንደሚል ፍላጐቱን አሳውቆ እያለ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት በኩል በተከሰተ መንተት የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ፍርደኛ የሚያቀርበው የማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ | 39722 | ግርማ ሃይሌ እና ዐቃቤ ህግ | ታህሣሥ 23/2001 | 7 |
| 4 | የዳኝነትን ሥራ በማከናወን ወቅት የሚፈፀሙ ስህተቶች እና ጥፋቶች ሁሉ ዳኛን በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ሊያስጠይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 214/74 | 33075 | አቶ ብርቁ ገላነው እና የአማራ ብ/ክ/መ/የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ጥር 19/2001 | 9 |
| 5 | አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉ የሚቋቋምበት ህጋዊ፣ ግዙፍዊና፣ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 | 38161 | እነ ጀሚላ መሐመድ ሐጐስ እና የፌዴራል የመ/ደ/ዐ/ህግ | የካቲት 19/2001 | 11 |
| 6 | በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ንብረት የሆነ ንግድ መደብር ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የንግድ መደብሩን በውስጡ ከያዘው ሸቀጦች በመለየት (በመነጠል) የሚሰጡት ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | 44594 | የፌ/ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ እና እነ ካፋ መሐመድ (አራት ሰዎች) | ሐምሌ 15/2001 | 13 |
| 7 | በወንጀል ጉዳይ በእስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሰው የእስራት ቅጣቱን ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ወይም እንዲለቀቅ ሊደረግ የሚችለበት አግባብ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 82,192,194 | 46382 | እነ ዳንኤል ገ/ዮሐንስ (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ሐምሌ 28/2001 | 16 |
| 8 | አንድ ተከሣሽ በተፈፀመ ወንጀል ላይ ተካፋይ ነበር ለማለት ተከሣሹ በሙሉ ፈቃዱና ዕውቀቱ በወንጀል ድርጊቱ ተሣታፊ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32, 33, 630, 25 | 44031 | ወ/ሮ ፈለቀች ኃ/ገብርኤል እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ | ሐምሌ 30/2001 | 19 |
| 9 | ከተሽከርካሪ ጋር በተያያዘ በድንገተኛ አደጋ ለሚከሰት የሰው ህይወት መጥፋት አሽከሪካሪው በቸልተኝነት ወንጀል በማድረግ ሊጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 59(1), 543(2) እና (3)፣57 (2) | 42703 | ፋሲል ብርሃኑ እና ዓቃቤ ሕግ/የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት/ | ሐምሌ 22/2001 | 22 |
| | **ንብረት** | | | | 27 |
| 10 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ካርታ በማቅረብ ብቻ የሚረጋገጥ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 | 36320 | ወ/ሮ ዘውዴ ገ/ስላሴ እና ወ/ሮ ህይወት ባህታ | ጥቅምት 18/2001 | 28 |
| 11 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተገናኘ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው ንብረቱን ለመገንባት የወጣው ወጪ (BooK value) ብቻ ሣይሆን ንብረቱ | 35003 | አቶ አሸናፊ አብዱልቃድር እና እነ ወ/ሮ ሽቶ አብዱራሂም | ህዳር 9/2001 | 30 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በወቅቱ ለገበያ ቀርቦ ሲያወጣ የሚችለው ዋጋ ( market value) ጭምር ስለመሆኑ | | (አራት ሰዎች) | | |
| 12 | አንድ ተከራካሪ ተገቢነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅርቧል ለማለት ለክርክር መንስኤ የሆነው ንብረት በእጅ አድርጎ መገኘትና በዚሁ ንብረት ላይ በእውነት ለማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጭበረበረና በማናቸውም መንገድ ህገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተገኘ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1) | 36645 | ረዳት ሳጂን አያኖ አንጀሎ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጫሌቦ | ህዳር 11/2001 | 32 |
| 13 | የጋራ ንብረትን ለመካፈል በሚደረግ ሽያጭ የጋራ ባለንብረት የሆነ ወገን የቅድሚያ ግዥ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261(2), 1386 — 1409 | 37297 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ እታለም ተስፋ | ታህሣሥ 2/2001 | 36 |
| 14 | የጋራ ሀብት የሆነ ንብረት በመያዣ የተያዘ በመሆኑ የቅድሚያ መብት ያለ ቢሆንም የጋራ ባለሀብት የሆነ ወገን ንብረቱ በግልፅ ጨረታ ቀርቦ የሚያወጣውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ግማሽ በመክፈል ማስቀረት የሚችል ስለመሆኑ | 37298 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ዋቅጂራ | ታህሣስ 2/2001 | 39 |
| 15 | የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታን ለማቅረብ አቤቱታ አቅራቢው ክርክር የቀረበበት ንብረት ባለሀብትነቱን ሳይሆን ባለይዞታነቱን ብቻ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ | 38228 | ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ እና እነ አቶ ዲኖ በሺር (ሁለት ሰዎች) | ታህሣስ 7/2001 | 41 |
| 16 | ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ ሰው የህንፃው ባለሀብት ሊሆን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179 | 36638 | በላይ አበበ እና እነ አበራሽ ዋቅጅራ<br>(ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2001 | 43 |
| 17 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያለው ባንክ በንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚችለው የመብት አድማስ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3088/1/, 3110/ሐ/ | 36013 | ወ/ሮ ዘምዘም ኑሩ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ታህሣሥ 21/2001 | 46 |
| 18 | የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን የሁከት ተግባር ፈጽሟል ከሚባለው ሰው የተሻለ የይዞታ መብት ያለው መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149 | 39940 | ወ/ሮ ነጂባ ነጋሽ እና ወ/ሮ ዚያዳ ጴታሞ | ግንቦት 27/2001 | 50 |
| 19 | ንብረትነታቸው የመንግስት የሆኑ ቤቶችን በተመለከተ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ መንግስትን ወክሎ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) | 38169 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና<br>የወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ወራሽ<br>አቶ እሸቱ ቦጋለ | ግንቦት 12/2001 | 52 |
| 20 | የይዞታ መብት ፍፁም ስላለመሆኑ እና በህግ አግባብ ይዞታው የተወሰደበት ሰው ተገቢ የሆነ ካሣ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1), (2)<br>አዋጅ ቁ. 7/1986 አንቀጽ 2(5), 21, 22, 24, 23<br>በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ- መንግሥት አንቀጽ 40 (8)<br>አዋጅ ቁ. 455/1997 | 39539 | የአዲስ አበባ አስተዳደር ግብርና ቢሮ<br>እና<br>እነ አቶ አበበ ዓባይ(ዘጠኝ ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 54 |
| 21 | ከህግ የሚመነጭ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ | 38666 | የኢትዮጲያ ልማት ባንክ<br>እና<br>ባላንባራስ ተስፋዬ ገ/እየሱስ | ሐምሌ 9/2001 | 57 |
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | 60 |
| 22 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 2143 ላይ የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን የሚያካትት ስለመሆኑ | 34544 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ | ጥቅምት 11/2001 | 61 |
| 23 | ማንም ሰው ሥራው በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ጥፋት ባይኖርበትም ከውል ውጭ ሃላፊነት ሊከተልበት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066- 2089(2069(1)) | 33201 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ሼል ኢትዮጵያ | ጥቅምት 27/2001 | 63 |
| 24 | ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው (ልጅ) ሃላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሰራ እንደሆነ ወላጆች በፍ/ብሔር | 31721 | ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ<br>እና | ጥቅምት | 65 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በሃላፊነት ሊጠየቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2125, 2124 | | ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ | 25/2001 | |
| 25 | የጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባር ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው በህጉ መሠረት ሊሟሉ የሚገቡትን ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ እንጂ በማናቸውም ጥርጣሬ ምክንያት የግለሰብን ንብረት በመያዝ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.60/89 አንቀጽ 6, 58<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 2(28)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26(1)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1193(1),(2), 2027, 2035, 2054, 2118 | 31171 | አብልሃሚድ የሱፍ እና የምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት | ጥቅምት 27/2001 | 67 |
| 26 | ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ከሆነና ጉዳቱ በተጐጂው የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ካሣ ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ | 35034 | እነ ወ/ሮ ጥሩቀለም ደሴ እና እነ ወ/ሮ ጽጌ ከፍያለው | ጥቅምት 6/2001 | 70 |
| 27 | ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት የሰው ህይወት የጠፋ እንደሆነና ለጉዳቱ መንስኤ (ምክንያት) የሆነው ወገን ሃላፊነት የተረጋገጠ ከሆነ በጠፋው የሰው ህይወት የተነሣ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተው ሰው ምን ያህል ጥቅም ያስገኝለት እንደነበር ወይም ምን ያህል ተጨማሪ ዕድሜ ሊኖር እንደሚችል ያላስረዳ ቢሆንም እንኳን ፍ/ቤት የጉዳት ካሣውን በርትዕ ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | 34314 | ወ/ሮ ግምጃ ኅበና እና እነ አቶ ወንድወሰን ወልዴ (ስድስት ሰዎች) | ህዳር 11/2001 | 73 |
| 28 | የጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ለሚያቆየው ንብረት በባለንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ | 31704 | አቶ አማረ መጃ እና የድሬዳዋ ለጋር ጉምሩክ | ጥር 29/2001 | 76 |
| 29 | በጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ የሚሄድ ተሣፋሪ ላይ ለሚደርስ አደጋ የመኪናው ባለቤት ካሣ የመክፈል ሃላፊነት የማይኖርበት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089 | 38457 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ተመኘሁ እንደሻው | ሰኔ 2/2001 | 79 |
| | **የዳኝነት ስልጣን** | | | | 81 |
| 30 | የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ውስጥ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1) (ሸ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1) | 35657 | እነ ወ/ሮ እመቤት መክብብ እና አቶ በድሉ መክብብ | ጥቅምት 6/2001 | 82 |
| 31 | የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ለክርክር መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የመብት ጥሰትን የተመለከተ በሆነ ጊዜ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 50(1), 39 | 36338 | ገ/መስቀል ደመወዝ እና ወ/ሮ አፀደ መኰንን | ጥቅምት 25/2001 | 86 |
| 32 | የቅኔ መምህርነት ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ሥራ በመሆኑ በሥራ ክርክር ችሎቶች ሊስተናገድ የሚችል ስላለመሆኑ | 34440 | መንበረፓትሪያክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና መጋቢ ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ | ጥቅምት 6/2001 | 88 |
| 33 | የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የቤት ባለቤትነት ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ረ) | 33841 | አቶ አስጨናቂ ረጋሣ እና እነ አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ (ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 6/2001 | 91 |
| 34 | በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በወታደርነት በማገልገል ላይ የሚገኙ የሠራዊት አባላት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ | 33368 | ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ እና | ህዳር 9/2001 | 93 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወንጀል አቤቱታዎችን ለማስተናገድ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.27/88, አዋጅ ቁ. 343/94 አንቀፅ 2(9),26(1) | | ወታደራዊ አቃቤ ህግ | | |
| 35 | የአ.አ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በከተማው አስተዳድር ሥር ካሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን ብቻ ለማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ | 34788 | የሟች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች እና ማርታ ሰለሞን (2 ሰዎች) | ህዳር 2/2001 | 96 |
| 36 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስላለመሆኑ | 31906 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች | ህዳር 4/2001 | 99 |
| 37 | በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ከተወረሱና በቀላጤ ከተያዙ ቤቶች ውጭ ያሉ ቤቶችን አስመልክቶ የሚነሣ የቤት ክርክር ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች ማየት የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ.47/67<br>አዋጅ ቁ. 110/87 | 37281 | አቶ አበበ ዓሊ እና እነ የ08 ቀበሌ ገ/ማህበር (ሦስት ሰዎች) | ታህሣሥ 16/2001 | 103 |
| 38 | በውጭ አገር የሚገኝ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክርን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስተናገድ ስለመቻሉ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37, አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ(4) | 37339 | ወ/ሮ ንግስት ኃይሌ እና አቶ ለገሠ ዓለሙ | ጥር 28/2001 | 106 |
| 39 | ወደ ቀድሞ የሥራ መደብ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ የወል ሥራ ክርክር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ142(1) (ሀ) | 37016 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ተስፋዬ ማሞ | የካቲት 3/2001 | 109 |
| 40 | ከጉምሩክ ፖሊስ አባላት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን ለመደበኛ የሥራ ክርክር ችሎቶች ያልተሰጠ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 368/96 , አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 8(2) , መመሪያ ቁ.4/1996 | 39085 | የኢትዮትያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ር አስረሳች ወርቅነህ (ሰማንያ ሰባት የጉምሩክ ፓሊሶች) | የካቲት 3/2001 | 111 |
| 41 | ቀደም ብሎ የተሰጠን የፍች ውሣኔ ወደጐን በመተው አዲስ የተደረገን ጋብቻ ህገ ወጥ ነው ማለት የማይቻል ስለመሆኑ | 38745 | እነ ወ/ሮ ሣሊያ ኢብራሂም (ሁለት ሰዎች) እና ሐጂ ሰማን ኢሣ | መጋቢት 10/2001 | 113 |
| 42 | የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የይዞታ ክርክርን ማስተናገድ የማይችሉ ስለመሆናቸው | 36677 | ወ/ሮ ሻምሺ የኑስ እና ወ/ሮ ኑሪያ ማሚ | ሚያዝያ 30/2001 | 116 |
| 43 | የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ስለመሆኑ | 37866 | ሙሉጌታ አባይ እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን | ግንቦት 19/2001 | 119 |
| 44 | የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶችም ሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳዬችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን በህግ ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ | 41608 | እነ ሙላቱ አንበርብር እና ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና | ሐምሌ 22/2001 | 121 |
| **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | | 123 |
| 45 | ዕቃዎችን ለሚያጓጉዝ የጭነት መኪና የተገባ የመድን ዋስትና ጋር በተያያዘ በመኪናው ላይ ተሣፍሮ ሲሄድ ለነበረና አደጋ ለደረሰበት ሰው መድን ሰጪው የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ | 42139 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ብያን ኡመር | ሰኔ 30/2001 | 124 |
| 46 | ኢንሹራንስ ሰጪ በውሉ መሠረት ከፈፀመ በኋላ በተሸሸገ ወይም በሀሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ አጋጥሟል በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ 674(1),(2) | 42309 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሰኔ 30/2001 | 126 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ውክልና** | | | | 128 |
| 47 | አደራ ተቀባይ የሆነ ወገን በአደራ የተቀበለውን ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው ስለመሆኑ | 38289 | ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ እና አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ | ሰኔ 23/2001 | 129 |
| 48 | መንግስታዊ የሆነ ተቋም በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ክርክር የሚቀርብ ሰነድ የኘሮቶኮል ቁጥር እንዲሁም ስለአቤቱታው ጽሁፍ ትክክለኛነት በሚመለከተው ኃላፊና በወኪሉ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80, 92, 93 እና 92(3) | 43875 | በወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አቶ ወንድሙ ኃይሌ | ሐምሌ 16/2001 | 131 |
| 49 | የዕቃ አስተላላፊ አካል እንደ አጓዥ ሆኖ የሚቆጠረው ከወደብ የተረከበውን ዕቃ በራሱ ማጓጓዣ ካጓጓዘ ብቻ ስለመሆኑ<br>ደንብ ቁ.37/90 አንቀጽ 2(1), 3(6),(7)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2251<br>የንግድ ህግ .ቁ. 683(3) | 37799 | የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሐምሌ 29/2001 | 134 |
| 50 | በወኪል በኩል የሚፈፀም የመኪና ጭነት ውል በአስጫኙ እና በመኪናው ባለቤት መካከል እንደተደረገ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 566 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2251 | 34621 | ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ እና አቶ ሐጎስ ገ/መድህን | ሐምሌ 30/2001 | 136 |
| | **የንግድ ሕግ** | | | | 140 |
| 51 | የንግድ ድርጅት በህግ አግባብ ለባለመብቶች ሊከፋፈል የሚችልበት ሁኔታ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 127 | 33954 | ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ እና አቶ ዘውዱ ቢረዳ | ጥቅምት 20/2001 | 141 |
| 52 | የእሽሙር ማህበር መፍረስ በንብረት ክፍፍል ረገድ የሚያስከትለው ውጤት | 33470 | ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ እና መገርሳ ጉደታ | ህዳር 2/2001 | 144 |
| 53 | የጋራ ሀብት የሆነ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሌላ ማናቸውም ንብረት ባለበት ሁኔታ በዓይነት ሊከፋፈል ወይም ደግሞ በሃራጅ ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 542 | 34945 | ወ/ሮ መስታወት በላቸው እና አቶ ለገሠ ሣህሉ | ህዳር 2/2001 | 146 |
| 54 | የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር ለሌላ ሶስተኛ ወገን ያለአከራዩ ፈቃድ ማከራየት ስለመቻሉ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 145 | 31264 | ወ/ሮ እመቤት መኰንን እና ወረዳ 20 ቀበሌ 29 አስ/ጽ/ቤት | ጥር 5/2001 | 148 |
| 55 | በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161<br>የንግድ ሕግ ቁ. 124 | 34586 | አቶ ያለው ድልነሳው እና እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረግ (አራት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 151 |
| 56 | ቼክን አስመልክቶ ክስ በቀረበ ጊዜ የተከሰሰው ወገን የቀረበበትን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበው ምክንያት ፈቃድ ሊያሰጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህግጋት አኳያ መታየት ያለበት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 717<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 284, 285 | 43315 | ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል እና አቶ መስፍን ታደሰ | ግንቦት 18/2001 | 154 |
| | **አእምሯዊ ንብረት** | | | | 156 |
| 57 | አንድን የሥነ-ጥበብ(ኪነ-ጥበብ) ሥራ ያለባለቤቱ ፈቃድ ኦርጅናሉ ወይም ቅጅው ለህዝብ እንዲታይ ማድረግ የኮፒ ራይት ህግ ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1791, 1771(1), 1790, 2090-2123<br>አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7 | 42253 | መምህር ሙሉ ኃይለሥላሴ እና ዘመናዊ ማተሚያ ቤት | ሐምሌ 8/2001 | 157 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ልዩ ልዩ | | | | | 160 |
| 58 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዋቅር ባልተዘረጋባቸው ክልሎች የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ወክለው/ተክተው/ ክርክሮችን ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 139/1//ለ/,154/1/,153,140 | 21214 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ለማ ኩማ (ሦስት ሰዎች) | ህዳር 4/2001 | 161 |
| 59 | • የጡረታ መዋጮ በመዘግየቱ ምክንያት በአዋጅ ቁ. 345/95 መሠረት ተጨማሪ ክፍያ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ እና<br>አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 7(3), 52(1),56<br>• የጡረታ መዋጮ በ2 ዓመት ውስጥ እንደተከፈለ የህግ ግምት ሊወሰድበት የሚችል የክፍያ ዓይነት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ሠ) | 35391 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና አንበሣ ጫማ አ/ማ | ህዳር 25/2001 | 163 |
| 60 | የጥብቅና ፈቃድን ለማግኘት በህጉ የተቀመጡት መስፈርቶች ራሣቸውን ችለው መታየት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 8(1) | 37375 | አቶ ሽምሱ ከድር አህመድ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር | ህዳር 11/2001 | 166 |
| 61 | በከባድ የወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ እና በራሣቸው ወጪ ጠበቃ ለማቆም ያልቻሉ ግለሰቦች በተመለከተ ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የግለሰቦችን በጠበቃ የመወከል ህገ-መንግሥታዊ መብት መከበሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 13 (1) | 37050 | ሻምበል ሁሴን አሊ እና የሱማሌ ክልል ዐ/ሕግ | ታህሣሥ 30/2001 | 168 |
| 62 | ከዘር የወረደ ርስት ነው በሚል የመሬት ባለቤት ለመሆን የሚቀርብ ክስ ህገ-መንግስታዊ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 38237 | አቶ በርገና ሸፈራው እና እነ አቶ አብራሃም ሸፈራው(አራት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2001 | 171 |
| 63 | በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍ/ብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት ለመወሰድ ብቃትና አግባብነት ያለው ስለመሆኑ | 37184 | የሰሜን ቀጠና ጉምሩክ እና እነ ቄስ ብርሃን ንዋይ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 9/2001 | 174 |
| 64 | የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጨረታ አማካኝነት የሽያጭ ውል አካሄዷል ተብሎ ሊገደድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1688(2), 3167(1), 1688(2), 3168 | 37163 | የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን እና ህያብ ገ/መድህን ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ | ታህሣሥ 23/2001 | 179 |
| 65 | አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ምንነት፣ የሚደረጉበት መንገድና ለአፈፃፀም የሚቀርቡበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3318, 3324, 3325, 3346, 1731<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 315, 319, 350, 357 | 38794 | አቶ ሙክሚል መሐመድ እና አቶ ሚፍታህ ከድር | መጋቢት 24/2001 | 182 |
| 66 | አስተዳደራዊ የሆኑ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ ካርታ እንዲሰጥ የሚወሰን ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ | 39529 | ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር እና እነ ወ/ሮ ግምጃ በዳኔ (ስድስት ሰዎች) | ግንቦት 11/2001 | 186 |
| 67 | ግምቱ ከብር 10,000 ብር በላይ ለሆነ የአፈፃፀም ክስ ሊከፈል የሚገባው ዳኝነት 25 ብር ብቻ ስለመሆኑ<br>የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 177/1945 አንቀጽ 2(ሠ) | 40752 | እነ ወ/ሮ ኢክራም መሃመድ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘኪ መሐመድ | ሐምሌ 28/2001 | 189 |
| 68 | ከፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኞች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር ምንም እንኳን ሥራው የሚካሄደው በክልሎች ቢሆንም ወይም ሠራተኞቹ የክልል ነዋሪዎች ቢሆኑም ገቢ የሚደረገው ለፌዴራሉ መንግስት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 96(3)<br>አዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ5(2)(ሐ)<br>ደንብ ቁ. 109/96 | 40133 | የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና በሶማሌ ብ/ክ/መ የፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ጽ/ቤት | ሐምሌ 2/2001 | 191 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | **አሰሪና ሰራተኛ** | | | | 195 |
| 69 | የግንባታ ዕቃዎች እጥረት አጋጥሟል በሚል የሚደረግ የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 26,28,30 | 41385 | ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ ተረፈ ዘርጋው (ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 3/2002 | 196 |
| 70 | የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት አድርጐ ከሚቀርብ ክርክር ጋር በተገናኘ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሣይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነት መካከል ወደ ሥራ የመመለስ ጉዳይ ላይ ብቻ ውሣኔ ከተሠጠና ሠራተኛው ወደ ሥራ መመለስ ሳይፈልግ ቢቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሣኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3) | 42361 | ወ/ት ትዕግስት ንጉሴ እና ኤስ.ኦ.ኤስ ኢንፋንት ኢትዮጵያ | ጥቅምት 5/2002 | 198 |
| 71 | በትርፍ ሰዓት በሌላ መሥሪያ ቤት ሰርተሃል በሚል ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ 377/96 አንቀፅ 27 | 42818 | አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ እና ወ/ር ሙሉታ ገዳ | ጥቅምት 10/2002 | 200 |
| 72 | አሰሪ በግልፅ ባልፈቀደበት ሁኔታ በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራት ሠራተኛውን የማታለል ተግባር እንደፈፀመ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) | 41767 | የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና አቶ አድማስ ደምሳቸው | ህዳር 8/2002 | 202 |
| 73 | አሰሪ የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት እና መስኪያ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ በሠራተኞቹ መካከል በክፍያ ረገድ ልዩነት ማድረግ ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 14(1)(ረ)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት 42(1)(መ) | 42923 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ነጻት አባስ | ህዳር 22/2002 | 204 |
| 74 | ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የሚለቅ ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት የሚችለው ቢያንስ የ5 ዓመት አገልግሎት ያለው እንደሆነ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(ሽ) | 44410 | ወ/ሮ ላይላ ረዲ እና ድሬ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግል ማህበር | ኅዳር 01/2002 | 207 |
| 75 | በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ወይም "በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" በሚል የተቀመጠው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95/2/,97,96 | 47807 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ ፈንታው (ሁለት ሰዎች) | ታህሳስ 06/2002 | 210 |
| 76 | አሰሪ ሠራተኞቹን በማስተዳደር ረገድ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በራሱ አነሣሽነት ሊያርም የሚችል ስለመሆኑ | 45889 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፓሬሽን ደቡብ ሪጅን እና ሳሙኤል ቂለቦ | ታህሣሥ 20/2002 | 213 |
| 77 | በክርስትና ሃይማኖት ተቋም ውስጥ በዲያቆንነት ሥራ ከማገልገል ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የሥራ ክርክር ጉዳዮች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ሊስተናገዱ የማይችሉ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 47806 | የሆህተሰማይ ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና ዲያቆን አያሌው አዲሱ | ታህሣሥ 20/2002 | 215 |
| 78 | በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10 | 47469 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ስዩም ገብረፃዲቅ(ሃያ ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 15/2002 | 217 |
| 79 | በሥራ ክርክር ጉዳይ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 164(3)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853,1852 | 47784 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አለምፀሐይ አያና | ታህሣሥ 20/2002 | 220 |
| 80 | በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የሥራ ግንኙነት በአንቀፅ 30 መሠረት ሲቋረጥ አሰሪ ማስጠንቀቂያ | 49057 | አስመላሽ እና ልጆቹ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል | ጥር 5/2002 | 223 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 30, 28(2) | | ማህበር እና ዮሐንስ እሺበል | | |
| 81 | የጡረታ መብት ያለው እና መደበኛ የጡረታ ዕድሜው ደርሶ የተሰናበተ ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2(ሰ) እና (ሸ) | 46276 | ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት<br>እናእነ ኃይሌ ይማም<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 11/2002 | 225 |
| 82 | • አንድ ድርጅት በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኞች የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ድርጅት ለዘለቄታው እንዲቆም የሚያደርግ ሁኔታ ሲከሰት ማስጠንቀቂያ ለሠራተኞች መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ | 42985 | ውድ መጣስ ኑሮ አስመጪና ላኪ ድርጅት እና እነ አቶ ሁነኛው ሰጠ (አስራ አንድ ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 227 |
| 83 | የጠብ አጫሪነት ኃይለ ቃልና ዛቻ አዘል ንግግር በሥራ ቦታ ላይ ማድረግ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ረ) | 49958 | ግዩን ትራቭልና ቱርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ ዳንኤል አስፋው | የካቲት 12/2002 | 229 |
| 84 | በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ለሠራተኛው ጥገኞች ስለሚከፈል ካሣ፣ ካሣው የሚከፈልበትና የሚሰላበት ሁኔታ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 110 | 40529 | የህፃን ዮናታን ነጋ ተሻገር ጠ/ጥ.ጋቡ ጌጤ<br>እና<br>አቶ ለገሠ አበራ | የካቲት 10/2002 | 231 |
| 85 | በአሰሪና ሰራተኛ በኩል በአጠቃላይ ለፕሮጀክት ሥራ በሚል የተደረገ የሥራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት የተደረገ እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ) | 48648 | የፃልቂ የትምህርትና የተቀናጀ የልማት ማህበር<br>እናእነ አቶ ታጠቅ ደጀኔ<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 234 |
| 86 | ሠራተኞችን ለማበረታታት በሚል የሚደረግ የደመወዝ (ጥቅማጥቅም) ጭማሪን መሠረት በማድረግ ጭማሪውን የሚፈቅደው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ የሚጠይቀው መብት የሌለ ስለመሆኑ | 47825 | የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ)<br>እና እነ አቶ ዘርዓየሁ ሰሜ<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 236 |
| 87 | አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ ከሚፈፅመው ጥፋት ጋር በተያያዘ ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ስለሚችልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 47535 | የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት<br>እና አቶ እንግዳው ላቀው | መጋቢት 20/2002 | 238 |
| 88 | • የአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አሰሪና ሰራተኛ ስምምነት ሊያደርጉባቸው የሚችሉበት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጥፋትንና ጥቅምን በተመለከተ የተለያየ አቋም የያዘ ስለመሆኑ<br>• አሰሪና ሠራተኛ በህብረት ስምምነታቸው ውስጥ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በሚል የተስማሙበት ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 134(2), 27(1)(ሸ) | 49750 | በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ<br>እና<br>አቶ ማስረሻ ሁሴን | መጋቢት 30/2002 | 240 |
| 89 | አሠሪ የሠራተኛውን የሥራ ውል ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሁፍ አለመግለፁ ብቻ ስንብቱ ህገ- ወጥ ነው ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2) | 49797 | አልህበሽ ሹገር ሚልስ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ተገኔ ገ/ሃዋሪያት | መጋቢት 30/2002 | 242 |
| 90 | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈፀም" በሚል የቀረበው አባባል (አነጋገር) ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) | 50009 | የአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል<br>እና<br>አቶ ዮናስ ጥላሁን | መጋቢት 6/2002 | 244 |
| 91 | አሠሪና ሠራተኛ የሥራ ውል መቋረጥ ጋር በተያያዘ በሥራ ውሉ ላይ የሚያመለክቱት ሁኔታ የአሰሪና | 50205 | የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት | መጋቢት 20/2002 | 246 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሠራተኛ ህጉን እስካልተፃረረ ድረስ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ | | እና<br>አቶ ምናለ በሪሁን | | |
| 92 | የሥራ ውል በተቋረጠ ጊዜ አሰሪው ከሠራተኛው በህግ አግባብ የሚፈልገው/ የሚጠይቀው ዕዳ ያለ እንደሆነ ለሠራተኛው የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት ከመስጠት ባሻገር የሥራ መልቀቂያ (ክሊራንስ) ለመስጠት የማይገደድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀፅ 78 (1),87 | 48476 | የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና አቶ ደረጀ መኮንን | ሚያዝያ 12/2002 | 248 |
| 93 | ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሚደርስበትን ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ወይም ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት በማለት ለመለየት የሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 101 (2) | 49273 | አቶ ደረጀ ውለታው<br>እና<br>ዋሊያ ሌዘርና ሌዘር ፕሮዳክትስ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 27/2002 | 250 |
| 94 | • አንድ ሰው በአፈፃፀም ሊገደድ የሚችለው በህግ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ<br>• በግልፅ ፍርድ ያላረፈበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | 50148 | እነ አቶ ወርቁ ደረጀ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አባርኪሮ ሁመድ | ሚያዝያ 4/2002 | 252 |
| 95 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ጋር ያለው ግንኙነት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቢመለስ ችግር ውስጥ እንደሚወድቅ በአሠሪው ስለተገለፀ ብቻ ሠራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በሚል የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/ | 49931 | የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሽ ባለንብረቶች ማህበር<br>እና<br>አቶ ተሰማ ኃይሉ | ሚያዝያ 21/2002 | 254 |
| 96 | የድርጅት መዋቅራዊ ለውጥ ያደረገ ተቋም በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሠረት ሠራተኞቹን አዲስ በሚያወጣው የሥራ መደብ ላይ ተመርኩዞ የሥራ ምደባ ሊያከናውን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28 | 50838 | ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት<br>እና እነ አቶ አማረ አበራ (ሰባት ሰዎች) | ሚያዝያ 12/2002 | 256 |
| 97 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪ ሠራተኛው የፈፀመውን ድርጊት መሠረት አድርጐ ለማሰናበት የሚችለው የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ነገር መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3) | 45746 | ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር<br>እና<br>አቶ በለጠ ጫላ | ሚያዝያ 6/2002 | 258 |
| 98 | ሠራተኛ የተረከባቸውን ንብረቶች አላስረከበም ወይም አጉድሏል በሚል የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚጠይቃቸውን ተገቢ ክፍያዎች ሊጠይቅ አይችልም በሚል በአሠሪው የሚቀርብ ክርክር ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 36,37,38 | 44405 | ፊንፊኔ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና አቶ ደጃ ደምሴ ጎበና | ግንቦት 19/2002 | 260 |
| 99 | ወደ ሥራ እንዲመለስ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነና በአሰሪው ችግርም ሆነ በሠራተኛው ፍላጐት በፍርዱ መሠረት ወደ ሥራ ለመመለስ ሠራተኛው ያልፈለገ ከሆነ ሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ በምትክነት በሰጠው መብት መሠረት በመመለሱ ፈንታ ካሣ እንዲከፈለው አፈፃፀሙን ለያዘው ችሎት ጥያቄውን ባቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3) | 53064 | አቶ ደሬሳ ኮቱ<br>እና<br>የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን | ግንቦት 17/2002 | 263 |
| 100 | በድርጅት ውስጥ የተከሰተ ተጨባጭ ችግርን ለመቅረፍና የድርጅቱን ትርፋማነት ለማስቀጠል በሚል በተመሳሳይ ሙያና ደረጃ ላይ ካሉ ሠራተኞች መካከል ተለይቼ ወደ ሌላ የሥራ መደብ ስለተዛወርኩኝ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ | 50182 | የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት እና አቶ አበበ ተፈራ ይልማ | ግንቦት 13/2002 | 265 |
| 101 | የሥራ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ይህንኑ የማስረዳት | 44218 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና | ግንቦት 13/2002 | 267 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሽክም የሚኖር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 9 | | እነ አቶ ታጁ አባጋሮ (ሃያ አንድ ሰዎች) | | |
| 102 | አንድ አሰሪ በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበትን ሰራተኛ ወደ ውጭ አገር ልኮ ስለሚያሳክምበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124,105 | 46363 | ሚሊኒ ኮንስትሩቶሪ ኤስ.ፒ.ኤ<br>እና<br>አቶ ትግሉ ፍሬህይወት | ግንቦት 19/2002 | 270 |
| 103 | • ከአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጋር በተገናኘ ሁለቱ ወገኖች አዋጅ ቁ. 377/96 "ን" ወደ ጐን በማድረግ በሌላ አገር ህግ ለመዳኘት ስምምነት ያደረጉ በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ህግ ጥያቄን ያስነሳል በሚል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑ<br>• አዋጅ ቁ. 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ የበጐ አድራጐት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3/ /ለ/ | 50923 | ፋውንዴሽን አፍሪካ<br>እና<br>አቶ አለሙ ታደሰ | ግንቦት 19/2002 | 273 |
| 104 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በማስላት ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 163(2) | 51912 | የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና<br>ወ/ሮ ሶፋኒት አጥናፉ | ሰኔ 7/2002 | 276 |
| 105 | • በአሰሪ የተፈፀመው የሥራ ስንብት ህገ- ወጥ ቢሆንም ከሥራ ግንኙነቱ ፀባይ የተነሣ ከፍተኛ ችግር የሚፈጠር በሆነ ጊዜ ሠራተኛውን ወደ ሥራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ<br>• የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀፅ 43(3) በአንድ በኩል የሠራተኛን የሥራ ዋስትና በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱስትሪን ሰላም በማመዛዘን ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ | 55189 | አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል<br>እና<br>አቶ ዘላለም መንግስቱ | ሰኔ 30/2002 | 279 |
| 106 | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ‹‹... ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት...›› በሚል የተመለከተው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3) | 53358 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና<br>አቶ ጥላሁን ኩማ | ሰኔ 18/2002 | 281 |
| 107 | አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9,10 | 43160 | እነ እንደገና ተሾመ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ኒው ጄኔሬሽን ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ | ሰኔ 22/2002 | 283 |
| 108 | በማናቸውም ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ያልወሰደው የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 77(5) ,24(2) | 52459 | እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ እና አለሙ መራ<br>ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራድርጅት | ሐምሌ 16/2002 | 285 |
| 109 | በክረምት ወቅት የማስተማር ሥራ እንዲሠራ የሚያዝ ግልፅ ደንብ ወይም መመሪያ የሌለ እንደሆነ ወይም አስተማሪው በክረምት ወራት ለማስተማር የገባው የውል ግዴታ (ስምምነት) በሌለ ጊዜ በክረምት ወቅት ሥራን ለመስራት ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ከሥራ ሊሰናበት የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 13(1) | 45170 | የቅድስት ማሪያም አፀደ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት<br>እና<br>መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ | ሐምሌ 8/2002 | 287 |
| **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | | 289 |
| 110 | በክርክር የግድ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው ወገኖች እና የፍ/ቤት ሚና<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 39,(1),40(2) | 43424 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና እነ አቶ መስፍን /ስምንት ሰዎች/ | ጥቅምት 10/2002 | 290 |
| 111 | የቃል ክርክር እንዲሰማ በተቀጠረበት ዕለት ግራ ቀኝ የሆኑ ወገኖች ያልቀረቡ እንደሆነ መዝገቡ መዘጋት ያለበት ስለመሆኑ | 43410 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል | ህዳር 30/2002 | 293 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 69(2) | | | | |
| 112 | አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህንን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ ዓይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ | 47551 | ንግድ ማተሚያ ድርጅት እና አቶ ካሱ ሙላት | ታህሣሥ 6/2002 | 295 |
| 113 | ጣልቃ በመግባት በክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጠይቆ የተፈቀደለትና የጣልቃ ገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባው ይህን ባለመፈፀሙ መብቱ ከተሰረዘበት በኋላ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41,358 | 40229 | ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መዲና በያን<br>(ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 15/2002 | 297 |
| 114 | በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከራካሪ ወገን ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታው ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 78,69,72 | 43731 | ሲ.ጂ.ሲ.ኦቨርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና ሰለሞን እንዳለ | ታህሣሥ 8/2002 | 299 |
| 115 | • በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 መሠረት መዝገብ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ<br>• ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ዳኝነት የሚጠይቁበትን ፍሬ ነገር በአግባቡ ከገለፁ ትክክለኛውን የህግ ድንጋጌ አለመጥቀሳቸው መብታቸውን የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280,69(2), 70(መ), 71(2) | 39581 | አቶ ውብሸት ካሣዬ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ማዕድን ሃብት ኮርፖሬሽን | ጥር 25/2002 | 302 |
| 116 | ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸውን የሰው ማስረጃዎች ሊለውጡ (ሊቀይሩ) የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223/2/,234 | 45984 | ኘሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት እና አቶ ልመንህ ተፈራ | ጥር 26/2002 | 304 |
| 117 | የክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው ከሳሽ የሚያቀርበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ የቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ የቃል ምርመራ ሲያደርግ የሚያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241,248 | 47252 | ወ/ሮ ፑሽፓላት ጆሴፍ<br>እና<br>አቶ ሠይፈ ጎሣዬ | የካቲት 26/2002 | 307 |
| 118 | ዳኝነት እንደገና እንዲታይ (Review of judgement) በሚል የሚቀርብ አቤቱታ አስቀድሞ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የተባለበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ),(ለ) | 43821 | ወ/ሮ ትርሃስ ፍስሀዬ እና ወ/ሮ ዘነበች በሪሁን | ጥር 5/2002 | 310 |
| 119 | ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ላይ በተሰጠ ትእዛዝ/ብይን ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6(3)(4) | 42871 | የቀድሞ ወረዳ 07 ቀበሌ 32 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ጆሮ ዋቅጅራ | ጥር 12/2002 | 315 |
| 120 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 421 መሠረት ክስ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418,421 | 37214 | አቶ ተስፋዬ አለሙ እና እነ ሐጂ ይማም ሙዘይን(ሦስት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 318 |
| 121 | በፍ/ብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ | 44634 | አቶ ታዬ ሆሳዕና እና ወ/ሮ መሠረት ወልደየስ | የካቲት 22/2002 | 320 |
| 122 | ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ክስ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ በቂ በሆነ ማስረጃ በተገነዘቡ ጊዜ ክሱን ሊዘጉት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 | 45371 | የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኩር ሰንበቱ<br>እና<br>እነ አቶ ማሞ ተሠማ<br>(ሦስት ሰዎች) | የካቲት 8/2002 | 322 |
| 123 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216 መሠረት በድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216(3) | 36776 | መብራቱ፣ተ/ማሪያም፣ገ/ማሪያም የሽርክና ማህበር እና አቶ መብራቱ ዓንዳይ | መጋቢት 7/2002 | 324 |
| 124 | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሣኔ ካሣለፈና የበላይ የሆነ | 44545 | ክፍሉ መሓሪ<br>እና | መጋቢት 7/2002 | 326 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፍ/ቤት ደግሞ የይግባኝ ውሳኔውን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በደፈናው በማፅናት የሚሰጠው ውሣኔ የተከራካሪ ወገን የይግባኝ መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግ ደንብን የሚጥስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341,342,343 | | በላይ ከመላ | | |
| 125 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘ ባለገንዘብ ባንክ መብቱ በይርጋ እስካልታገደ ድረስ የያዘውን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የሚገደድበት ተለይቶ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 97/90<br>አዋጅ ቁ. 216/92 አንቀፅ 2<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394 - 449 | 44883 | አቶ ፈንታ ምህረቱ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | መጋቢት 8/2002 | 328 |
| 126 | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ | 39799 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ገነት ስዩም | መጋቢት 21/2002 | 331 |
| 127 | • በተከራካሪ ወገኖች የሚቆጠሩ ማስረጃዎች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የሌላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ<br>• ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች የቆጠሩትን ማስረጃ ሳይሰሙ ወደ ጉን በመተው አቤቱታቸውን በበቂ ማስረጃ አላስረዱም በሚል የሚደርሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | 43845 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 20/2002 | 334 |
| 128 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 መሠረት በሥር ፍ/ቤት የተደረገ እርማትን መነሻ በማድረግ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ለመለወጥ የሚያስችለው የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 208,209,320,(1) ,348(1) | 44931 | ወ/ሮ ሰዓዳ ኢድሪስ<br>እና<br>አቶ ረሺድ ቡባ | መጋቢት 20/2002 | 337 |
| 129 | የፍ/ቤትን ክብርንና የዳኝነት ሥርዓቱን መልካም አመራር ለማስጠበቅ ሲባል የማንኛውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ በችሎት ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ቅጣት ሊወስን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 480 | 48237 | ወ/ሮ ሰኢዳ ሁሴን ይመር<br>ተጠሪ፡የለም | መጋቢት 6/2002 | 339 |
| 130 | ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ ተከሳሽ የሆነን ወገን በሌለበት ባለፅዳ የሚያደርግ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ተከሳሹ በአግባቡ ስለመጠራቱ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 97, 95(3) | 50022 | 5 ብራዘርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና ዓብደላ ኢብሮ ዩሴፍ | መጋቢት 29/2002 | 341 |
| 131 | የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በውሳኔው ወቅት ንብረቱን በእጁ አድርጐ የሚገኘው ወገን የንብረቱን ስመ ሐብት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን አዛውሮ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት ስለሚገባው አካሔድ | 45038 | እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጓዱ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና ወ/ሮ አስረስ አህመድ | መጋቢት 23/2002 | 343 |
| 132 | • ሐሰተኛ ቃል ተሰጥቷል በሚል ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ<br>• በአንድ የወንጀል ድርጊት ነፃ የተባለ ሰው እንደገና ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጐ የሚቀጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 የወንጀል ህግ ቁ. 452(1) | 43005 | እነ አቶ አውግቸው እርገጤ<br>(ሦስት ሰዎች)<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 19/2002 | 345 |
| 133 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ለሰጠ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 | 45839 | ወ/ሮ ይርጋለም ከበደ እና<br>እነ ወ/ሮ ፅጌ ሚካኤል<br>(አምስት ሰዎች) | ሚያዝያ 5/2002 | 348 |
| 134 | በፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 256, 345, 327 | 39853 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር (ሁለት ሰዎች) | ሚያዝያ 21/2002 | 350 |
| 135 | አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት | 41526 | ትራንስ አፍሪካ ትራንስፖርት አ.ማ | ግንቦት 2/2002 | 353 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(3), አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10 | | እና<br>ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | | |
| 136 | ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ የተስማሙና ይሄንኑም ስምምነት ለፍ/ቤት በማቅረብ ያስፀደቁ በሆነ ጊዜ ስምምነቱ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተቆጥሮ መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277 | 52752 | እነ ከድር ሐጂ ሁሴን (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ አሚን ዑስማን (ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 16/2002 | 355 |
| 137 | ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው አቤቱታ የክስ ምክንያት አለው ወይም የለውም ብሎ ለመወሰን በክስ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሽ የሆነው ወገን የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ህግ ይፈቅድለታል ወይስ አይፈቅድለትም የሚለውን ጥያቄ መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ | 45247 | አቶ ደጀኔ በላቸው እና አቶ ነስሩ አወል | ሰኔ 17/2002 | 358 |
| 138 | ሁለት ሰዎች ተጣምረው በተከሰሱ ጊዜ አንደኛው ወገን ጉዳዩ በሌለበት ከታየ በኋላ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተፈቀደለት እንደሆነ ሌላኛው ተከሳሽ አስቀድሞ ያነሳቸውን መቃወሚያዎች በድጋሚ ልታነሣና ልትከራከር አትችልም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 49857 | ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ<br>እና<br>ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን | ሰኔ 30/2002 | 361 |
| 139 | በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባሰማ ጊዜ ስለመሆኑና ድንጋጌው የካሣ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 235(2),83 | 48632 | አቶ ሙልሳ በየቻ<br>እና<br>አቶ ደበሌ በየቻ | ሰኔ 14/2002 | 363 |
| 140 | ክስ የቀረበበት ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚቆጥራቸው ማስረጃዎችን ተቀብሎ አለመስማት የመከላከል ህጋዊ መብትን የሚያጣበብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ5 223, 234, 137, 249, 256 | 49660 | እነ መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና መምህር ሲሳይ ደጀኔ | ሰኔ 22/2002 | 365 |
| 141 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) መሠረት በድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀደመው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑና የተከራካሪ ወገኖች አንድነት በመኖሩ ብቻ ሣይሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 52525 | ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ<br>እና<br>አቶ ሽዋረጋ ደመቀ | ሰኔ 29/2002 | 368 |
| 142 | የሥር ፍ/ቤት በመቃወሚያ ላይ የሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠ እንደሆነ በግራ ቀኝ ወገኖችን በኩል የሚቀርቡ የፍሬ ነገር ክርክሮችንና ማስረጃ በአግባቡ ለመስማት ብሎም የተከራካሪዎችን ይግባኝ መብት ላለማጣበብ ሲባል ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1) | 43331 | አቶ ገመቹ ቡቻሳ<br>እና<br>አቶ በቀለ ኩማ (ቡቻሳ) | ሐምሌ 19/2002 | 370 |
| 143 | ስልጣን ለሌለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብና ክርክር ማካሔድ የይርጋ ጊዜን የሚያቋርጥ ስለመሆኑ ( ከዚህ ቀደም የሰበር ችሎት በተቃራኒው የሰጠው የህግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ፡፡)<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 138, 147, 164(1)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 23,(1) (ለ) ,231,(1)(ለ), 278(3)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 (ለ),1852(1)<br>አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀፅ 2(4) | 36730 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ አማረ ገላው | ሐምሌ 30/2002 | 372 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 144 | • በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከሣሽ ለሆነ ወገን ከፍ/ቤት የሚላከውን መጥሪያ ለተከሳሹ ሊደርስ የሚችልበትን የተሻለ አማራጭ መንገድ በመለየት ሊላክ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• የመኖሪያ አድራሻው በግልፅ ለሚታወቅ ተከሳሽ ፍ/ቤቱ የሚልከውን መጥሪያ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ብቻ እንዲለጠፍ በማድረግ ተከሳሹ አልቀረበም በሚል በሌለበት ጉዳዩ እዲታይ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው ያልተደረገ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሣኔ እንዲነሣለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 105(1), 78, | 50376 | ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ገሰሰ<br>እና<br>በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 አስተዳደር ጽ/ቤት | ሐምሌ 12/2002 | 378 |



www.chilot.me

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበ ት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | **ቤተሰብ** | | 1 |
| 1 | በጋብቻ ውል ላይ ባልና ሚስት "መተዳደሪያቸችን" ነው በሚል ያመለከቷቸው ንብረቶች የጋራ ንብረት ተደርገው የሚቆጠሩ ስለመሆናቸው | 38544 | አቶ ብሩክ ኃ/እየሱስ እና ወ/ሮ ፋናዬ አበበ | ጥቅምት 5/2002 | 2 |
| 2 | • በጋብቻ ላይ የተደረገ ጋብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው (void ab initio) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>• የጋብቻ ውል ተጋቢዎች ንብረታቸውን በተመለከተ ጋብቻው የሚያስከትለውን ውጤት ስምምነት የሚያደርጉበት ሰነድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 42,44,33,11 | 39408 | አርጋው አባቺ እና የወ/ሮ አስቴር አበጋዝ ወራሾች (ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 24/2002 | 5 |
| 3 | የውርስ ሀብትድርሻ ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080(3) | 40418 | ተስፋዬ ሞላ እና እነ እሸቱ ምነ (ሦስት ሰዎች) | ጥቅምት 10/2002 | 7 |
| 4 | አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43 | 42682 | እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ በላይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ | ጥቅምት 10/2002 | 9 |
| 5 | ፀንቶ ባለ ጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት በጋብቻ ውስጥ ባል የሆነው ወገን ስለመሆኑና የዚህን ሰው አባትነት ለመቃወም የሚቻልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144,126,167,168,173 | 40624 | እነ ወ/ሮ መብራት ታደሰ (አራት ሰዎች) እና አቶ ኤፍሬም ዘውዴ | ጥቅምት 12/2002 | 11 |
| 6 | የጋራ የሆነን የውርስ ሀብት ከፍቃዱ ውጪ እንዲሸጥ የተደረገበት ወራሽ ከሽያጩ ዋጋ ድርሻውን ለማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1266,1060(1) | 41857 | አሕመድ ሑሴን እና እነ ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን (ሦስትሰዎች) | ጥቅምት 24/2002 | 14 |
| 7 | አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43 | 42682 | እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ | ጥቅምት 10/2002 | 17 |
| 8 | ከጋብቻ በፊት የግል የነበረ ንብረት በተጋቢዎች የጋብቻ ውል መነሻነት የጋራ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ | 42766 | እነ ወ/ት ሠናይት ኃ/ማሪያም እና ወ/ሮ አበበች ወርቁ | ጥቅምት 10/2002 | 19 |
| 9 | ልጅነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔ የህግ ግምት የሚፈጥር እንጂ አስገዳጅነት ያለው እና የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ መወሰድ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,155,156,157 | 42648 | ወ/ሮ ዘነበች በያን እና ወ/ት ብርቅነሽ ከበደ | ታህሣሥ 6/2002 | 21 |
| 10 | አባትነት በህግ አግባብ ሊታወቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126,1(1),(2),128(1),130(2),125,106(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 35(2) | 44612 | ወ/ሮ ዘውዴ ወ/ጊዮርጊስ እና ወ/ት ኤልሣቤጥ ኪዳኔ | ጥቅምት 10/2002 | 23 |
| 11 | • በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ<br>• የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1),1000(2),1060,1062 | 38533 | እነ ወ/ሮ ጽጌ ወልደመስቀል (ስድስት ሰዎች) እና አቶ ስዩም ክፍሌ | ህዳር 8/2002 | 27 |
| 12 | ልጅነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 156,168,158,169 | 42569 | እነ የዳግማዊ ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ (ሁለት ሰዎች) እና የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ | ታህሣሥ 212002 | 30 |
| 13 | ኑዛዜ ሊተረጐም የሚገባው ቃላቶቹና መልዕክቱ ግልፅ | | አቶ ሐይለራጉኤል ደበላ እና | ታህሣሥ | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሣይሆን ሲቀር ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 810(2) | 47487 | እነ ወ/ሪት አለምፀሐይ ፈለገ (ሁለት ሰዎች) | 27/2002 | 33 |
| 14 | የስጦታ ውል ሊተረጐም የሚገባው በውሉ ውስጥ የሚገኘን አንድ ሃረግ ነጥሎ በማውጣት ሳይሆን የውሉን አጠቃላይ ይዘት በመመልከት ስለመሆኑ | 41893 | ወ/ሮ ዮዲት ኃይሉ እና እነ ወ/ሪት ገነት አረጋይ (ሦስት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2002 | 36 |
| 15 | የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3) | 47957 | እነ አቶ ተፈሪ ሐጐስ (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ተስፋይ ገ/እግዚአብሔር | ጥር 5/2002 | 39 |
| 16 | • የስጦታ ውል ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት እንደሆነ በውሉ ውስጥ የተመለከተው ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ፈራሽ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>• በፍ/ብ/ህ/ቁ. 244(1) ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በስጦታ ውል ውስጥ የተመለከተ ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ሲጠየቅ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2452(1),2464(1),2441(1) | 42346 | እነ አቶ ፍስሐ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሐ | የካቲት 9/2002 | 41 |
| 17 | የጉዲፈቻ ስምምነት የሕፃናትን ጥቅምት ለማስጠበቅ ሲባል ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195(2) | 44101 | ሚስስ ፍራንስዊስ ፖስተር እና እነ ሚ/ር ዱክማን ቬኖ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 44 |
| 18 | የውርስ ንብረት በሆነ ቤት ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ወገኖች ንብረቱን ህጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ይዞ ከነበረ ሰው በመግዛት ስመ ሀብቱን ወደራሱ ስም አዛውሮ የሚገኝን ሰው ለመጠየቅ የማይችሉ ስለመሆኑ | 46527 | ወ/ሮ ገነት በቀለ እና ወ/ሮ ትዕግስት አሰፋ | የካቲት 24/2002 | 48 |
| 19 | ከውርስ ጋር በተያያዘ በቤት ላይ ህጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጭ አከናውኖ ሲገኝ ትክክለኛው ባለሃብት መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገኘ ሣይሆን ሻጩን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 997,2882, 2884,1060(1),1266 | 47378 | አቶ አለማየሁ ከተማ እና እነ ወ/ሮ ላቀች አይተንፍሱ (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 50 |
| 20 | ኑዛዜ በፍ/ቤት መፅደቁ በንብረት ላይ ያለ የባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጥ ስላለመሆኑ | 42482 | እነ አቶ ፍሬዘውድ ተካ ጉጂ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰለሞን ኃ/ማሪያም | የካቲት 3/2002 | 53 |
| 21 | የልጆች ቀለብ አከፋፈል ሁኔታ ጋር በተያያዘ ክፍያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ | 45819 | አቶ ካሣ ፋንታ እና ወ/ሮ እስካዳር ግጨው | የካቲት 12/2002 | 55 |
| 22 | በትዳር ወቅት የተወሰደ ብድር የአንደኛው ተጋቢ ፈቃድ የሌለበት ቢሆንም ፈቃዱን ያልሰጠው ተጋቢ የብድር ስምምነቱ እንዲፈርስ ያላደረገ እንደሆነ ወይም ደግሞ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን ማስረዳት ያልቻለ ከሆነ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(መ) | 45202 | አቶ ድንቁ ወርዶፋ እና ወ/ሪት ኤደን ድንቁ ወርዶፋ | መጋቢት 8/2002 | 57 |
| 23 | በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነትን አሳውጆ የውርስ ንብረት አካል የሆነን ቤት ስመ ሃብት ወደ ራሱ አዙሮ የሚገኝ ሰው ጋር የሽያጭ ውል በተደረገ ጊዜ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል ትክክለኛ ወራሾች የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍብ/ህ/ቁ. 2882, 2884, 997 | 45370 | እነ አቶ ዳንኤል አበበ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 21/2002 | 61 |
| 24 | የስጦታ ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ 10 (አስር) ዓመታት ውስጥ ለአፈፃፀም ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676(1),1845 | 42691 | አቶ አደፍርስ በቀለ እና አቶ ይቁም በቀለ | መጋቢት 22/2002 | 64 |
| 25 | • በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ<br>• የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ | 44237 | እነ ወ/ሮ ሙሉሸዋ ቦጋለ (አራት ሰዎች) | መጋቢት 20/2002 | 66 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1)1002,1060,1062 | | እና<br>አቶ መስፍን ቦጋለ | | |
| 26 | ሞግዚት የሆነ ሰው በሞግዚትነት የሚያስተዳድራቸውን ልጆች ሀብት የሆነን ንብረት ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ ሲል ሊሸጠው የሚችል ስለመሆኑ<br>የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ቤተሰብ ህግ አንቀፅ 292 | 46490 | እነ ወ/ሮ ቦጋለች ደባልቄ (አራት ሰዎች) እና<br>ወ/ሮ መሠረት በለጠ | መጋቢት 21/2002 | 69 |
| 27 | በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አለመፍረሱ ስለሚያስከትለው ውጤት | 51295 | አቶ ዮሐንስ ጡእማይ<br>እና<br>ወ/ሮ ምህረት ገብሩ | መጋቢት 6/2002 | 72 |
| 28 | ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ባለስልጣን ፊት የሚደረግ ኑዛዜ በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አሟልቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 882 | 49851 | ወ/ሮ ታሪኳ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 4/2002 | 75 |
| 29 | ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው እና ከህግ ውጪ ከውርስ የተነቀለ ያለኑዛዜ ወራሽ የውርስ ሃብትን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 939(3) ,850,,911(1) 912(1) | 43069 | አቶ አማረ ረታ እና አቶ ሰለሞን ካሣዬ | ሚያዝያ 6/2002 | 78 |
| 30 | የጉዲፈቻ ውል እንዲፈርስ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 195(1),(2) | 52691 | እነ ቤተ ዛታ ችልድረንስ ሆም አሶሴሽን (ሦስት ሰዎች)<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 22/2002 | 81 |
| 31 | ኑዛዜ መኖሩን የማስረዳት ሸክም (ግዴታ) የተጠቃሚዎች ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896,897 | 53279 | ወ/ሮ ትእግስት ግርማ የእነ አቤል ወርቁ ሞግዚት እና አቶ ኤፍሬም መንግስቱ | ሰኔ 8/2002 | 84 |
| 32 | በኑዛዜ የውርስ ሀብት ክፍፍል መደረግ ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነ ወገን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ሀብት መጠን ከአንድ አራተኛ በታች እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ኑዛዜውን እንዲፀና በማድረግ የተናዛዡን ፍላጐት ማክበርና መጠበቅ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 910, 913 1123(1) | 50901 | ወ/ሮ እልፌ ኃይሌ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ትዕግስት ደበሌ (ሦስት ሰዎች) | ሰኔ 10/2002 | 87 |
| 33 | በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማስረዳት የሚችሉት በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98,99,106 | 46613 | ወ/ሮ ኑኑ ሸህሞሎ<br>እና<br>ወ/ሮ አሰገደች ጫኔ | ሰኔ 24/2002 | 91 |
| 34 | በተከራካሪ ወገኖች ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ ፍ/ቤቶች በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል ወሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ | 51866 | ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ እና ወ/ሮ አዛለች ደበበ | ሐምሌ 2/2002 | 94 |
| 35 | ከኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ከጋብቻ በፊት በአንደኛ ተጋቢ በተደረገ ምዝገባ የተነሣ የቤት ዕጣው የወጣው ብሎም የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው በጋብቻ ወቅት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ለቤቱ መገኘት ምክንያት የሆነው ተጋቢ ቤቱ የግል መሆን አለበት በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(2) | 51893 | እንዳልካቸው ዘለቀ<br>እና<br>ወ/ሮ ብዙዓለም መንግስቱ | ሐምሌ 8/2002 | 96 |
| 36 | በፍ/ቤት የተሰጠ የኑዛዜ ወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የውርስ ሃብት ማጣራት ሳይደረግ የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ሊሰረዝ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 50836 | ወ/ሮ ቅድስት ተካ<br>እና<br>ወ/ሮ የኔነሽ ተካ | ሐምሌ 13/2002 | 99 |
| 37 | ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውል ላይ ባልተገለፀበት ጊዜ የሚች ባል | 44561 | ወ/ሮ ገነት በላይ | ሐምሌ | 101 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወይም ሚስት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ከወራሾች ጋር ሊካፈሉ የሚችሉበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 705,701(1)(ሀ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 827 | | እና አቶ ያፌት ተክሉ | 28/2002 | |
| 38 | ከውርስ ሃብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የውርስ ሃብቱን በእጅ አድርጐ በመገልገል ላይ ያለ ተከራካሪ የሆነ ወራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በጋራ ይዞ የቆየ ሰው ላይ የሚያነሳው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ታግዷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 44025 | እነ ወ/ሪት ፀሐይ ሐይሌ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ ፈልቃ ቤኛ | ሐምሌ 22/2002 | 110 |
| 39 | ወራሽ የሆነ ወገን በውርስ ሃብት ክፍፍል ድርሻው ላይ ከፍ ያለ የበለጠ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለፅ አውራሽ ባደረገው ኑዛዜ መሠረት ክፍፍል እንዳይፈፀም መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123(1) | 47622 | ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ እና እነ ወ/ሮ መንበረ ስላሴ ተኸሌ (አምስት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2002 | 112 |
| 40 | የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3) | 45587 | እነ ወ/ሮ አተረፈች ዘውደ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘውዱ ወሰኔ | ሐምሌ 29/2002 | 115 |
| 41 | በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጅን ከውርስ ያለ በቂ ምክንያት መንቀል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 938,842,915 | 42546 | አቶ ተስፋልደት ኪዳኔ እና እነ ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር (ሦስት ሰዎች) | ሐምሌ 28/2002 | 118 |
| | **ውል** | | | | 123 |
| 42 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ድረስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 | 44800 | አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ጥቅምት 05/2002 | 124 |
| 43 | ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትና የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግና ጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና ሊተረጐም የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732(1) | 42897 | አቶ አየለ ሐብተየስ እና እነ ሚ/ር ኖቺራ ጃካርሎ (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 10/2002 | 127 |
| 44 | ለጨረታ ማስከበሪያ በሚል የሚያዝ ገንዘብ ጨረታውን ባዘጋጀው አካል ሊወሰድ የሚችለው ተወዳዳሪው ጨረታውን ባሸነፈው መጠን ሆኖ በጨረታው መሠረት ውል ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ | 40947 | አቶ መዝገቡ መድህኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | ህዳር 15/2002 | 131 |
| 45 | ተከራካሪ ወገኖች ባላነሱበት ሁኔታ ፍ/ቤት የውል አፃፃፍ ሥርዓትን (ፎርማሊቲን) መሠረት በማድረግ በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል የተካሄደን ውል ፈራሽ ነው በሚል የሚሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1808(2) | 43825 | የህፃን ኮከቤ ተረፈ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እና እነ አቶ አያሌው ካሳዬ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 6/2002 | 133 |
| 46 | • የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገው የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 2473(2) ድንጋጌን ዋጋ በሚያሳጣ መንገድ ተፈፃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ<br>• የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) በባንኮችና በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና ደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የህግ ድንጋጌ ስለመሆኑ<br>• ባንኮች ለደንበኞቻቸው ያበደሩትን የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን በሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(1) ስር የተደነገገውን የህሊና ግምት ለማስተባበል የሚችሉ ስለመሆኑ | 29181 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ልየው ቸኮል (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 20/2002 | 135 |
| 47 | በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ሪ/ መሰረት እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችለው በብድር የተሰጠ ገንዘብ ሳይሆን የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ ክፍያ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 | 35758 | እነ አቶ ገብረመድኅን አየናቸው (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰብስቤ ኃይሌ | ታህሣሥ 20/2002 | 142 |
| 48 | የወለድ አግድ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው | | እነ አቶ ፈታኒ ባየህ | | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በመከተል የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑና በዚህ መሰረት ያልተደረገ መሆኑ ውሉን ፈራሽ ሊያደርገው የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3118,3045,3052 | 45422 | (ሰባት ሰዎች)<br>እና እነ ወ/ሮ አስራት ባየህ (ሦስት ሰዎች) | ጥር 13/2002 | 147 |
| 49 | የስልክ አገልግሎት ከማግኘት ጋር በተያያዘ በአገልግሎት የክፍያ መጠን ላይ በአገልግሎት ሰጪውና በአገልግሎት ተቀባዩ መካከል አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ የተጠየቀው የአገልግሎት ሒሳብ በእርግጥም ስልኩን በይዞታው ስር አድርጐ የሚጠቀምበት ወገን በተገለገለው መጠን የተመዘገበ ስለመሆኑ በባለሙያ እንዲጣራ በማድረግ እልባት መስጠት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732 | 48967 | አቶ ሳዲቅ ሐሰን<br>እና<br>የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | ሰኔ 30/2002 | 151 |
| 50 | መዋዕለ ነዋይን በማፍሰስ ግንባታን ለማካሄድ የከተማ ቦታን ከመንግስት ተረክቦ ግንባታን በተገቢው ጊዜ ለማጠናቀቅ አለመቻል ሊያስከትል የሚችለው ውጤት<br>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ደንብ ቁ. 41/97 አንቀፅ 8(3)<br>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ አዋጅ ቁ. 51/94 | 46052 | ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ<br>እና<br>የቦንጋ ማዘጋጃ ቤት ከፋ ዞን | ጥር 19/2002 | 154 |
| 51 | ከቤት ኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የኪራይ ውልን ለማቋረጥ በቂ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ተከራይ የሚፈፅማቸው የግንባታ አይነቶች<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2953,2954,1732 | 46394 | ወ/ሮ ስንቂ መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | የካቲት 11/2002 | 157 |
| 52 | ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ወስድን አስመልክቶ በውላቸው ካመለከቱት ሃሳብ ውጪ የራሱን ስሌት መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1731,2478 | 45559 | የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ የአቶ ኃይሉ ፈይሳ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 160 |
| 53 | ከሽያጭ ጋር በተያያዘ ውል ሲመሰረት ጉድለት የነበረበት መሆኑ ቢረጋገጥም ከውሉ መመስረት በኂላ በተሸጠው ንብረት ላይ ተዋዋይ ወገኖች ተጨማሪ ግንባታ ያካሄዱና ወደ ነበሩበት ለመመለስ አዳጋች ሁኔታ ያለ መሆኑ ከታመነ ውሉ ሊፀና የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) | 47800 | ወ/ሮ እመቤት ደርበው እና አቶ ታደሰ ሰዳማ | የካቲት 25/2002 | 162 |
| 54 | ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር የኪራይ ውል አከራይ የሆነ ወገን ለተከራይ ማስታወቂያ በመስጠት ምክንያቱን መግለፅ ሳያስፈልገው የኪራይ ውሉን ሊያቋርጥ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966(1) | 40336 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>የወ/ሮ አሰገደች ካሣሁን ወራሽ ሄኖክ ሣሙኤል | መጋቢት 22/2002 | 164 |
| 55 | በሌላ ሰው ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ባደረሰው ጉዳት መጠን ኪሣራ ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162 | 43381 | ወ/ሮ ፎዚያ ሁሴን እና አቶ ውብሸት ተ/ወልድ | መጋቢት 10/2002 | 166 |
| 56 | ከሳሽ የሆነ ወገን ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ለመክሰስ የሚችል (የሚገባው) የነበረ ቢሆንም ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ቀንሶ ያቀረበው በፍ/ቤት ፈቃድ የሆነ እንደሆነ የቀረው መብት ላይ በድጋሚ ክስ ለመመስረት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4) | 43992 | እነ አቶ ይልማ አንበሴ (አራት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ እመቤት መንገሻ (አምስት ሰዎች) | መጋቢት 6/2002 | 168 |
| 57 | ከሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ የሚያቀርበው የውል ይፍረስልኝ ክስ ገዥ ውል እንዲፈፀምልኝ በሚል ሊያቀርብ የሚችለው አቤቱታ ላይ የሚቆጠረውን የይርጋ ጊዜ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,1851 | 43636 | ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ<br>እና<br>እነ አቶ በየነ ወ/ሚካኤል (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 22/2002 | 173 |
| 58 | የኪራይ ውልን መሠረት በማድረግ ቤትን የያዘ ወገን የኪራይ ውሉን በቅድሚያ ሣያስፈርስ የባለቤትነት ጥያቄን መሠረት በማድረግ በኪራይ ውሉ አልገደድም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 46947 | አቶ ዘነበ ኃ/ማሪያም እና እነ ወ/ሮ አባይነሽ ዘለቀ (ሦስት ሰዎች) | መጋቢት 7/2002 | 175 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 59 | ከእጅ በእጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ገገር የሽያጩን ዋጋ የከፈለበትን ደረሰኝ ይዞ መገኘቱ የገዛውን ንብረት እንደተረከበ የሚያሳይ የመጨረሻ (conclusive) ማስረጃ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2266,2278(1) እና (2) | 45545 | ወ/ሮ ሽዋዬ ኑርዬ<br>እና<br>ምን አዩ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት .22/2002 | 178 |
| 60 | በፍ/ብሔር ጉዳይ ህጋዊ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ዋስትና የሚደረግበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922 | 47971 | ወ/ሮ ጅቦኒ ቱና እና ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ | ሚያዝያ 5/2002 | 181 |
| 61 | ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ ተከራይ የሆነ ወገን የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ በህግ የተጣለበት እንደሆነ አከራይ የሆነው ወገን ይህንኑ ክፍያ ለመፈፀም ይቻል ዘንድ ተከራዩን ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀፅ 2(3,5,7,8,9,12),6 | 48358 | አቶ ብርሃነ ገብረሐይሉ<br>እና<br>አንሲዩን ኮንትር ላፋም | ሚያዝያ 7/2002 | 183 |
| 62 | • አንድ ሰው ብድሩን አለመክፈሉን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>• 2024(ረ) ዋና ብድርን ሣይሆን ለብድር የሚከፈል ወለድን የሚመለከት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ረ) | 44691 | አቶ ሽባባው ወሌ<br>እና<br>አቶ ሙሉጌታ ዓባይ | ሚያዝያ 8/2002 | 186 |
| 63 | አንድ ውል ህግን የሚፃረር /የሚቃረን/ ነው በሚል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 | 48094 | እነ ሙና እንድሪስ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ግንቦት 10/2002 | 188 |
| 64 | በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት አሰሪው ሠራተኛው በውጭ አገር ትምህርቱን እንዲከታተል ለማስቻል የሚያስፈልጉ ወጭዎችን ደመወዙን ጨምሮ ለመክፈል ሠራተኛው ደግሞ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ አሠሪውን ለማገልገል ውል ገብቶ ሠራተኛው ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለ በሆነ ጊዜ አሠሪው የጉዳት ኪሣራ የመጠየቅ / የመከፈል/ መብት ያለው ስለመሆኑ | 49453 | የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት እና አቶ ተፈሪ ማሞ | ግንቦት 19/2002 | 192 |
| 65 | የሽያጭ ውል በህግ የተቀመጠውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተሉ ፈራሽ ሲሆን ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ወገን ንብረቱን ለውጦ ወይም በንብረቱ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1818 | 49326 | ወ/ሮ እታፈራሁ ኃ/ማሪያም<br>እና<br>እነ መምህር በቀለ ታችበሌ (ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 28/2002 | 195 |
| 66 | በፍ/ብሔር ጉዳይ (ክርክር) የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1846 | 42700 | የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ | ሐምሌ 12/2002 | 198 |
| 67 | የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024 ሥር በተመለከተው የህሊና ግምት የሚሸፈን ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 | 46019 | የአቶ ደሣለው ፋንታ ወራሾች<br>እነ ሙሉጌታ ደሣለው እና አየለ ደበላ | ሐምሌ 20/2002 | 202 |
| 68 | አንድ የስጦታ ውል በኃይል ወይም በተንኮል ተግባር ተደርጓል በሚል ስለሚፈርስበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2442(3),1698,1699,1704,1706 | 49900 | እነ ወ/ሮ ሐመልማል ዓለሙ(ሁለት ሰዎች)<br>እና ወ/ሮ ሀረገወይን ዘለቀ | ሐምሌ 19/2002 | 206 |
| | **አፈፃፀም** | | | | 210 |
| 69 | የውርስ ንብረት በጨረታ እንዲሸጥ ለማድረግ መነሻ ዋጋን ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083,1084 | 43888 | አቶ ፀሐይ ወንድም እና እነ አቶ አያለው መለስ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 23/2002 | 211 |
| 70 | አንድ ተጋቢ በግሉ ያመጣው ዕዳ ከሌለኛው ተጋቢ የጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚደረገው ዕዳውን ያመጣው ተጋቢ ዕዳውን ለመክፈል አለመቻሉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የደቡ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ እና የፌዴራል መንግስት የተሻሻለው | 39837 | አቶ ስመንጉስ አሰፋ<br>እና<br>መ/ት ምህረት ክበበው | ግንቦት 3/2002 | 213 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የቤተሰብ ህግ | | | | |
| 71 | አንድ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም የተነሣ ሊያዝ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ባለዕዳ የሆነው ወገን ሃብት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ | 46143 | ወ/ሮ ድልበኔ ራሕመቶ እና እነ የባህር ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2002 | 215 |
| | **ወንጀል** | | | | 217 |
| 72 | የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የንግድ ድርጅት ሠራተኛ፣ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ድርጅቱ በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦባቸው ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 56(1)(3)<br>አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀፅ 50(ለ)(1),22(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3),34(1) | 48850 | እነ አቶ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ (ሦስት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ታህሣሥ 8/2002 | 218 |
| 73 | በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የፈፀመው የግድያ ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1) (ሀ) ሥር የሚያስጠይቅ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ),84,86 | 45927 | የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ እና መሰረት መኮንን | ጥር 19/2002 | 221 |
| 74 | በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ክስ በዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ የከሳሽ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዘጋት በቀረበው ወንጀል ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ ከመሆን የሚያግደው ስላለመሆኑ | 45572 | ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ እና ፌ/ዐ/ህግ | የካቲት 26/2002 | 224 |
| 75 | ህጋዊ መካላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የሰው መግደል ተግባር በወንጀል ህግ ቁጥር 541(ሀ) የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 540, 541 | 43501 | እነ ረዳት ሳጅን ሽጋ ተካ ሞላ (ሦስት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ | መጋቢት 15/2002 | 225 |
| 76 | በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 እና 567 መሰረት አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543,567 | 44235 | ቄስ ጌታቸው ተሾመ እና ዓቃቤ ሕግ | መጋቢት 28/2002 | 229 |
| 77 | አንድ ሰው የማታለል ተግባር ፈፅሟል በሚል በወንጀል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 692(1) | 46189 | ሐረገወይን ተፈራ እና ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | ሚያዝያ 20/2002 | 232 |
| 78 | ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ የዘወትር ፀባይ መልካም የነበረ መሆኑ በተናጠል (በራሱ) ቅጣትን ለማቅለል የሚያስችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 82(1) (ሀ) | 53612 | እነ አቶ ፍስሐ ዓባይ(ሁለት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ህግ | ሚያዝያ 25/2002 | 234 |
| 79 | በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ወንጀለኛው በይቅርታ የተለቀቀ መሆኑ አስቀድሞ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር (በሪከርድነት እንዳይያዝ የሚያደረግ) ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 230 | 41248 | ቡርቂሶ ዋቆ እና ዐቃቤ ሕግ | ሰኔ 23/2002 | 237 |
| 80 | በሥር ፍ/ቤት የተሰጠ የቅጣት ውሣኔ ላይ አነሰ ወይም በዛ በሚል በግልፅ ይግባኝ ባልተጠየቀበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣትን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጥ የማይገባ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(መ) | 48617 | ተስፋዬ አደላ እና ዐቃቤ ሕግ | ሰኔ 18/2002 | 239 |
| 81 | • ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች የማስረዳት ሸክማቸውን ተወጥተዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>• በፍ/ቤት ፊት ቃለ- መሃላ በመፈፀም የተሰጠ የምስክር ቃል እውነት ነው በሚል የሚወሰደው ግምት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ | 51706 | አቶ ግርማ ትኩ እና የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ሐምሌ 21/2002 | 242 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111 | | | | |
| | **ንብረት** | | | | 251 |
| 82 | የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041,3052 | 38681 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ | ጥቅምት 3/2001 | 252 |
| 83 | ለረጅም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ሥር የነበረ ቤትን ይለቀቅልኝ በሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብትነቱን ሳያረጋግጥ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 47/67 | 45161 | እነ እናኑ ጀንበሬ (ሁለት ሰዎች) እና የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት | ታህሣሥ 24/2002 | 255 |
| 84 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677,1845,1206,1188-1192 | 43600 | ዳዊት መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥር 05/2002 | 257 |
| 85 | የአዋጅ ቁጥር 47/67 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠን ካርታ መሰረት በማድረግ ክሥ ለመመስረት የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67 | 48699 | አቶ አምሣለ ጀመሪ እና አቶ ፍርዱ ገበያሁ | ሚያዝያ 21/2002 | 262 |
| 86 | በአንድ ቤት ውስጥ ሲኖር ያልነበረ ወይም ቤቱን በእጁ አድርጐ ሲያዝበት ያልነበረ ሰው የሚያነሣው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149 | 43081 | አቶ ሣሙኤል ጦኖሮ እና እነ ወ/ሮ አይሻ አርጌሳ (አራት ሰዎች) | ግን ቦት 6/2002 | 266 |
| 87 | በሃይል ቤቴ ተይዞብኛል እንዲለቀቅልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206,1149 | 42861 | ወ/ሮ አጤነሽ አበበ እና አቶ ማንተጋፋቶት አጥላው | ሰኔ 28/2002 | 268 |
| 88 | • አንድን ንብረት በአደራ ለማስተደደር (ለመጠበቅ) የተረከበ ወገን አደራ ሰጪው ንብረቱ እንዲመለስ በጠየቀው ጊዜ ወዲያውኑ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ንብረትን በአደራ የሰጠ ወገን ንብረቱ እንዲመለስለት ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ (ይርጋ)የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2781 (1)(2),2779, 2989(1) | 48048 | ወ/ሮ ገብርኤላ ኒካላ ቶማስ ናክሶ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ሐምሌ 22/2002 | 270 |
| 89 | ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የጉዳት ኪሣራን ጉዳት ለሚደርስበት ወገን በመክፈል የመንገድ መተላለፊያ ( servitude right) መብት ሊከበር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1221 | 48783 | ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን እና እነ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 27/2002 | 273 |
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | 276 |
| 90 | የጉዳት ኪሣራ የሚከፈለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090,2091 | 39601 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ገዛኸኝ መንግስቱ | ጥቅምት 5/2002 | 277 |
| 91 | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ገቢ ያልነበረው መሆኑ በርትዕ ሊከፈለው የሚገባውን ካሣ የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | 42962 | አቶ አየለ አድማሱ እና አቶ አጀቡ ሹሜ | ታህሣሥ 28/2002 | 279 |
| 92 | በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋት የሌለበት መሆን በራሱ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍትሐብሔር ከቀረበ ክስ ነፃ ለመውጣት እንደ በቂና የመጨረሻ መስፈርት የሚወሰድ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149 | 43843 | ዶ/ር ተስፋነሽ በላይ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | መጋቢት 21/2002 | 289 |
| 93 | ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት በሥራ ወቅት በሌሎች ሰዎች | 45735 | አቶ ደረጀ ቸርነት እና | መጋቢት 21/2002 | 285 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አሠሪ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2131, 2132 | | ወ/ሮ ሕይወት የኃላሸት | | |
| 94 | በአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ችሎት ሠራተኛው የፈፀመው ድርጊት ከሥራ ለማሰናበት በቂ አይደለም ተብሎ መወሰኑ አሰሪው በሠራተኛው ላይ በፍ/ብሔር ጉዳይ ሊያቀርብ የሚችለውን ክስ የሚያስቀር የመጨረሻ ፍርድ /ውሣኔ/ ስላለመሆኑ | 44588 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና እነ ኃይለየሱስ ቱኪ.<br>(አራት ሰዎች) | ሚያዝያ 4/2002 | 290 |
| 95 | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ህይወቱ ካለፈ ሰው ጋር በተገናኘ የሚከፈለው የጉዳት ካሣ መብቱን የሚጠይቀው ሰው ዕድሜ ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ በመሆኑ የተነሣ ብቻ ካሳው ሊከፈለው አይገባም ለማለት የሚያስችል የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095/1/ | 50225 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና<br>እነ ወ/ት ዝናሽ አሰፋ<br>(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 5/2002 | 293 |
| | **የዳኝነት ስልጣን** | | | | 295 |
| 96 | የአ.አ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ደብተርን ለመሰረዝ የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ | 34665 | እነ አቶ ናትናኤል ዘውገ (ሁለት ሰዎች)እና እነ ወ/ሮ እግዜሩ ገ/ህይወት(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት1 2/2002 | 296 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 97 | የከተማ ቦታ ያለአግባብ ተወስዶብኛ በሊዝ ለሌላ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የቦታውን መውሰድ ውሣኔ ለሰጠው አካል በቅድሚያ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑና በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ያለበትና ይኼው አካል የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 272/1994 | 46220 | የደቡብ ክልል የሐዋሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት<br>እና የሐዋሳ ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ገዳም | ጥር 18/2002 | 298 |
| 98 | በውጪ አገር ሕግ መሰረት የተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገበ የንግድ ድርጅት ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊዳኝ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27(1), አዋጅ 25/88 አንቀጽ 11(2)(ሀ) | 42928 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና ድራጋዶስ<br>ኮንስትራክሽን | ጥር 12/2002 | 300 |
| 99 | በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለባለገንዘቡ ሊመለስ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 53(1),55 | 42866 | ብርሃነ ጥዑም እና<br>የጉምሩክ ባለስልጣን | መጋቢት 20/2002 | 302 |
| 100 | የሥራ መደብ ወይም እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የወል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ስለመሆኑ | 48111 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና አቶ ቂጤሳ ገብሬ | ሚያዝያ 13/2002 | 305 |
| 101 | በውድድር አሸንፌ ያገኘሁትን የሥራ መደብ እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ የሥራ ክርክር የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሚታይ ሰላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 52600 | የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ኃይሌ | ሚያዝያ 12/2002 | 308 |
| 102 | የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በከተማው የሚገኝ ቤት ባለቤትነቱ የማን ነው ከሚል ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚነሣ ክርክርን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 416/19 አንቀፅ 33 | 47134 | የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ፋንታዬ ምትኩ | ግንቦት 6/2002 | 310 |
| 103 | • የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከ5000 ብር በታች የሆነ ጉዳይን በሙሉ ተቀብሎ ለማስተናገድ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች በሕግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ | 52041 | የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክ/አ/ማህበር<br>እና<br>የኢት/መድን ድርጅት | ሰኔ 29/2002 | 313 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • የሥረ-ነገር ሥልጣን በሕግ ባልተሰጠው የዳኝነት አካል (ፍ/ቤት) የተሰጠ ፍርድ የማይፀና ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),5(9)<br>አዋጅ ቁ. 361/95 | | | | |
| 104 | በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 5(6) | 43912 | አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና<br>እነ የአቶ ኢብራሂም ሙሣ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 15/2002 | 315 |
| 105 | በሰዎች ወይም በሚንቀሳቀስ ሀብት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስን ለማስተናገድ የግዛት ክልል ሥልጣን ስለሚኖረው ፍ/ቤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 27 | 48018 | አቶ ተከተል ዘካሪያስ እና<br>እነ ወ/ሮ አስቴር ታደሰ(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 7/2002 | 317 |
| 106 | በሸሪአ ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ላይ ጣልቃ ገብቶ መከራከር በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ስምምነትን እንደመስጠት የሚያስቆጥር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 188(92) አንቀፅ 5(1) | 45806 | አቶ ፍፁም በረታ እና እነ ወ/ሮ ሶፊያ ዱላ(አራት ሰዎች) | ሐምሌ 8/2002 | 319 |
| 107 | • በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ እጅግ አስፈላጊ የህዝብ አገልግሎት ድርጅቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄን የያዘ የውል የሥራ ክርክር ካልሆነ በስተቀር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለማስተናገድ የሥረ- ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>• መሰል ጉዳዩችን ለማየት በህግ ስልጣን የተሰጠው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰየም ቦርድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 466/97 አንቀፅ 2(2)<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 142(1)(ሀ),(2),(3),136(2) | 49152 | የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር<br>እና<br>የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት | ሐምሌ 7/2002 | 324 |
| | **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | 328 |
| 108 | በብድር ለተሰጠ ገንዘብ በመያዣነት የተያዘ ንብረት መድን የተገባለት ሆኖ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ አበዳሪው ንብረቱን በመያዣ የያዘበት ብድር ዋጋ ዋስትና ከተገባለት የገንዘብ መጠን ያነሰ እንኳን ቢሆን መድን ሰጪው እንዲከፍለው ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2858 | 38572 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ጥቅምት 17/2002 | 329 |
| 109 | ባንክ በመያዣ መልክ የያዘውን የተበዳሪ ንብረት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት በመሸጥ ላይ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በተበዳሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ዕዳው እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ | 44164 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ሐሰን ኢብራሂም | ታህሣሥ 8/2002 | 332 |
| 110 | የኢንሹራንስ ውልን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 674(1),754(1) | 46778 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የካቲት 24/2002 | 336 |
| 111 | የመድን ሰጭ ኃላፊነት በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 665(2) | 46808 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ | ሚያዝያ 6/2002 | 339 |
| 112 | ለአንድ ንብረት መድን የገባ ሰው በንብረቱ ላይ የደረሰው ጉዳት ሙሉ ውድመት ሊባል የሚችል ቢሆንም ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 678 | 48698 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ<br>እና<br>አቶ ሣሙኤል አለሙ | ግንቦት 19/2002 | 341 |
| 113 | መድን ሰጪ የሆነ ወገን በመድን ገቢው እግር በመተካት ባለዕዳ የሆነ ወገን ላይ ጥያቄ ባነሣ ጊዜ ባለዕዳው ከመድን ገቢው ጋር የሚፈጠር አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ውጪ በሽምግልና ለመጨረስ የተስማማን በመሆኑ መድን ሰጪው በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ ሊጠይቅ አይችልም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ | 39902 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ | ሰኔ 18/2002 | 344 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የንግድ ህግ ቁ. 683(1) | | | | |
| 114 | አስቀድሞ የተደረገ ነገር ግን ባለመታደሱ ምክንያት የተቋረጠ (ያበቃ)ን የመድን ውል መሠረት በማድረግ ሊጠየቅ የሚችል የጉዳት ካሣ ስላለመኖሩ<br>የንግድ ህግ ቁ. 666(2) እና (3) | 52910 | አቶ አንዳርጌ ታደሰ<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሐምሌ<br>28/2002 | 347 |
| | **ጉምሩክ(ግብር)ታክስ** | | | | 349 |
| 115 | • የንግድ ቤቶችን የማከራየት እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ ከሆኑ ግብይቶች የማይመደብ ስለመሆኑ<br>• የንግድ ቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 8 | 39574 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ምልአተ ፀጋ<br>ቢዘን<br>(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት<br>3/2002 | 350 |
| 116 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያልተከፈለን ቀሪ ቀረጥ ሊያስከፍል የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ 57(1),48,53(1) | 45882 | የገቢዎችና ጉምሩክ<br>ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ<br>እጅጋየሁ አራምዴ (ሁለት<br>ሰዎች) | ታህሣሥ<br>6/2002 | 352 |
| 117 | የጉምሩክ አዋጅን በመተላለፍ ከሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ የኮንትሮባንድ ተግባር ሃይልን በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር የተፈፀመ እንደሆነ አዋጅ ቁ. 60/89 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ | 44862 | አሸናፊ አበበ እና የጉምሩክ<br>ባለስልጣን | ጥር<br>5/2002 | 355 |
| 118 | የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ክስ ሊቀርብበት የሚገባውና ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ህግ ሣይሆን የጉምሩክ አዋጆች መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 | 48693 | ነኢማ አወል እና<br>የገቢዎችና ጉምሩክ<br>ባለስልጣን | ጥር<br>5/2002 | 357 |
| 119 | የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው የድርጅቱን አስተዳደራዊ ሥራ ለሌላ ሰው የወከለ መሆኑ ድርጅቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ ከሚቀርብበት የወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የማያደርገው ስለመሆኑ | 54061 | አቶ መስፍን ሽፈራው እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎች<br>ባለስልጣን | ሚያዝያ<br>26/2002 | 359 |
| 120 | • የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ባለማከናወኑ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>• የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ግዴታውን ለመወጣት ሲንቀሳቀስ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐት ከሚቆየው ንብረት ጋር በተያያዘ የተቋረጠ ጥቅም ወይም የጉዳት ካሣ ሊከፍል የሚችልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ 60/98 አንቀጽ 6(5), 58,74<br>አዋጅ ቁ 368/95 አንቀጽ 78 | 49889 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና<br>ጉምሩክ ባለስልጣን<br>የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ዛኪ ሰይድ | ሰኔ<br>28/2002 | 361 |
| 121 | የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43(1) | 48621 | አቶ አብደላ ሁሴን ክሊር<br>ላብራቶሪ<br>ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና የፌዴራል አገር<br>ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | ሰኔ<br>30/2002 | 365 |
| | **ውክልና** | | | | 368 |
| 122 | ባንክ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው አልደረሰም በሚል ኃላፊነት አለበት ሊባል የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል የቀረ እንደሆነ ወይም መጭበርበሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ | 48269 | አቶ ሽረፈዲን አብደ እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | የካቲት<br>24/2002 | 369 |
| 123 | ወኪል የሆነ ሰው የውክልና ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ የራሱን ወይም ከራሱ ጋር ቤተሰባዊ ወይም ሌላ ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ሰውና የወካዩ ጥቅም ሊጋጭ | 50440 | አቶ ሃብቱ ወልዱ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሰሉ ደስታ | ግንቦት<br>16/2002 | 371 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚችልበት አጋጣሚ እንዳይፈጠር መከላከል ያለበት ወይም በተፈጠረ ጊዜ አስቀድሞ ለወካዩ ማሳወቅ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)2198,2208,2209 | | (ሁለት ሰዎች) | | |
| **የንግድ ሕግ** | | | | | 375 |
| 124 | • የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>• በግለሰቦች መካከል በውል የሚፈጠር የሽርክና ማህበር የንግድ ሕግ በሚያዘው መሰረት አይነቱ ተለይቶ ተመዝግቦ የማይገኝ በሆነ ጊዜ እንደ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 211,212,219 | 46358 | ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ እና<br>እነ አቶ ሚካኤል ፋሲሐ<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት<br>25/2002 | 376 |
| 125 | ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች ማህበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ያልተገባ ስራ ምክንያት በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 580 | 39608 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አምሳለ በላይ<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት<br>11/2002 | 378 |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | | 381 |
| 126 | አንድን መፅሐፍ ከተፃፈበት ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የተረጐመ ሰው እንደ ድርሰት አመንጪ ተቆጥሮ የሞራልና የቁሣዊ ጉዳት ሊወሰንለት ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 2(2),6(1) | 44520 | አርቲስቲክ ማተሚያ<br>ድርጅት<br>እና<br>ዶ/ር ጌታሁን ሽብሩ | ጥቅምት<br>10/2002 | 382 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | 385 |
| 127 | ለዋስትና የተያዘ ገንዘብን የአስያዢን ማንነትን ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ ገንዘቡን ያስያዘበት ደረሰኝ ኮፒን ያቀረበ እንኳን ቢሆን የተያዘው ገንዘብ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ | 53459 | አቶ ማሞ ገ/ማሪያም<br>ተጠራ፡የለም | ሚያዝያ<br>12/2002 | 386 |
| 128 | • በአስፈፃሚ አካላት የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የወጡ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አለመሆናቸው ህጋዊ ውጤት እንዳይኖራቸው የሚከለክል ስላለመሆኑ<br>• አዋጅን መሠረት በማድረግ የወጡ መመሪያዎችን የሚፃረር ድርጊት መፈፀም በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 83/86 አንቀፅ 39(2),1, 2, 59(1)(ሸ)<br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ. ሲ.ቲ.ጂ 001/97 | 43781 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና<br>ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ዳንኤል መኮንን | ሐምሌ<br>14/2002 | 388 |
| 129 | • የሕግ ክርክሮችን በሰበር ማየት /ማስተናገድ/ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠ ስልጣን (power) ስለመሆኑ<br>• በግልግል ዳኝነት (arbitration) የታየ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተዋዋይ ወገኖች የይግባኝ መብትን ለማስቀረት የሚያደርጉት ስምምነት ጉዳዩን በሰበር ችሎት ከመታየት የማያግድ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ፡፡)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3 (ሀ), አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 (4), አዋጅ ቁጥር 25/88, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 350(2) 351 እና 356 | 42239 | ብሔራዊ ማዕድን<br>ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግ/<br>ኩባንያ እና<br>ዳን ትሬዲንግ<br>ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ | ጥቅምት<br>20/2003 | 393 |



www.chilot.me